# ክፍል አንድ

## እስከ አልጋዋ ድረስ

‹‹ያቺ ድንክ አልጋ አመለኛ
ካለአንድ ሰው አታስተኛ››

-የሕዝብ ግጥም

# ምዕራፍ አንድ

## እኔና ኢሕአዴግ

ቤተኛው ባይተዋር

ዶ/ር ሐንሲ ሴሊ የተባለው እውቅ የአእምሮ ሐኪም "የሁለት ወንድማማቾች ወግ" የተባለውን በጣም የታወቀ ወግ ለማስተማሪያነት አዘውትሮ ይጠቀም ነበር። ወጉ አንድ ዓይነት አጋጣሚ እንዴት የተለያየ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል የሚገልጽ ግሩም አብነት ነው።

ሁለት ተቃራኒ አመል ያላቸው ወንድማማቾች ነበሩ። አብረው ነው ያደጉት፤ በአንድ እናትና በአንድ አባት ጉያ፤ በአንድ ቤት ውስጥ። ጠባያቸው ግን ለየቅል ነው፤ የእናት ሆድ ዥጉርጉር እንዲሉ። አንደኛው የወጣለት ሰካራም ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ፍጹም አልኮል መጠጥ የሚባል በአፉ የማይዞር ነበር። ልጅ ሳሉ አባታቸው ጠጪ እንደነበር ይነገራል። በፍጹም ሳይሰክር ወደ ቤት ገብቶ አያውቅም። ወደ ቤት ሲገባም እናታቸውን ይሰድባታል፤ አልፎ አልፎም ልጆቹን ይደበድባል።

አንደኛው ልጅ ልክ እንደአባቱ ሰካራምና ተደባዳቢ ሆነ። ሌላኛው ልጅ ግን መጠጥና ድብድብ በደረሱበት የማይደርስ ሆነ። ታዲያ እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች ስለጠባያቸው ሲጠየቁ፤ ሁለቱም አባታቸውን በምክንያትነት ይጠቅሳሉ። የአባታቸው ሰካራም መሆን አንደኛውን ስካር አስተማረ፤ ሌላኛውን ደግሞ አልኮል አምርሮ እንዲጠላ አደረገ። አንድ ዓይነት ምክንያት የተለያዩ ውጤቶችን አስገኘ። ለአንድ ዓይነት ችግር የተሰጠው ምላሽ ለየቅል ሆነ።

የምንኖርበት ሕይወት በአያሌ ክሥተቶች የተሞላ ሲሆን ክሥተቶቹ አንዳንዴ ሁላችንንም በጋራ የሚነኩ ይሆናሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ በግል እኛን ብቻ የሚመለከቱንና በግል የሚነኩን ሆነው ይበቅላሉ። እኔና ሌሎች የፖለቲካ ጓዶቼ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ውጥንቅጥ ውስጥ ከላይ በምሳሌ እንደተጠቀሰው ቤተሰብ፤ ከቤተሰቡም እንደ ሁለቱ ልጆች የጉዳት ሰለባዎች ሆነን ቆይተናል። በቆይታችን ምንም እንኳን የፖለቲካ ጉዳይ የጋራ ጉዳይ ቢሆንም፤ የፖለቲካ ተዋናዮቹ ግን የፖለቲካው ጉዳይ በተመሳሳይ ሁኔታ ሲመለከተንና ለጉዳዩም ተመሳሳይ ምላሽ ስንሰጠው አይታይም። በሀገራችን የፖለቲካ ውጣ ውረድ አንዳንዱ ተስፋ ቆርጦ ሀገራችን የምትፈርስበት ጊዜ መቅረቡ ይታየዋል። ሌሎቻችን ደግሞ ይህ ችግር የሀገራችንን አንድነት፤ ታላቅነትና ብልጽግና ለማምጣት ምክንያት ሆኖ ይታየናል።

በገሀዱ ዓለም የሆኑነትና እየሆኑ ያሉት ሐቆች አንድ ዓይነት ናቸው። ሁላችንም የምንሰማቸውና የምናያቸው ክሥተቶች ተመሳሳይ ናቸው። የሚለየው ለነገሮቹ የምንሰጠው ምላሽ ነው። ያለፍንበት ጎዳና አንድ ዓይነት ሆኖ ሳለ ጥሬውን ሐቅ የምንተረጉምበትና ነገን የምናይበት መነጽር ለየቅል ነው። በኢሕአዴግ ውስጥ የነበረው ሁኔታ ከእዚህ እውነታ የሚቀዳ ነው።

ጥቂት የማይባሉ ጓዶች የኢትዮጵያን ሁኔታ ወደ ውድቀት ማንደርደር ይቀናቸዋል። ለእነርሱ ከሩቅ የወደቀች ኢትዮጵያ ትታያቸዋለች። ጥቂት ከማይባሉ ጓዶቼ ጋር እንደ ሀገር ለተጋረጠብን የኋላ ቀርነት ቋጥኝ የምንሰጠው ምላሽ ሁልጊዜም በተቃራኒው ነበር። ሀገራችን ስትሻገርና ወደ ብልጽግና ጎዳና ስትራመድ ይታየናል። እንዴት እንደምትሸጋገርና የት እንደምትደርስ እንወጥናለን፤ እንናገራለን፤ እንመክራለን። በዚህ መካከል ነበር ክርክሩ፤ ፉክክሩ፤ መጓተቱና መጠላለፉ እየጨመረ የመጣው። አንዱ በዚህ ሲል ሌላው በተቃራኒው ምላሽ ሲሰጥ ቆየ። በመጨረሻም የመጣው ለውጥ የእዚህ እልህ አስጨራሽ ፍትጊያ ውጤትና

ከውስጥ በተፈጠረ ተቃርኖ የተወለደ መሆኑን ልብ ይሏል።

# ሰሚ ፍለጋ

የበዛው የፖለቲካ ሕይወቴ ከኢሕአዴግ ጋር የተቆራኘ ነው። የሕይወቴ መሥመር የተቃኘውም በኢሕአዴግ ጉዞ ላይ ነበር። ድርጅቱን በተቀላቀልኩበት ወቅት ዕድሜዬ ገና አሥራ አምስት ዓመትም በቅጡ አልሞላም ነበር። ከዚያ ወዲያ ሀያ ስምንት ዓመታት ተቆጥረዋል። ያኔ ወደ ድርጅቱ ስቀላቀል ከየትኛውም የፖለቲካ ቡድን ጋር ግንኙነት አልነበረኝም። ፖለቲካ የሚለውን ቃል እንኳን በቅጡ የማልረዳ ልጅ ነበርኩ።

ፖለቲካንም ሆነ ፖለቲካዊ ትግልን "ሀ" ብዬ የተማርኩትና አፌን የፈታሁት በኢሕአዴግ ውስጥ ነው። የመሪነትን አቡጊዳ ከመቁጠር ከፍተኛውን የኃላፊነት መጎናጸፊያም እስከ መደረብ የደረስኩበትም በዚሁ ድርጅት ውስጥ ነው። ስለዚህም ድርጅቱ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አለው። የሕይወቴን ትኩስና ወሳኝ ዘመን ያሳለፍኩት እዚሁ ነው። ይህ ማለት ግን ሙሉ እኔነቴ የተገነባው፤ ነገሮችን የምመለከትበት መንገድ የተቃኘው በኢሕአዴግ ብቻ ነው ማለት ፈጽሞ አይደለም። እንደማንኛውም ሰው ሕይወቴ የብዙ ግንኙነቶችና ሁነቶች፤ የአያሌ ክሥተቶችና የብዙ አጋጣሚዎች ድምር ውጤት ነው። እኔ ማለት የእኔና የሌሎች ውሳኔዎች ውጤት ነኝ።

እንደ ድርጅት ከኢሕአዴግ ፖለቲካን ተምሬያለሁ። ከጥሩነቱ ብቻ ሳይሆን ከስሕተቶቹም፤ ከድሎቹ ብቻ ሳይሆን ከሽንፈቶቹም፤ ከስኬቶቹ ብቻ ሳይሆን ከእንከኖቹም ብዙ ተምሬያለሁ። ከኢሕአዲግ ጋር ስቀላቀል በዕውቀት ያልደረጀሁና በዕድሜ ያልበሰልኩ ነበርኩ። በወቅቱ ኢሕአዴግ ሀገር ለማስተዳደር የሚያደርገው መፍጨርጨርና የእኔ የእድገት ጉዞ ተመሳሳይ ነበር። ወደላይ እየጨመረ የሚሄድ፤ ለከርሞ ተስፋ እንዲሰነቅ የሚያደርግ፤ ከታናሽነት ወደ ታላቅነት የሚገሠግሥ፤ ጤናማ ዕድገት ነበር።

ዓመታት እየተቆጠሩ ሲመጡ ግን በኢሕአዴግ እልፍኝ ውስጥ ከተስፋ ብርሃን ወደ ጽልመት የሚያንደረድሩ አጋጣሚዎች እየበዙ መጡ።

ፓርቲው እንደ አንድ የፖለቲካ ድርጅት ሥር የሰደዱ ነባር የፖለቲካ አስተምህሮዎችን በተጠየቃዊ መንገድ እየተቸ፤ የራሱን አቋሞች እየገመገመና እያረመ ለድል የበቃ ድርጅት ነበር። ድርጅቱ ሲመሠረት ከነበረው ፍጹም ሶሻሊስታዊ የግራ ዘመም አስተሳሰብ የመጣው በራሱ የውስጥ ትግል እና በዓለም አቀፍ ሁኔታዎች መቀያየር ነው። በድርጅቱ ባህልና የፖለቲካ ጥላ ሥር ሆኖ ጥላቻን በፍቅር ስለማሸነፍ ወጣ ያለ ሐሳብ ማሰብ ይቻል ነበር።

ለድል በበቃባቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት መተቻቸትና ሐሳብን በሐሳብ መቃወም አስፈላጊ ነገር ተደርጎ ይወሰድ ነበር። ዓመታት እየተቆጠሩ ሲመጡ ይሄ ባህል እንደቀይ ቀበሮ እየተመናመነ፤ በተቃራኒው ተቺ ሐሳቦችን የሚሰነዝሩ ሰዎችን በአፍራሽነት የመፈረጅ ጣጣ እየገነነ መጣ። ይህ በሽታ ብዙዎቹ የትግል ጓዶቻችን እዛው ባሉበት ተቸክለው እንዲቀሩ አደረጋቸው። ይሄ አስደንጋጭ ድርጅታዊ "አቀንጭራ" በውስጤ

እያቆጠቆጠ ከመጣው የመደመር አስተሳሰብ ጋር በእጅጉ ተጋጨ፡፡ አንድ ሰሞን በሀገራችን "አቀንጭራ" የተባለ፤ ለምንም የማይጠቅም፤ በፍጥነት የሚስፋፋና ደህነኛውን ሰብል አንቆ ሊገድል የሚተጋ አረም ተፈጥሮ ነበር፡፡ አረሙ በየአካባቢው ሕዝባችንን ሲያስጨንቅ እንደነበር ይታወሳል፡፡ የዚህ አረም ትልቁ ችግሩ አንዱ ሥር ከያዘ በኋላ ለመንቀል ሲታገሉነት ተሙለጭልጮ ሥሩ ተቆርጦ ባለበት ይቀራል፤ በዚህም ምክንያት ከላይ የተቆረጠ ቢመስልም ዳግም ያቆጠቁጣል፡፡

በኢሕአዴግ ውስጥ ቅርንጫፎቹን ዘርግቶ ሥር እየሰደደ የመጣው እኩይ ኃይል፤ በግምገማና በእርምት ንቅናቄ ከላይ የተቆረጠ ሲመስል፤ ከውስጥ ግን ሥሩን እንደሰደደ ይቀራል፡፡ በዚህም የተነሳ መልሶ ያቆጠቁጣል፡፡ ይህ አጋጣሚ በሕይወቱ ሌሎች አማራጮችን ማየት እንደሚያስፈልገኝ አነሣሽ ሞተር በመሆን ወሳኝ ሚና ተጫውቷል፡፡

በኢትዮጵያ ምድር እየሆነ ያለው አስፈሪና አሳፋሪ ክሥተት፤ እንዲህ እንደዛሬው የእልፍኙ በሠገነት ላይ ከመገለጡና በዜጎች ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳትና ጥፋት ከማድረሱ በፊት፤ ድርጅቴን ኢሕአዴግን ሊያስጠነቅቁ የሞከሩ ቀደምት የእውነት ፋና ፈንጣቂ የትግል ጓዶች ነበሩ፡፡ እኒህ የነገውን ዛሬ በነቃ አእምሯቸው ቀድመው መተንበይ የቻሉት ጓዶቻችን "ሕዝቡ 'አፍ እንጂ ጆሮ የላቸውም' እያለን ነው.....ለምን ሕዝቡን አንሰማውም? .... ለምን ልናዳምጠው አንሞክርም?.... ለምን ለጥያቄዎቹ ተገቢውን ምላሽ አንሰጥም?" በማለት ወትውተው ነበር፡፡

"የሕዝብን ጥያቄና ብሶት ለማስቀረት የምንችልበት የተሻለው መንገድ ማድበስበስና አፍኖ ማስቀረት አይደለም፡፡ ይልቁንም በአግባቡ በመወያየትና በመመካከር በተገቢው መንገድ መመለስ ያስፈልጋል፡፡ ዛሬ ሕዝቡን ካላዳመጥነው፤ ነገ እኛን አያዳምጠንም" በማለት ጥቂቶች ጠይቀዋል፤ በተደጋጋሚ መክረዋል፤ አሳስበዋል፡፡ አመራሩ ግን መስሚያ ጆሮውን ማስተወያ ልቡናውን ተነጥቋልና ጩኸቱን እንደማለፊያ ሙዚቃ ቆጠረው፡፡ ለማዳመጥም ሆነ ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ አጀንዳው በተደጋጋሚ ጊዜያት በየጉባኤዎቻችንና በየምክሮቻችን ወቅት ተነስቷል፡፡ ሰሚ ሲጠፋ ችግሩ ራሱን እየገለጠ መጣ፡፡

አመራሩ ለለውጥ ፈቃደኛ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን አስተያየቶችን ማጣጣልና ሰዎችን መፈረጅ፤ የተለያዩ ታርጋዎችንም መለጠፍ ቀጠለ፡፡ በአንድ በኩል ‹ትምክህተኛ› ና ‹ጠባብ› በሚል ጎራ መመደብ፤ ከዚያም ሲያልፍ የአክራሪና የጽንፈኛ አመለካከት ማራገፊያ ወደብ አድርጎ ማሸማቀቅ ዋነኛ የመከላከያ መንገድ አድርጎ ቆጠረው፡፡ "ሕመሙን የደበቀ፤ መድኃኒት አይገኝለትም" በሚል ማህበረሰብ ውስጥ ቢበቅልም ድርጅታችን ሕመሙን ጨክኖ ለማወቅ ባለመፍቀዱ በቀላሉ የመዳን ዕድሎቹን አባከናቸው፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ ሰው ሁሉ እየተማረረብን፤ 'ኢሕአዴግ' የሚለው ስም ሲጠራ መንገሽገሽ ጀመረ፡፡ በዚህም አልቆመ ጭራሽ 'ኢሕአዴግ' መባል ጣት የሚያጠቋቁምበት ደረጃ ላይ ተደረሰ፡፡ መራራ ወቀሳዎች ከሀገር ውስጥም ከውጭም እየተሰሙ፤ ድክመቶቻችን እንደ ግንባር ቁስል አፍጥጠው እየታዩ ሳንታከማቸው ዓመታትን ተሻገርን፡፡ "ሳይደግስ አይጣላም" እንደሚባለው በዚህ ጉዞ ውስጥ ከመካከላችን በላቀ "ከችግር ፈጣሪዎቹ" በላቀ "ችግር የፈጠራቸው ችግር ፈቺዎቹ" ማቆጥቆጥ ጀመሩ፡፡ ከአረጀ ጉቶ ላይ እንደሚበቅል

አዲስ ቁጥቋጦ በድርጅቱ ሞት ውስጥ ሕይወት የሰነቁ አመራሮች ብቅ ብቅ አሉ።

መቼም ቢሆን የሐሳብ ልዩነትን የአቋም እንጂ የጥላቻ ምክንያት ልናደርገው አይገባም። ወደ አንድ ግብ ለመድረስ ያሰቡ ተጓዦች ስለተሻለው አማራጭ መንገድ ቢጨቃጨቁ ምንም ነውር የለውም። የሀገራችን ሰው 'ሊጡ አንድ፤ ስልቱ ዓስራ አንድ' ይላል። አንዱን ሊጥ በአስራ አንድ መንገድ ዳቦ ማድረግ ይቻላል፤ ነው ነገሩ። ጉዞው እንደየስልቱ ቢለያይም መድረሻው ግን አንድ ነው።

እያንዳንዱ አስተሳሰብ ወይም የአካሄድ መሥመር ሊሰጥ ከሚችለው ጥቅም፤ ከወቅታዊነቱና ከተግባራዊነቱ አንጻር በመነሳት መተቸት፤ መታረምና በየጊዜው መፈተሽ አለበት። ይሄንን ማድረግ ራስን ማብቃት እንጂ ነውር መስራት አይደለም። ድርጅቱም ቢሆን የሕዝቦችንና የግለሰቦችን ነጻነት፤ ልማትና ሰላም ለማረጋገጥ የተቋቋመ መሣሪያ እንጂ አንድን ሐሳብ ወይም ግለሰብ ለማምለክ አልተፈጠረም።

የቀድሞ ሰዎች መጀመሪያ ራሳቸው የተለያዩ ቅርጾችን ሠሩ። እነዚያን ቅርጾችም ማምለክ ጀመሩ። በሂደትም ራሳቸው የሠሯቸውን ቅርጾች መፍራት ቀጠሉ። ለገዛ ሥራቸው እስረኞች ሆነው ቅርጾቹ ያመጡባቸውን ጣጣዎች ለመለወጥ ፈሩ። እኛንም የገጠመን ከዚህ የራቀ አልነበረም። አንድ ፖሊሲ ሲወጣ ድርጅቱ ከዘመን ዘመን እንዲቀጥል የሚያስችለው፤ ወቅታዊውን ችግር መነሻ ያደረገ ስልት መንደፊያ እንጂ፤ አንዴ ከወጣ ለዘላለም የሙጥኝ ተብሎ የሚያዝ የአምላክ ቃል ወይም የእምነት ቀኖና አይደለም። ድርጅታችን ለረጅም ዘመናት እንዲቀጥል ከተፈለገ በየወቅቱ የሚፈጠሩ ችግሮችን ማለፍ በሚያስችለው መልኩ እየታደሱ የሚሄዱ የፖሊሲ ማህቀፎች ሊኖሩት ይገባል። ፖለቲካዊ መሥመር እስከጠቀመ ድረስ መሣሪያ ነውና እየተከተልን እናበለጽገዋለን። ጠቃሚነቱ ሲያበቃ ደግሞ ጊዜው እንዳለፈበት ያረጀ እቃ በተሻለው መገልገያ ይተካል። ወደአንድ ቦታ ለመሄድ መኪና ውስጥ ከተሳፈረ በኋላ ከተሳፈረበት መኪና ጋር ጽኑ ፍቅር ይዞት እዚያው እንደሚቀር ሰው አይደለንም።

የመኪናው ዓላማ ወደምንፈልግበት እንዲያደርሰን ነው። ካላደረሰን መኪናው ሙሉ በሙሉ ይጣላል ወይም ለማድረስ በሚችልበት መልኩ ሊቀየር ይችላል። በቅርስነት ልናስቀምጠው ካልፈቀድን በቀር መጣሉና መወርወሩም አይቀሬ ነው። በየትኛውም ምድራዊ ስሌት የፖለቲካ ምልከታ እንደ አምላክ ቃል ተይዞና ተጠብቆ ለዘለዓለም አይኖርም።

አሁን የነገሩን ውል ከላይ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ ከጠቀስኩት ጋር፤ ከሁለቱ ልጆችና የጠጪ አባታቸው ታሪክ ጋር አያይዘን ለአፍታ እንመልከተው። ጥቂት የማይባሉ ወጣት ጓዶቻችን ‹‹ከሰካራም አባቱ መጠጥ መቀማመስን እንደለመደው ልጅ›› ሆነዋል። እኔና ጥቂት መሰሎቼ ደግሞ፤ በአባቱ ጠጭነት ምክንያት መጠጥ አምርሮ እንደጠላው ልጅ ሆነናል ማለት እችላለሁ። በኢሕአዴግ ውስጥ እያቆጠቆጡ በመጡ እና በሂደት በተደጋጋሚ በተፈፀሙ ነውሮች ምክንያት ግፍንና ህሊና ቢስነትን አጥብቀን መጸየፍ ጀምረናል።

# እይታ፤ ሐሳብና ወዳጅነት

በአንድ ወቅት ላይ ከአምባሳደር ግርማ ብሩ ጋር ሞቅ ያለ ጨዋታ ይዘን የሆድ የሆዳችንን እያወጋን ሳለ በመኃል “ነገሩ ትክክል ሳይሆን አይቀርም” የሚል ነገር ተናገርኩ፡፡

“ምኑ?” አለና በመነጽሩ ሥር አጮልቆ አስተዋለኝ፡፡ “ምኑ ነው ትክክል የሆነው?” በድጋሚ ጠየቀ፡፡ ጨዋታችን አቅጣጫውን ቀይሮ እንዲቀጥል እንደፈለግኩ ገብቶታል፡፡ “እኛ አፍሪካውያን ያለን የፖለቲካ ታሪክ ትውስታ አጭር እንደሆነ አንድ ቦታ ተጽፎ አንብቤ ነበር፡፡ ሳስበው ትክክል ሆኖ አገኘሁት…” አንተ ምን ታስባለህ? በሚል አኳኋን እያየሁት፡፡

“ሸጋ ነዋ!” ሲል መለሰ፣ ከስስ ፈገግታ ጋር፡፡

ፈገግታውን ለመተርጎም እየተጣጣርኩ “መጥፎ ነው እንጂ! ትውስታ ሲረዝም ነው እውቀት የሚደረጀው፡፡ ትውስታ አጭር ከሆነ ትናንት በሄድንበት መንገድ ለመመላለስ እንገደዳለን፡፡ አይመስልህም? አልኩ፡፡

“በአፍሪካ ግን ታሪካችን ሁሉ የጥፋት፤ የግፍና የበደል በመሆኑ፤ ፈጣሪ ከመከራ ሊያድነን ፈልጎ ይሆናል፤ የፖለቲካ ታሪክ ትውስታችንን ያሳጠረው፡፡ ደግሞም በቂም ስለት እንዳንቋሰል ሲባል፤ በጥላቻ ጦር እንዳንደማማ፤ በበቀል ሰይፍ እንዳንጨራረስ ትዝታችን ቢያጥር ይበጃል…” ብሎ፤ ብርጭቆው ውስጥ ከቀረው ቀዝቃዛ አምቦ ውኃ ተጎነጨ፡፡

“በእርግጥ እንዲያ አላየሁትም ነበር” አልኩ፡፡ እውነትም በዚያ መንገድ አይቼው አላውቅም ነበር፡፡

“ታዲያ እንዴት ነበር ያየኸው?”

“እኔማ…” ብዬ ለአፍታ ዝም አልኩ፤ የነገሬን ማጠንጠኛ ከሥር ከመሠረቱ እንዴት አሳጥሬ ለመግለጽ እንደምችል እያብሰለሰልኩ፡፡ “ያው እንደምታውቀው አመራሮቻችን ጥቂት ሆነው ጫካ ገብተው፤ በደል አጠንክሯቸው፤ መገፋት አንድ አድርጓቸው፤ ሰባ ሺህ ሆነው በድል እንዳልመጡ፤ አሁን ሁሉን ረስተው ‹ካልተስማማችሁ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ› ሲሉን፤ ወይ ትናንትን መርሳት እላለሁ፡፡

ግርማ የጨዋታዬ አቅጣጫ ስለገባው ሌላ ጥያቄ ሰነዘረ፡፡ “በደል ሁሉ ለድል ያበቃል ብለህ ታስባለህ እንዴ?”

“ዐውቃለሁ… ለድል የሚያበቃው መርህ፤ እውነተኛ ትግልና ህብረት ነው፡፡ ያለጋራ ግብና ያለ እውነተኛ መደመር የሚመጣ ድል ዘላቂ አይሆንም፡፡ ኢትዮጵያ ያደረገቻቸው ጦርነቶች ለዚህ ምሳሌ ይሆናሉ፡፡ በቅርቡ ከኤርትራ ጋር በተደረገው ጦርነት እንኳ፤ የቀድሞዎቹን የጦር ሠራዊት አባላት ከተባበሩበት ፈልገን መመለሳችን ምን ያህል እንደረዳን ታውቃለህ፡፡ ግን ብቻ…”

“ግን ምን?” ብሎ ፈገግ ሲል ፈገግታውን ተከትዬ እኔም ሳቅሁ፡፡

ወዲያው ግርማ ፊት ላይ ለአፍታ ብልጭ ያለችው ፈገግታ የነፋስ ሽውታ እንደዳበሳት ኩራዝ በድንገት ከሰመች፡፡ “በል የሰማነውን በልቡናችን ያሳድርልን” ብሎኝ ተነሣ፡፡ በዚህ ጉዳይ ብዙም መግፋት የፈለገ አይመስልም፡፡

አባባሉን ‹ተግባር እንጂ ማውራቱ እምብዛም ለውጥ አያመጣም› በሚል ተረጎምኩት፡፡ ተከትዬው ከመቀመጫዬ እየተነሣሁ ተንጠራራሁና እንደልማዴ እጄን ትከሻው ላይ ጣል አድርጌ መኪናው ድረስ ሸኘሁት፡፡

ታዲያ ጉዳዩን ዳግም ባስታወስኩት ቁጥር በሐሳብ ረጅም ርቀት ያስጉዘኛል፡፡ በኛ ትውልድ ያለችውን ኢትዮጵያንና እየገጠሟት ያሉትን ችግሮች ቅልብጭ አድርጎ ያሳየኛል፡፡ የዛሬዋ ሀገራችን ችግሮች መነሻና የምንሰጠው መፍትሔ ለየቅል መሆኑ ምን ያህል ከገባንበት አዙሪት እንዳንወጣ እንዳረገን ለማወቅ ነጋሪ አያሻውም፡፡ ዞር ብለን የመጣንበትን መንገድ በቅጡ ማስተዋል በቂ ነው፡፡ ቁንጽል እይታና መፍትሔ ለችግራችን ማስታገሻ እንጂ መፍትሔ አልሆነልንም፡፡

እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ማህበረሰብ የሚገጥሙንን ችግሮች ምንነት፤ በምሉእ እይታ በተቃኘ መነጽር ተመልክተንና ተንትነን እስካልተረዳን ድረስ የምናመጣው መፍትሔ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ‹አለባብሰው ቢያርሱ› እንደሚሆንብን እርግጥ ነው፡፡ ጥቂት ለማይባሉ ዓመታት የፖለቲካ ትግላችን መሠረቱ በደል ነበር፡፡ በደልን አስበን ወደ ትግል እየተቀላቀልን፤ ተበዳይነትን ሕዝብን ለማንቀሳቀሻ መሣሪያነት እየተጠቀምን፤ በደልን በከፊል ለጊዜውም ቢሆን ማሸነፍ ችለናል፡፡

ዳሩ ግን የቀደሙ በደሎችን ምንጭ በአግባቡ ካለመረዳትና ከፊታችን ሌላ ዓይነት በደል እንዳይወለድ ለማስቀረት ባለመቻላችን የበደል ቁልል አብሮን ዘመናትን ይሻገራል፡፡ የዚህ ምክንያቱ መፍትሔዎቻችን ጊዜያዊና ቁንጽል መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያ ችግሮቹን ያየንበት መንገድ ምሉእ አለመሆኑ ነው፡፡ ወደ እውነታ ለመድረስ የነገሮችን ግንኙነት መሰናሰልና መጠላለፍ በማጤን አጠቃላይ ምሉእ እይታ ሊኖረን ይገባል፡፡ ቁንጽል እይታ አንድን ቤት በቀዳዳ አጮልቆ እንደማየት ነው፡፡ የተወሰነውን የቤቱን ክፍል ብቻ እንድናይ ነው የሚፈቅድልን፡፡

ዐይኑ ላይ ጨርቅ የታሰረበት አንድ ሰው የዝሆን ጀርባ ከዳበሰ በኋላ ምን እንደሆነ እንዲነግረን ብንጠይቀው፤ ሊነግረን የሚችለው ነገር ከእውነታው ፍጹም የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሰውዬው የዝሆኑን ጭራ ዳብሶ "ገመድ ነው" ወይም "እባብ ነው" ሊለን ይችላል፡፡ ምናልባት ይህ ሰው የዝሆኑን ሆድ ቢነካው "ግድግዳ"፤ እግሩን ሲነካ "ዛፍ"፤ ኩምቢውን ሲነካ ደግሞ "ዘንዶ ነው" እያለ በመሰለው ከመበየን ወደኋላ አይልም፡፡ የሀገራችን የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ችግሮች በዝሆን ብንመስለው እይታችን ከዚህ የሚራራቅ አይደለም፡፡

እስከዛሬ ምሉእ ሊባል በሚችል መልኩ ድል ካስመዘገብንባቸው ሀገራዊ ስኬቶች መካከል ያለፍንባቸው ጦርነቶች ግንባር ቀደምቶቹ ናቸው፡፡ ለምን ልድ ተቀዳጀን? ቢባል "በህብረትና በወኔ ስለተዋጋን" የሚል መልስ እናገኛለን፡፡ በእርግጥ ይህ መልስ መልሶ ጥያቄ ከመጫር አይመለስም፡፡ "ኅብረቱና ወኔው" እንዴት መጣ? ይህ ህብረትና ወኔ ለምን በሁሉም ችግሮቻችን ላይ አይመጣም? የሚሉ ጥያቄዎችን ያስነሳል፡፡ "ኅብረቱና ወኔው"ን ያመጣው ስለገጠመን ችግር ምሉእ መረዳት ስለያዝን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትክክለኛ የመፍትሔ መንገድ ላይ እንድንቆም አስቻለን፡፡

"ጦርነት" እንደ ህልውና አደጋ ሆኖ ሲመጣብን "በጦርነት ተሸንፎ መወረር" ምን እንደሆነ በግልጽ እናውቀዋለን፡፡ ስለዚህ ጦርነት እንደ ሀገር በአራቱም አቅጣጫ ለምንኖረው ለማናችንም ግልጽና ምሉእ የሆነ እይታ ያቀብለናል፡፡ ምሉእ እይታ ብቻ የሆነ እይታ ያቀብለናል፡፡ ምሉእ እይታ ብቻ ሳይሆን የጋራ ግብም በውስጣችን እንዲያቆጠቁጥና በአንድነት ተንቀሳቅሰን በአንድነት ድል እንድንቀዳጅ ያበቃናል፡፡

እንደ ጦርነቱ ሁሉ ሀገራችን በታሪኳ ሽክም የሆኑባት ጉዳዮች አሉ፡፡ በድህነት፤ በጭቆና (የነጻነት፤ የእኩልነት፤ የዴሞክራሲ እጦት) እና በመሳሰሉት ችግሮች ምንጭና ምንነት ላይ ያለን እይታና መረዳት ወጥነት ያለው አይደለም፡፡ ባለመሆኑም ችግሮቹን ለመፍታት አዳጋች ሆኖብናል፡፡

ሌላው ቀርቶ ጦርነቱን በስኬት ለምንና እንዴት ልናጠናቅቅ እንደቻልን በጥልቀት ተንትነን እዚያ ጋር ያለንን ልምድ ወደ ሌሎች አጀንዳዎች ለማሸጋገር በቅጡ አላሰብንበትም፡፡ ድላችንን የምንመለከትበት መንገድ በራሱ ቁንጽል በመሆኑ የድላችንን ቁልፍ ምክንያት ነገሬ ብለን ሳናስተውለው ቀርተናል፡፡

የኢትዮጵያችን ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የዓለም ታሪክ የተሞላው በድልም፤ በሽንፈትም ነው፡፡ መጠኑ እንደ ተመልካቹ ቢለያይም የእኛ የኢትዮጵያውያን ታሪክ ሁለቱንም (ድሉንም ሆነ ሽንፈቱን) አዛንቆ ይዟል፡፡ ታዲያ ካለፉ ሽንፈቶቻችን መማር ባንችል እንኳን እንዴት ካለፉ ድሎቻችን መማር አቃተን? ስህተቶችን ከመኮነንና ስለ ድሎቻችን ከመዘመር ባለፈ ለሽንፈቶቻችንና ለድሎቻችን ቁልፍ መነሻዎች ምን እንደሆኑ ሳይንሳዊና አመክኖአዊ የሆነ ትንታኔ ለመስጠት ከቶ እንዴት አስቸገረን?

ደርግንም ሆነ ኢሕአዴግን ወደ መንበረ ሥልጣን ያመጡ ጉዳዮች በጥቅል ካየናቸው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ዜጎችን በእኩል እንዳይታዩ የሚያደርጉ በሀገር ውስጥ የሚስተዋሉ በደሎች ነበሩ፡፡ በሶሻሊዝም መነጽር የተቃኘው ደርግ፣ በሀገራችን ለዘመናት የቆየና ዜጎችን ከመደብ አንጻር በእኩልነት የማያይ ሥርዓት እንዳለ አምኖ፤ ያንን ችግር ለመፍታት ተንቀሳቅሶ ነበር፡፡ በተመሳሳይ ኢሕአዴግም ኢትዮጵያውያንን ከማንነት አንጻር ለጭቆና የሚዳርግና ለእኩልነት ፀር የሆነ ሥርዓት እንዳለ ተቀብሎ ያንን ለመገርሰስ ተንቀሳቀሰ፡፡ አንደኛው እኩልነትን በቁንጽሉ ከመደብ አንጻር ሲመለከት ሌላኛው ደግሞ እኩልነትን ከማንነት አንጻር ብቻ ቆንጽሎ ተመለከተ፡፡ በቁንጽል ምልከታ የተቃኘው የሁለቱም መፍትሔ ግን የኋላ ኋላ ምሉእ መፍትሔ ሊያስገኝ አልቻለም፡፡ የእኩልነት ጥያቄ እየተንከባለለ፤ የችግሩ ምንጭ የሆነው በደልም መልክና ጠባዩን እንደ እስስት እየቀያየረ አብሮን ዘመናትን ተሻግሯል፡፡

# ሚዛን ለመጠበቅ

በ1985 ዓ.ም የካቲት ወር ላይ በምዕራብ ኦሮሚያ ቄሌም ወለጋ፤ ቤጊ በምትባል አነስተኛ ከተማ ውስጥ የአሰፋ ብርጌድ ራዲዮ ኦፕሬተር ነበርኩ፡፡ ጊዜው ኢሕአዴግ በአንድ በኩል በሀገሪቱ አንጻራዊ ሰላም ያረጋገጠበት፤ በሌላ በኩል ከኦነግ ጋር የተፈጠረውን ልዩነት ተከትሎ ሁለንተናዊ የበላይነት ያገኘበት ወቅት ነበር፡፡ ይኼንን ተከትሎ የኦነግ ታጋዮችን የማሰርና ከዚያም የከፋ ርምጃዎችን እነሱ ላይ የመውሰድ ዘመቻ እንደተደረገ ብዙዎች ያውቃሉ፡፡ ታዲያ በዚሁ ወቅት ከዘመቻው ጋር በተያያዘ በእኛ ካምፕ ውስጥ በርከት ያሉ

እስረኞች ነበሩ። ከእነዚህ መካከል አንዱ ሹማ የሚባል በኦነግ ውስጥ በኃላፊነት ይሠራ የነበረ እስረኛ ነው።

በጊዜው ከዚያ የኦነግ ሰው ጋር መጠነኛ ትውውቅ ማድረጋችንን አስታውሳለሁ። ትሕትናው፤ ሥርዓቱና ሰው አክባሪነቱ ልዩ ነበር። አልፎ አልፎም የትግል ሕይወቱን አጫውቶኛል። በግንባሩ ውስጥ የነበረው የሥራ ድርሻ የከተማ አደረጃጀት መፍጠርና የፖለቲካ ማስተባበር ሥራ መስራት ነበር። አደረጃጀት ሲባል የወታደር አይደለም። በአጭሩ ሰውዬው ካድሬ እንጂ ተዋጊ አልነበረም። እንደ ድርጅታችን አካሄድ ተገቢ ባይመስልም በወቅቱ ታጋዩን የማየው፤ በሌላ ግንባር ለፍልሚያ እንደተሰለፈ ባላንጣ ሳይሆን ልክ እንደ እኔው በገባው መንገድ ለእኩልነትና ለነጻነት እንደሚታገል፤ ፍትሕን እንደሚወድና ግፍን እንደሚጠላ አንድ መልካም ሰው አድርጌ ነበር።

አንድ ቀን በሥራ ገበታዬ ላይ ሳለሁ ‹ጥብቅ ምስጢር› በሚል ከምዕራብ እዝ የተላከ የቴሌተግራም መልእክት ደረሰኝ። የተላከው መልእክት ያ ታጋይ እንዲገደል የሚያዝ መልእክት ነበር። ዐይኖቼን ማመን አልቻልኩም።

በወቅቱ እንድደነግጥ ያደረገኝ ከሰውዬው ጋር የፈጠርኩት መጠነኛ ቅርበት እንድሳሳለት ስላደረገኝ ይሁን ሌላ ምክንያት በቅጡ አልለየሁትም። እየቆየሁ ግን አሰላስል የነበረው ስለ ሰውዬው መገደል ምክንያታዊነት ነበር። እንዴት በሰላም ሀገር፤ አንዳችም ግድያ ላይ ባልተሳተፈ የፖለቲካ ታጋይ ላይ እንደዚህ ዓይነት ውሳኔ ይተላለፋል? ደግሞስ ያለ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዴት ይገደል ይባላል? የሚል ሐሳብ ክፉኛ አእምሮዬን ሰቅዞ ያዘኝ። የመገደሉ ተገቢነት ብቻ ሳይሆን አስፈላጊነቱም ሊታየኝ አልቻለም። እንዲዚህ ያለውን የፖለቲካ ሰው መግደል ማንን እንደሚጠቅም፤ ማንንስ እንደሚያስተምር ባወጣ ባወርድ አጥጋቢ የሆነ መልስ ለማግኘት አልቻልኩም። የዚያን ዕለት ማዕበል እንደጎበኘው ውቅያኖስ ስሜቴ ርብሽብሽ እያለ ቆየሁ። በፍፁም መወሰን አልቻልኩም፤ ልቤ ለሁለት ተከፈለ። ለሰዓታት የልቤን ሚዛን ከወዲያ ወዲህ በሚያላጋ ሁኔታ ውስጥ መቆየቴን አስታውሳለሁ።

በወቅቱ የሥራ ድርሻዬን መልእክቱን ተቀብዬ ማስተላለፍ ነበር። ወታደር እንደ መሆኔ እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን እምቢ የማለትም ሆነ የመጠየቅ ሥልጣን የለኝም። ወታደራዊ የእዝ ሰንሰለቱን አክብሬ መልእክቱን ካስተላለፍኩ ያለጥርጥር ያ ታጋይ ይገደላል። ይህ አማራጭ የሚያስከትልብኝ የሕግ ተጠያቂነትም ሆነ ወቀሳ እንደሌለ ዐውቃለሁ። ነገር ግን ጉዳዩ የኅሊናም ጥሪ እንጂ የሕግ ጉዳይ ብቻ አልነበረም።

በአንድ በኩል ሲታይ፣ መልእክቱን ለሚመለከተው ሐላፊ እኔ ካላስተላለፍኩ በቀር ማንም ውሳኔውን ሊያውቅ እንደማይችል ተረድቻለሁ። ይሄ ደግሞ የዚህ ንጹሕ ታጋይ ሕይወት በእጄ ውስጥ ያለ ሆኖ እንዲሰማኝ አደረገ። ኅሊናዬ ሕይወቱን ማትረፍ አለብህ ይለኛል። በአንጻሩ ቢታወቅብኝ ድርጊቴ ከባድ የሆነ ተጠያቂነትና አደጋም ሊያስከትልብኝ እንደሚችል ግልጽ ነው። እኔ ራሴ በኦነግነት ተጠርጥሬ ከእርሱ ላልተናነሰ ቅጣት ልዳረግ እችላለሁ። ኅሊናዬ ግን ንጹሕ እንደሆነ ይቆያል። እንዲህ ባለ የአእምሮ ሙግት ውስጥ ቆይቼ በመጨረሻ ወሰንኩ።

በጣም ከማምናቸው ጥቂት ጓዶች ጋር ተመካክረን አንድ ነገር አደረግን። ታጋዩንም በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ከእስር ቤት አስመልጠን የውሳኔውን ተፈጻሚነት አከሸፍነው። ከዚያ በኋላም ለፖለቲካ ትርፍ ሲባል ያለአግባብ

ርምጃ ሊወሰድባቸው ሲል መረጃ ደርሶኝ ያስጠነቀቅኳቸውና ምናልባትም በዚያ መረጃ መሠረት ከሞት እስከመዳን የደረሱ ሌሎች ሰዎች አሉ። ሆኖም የዚያን ታጋይ ያህል ስለሚተላለፉ ውሳኔዎች ጭንቀት እንዲገባኝ ያደረገ አጋጣሚ አልነበረም። ይህ ውሳኔዬ በኋለኛው የፖለቲካ ሕይወቴ ውሳኔዎችን እንድመረምርና ከእውነት ጎን እንድሰለፍ በር ከፈተ። አዎ ነገሮችን የመጠየቅና ውሳኔዎችን የመፈተሽ አዝማሚያ በጉልህ ማሳየት የጀመርኩት በዚያ ታጋይ ምክንያት እንደነበር አስታውሳለሁ።

ሀገር የሚመራበት ሥርዓት ሚዛኑን ጠብቆ እንዲጓዝ የሚያስችሉት ብዙ ነገሮች ይኖራሉ፤ ዋነኞቹ ግን ተቋማት ናቸው። እነዚህ ተቋማት ዐቅማቸው እየደከመ ሲሄድ በሥርዓቱ ውስጥ ግለሰቦች ጉልበታቸው እንዲፈረጥም ዕድል መፍጠሩ አይቀርም። ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ዴሞክራሲ ሊወለድባቸው ገና ብዙ ትግል በሚቀራቸው ሀገራት ነጻ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማካኼድ ሜዳውን ለሁሉም ክፍት ማድረግ ብቻ አይበቃም። ሂደቱ ያለ ችግር እንዲከናወን፣ ግለሰቦች ያለመሸማቀቅና ያለጥቃት እንዲሳተፉ፣ የዴሞክራሲና የፍትሕ አካላት ሚዛን የመጠበቅ ሚናቸውን በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል። ይህ ካልሆነ የሥርዓቱ ሚዛን የሚጠበቀው በግለሰቦች በጎ ፈቃድ መልካም ሰብእና ላይ ተመሥርቶ ይሆናል። የግለሰቦች ፈቃድ በተቀያየረና የሰብእና መዋዠቅ ባጋጠመ ቁጥር የሥርዓት ተዋናዮች ጤናማ የሆነ ቆይታ ማድረግ ይሳናቸዋል። ሥርዓቱም በጊዜ ሂደት እየታመመ ይመጣል።

በሀገራችን እውነተኛ ዴሞክራሲ መገንባት _ ካለብን የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥተን ልናከናውን የሚገባን ነገር ቢኖር፤ በሥርዓት ውስጥ የተቋማት ሚዛን የማስጠበቅ ሚና እየጨመረ፣ የግለሰቦች ሚዛን የማስጠበቅ ሚና እየቀነሰ መሄድ እንዲችል ማድረግ ነው።

# የመማር ዕድሎች

"ዕውቀትን ከአንቀልባ እስከ መቃብር ፈልጓት!"

- ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)

መደመር 'ላም አለኝ በሰማይ' ዓይነት የማይጨበጥ ሕልም አይደለም። መደመር ያለጥልቅ መረዳትና ሙሉ መሰጠት የሚጨበጥም አይደለም። መደመር ሩቅ አልሞ ከትንሽ የሚጀመር የሺሕ ማይል ጉዞ ነው። የመደመር መንገዱ የዛሬን ዐቅም ሰብስቦ በትናንት ጥሪት ላይ በማከል፣ ለነገው የብልጽግና መዳረሻ ወረት እያካበቱ መሄድ ነው። ለነገው ሥራችን ስኬት የዛሬ ጥረታችንና የትናንት ጥሪታችን እጅግ ወሳኝ ናቸው። የመደመር መንገድ ከሌላ ፍጥረታት ሁሉ በላይ በሰው ልጆች ዘንድ ይሠራል። ምክንያቱም ሰዎች ማሰቢያ አእምሮ አላቸውና ያልማሉ፤ ግብ ያስቀምጣሉ፤ ያቅዳሉ፤ ከዚያም የጊዜን ሥርዓት ጠብቀው ይተገብራሉ። በሕይወት ውስጥ መሻሻል የሚያመጣው ርምጃችን ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚከናወንና ሳይጨናገፍ የሚፈጸም ከሆነ ብቻ ነው።

በሕይወቴ ብዙ የመማር ዕድሎች አጋጥመውኛል። ብዙዎቹ ዐቅም የፈጠሩልኝ፤ ትናንት ከነበረኝ የተሻለ ብቃት እንዲኖረኝ በማድረግ፣ በዕውቀትና በቅልጥፍና፣ በትዕግሥትና በመሪነት እንዳድግ ረድተውኛል። መደመርም

አብሮኝ እንደ ሐሳብ እየጎለበተ የመጣው በዚሁ መልኩ ነው።

የመደመር ትርጉም ራሱ እንደሚጠቁመው የዛሬን ዕድል _ በመጠቀም፣ ትናንት ባከማቸሁት ልምድና ዕውቀት ላይ በመመሥረት፣ ለነገ የሚሆነኝን ዐቅም በማካበት ላይ ነበርኩ። ይህ ደግሞ በአንድ ወቅት ላይ የሰማሁትን ታሪክ ያስታውሰኛል።

አንድ የንሥር ጫጩት እናቱ መብረር ስታለማምደው ቆይታ በመጨረሻ "አሁን ያለእኔ ድጋፍ መብረር ስለምትችል ከእንግዲህ ብቻህን ከጎጆ ወጥተህ ክንፍህን ማንቀሳቀስ ትችላለህ" አለችው።

ጨቅላው ንሥርም በደስታ ከጎጆ ሲወጣ በአቅራቢያው አንድ አሳማ ሲሮጥ ያያል። በደስታ ውስጥ ሆኖ እንዲህ ሲል ለእናቱ ነገራት "እዬውማ! ያንን ጮማ የሆነ አሳማ" አለና ሄዶ ለቀም ሊያደርገው ተጣደፈ።

"ተው ተው የኔ ልጅ፣ እሱ ይቅርብህ" በማለት፤ ተቃወመች የንሥሩ እናት። "አንተ አሁን አሳማ ለማደን አልደረስክም፤ ገና ነህ። ባይሆን አነስ አነስ ያሉትን አይጦች በማደን ብትጀምር ጥሩ ነው፤ ጉልበትህ መጠንከር አለበት" አለችው።

ንሥሩ በእናቱ ክልከላ በመጠኑ ቅር ቢሰኝም ምክሯን ግን ለመስማት አላመነታም። ከዚያ እየዞረ አይጦችን እያደነ ይበላ ጀመር። መጀመሪያ ላይ አይጦቹን ለመያዝ በጣም ተቸግሮ ነበር። እየቆየ ግን አያያዙን ስለለመደው በቀላሉ ለቀም ያደርጋቸው ጀመር። እያደገ ሲመጣ አይጥ ማደኑ እጅግ በጣም ቀላል ሆነበት፤ ሥጋቸውም አላጠግብ አለው። በዚህ መሐል ግዙፉን አሳማ ሲሮጥ ተመለከተው።

"እሃ! አሁን ተገኘህ፣ መጣሁልህ ጠብቀኝ" ብሎ፤ ወደ አሳማው ሊወረወር ሲል እናቱ በድጋሚ አስቆመችው።

"አሁን ጥንቸል ምናምን ማደን ጀምር። አሳማውን ለጊዜው ተወው" አለችው።

ሳያመነታ ንሥሩ አሳማውን ትቶ ጥንቸል ማደን ጀመረ። ሆኖም ጥንቸሎቹ እንደ አይጥ ለማደን ቀላል አልሆኑለትም። ሲሮጡ አይጣል ነው። ደርሶ ለቀም ሊያደርጋቸው ሲል እጥፍ ብለው አቅጣጫ ይቀይሩበታል። መጀመሪያ አካባቢ ቀኑን ሙሉ ታግሎ አንድ ጥንቸል ለመያዝ ይከብደው ነበር። እየቆየ ሲሄድ በቀን ሁለትም ሦስትም መያዝ ለመደ። በዚህ መሐል የተለመደው አሳማ ትውስ ሲለው ከእንግዲህ እሱን ማደን አለብኝ ብሎ ተነሣ። ችግሩ ግን አሁንም እናትየው አልፈቀደችለትም።

‹‹በጥንቸሎቹ ቅልጥፍናን ብትማርም ክብደት ያለው ነገር መሸከምን ደግሞ በግና ፍየሎችን በማደን መለማመድ አለብህ!" ስትል ነገረችው።

ንሥሩም እንደተባለው አደረገ። ብዙ በግና ፍየሎችን እያደነ ሲበላ ከረመ። እንደተለመደው በግ ሊያድን ሲወጣ ያንን አሳማ አየው። ዞር ብሎ እናቱን ሲመለከት በዐይኗ "አሁን ነው ጊዜው" የሚል ምልክት ሰጠችው። ከንፉን እያማታ ሽቅብ ወጣና አነጣጥሮ ቁልቁል ተወረወረ። ተወርውሮም አልሳተው፤ አፈፍ አደረገው። የጊዜ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ዐቅሙን ሲያከማች መቆየቱ አሳማውን ያለ ችግር እንዲጨብጥ አደረገው።

አዘውትሬ እንደምለው ውዷ እናቴ በሕፃን ልቤ ውስጥ ተክላ በማይናወጥ እምነቷና በማይቋረጥ ንግግሯ ስትኮተኩተው የኖረችው የራእይ ቡቃያ አለ። ይህ ቡቃያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየደመቀ በውስጤ

የማይገረሰስ ኃይል እየሆነ እንዲመጣ ያስቻሉ ብዙ አጋጣሚዎች ነበሩ። በተለይም በኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ (ኢመደኤ - INSA) ያሳለፍኩት ጊዜ የሥራ ሕይወቴ ወርቃማው ነበር ማለት እችላለሁ። በኢንሳ በነበርኩባቸው ዓመታት ብዙ የመማር ዕድሎች ተፈጥረውልኛል።

ኢንሳ ውስጥ ልብ የሚያሞቁና በመሪነት ዙሪያ ጽኑ ተስፋ እንድሰንቅ የሚያደርጉ መልካም ተግባራትን ለመፈጸም ችያለሁ። ተደጋግሞ እንደሚባለው የመሪዎች ስኬት የሚለካው አንድም መሪነታቸውን ተጠቅመው በፈጠሩት ለውጥ፣ ሁለትም ባፈሯቸው ተተኪ መሪዎች ቁጥር ነው። ኢንሳ ውስጥ ሳለሁ በሰዎች ውስጥ የተዳፈነውን እምቅ ዐቅም በማቀጣጠል ከተራ ሞያተኞችና መደበኛ ሠራተኞች ውስጥ እንዴት ታላላቅ መሪዎችን ማውጣት እንደሚቻል ተረድቻለሁ። የፈጠራ ዐቅማቸው በቅጽበት እንዴት ሊጎለብት እንደሚችል ምስጢሩን ደርሼበታሁ። በተለይም የመደመር መሠረታውያንን በመጠቀም በተፋዘዘ ዐውድ ውስጥ ተነሣሽነትን መፍጠር እንደሚቻል አይቻለሁ። የጋራ ራእይንና ግብን ከማስታጠቅ በተግባር እስከ ተፈተነ የመሪነት ልምምድ ያደረግኩበት ቦታ ነው፤ ኢንሳ።

ኢንሳ በተቋቋመበት ወቅት ሠራተኞችን ስንቀጥር ለባለልዩ ተሰጥኦ ወጣቶች ልዩ ትኩረት ሰጥተን ነበር። ሠራተኞች የተቀጠሩት የአእምሮ ዐቅማቸው ብቻ ሳይሆን ስሜትን ተቆጣጥሮ የመሥራት ዐቅማቸው ጭምር ተገምግሞ ነበር። ከኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ጸጋዎች ለመማርና ኢትዮጵያን በተሻለ ለመረዳት ሠራተኞቹ ከተለያዩ ብሔሮች የተውጣጡ እንዲሆኑ አድርገናል። በዚህም መልኩ ኢንሳ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከ30 ብሔሮች የተውጣጡ ወጣት ምሁራንን አቅፎ የያዘ የትራንስፎርሜሽን ተቋም ሆነ።

ኢንሳን የትራንስፎርሜሽን ተቋም ማድረግ ጉዞው አልጋ በአልጋ፣ ስኬቱም ቀላል አልነበረም። መደመርን የተቋሙ ዕሴት ስናደርግ ለይስሙላ በባነር ላይ ተጽፎ ግድግዳ እንዲያሞቅ አልነበረም።

የመደመር መርሖች አነሰም በዛ ተግባራዊ የሆኑበት፣ ተፈትሸውም ውጤት ማስገኘታቸውን ያረጋገጥንበት ወቅት ነበር። ከተለያዩ የሞያ ዘርፎች፣ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችና ከተለያየ የልምድ ደረጃዎች የተውጣጡት ሠራተኞች ተግባብተው ለአንድ ዓላማ እንዲተጉ በጥንቃቄ ማሰናኘት ተቻለ። ተቋማት ተመሥርተው በእግራቸው ለመቆም ዓመታት በሚፈጅበት ሀገር በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢንሳ ሙሉ በሙሉ በራሱ ዐቅም የሚንቀሳቀስ ተወዳዳሪ ኢትዮጵያዊ ተቋም ሆኖ ወጣ። በተቋማት ውስጥ ሠራተኞችን በአግባቡ አሰናኝቶ ለማሠራት መጣጣር በሀገራችን በተለይም በመንግሥት ቢሮዎች ውስጥ ብዙም የተለመደ አይደለም። መደመር በተቋማትም ሆነ በየትኛውም የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ሠራተኞች በግላቸው የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ተደምሮ ከሚያመጣው ተጽዕኖ በበለጠ ውጤት ለማግኘት የሚያስችል የመሰናኘት ሂደት ነው።

የሀገራችን ገበሬ ያረጀ በሬውን ከወይፈን ጋር አቀናጅቶ ያርሳል። ገበሬው ሁለት ወይፈን ቢጠምድ የእርሻው ትልም ይበላሻል፤ ቀንበሩም ይሰበራል። ያልተገራ ጉልበት ትርፉ ብልሽት ነው። ሁለት ያረጁ በሬዎችን ቢጠምድ የዕለቱን በሳምንት፣ የሳምንቱን በወር አይጨርሰውም። ዐቅም ያጠረው ክዋኔ ትርፉ ጊዜ መውሰድ ነው።

ለዚህ ነው ገበሬው ያረጀውን በሬ ከትኩሱ ወይፈን ጋር በአንድ ላይ የሚጠምደው። በሬው ልምዱን፣ ወይፈኑ

ጉልበቱን ያዋጣል። ሁለቱ በየግላቸው ከሚያበረክቱት አስተዋጽዖ በላቀ መልኩ ተደምረው የተሻለ ውጤት ያስገኛሉ።

በዚህ ዓለም ስንኖር እያንዳንዳችን የብቸኝነት ጉድለት አለብን። ምንም ነገር በራሱ ምሉእ አይደለም። ይሄንን የተፈጥሮ ሕግ ከተቀበልን በዙሪያችን ያሉት ነገሮች ጉድለታችንን ሞልተው ለምሉእነት የሚያበቁን ናቸው። ለእኔ ይህ በኢንሳ ሳለሁ የተገነዘብኩት እውነታ ነበር። በነበረኝ ቆይታ የመደመርን ፅንሰ ሐሳብ ታላቅነት ሞክሬ አረጋግጫለሁ። ይህም በራሴ የነበረኝ እምነት ከፍ እንዲል አድርጎኛል።

‹‹መደመር›› ተቋምን በተሻለ ለመገንባት፤ ‹መደመር ሀብትን በተሻለ ለመፍጠር›፤ ‹‹መደመር›› ግብን በተሻለ ለማሳካት አዋጭ መንገድ ለመሆኑ እኔ ሕያው ምስክር ነኝ። ከምንም ነገር በላይ መደመር የተወሳሰበ ሥርዓትን በተሻለ ለመምራት እንደሚያስችል በእጄ ሠርቼ በዐይኔ አይቻለሁ። መደመር አንድ ተቋም ራሱን በራሱ ማረም ወደሚችልበት ሥርዓት ለማሳደግ እንደሚያበቃ በኢንሳ ቆይታዬ ዕውቀቶችን ገብይቻለሁ። ይህ ጊዜ በውስጤ ከተፈጠረው ለውጥ በተጨማሪ ሌሎች በእኔ ላይ ያላቸውንም አመኔታ አሳድጓል። የመደመር ጉዞውን ወደፊት ገፍቶ አፋጥኖታል።

‹‹መደመር›› ከብዙዎች ጋር ወዳጅነት ያፈራሁበትና የጠበቀ ግንኙነት እንድመሠርት ያስቻለኝ እሳቤ የመሆኑን ያህል፤ የብዙ አካላትን ጥርስ ያስነከሰብኝና ገናም ብዙ ዋጋ የሚያስከፍለኝ መሆኑን በግልጽ የተማርኩትም እዚያው ተቋም ውስጥ ነበር። ከዚያ ከወጣሁ በኋላ ዐይኖቼ ወደ ፖለቲካው መንደር በሰፊው ማማተር ሲጀምሩ ጥቂት ከማይባሉ ሰዎች ጋር መላተሙ _ አልቀረልኝም። እንደኔ አመለካከት ፖለቲካዊ እምነታችን በከረጢት እንደተሞላ የእህል ዱቄት በአንድ ቡድን ውስጥ አጠራቅሞ የሚቋጥረን መሆን የለበትም። በውስጣችን ያለውን እምቅ ዐቅም በማውጣት፣ የሐሳብ ነጻነትን በማንሸራሸር፣ ወደ ላቀ ከፍታ ወጥተን እንድንራመድ የሚያዘጋጀን መንገድ ሊሆን ይገባል። ፖለቲካችን እኛኑ መምሰልና ማንነታችንን ማገናዘብ ይኖርበታል። እኛን መምሰል ሲባል ደግሞ ኢትዮጵያን መምሰል ማለት ነው።

ኢሕአዴጎች ከአራቱም አቅጣጫ የተሰባሰብን፣ ከተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች የተውጣጣን ነን። ፖለቲካችንም ሐሳባችንን ብቻ ሳይሆን እኛነታችንን ጭምር አሰናኝቶና በሚዛን ቃኝቶ ማስኬድ አለበት የሚል እምነት ነበረኝ። ይኼንን ግን በወቅቱ ሀገሪቱን ይመሩ የነበሩት ፖለቲከኞች ሊቀበሉት የሚፈልጉት ሆነ፤ ሊሰሙት የሚችሉት ነገር አልነበረም። ስለሆነም የልብ እምነቴን እንደ ካህን በጣፈጠ አንደበት እያዋዙ፣ በፖለቲከኛ ጽናት ነክሶ ከመጓዝ ውጭ የተሻለ አማራጭ አልነበረኝም።

በዚህ ጉዞ አልፎ አልፎ በመገለልና በመገፋት ውስጥ አሳልፌያለሁ። ያንን ዘመን ለጥናት፣ ለምርምርና ለተሻለ ዕውቀት ተጠቅሜበታለሁ። ቀጣይ የፖለቲካ ሕይወቴን በተመለከተ አሻራው የሚነበብ ንድፍ ከመቅረጽ በተጓዳኝ ውጤታማ ብቃትን የመቀዳጃና ጉድለትን የመሙያ ጊዜ እንዲሆን አድርጌዋለሁ።

# ቤተኛ ባይተዋርነት

ጆርጅ ዚመል የተባለ የሥነ ማኅበረሰብ ጥናት ሊቅ ቤተኛው ባይተዋር (ዘ ስትሬንጀር) የተሰኘ ጽሑፍ አለው።

ይህ በብዙ መስኮች ላይ ተጽዕኖውን ያሳደረ ጽሑፍ ቤተኛ ባይተዋርነት ያለውን ልዩ ባሕርይ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ዚመል እንደሚለው ቤተኛ ባይተዋር ማለት፤ ቤተኛነትንም ባይተዋርነትንም በአንድ ላይ አጣምሮ የያዘ ሕይወት ማለት ነው። ቤተኛ ባይተዋር ከእንግዳ ይለያል፤ እንግዳ ዛሬ መጥቶ ነገ የሚሄድ ሲሆን ቤተኛ ባይተዋር ግን ዛሬ መጥቶ ነገም የሚቆይ ነው። የውጭ ሰው አይደለም፤ መጥቶ የሚሄድም አይደለም። በአንድ በኩል የውስጥ ሰው ነው፤ በሌላ በኩል የውጭ ሰው ነው። መንታ ሥሪት አለው። ቤተኛ ባይተዋር በአንድ ቡድን ውስጥ የቡድኑ አባል ሆነው ነገር ግን የተለየ የተግባር ወይም የአስተሳሰብ ልምድ ያላቸው ሰዎች ጠባይ ነው።

የቤተኛ ባይተዋርነት ንድፈ ሐሳብ ፈጣሪው ጆርጅ ዚመል በዚሁ የቤተኛ ባይተዋርነት ተፈጥሮ ውስጥ ያለፈ ይመስላል። ዚመረ በጀርመን የሚኖር አይሁዳዊ ሊቅ ነበር። በአንድ በኩል ጀርመናዊ ነውና ከጀርመን ጋር የነበረው ትስስርና ቤተኝነት አለ። በሌላ በኩል ደግሞ አይሁዳዊ በመሆኑ ምክንያት ዝናው የናኘ ምሁር ቢሆንም እስከ ሕይወቱ መገባደጃ ድረስ መደበኛ የዩኒቨርሲቲ መምህር ለመሆን አልተፈቀደለትም።

ተማሪዎች እየከፈሉት ነው ያስተምር የነበረው። ይህ ሁኔታ ለዚመል: የቤተኛ ባይተዋርነትን ጠባይ እንዲያዳብር አድርጎታል። ብዙ አዳዲስ ሐሳቦችን በመፍጠር ረገድም አስተዋጽዖ አድርጎለታል። ካርል ማርክስ፣ ሲግመንድ ፍሮይድ፣ አልበርት አንስታይን እና ሌሎች መሰል አይሁድ-ጀርመናውያን ሊቃውንት ይህ የቤተኛ ባይተዋርነት ጠባይ ነገሮችን በተለያየ አቅጣጫ ለማየት ዕድል የሰጣቸው ይመስለኛል።

ቤተኛ ባይተዋርነት የውስጥም የውጭም እይታ እንዲኖረን ዕድል ይሰጣል። ስለ አንድ ተቋም ከውስጥ የሚያዩት የተቋሙ ባልደረቦችና ከውጭ ሆነው ተቋሙን የሚመለከቱ እይታ አይኖራቸውም። የተቋሙ ባልደረቦች የተቋሙን ስኬት አጋንነው መመልከታቸው አይቀርም። በተቋሙ ውስጥ ሆነው እየለፉ ነውና የተቋሙን ብርታት እንጂ ስሕተቱን ለመመልከት ይከብዳቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ከውጭ ሆነው ተቋሙን የሚመለከቱ ሰዎች የተቋሙን የውስጥ ጥረትና ያለበትን ተግዳሮት አይመለከቱም። የተቋሙን ጥረትና ስኬት ዘንግተው ጉድፍ ፍለጋ ላይ ብቻ ያተኩራሉ። እውነቱ ያለው በእነዚህ በሁለቱ መካከል ነው።

ቤተኛ ባይተዋርነት የውስጥንም የውጭንም እይታዎች በማካተት ሚዛናዊ እይታ ይፈጥራል። ቤተኛ ባይተዋሮች በሌሉበት ከባቢ ውስጥ ለውጥ እንደ ከዋክብት የራቀ ጉዳይ ይሆናል። ይህ መንታ ሁኔታ ነው ቤተኛ ባይተዋሮችን የለውጥ ለኳሾች የሚያደርጋቸው።

ኢሕአዴግን ከውጭ የሚመለከቱ ሰዎች ኢሕአዴግ ውስጥ በተግባር የተሠራውን ሥራ፣ የተደከመውን ድካም፣ የተደረገውን ጥረትና የመጣውን ስኬት ሁሉ ገደል ከትተው የኢሕአዴግን ስሕተቶችና ድክመቶች ብቻ ያወራሉ።

እነዚህ ሰዎች ስሕተትን ለመጠቆም፣ ጎደሎን ለመሙላትና አቅጣጫ ለማሳየት የውጭ ተመልካችነታቸው ያግዛቸዋል። በአንጻሩ የመሪነት ቦታ ላይ ሆነው መሬት ላይ ያለውን እውነታና የውስጡን ውጣ ውረድ ስለማያስተያዩት ከተጨባጭ እውነታ መራቃቸው አይቀርም። እዚህ ጋር እውነት ሁሉ ተጨባጭ እውነት አለመሆኑን ልብ ይሏል።

በሌላ በኩል ኢሕአዴግን ከውስጥ የሚመለከቱት ሰዎች ሃያ አራት ሰዓት ስለ ኢሕአዴግ ስኬትና ድል ማውራት አይሰለቻቸውም። የኢሕአዴግ ድክመቶች ግን ፈጽመው አይሸቷቸውም። ችግሮቹን ከመላመዳቸው ብዛት የችግሮቹን መጥፎ ሽታ እንደ መልካም መዓዛ ለማጣጣም መሞከራቸው አይቀርም።

ኢሕአዴግ የውስጥና የውጭ እይታዎችን አጣምሮ ይዞ ድርጅቱን መለወጥ የሚፈልግ ሰው ያሻው ነበር። ኢሕአዴግ ተቃዋሚ ኢሕአዴግ ያስፈልገው ነበር። ተቃዋሚ ኢሕአዴግ የውጭንና የውስጥን እይታ አካትቶ ኢሕአዴግን የሚለውጥ የኢሕአዴግ ሰው ማለት ነው። ኢሕአዴግ ከውጭ በሚነሣ የአልፎ ሂያጅ ትችት ብቻ ሊለወጥ አይችልም። ከውስጥ በሚደረግ የመታበይ ስሜትና የድል ትርክት ብቻም ሊከርም አይችልም።

ቤተኛ ባይተዋርነት ባሳለፍነው ልምድ ወይም የአስተሳሰብ ጎራ ብቻ የሚመጣ አይደለም። ሰዎች ቤተኛ ባይተዋርነትን በራሳቸው ጥረት ሊያመጡት ይችላሉ። ጆሴፍ ሉፍት እና ሃሪ ኢንግሃም የተባሉ የሥነ ልቡና ምሁራን፤ “የጆሃሪ መስኮት” የተሰኘ ዝነኛ የጠባይ መግባቢያ ዘዴ ፈጥረዋል። ዘዴውን ጆሃሪ የሚል ስያሜ የሰጡት የስማቸውን የመጀመሪያ ፊደላት ጆሴፍ እና ሃሪ በማጋጠም ነበር። በጆሃሪ መስኮት ንድፈ ሐሳብ መሠረት ሰብእናችን በአራት መስኮቶች ሊታይ ይችላል። “ለሁላችን የሚታይ፣ ለእኛ የተሰወረ፣ ለሌሎች የተሰወረ፣ ለሁላችን የተሰወረ” ይሰኛሉ፤ አራቱ መስኮቶች።

**ለሁሉ የሚታየው ጠባይ -** ግልጽና ለመግባባት ምቹ የሆነው ባሕርያችን ነው። ይኼን ጠባያችንን እኛም ራሳችን እናውቀዋለን፤ ሌሎች ሰዎችም ይኼንን ጠባያችንን ያውቁልናል።

**ከባለቤቱ የተሰወረው ጠባይ -** ሰዎች የሚያውቁት እንጂ እኛ የምናውቀው አይደለም። “ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው” እንደሚባለው። ሰዎች ስለእኛ የሚያውቁት፣ እኛ ራሳችን ግን በፍጹም የማናውቀው ጠባይ አለን።

**ከሌሎች የተሰወረው ጠበይ** - እኛ ራሳችን እናውቀዋለን እንጂ ሌላ ሰው አያውቅልንም። እኛ እያወቅነው ሰው ግን በሌላ መልኩ ከተረዳን ይኼ ጠባያችን ለሌሎች ሰዎች የተሰወረ ነው ማለት ነው።

**ለሁሉ የተሰወረው ጠባይ -** ይህ እኛም ሆንን ሌሎች ሰዎች በግልጽ የማናውቀው በጨለማ ያለ ስውር ጠባያችን ነው።ለምሳሌ ያህል እኛም ሆንን ሌሎች ሰዎች የማናውቀው ድብቅ ዐቅምና ችሎታ ሊኖረን ይችላል። በአጠቃላይ ይህ የማንነታችን መስኮት ማንም ምንም ሊመለከትበት የማይችል ጸሊም መስኮት ነው።

የሰው ልጆች እርስ በርስ ለመተባበርና አንዱ ባንዱ ላይ እምነት ለማሳደር ይችል ዘንድ ለሁላችን የሚታየው የሰብእናችን መስኮት ሊሰፋ ይገባል። ይኼ መስኮት እየሰፋ ሲመጣ ነው መደመር እውን የሚሆነው። ይኼ መስኮት እንዲሰፋ ራስን በግልጽነት ተጋላጭ ማድረግና የሌሎችን ግብረ መልስ በጸጋ መቀበል ያስፈልጋል።

ለሌሎች የተሰወረውን ማንነታችንን ሌሎች እንዲረዱልን ለማድረግ ራሳችንን ተጋላጭ ማድረግ ያስፈልገናል። ሰዎች የማያውቁልን ብዙ መልካም ሐሳብና ቅን ምኞት ሊኖረን ይችላል። ሆኖም ይኼንን መልካም ሐሳባችንን ለሌሎች ለማስረዳትና ራሳችንን ለሌሎች ግልጽ ለማድረግ ካልቻልን ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ሊረዱን ይችላሉ። በረጅም ጊዜ ሂደት ሐሳቤን ለአጋሮቼ በግልጽ ባላስረዳ ኖሮ የገዛ ወዳጆቼ እንኳን እንቅስቃሴዬን በሌላ ሊተረጉሙብኝና የመደመርን ጉዞ ሊያጨናግፉት ይችሉ ነበር። ራሳችንን ለሌሎች ካልገለጽን ብዙ

መልካም ነገር ብናስብና ብንሠራ እንኳን ሌሎች ሰዎች ይኼንን አይረዱልንም። አልተረዱንም ብለን ከማዘንና ሰዎችን ከመከሰሳችን በፊት ራሳችንን በትክክል ስለ መግለጻችን ማሰብ ይኖርብናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ለእኛ የተሰወረውን ጠባያችንን ለማወቅና ለማስተካከል ከሌሎች ሰዎች ግብረ መልስ መቀበል ያስፈልጋል። ለራሳችን የማይታወቀን ብዙ ጉድለት ሊኖርብን ይችላል። ጉድለታችንን የምንሞላው ሰዎች ስለ እኛ የሚሉትን በመስማትና ስሕተታችንን በግልጽ እንዲነግሩን በማድረግ ነው።

ራስን ተጋላጭ ማድረግና ግብረ መልስ መቀበል የመደመር ዋልታና ማገር ናቸው። ሰዎች ባይረዱንም በትዕግሥት ስለራሳችን ማስረዳት፣ ማሳወቅና በተግባር ማሳየት ያስፈልገናል። በሌላ በኩል ደግሞ እኛ ስለራሳችን ያልተረዳነው ድክመትም ሆነ ጥንካሬ ካለ ሰዎች እንዲያስረዱን ዕድል መስጠት አለብን። ይህ ሲሆን ለሁላችን የሚታየው መስኮት እየሰፋ ይመጣል። አንዱ ስለአንዱ ስለሚያውቅ ለመግባባት፣ ለመተማመን፣ በጋራ ለመሥራት አንቸገርም። ለመደመር አንቸገርም።

ይህ የጆሃሪ መስኮት የቤተኛ ባይተዋርነትን የአስተውሎት ጥቅም ያላብሰናል። የውስጥና የውጭ እይታ እንዲኖረን ያደርጋል። የውስጥ እይታን ለሌሎች በማካፈልና የውጭ እይታን ከሌሎች በመቀበል መደመር እንችላለን። በመናገርና በማዳመጥ መደመር እንችላለን። ሌሎች ቀና ሐሳባችንን እስካልተረዱን ድረስ ቀና ማሰባችን ብቻ ትርጉም የለውም። ስለዚህ ሁሌም ሌሎች ሐሳባችንን እንዲረዱና ማንነታችንን እንዲያውቁ ከመናገር መቆጠብ የለብንም።

ሌሎች የሚነግሩንን እስካልሰማንና ራሳችንን እስካልፈተሸን ድረስ መናገርም ብቻውን እንደ ሸንቁር እንስራ ፍጻሜው ባዶነትና ለምንም የማይጠቅም ሆኖ መጣል ብቻ ነው።

ሁሌም ራሳችን የምናውቀውን ነገር ሰው ደግሞ እንዲነግረን ብቻ የምንፈልግ ከሆነ ቤተኛ ባይተዋርነታችን አይዳብርም። የራስን ጩኸት መልሶ እንደማዳመጥ ነው። ራሳችንን ማወቅ ይሳነናል። ኢሕአዴግ ለውጥ ማምጣት የሚችለው ከሁለት በኩል በሚመጣ ሰይፍ ነበር። ያሉበትን ስሕተቶች ከሌሎች አስተያየት እየተቀበለ በማረምና የሠራቸውን በጎ ሥራዎችና ሀገር በማስተዳደር ሂደት ውስጥ መሬት ላይ ያለውን ተግዳሮት ደግሞ በግልጽ ለሌሎች በማስረዳት ነው።

እኛ ያደረግነው ይኸንኑ ነው። ከጥርጣሬና ከመጠላለፍ ፖለቲካ ነጻ የምንወጣው በሌሎች መንደር ምን ይባላል? ብለን ካዳመጥናቸውና ሌሎች ስለእኛ የማያውቁትን ከነገርናቸው ብቻ ነው። ሁሉም በየጎራው የራሱን ብቻ የሙጥኝ ብሎ ካጉረመረመና ራሱን ብቻ ከሰማ ለውጥ አይኖርም። ሁለቱም ነገሮች ያስፈልጋሉ፤ ራስን ማወቅና ራስን ማሳወቅ። ይህ ሲሆን ነው ሁላችንም ነፍስ ለነፍስ መደማመጥ የምንችለው። በአራቱ የጆሃሪ መስኮቶች መካከል እየተመላለሱ የራስንና የሌሎችን ምልከታ ተጠቅሞ ራስን መፈተሽና ለማሳደግ መሞከር በእመርታ ለመደመር ወሳኝ ርምጃ ነው። ሐሳብን መናገርና የሌሎችን ሐሳብ (ግብረ መልስ) ማዳመጥ ቀስ በቀስ ተመሳሳይ አቋምና ራእይ ያላቸው ሰዎች እየተሰባሰቡ እንዲሄዱ ያደርጋል። ይኸም የብቸኝነትን ጉድለት በመሙላት ዐቅም ለመፍጠር ያስችላል። ኢንሳ ውስጥ በነበርኩባቸው ዓመታት ያደረግኩት አንዱ ስኬታማ ሥራ ሰዎችን ማብቃትና የተሻለ ነገን እንዲያልሙ ማነሣሣት እንደሆነ ቀደም ብዬ

ገልጫለሁ። ይህ ጥረቴም በአጭር ጊዜ ፍሬ ማፍራት ጀምሮ ነበር። እንደውም በአንድ ወቅት ኢንሳ ላይ እየተፈጠረ የነበረውን ዐቅም ይበልጥ በሁሉም ደረጃዎች ተደራሽ ለማድረግ አስበን ነበር። ለዚህም ከሀያ በላይ የሚሆኑ በኢንሳ ጥሩ ዐቅም የፈጠሩ መካከለኛ አመራሮችን ወደ ሌሎች የመንግሥት ተቋማት እንዲዘዋወሩ ማድረጋችን አብነት መሆን ይችላል።

# ኑ እንዋቀስ!

እንደ ሀገር በፖለቲካ ታሪካችን በርካታ ጉዳዮች ጥያቄ ውስጥ ከተውናል። በተለይ ደግሞ በአስተዳደር ሥርዓትና በመንግሥታዊ መዋቅር ላይ። የመደመር እሳቤ ለመፍታት የሚያልመው አንዱ ዕንቆቅልሽ ይኼንን ነው። የጋራ ሀገርና የጋራ ህልውና ሳይኖር፣ እንደ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ሳናስብ እኩልነት ነጻነትና ብልጽግና ሊኖር አይችልም።

“አትዮጵያዊነት" እንደ ሐሳብ ብዙ ዘመናትን አስቆጥሯል። አትዮጵያዊነት የነጻነትና የአሸናፊነት፣ በሌሎች አልገዛም ሌሎችንም አል'ገዛም የሚል አስተሳሰብ ድምር ነው። ይሄን አስተሳሰብ የተወሰኑ አፍሪካውያንና አፍሪካ አሜሪካውያን ይጋሩታል። ኢትዮጵያዊነት ሁሉንም ኢትዮጵያውያን የድርሻቸውን አዋጥተው፣ ሕይወታቸውንም ጭምር ሠውተው የፈጠሩትና ያዳበሩት አስተሳሰብ ነው። ሆኖም ግን ኢትጵያዊነት ገና ተሠርቶ ያላለቀ ቤትንም ይመስላል።

ኢትዮጵያዊነትን በመፍጠርም ሆነ በመገንባት ሂደት ሁሉም ሕዝቦች ሚና ነበራቸው፤ አላቸውም። ዳሩ ግን ኢትዮጵያን ወደ ራስ አምሳያ በመኀተትና በኢትዮጵያዊነት በመጠቀም ረገድ ሁሉም በአስተዋጽዖው ልክ የተወከለ አይደለም። የብሔር ጽንፈኝነት እንዲመጣ አንዱ ምክንያት የሆነውም ከዚህ የተወለደው “ኢትዮጵያዊነት እኔን አይገልጸኝም፣ በተገቢው መጠን አይወክለኝም" የሚለው አስተሳሰብ ነው። በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊነት እኔን ብቻ መምሰል አለበት የሚል አቋምም አለ። ‹የኢትዮጵያ አድራጊ ፈጣሪ እኔ ነኝ› የሚል፣ ባህሉና ወጉ ብቸኛ የሀገሪቱ መገለጫ እንዲሆን የመፈለግ ጠንካራ ዝንባሌም አለ። ከዚያ አልፎም የሀገራችን መልክና ቁመና በእኔ መልክና ምሳሌ ካልተፈጠረ ኢትዮጵያዊነት ይረክሳል ከሚል አስተሳሰብ የሚመነጭ ጽንፈኝነት ሥር ሰድዶ ይገኛል።

በአጭሩ አንዱ ‹ኢትዮጵያዊነት ለእኔ ምኔ ነው? እኔን አይመስልም፤ አይወክልም› ሲል፤ ሌላው ደግሞ ‹ኢትዮጵያዊነት እኔን መምሰል አለበት፤ እኔን መስሎ ያልኖረ ሁሉ እስከነአካቴው ኢትዮጵያዊም አይደለም› ብሎ ይሞግታል። እነዚህ ጽንፍ ላይ የቆሙ ሁለት አጀንዳዎች ኢትዮጵያዊነትን አደጋ ውስጥ ይከቱታል።

‹‹መደመር›› እንደ እሳቤ የመጣበት አንዱ ምክንያት ኢትዮጵያ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን እንድትሆን በሁለት ተቃራኒ ዋልታዎች የቆሙትን አቋሞች ማቀራረብ በማስፈለጉ ነው። ይህ ሊሆን የሚችለውም በማኅበረሰባዊ ማንነታችንና በሀገራዊ ማንነታችን መካከል ሚዛን የጠበቀ ግንኙነት ሲኖር ነው። ከዚህ ባለፈ መጨፍለቅም ሆነ መነጠል አጥፊ ውሳኔ ነው።

በዓለም ላይ ብሔረ መንግሥት ለመፍጠር፤ አንድ ሃይማኖት ብቻ፣ አንድ ባህል ብቻ፣ አንድ ቋንቋ ብቻ ብለው በሚናቆሩበት ዘመን፤ ክርስትና፣ እስልምና፣ ዋቄ ፈታ እና የአይሁድ አስተምህሮዎችን በአንድ ላይ ይዞ የቆየ፤

በአንድ ሀገር ንጉሣዊ ሥርዓት፣ የገዳ ሥርዓት፣ የሱልጣን አሚር ሥርዓቶችን አዛንቆ የኖረ፣ ምናልባትም በዓለም ላይ በዚህ ደረጃ ዘመናትን የተሻገረ ስብጥሮሽ ያለው ብቸኛ ሕዝብ ሊያስብለን ይችላል። ብሔረ መንግሥትን ወደ አንድ ጎሳ፣ ወደ አንድ ብሔር ወይም ወደ አንድ ቋንቋ አጠጋግቶ መፍጠር የተለያዩ ብሔሮችን ባህል፣ ቋንቋ ብሎም የግዛቱ ስያሜን ወደ አንድ በማምጣት ይጠናቀቃል።

ጥቂት የማይባሉ የምዕራቡና የምሥራቁ ሀገራት ስያሜዎቻቸውን ያገኙት በአንድ ወቅት ጠቅላይ ወይም የበላይ ከነበረው ብሔር ስያሜ ተቀድቶ ነው። በአሁኑ ወቅት ታላቋ ብሪታኒያ የምትባለው ሀገር (ሰሜን አየር ላንድን ሳይጨምር፤ ምክንያቱም ሰሜን አየር ላንድ ከተጨመረ ዩናይትድ ኪንግደም ነው የሚሆነው) በውስጧ ያሉትን ስኮትላንዳውያንንና ዌልሳውያንን መኖር ከግምት ሳታስገባ በእንግሊዛውያን ስም እንግሊዝ ተብላ ትጠራለች። በዚህ ምክንያት ስኮታላንዳውያንና የዌልስ ብሔሮች ከፍተኛ የሆነ ቅሬታ ይሰማቸዋል። ስኮቶች ለመገንጠል ተደጋጋሚ ሙከራ የማድረጋቸው አንዱ ምክንያትም ይህ ነው።

ሰሜን አየር ላንድን ጨምሮ ዩናይትድ ኪንግደም የሚባለው ሀገርም ቢሆን በእንግሊዙ ንንነዊ ወይም ንግሥታዊ ሥርዓት የሚጠራ ነው። ጣሊያን በኃይል በምትመሠረትበት ጊዜ (1860ዎቹ) ጣልያንኛ ተናጋሪዎች ከግማሽ በታች እንደነበሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የግዛቲቱ ብሔሮች (ከጣሊያንኛ ተናጋሪዎቹ በተጨማሪ) ሮማኖቱ፣ ቴቶኖች፣ ግሪኮቹና ዓረቦቹ በጣሊያን ብሔር ተጨፍልቀው ነበር ጣልያንን የመሠረቱት።

ከ1870 በፊት ፈረንሳይ ከዐርባ በመቶ በታች የነበረው የፈረንሳይ ብሔር (በዋናነት በፓሪስ አካባቢ የሚኖሩ) ወደ ፈረንሳይ ሀገረ ብሔርነት ሲያድግ በግዛቱ የነበሩት ጋሉስ፣ ሮማኖት፣ ብሪቶኖች፣ ቲቶኖች እና ሌሎችም ተገደው ፈረንሳዊ ብሔር እንዲሆኑ ተደርገው ነው። ጀርመንም ከሠላሳ በላይ ልዩ ለዩ ብሔሮች በዶቾቹ ተጨፍልቀው የፈጥሯት ሀገር ናት። በዚህ መልኩ የተፈጠሩ እና የአንዱን ብሔር ስያሜ ይዘው የተመሠረቱ ሀገራት በርካታ ናቸው። ብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገራትም ቅኝ ገዥዎች በሰጧቸው ስያሜዎች ሀገር ሆነው የተመሠረቱ ናቸው።

በኢትዮጵያ ሀገራችን ሰማንያ ያህል ብሔሮች ያሉ ሲሆን አንድም ብሔር ኢትዮጵያ በሚለው ስያሜ አይጠራም። ካሉት ሰማንያ ብሔሮች ኢትዮጵያ የሚባል ቦታ የኔ ብሔር ስም ነው ወይም የአካባቢ ስም ነው› የሚል የለም። ገናናው የአክሱም ንጉሥ ኢዛና በተለይም ለዓለም አቀፍ ግንኙነት ይጠቀምበት በነበረው የግሪክ ቋንቋ የአክሱም ንጉሥ ከማለት ይልቅ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እያለ ይጽፍ ነበር።

ኢዛና በወቅቱ ኢትዮጵያን ጨምሮ የዘጠኝ ሀገራት ንጉሠ ነገሥት እንደነበረ ሲገልጽ ቆይቷል። በተለይም ከክርስትና መቀበል በኋላ ግዛቱን እንዳለ ኢትዮጵያ ብሎ መጥራት መጀመሩ ይነገራል።

አባቶች ከየትም ይምጡ ከየት የተከተሉትን መንገድ ላንስማማበት እንችላለን እንጂ የራሳቸውን “ብሔር” የሀገራቸው ስም ባለማድረጋቸው ግን የሚያስመሰግናቸው ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሀገራት የሚጠሩት አንድም በግለሰብ _ ስም (ቦሊቪያ በስምዖን ቦሊቫር፣ አሜሪካ በአሜሪጎ ቬስፑሲ እንደተጠሩት) ወይም በአንዱ ብሔር ስም፣ ወይም ደግሞ ቅኝ ገዥዎች ባወጡት ስም (ካሜሩን፣ የማርሻል ደሴቶች) ነው።

የእኛ ሀገር ከፍ ያለና ረጅም ታሪካዊ ስም ካላቸው ጥቂት ሀገሮች አንዷ ናት። ከእያንዳንዳችን ብሔር በላይ

የሆነ የጋራ ሀገረ መንግሥት ዘመናትን ተሻግሮ እነሆ እያንዳንዳችን መዳፍ ላይ ተቀምጧል። የሚቀረው ትልቁ የቤት ሥራ ኢትዮጵያ እያንዳንዳችንን እንድትመስልና የጋራ ማንነታችንን የምታንጸባርቅ እንድትሆን በጥንቃቄ መሥራት ነው። ኅብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያን መውለድ የእኛ ውዝፍ የቤት ሥራችን ነው።

በታሪካችን ውስጥ ማንነታቸውን፤ ባህልና ወጋቸውን የጋራ በሆነች ሀገራችን እንዲገለጽና እነርሱን እንድትመስል የማድረግ ዕድል ያገኙ ሕዝቦች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ እንኳን ኢትዮጵያን በመልክና በምሳሌያቸው ሊገልጹ ይቅርና ራሳቸውን እንዳይሆኑ ተገድበው የነበሩ ሕዝቦችም አሉ። በመካከል በነበረው ታሪካዊ መስተጋብር የተነሣም ዛሬ እንደ ማኅበረሰብ የማናገኛቸው ሕዝቦችም አሉ። ለሀገራችን ታሪክ ግን እነርሱም _ አስተዋጽዖ አድርገው ነበር። ያ ሁኔታ ዛሬ ሀገራችን የተሟላ ቁመና እንዳይኖራትና የሕዝቦቿ ሁሉ መግለጫ እንዳትሆን አድርጓታል።

ታዲያ አሁን ምን እናድርግ? ላለፉት ዘመናት እንደ ኅብረ ብሔራዊ ሕዝቦች እኩል ዕድል አግኝተን እኩል ተጽዕኖ ባለመፍጠራችን የተነሣ ስላለፈው ታሪክ እያወራን እንቆዝም? ወይስ አሁን በእኩል ተጽዕኖ የመፈጥር ዕድላችንን ተጠቅመን ወደፊት እንራመድ? ባለፈው ኢፍትሐዊነት እንነታረክ ወይስ ስሕተቱን አርመን ወደፊት ሀገራችንን በጋራ ምሳሌአችንና በመልካችን እንፍጠራት?

ሀገራችንን ልጆቿ በጋራ የገነቧት፣ በመልካቸውና በምሳሌያቸውም የፈጠሯት ሀገር ማድረግ ይቻላል። የአሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን የሚመጣውም ትውልድ ከራሱ ባሕርያት ጋር እንዲያዋሕዳትና የራሱን አሻራ እንዲያሳርፍባት በማድረግ በማያቋርጥ የለውጥ ሂደት ውስጥ ያለ ከፉ ችግር እንድታልፍ እንዴት እናድርግ? የሚለው ሁላችንም ልንመልሰው የሚገባንና የእያንዳንዳችንን አስተዋጽዖ የሚፈልግ የወቅቱ ጥያቄ ነው።

ቤተሰብ ሲባል የወንድ ወይም የሴት ብቻ ማለት አይደለም። በተለምዶ ቤተሰቡን ፈጠረው የሚባለው በዋናነት ወንዱ ነው። በዚህም ምክንያት ቤቱ የወንዱ ነው ሊባል ወይም በወንዱ ስም ሊጠራ ይችላል። ይሄን ያደረገው ለዘመናት የተገነባው ባህልና ወጋችን ለሴቶች የሚመች ባለመሆኑ ነው።

ታዲያ በታሪካችን የነበረውን ክፍተት አርመን የሴቶችን ከብር የሚጨምር፣ በእኩልነት የሚወስኑበት ሥርዓት ፈጥረን የቤተሰብን ተቋም እንጠበቃለን እንጂ ታሪክ ጠቅሰን ቤተሰብ የሚባለውን ተቋም እናፈርሰዋለን እንዴ? ኢትዮጵያዊነትም ልክ እንደዚሁ ነው። ሲመሠረት እንከኖች ነበሩበት።

ሀገር ልክ እንደ ቤተሰብ አስፈላጊ ነው። በሆነ ወቅት ሴቶች ይጠለፉ ስለነበር፤ ሴቶች ያለፈቃዳቸው ያገቡ ስለነበር፣ ወንዶች የበላይ ስለነበሩ የቤተሰብ ተቋም ይፍረስ አላልንም። ይልቁንም ቤተሰብ የሁሉም ነገር መሠረት ስለሆነ እንዲያብብ እናደርጋለን፤ እንከኖቹ ግን ተለቅመው መወገድ አለባቸው። ሀገርም እዚህ ለመድረስ ሕመምና እንከኖች ነበሩት። ሀገር የግድ አስፈላጊ በመሆኑ ላለፉት እንከኖች ሲባል ይፍረስ አይባልም። ሀገራችን ደግሞ ለዘመናት ጥሩ ስም ነበራት። በታሪክ የደመቀ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የጸደቀ፣ በቅዱስ ቁርዓን የታወቀ፣ በቀደምት ድርሳናት የላቀ ዝና ያላት ሀገር ናት።

የቤተሰብ ሕግን በማስተካከልና ቤተሰባዊ ባህልን በማሻሻል አባላቱን ሁሉ የሚመስላቸው፣ በእኩል የሚታዩበት እና እኩል የሚወስኑበት ቤተሰብ እየፈጠርን ነው። ሀገራችንንም ሁላችንን የምትመስል፣ እኩል

የምታይ፣ እኩል የምንወስንባትና የሁላችን የሆነች ሀገር ማድረግ እንችላለን። ከዚያ ባለፈ ሀገራችን ያላት ስም፣ ክብርና መልካም ወረቶች ሁሉ የበለጠ ከፍ እንድንል መነሻ ወለል ይሆኑልናል። ከፍ ያለ ወለል ላይ ከቆምን ምንጊዜም ከፍ እንጂ ዝቅ ልንል አንችልምና።

የተጋቡ ባል እና ሚስት ኃይላቸውን አስተባብረው ኑሯቸውን እንዴት እንደሚያሻሽሉ፤ እንዴት እንደሚበለጽጉ እንጂ፤ አንድ ቀን እንዴት መፋታት እንደሚችሉ ማታ ማታ አያወሩም። አንድ ቀን ሊፋቱ እንደሚችሉ በየቀኑ እያሰቡ የሚመሠርቱት ቤተሰብ እንዴትም ሆኖ ወደፊት መጓዝ አይጀምርም። ምክንያቱም ቤቱ የፈረሰው ሳይመሠርቱት በፊት ስለሆነ። ሀገራችንን በፍጥነት ወደፊት ለማስጓዝ የሚቀድመው ነገር መሠረቱን ማጠንከርና ኅብረ - ብሔራዊ አንድነት ያለውን ሀገረ መንግሥት የመገንባቱን ሂደት ቀጣይነት ባለው መንገድ እንደምንፈጽመው ማመኑ ላይ ነው።

ይኼንን ለማድረግ ወሳኙ የመደመር ዓምዶችን ማጽናት ነው። ምሉእ እይታ፣ ተባብሮ መኖር፣ ሚዛናዊነት፣ ልዩነትን በጸጋ መቀበልና የመሳሰሉትን ማስፋት። የመደመር ዓምዶች የመደመርን ምንነት ብቻ ሳይሆን የመደመር ሂደትንም የሚያሳዩ ናቸው። የመደመር ተዋንያን የሆኑ ሕዝቦች በሀገር ውስጥ አብረው ሲኖሩ ኪሣራ ሳያስተናግዱ አትራፊ የሚሆኑበትን ግንኙነት የሚመሠርቱባቸው ዘዴዎች ናቸው።

የመደመር እሳቤ ከተፈጥሮም ሊቀዳ ይችላል። እንደ ሰው ልጆች ቋንቋን ተጠቅመው መግባባት ሳይገባቸው እንስሳትና ዕፅዋት የሚያተርፉበትን ዘዴ ቀይሰው መደመርን ሲኖሩት እናያለን። ለመደመር ግዴታ በሁሉም ነገር መግባባት የለብንም። የጋራ የሆነ ግብ ማስቀመጥ እስከቻልን ድረስ መደመር ብዙም ከባድ አይሆንም። የሜዳ አህያና ሰጎን ህልውናቸውን ከቀጥተኛ ጥቃት መከላከል የጋራ አጀንዳ ሆኗቸው በጋራ ይኖራሉ። ሰጎን በተፈጥሮዋ ማሽተትና ከርቀት ድምፅ መስማት ይከብዳታል፤ በሌላ በኩል ከርቀት የማየት ችሎታዋ ከፍተኛ ነው። በአንጻሩ የሜዳ አህያ የጠላትን ጠረን የማነፍነፍና ኮቴውን ከርቀት የመስማት ዐቅም ተሰጧታል። ዓይኗ ግን ደካማ ነው።

እነዚህ ሁለት እንስሳት ተመሳሳይ ዝርያ የላቸውም። ተመሳሳይ አመጋገብና የአኗኗር ዘይቤም የላቸውም። ነገር ግን የጋራ ህልውናቸውን የሚፈታተን የጋራ ጠላት አላቸው። በዚህም የተነሣ ጠላታቸውን የጋራ አጀንዳ አድርገው በመደመር ለመንቀሳቀስ የሚያግዳቸው ምንም ነገር የለም። የአቋም ድማሬያቸው ዐቅማቸውን ለመደመር ወደ አንድ መድረክ እንዲመጡ አድርጓቸዋል። አንዳቸው የጎደላቸውን ሌላኛው እየሞላ፣ ክፍተታቸውን በጥንካሬያቸው እየሸፈኑ፣ ተሰናኝተው በመሥራታቸው፣ የሚጎዳ ሳይኖር፣ ሁለቱም አትራፊዎች ሆነዋል።

በጋራ ለመሥራት እንቅስቃሴ በሚደረግበት ወቅት ትብብር ብቻ ሳይሆን ፉክክርም ሊፈጠር ይችላል። ቀደም ብለን ባስቀመጥነው ጉዳይ ዙሪያ ሰጎን እና የሜዳ አህያው ትብብርን አስቀድመዋል። ይህ ማለት ምንም የሚያፎካክራቸው ነገር የለም ማለት አይደለም። በምግብ ሽሚያ ባይፎካከሩ በመጠጥና በመጠለያ ምክንያት ፉክክር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ። በዚህ ወቅት እነዚህ ሁለት ተደማሪዎች በፉክክራቸውና በትብብራቸው መካከል ሚዛን እንዳይዛባ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል ማለት ነው።

ልክ እንደ ሰጎንና የሜዳ አህያ ሁሉ ሌሎችም በተፈጥሮ ውስጥ ተባብሮ ኑሮ ምርጫቸው በማድረግ ያለ ጉዳት ትርፍ የሚያገኙበትን መንገድ ቀይሰው የሚኖሩ አሉ:: ንብ እና አበባን ብንመለከት ንቧ ምግቧን ለመሥራት አበባ ስትቀስም፣ አበባው በአንጻሩ በንቧ አማካኝነት ዘሩን ያስተላልፋል። አዞ እና ወፍም በተመሳሳይ፣ ወፏ ከአዞው ጥርስ ውስጥ የተቆራረጠ ሥጋ ለቅማ ስትመገብ፣ አዞው በአንጻሩ ንጽሕናው ይጠበቅለታል። በዚህ መልኩ መጎዳዳት ሳይኖርባቸው ይጠቃቀማሉ።

ይኼንን ወደ ሰው ልጆች እናምጣው። በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው፣ በማኅበራዊውና በሌሎች ዘርፎች የጋራ የሚያደርጉን ብዙ አጀንዳዎች አሉ። በእነዚህ አጀንዳዎቻችን ላይ አተኩረን፣ በሚያፎካክሩን ጉዳዮች ላይ ደግሞ ጤናማና ሚዛናዊ የሆነ ፉክክር እያደረግን በመደመር ከሠራን፣ የማንሻገረው ምንም ዓይነት ችግር አይኖርም። "ድር ቢያብር አንበሳ ያስር"፣ "ለአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ" እያለ ለሚናገር ማኅበረሰብ መደመር በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ እንግዳ አይሆንበትም። አባባሉን ከአባባልነት በዘለለ ወደ ተግባር መመንዘር ብንችል ምን ያህል አዎንታዊ ለውጥ በሀገራችን ሊመጣ እንደሚችል እሙን ነው።

ወደ ምሉእነት በምናደርገው ጉዞ ውስጥ የሀብት ውሱንነት ሊገጥመን ይችላል። ይህንን ለማለፍ በዙሪያችን ካሉ አካላት ጋር በምናደርገው ግንኙነት ፉክክር ውስጥ መግባታችን አይቀሬ ነው። ፉክክሩ እጅግ ሲገን ያለመደመር ቀይ መብራቶች መታየት ይጀምራሉ። ሆኖም ፉክክር በራሱ ከብቸኝነት ጉድለት ውስጥ ለመውጣት የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ነገር አይደለም። ከልክ በላይ ሲሆን ወይም ከልክ በታች ሲሆን ነው ችግር የሚፈጠረው። ፉክክሩ ከልክ በታች ሲሆን ጥገኝነት እየዳበረ በቀላሉ መርካት ይጀመራል፤ ይህም እየቆየ ስንፍናን ያመጣል። በዚህም ምክንያት ለለውጥ የምናደርገው ጉዞ መድረሻው ላይ ሳይደርስ ይቋረጣል ወይም ለማደግ የምናደርገው እንቅስቃሴ በሙሉ ዐቅሙ ዕድገቱን ሳይጨርስ ይጨነግፋል። በተቃራኒው ፉክክር ከልክ በላይ ከሆነ ከአካባቢያችን ጋር የሚኖረን ግንኙነት የድምራዊ አጥፊ ወይም የዜሮ ድምር ጨዋታ ይሆናል። በዚህ ምክንያት መጨረሻችን መልሶ ብቸኝነት ይሆናል ማለት ነው።

ስለዚህ ሁልጊዜም ለጭማሪያዊ ለውጥ በምናደርገው ጉዞ ላይ በትብብርና በፉክክር መካከል ሚዛን የጠበቀ አካሄድ መከተል ይኖርብናል። በመሆኑም በመደመር ሕግ ወርቃማዋን አማካይ, ማግኘት የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። በመደመር ጉዞ ውስጥ ታሪክን የምንመለከትበት መነጽር የጉዟችንን ፍጥነትና መዳረሻ ሊወስን ይችላል። እንደሚታወቀው ሀገራችን የተወሳሳበ ረጅም የፖለቲካና የሕዝቦች መስተጋብራዊ ታሪክ አላት። የሀገራችን የሕዝቦች መስተጋብራዊ ታሪክ በመቻቻልና መከባበር የተመሠረተና በዓለም ደረጃ በሞዴልነት የሚጠቀስ ታሪክ ነው።

የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ታሪክ የውጭ ገጽታውም ቢሆን የሚያኮራ ነው። ሕዝቦችን አስተባብሮ የሀገርን ሉዓላዊነት ለመጠበቅ የተደረገው ጥረትና የተገኘው ስኬት አኩሪና ወረት ተደርጎ ለትውልድ መተላለፍ የሚገባው ነው። የቀደሙ መሪዎች ሀገራችን በዓለም አቀፍ መድረኮች ሚና እንዲኖራት ያደረጓቸው ጥረቶችና ያስገኟቸው ስኬቶች አሁንም ተጠናክረው መጠበቅ ያለባቸው ናቸው። የሀገረ መንግሥታችን የውስጥ ታሪክ ግን ከእንከኖች የጸዳ አልነበረም። የገዥው ፓርቲም ሆነ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ፕሮግራሞች መሠረተ ሐሳቦች የሚያተኩሩት በአጨቃጫቂውና እንከን በበዛበት የትናንት የውስጥ ታሪክ ገጽታ ላይ ነው። ፕሮግራሞቹም

ቢሆኑ የተመሠረቱት የመረጡትን የታሪክ ገጽታ ለማጉላት ነው። ስለሆነም በአሁኑ ሰዓት የሀገራችን የፖለቲካ ውይይቶችና መገናኛ ብዙኃን በታሪክ ንትርክ የተሞሉ ሆነዋል።

ታሪክን በተመለከተ ልንረዳው የሚገባን ነገር ቢኖር ሊቀየር የማይችል የትናንት ፎቶ መሆኑን ነው። በሁለት ጎራ ተከፍለን ስለ ፎቶው እንዴትም አድርገን በንግግሮቻችን ብንኩለው ወይም እንዴትም አድርገን ብናጠለሸው ንግግራችን ንግግር ሆኖ ይቀራል እንጂ ፎቶው አይቀየርም። ምናልባትም ዛሬያችንን ያበላሸዋል እንጂ ትናንታችንን አያስተካክለውም።

ይህ ሲባል ግን ትናንታችን እንደተዘጋ ይቆያል ማለት አይደለም። ከትናንት ሁለት ነገሮችን አንጥረን ልናተኩርባቸው እንችላለን። በወረቶቻችንና በውዝፍ ሥራዎቻችን ላይ። ትናንት የሠራናቸው ጥሩ ነገሮች ሁሉ ለዛሬያችን ጥሩ መነሻ ወረት ይሆኑናል። በእነርሱ ላይ የዛሬን ጉልበት፣ ዕውቀትና ሀብት ሰብስበን ስናክልበት የብልጽግና ጉዟችን ቀላልና የተፋጠነ ይሆናል። በአንጻሩ በተሳሳተ ፖሊሲ፣ ግንዛቤ፣ አመራርና መሰል ምክንያቶች ከትናንት ሲንከባለሉ የቆዩ ውዝፍ ሥራዎች ዛሬ ተነሥተን በቀላሉ እንዳንጓዝ የእግር ብረት ሆነው ይይዙናል። እነዚህን ውዝፍ ሥራዎች ለመናድ ካልተረባረብንባቸው ወደ ልጅ ልጆቻችን የምናስተላልፈው ችግር እንዲበዛ ያደርጋሉ። ከዚያም አልፎ ዛሬ ላይ እኛኑ ጨፍልቆ ሊገድለን ይችላል።

ከዚህ በመነሣት ሁላችንም ቆም ብለን ልንመልሰው የሚገባን ጥያቄ አለ። ትናንትን እየኮነንን ወደ ባዶነት እንሂድ? ትናንትንስ እያወደስን ወደ አዙሪት ውስጥ እንግባ? ሁለቱም የሚጠቅሙን አይደሉም። ትናንትን ስንኮንን ዕድሜያችንን ብናጠፋ መነሻ ወለል የሌለን ባዶዎች እንሆናለን። ትናንትን እንከን አልባ አድርገን ውዳሴ ብቻ ማከናነቡም _ ከትናንት ባለመማር ስሕተቶቻችንን ደግመን ደጋግመን የምንደግም አዙሪታሞች ያደርገናል።

በሌላ በኩል ከትናንት ያገኘናቸውን መነሻ ወረቶች እያሰፋን፣ ውዝፍ ዕዳዎችን እየቀረፍን ወደፊት ብንራመድ ውጤቱ ሁለንተናዊ ብልጽግና ነው። ትናንትን በልኩ መዝነን በልኩ ማወደስና በልኩ መውቀስ ከቻልን እንክርዳዱን አርመን ስንዴውን ለቅመን ለመጓዝ ይረዳናል።

ኢሕአዴግ መራሹ መንግሥታዊ ሥርዓት የኢትዮጵያ ተራማጅ ኃይሎች ከ1960 አንሥቶ የታገሉለትን መሬት ለአራሹን፣ የብሔር ማንነትና የመብት ጥያቄዎችን እንዲያዳግም አድርጎ ምላሽ ለመስጠት የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ለዘመናት ሲንከባለል ለመጣው የማንነት ጥያቄ መሠረታዊ ሊባል የሚችል ፌዴራላዊ መፍትሔን በመተግበር አንድ ርምጃ ተራምዷል።

ፌደራሊዝም በሁለት ዋልታዎች መካከል የቆመ ሚዛን ነው። በአንድ በኩል ብዝኃነትና ልዩነት፤ በሌላ በኩል ደግሞ አብሮነትና አንድነት የሚስተናገዱበት ዐውድ ነው። ኢሕአዴግ በዋናነት የብሔር ማንነትን የማክበር ዓላማ አንግቦ በመምጣቱ የተነሣ ዋነኛ ትኩረቱ ማንነትን በማስከበር ላይ ሆነ። ወደ አንድ ዋልታ በመሳቡ ምክንያት የድርጅቱ ስኬት የተሟላ ሊሆን አልቻልም። ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ድርጅቱ ለሁሉም የምትሆን ሀገር በመፍጠር ረገድ ስሕተት መሥራቱ ነው።

ኢሕአዴግ በተደጋጋሚ ያጋጠሙትን መልካምና ወርቃማ ዕድሎች በፍረጃና በመጠላለፍ ፖለቲካ ውስጥ

ገብቶ ሳይጠቀምባቸው ቀርቷል። ምናልባትም በሥልጣን ዘመኑ ከፈጸማቸው መሠረታዊ የስትራቴጂ ስሕተቶች መካከል ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ተጠቃሽ ይሆናሉ።

**የመጀመሪያው ስሕተት፡-** ኢሕአዴግ የአሸናፊነት ዘውዱን ሲደፋ ነገሮችን በዕርቀ ሰላም መቋጨት የሚችልበትን አጋጣሚ አለመጠቀሙ ነው። ጭቆናን አስወግዶ ጠንካራ የሆነ ፍትሐዊ መንግሥት መመሥረት እንደሚፈልግ ፓርቲ ሁሉንም ኃይሎች አስተባባሮና ደምሮ ወደፊት መሄድ ይገባው ነበር። በዚህ ፋንታ ድርጅቱ የመረጠው አማራጭ ዜጎችን በመከፋፈል፣ አንዱን ትምክተኛና የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂ፣ ሌላኛውን ጠባብ፣ አንደኛውን ዋና ክልል፣ ሌላኛውን አጋር ክልል እያለ በልዩ ልዩ ጎራ መፈረጅና መግፋት ነበር። ይህ ማለት የፖሊሲ ልዩነቶችና የተሳሳቱ አስተሳሰቦች አልነበሩም ማለት አይደለም። ሆኖም ሁሉንም የሚያስተናግድ ሥርዓት መፍጠር እንጂ ዜጎች በያዙት አቋም ምክንያት በገዛ ሀገራቸው ተሳቀው እንዲኖሩ ማድረግ አይገባውም ነበር።

በዚህ ረገድ ተጠቃሽ የሚሆነው ረጅም ልምድ ያካበተውን የሀገሪቱን ሠራዊት እንዳለ መበተኑ ነው። በወቅቱ የነበረው ሠራዊት የነበረበት የቅኝት ችግር የሠራዊቱ አጠቃላይ ችግር ሳይሆን የፖለቲካ አመራሩ ውሳኔ ነበር። ሠራዊቱ ግን በበርካታ ዐውደ ውጊያዎች የተሳተፈ፣ ሀገሩን ከሶማሊያ ወረራ የታደገና ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ በረጅም ጊዜ ሂደት ያለማቋረጥ እየተገነባ የመጣ ሠራዊት ነበር።

በመሆኑም እንዳለ ሠራዊቱን ከመበተን ይልቅ በሌሎች ከእርስ በርስ ውጊያ በወጡ ሀገራት እንደተደረገው የፖለቲካ ቅኝቱን አርሞ ፕሮፌሽናል ሠራዊት መገንባት ይቻል ነበር። ይህም ኋላ ላይ ከኤርትራ ጋር በተደረገው ጦርነት ወቅት እንደታየው ከየአሉበት ከመጥራትና የአባረርናቸውን ዳግም ለመሰብሰብ ከመሯሯጥ ያድነን ነበር።

ግንባሩ በትጥቅ ትግል ዘመን የፈጸማቸውን ጀብዱዎች እያጋነነ፣ የሞቱና የተማረኩ ወገኖችን ውርደት እያሳየ፣ በቀረው ሕዝብ ዘንድ ቅያሜንና ቅራኔን እንዲስፋፉ አድርጓል። የመንግሥት ሠራዊትን ተቀላቅለው ሀገራቸውን በማገልገል ላይ የነበሩ ወታደሮች ዘመድ፣ ልጆችና ቤተሰቦች ምን ሊሰማቸው እንደሚችል የገመተ ቀርቶ ምንም ቢሉ ደንታ የሰጠው ሰው አልነበረም። ከድል ፌሽታው ባሻገር ሊወራረስ ስለሚችለው ቂም በቀል ምንም ጥንቃቄ አልተደረገም። የነገሩን ፍጻሜ መገመት ግን ላስተዋለው ቀላል ነበር።

የወጡበት ዓላማ ምንም ይሁን ምን ወገኖቻችን በዘመዶቻቸው ሞት፣ በልጆቻቸው ኅልፈትና እንደወጡ መቅረት ልባቸው መሰበሩን መረዳት ጥልቅ ሳይንስ አልነበረም። ምክንያቱም ልጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን የላኩት ወደው በፈቃዳቸው አልነበረምና። አንዳንዶቹ ወደ ውትድርና ሞያ ሀገርን ለማገልገል ገብተው፣ አብዛኞቹ ግን በግዳጅ ታፍሰው ተወስደው ነው። የሟቾች ወገኖች በአንድ በኩል በወገኖቻቸው በግዳጅ መወለድ፣ በሌላም በኩል ሞታቸው በውርደት በመነገሩ በሁለት በኩል ተጎድተዋል። በከፈሉት ውድ መሥዋዕትነት ላይ የፖለቲካ ዘለፋ ሲጨመርባቸው የመጠቃት ስሜት እንዲያዳብሩ፣ አንጀታቸው እያረረ ለበቀልና ለጥቃት ቀን እንዲጠብቁና እንዲነሣ ምክንያት ይሆናል እንጂ የሚያስገኘው ጥቅም አልነበረም።

ይህ ቀላል የሚመስል የአሸናፊና የተሸናፊ ትርክት ውሎ አድሮ ሀገር በተለያዩ ጽንፎች እንድትወጠር

አድርጓታል። ይህም ቀደም ብሎ የነበረው በመሪዎች ወይም በገዥ መደቦች ላይ የነበረ እምነት ማጣት ተጨምሮበት በአጠቃላይ ሕዝቡ በመንግሥት ላይ እንደ ተቋም ያለውን እምነት እያጣ እንዲመጣ አድርጓል። ከሁሉም እጅግ የከፋ የሆነውም ይህ ሁኔታ መፈጠሩ ነው።

**ሁለተኛው ስሕተት፦** ኢሕአዴግ ለሀገራዊ አንድነት ትኩረት ባለማድረግ፣ የብሔር ማንነት እየጎላ የጋራ ሀገራዊ ማንነትና አንድነት እየከሰመ እንዲሄድ ዕድል መፍጠሩ ነው። የአንድነት ጉልበት፣ የመደመር ረቂቅ ኃይል ቀስ በቀስ እየከሰመ ሄዶ ሁሉም ሰው ከብሔሩ አልፎ ማሰብ እንዳይችል አድርጎታል። በታሪክ ሂደት ቀስ በቀስ ተገንብቶ የነበረውና በሕገ መንግሥት ሳይቀር ዕውቅና የተሰጠው "በጋራ ያፈራነው ሀገራዊ ዕሴት" ተጠራርጎ ሀገር በትዝታና በካርታ ላይ ብቻ ያለች ተረት ወደ መሆን ደረሰች። ይሄም በፊናው የአብሮነትን ፋይዳና ተደምሮ ትልቅ የመሆንን ተስፋ ትቢያ ላይ ጥሎታል።

**ሦስተኛውና ከሁሉ የባሰው ስሕተት፦** የማፊያ ቡድን በድርጅቱ ውስጥ ማቆጥቆጡ ነው። ይህ ቡድን የድርጅቱን ህልውና ሳይቀር ለመዋጥ ጫፍ ላይ ደርሶ ድርጅቱን አሽመድምዶት ነበር። በድርጅቱ ውስጥ የተፈጠረው የማፊያ ቡድን ኢሕአዴግ የቆመለትን፣ የታገለለትንና የሞተለትን ዓላማ ወደ ጎን አሽቀንጥሮ፣ መለያ ዕሴቶቹን ሰባብሮ፣ ሌላ መልክ ያለው ድርጅት በመፍጠር ውስጥ ውስጡን ሲቦጠቡጠው ቆይቶ ባዶውን ለማስቀረት ጫፍ ላይ ደርሶ ነበር። ከድርጅትም አልፎ ነጣቂ መንግሥት ወደ ሆነ አደገኛ ቡድንነት መሸጋገሩ ሀገሪቱን ቀይ መሥመር ውስጥ አስገብቷታል።

የሚወጡ ፕሮግራምና ፖሊሲዎችን የማፊያ ቡድኑ ለራሱ እንዲመቹት አድርጎ ለመቅረጽና ለመተርጎም ድፍረት እስከማግኘት ደርሶ ነበር። በዚህም ዐቅሙ ኢሕአዴግን ወደ አስፈሪ ድርጅትነት ለመቀየር ተቃረበ። ይህ በድርጅት ውስጥ የተፈጠረ ተውሳክ ቡድን የፖለቲካ መዋቅሩንና የመንግሥትን ሥልጣን ለኪሱ ማደለቢያ፣ ለዓላማው ማሳኪያ ማዋል ጀመረ። በመጨረሻም የመንግሥትን እጅ መጠምዘዝ ወደሚያስችለው ደረጃ ተሸጋገረ።

በመደበኛው ንግድ ያጋበሰው ሀብት አልበቃ ሲለው በኮንትሮባንድ ንግድ ተሠማራ። በጦር መሣሪያ ንግድ ላይ ሳይቀር በመሠማራት ጡንቻውን አፈርጥሞ ሌላ መንግሥት ወደ መሆን አደገ። ድርጅቱ ለይስሙላ ቆሞ ውስጥ ለውስጥ በዚህ ኃይል ቁጥጥር ሥር መዋሉ የአደባባይ ምስጢር ሆነ። ይህ ቀስ በቀስ የፓርቲንና የመንግሥትን መዋቅር የተቆጣጠረ ኃይል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ብሔርን ከብሔር እያጋጨ፣ አለፍ ሲልም በክልሎች መካከል ጦርነት እንዲቀሰቀስ እያደረገ ዘልቋል። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን በአንድ ጊዜ የማፈናቀል ዐቅም እስከማዳበርም ደርሷል።

ስውሩ ኃይል ኀብረ ብሔራዊና ቀጣናዊ ኃይል ወደመሆን ቀስ በቀስ እየገዘፈ ሄደ። የሚፈልገውን ፖሊሲና ሕግ ለማጽደቅ አሻንጉሊት ሆነው ያገለግሉኛል ብሎ ያሰባቸውን አካላት የመሾምና የመሻር ዐቅምም ገነባ። ዳኛን ማስፈራራት፣ ዐቃቤ ሕግን መመርመርና ፖሊስን ማሰር ቻለ።

በኢሕአዴግ ውስጥ የተፈጠረው ይህ ኀቡእ አውሬ የራሱ ፍርድ ቤቶችና ድብቅ ወኅኒ ቤቶች ስለነበሩት፤ የፈለገውን ሰው ለማሰር፣ ለመሰወርና ለመግደልም በቃ። የፈለገውን ዕቃ ከጉምሩክ ሕግ ውጭ ያስገባል፤

የፈቀደውን ሕንጻ ከከተማው ሕግና ፕላን ውጭ በፈለገው ቦታ ላይ ይገነባል። የፈለገውን ንግድ በፈለገው መንገድና መጠን፣ ያውም ያለ የመንግሥትን ጨረታዎች ያለተወዳዳሪ ይወስዳል፤ ፈቃድና ግብር ይነግዳል። በመንግሥት በጀትም የግል ጥቅሙን ያከናውናል። የመንግሥትን ንብረትም ለፈለገው ዓላማ ያውላል።

እነዚህ ሁሉ ነገሮች ተደራርበው ሀገረ መንግሥቱ ቅቡልነት እንዲያጣ አደረጉት። ይህም ከምንም በላይ ለኢትዮጵያ ትልቅ ጉዳት አስከተለ። ኢትዮጵያ የሁላችንም ቤት መሆኗ ምንም ጥርጥር የለውም። የትም እንወለድ፣ የየትኛውም ብሔር አባል እንሁን፣ ኢትዮጵያ ሁላችንንም በእኩልነት ማገልገል አለባት። ይህ አቋማችን ነበረ፤ አሁንም በጽኑ እናምንበታለን።

ይህን ተግባራዊ ስናደርግ ግን ሁለት ሕመሞች ፈጥረናል፡፡ እኩልነትን በትክክል አለማስፈናችንና ልዩነቶችም ሥር እንዲሰዱ መንገድ መክፈታችን። ይህ ጉድለት የተከሠተው በዋናነት ወደ ማንነት ዋልታ የተጠጋ ሥርዓት ስለገነባን ነው። “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ” ከ'ማፊያዉ ቡድን' አጀንዳና ተግባር ጋር ተዳምሮ ለገባንበት የችግር አረንቋ አንዱ ምክንያት ሆኖ አገልግሏል።

እንደ እምቦጭ አረም በኢሕአዴግ ውስጥ ያቆጠቆጠውና ቀስ በቀስ በመላ ድርጅቱ ውስጥ የተንሰራፋው የማፊያዉ ቡድን፣ መንግሥታዊና ድርጅታዊ ሥልጣንን በመዳፉ ውስጥ ለማስገባት ችሎ ነበረ። የማፊያውን ቡድን በመገዳደር ወደ ተስተካከለ ቁመና ለማምጣት በእያንዳንዱ ብሔራዊ ድርጅት እንደ ቡድንና እንደ ግለሰብ አያሌ ሙከራዎች ተደርገዋል።

በኦሕዴድ ውስጥ የማፊያውን ቡድን ለመገዳደር ትግሉ የተጧጧፈው በቅርቡ ቢሆንም ነገሩን መረዳትና አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ የተጀመረው ገና ድሮ፤ በድርጅቱ ምሥረታ የመጀመሪያ ዓመታት ላይ ነበር። በወቅቱ በዚህ እንቅስቃሴያቸው እንደ ሥጋት በመቆጠራቸው፣ ከድርጅቱ አመራርነትና አባልነት በልዩነት የተሰናበቱትን የዚያን ዘመን አመራሮች ማስታወስ ይቻላል።

በግንባሩ ውስጥ በነጠላና በቡድን የተካሄዱ እንቅስቃሴዎች ግን፣ ግንባሩን ወደ እርምትና መስተካከል ከማምጣት ይልቅ፣ ኦሕዴድ እንዲደፈጠጥና የማፊያዉ ቡድን ካርቦን ኮፒዎች እንዲበዙ ምክንያት ሆኗል። ጭራሽ የማፊያዉ ቡድን ጉልበቱን አደርጅቶ ሁሉም ኃይል በጥቂቶች እጅ ላይ እንዲቆይ በማድረግ፣ በፓርቲው ውስጥ ገዥ መደብ ፈጠረ።

እርግጥ ነው፣ ኢሕአዴግም ሆነ አባል ድርጅቶቹ ለሀገሪቷ ይበጃል፣ የሕዝቦቿንም _ ሕይወት ያሻሽላል' ብለው ያመኑበትን መሥመር ለመከተል ሲነሡ፤ ይህ ይመጣል የሚል ጥርጣሬ በውስጣቸው አላሳደሩም ነበር። ነገር ግን ትክክል ነው ብለን ያመንነው መሥመር ተግባር ላይ ሲውል፣ ያልታሰቡ ችግሮችን ፈጥሮ ሕዝባችንን ለምሬት፣ ሀገራችንንም የአደጋ ጠርዝ ላይ እንድትደርስ ማድረጉን በግልጽ ለማየት ችለናል። የለውጡም ዋና ዓላማ በኢሕአዴግ የተፈጸሙ ስሕተቶችን ከማረም ባሻገር፣ የሀገራችንን ዘመን ወለድ ችግሮች ቀርፎ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ወደ ከፍታ ማሻገር ነው።

“መሪ የሚያስተምረው በምግባሩም በቃሉም ነው” ማለት ታዘወትር ነበር ውዷ እናቴ። ለውጡን ለመምራት ሐላፊነት የተቀበልነው የዛሬዎቹ መሪዎች በቃልም፣ በተግባርም አስተማሪ ሆነን፣ ሀገርን የሚያሻግር ሥራ

ለመሥራት ፍላጎታችን የጸና ነው።

# ምዕራፍ ሁለት
## የፖለቲካ ትግል

**“ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሠማራ**
**እንደ ሆቺሚኒ እንደ ቼ ጉቬራ”**

~ የተማሪዎች ንቅናቄ መዝሙር

**የለውጥ ንጽጽራዊ እይታ**

‹‹ለውጥ›› የሕይወት አንዱ መልኳ ነው። በዚህ ዓለም ላይ የማይለወጥ ነገር የለም። ቋሚ የሆነ ነገር ቢኖር ራሱ ለውጥ ብቻ ነው። ሰዎችን ሁሉ የጋራ የሚያደርጋቸውም ለውጥ ነው። በለውጥ ውስጥ የማያልፍ፣ ቢፈልግም ባይፈልግም ለውጥ ሳይጎበኘው የሚቀር ምንም ነገር የለም። አንዳንዱ ይሄንን የሕይወት ሕግ ዐውቆ ትርጉም ያለው ለውጥ ያስተናግዳል።

ግሪካዊው ፈላስፋ ሶቅራጠስ እንደተናገረው፣ ለውጥ ትርጉም እንዲኖረው ከፈለግን አሮጌውን ለመቀየር በመታገል ሙሉ ኃይላችንን ከመጨረስ ይልቅ አዲስ ጡብ ለማስቀመጥ ብንፍጨረጨር የበለጠ እናተርፋለን። አሮጌውንና የማያስፈልገውን ነገር ራሱ ጠርጎ ይጥለዋል። ምን ጠንካራ ቢሆን፣ ለመሬት ለሰማይ የከበደ፣ ለሰው ሁሉ ያስቸገረ፣ ጊዜውን ጠብቆ ይፈርሳል።

የሰው ልጅ በሁለት ዓይነት የለውጥ ሂደቶች ማለፉ የማይቀር ሐቅ ነው። ለውጥ በአንድ በኩል በአዝጋሚነትና ማንም ሰው ልብ ሳይለው የሚመጣ፣ በሂደት የሚከማች ኢ-ንቁ ነው። ይህም በማይታዩ እጆች የሚከናወንና የነገሮች ክምችት የሚወልደው የለውጥ ሂደት ነው። ነገሬ ብለን የማናያቸው፣ ችላ ብለን የተውናቸው ጥቃቅን ነገሮች፣ በጊዜ ሂደት እየተሰባሰቡና እየተገናኙ ቀደም ብለን ባልጠበቅነው ልክ እጅግ የገዘፈ ነገር ይፈጥራሉ። በተፈጥሮ ውስጥ የምናያቸው ቁጥራቸው የበዙትና የተወሳሰቡ ሥርዓቶች፣ ቀደም ብለው ያልነበሩ በሚመስሉ ትናንሽ ቅንጣቶችና ትናንሽ ሥርዓቶች በመሰባሰብና በመከማቸት የተፈጠሩ ናቸው።

የፊዚካል ሳይንስ መላምቶች እንደሚጠቁሙት በብዙ ዓመታት ጉዞ ውስጥ ጥንት የነበሩ ሞሎኪውሎችና አተሞች ተሰባስበው ዛሬ የምናያቸውን ግዙፋን ነገሮች ፈጥረዋል። ቢሊዮኖችን ያቀፈችው ዓለማችን (አንድ መንደር፣ አንድ ማኅበረሰብ ሆናለች የምንላት) በዘመናት ውስጥ ጥቃቅን የሚባሉ ቤተሰቦች ወደ ጎሳ፣ ጎሳም ወደ ብሔር፣ ከዚያም ወደ ሀገርና ወደ አህጉር አድገው የአሁኑን ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ፈጥረዋል። ፖለቲካዊ ለውጥም እንደማንኛውም ለውጥ ኢ-ንቁ በሆነ መንገድ ሊመጣ ይችላል። ጥቃቅን ሁነቶች እየተገናኙ ራሳቸውን በትልቅ ማንነት ለመግለጥ በሚያደርጉት መሰባሰብ ያድጋሉ። ስብስቦቹ ሲያድጉ ከፍ ባለ መልኩ ለውጥ ሊመጣ ይችላል።

በሌላ በኩል ለውጥ በማኅበረሰቡ ንቁና ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲሁም በተቋማት ንቁ እንቅስቃሴ ሊመጣ ይችላል። ማኅበረሰቦች በፖለቲካም ይሁን በማኅበራዊ መስክ ለውጥ ለማምጣት ከተነሡ ማንም ኃይል ሊያስቆማቸው እንደማይችል የሀገራችንም ሆነ የሌሎች ሕዝቦች ታሪካዊ እውነታዎች ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ። በዚህ ረገድ የሀገራችንን ወቅታዊ ንቁ የለውጥ ሥርወ ነገርና ፍሬ ጉዳይ በቀጥታ ከማየታችን በፊት እንደ መንደርደሪያ የሚሆኑ ዕውቅ ሕዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን ለንጽጽር መመልከት ተገቢ ይሆናል።

# ፈጣሪን የተገዳደረ የእስራኤል ሕዝብ

የጥንት እስራኤላውያን፣ የግብጽ ፈርዖኖችን የፈጣሪ ያህል ይመለከቷቸው ነበር። በዚያን በባርነት ዘመናቸው፣ ለአራት መቶ ሠላሳ ዓመታት በግብጽ ሳሉ የግብጾች ባሪያ መሆናቸውን አምነው ተቀበለው ጉልበታቸውንና ዕውቀታቸውን ሁሉ ያለምንም ምንዳ ያፈስሱ ነበር።

ፈርዖኖቹ በወቅቱ የአማልክት ልጆች ናቸው፤ ተብለው ይታመኑ ስለነበር ውሳኔዎቻቸውን መቃወምም ሆነ መገዳደር የማይታሰብ ነበር። ተግባራቸውም፣ ሐሳባቸውም እንደ ፈጣሪ ሥራ፣ እንደ ፈጣሪ ሐሳብ ተደርጎ ይወሰዳል። ከዚያ ባርነት መውጣት ማለት እንኳን ለፈርዖኖቹ ለራሳቸው ለእስራኤላውያኑም የማይታሰብ ነበር። ምክንያቱም ባርነቱ ለአራት መቶ ሠላሳ ዓመታት የቆዩበት ስለሆነ።

ከብዙ የባርነት ዓመታት በኋላ ሙሴ እስራኤላውያንን ነጻ ለማውጣት ራእይ ሰንቆ መጣ። ይህ ሰው የእስራኤልን ሕዝብ አንቅቶ፣ የነጻነትን ክብር አስረድቶና አደራጅቶ ካበቃ በኋላ ያንን ለአራት መቶ ሠላሳ ዓመታት በባርነት ይማቅቅ የነበረውን ሕዝብ አስከትሎ ተነሣ። እንዲያ ለሰማይ ለምድር የከበደውን ፈርዖን ተገዳደረው። መገዳደር ብቻ አይደለም፣ ከመንበሩ ወርዶ እንዲከተለው አስገደደው። እንደ ፈጣሪ ይታይ የነበረው የግብጽ ፈርዖን ሰማይ ለነካው ለዚያ ክብሩ ሲል እስራኤላውያንን ለመቅጣት በረሓውን፣ ጋሬጣዉንና እሾሁን ተሻግሮ ባሕሩ ላይ ሲደርስ ሰጥሞ ቀረ። በዚህ መልኩ እስራኤላውያን የግብጽ የሰቆቃ ጊዜያቸው አብቅቶ ወደ ተስፋቸው ምድር ገቡ።

በዚህ መልኩ ነጻነትን የተጎናጸፉ ሕዝቦች ከዘመናት በኋላ ሀገረ መንግሥታቸው ፈርሶ በመላው ዓለም ለመበተን በቅተዋል። የባርነትና የነጻነትን ልዩነት በተግባር ያዩት እስራኤላውያን ሀገረ መንግሥታቸው በመፍረሱ ለሺዎች ዓመታት በመላው ዓለም ተበታትነው፣ ከሰው በታች ሆነው እንዲኖሩ ተገድደዋል።

በቴላቪቭ ዩኒቨርሲቲ የባዮ ማቲማቲክስ ፕሮፌሰር የሆኑት ሌዊ ስቶን የቅርብ ጊዜ ጥናት እንደሚያመለከተው፣ ከፈረንጆቹ መጋቢት 1942 እስከ ኅዳር 1943 (እ.አ.አ) ባለው ጊዜ ብቻ 1.7 ሚልዮን አይሁዳውያን አልቀዋል። ከነዚያ ውስጥ 1.3 ሚሊዮኖቹ የተጨፈጨፉት ሦስት ወር ባልሞላ ጊዜ ነበር። በአጭሩ በእነዚያ ጥቂት ወራት ናዚዎች በየቀኑ 5 ሺሕ ሰዎችን ይጨፈጭፉ ነበር ማለት ነው። በአሰቃቂው የሩዋንዳ ፍጅት እንኳን ሰዎች በዚህ ፍጥነት አልተጨፈጨፉም ነበር። በፕሮፌሰር ስቶን እምነት፣ በዚያን ወቅት በአጠቃላይ ወደ ስድስት ሚልዮን የሚሆኑ አይሁዳውያን በናዚዎች እና በደጋፊዎቻቸው ተጨፍጭፈዋል።

ዛሬ ከሞትና ከእልቂት የተረፉት የእስራኤል ሕዝቦች ራሳቸውን አጠንክረው የደረጀ ሀገር ገንብተው መኖር ጀምረዋል። ለሀገር ግንባታቸው መሳካት አስተዋጽዖ ካበረከቱ ጉዳዮች መካከል፤ ምንም እንኳን ሕዝቦቻቸው በመላው ዓለም የተበተኑ ቢሆኑም፤ እንደ ሕዝብ አንድ የሚያደርጓቸውን ዕሴቶች፣ ወጎችና ልማዶች አለመተዋቸው ተመሳሳይ ሥነ ልቡና እንዲኖራቸው ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። በዚያ ላይ እንደ ቡድን ሲካሄድባቸው የነበረው መገፋትና መሳደድ ወደ አንድ መጥተው ጠንካራ ሀገር እንዲመሠርቱ ረድቷቸዋል። ያም ሆኖ ግን ያለ ሀገረ መንግሥት ረጅም ዘመን መቆየታቸውና ቀደም ሲል የኔ የሚሉት ሀገር በሌሎች ሕዝቦች ተይዞ መቆየቱ መልሰው በያዙት ሀገር ላይ የባለቤትነት ጥያቄ እያስነሣ ዕረፍት እንዲነሣቸው አድርጓቸዋል።

በዚህም በዙሪያቸው ካሉ የዓረብ ሀገራት ጋር የጎሪጥ እየተያዩ ለመኖር ተገድደዋል። የሀገረ መንግሥት መፍረስና የሕዝብ መበተን የሚያሳየውን ፍዳ፣ መልሶ ሀገርን ለመገንባትም ያለውን ፈተና ከእስራኤል በላይ ምሳሌ የሚሆን አንዳንድ ነገሮችን እንከናቸውን እያሻሻሉ አጽንቶ መያዝ እንጂ ካጧቸው በኋላ መልሶ

ለማግኘት መሞከር ከባድ ነው። ሀገር አንዴ ካጣናት ለማግኘት እጅግ ከሚከብዱን ነገሮች ውስጥ መሆኗን ልብ ልንል ይገባል።

# ቻይና - በቢልዮንን ያሸነፈ ሀገር

ቻይና፣ ለበርካታ ዓመታት ባለ መንታ አሐዝ ዕድገት በብቸኝነት ስታስመዘግብ የቆየች፣ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦቿን ከድህነት አላቅቃ ዘመናዊ ለመባል የበቃች፣ የ20ኛው ክፍለ ዘመን አስደናቂ ሀገር ነች። የቴክኖሎጂ ዐቅሟ ምዕራባውያንን ጭምር የሚያሠጋ፣ በኢኮኖሚ ትልቅነትም ከመሪዎቹ አንዷ የምትባል ሀገር ሆናለች።

ለዚህ ሁሉ ትልቅነት የበቃችው ሀገር ቻይና፣ በአንድ ወቅት ህልውናዋ ቋፍ ላይ የደረሰበት መጥፎ ጊዜ አጋጥሟት ነበር። የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ፣ በ1949 (እንደ አውሮፓ አቆጣጠር) ሀገሪቱን ከኮሚንታንግ አገዛዝ አላቅቆ ነጻ ያወጣት ቢሆንም፤ ከአንድም ሁለት ሦስት ጊዜ የራሱንም የሀገሪቱንም ህልውና ገደል ውስጥ ሊጨመር ከጫፍ ደርሶ እንደነበር ይታወሳል። ፓርቲው ከዚያ የቀውስ ወቅት አገግሞ ዛሬ ታላቅ ሀገርን ለመገንባት በቅቷል። ሆኖም ከምሥረታው ጊዜ ጀምሮ በወቅቱ በሥልጣን ላይ የነበረውን ኮሚንታንግን ጥሎ ሥልጣን እስኪቆናጠጥ ድረስ ከፍተኛ ተጋድሎዎችን አድርጓል።

የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት በሚታገሉበት ወቅት በቻንግ ካይ ሼክ የሚመራው የኮሚንታንግ መንግሥት፣ የኮሙኒስት ፓርቲውን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ ከፍተኛ ዘመቻ ከፍቶባቸው ነበር። የዘመቻው ዋነኛ ዓላማ፣ የኮሙኒስት ፓርቲውን ሠራዊት በየቦታው እየከበቡ፣ መደምሰስ እና ከነአካቴው ማጥፋት ነበር። ከ1930 እስከ 1934 በነበሩት ዓመታት፣ ቻንግ ካይ ሼክ እንዲህ ያሉ አምስት ታላላቅ ወታደራዊ ጥቃቶችን በኮሙኒስት ፓርቲው ላይ ሰንዝሯል።

በሊቀመንበር ማኦ የሚመራው የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ቀዩ ጦር፤ አራቱን ከሆነ እና የመደምሰስ ዘመቻዎች በተሳካ ሁኔታ ማክሸፍ ቢችልም፤ አምስተኛው ከግን በፍጹም ሊቋቋሙት የሚችሉት ኃይል አልነበረም። ቻንጋይ ሼክ ቀዩን ጦር ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ በርካታ ምሽጎችን መገንባቱ አልበቃህ ብሎት፣ 700,000 ወታደሮች ያሉበትን ሠራዊት ነበር ያዘመተባቸው። ቀዩ ጦር፣ በሻንግ ካይ ሼክ ጦር ሙሉ በሙሉ ተከበበ።

በዚህ አስጨናቂ ወቅት ነበር፣ ኦክቶበር 16፣ 1934 ዓ.ም.፣ ረጅሙ ጉዞ (ዘ ሎንግ ማርች) እና ሽሽት የተጀመረው። ቀዩ ጦር፣ በትጥቅና ድርጅት ሳሳ ያለውን የቀለበቱን ክፍል፣ ባልተጠበቀ ሰዓት ሰብሮ በመውጣት የሞት ሞቱን ከከበባው ለማምለጥ ቻለ። ከበባውን ጥሶ መውጣት ግን የፈተናው መጀመሪያ እንጂ መጨረሻው አልነበረም። የኮሚንታንግ ጦር ቀዩ ጦር ከበባውን ሰብሮ መውጣቱን ሲረዳ ያለ የሌለ ኃይሉን አሰባስቦ ቀዩን ጦር ማሳደድ ጀመረ። በዚህ ወቅት ቀዩ ጦር 85 ሺሕ ወታደሮችና 15 ሺሕ አዋጊዎች ነበሩት። ስንቅና ትጥቅ በሰው ትከሻ እንዲሁም በጋማ ከብት ተጭኖ፣ ቀዩ ጦር ተራሮችን እያቋረጠ፣ ወንዞችን እየተሻገረ፣ እየሸሸም፣ እየተዋጋም 368 ቀኖችን በጭንቅ አሳልፏል። በመጀመሪያዎቹ የጉዞ ሳምንታት፣ የጦሩ

መሪ ማኦ ሴ ቱንግ ራሱ በጠና ታሞ የሚጓዘው በሸከም ነበር። ረጅሙ ጉዞ ሲጀመር ርጉዝ የነበረቺው ባለቤቱ ልጇን የተገላገለችው በዚህ አስጨናቂ የሽሽትና የውጊያ ወቅት ነበር። በዚያ ወቅት ሌላ ምርጫ ስለአልነበረ ልጇን ለአንድ የገበሬ ቤተሰብ ሰጥታ መንገዷን ቀጥላለች።

በወቅቱ ከተከናወኑና እስከዛሬም ከሚታወሱ የጀብድ ሥራዎች አንዱ የ29 ዓመቱ ቼን ተጋድሎ ነው። ከኋላ እየተተኮሰበት ወደ ፊት መሸሽ የያዘው ቀዩ ጦር ሄዶ ሄዶ ከፊት ለፊቱ ከባድ ወንዝ ያጋጥመዋል። ወንዙን ከመሻገር ውጭ ሌላ ማምለጫ መንገድ የለም። ጊዜም የለም። በዚህ ጊዜ የ34ኛው ቀዩ ጦር አዛዥ የነበረው ወጣቱ ቼክ ወታደሮቹን ይዞ ወደ ኋላ በመመለስ ከኮሚንታንግ ጦር ጋር ውጊያ ገጠመ።

እሱና ጓዶቹ ከነጩ ጦር ጋር ሲፋለሙ፤ ቀዩ ጦር ወንዙን መሻገር ይዟል። ቼን እና ዶቹ የኮሚንታንግን ጦር ገትረው ተፋለሙ። እንደ ማዕበል የሚተመውን የኮሚንታንግ ጦር ፊት ለፊት ገጥመውና አግደው ይዘው ኃይላቸው ሲዳከም፣ ነጩን ጦር በደፈጣ ውጊያ ተያያዙት። አዛዣቸው ቼን ቆስሎ በጠላት ተማረከ። ከነሕይወቱ ላለመማረክ ቼን የራሱን አንጀት ዘርግፎ ሞተ። በዚያ አንድ ዓመት ገደማ በፈጀ የሽሽትና የነፍስ አድን ዘመቻ ወቅት፣ ቀዩ ጦር በጠቅላላው 660 ውጊያዎችን ለማድረግ ተገዶ ነበር። በእያንዳንዱ ኪሎ ሜትር ጉዞ ላይ የሦስት ወይም የአራት ተዋጊዎቹን ሕይወት እየገበረ ነበር ጦሩ የሚጓዘው።

ረጅሙ ፈተና ሲጀመር ወደ መቶ ሺሕ ይጠጋ የነበረው የቀዩ ጦር ሠራዊት፤ ሽሽቱ ሲጠናቀቅ ሠላሳ ሺሕ ብቻ ሆኖ ነበር። በጦር ሜዳ ከመሠዋት የተረፈውም አንዳንዱ በረኃብ እና በበሽታ አለቀ። ግማሹም የደረሰበት ጠፋ። በዚህ ቀውጢ ጊዜ ጠፍተው ከቀሩት መሐል የሊቀ መንበር ማኦ ሁለት ሕፃናት ልጆች እና ወንድሙ ይገኙበት ነበር። የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ከዚህ አስከፊ ውጊያ ተርፎና ያን ሁሉ አሰቃቂ ጊዜ ተሻግሮ በ1949 ሀገሪቱን ተቆጣጠረ። ቀስ በቀስም ቻይናን በዓለም ሁለተኛዋ ባለ ታላቅ ኢኮኖሚ ሀገር ሊያደርጋት ቻለ። አሁን በመግዛት ዐቅም በተለካ አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (GDP, PPP)፣ የቻይና ኢኮኖሚ በዓለም ትልቁ ኢኮኖሚ ነው።

ዛሬም ድረስ በድህነት የምትታወቀዋ አፍሪካ፣ ከዐርባ ዓመታት በፊት የዜጎቿ የነፍስ ወከፍ ገቢ 499 የአሜሪካ ዶላር ነበር። በተመሳሳይ ያኔ የቻይና የነፍስ ወከፍ ገቢ 155 የአሜሪካ ዶላር ብቻ ነበር። በዚያን ጊዜ ከሁለት መቶ የዓለም ሀገሮች ቻይና ከመጨረሻዎቹ ሦስት ድሀ ሀገሮች አንዷ ነበረች። በ2017 የቻይና የነፍስ ወከፍ አጠቃላይ ምርቷ ወደ 8836 የአሜሪካ ዶላር አድጓል። ከ2009 ወዲህ ቻይና የዓለም ሁለተኛዋ ግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት ሆናለች። በ2010 አውሮፓዊቷን የቴክኖሎጂ ዋርካ ጀርመንን አልፋ ሸቀጥ ወደ ውጭ በመላክ በዓለም ግንባር ቀደሟ ሀገር ሆናለች።

በ2013 ደግሞ አሜሪካንን ራሷን አልፋ በዓለም የመጀመሪያዋ ንግድ የምታቀላጥፍ ሀገር ለመሆን በቅታለች። በዚህ ፈጣን ግሥጋሴ ውስጥ የአሁኗ ኢትዮጵያ ያላትን የሕዝብ ቁጥር ሰባት እጥፍ በሆነ ደረጃ (ከ700 ሚልዮን በላይ ቻይናውያንን) ከድህነት አዘቅት አውጥታለች።

ቻይና ለዚህ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያበቃት የሀገረ መንግሥትና የሀገረ ብሔር ግንባታው በተሻለ ሁኔታ በመካሄዱ ነው የሚል አስተያየት ይሠነዘራል። ለዚህም ትልቅ አስተዋጽዖ ያበረከተው ቻይናን ከኮሚንታግ

ነጥቆ ሙሉ ለሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ያደረጋት የኮሙኒስት ፓርቲው በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ለሀገረ መንግሥትና ለሀገረ ብሔር ግንባታ የቅድሚያ ቅድሚያ መስጠቱ ነው።

የቻይና የሀገረ ብሔር ግንባታ ለረጅም ዘመን የምስለት ርምጃ ሲካሄድበት የቆየ ቢሆንም፤ በኮሙኒስት ፓርቲው የመጀመሪያ ጥቂት ዓመታት ላይ ቻይናውያን የጋራ የሚያደርጓቸው ዕሴቶች እንዲገነቡ የተደረጉ ጥረቶች ትልቅ ድርሻ ነበራቸው። በተለይም ደግሞ የቻይናውያን ባህል፣ ወግና ልማድ በኮንፊሽያኒዝም አስተምህሮ ላይ መመሥረቱ ቻይናውያን ራሳቸውን እንደ አንድ ቤተሰብ እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ በአቅራቢያቸው በምትገኘው ጃፓን የመወረር ሥጋት በማኦ ሲመራ የነበረው የሀገረ/ብሔረ መንግሥት ግንባታ የተፋጠነ እንዲሆን የበኩሉን ድርሻ አበርክቷል።

የሀገረ/ብሔረ መንግሥት ግንባታ ሂደቱን ተከትሎ ወዲያውኑ በእነ ዴንግ ሻኦ ፒንግ የተመራው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ተተገበረ። በዚህ ትግበራ ተአምራዊ የኢኮኖሚ አብዮት ከመፍጠር ባለፈ ቻይና በቀላሉ የማትናወጥ ጠንካራ ሀገረ ብሔር ወደ መሆን ተሸጋግራለች። ያም ሆኖ በቻይና የፖለቲካ ሪፎርምና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እምብዛም ያልተነካ ጉዳይ በመሆኑ ወደፊት የሚጨነቁበት የቤት ሥራቸው ነው።

# የአፍሪካ ሕዝቦች

አፍሪካ ‹‹ጨለማዋ አህጉር›› ተብላ፣ አውሮፓውያን እንደ ቅርጫ ተከፋፍለዋት፣ ለበርካታ ዓመታት ከሞላ ጎደል በባርነት ሥር ትማቅቅ ነበር። ከኢትዮጵያና ከላይቤሪያ በቀር መላ አፍሪካ በቅኝ ግዛት ቀንበር ሥር ወድቀው ነበር። በወቅቱ የዓለማችን ኃያላን የሆኑት ሰባቱ የአውሮፓ ሀገሮች ማለትም፤ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ቤልጂየም፣ ስፔን፣ ፖርቹጋል እና ጣልያን ተከፋፍለዋት ነበር።

አፍሪካውያን በዕውቀት፣ በሀብት፣ በመሣሪያ ከጌቶቻቸው በታች ነበሩ። ሆኖም አፍሪካውያን ንቃትን ካገኙ በኋላ ወራሪዎችን አሽቀንጥረው ለመጣል እንዲረባረቡ አድርጓቸዋል። በተለይም ደግሞ ኢትዮጵያ አውሮፓዊውን ሀገር ጣልያንን በዐድዋ ጦር ሜዳ የማንበርከኳ ዜና ታላቅ መነሣሻ ምክንያት ሆኗል። የዐድዋ ድል በአፍሪካውያን ዘንድ እየተዛመተ ሲመጣ በድል ዜናው እየተነቃቃ የመጣውን የአፍሪካውያንን የፀረ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ ሊያቆመው የሚችል አንዳች ኃይል አልተገኘም። የአፍሪካ የፀረ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴና ስኬቱ ሕዝቦች ለለውጥ ቆርጠው ከተነሡ ማንም ኃይል ሊያቆማቸው እንደማይችል ማሳያ ነው።

ያም ሆኖ ግን የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ ገዥዎቻቸው ነፃ መሆናቸው ብቻውን ጠንካራ የሆነ ሀገር እንዲገነቡ አላስቻላቸውም። በሁለት ምክንያቶች የሀገር ግንባታው ፈተና የበዛበት ሆኗል። የመጀመሪያው ቅኝ ገዥዎቹ የፈጠሯቸው ሰው ሠራሽ ድንበሮች ቋሚ መሆናቸው ነው። በሰው ሠራሹ ድንበር ምክንያት ቀደም ብለው አንድ ላይ የነበሩ ጎሳዎችና ብሔሮች ለሁለት ተከፍለዋል። ቀደም ብለው አንድ ላይ ያልነበሩ ጎሳዎችና ብሔሮች ደግሞ በአንድ ክልል ውስጥ እንዲቀመጡ ተደርገዋል። ይህ ደግሞ ለማያባራ ሽኩቻና ጦርነት ዳረጋቸው።

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከነጻነት በኋላ መንበረ ሥልጣኑን የወረሱት አስተዳዳሪዎች ለሀገረ/ብሔረ መንግሥት ግንባታ አስፈላጊና መሠረታዊ የሆኑ ርምጃዎችን በአፋጣኝ አለመውሰዳቸው የፈጠረው ጦስ

ነው። ለሀገረ ብሔረ መንግሥት ግንባታ ተገቢው ቦታ አለመሰጠቱ ከመሪዎቹ ከራሳቸው አልፎ የሀገረ መንግሥቱ ተቀባይነትን ጥያቄ ምልክት ውስጥ እንዲወድቅ አድርገውታል።

# ኢትዮጵያና ሕልሟ

ልክ በሌሎች ሕዝቦች ላይ እንዳየነው፣ የሀገራችን ሕዝቦችም በሀገረ መንግሥታችን ታሪክ ከብዙ ዕንቅልፍ በኋላ እየነቁ ከሕይወት የገዘፉ መሪዎቻችውን አሽቀንጠረው ሲጥሉ ታይቷል። የረጅም ጊዜ ታሪኩን ትተን የቅርብ ጊዜውን ስንመለከት ይሄንኑ ተመሳሳይ ሁኔታ እናያለን። በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ እንደ ሀገርና ሕዝብ ተጭኖና ተደቅኖ የነበረው መከራና የመበታተን አደጋ፣ የመብት ረገጣና አፈና፣ ድህነትና ጉስቁልና ከባድ ነበር። ይህ ሲታሰብ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ያለውን የለውጥ ሂደት አጠናክሮ ከመቀጠል ባሻገር አማራጭ መንገድ እንደሌለን እንረዳለን።

በተለይም በንቁ የሕዝቦች ተሳትፎ የሚመጣ የለውጥ ማዕበል ከችግር የጸዳ ሊሆን አይችልም። የተያያዝነው ለውጥም ቢሆን ሂደቱ ከችግር የጸዳ ነው ለማለት አይቻልም። ይጠቀስ ቢባል ከአንድ ሺሕ አንድ በላይ የችግር ዓይነቶች ሞልተውናል። ከፍ ብለን በማነጻጸሪያነት ያቀረብናቸው ሌሎች ሕዝቦችም የገጠማቸው እኛ ላይ ከተደቀኑት ችግሮች ቢብሱ እንጂ የሚያንሱ አይደሉም።

በተቃራኒው እኛ መጠቀም ሲገባን ያባከንናቸው በርካታ ዕድሎችና አሁንም ለመሥራት ቆርጠን ከተነሣን መነሻ ዐቅም የሚሆኑን ወረቶች አሉን። ያባከንናቸው ዕድሎችም ሆኑ መነሻ ወረቶቻችን የሚገኙት ትናንት ላይ ስለሆነ ጥቂት ዓመታትን ወደ ኋላ ተመልሰን ቃኘት ቃኘት ብናደርግ የበለጠ ግልጽ ይሆንልናል። ከዚያ በፊት ግን እንደ ሀገር መሥራትና መመለስ የሚገቡን የሕዝብ ጥያቄዎችን (ፍላጎቶችን) አጠር ያለ ዳሰሳ አድርገንባቸው ብናልፍ ጠቃሚ ነው።

ጥቅል ከሆነው የህልውና ፍላጎት የሚቀዱት ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ፍላጎቶች የኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካዊ አጀንዳዎቻችን ማጠንጠኛዎች ናቸው። ቀጥተኛ የህልውና ፍላጎት ሲባል እንደ ግለሰብም ይሁን እንደ ሀገር ከቀጥታ የህልውና ጥቃቶች ራስን የማዳንና ህልውናን አስጠብቆ የመቆየት ፍላጎትን የሚያመለክት ነው። ግለሰቦች አካላዊ ጥቃት እንዳይደርስባቸው፣ እንዳይገደሉና እንዳይሰቃዩ ይፈልጋሉ። ሰዎች ቀጥተኛ የሆነ አደጋ ሲገጥማቸው ተፈጥሮ የሰጣቸው ደመነፍስ እንኳን ይታዘዛል። መኪና ሊገጨው ወይም አውሬ ሊያጠቃው የመጣ ሰው ይሮጣል፤ ወይም ይዘላል፤ ወይም ደግሞ ባልተጠበቀ መልኩ በደመነፍስ ፊት ለፊት ተጋፍጦ ራሱን ይከላከላል።

ይሄንን የዜጎች ቀጥተኛ ፍላጎት ለማሟላት መንግሥት እንደ ፖሊስ፣ የጸጥታና የደኅንነት ተቋማትን አቋቁሞ ምላሽ ይሰጣል። በተመሳሳይ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ከቀጥተኛ ጥቃት፣ ከውጭ ወረራ እና ከሉዓላዊነት መደፈር መጠበቅ፣ ክብሯንና ነጻነቷን ሳታስነካ መቆየት አለባት። ይህንን ለማሳካትም በአራቱም ዐውደ ውጊያዎች ማለትም በመሬት፣ በአየር፣ በሳይበር እና በባሕር የሚሰነዘሩ ጥቃቶችን መመከት የሚችል የሀገር መከላከያ ተቋም ተገንብቶ ተልእኮውን በአግባቡ መወጣት ይኖርበታል።

ቀጥተኛ የህልውና አደጋው ግዴታ ከውጭ የሚሰነዘር ብቻ ላይሆን ይችላል። አልፎ አልፎ ሀገር እንደ ሀገር እንዳትቆይ የሚያደርጉ አደገኛ እንቅስቃሴዎች የሀገርን ህልውና ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ ይችላሉ። ለአብነት በለውጡ ጅማሮ ሰሞን ያጋጠሙና ሀገር ላይ ከፍተኛ አደጋ የማድረስ አዝማሚያ የተስተዋለባቸውን አጋጣሚዎች መጥቀስ ይቻላል። በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል፣ በተለይም ደግሞ በሶማሌ ክልል የተፈጠረና በሀገር ደረጃ እንዲዛመት ታስቦ በለውጡ ጥቅማቸው በተነካባቸው ሰዎች ሲቆሰቆስ የቆየው የሃይማኖትና የብሔር ግጭት ነበር። ይህ አደገኛ የግጭት ጥንስስ በፍጥነት በቁጥጥር ሥር ባይውል ኖሮ፣ በሀገር ህልውና ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ እጅግ ከፍተኛ በሆነ ነበር። ሌሎችም ተመሳሳይ ግጭት ፈጣሪ እንቅስቃሴዎች፣ የሀገርን ህልውና በእጅጉ አደጋ ላይ የሚጥሉ ብቻ ሳይሆን ሀገር አልባ ሊያደርጉን የሚችሉ በመሆናቸው፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በንቃት እየተከታተለ ሊመክታቸው ይገባል።

ሰዎች ቀጥተኛ የህልውና ፍላጎታቸው ከተሟላ ፍላጎቱ እዚያ ላይ ያቆማል ማለት ግን አይደለም። ተዘዋዋሪ የሆኑት የህልውና ፍላጎቶች፤ የሥጋ ፍላጎቶች (የመብላት፣ የመጠጣት፣ የመጠለልና የመሳሰሉት በቁስ ሊመለሱ የሚችሉ)፣ የስም ወይም የክብርና የነጻነት ፍላጎቶች እንዲሟሉላቸው ዜጎች አጥብቀው ይፈልጋሉ። ሰዎች ስማቸው በመልካም እንዲነሣ፤ የግልም ይሁን የቡድን ማንነታቸው እንዲከበርላቸው፤ በሃይማኖታቸው፣ በብሔራቸውና በባህላቸው ምክንያት ምንም ዓይነት አድሎ፣ መገለል፣ መንጓጠጥ እንዳይደርስባቸው፣ ከሌሎች ጋር እኩል ሆነው እንዲታዩ ይሻሉ።

ዜጎች ከሌሎች ጥምዘዛ ነፃ የመሆን ፍላጎታቸው በተመሳሳይ ሌላኛው ተዘዋዋሪ ፍላጎታቸው ነው። ውሳኔያቸውን በራሳቸው እንዲያሳልፉ፣ የሚወዱትን ራሳቸው እንዲመርጡ፣ ዕጣ ፈንታቸውን በራሳቸው መንገድ እንዲከውኑ፣ ሐሳባቸውን ያለ ከልካይ እንዲያንጸባርቁ ይፈልጋሉ።

እነዚህ ፍላጎት አለመሟላታቸው በተዘዋዋሪ ጥቅል በሆነው ህልውናን አስጠብቆ በመቆየት ፍላጎት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ቀጥተኛ ፍላጎቶችም ሆነ ተዘዋዋሪ ፍላጎቶች በቋሚነት አንዳቸው ቀድመው የሚመጡ ወይም አንደኛው ከሌላኛው በቋሚነት የሚበላለጡ አይደሉም። አልፎ አልፎ በጋራ አንድ ላይ ተሳስረው፣ አንዳንዴ ደግሞ አንዳቸው ከሌላኛው ጋር ተቃራኒ ሆነው (መስለው) የመምጣታቸውን እውነታ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይሄንን አለመረዳት፣ ፍላጎቶቹን ለመመለስ በምንንቀሳቀስበት ወቅት የአንደኛው ሰው ፍላጎት ሲሟላ በሌላ በኩል የሌላው ሰው ፍላጎት ሊደፈጠጥ ይችላል። ለምሳሌ የብዙዎችን የህልውና አደጋ ለማስጠበቅ ሲባል በሚፈጠር የጠበቀ ቁጥጥር ጥቂቶች ነጻነት ሊያጡ ይችላሉ። ወይም የክብር ፍላጎት እንዳይደፈጠጥ ሲባል በአንዳንድ ነጻነቶች ላይ (ለምሳሌ የመናገር ነጻነት) ገደብ እንደሚደረገው ያለ ነው።

ከአሜሪካው የመስከረም 11ዱ (እ.አ.አ ሴፕቴምር 11፣ 2001) ጥቃት በፊት በየአውሮፕላን ጣቢያዎች ሁሉን ነገር የመበርበር እንዲሁም የገንዘብ ዝውውርና የመሳሰሉት ላይ እምብዛም ገደብ አይደረግም ነበር። ነገር ግን ከዚያ የሽብር ጥቃት በኋላ የተደረገው ገደብ የሕዝብን ደኅንነት ለመጠበቅ በሚል ስለሆነ በብዙዎች የዓለም ሕዝቦች ቅቡልነት አግኝቷል።

ተደጋግሞ እንደሚነገረው ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት ወሳኝ የሚባሉ የለውጥ ምዕራፎች ተከፍተውላት ነበር።

ነገር ግን የሕዝብን ፍላጎት አመርቂ በሆነ መልኩ የመመለስ ዕድል ኖሯት ሳትጠቀምበት አምልጧታል። በዚሁ ምክንያት ተመሳሳይ ጥያቄዎች ለሃምሣና ለስድሳ ዓመታት እየተንከባለሉ ደጋግመው ሲጠየቁ ይደመጣሉ። ዛሬም ዜጎች ከነጻነት፣ ከእኩልነትና ከዴሞክራሲ ጥያቄዎች ባልተናነሰ የምግብና የመጠጥ ጥያቄ አላቸው። አስፈላጊ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ሪፎርሞች ባለመከናወናቸው ምክንያት ከሃምሣ ዓመታት በፊት የነበረ የሀገር የህልውና ሥጋት ዛሬም አልተለየንም።

ሕዝቦች በቋንቋቸው ለመገልገል፣ ባህላቸውን ለማጎልበት፣ ሌሎች መብቶችን ለመጎናጸፍ እንዲችሉ ፌደራሊዝምን ተግባራዊ አድርገናል። ከፌዴራሊዝም ሥርዓት ጎን ለጎን ማጎልበት ያለብንን የትውልድና የወንድማማችነት ግንባታ በቂ ትኩረት ሰጥተን አልሠራንም። በዚህም የተነሣ ከመቀራረብ ይልቅ መራራቅ እየሰፈነ ሌላው ቀርቶ የሀገረ መንግሥቱ ቅቡልነት ዛሬም ጥያቄ እንዲነሣበት ሆኗል።

ሀገረ መንግሥቱን ቅቡልና ከሥጋት ነጻ ከማድረግ ባልተናነሰ፣ የትውልድ ግንባታን፣ የዴሞክራሲና የፖለቲካ ሪፎርምን፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ብልጽግናን ባንድ ላይ ለማከናወን አስገዳጅ ነገሮች ተፈጥረዋል። በዚህ ረገድ ለውጡን የምንመራበት የመደመር እሳቤ ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል።

መደመር የችግሮቻችን መፍቻ ሆኖ ሲመጣ መነሻ የሆነው ዋነኛው ምክንያት፤ ብዙዎቹ ችግሮቻችን ከመደመር ዕሴት መላላት የመነጩ ናቸው የሚል ነው። በአስተሳሰብም ይሁን በተግባር የተናጠል፣ የመበታተን፣ የማጥለል፣ አንዱን ይዞ አንዱን የመጣል ችግሮች ከመደመር ዕሴት መላላት ጋር የሚገናኙ ናቸው። ከዚህ አኳያ መደመር ችግሮቻችንን ለመፍታት ሲንቀሳቀስ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ መሠረቱን ይጥላል።

**አንደኛ - የጋራ ራእይ መፍጠር ፦** የምንፈልገው ምን ዓይነት ሀገር ለመፍጠር ነው? ምን ዓይነት ሕዝብ ነው ለማየት የምንመኘው? እንደ አሁኗ ቻይና፣ ሲንጋፖርና ታይዋን ያለች ጠንካራ ኢኮኖሚ ያላት ሀገር ነው? ወይንስ እንደ ደቡብ አፍሪካ፣ ጋና፣ ታንዛኒያና ብራዚል ያለ ከነእንከኑም ቢሆን መሠረታዊ መመዘኛዎችን ዴሞክራሲያዊ መርሖችን የሚያሟላ ሀገር ለመፍጠር? አሁን ያለው የቀጣናችን፣ የአህጉራችን ብሎም የዓለም ሁኔታ ሲታይ፤ ሁለቱም መንገድ ለየብቻ የሚያዋጡ አይመስሉም።

ታድያ ኢኮኖሚውንም፣ ዴሞክራሲውንም አቻችሎ የሚበለጽግ _ ሀገር ለመፍጠር የምንችለው እንዴት ነው? መፍጠር የምንፈልገውን ሀገር በግልጽ ማወቅ ይኖርብናል። ይሄን የጠራ ሕልም ማወቅና መለየት ከቻልን፣ ሌሎችም እንዲያዩት፣ ሕልማቸውና ራእያቸው አድርገው እንዲይዙት፣ እንዲዋጉለት ማድረግ ከባድ አይሆንም። ትክክለኛና ጥርት ያለ ሕልም ካለው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚያ ሲል ምን ማድረግ እንደሚችል ደጋግመን አይተናል። ጫማ ሳይኖረው፣ የረባ ልብስ ሳይኖረው፣ በቂ መሣሪያ ሳይኖረው፣ ጣልያንን ዐድዋ ላይ ድል ያደረገው ትልቅ ሕልም ስለነበረው ነው። ሕዝብ የኔ የሚለው ትልቅ ሕልም ሲኖረው፤ ምን ማድረግ እንደሚችል፣ በአምስት ዓመቱ የዐርበኝነት ዘመን፣ በ66ቱ አብዮት መባቻ፣ በሶማልያ ወረራ ጊዜ ደጋግሞ አሳይቶናል። ሕዝብ ለትልቅ ጉዳይ ከተነሣ፣ ከነድህነቱ፣ ከነበሽታውና ከነእርዛቱም ቢሆን ተአምር መሥራት ይችላል። እስራኤላውያን አድርገውታል፤ ቻይናውያን ደግመውታል። እኛም ደግመን ደጋግመን አድርገነዋል። ወደፊትም ልናደርገው እንችላለን። የጠላት ወረራ ወይም የድንበር መገፋት በሕዝብ ልብ ውስጥ ትልቅ ሕልም

መሣል እንደሚችል ደጋግመን አይተናል።

መራብ፣ መታረዝ፣ በበሽታ መሰቃየት፣ በአምባገነኖች እየተረገጡ መኖር፣ እየተዋረዱ መሞትና የመሳሰሉት በሕዝብ ልብ ውስጥ ትልቅ ሕልም፣ ትልቅ ቁርጠኝነትና ከባድ እልህ መፍጠር የማይችሉት ለምንድነው? እነዚህ ከወረራም፣ ከድንበር መገፋትም ያላነሱ፣ እንዲያውም በብዙ እጅ የሚልቁና ለዘመናዊ ኑሮ አንገብጋቢ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህን ለትልቅ ሕልም መፍጠሪያነት በማብቃት፣ ሕልሙንም የሕዝብ ሕልም በማድረግ፣ በመደመር ሀገራዊ ተአምር መሥራት ይቻላል። መደመር ቃሉ ሲጠራ ለማስታወስ እጅግ ቀላል መስሎ ይታያል። በውስጡ የተሰደረው ዓላማና ሐሳብ፣ አቅጣጫና ግብ ግን ነገሩ ረቂቅ ትንታኔውንም ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል።

የሀገራችንን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጉዳዮች ውስብስብ ጥልፍልፎሽ፣ ችግሮችንና ስብራቶችን በትክክል ለመረዳት ጥልቅ እይታ የሚሻ ነው። ምላሽና አማራጭ የመፍትሔ ሐሳብ የማመንጨቱ ሂደትም በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በማኅበራዊ ዘርፎች አጠቃላይ የንድፍና የግንባታ ምሕንድስና ይፈልጋል። በጥሞና ማሰላሰልና መቅረጽ ይጠይቃል። በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከሠተው ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ መደመርን እንደ አዲሱ የለውጥ እንቅስቃሴ መሪ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ የአስተሳሰብ መንገድ ጎልቶ እንዲወጣ ምቹ መንገድ ፈጥሮለታል።

መደመር ሀገረ መንግሥት፣ ዴሞክራሲ፣ ፍትሕ፣ ኢኮኖሚና የሰላም ግንባታ ነባር ሀገራዊ ፅንሰ ሐሳቦችን በመመርመር፣ በማሰናሰልና በማጥለል፣ አዲስና አማራጭ የመፍትሔ ጎዳና ያቀረበ እሳቤ ነው። መደመር የመፍትሔ ጎዳና ብቻ ሳይሆን መጓጓዣ ትራንስፖርቱንና የመንገድ ላይ ሥነ ሥርዓቱን አደራጅቶ ያቀረበ እሳቤ ነው። የኢትዮጵያ ነባር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ስብራቶች ካጋጠማቸው የሞትና የሽረት አማራጮች መካከል ትንሣኤው የተቀነበበበት ስኬታማ መፍትሔ ነው።

በሌላ አገላለጽ የመደመርን መርሕና አስኳል መሠረት በማድረግ ሁለንተናዊ የችግር የእይታ መነጽር መፍጠር አስፈላጊ ነው። በዚህ ሁለንተናዊ የችግር የእይታ መነጽር አማካኝነት አሁን ላጋጠመን ፈተናና ወደፊትም ለሚገጥሙን ችግሮችና ጋሬጣዎች መፍትሔ በመስጠት ወደላቀ ምዕራፍ መሸጋገር የሚያስችለን የስኬት መሰላል ነው። ነባሩን የኋልዮሽ ጉዞ በአስቸኳይ በመግታት፣ ሀገርን ከቀውስና ከእልቂት የሚታደግ ነው። ሀገርን ከእልቂት ታድጎ ወደቀናውና ዘላቂ ወደሆነው የሰላምና የብልጽግና ጎዳና ለማሸጋገር ሁሉም ዐቅሞች በትብብርና በአብሮነት የሚሰለፉበት ጎዳና ነው።

ፍቅርና ይቅርታን ወደፊት በማምጣት፣ ዕርቀ ሰላምና ፍትሕን በማስገኘት ጽንፈኝነትና አግላይነትን በማስቀረት፤ ለጋራ ዕድገትና ብልጽግና በጋራ ለመቆም የሚያስችለንን ወርቃማ አማካይ በመደመር እሳቤ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። የመደመር የመጨረሻ ውጤቱ ሥሉጥ (ዳይናሚክ - ከሚለዋወጡ ሁኔታዎች ጋር ፈጥኖ ራሱን ማስተካከል የሚችል) ሥርዓት መፍጠር ነው። ራሱን በራሱ የሚያርም፤ ችግሮች ሲገጥሙት በቀላሉ ፈትቶ የሚሻገር ሥርዓት መገንባት ነው።

**ሁለተኛ - ትክክለኛ መሪ መፍጠር ፡-** ቁልጭ ብሎ የሚታይ የሀገር ሕልም ያለ ጥበብ የትም አይደርስም።

ምርጥ ምርጥ የተባለ ሐሳቦች፣ ሕልሞችና ራእዮች ትክክለኛ መሪ አጥተው ሲባክኑ ታሪክ ደጋግሞ አሳይቶናል። የእስራኤላውያኑ የነጻነት ሕልም፤ ሙሴን የመሰለ ትክከለኛ መሪ አስፈልጎታል። አዎ ሙሴም ራሱ፣ ሰው ነውና የሚይዘው የሚጨብጠው ሲጠፋው ልክ እንደሚመራቸው ሕዝቦች ተስፋ ይቆርጥ ነበር። ያጉረመርምና ፈጣሪውንም ያማርር ነበር። ነገር ግን ዋናውን ግብ፣ ትልቁን የሕዝቡን ሕልምና የተቀበለውን አደራ፤ ለአንድም ቀን ቢሆን ዘንግቶት አያውቅም ነበር። እንደ ማንኛውም ትክክለኛ መሪ ለጊዜው እንደ ዛር የሰፈረበትን ጥርጣሬ፣ ተስፋ መቁረጥና ፈጣሪን ማማረር ወዲያ አሽቀንጥሮ ጥሎ በጽናት ወደ ትልቁ ሕልሙ ይመለሳል።

በተለመደ የአስተሳሰብ መንገድ በመጓዝ ከአዲስ አምባ መድረስ አይቻልም። በትናንት ዕውቀትና ታሪክ መታሰር ተቸክሎ መቆምን ሲከፋም ወደ ኋላ መንሸራተትን ያስከትላል። መንቀራፈፍን ያመጣል። ዕንቁላል ቅርፊቱን ሰብሮ በራሪ ወፍ የሚሆነው በትናንት ዕውቀት ባለመታሰሩ ነው ። በትናንት ዕውቀት የታሰረ ዕንቁላል ግፋ ቢል ተንፏቃቂ እንስሳ፣ አልያም የሌላው ስንቅ እንጂ በራሪ ወፍ ሊሆን የሚችልበት መንገድ አይኖርም። ለውጥ እንደ ውጤት የሚረጋገጠው በለውጥ ድርጊትና ሂደት በቻ ነው።

አዲስ ዓለም አዲስ እይታና አዲስ ጎዳናን ይሻል። ነባሩን ጎዳና ተከትሎ በመጓዝ እዚያው የጥንቱ ነባር መንደር እንጂ አዲስ ከተማ መድረስ አይቻልም። በትናንት ዕውቀት መታሰር የመሻሻልና የመስፈንጠር ዋነኛ ዕንቅፋት ነው። የዓለማችን ታላቁ ሳይንቲስት አልበርት አንስታይን በአንድ ወቅት እንደተናገረው ከዕውቀት ይልቅ ምናብ ይልቃል። በሌላ አገላለጽ ከነባር ውስብስብ ችግሮች ፈልቅቆ ለመውጣት ታላላቅ አስፈንጣሪ ሐሳቦችን ማመንጨት ያስፈልጋል። ያን መሰሎቹ ታላላቅ የለውጥ ሐሳቦች የሚመነጩት በትናንት ውስጥ ከችግሮቹ ጋር በተላመደና በታሰረ አእምሮ ሳይሆን አዳዲስ እሳቤዎችን ማፍለቅ በሚችሉ መሪዎች ብቻ ነው። ሀገራዊ የለውጥ ርምጃን ወደ ትክከለኛ ግብና ዓላማው የሚያደርስ ትክክለኛ መሪ የሚያስፈልገውም በዚህ የተነሣ ነው። በሀገር፣ በክልል፣ በተቋም፣ በፕሮጀክት እና በተሠማሩበት ሐላፊነት ሁሉ ሥራቸውን በትክክል መከወን የሚችሉ መሪዎችን መፍጠር ሀገራዊ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ተግባር ነው።

**ሦስተኛ - የለውጥ አስፈንጣሪዎች ሚና ፦** እነዚህ እንደራሴዎችና የሕዝቡ ክፋዮች የሆኑ በቁጥር ያልበዙ ራእዩንና ሕዝቡን የሚያገናኙ የሕልም ድልድዮችና ቁልፍ የለውጥ ሞተሮች ናቸው። እሺ ባይ ካድሬዎች ሳይሆኑ ማሰብ፣ መሞገትና ሐሳብ ማመንጨት የሚችሉ ተተኪና አጋዥ መሪዎች ናቸው። በተሰማሩበት መስክ በተግባር የተፈተኑ፣ ተግብረው የሚያሳዩና ለውጤት የሚተጉ ሰዎች በለውጡ ውስጥ የመሪውን ቅኝት ተከትለው ይተገብራሉ።

በተሾሙ በዓመታቸው በወንድም በእኅታቸው ስም መሬት አይይዙም፤ ቤት ኢያንጹም፤ መኪና አይገዙም። የለውጥ አስፈንጣሪዎች የሐሳብና የተግባር አምባሳደሮች ናቸው። ጉጉታቸውና የልባቸው መሻት ሹመትና ሥልጣን ሳይሆን፤ እንደ ቻይናዊው አዋጊ ቼን የሕይወት መሥዋዕትነትንም ቢሆን በመክፈል ብዙኃኑን ወደ ለውጡ መዳረሻ ማሻገር ነው።

ሀገራዊ ራእይንና ሕዝቡን የሚያገናኙ ብቸኛ የራእይ ድልድዮች ናቸውና ያለ እነርሱ ሕልሙ ሕልም፣ መሪውም

መሪ፣ ትግሉም ፍሬያማ ሊሆን አይችልም። አንዳንዴ በአላስፈላጊ የሕይወት ፉክክርና ውድድር ውስጥ በመግባት ከትክክለኛው መንገድ ወጥተን ለአላስፈላጊ ጥፋትና ጉዳት ስንጋለጥ እንስተዋላለን። በብዙ አጋጣሚዎች ተፈላጊውን ቁም ነገር ከአጫፋሪው ክሥተት አንጥሮ ያለመለየት ጣጣ ዛሬም እንደ ትናንት ሁሉ የሚጎበኛቸው ጓዶች ጥቂቶች አይደሉም። በመደመር እሳቤ ግን እውነታው ከዚያ የተለየ ምስል ያለው መሆኑን በሚከተለው ምሳሌ እንመልከት።

በአሜሪካ በሲያትል ግዛት የአካል ጉዳተኞች የኦሎምፒክ ውድድር ላይ ያጋጠመ አንድ ትዕይንት ነው። በአንድ የመቶ ሜትር የሩጫ ውድድር ላይ ተካፋይ ለመሆን ወደ መሮጫ መሥመሩ የቀረቡት ተወዳዳሪዎች ዘጠኝ አካል ጉዳተኞች ነበሩ። ውድድሩ እጅና እግርን ማጣት ብቻ ሳይሆን የአእምሮ ዕድገት ውሱኑነት ያለባቸውን ተወዳዳሪዎችንም ያካተተ ነበር። ስምንቱ ተወዳዳሪዎች ወንዶች ሲሆኑ አንዷ ግን ሴት ነበረች።

ዘጠኙ የውድድሩ ተካፋዮች 'ተዘጋጅ - ተጠንቀቅ ሩጥ' የሚለው ድምፅና አጃቢ ተኩሱ እስኪሰማ ድረስ በየመሥመሮቻቸው ላይ ቆመው ውድድሩን በስሜት ተሞልተው ይጠባበቁ ነበር። ከተመልካቹ ይቸራቸው የነበረው ድጋፍና ማበረታቻም ደማቅ ነበር። ውድድሩ ተጀመረ። ዘጠኙም የአካል ጉዳተኞች እንደየራሳቸው የጉዳት አግባብ ሩጫቸውን ጀመሩ። ግን ብዙም ሩጫው ሳይገፋ ከመካከላቸው አንዱ ተወዳዳሪና የእግር ጉዳት ያለበት ወጣት ሯጭ ሚዛኑን መጠበቅ አቅቶት ተደናቅፎ ወደቀ። ወደ ኋላ የቀሩትም ሆኑ ቀድመው የነበሩት ተወዳዳሪ አትሌቶች ጩኸቱን ሰምተው ሩጫቸውን ትተው ወደ ወጣቱ መጡ። ደግፈው ሊያነሡት ጥረት አደረጉ። የውድድሩ ተካፋይ የነበረችው ልጃገረድ ተንጠራርታ ሳይጠቅምህ አይቀርም ብላ ጉንጩ ላይ ሳመችው። ወጣቱም በድጋፋቸው ተበራትቶ ተነሣ።

ስምንቱ የአካል ጉዳተኞች ወጣቱን ከወደቀበት ደግፈው ካነሡት በኋላ ተመልሰው ወደ ውድድሩ ያመሩት እንደ መጀመሪያው ተለያይተው አልነበረም። ይልቁንም ዘጠኙም ክንዳቸውን እርስ በርስ በማቆላለፍ ወደ ጎን ተያይዘውና ተደጋግፈው ነበር። አካል ጉዳተኞቹ አትሌቶች በርምጃ የውድድሩን መግቢያ መሥመር በአንድነት በማለፍ ውድድራቸውን በድል አጠናቀቁ። በስታዲዮሙ ተገኝቶ የነበረው ታዳሚ በሙሉ ከመቀመጫው ተነሥቶ፣ ድጋፉን በሆታና ከዐሥር ደቂቃ በሚያልፍ ጭብጨባ ገለጸላቸው።

የመደመር የለውጥ አስፈንጣሪዎች አንድና ሁለት ጠንካሮችን ብቻ ሳይሆን ሁላችንንም የድል ባለቤት ማድረግ የሚያስችል ዐቅም ያላቸው አነቃናቂዎች ናቸው። እንደ አሜሪካውያኑ አትሌቶች ኢትዮጵያውያንም በትክክል ተፈላጊው ቁም ነገር ምን እንደሆነ በመረዳት ተግባራዊ ልናደርገውና ልናተርፍበት እንችላለን። የለውጥ አስፈንጣሪ የምንላቸው ለሁሉ ማሸነፍ ሲሉ ሁሉ ነገራቸውን መሥዋዕት የሚያደርጉ፣ እየመሩ የሚከተሉ፣ እየተከተሉ የሚመሩ፣ የለውጥ ከዋክብቶች ናቸው።

**አራተኛ የሕልሙ ባለቤት ብዙኃኑ ነው፡-** እንደ ሀገር ስናየው መሪዎችም ሆኑ የለውጥ አስፈንጣሪዎች ለዕድገቱ፣ ለብልጽግናውና ለሥልጣኔው አስፈጻሚዎች እንጂ ፈላጭ ቆራጭ ባለቤቶች አይደሉም። ዋናው ሞተርና ባለቤት ተርታው ብዙኃኑ ሕዝብ ነው። መሪው መርቶና የለውጥ አስፈንጣሪዎቹን አዝምቶ፣ ሕልሙ ከግብ እንዲደርስ ብዙኃኑ ሕዝብ የለውጡ ባለቤት መሆን አለባቸው። አፍአዊ ያልሆነ እውነተኛ ባለቤት።

የለውጡ መሪም ሆነ አስፈንጣሪዎቹ የብዙኃኑ አገልጋዮችና የሕልሙ አስፈጻሚዎች መሆናቸውን በትክክል የሚያውቅ ሕዝብ ያስፈልጋል።

በሲና በረሐ፣ በሮም ግዛቶች፣ በአውሮፓና በመካከለኛው ምሥራቅ ጫካዎች፣ በኢትዮጵያ ተራራሮችና ሸንተረሮች እንደታየው፣ ትልቅ ሕልም እንዲሳካ፣ ከመሪዎችና ከአስፈንጣሪዎቹ ጎን ቆሞ የሚዋጋ፣ ሲራቡ የሚመግብ፣ ሲታረዙ የሚያለብስ፣ ሲታመሙ የሚያክም፣ ሲወልዱ ልጆቹን የሚከባከብ፣ የሚያሳድግ፣ ሲጠቁ የሚደብቅ፣ ሲሞቱ የሚቀብር ደጀን ሕዝብ ያስፈልጋል።

‹ያለ ሕዝቡ ባለቤትነት ለውጡ በፍጹም ግቡን አይመታም!› ብሎ መደመር ያምናል። እንደ መደመር እሳቤ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የሕዝብን ባለቤትነትና አካታችነት ማረጋገጥ በሕገ መንግሥት ላይ ብቻ የተጻፈ አይደለም። መሪዎቹና የለውጡ አስፈንጣሪዎች በላቀ ደረጃ የሚያከብሩትና በፈቃድም የሚያገለግሉት ሕዝብ እስከ መፍጠር የሚዘረጋ ነው። መደመር ሕዝብ በሁሉም ደረጃ ያሉ መሪዎቹን በራሱ ፈቃድ መምረጥና መሻር የሚችልበትን ዴሞክራሲያዊ አሠራርና አደረጃጀት ፈጥሮ አያቆምም። የሕዝብን ትክክለኛ የሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤትነትም ያረጋግጣል።

## ለማጠቃለል ያህል ፦

- በአስከፊ ሁኔታ ለ430 ዓመታት በግብጽ በባርነት ከተገዛው፣ በሲና በረሐ ለዓመታት ከተቃጠለው፣ ሚሊዮኖች ወገኖቹ በናዚያውያን ከተጨፈጨፉበት የአይሁድ ሕዝብ ጋር፣
- መጀመሪያ በታላቁ ሽሽትና ውጊያ፣ ከዚያም ወጣቶች ባነደዱት የባህል አብዮት ብዙ ሚልዮን ዜጎቹን መሥዋዕት አድርጎ ከከፈለው የቻይና ሕዝብ ጋር፣
- ቀድሞ በባርነት ግዞት፣ ቀጥሎም በግፈኞች ቅኝ ገዥዎች ጭፍጨፋ ካለቁት አፍሪካውያን ወገኖቻችን ጋር ሲነጻጸር፣

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለምንም ማጋነን አሁን ከፊቱ ተደቅነዋል የሚባሉት ፈተናዎች ያን ያህል ወገብ አጉባጮች አይደሉም። ከድህነቱና የፖለቲካ ነጻነት ከማጣቱ ውጭ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሦስት ሺህ ዘመናት ለሚበልጥ ጊዜ፣ በአንጻራዊ ሥልጣኔ ውስጥ ነበር የቆየነው ማለት ይቻላል። በተለይም ዘመነ መሳፍንት ሳይደቁሰን በፊት ባሉት ዘመናት ዓለም ላይ የመንግሥት ተቋማት በተሻለ ከሚንቀሳቀሱባቸው የዓለም ሀገራት መካከል ከፊት ተሰላፊዎች ነበርን። በታሪካችን በሕዝብ ላይ ከፍተኛ መጎሳቆል የተከሠተባቸውን ጊዜያት ልብ ያልን እንደሆነ፤ በአብዛኛው ከእርስ በእርስ ግጭትና የየአካባቢ ገዢዎች የበላይ ለመሆን ከሚያደርጉት ሽኩቻ ጋር የተቆራኘ ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህ ባለፈ ዐልፎ ዐልፎ ድርቅና ቸነፈር ሀገራችንን የጎበኘባቸው ጊዜያት እና ለአምስት ዓመታት ከጣልያን ጋር እየተዋጋን ያሳለፍነው ጊዜ የጨለማ ጊዜ ነበር። የመጨረሻውም ቢሆን ከአፍሪካውያኑ የቅኝ ቀንበር ከእስራኤላውያኑ ባርነት እና በመርዝ ጋዝ መቃጠል፤ ከቻይናውያኑ ተደጋጋሚ መከራ ጋር ሲነጻጸር የነፃነት ዘመናችን ሚዛን የሚደፋ ነበር ለማለት ይቻላል።

እነዚህ ሁሉ ሕዝቦች ከነበሩበት ድቅድቅ ጨለማ ወጥተው ዛሬ ካሉበት እጅግ ከፍ ያለ የብርሃን ዘመን ላይ ደርሰዋል፣ ወይም ለመድረስ እየተንጠራሩ ነው። እኛ ይሄን ማድረግ የሚከለክለን ሊታለፍ የማይችል ምን

መሰናከል አለ? ሌሎች ማድረግ የቻሉትን ብቻ አይደለም፣ እነርሱ ከሠሩት በላይ ለመሥራት የማንችልበት ከቶ ምን ምክንያት ማቅረብ እንችላለን በለውጡ የመጀመሪያ ምዕራፍ ያረጋገጥናቸው ድሎች ከምንም በላይ ለዚህ ምስክር ይሆናሉ። ቢሆንም አሁንም ችግሮቻችን በርካታና ፋታ የማይሰጡ መሆናቸውን ፍጹም አንዘነጋም። ሀገራችን ምንም እንኳ ከፍተኛ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እመርታን ብታሳይም አሁንም በድህነት ከሚጠቀሱ የዓለም ሀገሮች አንዷ ነች። እነዚህን ውስብብስብና ፋታ የማይሰጡ ችግሮች ተለያይተንና ተከፋፍለን ቀርቶ፣ ተባብረንና ተዋደንም ለመፍታት ዘመናት ያስፈልጉናል።

ያን የመፍትሔ ዘመን ዛሬውኑ አንድ ብለን እንጀምረው። በመደመር እሳቤ በመመራት የጋራ ችግሮቻችንን በጋራ ለመፍታት ቆርጠን ከተነሣን ችግሮቻችን ሁሉ የአንድ ትውልድ ዕድሜ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከትከሻችን ላይ አሽቀንጥረን ማራገፍ እንችላለን። በዚህም ክፉው ዘመን ማለፉንና ሀገራችን ከአረንቋ ወጥታ በድል መቀጠሏን ለዓለም እናረጋግጣለን።

# ሰላማዊ ትግል

ሕዝብ ለለውጥ ከተነሳ የትኛውም ኃይል እንደማያቆመው የሀገራችንም ሆነ የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ አሳይቶናል። ሆኖም ለውጥ ውጤታማና ዘላቂ እንዲሆን ሰላማዊ የትግል ዘዴን መምረጥ አለበት። ትግሉ ከአምባገነን መሪዎች ብቻ ሳይሆን ከአምባገነንነት አስተሳሰብ ጭምር ለመላቀቅ የሚደረግ ሰላማዊ ትግል መሆን አለበት። እንኳን ሀገራዊ አምባገነኖችን ለማሽቀንጠር፤ ለክፍለ ዘመናት የነገሰባቸውን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ለማስወገድ፤ ማህተመ ጋንዲ ስኬታማ የሆነ ሰላማዊ የትግል ዘዴ ተከትሏል። እስከ ዛሬ አለን በምንለው የዘመናት ታሪካችን ሁሉንም ዓይነት የጥፋት መንገድ ሞክረናቸዋል። ጦርነትን ጨምሮ የጦርነት ልጆች የሆኑትን ስደት፣ መፈናቀል፣ በሽታ፣ ረሐብ፣ እርዛት፣ ሞት ተፈራርቀውብናል። አንዳንዶቹ መለያዎቻችን እስኪመስሉ ድረስ ለዘመናት አብረውን ከኛው ጋር ኖረዋል። እስከዛሬ ሁላችንም ከልባችን ያልሞከርነው የሰላሙን መንገድ ብቻ ነው። እንደ ዜጋ፣ የምንፈልገውን ትንሽም ይሁን ትልቅ ነገር፣ የሐሳብ ልዕልናን አንግበን፣ በሰላም ታግለን፣ አሸንፈን ልናገኘው እንችላለን ብለን አስበን አናውቅም።

ወላጆቻችንም ሰለማዊ ትግል እንደሚቻል አላስተማሩንም። ጨካኝነት በተለመደበት ሀገር በሐሳብ ታግሎ ማሸነፍ፤ በእሳት እንደ መጫወትና በራስ ላይ አደጋን እንደመጋበዝ ይታያል። አሁን ግን ይሄው ወጣ ገባነት ቢኖረውም ከመነሻችን የሁለት ዓመት ርቀት ተጉዘናል። በደስታ ተሞልተን እንዳሳለፍናቸው ጊዜዎች ሁሉ በርካታ ተስፋ አስቆራጭ ቀንና ሌሊቶችም ነበሩ። የጅግጀጋ፣ የሐዋሳ፣ የወልቂጤ፣ የቤኒሻንጉል፣ የቡራዩ፣ የቅማንት፣ የራያ፣ የምዕራብ ወለጋና የምስራቅ ሐረርጌ ግጭቶች ዛሬም ድረስ ትውስታቸው ልቤን በሐዘን ያደማዋል። በዚያው ልክ መንፈሴን ማንቃትና ልቤን ቀለል ማድረግ የቻሉ ትዕይንቶችም አልፈዋል።

በዓለማችን ጭካኔን አሸንፈው፤ አደጋውንም አልፈው፣ ክብርን የተቀዳጁ አያሌ ሰዎች አሉ። በአንጻሩ

በሀገራችን ሰላማዊ የትግል ሒደትን የተከተሉ ሰዎች ቁጥር እምብዛም ነው። እንደማርቲን ሉተር ኪንግ እና እንደ ማህተመ ጋንዲ በሰላማዊ ትግል ጎልተው የወጡ ሰዎች የሉንም ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል። ይህ ሲባል ግን ሰላማዊ ትግል አማራጭን የደፈሩ፤ አስቸጋሪ መንገዱን የተጋፈጡና ትግሉ ያስከተለባቸው መጎሳቆል ሰላማዊ አቋማቸውን ሳያስለውጣቸው ለረጅም ዘመናት በጽናት የታገሉ ኢትዮጵያውያን የሉም ማለት አይደለም። ከዚህ አንጻር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ከሰላማዊ ታጋዮቻችን መካከል ለየት ብለው ሊታዩ ይችላሉ።

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ አንጋፋ ታጋይ ናቸው። ዕድሜ ዘመናቸውን በፖለቲካ ትግል አልፈዋል። የሚከተሉትም የትግል ስልት ሰላማዊ ነው። ትግላቸውን ከጀመሩበት ጊዜ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት አንስቶ እስከዛሬ ድረስ በፖለቲካው ዘርፍ ሰላማዊ ትግል አማራጭን እንደያዙ ዘልቀዋል። ዘጠና ዓመታቸውን እስኪደፍኑ ድረስ ከሰላማዊ ትግላቸው ዝንፍ ሳይሉ እስከ እድሜያቸው ማክተሚያ ተጉዘዋል። እንደ ማንኛውም ታጋይ ታስረው፣ ተግዘውና ተደብድበው ብዙ መከራ ቢቀበሉም፤ ሁሉንም በድል አልፈው እስከመጨረሻው በክብር ቆመዋል። በእድሜ ገፍተውና በጉልበት ደክመው እንኳን፣ በመንፈስ እንደበረቱ እስከ እድሜ ማክተሚያቸው ሰዓት ድረስ ዘልቀዋል። እንደ ወጣት ዝሆን ለትግል ዝግጁ እንደሆኑ ዘጠና ዓመት እድሜያቸውን ተሻግረዋል። እስከ እለተ ሞታቸው ድረስ ዐመፅን እና የመሳሪያ ትግልን ሲጠየፉ ነበር። ከወጣቶች ቢበልጥ እንጂ በማያንስ መልኩ በየጋዜጣው ሲታገሉ፤ የተሳሳተውን ነቅሰው ሲተቹ ነበር። መንግስትን ለማስተካከል መሣሪያ ሳይሆን ብዕር አንስተው በሐሳብ ይፋለሙታል። ሕዝቡንም ሳይፋሩና ሳያፍሩ ጥፋትህን አርም ብለው ይሞግቱታል። ፊት አይተው ሳያዳሉ ግፍን እየተቃወሙ፤ ስህተት ውስጥ ያሉትን እያስተማሩና እየገሰፁ፤ በስድብና በማንጓጠጥ ሳይበገሩ ዘልቀዋል።

ዛሬም እንደ ትናንቱ ዐመፅን እና የመሣሪያ ትግልን ይጠየፋሉ። ዛሬም እንደ ትናንቱ ከወጣቶች ቢበልጥ እንጂ በማያንስ መልኩ በየጋዜጣው ይሞግታሉ፤ የተሳሳተውን ነቅሰው ይተቻሉ። መንግስትን ለማስተካከል መሣሪያ ሳይሆን ብዕር አንሥተው በሐሳብ ይፋለሙታል። ሕዝቡንም ሳይፋሩና ሳያፍሩ ጥፋትህን አርም ብለው ይሞግቱታል። ፊት አይተው ሳያዳሉ ግፍን እየተቃወሙ፤ ስህተት ውስጥ ያሉትን እያስተማሩና እየገሰፁ፤ በስድብና በማንጓጠጥ ሳይበገሩ ዘልቀዋል።

ፕሮፌሰር መስፍን በአሸናፊነታቸው እስከ እለተ ሞታቸው ከመዝለቃቸው እኩል የሚያስገርመው ነገር፤ በመቶ ሚሊዮን ወገኖቻቸው ውስጥ የእርሳቸውን የሰላማዊ ትግል ስልት የሚከተሉ ዐርበኞች በብዛት አለመፈጠራቸው ነው። እርሳቸው በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ላይ ያሳደሩትን ተጽዕኖ አይተን፤ እንደ እርሳቸው ብዙ ሰዎች ቢኖሩ ሊፈጠር የሚችለውን ዐቅም ስናስብ እውነተኛ ለውጥ ፈላጊዎችን ሁሉ ያንገበግባል። ብዙዎች እንደ እርሳቸው ሰላማዊ ትግር ይጀምሩና ወዲያውኑ ተማርረው ይተውታል፤ ወይም ወደ መሣሪያ ትግል ይዞራሉ።

በውጭው ዓለም ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ የሰላማዊ ትግል ዐርበኞች አሉ። እነዚህ የሰላማዊ ትግል አርበኞች ጠመንጃ ሳይሆን ሐሳብ አንግበው ለሰዎች መብት፤ ለእኩልነትና ለፍትህ በመታገል እያሌ ድሎችን በየሀገሩ

ሲያስመዘግቡና ደማቅ ታሪክ ሲጽፉ አይተናል።

በ1960ዎቹ በአሜሪካ ዴላኖ ካሊፎርኒያ ውስጥ በእርሻ ሥራ በተሰማሩ ድሆች ላይ ከፍተኛ በደል በአሰሪዎቹ ይፈፀም ነበር። የሰለማዊ ትግል ዐርበኛው ሴዛር ቻቬዝ፣ ከእርሻው የሚመረተውን ወይን አትግዙ፤ ብሎ ሕዝቡን ለአድማ ጠራ። ለ25 ቀናት የረሃብ አድማ አደረገ። እርሻው ላይ እጅግ ዝቅ ባለ ክፍያ የሚሠሩ ላብ አደሮች ደመወዝ እንዲጨመር፤ አምስት ዓመታት የፈጀ ከባድ የሥራ ማቆም አድማ አደራጀ። 17 ሚሊዮን አሜሪካውያን የቻቬዝን ጥሪ ሰምተው ከእርሻው የሚመረተውን ወይንና ሌላም ዓይነት ተክል መግዛት አቆሙ። የነቻቬዝ አድካሚ ትግል ለፍሬ በቃ። የእርሻ ሠራተኞችን መበዝበዝና መበደል የሚያስቀርን ሕግ ካሊፎርኒያ አፀደቀች። ታጋዩ ቻቬዝም ‹‹ከሁሉም እውነተኛው የጀግንነት ሥራ፤ ከሁሉም የላቀው ሰብአዊ ክንዋኔ፤ ለፍትሕ የሚደረግ ፍጹም ሰላማዊ ትግል፤ ራስን ለሌሎች አሳልፎ መስጠት ነው›› በማለት ደስታውን ገለጸ።

እኩልነትን በመስበክ ከአሜሪካውያኑ ከዋክብት ታጋዮች አንዷ የሆነችው ጥቁሯ ሮዛ ፓርከስ ተጠቃሽ ናት። የራሷን ድንቅ ታሪክ ለመሥራት ከመሰሎቿ ጋር መሰባሰብ ወይም ሚሊዮኖችን ለአድማ መጥራት አላስፈልጋትም። በተሳፈረችበት አውቶቡስ ውስጥ ‹ወንበርሽን ለነጭ ተሳፋሪ ልቀቂ› ስትባል ‹አሻፈረኝ› አለች። በዚህ ጦስ መታሰሯ የሕዝብን ቁጣ ቀሰቀሰ። ይሄ ድርጊቷ በአሜሪካ የጥቁሮች መብት እንዲከበር የተነሳውን ሀገር አቀፋዊ ሰላማዊ ትግል ያጫረ ክብሪት ነበር። ሮዛ በሞንትጎመሪ አላባማ ውስጥ ይሄን ድርጊት በፈፀመች በዓመቱ በ1956 (እኤአ) የአሜሪካ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሕዝብ አውቶቡሶች ውስጥ መንገደኞችን በዘር ከፋፍሎ ማስቀመጥ ‹ሕገ ወጥ ነው› ሲል ደነገገ።

የምግብ ዋጋ መጨመርን በመቃወምና ሌሎችንም የመብት ጥያቄዎችን በማንገብ፤ 17 ሺህ ሠራተኞችን አስተባብሮ አንድን የመርከብ ጣቢያ በኃይል የተቆጣጠረው፤ የፖላንድ ሠራተኞች መሪ ዋሌሳ ‹ሶሊዳሪቲ› የተሰኘውን ዝነኛ ማህበራቸውን የመሰረተው በ1980 ዓ.ም ነበር። ማህበሩ በተመሰረተ 15 ወራት ውስጥ ብቻ የሶሊዳሪቲ አባላት ቁጥር ከአንድ ሚሊዮን ወደ 9 ሚሊዮን አድጓል።

የሠራተኞቹና የማህበራቸውን ጥንካሬና ተሰሚነት ከፖላንድ አልፎ የምስራቁ ኮሙኒስት ዓለም ጌታ የነበረችውን ሩሲያን ማሳሰብ ሲጀምር፤ የፖላንዱ መሪ ጄኔራል ያሩዜልስኪ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሀገሪቱ አውጀው ሶሊዳሪትን በሕግ አፍርሰውታል። ከዚህም ባለፈ የሰላማዊ ንቅናቄ መሪው ሌህ ዋሌሳ አንድ ዓመት ገደማ ሲታሰር ተከታዮቹ ሰባት ዓመታት ታስረዋል።

ታጋዩ ዋሌሳና ተከታዮቹ ፖላንዳውያን ትግላቸውን በኅቡዕ ቀጠሉ። በወቅቱ ሰላማዊ ንቅናቄውን በሠራተኛው ትግል ብቻ ዳር ሊደርስ እንደማይችል የተረዱት መሪዎቹ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች፤ ከአርሶ አደሮችና ከምሁራን ጋር ተደምረው ንቅናቄውን ይበልጥ ሕዝባዊ አድርገውታል። ከዋና ዋናዎቹ ምዕራባዊ ሀገራት በተጨማሪ የዓለም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን መሪ የነበሩት ዳግማዊ ጆን ፖል ድጋፋቸውን ለንቅናቄው በመስጠታቸው ቀውሱ ተባብሶ ቀጠለ። ጀኔራል ያሩዜልስኪ ከሶሊዳሪቲ ጋር በይፋ ለመደራደር ተስማሙ።

በመጨረሻ ፖላንድን ከገባችበት የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ቀውስ ለማውጣት በዋሌሳ የሚመራው

ሶሊዳሪቲና በጄኔራሉ የሚመራው የፖላንድ መንግስት የአራት መቶ ገጽ ስምምነት ከተፈራረሙ በኋላ ሀገር አቀፍ ምርጫ በፖላንድ ተካሄደ።

በፖላንድ ብቻ ሳይሆን የኮሙኒስቱ ዓለም ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው በዚህ ታሪካዊ ምርጫ፤ በዋሌሳ የሚመራው ሶሊዳሪቲ ምርጫውን በማሸነፍ በኮሙኒስቱ ዓለም ውስጥ ኮሙኒስት ያልሆነ የመጀመሪያውን መንግስት መመስረት ቻለ። ከስድስት ወራት በኋላ ምስራቁንና ምዕራቡን ዓለም ለሠላሳ አመታት ገደማ ከፍሎ የቆየው የበርሊን ግንብ ፈረሰ። በ2018 (እኤአ) የኅዳር ወር መጀመሪያ ላይ በጀርመን በርሊን ባደረግኩት የሥራ ጉብኝት እንዳየሁት ያ የድንጋይ ግንብ እንደ ቀድሞ የመለያየት ወሰን መሆኑ ቀርቶ በቱሪስቶች የሚጎበኝ ቀርስ ሆኗል።

ወደ አገራችን ስንመለስ ኢትዮጵያዊቷን ጀግና ብርቱካን ሚደቅሳን እናገኛለን። የፖለቲካ ሕይወቷን በሙሉ ከዐመጽ ለራቀና ሰላማዊ ለሆነ የትግል ስልት ያበረከተች፤ በትጋት የታገለችና እስከ መጨረሻው በእምነቷ የጸናች ብርቱ ፖለቲከኛ ነች። ቆራጥነቷና ጽናቷ እንዲሁም ለእውነት ያላት ቦታ መራራ ጽዋን በተደጋጋሚ እስከ መጋት አድርሷታል። እውነት በመናገሯ ግፍ ደርሶባታል። ‹‹ቃሌ›› ብላ ጽፋ ቃሏን በግፍ ተነጥቃለች። ከፍትህ ደጅ ማንንም ሳትፈራ መዶሻዋን በግፈኞች አናት ላይ አሳርፋለች።

ዛሬ ከስደት መልስ ወደ ሀገሯ ገብታ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሊቀ መንበር እንድትሆን ስትታጭ፤ ዓላማው ለቀጣይ ጉዞ ምቹ መደላደል መፍጠር ብቻ ሳይሆን በባህላችን ውስጥ ጀግንነት ከሰላማዊ ትግልና ከአዲስ ኢትዮጵያ አርበኝነት ጋር የማስተዋወቅ እርምጃ ጭምር ነው።

ኢትዮጵያ ወደ ብልጽግናና ነጻነት እንድትገሰግሥ ብዙ መስፍን ወልደ ማርያሞችና አያሌ ብርቱካን ሚደቅሳዎች ያስፈልጓታል። ኢትዮጵያ ሀገራችን እውነተኛውን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዘርግታ በስሟ ሳይሆን በሥራዋና በስልጣኔዋ እንድትኮራ ብዙ ሮዛ ፓርክሶችንና በርካታ ሌህ ዋሌሳዎችን በብርቱ ትሻለች። ነገ ሳይሆን ዛሬ። በኋላ ሳይሆን አሁን።

በትልቁ ምስል ውስጥ በትልልቅ ጉዳዮች ዙሪያ በጋራ መታገልን በመተው፤ በአናሳ ጉዳዮች መካረር የእውነተኛ ተራማጅነት ዘውድ ማስደፋት በጀመረበት በ1960ዎቹ ዘመን ብዙኃኑ አብዮተኛ ከሚነጉድበት ፈንጠር ብሎ በመውጣት ‹አብዮተኛ ሽብርን› በማውገዙ ኃይሌ ፊዳ ለሰከነ ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል እንደ አንድ ምሳሌ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። ኃይሌ የፖለቲካ ግብን ለማሳካት አውሮፕላን መጥለፍ ‹አብዮታዊ ጀግና› በሚያስብልበት በዚያ ዘመን፤ ለሽብር የሚውለው ቆራጥነት ጭቁኑን ሕዝብን በትዕግስት ለማስተማርና አንቅቶ ለማደራጀት ቢውል ብሎ ለሰከነ ፖለቲካ ሞግቷል። የኤርትራ ጉዳይ ከጦርነት ይልቅ ሰላማዊ እልባት የሚያገኝባቸውን መንገዶች ጠቁሟል። የጭቁን ብሔሮች ጥያቄ በአድማስ ጠበብ አደረጃጀት በመገንጠል ሳይሆን፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የእኩልነት ጥያቄ ወንድማማችነትን መሰረት በሚያደርግ እውነተኛ ዴሞክራሲ እንደሚመለስ በመግለጽ ለዚህ አቋሙ እስከ ሞት ድረስ ታግሏል።

ከምዕራብ ወለጋ ቦጂ የተገኙት ቄስ ጉዲና ቱምሳ ሌላኛው የሀገራችን ሰላማዊ የፍትህ አርበኛ የነበሩ ሰው

ናቸው፡፡ ቄስ ጉዲና፤ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የሃይማኖት አባቶች ሁሌም መቆም ያለባቸው ፍትህ ከተጓደለባቸውና ከተገፉት ጎን እንደሆነ በማቀንቀን ይታወቃሉ፡፡ የሰው ልጆች ሁሉ ከጭቆና እንዲወጡ በሚደረገው ትግል ውስጥ የቤተ አምልኮዎች ሚና እከሌ ከእከሌ ሳይሉ የዜጎች ሰብአዊ መብት እንዲጠበቅ፤ የሕግ የበላይነት እንዲከበር እና ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴዎች እየጎለበቱ እንዲመጡ መሆን አለበት ባይ ናቸው፡፡ ጥቂቶች ብቻ ነጻ ወጥተው ፍትሕ ሊሰፍን እንደማይችል በማመን ቄስ ጉዲና ስለመላው የሰው ልጆች ነጻነት ታግለዋል፡፡ ንጉሠ ነገሥቱን በአምልኮ ማወደስ ግዴታ በነበረበት በዚያ ዘመን ኢፍትሐዊነትን ተቃውመው የግፉዓን ድምጽ ነበሩ፡፡ ከኢትዮጵያም አልፎ በአፍሪካ ተንሰራፍቶ የነበረውን ጭቆና ተቃውመው ስለሰው ልጆች እኩልነትና ስለ ማኅበራዊ ፍትሕ ሰብከዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነቷ ከሞት በኋላ ስላለው ዓለም ብቻ ሳይሆ ክርስቲያኑም፤ ክርስቲያን ያልሆነው የሰው ልጅ እየኖረው ስላለው ኢፍትሐዊ ዓለም መሻሻልም ጭምር ሚና ሊኖራት ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የክርስቲያኖች ህብረትና መሰብሰብ ለሀገራዊ አንድነት የሚኖረውን ፋይዳ በመረዳት ለክርስቲያኖች ህብረት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ለፍትሕ የሚታገል ክርስቲያን ለግላዊ ጀብደኝነት ከንቱ ሰማዕትነትን ከመሻት ተቆጥቦ፤ ሰላማዊ የትግል መስመር እንደሚከተል በተለያዩ መድረኮች ከመናገርና ከመጻፍ አልቦዘኑም፡፡ ይህ አቋማቸው እየቆየ ሲሄድ መዘዝ ይዞ መምጣቱ አልቀረም፤ በተለይም በደርግ ዘመን ተደጋጋሚ እስርና እንግልት የገጠማቸው ሲሆን፤ በመጨረሻ እዚያው በእስር ቤት እያሉ እንዲከተል ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ያለን እውነተኛ የማሸነፊያ አማራጭ የሰላም መንገድ ብቻ ነው፡፡ ከሰላምና ከሰላማዊ ትግል ውጭ ሌላ ማሰብ ክስረትም መሸነፍም ነው፡፡ እስከ ዛሬ በዐመጽ ለሞከርነው አውዳሚ የማሸነፍ ጥረት ሊለካ የማይችል ኪሳራ ደርሶብናል፡፡ ያለ ጦር መሣሪያ በሐሳባቸው ጉልበትና በስብዕናቸው ውበት ብቻ ብርቱውን ጦር አንበርክከው የሕዝብን ሕይወት መለወጥ የሚችሉ ጋንዲዎችን መፍጠር ጊዜ የምንሰጠው ወይም አማራጭ የምንፈልግለት ጉዳይ አይደለም፡፡

ታሪካችን ከውጭና ከውስጥ ጦርነቶች ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ አብዛኞቹ ጦርነቶች ተገደን የገባንባቸው ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ለሀገርና ለነጻነት መሰዋት ክብር ቢሆንም፤ በጦርነት መኖር ግን በሕዝብ አስተሳሰብና አኗኗር ላይ የሚፈጥረው ጫና ልክ የለውም፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ማሸነፍን ከውጊያ፤ ጀግንነትንም ከመግደል ጋር ያቆራኘና የጦርነት አባዜ የተጠናወተው ሕዝባዊ አስተሳሰብን ይፈጥራል፡፡ የፓርቲ ፖለቲካችን በዚህ የጦርነት ባህል በመቃኘቱ ከ‹ጠላትና ወዳጅ› ትርክት ሊላቀቅ አልቻለም፡፡ ያለ ጠላት የማይንቀሳቀስ ፖለቲካ እንዲኖረን አድርጓል፡፡ የሰላማዊ ትግል ባህል እጥረትም ከዚሁ ይመነጫል፡፡

‹መግደል መሸነፍ ነው› የምንለው ያለምክንያት አይደለም፡፡ መግደል ፍትህ መስጠት አይሆንም፡፡ ብልፅግናና ድል በመግደልና በመጋደል የሚገኝ ቢሆን የት በደረስን፡፡ የጥንቱ ዘመን ቀርቶ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት በፖለቲከኞችና በሐሳብ መሪዎች ግፊት ምክንያት ሕዝባችን እርስ በእርሱ ሲቆራረስ ነበር፤ የፖለቲከኞቻችን ሆድ አልሞላ እያለ ዜጋችን ወገን ለወገን ተዳምቷል፤ ሞቷል፡፡ የባሌ ገበሬ ዐመፅ፤ የጎጃም ገበሬ ዐመፅ፤

የሐዲያ ገበሬ ዐመፅ፤ ጀብሐ፤ ሻዕቢያ፤ ኦነግ፤ ኦብነግ፤ ኢድሕ፤ ኢሕአፓ፤ ሕወሓት፤ መኢሶን የሸኩቻ ሙከራዎቻችን መገለጫዎቻችን ናቸው። በ1953፤ በ1966፤ በ1981፤ በ1983 ዓ.ም ሞክረነዋል። ከጭንቅ አልወጣንም። በ1983 ዓ.ም ላይ እንደ ዩጎዝላቪያ እንሆን ይሆን ብለን ስንጨነቅ ነበር። ይሄው ዛሬም ከሩብ ክፍለ ዘመን በኋላ ከዚህ ጥያቄ የጭንቀት ምጥ ሙሉ በሙሉ አልተላቀቅንም።

በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ የትኛውም ፖለቲካዊ ፍጥጫ በማናቸውም መንገድ ሲቋጭ አሸናፊና ተሸናፊ ይኖራል። አሸናፊና ተሸናፊ ሳይኖር ግብግቡ ሊደመደም አይችልም። በግብግቡ ውስጥ ገዳይና ሟች ይኖራል። ከግብግቡ በፊትም ሆነ ከግብግቡ በኋላ አሳዳጅና ተሰዳጅ ይኖራሉ። ትግሉ ምንጊዜም አሸናፊና ተሸናፊ፤ አሳዳጅና ተሳዳጅ፤ ገዳይና ሟች ያለበት በመሆኑ ትግሉ ውስጥ የሚገባ የትኛውም ኃይል የቀንም ሆነ የማታ ህልሙ ማሸነፍ፤ መግደልና ማሳደድ ከመሆን ሊያልፍ አይችልም። መግደልና  ማሸነፍ የሚቻለው በዐመፅና በመሣሪያ ብቻ ነው። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ሳይተኩሱ፤ ሳይገድሉና ሳያሳድዱ ማሸነፍ አይቻልም። ከዘመነ ነገስታት ወደ ዘመነ መሳፍንት፤ ከዘመነ መሳፍንት አሁን እስከ አለንበት ዘመነ ፓርቲ የደረስነውም ያንኑ መንገድ ተከትለን ነው። በኢትዮጵያ የተካሄዱ የለውጥ ጅምሮች ሁሉ በዐመፅ ተጀምረው በማሸነፍና በመሸነፍ፤ በማሳደድና በመሰደድ ስለሚለመደው የሌላ ዙር ውጊያና ዐመፅ መጀመሪያ ይሆናሉ።

ማሳደድና መሰደድ፣ መግደልና መሞት ሳይኖር በሁለቱም ጎራ ያሉ ኃይሎce አሸናፊ የሚሆኑበትን የፖለቲካ ባህል እኛ ኢትዮጵያውያን አይተነውም ሞክረነውም አናውቅም። ማየትና መሞከር ይቅርና ሳይገድሉና ሳይሞቱ፣ ሳያሳድዱና ሳይሰደዱ ሁለቱንም ጎራ አሸናፊ የሚያደርግ የትግል መንገድ መኖሩን በእሳቤ ደረጃ እንኳን ለመቀበል ዝግጁነቱ የነበረን ሕዝቦች አልነበርንም።

በሁላችንም እንደሚታወቀው እስከ ዛሬ የነበረው የፖለቲካ ባህላችን ለመሣሪያ ትግልና ለዐመፅ እንጂ ለሐሳብ ትግል ክብር የሚሰጥ አልነበረም። ጦር አዝምቶና ሀገር ወርሮ ሕዝብን ስለማሸነፍ እንጂ የሕዝብን ልብ ስለማሸነፍ አይጨነቅም። የፖለቲካ ግብግቡ ውስጥ ገዳይና ሟች፣ አሸናፊና ተሸናፊ በግድ ስለሚኖር ከሐዲና ታማኝ፣ ፈሪና ጀግና፣ እኛና እነርሱ መኖራቸውም እንዲሁ የግድ ነው።

ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም በግለ ታሪካቸው ላይ እንዲህ ይላሉ፤ ‹‹በታሪካችን ውስጥ ጎልቶ የሚታየው እርስ በርስ መጠቃቃትና መዘራረፍ ነው። ለሥራና ለሰላም ሕዝብ ፋታ ያገኘበት ጊዜ በጣም ጥቂት ነው። ሰላም ወዳዶቹም ንጉሦች በጣም ጥቂቶች ናቸው። ሕዝቡ ኑሮውን እንዲያሻሽል በሥራ፣ በጥረት፣ ንብረትና ሀብት አበጅቶ እንዲበለጽግና ትዳሩን እንዲያሣምር አልረዱትም። ጦርነትና ዝርፊያን ዋና ተግባር አድርገው ይኖሩ ነበር። ሕዝቡንም ሠርቶ ከመበልጸግ መንጠቅንና መዝረፍን፣ ከመተባበርና ከመግባባት ይልቅ መጨቃጨቅና መሟገትን መጠላላትን አስለምደውት በዚሁ ኖሯል።››

በኋላ ቀር የፖለቲካ ባህል የተተበተበ መሪ ባላንጣውን ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ማዋረድም ጭምር ይፈልጋል። ባላንጣውን ካላዋረደው ያሸነፈው አይመስለውም። ጠላትን ማዋረድ ብቻ ሳይሆን ዕድሜ ልክ በውርደት ውስጥ እንዲኖር ማድረግ የአሸናፊና ተሸናፊ የፖለቲካ ባህል መለያ መታወቂያ ነው። ገዳይነትህ ወይም ገዳይነትሽ እስከታየና እስከተመሰከረ ድረስ ምንም ዋጋ ቢከፈል፣ ማንም ምንም ቢሆን ችግር አይኖረውም።

አሸናፊነታቸው ይታመን እንጂ የሕንጻ መዓት ተደርምሶ በምድረ በዳ ቢተካ አቶ ገዳይ፣ አቶ አሸናፊ የሚጨነቁበት ጉዳይ አይሆንም።

በዚህ የፖለቲካ ባህል ውስጥ 'እኔ' እንጂ 'ሀገሬ' የለም። ዛሬ እንጂ ነገ የለም። ትናንት እንጂ ወደፊት የለም። ሁሉ ነገር ጊዜያዊ ነው። በመግደል፣ በማሸነፍ፣ በማሳደድና በማዋረድ ላይ ያነጣጠረ የፖለቲካ ባህል ስለአሁንና ስለዛሬ እንጂ ስለነገና ስለ ሕዝቦች የወደፊት ዕጣ ፈንታ ማሰብ ቢሳነው የሚገርም አይሆንም። ፊታውራሪ እንዲህ ይላሉ፤ ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ መገንባት አይሆንለትም። ማፍረስና እርስ በርስ መፋጀትን ልማድ አድርጎታል። ሐሳብ በሐሳብ ላይ እየቀጠለ በሥራ በመተርጎም ወደፊት መራመድ አይሆንለትም። ኢትዮጵያውያን ከመተባበርና ከመግባባት ይልቅ መቀናናትና መመቀኛኘት ያጠቃናል።»

# ትግልና ወጣትነት

በወጣትነት ውስጥ ነጻነትና መሻት አለ። ነጻነት ማለት ለጭቆናና ለሽንፈት፣ ለረኃብና ለእርዛት፣ ለአረጀ አስተሳሰብና በዐጽሙ ለቀረ ሥርዓት እምቢ አልገዛም ባይነትን ያካትታል። ወጣትነት ከውስጡ በሚወጣው አፍላ ጉልበትና ትኩስ ኃይል ነጻነቱን ከሚገታና ከሚያፍንበት ነገር ሁሉ በእምቢ ባይነት ጥሎና ገርስሶ “የመውጣት ማንነት መገለጫ ዕድሜ ነው። በሀገር ውስጥ አድልዎ የሰፈነበት ሥርዓት ሲፈጠር፣ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ሳይኖር ሲቀር፣ የዜጎች ሰብአዊ መብትና እኩልነት ሲሸረሸር ከየትኛውም የኅብረተሰብ ክፍል ቀድሞ አሻፈረኝ! እምቢ! ማለት የወጣትነት ተፈጥሯዊ ባሕርይ ነው። ይህንን የነጻነትና የእምቢ ባይነት ኃይል እንደተቀጣጣይ እሳት የሚያንበለብለው ደግሞ በወጣቱ ውስጥ ያለው ወሰን የሌለው ተነሣሽነትና ሆኖ የመገኘት መሻት ነው።

ዛሬ የሚነገር ታሪክ ያላቸው አዛውንቶች የታሪካቸው መሠረት በዋናነት የወጣትነት ዘመናቸው እምቢ ባይነት የወለደው ተግባራቸው ነው። ስማቸው በታሪክ ማኅደር ደምቆ የተጻፈው ባሮ ቱምሳ፣ ጥላሁን ግዛው፣ ማሞ መዘምር፣ ማርታ መብራህቱ፣ ታደለች ኪዳነ ማርያምና ኃይሌ ፊዳ በዐፄውና በአብዮቱ ዘመን በሶሻሊዝም ሐሳብ የነደዱ እምቢ ባይ ወጣቶች ነበሩ። ብርሃነ መስቀል ረዳ፣ ነገደ ጎበዜ፣ ፍቅሬ መርዕድ፣ ሠናይ ልኬ፣ እንድርያስ እሸቴ፣ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም፣ ጌታቸው ማሩ፣ ዶክተር ይርጋ፣ ፕሮፌሰር መረራ ጉዲና፣ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ አቤ ጉበኛና በዓሉ ግርማ ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር፤ የዘመናቸው ፋና ወጊና እምቢ ባይ ወጣቶች መሆናቸው ነው። መለስ ዜናዊና ጓደኞቹም ከትምህርት ቤት ወደ ጫካ ሲገቡ እምቢተኛ ሆነው ነው። የያኔዎቹ ወጣቶች የልጅነት የእምቢታ ገድላቸውን በስተርጅናቸው ዘመን ላይ ታሪክ ብለው ያወጉናል።

በሌላ በኩል ሙሉ ጊዜያቸውን በዳንኪራና በጭፈራ፣ በእሽኮለሌና በአልባሌ የሚያሳልፉ ወጣቶች በዚህ ውስጥ ዕጣና ዕድል ፈንታ የላቸውም። እንዲህ ያሉት ወጣቶች የልጅነት ትዝታ ባያጡም የደመቀ ታሪክና የለውጥ አሻራቸውን የጣሉበት እዚህ ግባ የሚባል የእምቢታ ታሪክ ግን አይኖራቸውም። ቢኖራቸውም የአልሞት ባይ እንትን በኛ ጊዜ ቀረ' ዓይነት፤ ለትውልድና ለሀገር እዚህ ግባ የሚባል አስተዋጽዖ የሌለው የባከነ ወጣትነት የፀፀት ድምፀት ብቻ ነው።

‹ወጣትነት› እምቢ ባይነትን ብቻ ሳይሆን ለአዳዲስ አስተሳሰቦች የተከፈተ ልብንም ያጎናጽፋል። አዳዲስ ርእዮቶች፣ አሠራሮች፣ አደረጃጀቶች፣ እንቅስቃሴዎችና ያልተለመዱ ነገሮች ወጣቱን ይስቡታል። የወጣት ነፍስ በእምቢተኝነትና ሌላ አዲስ ነገር የመሻት ቅይጥ ፍላጎት በፈጠሩት አንዳች ምትሐታዊ ስበት የተጠመደች ናት። የትም ሀገር ብትሄድ ቀመሩ አንድ ነው። ፊደል ካስትሮ ብትል ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ቼ ጉቬራ ቢሆን ማልኮልም ኤክስ፣ ማኦ ሴቱንግንና ኔልሰን ማንዴላን ጨምሮ ‹ወጣትነት› በአብዮትና በለውጥ እንቅስቃሴ፣ በእምቢ ባይነትና አዳዲሱን በመሻት የተሞላ፣ ቁም ነገር የመከወኛ ዕድልን የተሸከመ የእምቅ ዐቅም ሙላት ወቅት ነው።

ወጣትነት የዘመን ግለት ነው። ግለቱ ደግሞ ለውጥ ይዞ ይመጣል። ይሄን ያልተረዱ ጥቂቶች የግለት ሂደቱን ‹ሊገድቡት› ይሞክራሉ። ሆኖም በማዘግየት ይበልጥ ያግሉት ይሆናል እንጂ እስከ መጨረሻው አይገድቡትም። ሂ‹ደቱ የት እንደሚያደርስ ጉድ እናያለን› በማለት ሊያጣጥሉት የሚሞክሩ የድሮ ወጣት የዘንድሮ ሽማግሌዎች መኖራቸው አይቀርም። የወጣትን ትኩስ ልብ የሚገራ ጠቢብ የሽማግሌ ልብ ካልተገኘ፣ ወጣት እሳት ሽማግሌ የደረቀ እንጨት፣ ወይም ደግሞ ወጣት የነበር ጣት እርጅናም የደካማ ሚዳቋ ሰውነት መሆናቸው አይቀርም። አብዮትም ይሄን ማየት ካልሆነ ምንድን ነው?

በተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት ወላጆች ልጆቻቸው የሚያደርጉትን እየተመለከቱ ‹እነዚህ ልጆች ምን መዓት ይዘውብን መጡ› እያሉ ያጣጥሏቸውና ይገሥጿቸው ነበር። ‹ልጅ ይሮጣል እንጂ አባቱን አይቀድምም ማለት› ይቀናቸው ነበር። ታዲያ እነዚሁ ልጆች የተባሉት ወጣቶች የተማሪ እንቅስቃሴ አውራዎች በመሆን በየአካባቢው እየተዘዋወሩ ያልነቃውን ሌላ ወጣት እያነቁ፣ ለወጣት የቀረበ ልብ ያለውን ጎልማሳ እያጀገኑ ሊገታ የማይቻል ማዕበል ፈጥረዋል። በፈጣሪ መልክ የሚታየውንና የሚፈራውን ንጉሠ ነገሥታዊ ሥርዓት ከነአይነኬ ማኅበረሰባዊ ትውፊቱ ጠቅልለው በመገርሰስ፤ የሀገርንና የሕዝብን የወደፊት መንገድ መቀየስ ችለዋል። እንደ አላዋቂ የቆጠሯቸውን ሁሉ ዕጣ ፈንታቸውን በመወሰን፣ በዓይነቱ አዲስ የሆነ አብዮትን አቀጣጥለዋል።

በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚዘጋጀው "አፍሪካ" መጽሔት በቁጥር 39 ዕትሙ ላይ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተደረጉ ተቃውሞዎችን፤ "በአፍሪካ ውስጥ በደሎች በመቃወም የኢትዮጵያ ተማሪዎችን የሚወዳደር አይገኝም" በማለት ነበር የዘገባቸው:: ይህ ዓይነቱ ዘገባ በዚያ ዘመን ለነበሩት ወጣቶች ብቻ ሳይሆን፣ አሁን በዚህ ዘመን ላሉት ወጣቶችም ይሠራል። ወጣትነት የእምቅ ኃይል፣ የአሸናፊነት፣ የአዲስነትና የ ተስፋነት ምልክት ነው። ወጣትነት ትልቅ የእችላለሁ ባይነት እምነትን ያዘለ ጉጉነትና ድፍረት ነው። ሞትን ፊት ለፊት እስከ መጋፈጥ የሚደርስ ድፍረት። ወጣትነት ተፈጥሮ በራስዋ መንገድ አሮጌውን አስወግዳ በአዲስ ኃይል የመተካት መርሕ እንዳላት ጠቋሚና ለውጥ የተፈጥሮ ሕግ እንደሆነ ትልቁ ማሳያ ነው።

ወጣትነት መልካሙን ጠብቆ መጥፎውን አርቆ፣ ያረጀውን ለማደስ የማይጠቅመውን ለማፍረስ የተሰጠ ጸጋ ነው። የሰውን ልጅ ከሌላው ፍጡር የሚለየው አንዱ ምሥጢር አዝጋሚውን የተፈጥሮ ሂደት ሳይጠብቅ፤ በራሱ ዘዴና ብልሐት፣ ለፈቀደው ዓላማ፣ በሚያመቸው መንገድና በፈለገው ጊዜ፣ የለውጥ መሪና ኃይል ለመሆን መቻሉ ነው። በሀገራችን የተነሡ ለውጦችን ሁሉ በማቀጣጠልና በመምራት ረገድ ወጣቱ ሚናው

የላቀና ግንባር ቀደም ነው። የትናንቱንም ሆነ ዛሬ የምናየውን ለውጥ ለማምጣት ታላቁን ዋጋና የሕይወት መሥዋዕትነት የከፈለውም ወጣቱ ነው።

የወጣቶችን ሚና በሁለት ከፍለን ማየት አለብን። ወጣት የለውጥ መንገድ ቀያሽ አልያም ቀልባሽ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አሁን ያለውን ለውጥ ብንመለከት፣ የለውጡ ዋነኛ ሞተሮቹ ወጣቶች ናቸው። ኢትዮጵያ ዛሬ ያለችበት ደረጃ ላይ እንድትገኝ ቁልፉን ሚና የተጫወቱት ዋነኛ ኃይሎች ወጣቶች ናቸው። በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች ሀገሮች የሚካሄዱ ለውጦች በቀላሉ የተከናወኑ ወይም የሚከናወኑ አይደሉም። ውስጡ ፍጭት አለው። አንዱ ገመዱን ወደ አንድ አቅጣጫ ሲስብ፣ ሌላው ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ይጎትታል። አንደኛው ለሌላኛው ተግዳሮት ይሆናል።

ለውጡን በመቀስቀስም ሆነ ከዳር ዳር በማድረስ የወጣቱ ሚና ቁልፍ እንደሆነ ሁሉ ለውጥን በመገዳደር ረገድም የወጣቶች ሚና ተመሳሳይ ይሆናል። በወጣቶች ግፊት የተጀመረ የሽግግር ሂደት መልሶ በወጣቶች ዕንቅፋትነት ሊደናቀፍም ይችላል። እስከነ አካቴው ባይጨነግፍም የለውጡ ፍጥነት እንዲቀንስ የወጣቶች ሚና ጉልህ ሊሆን ይችላል። ያ ብቻ አይደለም። የዛሬውም፣ የነገውም፣ የወደፊቱም የሀገር ዕጣ ፈንታ መልሶ የሚወድቀው እስካሁን ባወራንለት ወጣቱ ኃይል ላይ በመሆኑ ሁልጊዜም ይሄንን ኃይል በጥንቃቄና በብልሐት ማስተናገድ ይሻል። የመሪዎች ሚና የሚመጣው እዚህ ጋ ነው።

ወጣትነት ነጻነት ይመጥነናል፤ ይገባናልም፤ ብለው እሳት ከታጠቀ ሠራዊት ፊት የተጋፈጡትን እልፍ ቄሮና ፋኖዎችን ይመስላል። ወጣትነት ሚልዮኖች ለእሬቻ በታደሙበት አደባባይ ከተቀባበለ ክላሽ፣ ካፈጠጠ ወታደር፣ ዓይኑ እሳት ከሚተፋ ባለ ሥልጣን፣ ከተወደረ የሚድያ ካሜራ ፊት "ዳውን ዳውን ወያኔ" ለማለት የጀገነውንና ትግሉን ያቀጣጠለውን ገመዳ ዋሪኦን ይመስላል።

በሰው ልጅ የሕይወት ዘመን ውስጥ ወርቃማው የዕድሜ ክልል ወጣትነት ነው ይባላል። እውነት ነው፤ ወጣትነት ወርቃማ ዕድሜ ነው። ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንደ ወርቅ ቀልጠው አዲስ መልክ፣ አዲስ ቅርጽ የሚይዙበት ወቅት ቢኖር ‹ወጣትነት› ነው። ታላቁ የሀገራችን ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔር ትኩሳት በተሰኘው መጽሐፉ ‹‹ጥሩ ነው ወጣት መሆን። ገንዘብ ባይኖርህም ጤና ይኖርሃል፤ መልክ ባይኖርህም አንጎል ይኖርሃል፤ ደስታ ባይኖርህም ንዴት ይኖርሃል፤ ፍቅር ባይኖርህም ጉራ ይኖርሃል፣ ሰው ባያውቅህም ቅሉ ታሪክ ይኖርሃል፤ ወጣት ነህና›› እንዲል ወጣትነት በብዙ መልኩ ጸጋው ይበዛል።

በኢትዮጵያ የለውጥ ታሪክ ውስጥ በርግጥም የወጣቱን ያህል ሚና የተጫወተ የኅብረተሰብ ክፍል አልነበረም። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጉልህ ቦታ የያዘ የወጣቶች ትግል ነው። ለረጅም ጊዜ በሕዝብ ጫንቃ ላይ የመኖር ዋስትና የሆነውን የመሬት ባለቤትነትና ተጠቃሚነትን ነጥቆ፣ ዜጎችን ለድህነትና ለኋላ ቀርነት የዳረገውን የፊውዳል ሥርዓት ‹‹መሬት ለአራሹ» በሚል መፈክር የታገለው ወጣቱ ነው። የብሔራዊ ማንነትና የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን በማንሣት የታገለው ወጣቱ ነው። የዐፄውን ፊውዳላዊ ሥርዓት በአደባባይ በመሞገት የ1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ ለውጥ እንዲቀጣጠል ዐቢይ አስተዋጽዖ ያደረገው ወጣቱ ነው።

የወጣቶችን እንቅስቃሴ በመጥለፍ ወታደራዊው መንግሥት ሥልጣን ላይ ፊጥ ቢልም ወጣቱ ግንባር ቀደም ታጋይ ነበር። የዚህን ቡድን አዝማሚያ አይተው መጀመሪያ የተቃወሙትም ወጣቶች ናቸው። በማይገባው መንበር ላይ ተፈናጥጦ በአምባገነንነት 17 ዓመታት የዘለቀው ወታደራዊው የደርግ ሥርዓት ከመነሻው እስከ ፍጻሜው ተቃውሞ የገጠመው በወጣቱ ነው። የኢሕአፓ፣ የመኢሶን፣ የኦነግ፣ የወዝ ሊግ፣ ወዘተ አባሎቻቸውና አብዛኞቹ አመራሮች በወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኙ ነበር። እነ ጌታቸው ማሩ፣ ማርታ መብራህቱ፣ ብርሃነ መስቀል ረዳና ኃይሌ ፊዳ የዚያ ዘመን ወጣቶች መሪዎች ነበሩ። ደርግ በመሣሪያ ኃይል ተገፍቶ ሊወድቅ የቻለውም በዋነኝነት በኢሕአዴግ እና በሌሎችም ብሔራዊ የነጻነት ድርጅቶች ውስጥ በነበሩ ወጣት ታጋዮችና መሪዎች ነበር።

እንደ ቀደመው ትውልድ ሁሉ የዚህ ትውልድ ወጣቶችም ለድል የበቁት ታላቅ መሥዕዋትነት በመክፈል ነው። ወጣቶች በድፍረትና በልበ ሙሉነት አምባገነኖችን ከመፋለም ወደኋላ አይሉም። ይህ ብቻ ሳይሆን ዘመኑ የሚጠይቀውን የፖለቲካ ሀልዮትና የትግል ስልት በሚገባ አጥንተው ኃይልና ጥበብን ገንዘብ አድርገዋል። ያ ትውልድ በወቅቱ ገንኖ የነበረውን የኮሙኒስት ርእዮተ ዓለምና ኃይል የተቀላቀለበትን የትግል ስትራቴጂ በጥልቀት የተረዳና የተገበረ / ነበር። የአሁኑ ትውልድም ዘመኑ የሚጠይቀውን ሰላማዊ የትግል ፍልስፍናና ስልት በመጠቀም አስተዋይነቱን አሳይቷል። ሲሆን ዘመን ወጣት ትውልድ ትግልና ድል ልዩ የሚያደርገውና ጊዜ ተወስዶ የበለጠ ሊመረመሩ የሚገባቸው ሦስት ጉዳዮችን ይዟል። እነዚህም፦

- o ይህ ትውልድ ትግሉን እንደ ቀደሙት ትውልዶች በፖለቲካ ፓርቲዎች ጥላ ሥር ተሰባስቦ ሳይሆን በራሱ ተነሣሽነት ያካሄደው መሆኑ፤
- o ወደ በረሐ ወይም ወደ ጫካ ሳይገባ በአካባቢው ተወስኖ ያደረገው ትግል መሆኑ፤
- o በሦስተኛ ደረጃም በሰላማዊና በሕዝባዊ እምቢተኝነት ላይ የተመሠረተ ትግል መሆኑ ናቸው::

ይህ ትውልድ ጠመንጃ ሳያነግብ ማኅበራዊ ሚዲያና ኢንተርኔትን በመጠቀም በእምቢ ባይነት መንግሥትን ያንበረከከ ትውልድ ነው። ‹ድምፃችን ይሰማ› ብለው ሙስሊሞች አስደናቂ የሰላማዊ ትግል አድርገዋል። በቄሮ፣ በፋኖ፣ በዘርማ የተደራጁ የሀገራችን ወጣቶች ከመሣሪያ ጋር በሰላማዊ ትግል ተገዳድረዋል። ወጣቶች በአክቲቪስትነት፣ በጋዜጠኝነትና በጦማሪነት የማንቃት፣ የማደራጀትና ግፍን የማጋለጥ ትግል አድርገዋል። በዚህ ሁሉ ትግል የተከፈለው የሕይወት መሥዋዕትነት ነው ለውጡን እውን ያደረገው።

በሰላማዊ መንገድ አፈናንና አግላይነትን በመገርሰስ ረገድ ወሳኙን ሚና ከተጫወቱት የትግል ጎራዎች አንዱ ኦሮሚያ ክልል ነበር። በዚህ ክልል ውስጥ ሕዝቡ ያካሄደው ግብግብ አፍራሽ ኃይሎች ከነዙት ወሬ በተቃራኒው ገና ከመነሻው እስከ ፍጻሜው ድረስ ሰላማዊ ነበር። ምንም ተባለ ምን የቄሮ ንቅናቄ ሰላማዊ የወጣቶች ትግል ነበር። ከጠመንጃ የተጣበቁ አምባገነኖች በየቦታውና በየሰበቡ ሕዝቡን ሲገድሉት፣ ሲያሥሩት፣ ሲያቆስሉትና ሲያስለቅሱት ቢኖሩም፣ የሕዝቡ በተለይም የወጣቶች ምላሽ እስከ መጨረሻው ሰላማዊ ነበር።

አንድ ቦታ ተቃውሞ ሲነሣ በመሣሪያ ኃይሉ ሲዳፈንና ሲቀዘቀዝ በሌላ ቦታ በሌላ ጊዜ አዲስ ተቃውሞ ሲቃጠል፣ አስረውና ገድለው ሊያዳፍኑ ሲሞክሩ እሳቱ ቋያ ሆነ እንደ አልጠፋም ነበር። ዓመቱ ሲገፋና በሌላ

ዓመት ሲተካ፣ የሕዝቡ እምቢተኝነት ኦሮሚያ ውስጥ ሥር እየሰደደ መጣ ሆኖም ግን በየትኛውም ቦታ የተደራጀና ይህ ነው የሚባል የትጥቅ ትግል አልተካሄደም። እዚያና እዚህ አልፎ አልፎ ከሚሰሙ የተቃውሞ ተኩሶች በስተቀር በድፍን ኦሮሚያ ከአርሲ እስከ ሞያሌ ከነቀምት እስከ ባሌ፣ ከሐረር እስከ ሰላሌ ትግሉ በየሥፍራው ሰላማዊ ነበር። እርግጥ ነው አልፎ አልፎ መንገድ የመዝጋትና አንዳንድ ንብረቶችን የማውደም ተግባራት እዚህና እዚያ ይታዩ ነበር። ነገር ግ የሰጧቸው ትእዛዞችና ምላሾች በወጣቱም ሆነ በለውጥ አመራሩ በትዕግሥት ባይያዙ ኖሮ ውጤቱ ከሳራ፣ መንገዱም የደም አበላ ሊሆን በቻለ ነበር።

ከኦሮሚያ ወደ አማራ ክልል ስንሻገር ፋኖዎች የኦሮሞ ወጣቶች ደም የእኛም ደም ነው በሚል የጀመሩት ተቃውሞ በሰላማዊ ትግሉ ላይ የበለጠ ነፍስ ዘራበት። የሀገሪቱን ሕዝቦች በመነጣጠል ለአገዛዝ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ይቻላል ብለው ሲያስቡ የኖሩ ነበሩ። የአማራ ፋኖዎች የታሰሩ የነጻት ታጋዮችን እንዲፈቱ ብሔር ሳይለዩ በአደባባይ መጠየቃቸው የሕዝቦችን ኅብረት አንድ ደረጃ ከፍ አደረገው። ሁላችንም ነጻ ካልወጣን ማናችንም ተነጥለን ነጻ ልንወጣ አንችልም የሚለውን የነጻነት መርሕ በተግባር አሳዩ።

መደብሮችንና ገበያዎችን በመዝጋት ከሥራ ገበታ በመቅረት፣ ቤት የመቀመጥ አድማዎችን በማድረግ፣ ሲያስፈልግም ጥያቄዎችንና መፈክሮችን አንግቦ ሰልፍ በመውጣት የአማራ ፋኖዎች ተቃውሟቸውን ባገኙት አጋጣሚ ሲገለጡ ቆይተዋል። በጎንደር ከተማ የተጀመረው የፋኖዎች ለውጥ ቀያሽ ሰላማዊ ትግል ተፋፍሞ በጎጃም፣ በወሎና በሸዋ በአራቱም አቅጣጫ ቀጠለ። የኦሮማራ ጥምረትም በዚሁ አጋጣሚ ተወለደ። የደቡቦቹ ዘርማዎችም ቢሆኑ መታወቂያቸው ጠመንጃና የጦር መሣሪያ ሳይሆን፣ ሰላማዊ የትግል ስልት ነበር። በአማራና በኦሮሚያ እንደተደረገው ሁሉ፤ እዚህም አልፎ አልፎ የንብረት ውድመት፣ የሰው ሕይወት መጥፋትና የመኪኖች ማቃጠል ቢከሠትም፣ ዋናው የትግሉ መንገድ ግን ሰላማዊ ነበር። ከዐርባ ምንጭ እስከ አላባ፣ ከዲላ እስከ ሐዋሳ፣ ከወልቂጤ እስከ ወራቤ ባለው የደቡብ ከፍል ሁሉ ትግሉ ከጥፋት የጸዳ ነበር ማለት ይቻላል።

ሆኖም ወጣቱ የለውጥ ኃይል በመሆኑና ለውጡን በመደገፉ ብቻ ተፈላጊው ለውጥ ሊረጋገጥ እንደማይችል የታወቀ ነው። የወጣቱ ትኩስ ጉልበት ልክ እንደ ምድር ውስጥ የእንፋሎት ኃይል ነው። ይህ እንፋሎት ምድር ውስጥ ታፍኖ ከቆየ ተፈላጊውን ጥቅም ለማስገኘት አይችልም። የእንፋሎቱ ኃይል ጥቅም ለማስገኘት የሚችለው ምድሩን ጥሶ ስለወጣም አይደለም። ከምድር ጥሶ ሲወጣ በውስጡ የታመቀው ኃይል እንዳይበተን በጥንቃቄ መርቶ ወደማመንጫ ተርባይኑ እንዲሄድ ከተደረገ ብቻ ነው።

ይህ ከሆነ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨትና ሞተር ማንቀሳቀስ ይችላል። በተቃራኒው መገደቢያ ካልተበጀለትና የሚመራው ካላገኘ ትኩሱ እንፋሎት በዙሪያው ያለውን ሕያው ነገር ሁሉ አቃጥሎ ወይም አየሩን በማሞቅ ኃይሉን አባክኖ ይጠፋል። ለዚህም ነው፣ የወጣቱን ጉልበትና ዕውቀት ወደ ውጤት ለማሸጋገር መሪ ያስፈልጋል የሚባለው።

አዲሱ የለውጥ ቡድን ወጣቱ ለፍትሐዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትና ለአጠቃላይ ማኅበራዊ ፍትሕ መረጋገጥ ዘብ እንዲቆም፣ በደልን ስርቆትና አፈናን በሰላማዊ መንገድ እንዲቃወም መንገድ ለማሳየት የበኩሉን ጥረት

አድርጓል። ወጣቱ በከፍተኛ ቁጥር ለሚሳተፍባቸው ሁሉም አደረጃጀቶች የተለየ ትኩረት በመስጠት፤ የአዲሱ ለውጥ መርሕ ከሆነው የመደመር እሳቤ መርሖች ጋር እንዲተዋወቅ ለማድረግ አነቃቂ ትምህርቶችን በመስጠትና የፊት ለፊት ግልጽ መድረክ በመፍጠር፣ ኅብረቱን የሚያጠናከርበትና ትኩስ ኃይሉን ጥቅም ላይ ማዋል የሚችልበትን አቅጣጫዎች አስቀምጧል። ከፍ ያለ ውጤትም ለማግኘት ቿሏል።

ወጣቱ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርግባቸውን ማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን በመጠቀም መልእክትን በጥበባዊ መንገድ በመቅረጽ፣ ትስስሩን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ ጥረቶች ተደርገዋል። ትክክለኛውን ዓላማ ከጨበጠ፣ በተገቢና በእውነተኛ ሐሳብ ከተመራ፣ ወጣቱ ኃይል እስከ አፍንጫው ድረስ የአፈናና የማውደሚያ መሣሪያዎችን የታጠቀውን መንግሥት መረብ መበጣጠስ ይችላል። ከብስ አልፎ በተጨባጭ ያንበረክካል። ይህንንም ባለፉት ዐሠርት ዓመታት ከቱኒዚያና ከግብጽ ሕዝባዊ አብዮቶች አይተናል። በሀገራችን በኢትዮጵያ : ምድርም : በቄሮ፣ በፋኖና በርማ የተደራጁ ወጣቶች ያስመዘገቡት ድል ለዚህ ምስክር ነው። ይህ በስፋት ሊዘከር የሚገባው የኢትዮጵያ የአዲሱ ትውልድ የለውጥ ርምጃ ማሳያ ነው። እንግዲህ ለለውጥ መገኘት ወሳኙን ሚና የተጫወተው ይህ ወጣት ኃይል ተመልሶ ለሽግግሩ አደጋ የሚሆን ነገር እንደምን ይፈጽማል? የሚል ጥያቄ ይነሣል። ጥያቄው እጅግ ተገቢ ነው። ችግሩን ለመረዳት የግድ ጥያቄው መጠየቅ አለበትና፤ ይሄንን ጥያቄ ለመመለስ ካልተቻለ የእስካሁኑ ጉዞ በጠቅላላ በዜሮ ሲባዛ ይቻላል።

ተደጋግሞ እንደሚባለው፤ ወጣትነት እንደሚንቀለቀል እሳት ነው። እውነት ነው ወጣትነት ጉልበት፣ ኃይልና ድፍረት የሚያይልበት ዘመን ነው። ወጣትነት ሁሉንም ነገር አሁን እንዲሆን የመፈለግ አዝማሚያ የሚታይበት ገፊ ኃይል ነው። ጥያቄዎችን ጠይቆ መልሱን አሁኑኑ ሰጡኝ ባይነት ነው። ከዘገየ በእምቢተኝነት ይቀጥላል።

የዛሬው የኢትዮጵያ ወጣት፣ አሁኑኑ እንዲመለሱለት የሚሻቸው እልፍ ጥያቄዎች እንዳሉት ሐቅ ነው። ሆኖም የሀገራችን ችግር ውስብስብ፣ የአስተሳሰብ፣ የሥርዓትና የመዋቅር ለውጥ የሚፈልግ ነው። ይህ ደግሞ ጊዜ ይፈልጋል። ጊዜ ሲባል ለመዝናናት ወይም ለመተኛት የሚመደብ ጊዜ አይደለም። እኛ የሚያስፈልገን የመተኛ ጊዜ አይደለም።

አንዱን ነቅሎ ሌላውን መትከሉ በፍጥነት ቢከናወን የሚደረማመሱና እንዳልነበር የሚሆኑ ሀገራዊ ዕሴቶችና ሀብቶች አሉን። እህሉን ከአረሙ፣ ስንዴውን ከእንክርዳዱ ለይተን በመንቀል አደጋን የመቀነሻ ጊዜ ነው የሚያስፈልገን። የምንወስደው የእርምት ሥራ ችግሩን ዳግም እንዳይመጣ ማድረግ አለበት። ዓላማችን መፈወስ እንጂ የሕመም ማስታገሻ ሰጥቶ ሕመምን ማስረሳት አይደለም። አሁን ያለንበት ደረጃ አንዱን ስትነካ ሥርዓቱ የሚናወጥበት፣ አንዱን ዘለላ ስትመዝ ሙሉ ክምሩ ሊናድበት የሚችልበት አስቸጋሪ ወቅት ነው።

ለዚህ ነው፤ ‹ለውጡን ያመጣው ኃይል፣ ለውጡን ማስከንና መጠበቅ ይኖርበታል› የምንለው። እስካሁን የተደረገው ትግል አሮጌውን አስተሳሰብ ለማስወገድ ሲሆን፣ ቀጣዩና ዋነኛው ደግሞ አዲሱን ሥርዓት ለመትከል ነው። አዲሱን ሥርዓት መትከልና መጠበቅ ደግሞ ለውጡን ለማምጣት የተከፈለውን መሥዋዕትነት ያህል ባይጠይቅም የበለጠ ትዕግሥትና ጥንቃቄ የሚጠይቅ መሆኑ ግን ልብ ሊባል ይገባል።

ከለውጥ ጋር በተያያዘ ሰዎች በሦስት እንደሚከፈሉ ጥናቶች ያሳያሉ። ለውጥን በፍጥነት የሚቀበሉና በለውጥ ሂደቱ በከፍተኛ ፍላጎት የሚሳተፉ፣ ለውጡን በጥርጣሬ የሚመለከቱ ወይም የሚወላውሉ እና ለውጡን የሚቃወሙ ናቸው። ምክንያቱ አንድ ጸሐፊ እንዳለው "ለውጥ ሁሌም ባለ ሁለት ጽንፍ፣ ባለ ሁለት ገጽታ ነው። ከመንቀል ጋር መትከልን፤ ከማስወገድ ጋር መተካትን የግድ ይላል።"

የነባራዊ ሁኔታ ተጠቃሚዎች የሚነቀለውን ያውቁታል ተላምደውታል፤ ተጠቃሚ ናቸውና ይወዱታል፤ ይፈልጉታል። ወላዋዮቹ ደግሞ የሚተከለውን ነገር አያውቁትም፤ ርግጠኛ አይደሉምና ይፈሩታል፤ በመንታ ልብ ይመለከቱታል። ምክንያቱም ለውጡ ያላቸውን እንዳይነጥቃቸው ይሠጋሉና ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ለውጡን ይፈልጉታል፤ የተሻለ ነገር ይፈልጋልና። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ‹‹ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል›› የሚባለውን ብሂል ይጠቀማሉ። በዚህም ምክንያት ከለውጡ በፊት ስለነበረው ጥሩነት ሲወሳም ሆነ ስለአዲሱ ክሥተት ‹ጉድለት› ሲነሣ “አላልኳችሁም!" ማለት ይቀናቸዋል። ምንጊዜም ለውጥ ወደፊት መሄድ የሚፈልጉ እና መርጋት የሚፈልጉ ኃይሎች ፍትጊያ ነው። ይሄም የለውጡን ጠንሳሾችና አራማጆች የሚፈትን ተግዳሮት ነው። የአንድ ለውጥ ጠንሳሽ ስኬታማነትም ይሄንን ለውጥ ያለመፈለግ ፍትጊያ ለማሸነፍ መቻል ነው። በማኅበረሰቡ ውስጥ ለውጥን በሩቁ የሚያስፈሩና የሚያስሸሹ ወይም ደግሞ በተጠና አካሄድ ሳይሆን በጀብደኝነት እንዲገባበት የሚያበረታቱ አባባሎች አስተሳሰቦች ይገኛሉ። ወጣቶች የሀገር አጀንዳና ቁልፍ ጉዳይ ቢሆኑ ያንሳቸዋል እንጂ አይበዛባቸውም። በአሁኑ ጊዜ ወጣቶች የሀገራት ብቻ ሳይሆን የዓለምም ትኩረት ናቸው።

ዓለም ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በወጣቶች የተሞላች ምድር ሆናለች። መቼም ጊዜ ቢሆን የወጣቶች ቁጥር ይሄንን ያህል ደርሶ አያውቅም። በአሁኑ ሰዓት በመላው ዓለም ከ1.8 ቢልዮን በላይ ለመፍጠር፣ ለመገንባት፣ ለመፈላሰፍ፣ ቤተሰብ ለመመሥረትና ሀገርን ለመገንባት እምቅ ኃይል ያላቸው ወጣቶች አሉ። ይኼ ግዙፍ የለውጥ ኃይል የዓለም አጀንዳ ቢሆን ልንገረም አይገባም።

በአሁኑ ጊዜ የወጣት አፍሪካውያን ቁጥር ከ200 ሚልዮን ይበልጣል። በ2045 ዓ.ም. ደግሞ ይህ ቁጥር በእጥፍ ይጨምራል ተብሎ ይገመታል። ከጥቂት ዓመታት በፊት የመንግሥታቱ ድርጅት ጥናት እንዳመለከተው ወጣት ከሚበዛባቸው 10 የዓለም ሀገሮች መካከል ስምንቱ አፍሪካውያን ነበሩ። ኢትዮጵያ ከእነዚህ አንዷ ናት። በኢትዮጵያ አቆጣጠር 2010 ዓ.ም. የተደረጉ ሞያዊ ግምቶች እንደሚያሳዩት፤ ከአጠቃላይ 108 ሚልዮን ሕዝብ ውስጥ 46.3 በመቶ የሚሆነው ዕድሜው ከ15 ዓመት በታች ነው።

በአሁኑ ጊዜ ዓለምን ከሚያስጨንቋት የጸጥታና የደኅንነት ሥጋቶች አንዱ የወጣቶች ሥራ አጥነት እንደመሆኑ መጠን፣ በኢትዮጵያም የወጣቶች ሥራ አጥነት ምጣኔ 7 በመቶ አካባቢ ሆኖ ቆይቷል። ዕድሜያቸው ከ15 - 26 ዓመት ከሆነ ወጣቶችና አዳጊዎችም መካከል 25 በመቶ የተሟላ ሥራ ለማግኘት አልቻሉም። አንድ የቅርብ ጊዜ ጥናት እንዳመለከተው ኢትዮጵያ ውስጥ በየዓመቱ ሁለት ሚልዮን ወጣቶች ሥራ ይፈልጋሉ።

ሥራ አጥነት ምን ያህል አስከፊና ተስፋ አስቆራጭ ፈተና እንደሆነ ከማንም ይልቅ ራሳቸው ወጣቶች የሚረዱት እውነታ ነው። ሥራ አጥነት ወጣቶቻችንን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ለወል፣ ለሱስ፤ እንዲሁም

ለስደት ሊዳርግ ይችላል። የብዙ ሀገሮችን ድንበር ተሻግረው፣ በዱር በገደሉ ተጉዘው፣ በረሐ አቆራርጠው፣ ሕገ ወጥ ስደተኞች ተብለው በየሀገሩ የሚዋከቡት ኢትዮጵያውያን ቁጥር ቀላል አይደለም።

በየመንገዱ አውሬ የበላውን፣ ሽፍታ የዘረፈውንና የገደለውን ኢትዮጵያዊ ቁጥር ሌላው ቀርቶ ቤተሰቦቻቸውም እርግጡን ያውቁታል ለማለት ያዳግታል። ባለፉት ዓመታት የወጣት ሥራ አጥነት ቁጥር ከዓመት ወደ ዓመት ሽቅብ ተተኩሷል። በሥልጣን ላይ የነበረው ቡድን ግን በበቢልዮን የሚገመት የሀገሪቱን ሀብት እየዘረፈ ለራሱ ጥቅም ለማዋል በውጭ ሀገራት ባንኮች ያከማቸ ነበር። ይህ ሳይበቃ ወባቱ በተለያዩ ኮሮጆዎች እየተፈረጀ ‹አደገኛ ቦዘኔ› በሚል ፕሮፓጋንዳ እየተዘመተበት ቆይቷል። በዚህና በሌሎች ምክንያቶች የሞራል ውድቀትና ዝቅጠት እንዲያጋጥመው፤ ከምክንያታዊነት ይልቅ ስሜታዊነት እንዲያይልበት ተደርጓል። በዚህ ሁሉ መንገድ የመጣ ወጣት ሕግን በእጁ አስገብቶ ርምጃ ቢወስድ፣ የጅምላ ፍርድና ጥቃት ግንባር ቀደም ተዋናይ ቢሆን ኣይደንቅም።

ሀገራት ለዜጎቻቸው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎትን ሲያዳርሱ፤ የቤተሰብ አባሎቻቸውን ቁጥር ሲቀንሱ፤ በአንጻሩ የሠራተኞቻቸውን ቁጥር ሲጨምሩ፤ ሥነ ሕዝባዊ በረከት ማግኘት እንደሚችሉ ይታወቃል። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሕጻናትንና ሌሎችም ድጋፍ ፈላጊዎችን ቁጥር ቀንሶ የሠራተኛ እጆችን ቁጥር ማብዛት ቁጠባን ይጨምራል። የሀገር ሀብትና የሀገር ዕድገትም በዚያው መጠን ከፍ ይላል።

በዚህ ሥነ ሕዝባዊ በረከት የተነሣ በርካታ የምሥራቅ እስያ ሀገሮች ከፍተኛ ዕድገት ለማስመዝገብ ችለዋል። ለምሳሌ ከ1950 እስከ 2008 ባለው ጊዜ ደቡብ ኮሪያ ይኸን ሥነ ሕዝባዊ በረከት ተጠቅማ የነፍስ ወከፍ የሀገር ውስጥ ምርቷን በ2200% በዛ ለማሳደግ ችላለች። እኛም የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ለብዙዎች ተዳርሶ የሕፃናትና የሌሎች ድጋፍ ፈላጊዎች ቁጥር ቀንሶ፣ የሠራተኛ እጆች ቁጥር እንዲጨምር በማድረግ፤ ይኸን በረከት ለመቋደስና የወጣቶችን ሕይወት ለማሻሻል የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ ይኖርብናል።

ለዚህ ጥረት መሳካት ቁልፍ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ ትምህርት በመሆን ለትምህርት ዕድል መስፋፋት ብቻ ሳይሆን፣ ለጥራቱም ተገቢውን ትኩረት እንሰጣለን። ወጣቶች የቴክ ሞያ በበቂ እንዲያገኙ ከማስቻልም ባለፈ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አሮን የሚለውጡ የምርምር ማዕከላት እንዲሆኑ በከፍተኛ ደረጃ እንተጋለን። አዲሱ የትምህርት ፍኖተ ካርታ ወይ ትኩረት እዚህ ላይ ያነጣጠረ ነው። የቤተሰብ ምጣኔ እንደ ኑሮ ባህል ተለምዶ፣ የሠራተኞችና የሀገር ዕድገት እንዲጨምር፣ የጤና ፕሮግራሞቻችንን ከመቼውም ጊዜ በላይ ለማጠናከር ዘወትር እንሠራለን። አበውና እመው ‹አሣምር ያሉት አይክፋ፣ ጠብቅ ያሉት አያጠፋ› የተባለውን በሚከተለው ምሳሌ አቅርበነዋል።

አዛውንቱ ታመው የአልጋ ቁራኛ ከሆኑ ሰነባብተዋል። በመኝታ ክፍላቸው ውስጥ ባሉት የሳማ ማስቀመጫ ዕቃዎች ላይ በአራቱም ማዕዘን ሻማዎች በርተው ተቀምጠዋል። የአዛውንቱ ባልንጀራ የሆኑት ሽማግሌ እንደ ሁል ጊዜያቸው ታመው አልጋ ከያዙት ወዳጃቸው ቤት በመገኘት ከአልጋቸው ራስጌ ተቀምጠው እያጫወቷቸው ነበር። የአዛውንቱ ወዳጅ የመጨረሻ እስትንፋሳቸው እስከምትወጣ ድረስም ከጎናቸው አልተለዩም ነበር። እናም የአዛውንቱ እስትንፋስ እንዳለፈች ሽማግሌው ወደ አዛውንቱ የሻማ ማስቀመጫ ዕቃዎች በመቅረብ

ከአራቱ ሦስቱን ሻማዎች ያጠፋሉ። በዚህ የሽማግሌው ተግባር የተገረሙ አንድ ቤተ ዘመድ ሽማግሌውን እንዲህ ሲሉ ይጠይቋቸዋል። ‹‹በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ይበልጥ ብርሃን እንዲሆን ተጨማሪ ሻማ ይለኮሳል እንጂ እንዴት ያለው በዛ ተብሎ ይጠፋል?››

‹‹እውነት ነው። ግን ደግሞ ልብ በሉ። ቀድሞ ሻማው የራሱ የባለቤቱ ነበር። አሁን ግን ባለቤቱ ሕይወቱ አልፋለች። የሻማው ብቸኛ ባለቤትም ወራሾች ናቸውና የራስ ያልሆነን ሀብት ካለፈቃድ ማባከን ተገቢ አይደለም።» በማለት ሽማግሌው ምላሽ ሰጡ።

የሕዝብ አገልጋዮች ይሄን በትክክል ጠንቅቀው መገንዘብ ይኖርባቸዋል። እነርሱ የትውልድ ጠባቂና አሸጋጋሪ ድልድዮች ናቸው። እኛ የዚህ ዘመን የሕዝብ አገልጋዮች ብክነትን ማስወገድ፣ ጥፋትን ማስቀረት ይኖርብናል። ሥራን ስኬታማ የሚያደርገው መደመርን መንገዱ ያደረገ አሳታፊነትና አካታችነት ብቻ ሳይሆን ብክነትና ልግመኝነትንም የሚያስወግድ ሕዝባዊ ሐላፊነትና ተጠያቂነትም ጭምር ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ወጣቶች ያልተሳተፉበት ወጣቶችን የሚመለከት ውሳኔ እንዳይኖር መንግሥት የሚችለውን ሁሉ ለማድረግ ራሱን ሲያዘጋጅ፣ ወጣቶችም የበኩላቸውን ለማድረግ መነሣት ይኖርባቸዋል።

ዋናው ዓላማችን ነገን ለውጣቶች ምቹ ማድረግ ብቻ አይደለም። ወጣቶቹ ለነገ ማዘጋጀት እንጂ። ሁለቱ አብረው ካልተሠሩ ውጤት አይኖርም። ታዋቂው የአሜራ ፕሬዚዳንት ፍራንክሊን ሩዝቬልት በአንድ ወቅት እንደተናገሩት፤ ‹‹ነገን ለወጣቶቻችን የተሻለ እንዲሆን አድርገን ሁልጊዜ ላንገነባው እንችላለን፤ ወጣቶቻችን ግን ለነገ የተሻሉ ሆነው እንዲገኙ አድርገን መገንባት እንችላለን።››

ደጋግመን እንዳልነው፣ ወጣትነት ትኩስነት ነው። በወጣትነት ውስጥ በርግጥም እሳትነትና ማለት አለ። ይኸንን እሳት ብረት ቢቀልጥበት፤ መስኖ ቢጠለፍበት፣ ተራራ ቢናድበት ግለሰቡም ሀገርም ይጠቀማል። ይኸ እሳት ፋብሪካ ለመገንባት እንጂ ፋብሪካ ለማቃጠል ከዋለ ደግሞ ሁሉም ይከስራል። ድልድይ ለማነጽ እንጂ ድልድይ ለማፍረስ ከዋለ በከንቱ ይባክናል። ተአምር ለመሥራት እንጂ መዓት ለማውረድ ከዋለ ትርጉም የለውም። ከምንም በላይ ይኸንን እሳት ሕይወት ለማዳን እንጂ ለማጥፋት መዋዕ የለበትም። የሀገራችን ሰዎች አፍ ያነዳል፤ እፍ ያጠፋል›› ይላሉ። ‹‹እፍ›› ብሎ እሳትን ማንደድ ይቻላል። ‹‹እፍ›› ብሎም እሳትን ማጥፋት ይቻላል። ወጣትነትም እንደዚሁ ነው። ‹‹እፍ›› ብለው ሊያበሩበት፤ ‹‹እፍ›› ብለውም ሊያጠፉበት ይችላሉ።

ኢትዮጵያን የማልማት ከልማቱም የመጠቀም ጉዳይ ቀዳሚ የትኩረት ነጥብ ሊሆን ይገባል። የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ዕድል ለጊዜው ፊቷን በማዞሯ የተነሣ የሀገራችን ወጣቶች በሀገራቸው ማዘን፣ በሕዝቧ ተስፋ መቁረጥ አይኖርባቸውም። ከሆነም በመንግሥት እንጂ በሀገራችው ተስፋ መቁረጥ አይገባቸውም። መንግሥትና አስተዳደሩ ጊዜያዊና አላፊ ናቸው። ሀገር ማን በሞትም በሕይወትም ወጣቶችን አቅፋ የምትኖር ዘላለማዊ ቤትና መኖሪያ ናት። በእርግጥም ወጣቶቻችን የቁዘማ ፀሐይ እየጠለቀች፡ የተስፋ ዘመን እየመጣች መሆኑን በልበ ሙሉነት መረዳት ይኖርባቸዋል። አሁን ያለው የሀገራችን ሁኔታ ለብዙ ጊዜ የያዘ ሰይጣን ሳያንፈራግጥ አይለቅም እንደሚባለው ይመስላል። መንፈራገጥ ካለ ደግሞ መላላጥ አይቀርም። ደግነቱ ሰይጣኑ እየገባ

ሳይሆን እየወጣ መሆኑ ነው።

ዕውቁ ግሪካዊው የድራማ ጠቢብ ዩሪፒደስ በአንድ ወቅት እንዳለው፤ “ሀብታም ለመሆን ከሁሉም የተሻለው ጊዜ ወጣትነት ነው። ድኻ ለመሆንም ከሁሉም የተሻለው ጊዜው ወጣትነት ነው። የመጥፋትም የመልማትም ዕድል ያለው በወጣቶች እጅ በመሆኑ ሁሌም የተሻለውን እንዲመርጡ እማጸናቸዋለሁ። እንግሊዝን ሁለት ጊዜ በመሪነት ያለገለው ቤንጃሚን ዲዝራሊ፣ ጊዜ በማይሽረው ንግግሩ፤ 'የአንድ ሀገር ወጣቶች የመጭው ትውልድ ሁሉ ባለ አደራዎች ናቸው ሲል ወጣቱን ትውልድ አሞካሽቷል። ኣልተሳሳተም፡ አላጋነነም። የሁላችንም ነ ያለው በወጣቶቻችን መዳፍ ውስጥ ነው።

ወጣቶች ተስፋ ካላቸው ሁላችንም ተስፋ ይኖረናል። ሀገራችን ተስፋዋ በወጣቶቿና በነገው ትውልድ ላይ ነው። ሁላችንም ወጣቱን ትውልድ ከውስጡ ያለውን በጎ ዐቅም እንዲያወጣ፣ ከፊቱ ያለውንም የተስፋ አቀበት በድል እንዲወጣ የማገዝ ሐላፊነት አለብን። ወጣት የነብር ጣት ነውና ታግሎ የማሸነፍ፣ አባሮ የመያዝ ልብም ዐቅምም አለው።

በወጣትነት ውስጥ ‹‹መደመር›› ሲኖር ደግሞ ኃይሉና ጉልበቱ፣ ፍሬውና ውጤቱ እጥፍ ድርብ ይሆናል። ወጣቶች የሚያምርባቸውም ሆነ የሚሆንላቸው ተደምረው ታሪክ ለማጥፋት ሳይሆን ታሪክ ለመሥራት ሲተጉ ነው። ታሪክ ለመሥራት ጊዜንና ጉልበትን በጥበብ መጠቀም ይፈልጋል። ጊዜውንና ጉልበቱን በጥበብ ተጠቅሞ ለሀገሩ ያልሠራ ወጣት የሚነገር ታሪክ የለውም። በምድር ላይ ትርጉም አልባ ሕይወት ስላሳለፈ መቆጨቱ አይቀርም። ከዚህ በላይ ለወጣቱ ልንለው የምንችለው ሌላ ምንም አይኖርም።

ጃፓኖች ኃይለኛ ነፋስ ሲነፍስ ብልሕ ሰው የነፋስ ወፍጮ ይተከላል፤ሞን ግ የመከለያ ግብ ያቆማል ይላሉ። ብልሕ ወጣት ማለት በተከለው የነፋስ ወፍጮ የነፋስን እምቅ ዐቅም ወደ እውናዊ ኃይል የሚለውጥ ነው። እነሆ በሀገራችን ዐቅም ሞልቷል። ወጣቶች ሆይ! ተነሡና ወደ እውን ኃይል ቀይራችሁ ሀገራችሁን አሳድጉበት፡፡ የብቸኝነትና የእኔነት ግንብ ሠርታችሁ አትሸሸጉ። የነፋሱ ኃይል ሲጨምር ፍርሃትና ግለኝነት በፊቱ ሊቆሙ ኣይችሉምና። የሚነፍሰው ነፋስ ለሚሠሩ ሀብት ለሚሰንፉና ለሚዘርፉ ደግሞ አፍራሽ ጉልበት መሆኑ አይቀርም፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የለውጡ ጥንስስ

ለጌሾ ወቀጣ ማንም ሰው አልመጣ
ለመጠጡ ጊዜ ከየጐሬው ወጣ።

~ ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ

# ዓሥር ዓመታት ወደ ኋላ

## ኢዲስ ዘመን ሲመጣ፣ አዲስ ትግል ሊወለድ.......

በሀገራችን በየዓመቱ አዲስ ዘመን በመጣ ቁጥር ሰዎች በፌሽታ ይቀበሉታል። ክረምቱን ከዝናብና ከዶፍ፣ ከጭጋግና ከጎርፍ፣ ከበረዶና ከነጎድጓድ ጋር ሲዋከቡና ሲታገሉ ቆይተው፣ ከዘመድ አዝማድ ሳይጠያየቁ ከርመው፣ መስከረም ሲጠባ፣ አዲሱን ዘመን በአዲስ ተስፋ እንኳን ደኅና መጣህ› ይሉታል። ዳቦና ጠላውን አዘጋጅተው፣ አበባዬ ሆይ ለምለም እያሉ የዘመን መለወጫውን ዕለት በከፍተኛ ደስታ ያሳልፉታል። ያለፈውን ዓመት እየረሱ፣ አዲሱን ዓመት እያወደሱ፣ በተስፋ ተሞልተው፣ በጊዜ ባቡር ላይ ሐዲዱን ተከትለው መጓዛቸውን ይቀጥላሉ። ያም ዓመት በተራው ያልፍና፣ አሮጌው አምና ይባልና፣ እርሱም ይሸኛል ከልብ ተዘንግቶ፤ በሌላ አዲስ ዓመት ተተክቶ።

ሁልጊዜም አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር ለዘመን መለወጫ እንደዚያ መሆናችን ይደንቀኛል። አሁን ደግሞ የዓሥራ ሁለት ወራት ዑደታዊ ለውጥ አዲስ ዓመት ሳይሆን አንድ ሺሕ ዓመታት ወይም ዐሥር ክፍለ ዘመናት ተግተልትለው ከሚሰናበቱበት የዘመን አንጓ ላይ ደርሰናል።

እነሆ ሀገራችን ኢትዮጵያ አዲሱን ሚሊኒየሟን ልትቀበል ሽር ጉድ ላይ ናት።

ሀገራችን ባሳለፈችው እልፍ ዘመን ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶችን አይታለች። ዘመን ፈገግ ያለላት ወቅት በስኬት ስትፈካ፣ በዓለም ሀገራት ፊት ደምቃ ስትታይ፣ ሕዝቦቿ በድል ሲፈነድቁ የመቆየታቸውን ያህል፤ ዘመን ሲከፋ ደግሞ ድርቅና ቸነፈሩ፣ ጦርነትና በሽታው፣ ድህነትና ጉስቁልናው እየደቆሳት አሳልፋለች።

አሁን ደግሞ አዲስ ዘመን እየመጣ ነው። ምን ይዞ እንደሚመጣ ባታውቅም በደስታ ልትቀበለው ሀገራችን ሽር ጉድ ማለት ጀምራለች።

እኔ በግሌ ቀጣዩ ሚሊኒየም ለሀገሬ ከፍተኛ የለውጥ ተስፋ ይዞ ይመጣል የሚል ግምት ይዤ እየጠበቅኩት ነው። ሌሎች ኃያላን ሀገራትን ባሰብኩ ቁጥር የኃያልነትን ካባ የምንደርብበት መልካም ዘመን እንዲመጣ ስናፍቅ ቆይቻለሁ። የዘመን መለወጥ የአዲስ ተስፋ መምጣት በመሆኑ የሚሊኒየሙ መምጣት ለምን እንደሆነ አላውቅም፣ ብቻ ያ የረጅም ዘመን ተስፋዬ እውን የሚሆንበት ዕድል እየቀረበ እንደሆነ እንዳስብ አድርጎኝ ነበር። በተለመደው መንገድ ለውጥ እንደማይመጣ ጥርጥር ባይኖረኝም፣ በትክክል በምን ዓይነት መልኩ ለውጥን እናስተናግዳለን? ለሚለው ጥያቄ ግን ምንም መልስ አልነበረኝም።

ኢሕአዴግ በትረ ሥልጣኑን ከጨበጠበት ጊዜ አንሥቶ ለዓሥራ ምናምን ዓመታት ብዙ የድልና የውድቀት አጋጣሚዎችን አሳልፈናል። የሽግግር መንግሥት ምሥረታን በማከናወን፣ ሰላምና መረጋጋትን በማስፈን፣ ሀገራዊ ምርጫዎችን በማድረግ፣ በገጠር ልማትና ኢኮኖሚውን ለማሳደግ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎችና በመሳሰሉት ውጣ ውረዶች አልፈናል። ከኤርትራ ጋር የተደረገው ጦርነት፣ የድርጅታችን ለሁለት መከፈልና ሌሎችም የፈተና ጊዜያትን አይተናል። በተለያየ ጊዜ በድርጅታችን ውስጥ አያሌ ችግሮች ተፈጥረው በተለያዩ መንገዶች አልፈናቸዋል። ታዲያ በዚህ ጉዞ ውስጥ ድርጅቱ ለኢትዮጵያ የሰነቃቸው ራእዮች ከሞላ ጎደል

መልካም እንደሆኑ እያሰብኩኝ፣ ያሉ ችግሮችም በግምገማና በምክክር እንደሚቀየሩ እያመንኩኝ ነበር የቆየሁት።

ኢንሳን እስከ ፈጠርንበትና ለሁሉ ነገር ቅርብ ሆኜ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት እስከ ጀመርኩበት ጊዜ ድረስ ስለእኛ ከፍተኛ አመራሮች ሁኔታ የነበረኝ ግንዛቤና ዕውቀት ጥልቀት የጎደለው ነበር ማለት እችላለሁ:: በድርጅታችን ውስጥ የሚፈጠር እያንዳንዱ ችግር በሂስና ግለ ሂስ እየታረመ መሄድ እንደሚችል እንጂ ያን ያህልም የተጋነነ ለውጥ የሚያስፈልገው መስሎ አይሰማኝም ነበር። እርግጥ ነው፤ ድርጅታችን ላይ ብዙ ትችቶች ሲሰነዘሩ እሰማለሁ፤ አንዳንድ እንከኖችንም አያለሁ። ኢንሳ መግባቤ ለብዙ ነገሮች ቅርበትን እየፈጠረልኝ ሲመጣ፣ ከድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ጋር መተዋወቅና መግባባት ስጀምር፣ ኢሕአዴግን እንደ መጽሐፍ፣ ገጾቹን እየገለጥኩ ወደ መሐሉ ላይ ስደርስ ቀደም ብሎ የነበረኝ ግምት በከፍተኛ ሁኔታ መቀየር ጀመረ።

በዚያን ወቅት ነበር ለመጀመሪያ ጊዜ የድርጅታችንና የመንግሥታችን ውቅር መሠረታዊ ለውጥ እንደሚያሻው ማሰብ የጀመርኩት። አዎ ድርጅታችን ላይ መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ማድረግ ካልተቻለ ሀገራችን ላይ ከፍተኛ የሆነ አደጋ እየተጋረጠ ይሄዳል። ድርጅታችን ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን መልካም በማይመኙና ለግል ጥቅማቸው በሚያድሩ ሰዎች እስከ አንገቱ ድረስ ተተብትቧል። ይህ ትብታብ በሂስና ግለ ሂስ የሚወገድ እንዳልሆነ፣ ይህ መጥፎ ሰንሰለት በግምገማ ወይም በአንድ ሰሞን ዘመቻ የሚበጠስ እንዳልሆነ ግልጽ እየሆነልኝ የመጣው ኢንሳ የመግባቴ አጋጣሚ ነው። ብዙም ሳልቆይ ነገሩን ከሌሎች ጋር በመሆን መታገል እንዳለብኝ ከልቤ የወሰንኩት እዚያው ሳለሁ ነበር። በወቅቱ ትግል ለማድረግ መወሰን ብቻ ሳይሆን ትግሉን ከውስጥ ሆኖ ማከናወንም እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ማመን ጀመርኩ። እርግጥ ነው፤ ፈረንጆች እንደሚሉት "ጓደኛህን ቅርብ አድርገው፣ ጠላትህን ደግሞ የበለጠ አቅርበው" በሚለው መርሕ የመመራት ፍላጎት አይደለም ከውስጥ ሆኖ የመታገል ፍላጎት እንዲያድርብኝ ያደረገው። ከዚያ ይልቅ ውጭ ያለው አማራጭ ደካማና የማያወጣ አማራጭ መስሎ ስለተሰማኝ እንጂ።

እንደሚታወቀው በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ላይ የተጋረጠው አደጋ ታይቷቸው ትግል ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ ሌሎች አካላትም ነበሩ። ጊዜው በምርጫ ዘጠና ሰባት ማግስት የተፈጠሩ ቀውሶች የፖለቲካችንን አቅጣጫ የቀየረበት ጊዜ ስለነበር ብዙዎች _ ኢሕአዴግን ለመጣል _ በተለያዩ መንገዶች መንቀሳቀስ ጀምረዋል።ከእነዚያ ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ አካላት ትግላቸውን ከውጭ አድርገው በማቀጣጠል ኢሕአዴግን ዐቅም አሳጥተው ኢትዮጵያን ከአደጋ እንደሚታደጓት ያስቡ ነበር። ሕዝቡም በተወሰነ በእነዚህ አካላት ላይ ተስፋ ማድረግ ጀምሮ እንደነበረ አስታውሳለሁ። በተለይም በኤርትራ መሽገው ትግል ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ አካላት በአንድም በሌላም መንገድ ከዲያስፖራው ወገን የተለየ ድጋፍ ስለሚቸራቸው፣ የሚዲያ ትኩረትን ያገኙም ስለነበር ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በኢሕአዴግ ላይ ተጽዕኖ ፈጥሮ ድርጅታችንን ዐቅሙን አዳክመው እንደሚጥሉት ከፍተኛ ግምት ነበራቸው። እውነታው ግን ከዚያ የተለየ ነበር።

በኢንሳ ቆይታዬ ወቅት በውጭ ሆነው ትግል የሚያደርጉ ኃይሎች ያለባቸውን ሁለንተናዊ ውሱንነት መረጃ የማግኘት ዕድል ነበረኝ። እነዚህ ኃይሎች የዐቅማቸው ልክ በየሰው አእምሮ ውስጥ እንደገዘፈውና በሚዲያ

እንደሚነገረው እንዳልሆነ፣ ኢሕአዴግንም በአጭር ጊዜ የማንኮታኮት ዐቅም እንደሌላቸው መገንዘብ ችዬ ነበር። ይኸም “ከውጭ በመታገል በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር መፍታት" የሚለው ሐሳብ እምብዛም እንደማያዋጣ፣ ለማሸነፍም በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ጠቁሞኛል። ስለዚህ ሀገራችን የተጋረጠባትን አደጋ ለመከላከል ትግል መደረግ ያለበት ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ እንደሆነ ሙሉ ለሙሉ አምን ጀመር። ችግሩ ግን ከውስጥ የሚደረግ ትግል እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ በመሆኑ ነገሮችን ማክበዱ አልቀረም።

አንድ ወጣት ወታደር ነው አሉ... ብዙ ስኬቶችን ወደአስመዘገቡ ከፍተኛ ጀኔራል ዘንድ ሄዶ ስለሕይወት ልምዳቸው እንዲነግሩት ይጠይቃቸዋል።

“አለቃዬ! ለመሆኑ የስኬትዎ ምስጢር ምንድን ነው?”

የጀኔራሉ ቤት በብዙ ኒሻኖችና ሽልማቶች የተንቆጠቆጠ ነው። ወታደሩ የጀኔራሉን ሽልማቶች አይቶ እየቋመጠ “እኔም እንደርስዎ ስኬታማ መሆን እፈልጋለሁ፤ እባክዎ ይምከሩኝ?" ይላቸዋል። ይኼን ጊዜ ጀኔራሉ ወጣቱን ወታደር ለሦስት ደቂቃ ያህል አተኩረው ካዩት በኋላ አንድ ትእዛዝ ይሰጡታል። ትእዛዙ ላይ ላዩን ሲታይ ቀላል የሚመስል ነገር ግን ሕይወቱን ሊያሳጣ የሚችል ትእዛዝ ነበር። በውኃ የተሞላ አንድ ብርጭቆ እንሥተው ከሰጡት በኋላ፣ በአገጫቸው ከቤቱ በቅርብ ርቀት ወደሚገኝ የወታደር ማሠልጠኛ እየጠቆሙ፤ “ሄድና ያንን የማሠልጠኛ ሜዳ አምስት ዙር ዞረህ ተመለስ። ታዲያ ከዚህ ብርጭቆ ላይ ጠብታ ውኃ መፍሰስ የለበትም፤ ስናይፐር ይዞ የሚከታተልህ ወታደር _ እመድባለሁ፤ ከብርጭቆው ውኃ ሲፈስ ከተመለከተህ ይተኩስብሃል” አሉት።

ለወጣቱ ያልጠበቀው ዱብ ዕዳ ነበር።

በተሰጠው ትእዛዝ ተደናግጦ አንዴ ብርጭቆውን፣ አንዴ ጀኔራሉን ሲመለከት ቆየና እየፈራም ቢሆን የሞት ሞቱን ተነሣ፤ ትእዛዙን ሊፈጽም። ዐይኑን ከብርጭቆው ላይ ሳይነቅል በጥንቃቄ እየተራመደ እንደ ምንም ማሠልጠኛው ጋ ደረሰ። ከዚያም ቀስ በቀስ አንድ ዙር፣ ሁለት ዙር እያለ ሦስት ዙር ሲሄድ መንገዱ እየቀለለው መጣ። በዚህ መልኩ ቀጣዮቹን ዙሮች በደንብ ራመድ ራመድ እያለ፣ ፍጥነቱን እየጨመረ ሄዶ አንዲት ጠብታ መሬት ሳትነካበት ዙሩን ጨርሶ ጀኔራሉ ዘንድ ደረሰ። ልክ እንደደረሰ የጀኔራሉ ጥያቄ ቀጠለ፤

“ለመሆኑ እነዚያን ቆነጃጅት ኮረዶች ራቁታቸውን ሲደንሱ አይተሃቸዋል?” አሉት። “አላየኋቸውም ጌታዬ” ሲል ወጣቱ መለሰ።

“ከማሠልጠኛው አጠገብ ያሉትንስ ስፖርተኞች ሲደባደቡ አላየሃቸውም?”

“አዎ ጌታዬ... አላየኋቸውም!”

“ከዚያ ከዓሣ ቤቱ የሚወጣው የዓሣ ጥብስስ አልሸተተህም?”

“እንዲያውም... አልሸተተኝም!”

ይኼን ጊዜ ጀኔራሉ ወጣቱን ለአፍታ ትክ ብለው ከተመለከቱት በኋላ፤ “አየህ! ዓላማህ ላይ ስታተኩር ስኬታማ

ትሆናለህ፤ ሕይወትህንም በከንቱ አታጣም። አሁን ምክሬን ጨርሻለሁ፤ መሄድ ትችላለህ።” ብለው አሰናበቱት።

የጀመርነው ከውስጥ ሆኖ የሚደረግ ትግል የውስጥ ዐርበኛነት መሆኑ ግልጽ ነው። ያ ደግሞ ምን ቅጣት እንደሚያስከትል ጠንቅቄ ዐውቀዋለሁ። የውስጥ ዐርበኝነት ክፋቱ ግማሽ ስኬት ብሎ ነገር አለመያዙ ነው። በውስጥ ዐርበኝነት ውስጥ ወይ በስኬት ትጨርሳለህ ወይም በዜሮ ትቀራለህ፤ ግማሽ ድል ብሎ ነገር የለም። በሌላ ሳይሆን በዚህ መርሕ ነው የሚመራው። ትኩረት ሳያደርጉ የሚደረግ ጉዞ ትግሉን ከማሰናከል አልፎ ከባድ አደጋ ያስከትላል። ጥንቃቄ ሳያደርጉ መጓዝ በከሀዲነት አስፈርጆ ማሳሰር ብቻ ሳይሆን ያስገድላል። የዚህ ደግሞ ትልቁ ጉዳቱ መሞቱ አይደለም፤ በውርደት መታወሱ እና የተጀመረው ትግል መቀጨቱ እንጂ። በዚህ ምክንያት ከውስጥ ሆኖ መታገል በእሳት የመጫወት ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ቢገባኝም ከዚያ የተሻለ አማራጭ ግን ሊታየኝ አልቻለም። ከውስጥ የተደራጀና ጠንካራ ኃይል ካልተፈጠረ በስተቀር ሥርዓቱን ማስተካከልና መለወጥ እጅግ አዳጋች እና ጊዜ ወሳጅ እንደሆነ ግልጽ ነበር። ይኸም በጥንቃቄና ጥበብ በተሞላበት አካሄድ መደገፍ ይኖርበታል።

ጀኔራል ከማል ገልቹና ኮሎኔል አበበ ገረሱ ወደ ኤርትራ ለመሄድና ከዚያ ሆነው ለመታገል የወሰኑ ሰሞን መረጃ ደርሶኝ ነበር። እናም ሁለቱን ግለሰቦች ከአባዱላ ጋር በመሆን ረጅም ጊዜ ወስደን ለማነጋገር ሞከርን። በሰዓቱ በድርጅታችን ውስጥ በምናያቸው ችግሮችና እነዚያን ችግሮች ለመፍታት ከፍተኛ የሆነ ትግል እንደሚያስፈልጋቸው ቅንጣት ታህል ልዩነት አልነበረንም። ሆኖም ግን በመሠረታዊ ጉዳዮች ብንግባባም የትግል ስልቱ ‹‹ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ ነው›› የሚለው ነገር እኛና እነሱን የተለያየ አቋም እንድንይዝ አደረገን። እኛ “ተደራጅተን ከዚሁ ሆነን ዐቅማችንን አጠንክረን እንታገል፣ ስደት ውጤታማ አያደርገንም” ስንል፤ እነሱ ደግሞ “የለም. እዚህ ሆነን ለውጥ አናመጣም" በሚለው አቋማቸው ጸኑ። መጀመሪያ ላይ በአቋም የተግባባን መስሎን የነበረ ቢሆንም መጨረሻ ላይ ግን ንግግራችን ምንም መቋጫ ሳያገኝ ወደ ኤርትራ መሄዳቸው በሐሳባችን እንዳልተስማሙ አረጋገጠልን።

በትግል ውስጥ ተቀናቃኝን ለማዳከም መንቀሳቀስ እና ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣት መታገል ሁለት የተለያዩ አካሄዶች ናቸው። ተቀናቃኝን በተበታተነ መንገድ ሆኖ በማጥቃትም ማዳከም ይቻል ይሆናል፤ ማሸነፍ ግን አስቸጋሪ ነው። ለማሸነፍ መደርጀት፣ ለማሸነፍ ተናብቦ መንቀሳቀስና የጋራ ስትራቴጂን እየቀየሱ መንቀሳቀስ ይጠይቃል። የእኛ ፍላጎት ይህ ነበር።

ከእነ ከማልና አበበ በተጨማሪ፣ በተለያየ ሀገር ለትምህርትና ለሥራ የሚጓዙ የቅርብ ወዳጆቻችን ተሰደው እንዳይቀሩ፣ በቶሎ ተመልሰው ጠንከር ብለን እንድንታገል ብዙ ግፊት ማድረጋችንን አስታውሳለሁ። በተለይም ወደ ጀርመን ሀገር የሄዱት እነ ሻለቃ ተስፋዬ የማነ ሌሎች እሱን መሰል ጓደኞቻችን ጋር ንግግር እናደርግ ነበር። መሳፍንት ጥጋቡም የቅርብ ጓደኛችን ስለነበር ከእሱም ጋር ስለ ትግሉ ስንመካከር፤ እዚያ እንዳይቀሩና ተመልሰው መጥተው እንዲቀላቀሉን ስንወተውት ነበር።

በወቅቱ እየተበታተንን ከሄድን የምንፈልገውን ነገር እንደማናሳካና ሰብሰብ ብለን በመታገል ለውጥ ማምጣት

እንዳለብን በማመን ከመጠየቅ አልቦዘንም ነበር። ያም ሆኖ እንደፍላጎታችን ሳይሆን ቀርቷል። ብዙዎቹ እዚህ በነበሩበት ወቅት በገጠማቸው ምሬት የተነሣ መሰደድንና ባሉበት ቦታ ሆነው በተለያዩ መንገዶች መታገልን መርጠዋል።

እኛም ደግሞ በፊናችን በመሰለን መንገድ ከውስጥ ሆነን ለመታገል ወስነናል። ዋናው ነገር በትግላችን ሳንዘናጋ በጥንቃቄ መጓዛችን ነው፤ እንጂ የእኛ መንገድ በስኬት እንደሚጠናቀቅ ጥርጥር የለውም። የጀመርነው ትግል ለራሳችን እና ለሀገራችን ስንል የምናሳካው ግባችን ነው። መንገዱ አዳጋች ሊሆን ይችላል፤ ስንጀምር እንፈተን ይሆናል፤ ብዙ የሚያማልሉ ነገሮች ይገጥሙን ይሆናል። ሆኖም ግን አተኩረን በመጓዝ ትግሉን እናሳካለን። እንቅፋቶች ካሸነፉን፣ ልባችን ወደ ሌላ ከቀላወጠ ያለ ጥርጥር ባክነን እንቀራለን። ፈተናውን አልፈን ሁላችንም ስኬታማ ከሆንን ሀገራችን የምትሻገርበትን የለውጥ መንገድ እንቀይሳለን።

# "እግሮች ሁሉ ወደ ትክክለኛው የትግል ሜዳ ያመራሉ!"

የእግር ኳስ ግጥሚያ የሚካሄደው በእግር ኳስ ሜዳ እንጂ በእጅ ኳስ ወይም በቴኒስ ሜዳ ላይ አይደለም። ውጊያ ለማድረግም ሆነ በጦርነቱ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ትክክለኛውን የግጥሚያ ሜዳ ዐውቆ ለዚያ ራስን ማዘጋጀት ተገቢ ነው።

የኢንሳ አመራር የሆንኩት ወታደር እያለሁ ነበር። በዚያ ተቋም መሥራቴ ለብዙ ነገሮች ያለኝን መረዳት ከፍ አድርጎ ዐይኔን ቢገልጠውም ቦታው ለፖለቲካ ትግል ብዙም የሚመች አይደለም። በኢሕአዴግ ውስጥ ትግል የማድረግ ፍላጎቴ እያደገ ሲሄድ መከላከያ ውስጥ ሆኖ ትግሉን ማካሄድ ያን ያህል አዋጪነት እንደሌለው ገባኝ። እንዲሁም በሀገራችን ሕገ መንግሥትም የተከለከለ በመሆኑ ምክንያት መከላከያን ስለመልቀቅ ማሰብ ጀመርኩ። እናም በገዛ ፍቃዴ 1999 ዓ.ም. ላይ ከውትድርና ዓለም ለመቀጠል ወሰንኩ።

ከኦሕዴድ ጋር በመሆን ትግል ለማድረግ የወሰንኩ ጊዜ፣ ገና ከመከላከያ መልቀቂያ ሳልጠይቅ በፊት፣ በቅድሚያ ኦሕዴድ ውስጥ ከአሉ አመራሮች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር የሚያስችለኝን መደላድሎችን ማከናወን እንደሚገባኝ በማመን አንዳንድ ነገሮች ሠርቻለሁ። በተለይ አባዱላ ቀደም ብሎ ከመከላከያ በመልቀቅ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት የነበረ በመሆኑ ምክንያት በርካታ ሥራዎችን በጋራ ለመሥራት ችለን ነበር። ለምሳሌ የኦሮሚያን ሚዲያ መክፈት፤ በክልሉ የተለያዩ ሥልጠናዎችን መስጠት፤ በአስተዳደር ዙሪያ የሚታዩ የቴክኖሎጂ ውስንነቶችን ለመቅረፍ የክልሉን መስተዳድር ማገዝ፣ የግብርናውን ዘርፍ _ በተወሰነ _ ለማዘመን _ ስለሚቻልባቸው ሁኔታዎች በመመካከርና በማገዝ ከአመራሮች ጋር ያለንን መግባባት ከፍ እያደረግን ቆየን። በዚህም ምክንያት በኦሕዴድ ውስጥ አብሮ ለመታገል የሚያስችል፣ ትልቅም ባይሆን መጠነኛ ዕድል መፈጠር ጀመረ። ይሄንን ተከትሎ ነበር ከመከላከያ በይፋ መልቀቂያ አስገብቼ ወደ ሲቪል ሥራዎችና ወደ ፖለቲካው ዘርፍ ሰተት ብዬ የገባሁት።

በኦሕዴድ ውስጥ የተለየ ቅርበትና ወዳጅነት የነበረኝ ከአባዱላ ገመዳ፣ ከለማ መገርሳ እና ከወርቅነህ ገበየሁ

ጋር ነበር። ከሌሎች ጓዶች ጋር የመነጋገር፣ የመገናኘትና በጋራ ሥራዎችን የመሥራት ዕድል ቢኖረኝም፤ ከእነ ለማ፣ ወርቅነህ እና አባዱላ ጋር እንዳለኝ በብዙ ነገሮች ልብ ለልብ መግባባትና መተማመን ደረጃ ሳንደርስ ዓመታት ተቆጥረዋል። ምናልባትም ከእነ ለማ ጋር ትውውቃችን ከዚያ በፊት ዓመታትን የተሻገረ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም አንዳችን የሌላችንን ጀርባ የመጠበቅ የቆየ ልምድ ስለነበረን ሊሆን ይችላል፤ ብቻ በትግል ስትራቴጂ ደረጃ ዝርዝር የሆኑ ምክክሮችን ለማድረግ እደፍር የነበረው ከእነሱ ጋር ነበር። ወደ ፖለቲካው መስመር ካቀናሁ ወዲህ ከሦስቱ ጓዶቼ ጋር ብዙ የትግል ስትራቴጂዎችን ነድፈናል። ነገሮች እንዴት መቀየር እንዳለባቸው ሰፋፊ ጊዜዎችን እየወሰድን እንወያይ፣ ሐሳቦችን እንጋራ፣ አካሄዳችንን በጥበብ የተቃኘ እንዲሆን እንመካከር ነበር። አልፎ አልፎ ምክክራችን በጽሑፍ መልኩ ተዘጋጅተው የሚካሄዱ ነበሩ። ታዲያ የጀመርነው ትግል እንዳይሰናከል የተለያዩ ጥንቃቄዎችን ከማድረግ አልተቆጠብንም ነበር።

በዚህ መልኩ ምክክራችን ቀጥሎ የምናዘጋጃቸውን ጽሑፎች ከእኛ ቡድን ውጭ ለሆኑ አካላት ጭምር ማሳየት መጀመር እንዳለብን ተስማምተን በ2004 ዓ.ም. አካባቢ አንድ ጽሑፍ አዘጋጀን። ጽሑፉ ጠንከር ጠንከር ባሉ የሪፎርም ጉዳዮች ዙሪያ የሚያጠነጥን ነበር። ይኸንን ጽሑፍ ይዘን የኦሕዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አጀንዳ ይዞ እንዲወያይበት ጥያቄ አቀረብን።

“የራስህን ዕቅድ ዲዛይን ካላደረክ ዕጣ ፈንታህ በሌሎች ዕቅድ ውስጥ መኖር ይሆናል” የሚሉት አባባል አለ። የዚያን ዘመኑን ኦሕዴድ በትክክል የሚገልጽ አባባል ነው ማለት ይቻላል። በወቅቱ በኦሕዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ለውይይት የሚቀርቡ አጀንዳዎች ምንጫቸው ሁለት ነበር። አንደኛው እዚያው ባሉ የኦሕዴድ የበላይ አመራሮች የሚዘጋጁ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በኢሕአዴግ ከፍተኛ አመራሮች የተዘጋጁ ሰነዶች ቃል በቃል ወደ ኦሮምኛ ተተርጉመው ይመጣሉ። ከዚያ ውጭ የማድረግ ባህል በድርጅቱ ውስጥ አልነበረም። በመሆኑም እኛ ሪፎርም ያስፈልጋቸዋል ባልናቸው ጉዳዮች ላይ ጽሑፍ አዘጋጅተን አጀንዳ ለማስያዝ ስንጠይቅ ከፍተኛ የሆነ ውዥንብር ፈጠረ። ይሄንን ተከትሎ ‹‹አጀንዳው ይያዛል አይያዝም›› በሚል ጭቅጭቅ ተነሥቶ ቀኑን ሙሉ በክርክር አሳለፍን። ማታ ስብሰባው ተጠናቆ ሁላችንም ወደየቤታችን ስንበታተን ስለተነሣው ክርክር ‹‹አጀንዳው ተይዞ፣ ነገር ግን ውይይቱ የሚደረገው ከሁለት ሳምንት በኋላ ነው›› የሚል ውሳኔ ተላልፎ ነበር።

ታዲያ የዚያን ሰሞን ‹አጀንዳ ይያዝ› ባልነው ሰዎች ላይ የተከፈተ ዘመቻ አይጣል ነበር!! ለሁለት ሳምንት የቆየ ዘመቻ ተደረገብን። ‹‹ድርጅት ልናፈርስ ታጥቀን የተነሣን›› ተደርጎ በድርጅታችን ውስጥ ሲነገር ተከረመ። ነገሩ ወደሌሎች እኅት ድርጅቶችም ተዛምቶ ከዚህም ከዚያም “ድርጅት አፍራሾች" የሚል ታርጋ ይለጠፍብን ጀመር። እኛ አስበንበት ቀደም ብለን የተዘጋጀንበት ነገር ባይሆን ኖሮ በእጅጉ እንበረግግ ነበር።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ከዘመቻው ጎን ለጎን ለካ ሌላ ጽሑፍ እየተዘጋጀም ኖሯል፤ እኛ ምንም አላወቅንም። ልክ ለእኛ አጀንዳ የተቀመጠው ጊዜ ደርሶ ለውይይት ልንገባ ስንል እነሱ ባዘጋጁት ጽሑፍ ላይ እንደምንወያይ ተነገረን።

ወዲያው እኛም በጎን ተገናኝተን እነሱ _ ስለአዘጋጁት ጽሑፍ ያሉንን መረጃዎች አሰባስበን፣ ክፍተቶችን ነቅሰን፣ እጅግ ጠንካራ የሚባልና ለቀናት የዘለቀ ክርክር አደረግን። ከፍተኛ የሆነ ሌብነት እንዳለ፤ ሕዝብ እየተበደለ

ስለመሆኑ፤ ዝርክርክነትና ዝርፊያ ስለመስፋፋቱና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ በማስረጃ ጭምር እያስደገፍን ተከራከርን። እነዚህንም የሚያደርጉት በዋናነት ከፊት ለፊት ያሉት ከፍተኛ አመራሮች መሆናቸውን ጠቀስን። እነሱ ከፊት ሆነው እየመሩ እንደ ክልል በኦሮሚያና እንደ ሀገር _ በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ሊመጣ ከቶ እንደማይችል መናገር ስንጀምር፤ በድርጅቱ ውስጥ ከዚያ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ድንጋጤ ተፈጠረ።

ምንም እንኳን የዚያን ጊዜው ድንጋጤ በድርጅቱ ውስጥ ተጨባጭ ውጤት አስገኝቶ የነበረ ባይሆንም፤ የኋላ ኋላ ኦሕዴድ ወደ ሁለት ጎራ እንዲከፈል ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል። ጥቂት የማይባሉ የድርጅቱ አባላት ዐይናቸውን እንዲያማትሩ እና ቀልባቸው ወደ እኛ እንዲሳብ ያደረገ የመጀመሪያው አጋጣሚ ነበር ማለት ይቻላል። ከዚያን ጊዜ ወዲህ አብዛኛው የኦሕዴድ ማዕከላዊ አባል በይፋ እጁን አውጥቶ የእኛን አጀንዳዎች ለመምረጥ ሙሉ ድፍረት ባያገኝም ወይም በድርጅቱ ውስጥ እኛ የኃይል የበላይነት እንድንይዝ ባያደርገንም፤ ዓላማችን ነጻነትና እኩልነትን ግቡ ያደረገ ድርጅት መፍጠር መሆኑን ተገንዝቦ አባላቱ በሚገባ እንዲያውቀን አስችሎናል። ትግላችን ከእውነት ጎን ለመቆም ያለመ እንደሆነ አባላቱ እንዲያውቅ የፈጠረው ዕድል እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አልነበረም።

በሀገራችን አንድ አባባል አለ። "የነብርን ጭራ አይዙም፤ ከያዙም አይለቁም" ይባላል። ያቺ የኦሕዴድ ማዕከላዊ መድረክ ላይ ያነሣናት አጀንዳ ላይ ላዩን ስትታይ ኩራት ውስጥ የምትከተን ብትሆንም የጊዜ ጉዳይ እንጂ አንድ ቀን ይዛን እንደምትጠፋ እናውቅ ነበር። ስለዚያም እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ ብሎ ነገር ከሐሳባችን እንዲወጣ አደረግን።

ከዚያ ይልቅ ከቀደመው ጊዜያችን በበለጠ መሥራትና ራሳችንን ለሚመጣው ነገር እያዘጋጀን መቆየት አለብን። ዳክዬ በውኃ ላይ ስትንሳፈፍ ከላይ ሆኖ ለሚያያት ሰው ውኃው ራሱ እየገፋት ተረጋግታ ፍስስ እያለች የምትጓዝ ትመስላለች። ሆኖም ግን ከውኃው በታች ያሉት እግሮቿ በከፍተኛ ኃይልና ፍጥነት ይወራጫሉ። እኛም አካሄዳችንን እንደዚያች ዳክዬ ማድረግ እንዳለብን ዐውቀን ተንቀሳቀስን። ከድርጅቱ አባላት ውስጥ ለጊዜያዊ ጥቅም ሲሉ ሊደለሉ የማይችሉትን እና ጠንካራ አቋም ያላቸውን ሰዎች እየለየን ቆየን። ባገኘነው አጋጣሚ ድርጅቱ የደከመባቸውን ጉዳዮች እየገመገምን ከአባላት ጋር በሚኖረን የሁለትዮሽ ቆይታ ወቅት ሐሳብ በማንሣት እናስገነዝባለን።

ይኽም ቀስ በቀስ የእኛ ድምፅ በሌሎች በኩል መሰማት እንዲጀምር እና እኛ ላይ ብቻ የሚሰነዘሩ ዐይኖች ወደ ሌሎች አቅጣጫም እንዲበተን አገዘ። በዚህ መልኩ ዐቅማችንን በደንብ ካደረጀን በኋላ ደረጃውን ከፍ ለማድረግ ተስማማን።

አዎ! ትግሉን ለማጠናከር በኦሕዴድ መታጠር የለብንም። በኢሕአዴግ ምክር ቤት ላይም ጠንከር ያሉ ሐሳቦችን በማንሣት መሰል አቋም ያላቸውን ሰዎች መሰብሰብ ያስፈልገናል። ይኽንን ለማድረግ ግዴታ ከሌሎች ጋር መነጋገር አስፈላጊ አልነበረም። በምክር ቤቱ የተለያዩ የሪፎርም አጀንዳዎች በሚነሡበት ጊዜ በውስጠ ታዋቂነት በሐሳብ ደረጃ የሚግባቡን ሰዎች እየበዙ መምጣታቸው አልቀረም። ይኽም በሻይ ዕረፍትም ሆነ ከስብሰባ ውጭ ባሉ ጊዜዎች ተቀራራቢ አቋም ካላቸው ሰዎች ጋር የመነጋገርና አብሮ የመብላት

ዕድሎችን ፈጥሮልናል። እንደነ አምባቸው መኮንን፣ ገዱ አንዳርጋቸው፣ ብናልፍ አንዷለም እና ተስፋዬ ጌታቸው ያሉ ሰዎች በጋራ መድረኩ ላይ ደፈር ብለው ለመናገር ወደ ኋላ የማይሉ ሰዎችን ማግኘታችን ይበልጥ ብርታት እንደሆነን ጥርጥር የለውም። ቀስ በቀስም ከብአዴን ጓዶች ጋር ያለን ቅርርብ እየተጠናከረ ሲመጣ በአንድ አፍ መናገር ወደ መቻል ደረጃ የደረሰ ግንኙነትና ትስስር ተፈጠረ።

እኛና የብአዴን ጓዶችን በአንድ ሜዳ ላይ እንድንቆም፣ ልብ ለልብ እንድንግባባ ያደረገንም ሌላ ሳይሆን የሕዝባችን ሁኔታ እና የሀገራችን ጉዳይ ነበር። በርግጥ ሌሎች "እሳትና ጭድ" ብለው የሚያስቧቸውን ሕዝቦች ስለወከልን የጋራ የሚያደርገን አጀንዳ መቼም የማይፈጠር መስሏቸው ነበር። እኛ ግን ኢትዮጵያን ከሚመጣው አደጋ እንዴት አድርገን ማዳን እንደምንችል እና ሀገራችንን ወደ ትክክለኛው የዴሞክራሲ ጎዳና _ ስለማስገባት አስፈላጊነት ልብ ለልብ እየተመካከርን፤ በመካከላችንም የተሻለ መቀራረብ፣ የተሻለ መደጋገፍና መተማመን መፍጠር ቻልን። ይኽም በኢሕአዴግ ውስጥ ድምፃችን ጎልቶ እንዲሰማ አደረገ።

ወቅቱ በሀገራችን የ2007 ዓ.ም. ምርጫ ተካኺዶ፣ ኢሕአዴግ የፓርላማ መቀመጫን መቶ በመቶ ማሸነፉን በገለጸ ማግስት ጥቂት ወራት እንዳለፉ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ተቃውሞዎች የተነሡበት ጊዜ ነው። አጋጣሚው ከሁለታችን ግንኙነት መጠናከር ጋር ጥሩ ግጥምጥሞሽ ፈጠረ። ኢሕአዴግም ከየአቅጣጫው ተጽዕኖ ሲበዛበት የተለያዩ የግምገማ፣ የሥልጠናና የጥልቅ ተሐድሶ እንቅስቃሴዎችን ማከታተሉን ተያያዘው።

በተለይ ሥልጠናዎች ሲዘጋጁ የቀድሞ ቱባ ቱባ ባለሥልጣናት በአሠልጣኝነት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ካድሬዎች በተሰብሳቢና በሠልጣኝነት ይታደማሉ። እነዚህን አጋጣሚዎች በጋራ መጠቀም እንደሚያስፈልገን ተግባብተናል። እናም ጠንከር ጠንከር ያሉ ሐሳቦችን በእነዚያ መድረኮች ላይ በማቅረብ ካድሬው እነዚያን ሐሳቦቻችንን እንዲቀበል ማድረግ ቻልን። በአሠልጣኝነት የሚመጡትንም በዕውቀት በመፈተን አዲስ እየተወለደ ባለው የለውጥ ኃይል እና በእነሱ መካከል ያለውን የአካሄድ ልዩነት በማሳየት ከጎናችን የሚሰለፉ ሰዎችን አበዛን።

በዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ዴሞክራሲና ለውጥ የመፍጠሪያ ምዕራፎች በተለያየ ጊዜ ተከፍተው ነበር። ግማሽ ምዕተ ዓመት ባልሞላ አጭር ጊዜ ውስጥ (በ1966፣ በ1983 እና በ1997 ዓ.ም.) ታላላቅና ተከታታይ የፖለቲካ ምዕራፎች ተከፍተው አዲስ ለውጥ የመጀመር ዕድሎችን አግኝተን ነበር። ብዙዎቹን በውኑ ሳንጠቀምባቸው፣ በተራ ጉዳዮች ተጠምደን ባክነዋል።

ታላቁ የሀገራችን ደራሲ በዓሉ ግርማ በአንድ ወቅት እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር። "ነጻነትን እንካ ብሎ የሚሰጥ ማንም የለም፤ ነጻነት በትግል ነው የሚገኘው፤ ለዚያ ደግሞ ቆራጥነትን ይጠይቃል።"

ኦሕዴድን ነጻ አድርገን በሙሉ እግሩ እንዲቆም ማድረግ ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣት ወሳኝ እርምጃ እንደሆነ መግባባት ላይ ከደረስን ረጅም ጊዜ ሆኖናል። ሆኖም ግን ይኼንን በሙሉ ዐቅም የመፈጸም ምቹ ጊዜ ያገኘነው በ2008 ዓ.ም. ክረምት ላይ ነበር። ድርጅቱ እንደ ድርጅት ነጻና ራሱን የቻለ እንዳይሆን በረጅም ገመድ ለመጎተት መሣሪያ ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩ ሰዎች ቁልፍ ቦታቸውን የሚያጡበት እና የለውጥ ቡድኑ ሁለንተናዊ የበላይነት የተቀዳጀበት ጊዜ በመሆኑ 2008 ዓ.ም. በለው ታሪክ ደምቆ የሚጻፍ ዓመት ሆኗል።

በዚያ ክረምት ድርጅታችን ጉባኤውን ለማድረግ ሲጠራ በጉጉት ስንናፍቀው የነበረው ጊዜ እንደመጣ ተገንዝበን ዕድሉን ላለማባከን ወስነን ነበር የገባነው። በዚያኛውም ጎራ ቀላል ፈተና አልነበርም የገጠመን። ሆኖም ጉባኤው ሲጠናቀቅ የኦሕዴድን ምክር ቤትና የሥራ አስፈጻሚ ወንበሮቹን በማያሻማ የበላይነት ለመቆጣጠር ተችሏል። የለውጥ ሐሳብን የሚደግፉና የተሻለ አቋም ያላቸው በርከት ያሉ ግለሰቦችን የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ማድረግ ተቻለ። ኦሕዴድ ውስጥ በወሳኝ ጉዳዮች ላይ በአብላጫ ድምፅ መወሰን የሚያስችለንን መሠረት ፈጠርን።

የኦሕዴድን ነጻነት በሚገባ ካረጋገጥን በኋላ አካሄዳችንን ዳግም በዳክዬዋ የጉዞ ጥበብ መቃኘት ጀመርን። ግልጽ የሆነ፣ ኃይል የተቀላቀለበት፣ ለሚዲያ ግብዓት የሚውል የትግል ስልትን አስወግደን እግር የመትከል ሥራዎችን አደረግን። አሁን ለኦሕዴድ አጀንዳ ለመስጠት የሚሞክርም የለም። ቢላክም በቀላሉ ከመቀልበስ ወደ ኋላ እንደማንል ግልጽ ነበር።

ተቀናቃኞችን ኦሕዴድ መድረክ ላይ ከእኛ ጋር መታገል እንደማይሆንለት ሲገባው እኛን የማሸማቀቅ ተግባሩን ወደ ዋናው የኢሕአዴግ መድረክ ወሰደው። ሐሳቦችን ስንሰነዝር ሐሳቦቻችን ጠቃሚ እንዳልሆኑ ማሳየት፣ ገፋ ሲልም ፍርሀት ለመፍጠር የተለዩ ክትትሎችን ወደ ማድረግ ተሸጋገረ። ለዚህም የደኅንነት ሰዎች ትብብር እያደረጉላቸው እኛን መከታተልና ማሸበር ዋነኛ ሥራቸው አድርገው ባላቸው ዐቅም ሁሉ ይተጉ ነበር። ይኽ እንቅስቃሴያቸው በተቃራኒው ተቀናቃኞቻችን ዐቅማቸው መዳከሙን ስላመለከተን ጠቀመን እንጂ አልጎዳንም።

በዚህ መሐል የ2009 ዓ.ም. መግቢያ ሰሞን፣ አንድ ዓመት ከሠራሁበት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትርነት ያለበቂ ምክንያት እንድነሣ ተወሰነ። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ትግሉን ለማጠናከር ወደ ፖለቲካ መድረክ መግባቴ አስፈላጊነቱ ታይቶኝ ከውትድርናው ዘርፍ ከወጣሁ ዐሥር ዓመታት አልፎኛል። ታዲያ በፖለቲካውና በሲቪል ሥራዎቼ የሳይንሳና ቴክኖሎጂ ሚኒስትርነት ከፍተኛው የሐላፊነት ደረጃ ነበር። በዚያ ሳለሁ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ የሚያስደስቱና ተገቢ የመሰሉኝን ሥራዎች አከናውኛለሁ። የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትርና ምክትላቸውን ጨምሮ በተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ ከሚሠሩ ሐላፊዎች ዘንድ የሚያስመሰግን ሥራ እንደሠራሁ አስተያየቶች ይሰጡ እንደነበር አስታውሳለሁ።

ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትርነቴ የመነሣቴ ዜና ሲሰማም ብዙ ሰዎች መደንገጣቸው ትዝ ይለኛል። ለምን? ብለው የሚጠይቁ ጋዜጠኞች፣ እንዴት? ብለው የሚደነቁ መጽሔትና ጋዜጦችም ነበሩ። በወቅቱ የኦሕዴድ የሥራ አስፈጻሚ አባል የነበርኩ ቢሆንም እኔን ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ለማንሣት የኦሕዴድ ዕውቅናና ፍቃድ አልተጠየቀም። የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚም ፈቃድ አልተጠየቀም፤ እንዲያውም ተቃውሞ ጭምር ያስነሣ ነበር። ሊቃነ መናብርቱ አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ እና አቶ ደመቀ መኮንን ፍላጎታቸው አልተጠየቀም። ድርጅትን ከውድቀት ለማዳን በሚል ከጡረታ ተመልሶ ዳግም ወደ ድርጅቱ የተቀላቀለው ኃይል ቤቱን ዘግቶ ሲመካከር ቆይቶ፣ እኔ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እንድነሣና ወደ ክልል እንድዛወር ወስኖ መጣ። ለዚያ ውሳኔ ያበቃው በሳይንስ ቴክኖሎጂ የነበረኝ አፈጻጸም ተገምግሞ እንዳልሆነ ሁላችንም እናውቅ ነበር። ፍላጎታቸው የእኛ አካሄድ የትም እንደማያደርስ ለማሳየት፣ ለሌሎች እንደኛ ለሚደፍሩ የለውጥ አመራሮች

ትምህርት እንዲሆን አስበው እንደነበር ግልጽ ነው። እኔም ውሳኔያቸውን ከመግፋት ይልቅ አጋጣሚውን እንደ መልካም ዕድል በማሰብ ተቀበልኩት። ወደ ክልል መሄድ ብዙ ነገሮችን ለማስተካከልና ኃይል ለማሰባሰብ ጥሩ መደላድል ሆኖም አገኘሁት።

ወደ ኦሮሚያ ከሄድኩኝ በኋላ ከለውጥ ቡድኑ ጋር በመናበብ ሰፋፊ ሥራዎችን ሠራን። ሥልጠናዎችንና የምክክር መድረኮችን በማድረግ በዚያ ያለው አመራር የማሸነፍ ሥነ ልቦና እንዲጨብጥ አደረግን። ከካድሬው ባለፈ በክልሉ ከሚገኙ የዩኒቨርስቲ መምህራን፣ ከሌሎች ምሁራን፣ ከኦሮሞ አርቲስቶች፣ ከባለ ሀብቶች እና ከሌሎች ሊያግዙን ከሚችሉ አካላት ጋር ምክክሮችን ለማድረግ፣ ሐሳብ ለመለዋወጥ፣ ስለ ለውጥ ለመነጋገርና ለመወያየት ዕድል አገኘን።

ለረጅም ዘመን ኦሕዴድ ዐቅሙን ሳያውቅ በቀጭን ገመድ ቁጥቋጦ ላይ ታስሮ እንደቆመ ፈረስ እንደነበር በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ለብዙ ሺሕ የኦሕዴድ አመራር ማስረዳትና መተማመን ላይ መድረስ ቻልን። ያ ጊዜ አሁን አክትሟል። በሥነ ልቦና ተሸንፎ አጀንዳ ተቀባይ መሆን አብቅቷል። ኦሮሚያ ላይ ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀስን በምናሠለጥንበት ወቅት፤ በዚያ ካለው አመራር ጋር ልብ ለልብ በመነጋገር ስትራቴጂዎችን በመንደፍና የሚፈጠሩ የቦታ ክፍተቶችን በመሸፋፈን ተደራሽነታችንን ማስፋት ችለናል። በዚህ ስለሚመስል ተቀናቃኞቻችን የደከምን፣ ወቅት አካሄዳችን የዳከዬዋን ጉዞ የተሸነፍንላቸውና እንደጠፋን አድርገው እንዲያስቡ ዕድል ፈጥሮልናል። እኛም በተቻለን ዐቅም ውስጥ ውስጡን አመራሩን በሚገባ ለማደራጀት ቻልን።

በዚህ መልኩ አመራሩን አደራጅተን፣ ከምሁራን ጋር ጥብቅ ትውውቅ ከፈጠርንና ከተወሰነው የዳያስፖራው ማኅበረሰብ ጋር ምክክር ካደረግን በኋላ፤ የበለጠ መሠረታችንን ለማጠናከር አጠቃላይ ማኅበረሰቡን ለማንቀሳቀስ ስትራቴጂ ነድፈን ወደ መተግበር ተሸጋገርን። በዚያን ወቅት ነበር በኦሕዴድ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ለአምስት ዓመት ስትራቴጂ የቀረጽነው። የዚያን ጊዜ በድርጅት ደረጃ ስትራቴጂክ ዕቅድ ማዘጋጀት የተለመደ አልነበረም። በእርግጥ ኢሕአዴግም እንደ ግንባር አዘጋጅቶ አያውቅም። በኦሕዴድ ውስጥም ታስቦ አያውቅም። ይሄም አንድ ሰሞን በኢሕአዴግ ውስጥ መነጋገሪያ ሆኖ ቆየ። እኛ ኅብረተሰቡን የማሳተፍ ፍላጎታችን ከፍተኛ ስለነበረ የኢኮኖሚ አብዮት ብለን እንቅስቃሴዎችን ጀመርን። ወጣቱ ተጠቃሚነቱን እንዲያረጋግጥ እንዲደራጅ ዐውዶችን ፈጠርን። የኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትዎርክ ላይ መጠነኛ የአሠራር ማሻሻያዎችን በማድረግ የሕዝብን ጥያቄ እንዲያነሣ ተደረገ። ባለሀብቶች፣ ምሁራንና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲቀላቀሉን በማድረግ፤ ትግሉ ከእኛ ወጥቶ ወደ ሕዝቡ እንዲገባ ለማድረግ ተንቀሳቀስን።

የምንታገለው ለማሸነፍ እንደሆነ፣ ሕዝቡም ለዚያ እንዲዘጋጅ በግልጽ በአደባባይ በመድረኮችና በሚዲያዎች ላይ መግለጽ ጀመርን። ይህ እንግዲህ በክልል ደረጃ ያለው ነው። ከክልል ውጭ በተለይም ከአማራ ክልል አመራሮች ጋር ከፍተኛ የሆነ ጥምረት ፈጥረን ትግሉን በጋራ ማከናወናችንን ቀጠለን። የኦሮማራ ፕሮግራሞችን በመንደፍ፤ "እምቦጭን በጋራ እንከላከል" ዓይነት እንቅስቃሴዎችን ማድረጋችን የሁለቱን ክልል ሕዝቦች ግንኙነት ከማጠናከር በዘለለ ትግሉን በእጅጉ አግዟል። በደቡብ ካሉ አንዳንድ ዞኖች ጋርም በተወሰነ ግንኙነት ለመፍጠር ችለን ነበር። በዚህ መልኩ ጉዳዩ ሀገራዊ መልክ መያዝ ሲጀምር በተቃራኒው የቆመው ኃይል

በንግግር ማሸነፍ እንደማይችል ሲገነዘብ ወደ ኃይል እርምጃ ለመግባት እንቅስቃሴ ጀመረ። ትግሉን ከፊት ሆነን በምንመራው አመራሮች ላይ ክትትል ማድረግ ተጀመረ፤ የምንሄድበትንና የምንገባበትን ብቻ ሳይሆን የምናወራውን ጭምር ለመስማት ስልካችንን መጥለፍ የዘወትር ሥራቸው ሆነ። ከአንድም ሁለት ሦስት ጊዜ እኛን ለማሰር ማዘዣዎችን ማዘጋጀት፤ በግል ሲያገኙንም ሆነ በስብሰባ ላይ የሚያሸማቅቁ ንግግሮችና ስድቦችን በመናገር፣ ትግላችንን እንድናቋርጥ የመጨረሻ ሙከራዎችን ማድረግ ቀጠለ። አልፎ አልፎም ሽምግልና መላክ፤ ባስ ሲልም ሀገር ጥለን ካልሄድን እንደምንጠፋ በመልእክተኛ በኩል ምክር መስጠትና የመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል።

እነዚህ እንቅስቃሴዎች ለእኛ ብርታትን እንጂ ድክመትን አላመጣብንም ነበር። ያ በዝባዡ ኃይል ዐቅሙ መዳከሙን በግልጽ ስለጠቆመን ትግላችንን ማፍጠንና ጊዜ ሳንሰጥ ማሸነፍ እንደሚገባን ተገነዘብን። በየስብሰባዎች ላይ ያለ ፍርሀት የሚደረግብን ክትትልና የስልክ ጠለፋ እንዲቋረጥ ስንጠይቅ፤ ሕዝቡም እንዲያውቀው ስንናገር፤ በዚህም ብዙ ሕዝብ ከጎናችን _ ሲሰለፍ፤ እኛን ማሰርና መግደል ትግላችንን እንደማያቋርጠው ሲገባቸው፤ እኛን ለመከፋፈልና ለማዳከም ተጨማሪ ጥረቶችን ቢያደርጉም፤ እጃቸው ላይ ያሉት ካርዶች ተሟጥጠው አልቀው ነበርና ጉዟችንን ማስቆም ሳይችሉ ቀሩ።

# እነዚያ የምጥ ቀናት!

ወርኃ የካቲት በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አይረሴ የለውጥና የነውጥ ወር በመሆን ይታወቃል። በጣም ብዙ ወደ ኋላ ርቀን ሳንጓዝ የዐድዋ ድልና አሳዛኙ የየካቲት 1 ጭፍጨፋ የተፈጸሙት በተመሳሳይ በየካቲት ወር ነው። የዐፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሣዊ አገዛዝ ያከተመበትና የአብዮት ፍንዳታ ዜና የተሰማበትም በዚሁ በየካቲት ወር ነው። የኢትዮ ሶማሊያ ጦርነት የመልሶ ማጥቃቱ ወሳኝ ምዕራፍ ተደርጎ የሚወሰደው የካራማራ ውጊያ በድል የተደመደመው በዚሁ በወርኃ የካቲት ነው።

የ2010 ዓ.ም. ወርኃ የካቲትም የዚሁ ግዙፍ የሀገራችን ታሪክ ተከታይ ሆኗል። የካቲት 6 ቀን፣ በዕለተ ሐሙስ የወቅቱ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የሥልጣን መልቀቂያ ዜና የተሰማበት ዕለት ነው። ሀገራችን በችግር መናጧን በመገንዘብ፣ የለውጥ ጥያቄውን ጥልቀት በመረዳት፣ አንድ ታሪካዊ ውሳኔ ወሰኑ። አቶ ኃይለ ማርያም የችግሩ ብቻ ሳይሆን የመፍትሔው አካል ለመሆን በማሰብ ከፓርቲና ከመንግሥት ሐላፊነት በፈቃዳቸው የሥራ መልቀቂያ ጥያቄ ማስገባታቸው በየዜና አውታሩ ተነገረ።

የለውጥ ቡድኑ ይኼንን የሥልጣን እለቃለሁ ጥያቄ የመጨረሻው መጀመሪያ አድርገን ወሰድነው። ለዚህም ከበቂ በላይ ምክንያቶች ነበሩን። ርምጃው አዲስ የግንባሩን ሊቀ መንበርና የሀገሪቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ወደፊት ለማምጣት ታላቅ አጋጣሚን የሚፈጥር ወርቃማ ዕድል ነበር። ይኽ ዕድል በጥንቃቄ ከተያዘና በጥበብ ከተመራ፤ መንኮታኮት የጀመረውን የላይኛውን የመንግሥት መዋቅር ከመውደቁ በፊት በተሐድሶ ጎዳና እንዲጓዝ ለማድረግ ያስችላል፤ የሚል እምነትን ፈጥሮ ነበር።

ምናልባትም ሥልጣን በለውጥ ቡድኑ እጅ ከገባ በሀገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለ ደም መፋሰስና ያለ

ፍጅት በሰላማዊ መንገድ፤ ሀገር አቀፍ ዴሞክራሲያዊ ሽግግርን መትከል የሚያስችል አዲስ የለውጥ ጎዳና ሀገራችንና ሕዝቦቿ ለማየት ይታደላሉ። በሌላም በኩል ይህ ክሥተት ብዙ ጥያቄዎችን አጭሯል። የፍጻሜው መጨረሻ በለውጥ ርምጃው ውስጥ ምን ትርጉም ይኖረዋል? እንደ ቡድን፣ እንደ ሀገርና እንደ ገዥ ፓርቲ የሚፈጥራቸው አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች ምን መልክ ይኖራቸዋል? አዎንታዊ ገጽታዎችን በማጠናከር አሉታዊ ጎኖቹን ለማመናመን ሊደረጉ የሚገባቸው ቅድመ ዝግጅቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን ስናወጣ ስናወርድ ቆየን። በወቅቱ እናምንበታለን ብለው የሚናገሩትን ትተው የሚቃወሙትን ነገር በተግባር የሚፈጽሙ ነበሩ። ይህ ሁኔታ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን ቅስም ሰባሪም ነበር። ዋነኛ ምክንያቱ ማድረግ ከመናገር በላይ መሥዋዕትነትን ስለሚጠይቅ ሊሆን ይችላል። ለፍትሕና ለሰብአዊ መብት ጠበቃ ሆኜ እንድቆም የተገደድኩባቸው አጋጣሚዎችን አንድ በአንድ በግልጽ አስታውሳለሁ። ይህም ለዛሬ ማንነቴ ጥሩ ልምድ እንደሆነኝ አልጠራጠርም። ጊዜው ሲመጣ ይኽንን ወደፊት በብዙ እናወራዋለን።

## የካቲት 6 ቀን 2010 ዓ.ም.

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ከኢሕአዴግ ሊቀ መንበርነትና ከጠቅላይ ሚኒትርነት ለመልቀቅ ጥያቄ ማቅረባቸው በጽ/ቤታቸው በሰጡት መግለጫ አስታወቁ። ከዚህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ መልቀቂያ ጋር ያልጠበቅነውና ያልገመትነው ታሪካዊና ሰፊ የዕድል በር ከፊታችን ተከፍቷል። ይኽንን ልዩ ዕድል እንደሌላው ጊዜ በከንቱ ከአባከንነው የሚያስከፍለን ዋጋ ከመቼውም ጊዜ በላይ የከፋ ሊሆን ይችላል።

በመሆኑም በታላቅ ጥንቃቄ፣ ያለንበትን ነባራዊ ሁኔታ _ መርምረን፣ በቀጣይ የምንከተለውን አቅጣጫና ተግባራዊ የምናደርገውን ታክቲክ በግልጽ ለማስቀመጥ ሞክረናል። ሀገር ለውጥ ማርገዟ ለማንም ግልጽ ነበር። ያ ጊዜ ደግሞ ከእርግዝና ባሻገር የመውለጃ ወሯም መግባቱን ያሳያል። ሀገር ያረገዘችውን ልትወልድ እያማጠች ነው። የምጥ ጣዕር ምልክቶች ይታያሉ።

## አንደኛ ደረጃ ምጥ

በእርግዝና ማብቂያና ፅንሱ ከማኅፀን በሚወጣበት የተፋፋመ ምጥ መካከል የሚገኝ፣ የሽግግር የመጀመሪያ ምዕራፍ ነው። በዚህ ምዕራፍ ለዋናው ምጥ መነሻ የሚሆነው እርምጃና አካላዊ ለውጥ በረጋ እንቅስቃሴ የሚጀመርበት ቢሆንም የበረታ ሥቃይ የሚታይበት አይደለም። የለውጥ ቡድኑ በድርጅታዊ የለውጥ ምጥ ሂደት ውስጥ የመጀመሪያውን ምዕራፍ በጥንቃቄ ነበር ያካሄደው። ይኽም የለውጥ ቡድኑ ግራ ቀኙን በመገምገም በኦሕዴድ የውስጥ አመራር አስፈላጊውን ሽግሽግ በተሳካ መንገድ የማካሄዱ ሥራ ነበረ። ይሄንን ካደረግን በኋላ የምክር ቤቱን የአመለካከትና የተግባር አንድነት በማጠናከር፣ ለቀጣዩ ጉዟችን ራሳችንንና የቅርብ ደጋፊዎቻችንን ወደ ማዘጋጀት ተሸጋገርን።

## ሁለተኛ ደረጃ ምጥ

ሁለተኛ ደረጃ ምጥ ልክ እንደ መጀመሪያው ምዕራፍ የዝግጅት ምዕራፍ ቢሆንም በሰውነት ላይ የሚታዩት ለውጦች ከባድና ጠንካራ በመሆናቸው የአስጨናቂነታቸው ደረጃ የበረታ ነው። በቀድሞው የኢፌዲሪ ጠቅላይ

ሚኒስቴር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የመጨረሻው የሥልጣን ዘመን የተካሄደ ነው።

በዚህ ጊዜ በምስጢር፣ በሽኩቻና በውጥረት የተከበበ መደበኛ ያልሆነ የኢሕአዴግ የሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ ተካሂዷል።ጉባኤው የኢትዮጵያን ፖለቲካ በከባዱ የለወጠ ጉባኤ ነበር። በአጀንዳው የተካተተው ርእሰ ጉዳይ በዋናነት ግንባሩን በመሠረቱት ብሔራዊ ድርጅቶች ውስጥ የተካኼደውን ጥልቅ ተሐድሶ በመገምገም ላይ ያተኮረ ነበር። ነገር ግን ከጀርባው የተጠመደውን ሤራ በማሰብ ውይይቱ በኃይለ ቃልና በሽሙጥ፣ የቀረበውን ሐሳብ ሳይሆን አቅራቢውን በመዝለፍና በመጥለፍ ላይ ያተኮረ ፈታኝ ገጽታ ነበረው። በተለይ ኦሕዴድ እኔን በለማ መተካቱና ሊቀመንበሩ አድርጎ መምረጡ ከፍተኛ ራስ ምታት የፈጠረባቸው ኃይሎች በቀላሉ በጄ ሊሉ አልፈቀዱም:- ይኼንን ከመጋረጃ ጀርባ ሲካኼድ የነበረውን ፍጥጫ ያልተረዳው ሕዝብና ያልተረዱት መደበኛ አባላት ጉባኤው በጥቂት ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃል የሚል ግምት ነበራቸው::

በሕዝቡና በመደበኛ አባላት ዘንድ የድርጅቱ ሊቀ መንበር በቀላሉ ይመረጣል ተብሎ ታስቦ ነበር። ነገር ግን ለሳምንታት በዘለቀው ንትርክና ቁርቁስ በተፈጠረው ትንቅንቅና እልህ አስጨራሽ ግብግብ የተነሣ ሊመረጥ ሳይቻል ቀረ። ድፍን ኢትዮጵያ እንደ አንድ ሰው የጉባኤውን መጨረሻ በአንክሮና በጭንቀት ነበር የሚጠብቀው። ለወትሮው አንዳንድ መረጃዎችን ለሕዝቡ በመስጠት ለራሳቸው ስምና ዝና ያተረፉ የውስጥ ዐርበኞች ሳይቀሩ የመረጃ ድርቅ መታቸው። ኢሕአዴግ ጉባኤው እስኪጠናቀቅ ድረስ በሩን ከርችሞ የውሾን ነገር ያነሣ... በሚል ዓይነት ጸጥ አለ። በአንዳንዶች አገላለጽ የወቅቱ ሁናቴ ከዓመታት በፊት ሕወሓት ለሁለት ተሰንጥቆ እነ መለስና ተወልደ በዝግ ጉባኤ ሲፋጁ እንደ ነበረው ዓይነት ነበር። በዚያን ጊዜ እንኳን የተሸራረፉ ቢሆኑም፣ ጥቂት መረጃዎች አፈትልከው እየወጡ ለሕዝብ ይደርሱ ነበር። አሁን ግን ከስብሰባው አዳራሽ እንኳን መረጃ የገባ ነፋስም ተመልሶ አይወጣም ማለት ይቻል ነበር። ለውጡን ለማደናቀፍ ለተዘጋጀው ቡድንና በተቃራኒ ለተሰለፈው አዲሱ የለውጥ ኃይል ቅርብ ነን ባይ ጸሐፊዎችና ፖለቲከኞች ጧትና ማታ ወሬ ይነዛሉ።

ሕዝቡም እየተቀባበለ በማኅበራዊ ሚዲያ የሚያራግበው የግምት ዜና፣ ጅራትና ቀንዱ የማይለይ ድቡልቡል ወሬ ነበረ። ለውጡን የሚደግፉ የማኅበራዊ ሚዲያ ሰዎች በበኩላቸው፤ "ሁሉም ነገር በታሰበው አኳኋን እየሄደ ነውና አትደናገጡ፣ የለውጡ ሰው እየመጣ ነው" የሚል አጸፋዊ መልስ በመስጠት፣ የተረበሸውን አየር ለማረጋጋት ሲሞክሩ ቆዩ። የቀረው ደግሞ የሰማውን ብቻ ሳይሆን ያሰበውን፣ የተመኘውንና ያለመውን ሁሉ ሳይቀር በየአቅጣጫው ይወረውር ነበር። በዚህም ሆነ በዚያ በውዥንብር ምጡን የሚያባብስ እንጂ የሚያጠራ ሁነኛ የመረጃ ሰው አልነበረም። በዝምታ ለመጽናት መወሰናቸው የለውጥ ቡድኑም ሆነ የለውጥ አደናቃፊው ውጥረቱን ይበልጥ አባባሰው፡

ኢሕአዴግ ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ያዳበረው አንድ የግምገማ አካሄድ አለው። አንድ አባል በሐላፊነቱ የተሰጠውን ተልእኮ በብቃት ቢወጣ እንኳን እንዲወገድ የተፈለገን የሥራ ሐላፊ በግምገማ ስም ማስወገድ። እንዲህ መሰሉን ሰው በስመ ግምገማ በሚዘንብበት ውኃ የማይቋጥር ሂስና ውርጅብኝ አበሳጭቶ ወይም አታክቶ፣ አድክሞና ቅስሙን ሰብሮ ማሳመን የተለመደ ሤራ ነው። ሲደክምህ እጅ ትሰጣለህ ተብሎ ይታመናል። ፀረ ለውጥ ኃይሉም ይሄንን የግምገማ ዘዴ በእጅጉ መጠቀም ተያይዞታል። ቡድኑ ነጥብ ለማስቆጠር ያስችለኛል ያለውን ትችት፣ ሂስ፣ የተፈበረከ ወንጀል፣ የርእዮተ ዓለም ድሪቶ፣ እንደ ሙዚቃ እያፈራረቀ ቀንና ማታ ቀጠለ።

ይህ ወቅት ታሪክ የሚሠራበት፣ የሀገር ጉዳይ በቀጭን ክር ላይ የተንጠለጠለበት ጊዜ እንጂ የግል ጉዳይና ክብርን የማስጠበቂያ ጊዜ አለመሆኑን የለውጡ ቡድን በሚገባ ተረድቷል። ስለዚህም ጥርሱን ነክሶና የሐቅ ምሽጉን አጠናክሮ ላለመሸነፍ ከብረት ጠነከረ። ፀረ ለውጥ ቡድኑ ከፈጠረው ውሸት ጋር የሙጥኝ ብሎ በእውነት ላይ ማላገጡን ሲቀጥል፤ የለውጥ ኃይሉም ያለ ቃል በሐሳብና በእውነት ቋንቋ ተግባብቶ ቀዳዳ ሳይፈጥር ተቀመጠ። ውሳኔው ታሪካዊ፣ ውጤቱ ትውልዳዊ፣ አጀንዳው ደግሞ ሀገራዊ መሆኑን ከማንም በላይ ለለውጥ ቡድኑ ቁልጭ ብሎ ታይቶታል።

በየዕለቱ "ዛሬ በቃ ይለያል" ይባላል። ምኑም ሳይለይ፣ አንድም ነገር ሳይጨበጥ፣ ቀኑ መሽቶ ያልቃል። መግባባትም ሆነ መስማማት ባለመቻሉ፤ ጉባኤው ቀድሞ ከተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ውጭ በአንድ ቀን ተራዘመ እየተባለ፣ ቀን ቀንን እየወለደ፣ ምጡም እየተራዘመ፣ ሳምንቱ እንደ ዋዛ አለፈ።

በረቀቀ ሤራ በመሳሳብና በመደነቃቀፍ የተወጠረው ውይይት ሳይረግብና ሳይላላ ወደ ምሽት ይሸጋገራል። አንዳንድ ቀን ለዕረፍት ስንወጣ ቀኑ በምሽት ተተክቶ የሚጠብቀን ጊዜ አለ። የጉባኤውን ተሳታፊዎች ይዘው የመጡት መኪኖች በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት አዳራሽ ደጃፍ ላይ ተሰጥተው ይውላሉ። የሾፌሮቹን መሰላቸትና መታከት ከርቀት ለማየት ይቻላል። ቀን ቀን ካርታ ሲጫወቱ፣ ሲጋራ ሲያጨሱ፣ በእጅ ስልካቸው ጌም ሲጫወቱና ሲንቆራጠጡ ይውላሉ። ወታደሮች ደግሞ አካባቢውን በንቃት ይጠብቃሉ። አንዳንድ የጸጥታ ሠራተኞች መኪኖቻቸውን ይዘው ወደ ግቢው ይገባሉ ይወጣሉ። ሁሉም የትም ላይደርስ ይፈጥናል፤ ምንም ልዩነት ላያመጣ ይጨነቃል። ምጡ ግን እንደ ቀጠለ ነው።

ሥራ አስፈጻሚው የተከተተበት ዝግ ስብሰባ በቤተ መንግሥቱ ደጃፍ ላይ ከሚታየው ውጥረትና ጥድፊያ ጋር ተዳምሮ አካባቢውን የማዋለጃ ሆስፒታል አስመስሎታል። በአዳራሹ ውስጥ የመሸጉ ተሰብሳቢዎች ደግሞ፤ ድንገት ምጧ መጥቶ ልትወልድ ሐኪም ቤት እንደ ገባች እናት፤ ውጪ ነፍስ ግቢ ነፍስ ላይ ናቸው። በውጭ የሚርመሰመሱት ሾፌሮችና የጸጥታ ሠራተኞች እናቲቱ በሰላም ተገላግላ፣ ዜናውን ማን ነገሮን እፎይ እንል ይሆን? በማለት በጭንቅ የሚጠባበቁ ቤተሰቦችን ይመስላሉ። የማዋለዱ ሂደት ቢረዝምም ያለ ዕረፍት ቀጥሏል። የፖለቲካ ሐኪሞቹና አዋላጅ ነርሶቹ ያላቸውን መድኃኒት ሁሉ ተጠቅመው ምጥ የገባችውን ሀገር ለማሳረፍ ላይ ታች ይላሉ። ምክክሩ ጦፏል፣ ትንቅንቁ ግሏል።

## ሦስተኛ ደረጃ ምጥ

ሦስተኛ ደረጃ ምጥ የዝግጅት ምዕራፍ አይደለም። የተግባርና የማጠናቀቂያ እንጂ። ፅንሱ በሕይወት ይወለዳል ወይም ሕይወት አልባ ይሆናል። በመጨረሻም እንግዴ ልጁ ፅንስ የመሸከምና የመመገብ ግብሩን ፈጽሞ ይሰናበታል። ሦስተኛ አማራጭ የለም። የመጨረሻ ትንፋሽና ዐቅምን ለመጠቀም ሥቃዩ እጅግ ከባድ ነውና ጥርስን መንከስ ይጠይቃል።

ቀኑን ሙሉ ተሰብስበን፣ እስከ ምሽቱ ሦስትና አራት ሰዓት ድረስ በምርጫ አካሄድ ላይ ስንነታረክ እንቆያለን። ወደ ውጭ ሳንወጣ፣ ትንፍሽ ሳንል በራችንን ከርችመን እንቆያለን። በነገታውም ያው ዙር ይደገማል። በተባበረ ድምፅ እጩ ማቅረብም ሆነ ሊቀ መንበር መምረጥ ሊሆንልን አልቻለም። ከዚህ በኋላ ነበር በምስጢራዊ

የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ያበጠውን ለማፈንዳት የተወሰነው። ማንም ውጤቱን የማይገምተውን ድምፅ ለመስጠት 180 አባላት ያለው የግንባሩ ምክር ቤት ተሠየመ።

## መጋቢት 18 ቀን 2010 ዓ.ም.

ያ ዕለት አዲሱ ሊቀ መንበር የሚመረጥበት የመጨረሻው ቀን ሆነ። እጩ የማቅረቡ ሥራ ተጀመረ። በዚያ ዕለት አንድ ነገር አስታውሳለሁ። የያኔው የደቡብ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ ደሴ ዳልኬ ከጎኔ ተቀምጧል። አልፎ አልፎ ሰረቅ እያደረገ ይመለከተኛል። እጩዎች መጠቆማቸው ቀጥሏል። የእኔ ስም ሲጠራ ታላላቅ የምንላቸው ጉምቱ አባላት ሲቃወሙ አያለሁ፤ እሰማለሁ። ስለእኔ የማይሰነዝሩት የበደል ዓይነት የለም። በየመሐሉ ትኩረቴን ለመሰብሰብ እየሞከርኩ በአእምሮዬ ጓዳ ብልጭ የሚሉትን ሐሳቦች ወረቀት ላይ እሞነጫጭራለሁ። ነገረ ሥራዬ አላምር ያለው አቶ ደሴ “አንተ ሰው ምን እያደረክ ነው?” ሲል ጠየቀኝ።

“ምጡን ትቼ ልጁ ላይ ባተኩር ይሻላል ብዬ ነው” ስል መለስኩለት። በዚያን ሰዓት ከተመረጥኩ በኋላ የማደርገውን ንግግር ማርቀቅ ጀምሬ ነበር።

ከኢሕአዴግ ባህል በወጣ መልኩ ለሰዓታት የቆየው የእጩ ጥቆማ በመጨረሻ ተጠናቆ ድምፅ መሰጠት ሲጀምር ሰዓቱ ከምሽቱ 4፡45 ገደማ ሆኖ ነበር። የዚያን ዕለት የምክር ቤቱ ውጥረትና የለውጡ ደጋፊዎች የፈጸሙት ተጋድሎ መቼም የማይረሳ ታሪካዊ ክሥተት ነበር። ድምፅ አሰጣጡ ተጠናቆ ቆጠራው _ ሲጀመር እናቲቱ በሰላም ተገላግላለች' የሚለውን ዜና ለሕዝቡ ለማድረስ ሚዲያ እንዲጠራ ተደረገ። ውጤቱ ለተሰብሳቢው ይፋ ሲደረግ አዳራሹን የተደበላለቀ ስሜት ሞላው። ሆታ፣ ጭብጨባ፣ መተቃቀፍ፣ መጨባበጥ… በአዳራሹ ውስጥ፡ ከአዳራሹ ውጭ ግን አሁንም ጥበቃው እንደቀጠለ ነው፤… ረጅም ጥበቃ… ጥበቃው የጀመረው ገና በእኩለ ቀን ነበር። እንዳይመሽ የለም መሸ… አንድ ሰዓት፣ ሁለት ሰዓት፣ ሦስት ሰዓት… ብርቱና የተጎተቱ ሰዓቶች አለፉ። ገና በሀገር ውስጥም፣ በውጭም በሚገኙ የዜና ማሠራጫዎች ልዩነት ፈጣሪ መረጃ አልተነገረም። ማኅበራዊ ሚዲያው ግን ግምቱን ቀጥሏል። አብዛኛው ሰው፣ ተስፋ ቆርጦና ግራ ተጋብቶ ወደ መኝታው ከሄደ በኋላ፣ ከምሽቱ 5፡20 አካባቢ ነበር ኢሕአዴግ አዲስ ሊቀ መንበር መምረጡን በሰበር ዜና ይፋ ያደረገው።

የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን ይህ ምርጫ በፓርላማው ጉባኤ መጽደቅ ቢኖርበትም፣ ለደጋፊዎቻችንና ለውጥን ሲመኙ ለነበሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ፣ ዜናው ፌሽታን ፈጥሯል። በድፍን ኢትዮጵያ ብዙዎች በደስታ እንደጨፈሩ፣ አንዳንዶችም እንባ እንደተራጩ አድሮ ሰማን። በዚህ መልኩ የመደመር ኃይልና ጉልበት በግልጽ የታየበት አስጨናቂና አስደናቂ ድራማ አንዱ ምዕራፉ ተቋጨ። ለረጅም ጊዜ የመወለጃ ጊዜውን ሲጠብቅ በእርግዝና ደረጃ የቆየው የመደመር ፅንስ አካል ነሥቶ፣ ነፍስ ዘርቶ ባልተጠበቀ ሰዓትና መንገድ ኢትዮጵያ ላይ የተጋረደውን የጽልመት መጋረጃ ገሥሦ ሊወለድ በሩን ማንኳኳት ጀመረ።

# ምዕራፍ አራት

## የለውጡ ፈለግ

“መንገድ ዐይኑ ይጥፋ፣ አይባልም ደርሶ
የወሰደውን ሰው፣ ያመጣል መልሶ!”

~ ሀገርኛ አባባል

በአንድ ወቅት፣ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን የሚመራው የልዑካን ቡድን ወደ ሩሲያ አቅንቶ ለቀናት የፈጀ ጉብኝት አድርጎ ነበር። ያኔ እኔ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ነበርኩ። በልዑካን ቡድኑ እንደ አንዱ ተሳታፊ ሆኜ ከነደመቀ ጋር በሩሲያዋ ዋና ከተማ በሞስኮ ተዘዋውረን ልዩ ልዩ ተሞክሮዎችን ስንቀስም መቆየታችንን አስታውሳለሁ።

በዚያ ጉዞ ወቅት ይበልጥ የማይረሳኝ ሞስኮ ላይ ከደመቀ ጋር ያደረግነው ወንድማዊ ወግ ነበር። ወጋችን እንዴት እንደ ጀመረ እምብዛም ትዝ ባይለኝም፣ የወጋችን ማጠንጠኛ ግን የአማራና የኦሮሞ ልሂቃን ግንኙነት ስለማጠናከር ያለመ እንደነበር አይረሳኝም።

ብቻችንን የምንሆንባቸውን አጋጣሚዎች እየተጠቀምን፣ብአዴንና ኦሕዴድ በጋራ ሆነው የሁለቱን ክልል ሕዝቦችና ልሂቃን አስተባብረው ለሀገራችን አዎንታዊ ለውጥ ማበርከት ስለሚችሉበት መንገድ አንሥተን ብዙ ስናወራ ነበር። አማራና ኦሮሞ የጎሪጥ የሚተያዩባት ኢትዮጵያ "ኢትዮጵያ" እንደማትሆን አስረግጬ በነጻነት ደመቀን አወራሁት። እሱም የመሰለውን ሐሳብ አነሣ። ንግግሩ ቁጥብነት ባይለየውም ከሞላ ጎደል የአማራና የኦሮሞ ልሂቃን በጋራ እንዲቆሙ መንገድ ስለመጥረግ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት መደረግ ስላለበት ትግል ጊዜ ወስደን ተጫወትን።

"ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ቆማ ሁሉንም ሕዝቦች፣ ሁሉንም ብሔሮችና ብሔረሰቦች እንድትጠቀም፣ መጀመሪያ ሁለቱን ሕዝቦች እንወክላለን የሚሉ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ልሂቃን እንደ አንድ ሆነው መቆም አለባቸው። እንደሚታወቀው ሕዝብ ሕዝብ ነው፣ ሰላምና በጋራ መኖርን ነው የሚፈልገው።

ልሂቃንና የሐሳብ መሪዎች ግን እንደ ሕዝቡ አይሆኑም። ልዩ ልዩ ጥቅማቸውን እያሰላሰሉ ነው እንቅስቃሴያቸውን በተለያየ አቅጣጫ የሚቃኙት፡፡ የአማራና የኦሮሞ ልሂቃንም በተመሳሳይ በልሂቃኑ ምክንያት ሕዝቡ ዕረፍት ሊያጣ አይገባም" የሚለው ሐሳብ ሁለታችንን በስፋት ያግባባን ጉዳይ ነበር። በሁለቱ ልሂቃን ዐይንና ናጫነት, ላይ የሚመሠረት ማንኛውም የፖለቲካ አካሄድ፣ እንደ ሀገር መቀመቅ ይዞን ይወርድ ይሆናል እንጂ፣ ከፍ እንደማያደርገን እርግጥ ነው። ልዩ ልዩ ጥቅማቸውን እያሰላሰሉ ነው፡፡ እንቅስቃሴያቸውን በተለያየ አቅጣጫ የሚቃኙት። የአማራና የኦሮሞ ልሂቃንም በተመሳሳይ። በልሂቃኑ ምክንያት ሕዝቡ ዕረፍት ሊያጣ አይገባም" የሚለው ሐሳብ ሁለታችንን በስፋት ያግባባን ጉዳይ ነበር። በሁለቱ ልሂቃን ዐይንና ናጫነት ላይ የሚመሠረት ማንኛውም የፖለቲካ አካሄድ እንደ ሀገር መቀመቅ ይዞን ይወርድ ይሆናል እንጂ ከፍ እንደማያደርገን እርግጥ ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያን እንደ ቤት ብናያት፣ እኛ ልጆቿ እንድንጠለልባት ታስባ የተሠራች ባለ አንድ ጣሪያ ጎጆ ብንመስላት፣ ጣሪያውን ደግፈው ሊቆሙ የሚችሉት ዋልታዎች እነዚህ ሁለት ሕዝቦች ናቸው። ሌሎች ሕዝቦችም በበኩላቸው ግድግዳና ጣሪያ፣ መስኮትና መዝጊያ፣ ማገርና ወራጅ ወዘተ. ሆነው ቤቱን ቤት ያደርጉታል። በርና መስኮቱ ባይኖር ቤቱ ድፍን ወይም ማንም እንዳሻው ዘው የሚልበት ኦና ቤት እንደሚሆነው

ሁሉ፣ ያለ ጣሪያና ያለ ግድግዳው በቀኑ ሐሩርና ከሌሊቱ ቁር ልንጠበቅ አንችልም፤ ጥላና ከለላ አናገኝም። በተመሳሳይ ቤቱን ያቆሙት ዋልታዎች ከሌሉ ሙሉ ቤቱ እንደ ቤት ሊቆም አይችልም።

ታዲያ ኢትዮጵያችን፣ሁሉም ዜጋ እና ሁሉም ብሔር በእኩልነት የሚኖርባት ሀገር እንድትሆን ማድረግ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ትልቅ የቤት ሥራ ቢሆንም፣ ይሄን ለማድረግ መጀመሪያ ሀገር ሊኖረን ይገባል። የጋራ ቤታችን በቅድሚያ በቅጡ መቆም አለባት። ውኃ ላይ እንደ ተጣለ ኩበት ከወዲያ ወዲህ ዥዋዥዌ በሚጫወት ቤት ውስጥ የግለሰቦች ነጻነት እና የብሔሮች እኩልነት ትርጉም አይኖረውም።

በአንድ ወቅት የብሔር እኩልነት የሚያቀነቅኑ ኃይሎች ፈጣን ምላ መስሏቸው ቤቱ የቆመባቸውን ዋልታዎች በመነቅነቅ ሀገረ መንግስቱን ትንፋሽ ማሳጣቱን እንደ ስትራቴጂ ቆጥረውት ነበር። ያ ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለንና የት ድረስ እንዳመጣን ሁላችንም እናውቃለን። ሕዝቦች ጠዋት ማታ በጥርጣሬ እየተያዩ በሰቀቀን እንዲኖሩ አድርጓል። ከአንድነት ይልቅ ልዩነቱን እየሳቡ የጋራ ቤት ከማቆም ይልቅ ሁሉም የየራሱን ክፍል ለመቀለስ እንዲሯሯጥ ምክንያት ሆኗል። ያ አካሄድ የምናልመውን እኩልነት ሊያጎናጽፈን ቀርቶ ጭራሽ ቤት አልባ ሊያደረገን መንገድ ጀምሯል። በጊዜ አንድ ካልተባለ ልዩነት ላይ የሚያነጣጥረው ትርክት፣ ጠንካራ ሀገር ገንብተን ገዝፈን የምንታይበትን አጋጣሚ፣ በትንንሽ ጎጆ ኮስምነን እንድንቀርብ ሊያደርገን ይችላል።

ከደመቀ ጋር ሞስኮ በቆየንባቸው ጥቂት ቀናት ውስጥ፣ ከሞላ ጎደል በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የጋራ አቋም ኖሮን ዘለግ ያለ ውይይት ማድረጋችንን አስታውሳለሁ። ምናልባትም ከዚህ አጀንዳ ውጭ ነገሬ ብለን ያወራነው ጉዳይ ቢኖር ስለ ሩሲያ የአስተዳደር ታክሪ ነበር። በተለይም ደግሞ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማግስት ስለአለችው ሩሲያ። ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት በኋላ ሩሲያን ፕሬዚዳንት ሆኖ የመራት ቦሪስ ዬልሲን መንበር ሥልጣኑን ሲረከብ፣ ያቺ ሀገር ከአፈር ተነሥተው ፈላጭ ቆራጭና እጅ ጠምዛዥ በሆኑ በዝባዥና ሕገ ወጦች መዳፍ ውስጥ ገብታ ነበር። የዬልሲን አገዛዝ ያቺን ትልቅ ሀገረ የጥቂት ቡድኖችና የጥቂት ቤተሰቦች ንብረት እስክትመስል ድረስ በአጭር የነጣቂ-መንግሥት ዝርፊያ (state capture corruption) ውስጥ እንድትዘፈቅ አድርጓት ነበር።

ከዚህ አኳያ ሩሲያ ከኢትዮጵያ ጋር የምትመሳሰልበትን ሁኔታ እያነሣን ከደመቀ ጋር ጉዳዩን ተንትነን አየነው። እያይዘንም ሩሲያውያን እንዴት አድርገው ያንን ነጣቂ- መንግሥት ዘራፊ ኃይል ሊያስወግዱት እንደቻሉ ተነጋገርን።

አፍ አውጥተን እከሌ ነው ባንልም፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የነጣቂ-መንግሥት ዝርፊያ ውስጥ የተሠማራው ኃይል፣ ማን እንደሆነ ስም ጠቅሰን ባንነጋገርም፣ የሕወሓት ሰዎች ደግመው ደጋግመው በሁለታችንም አእምሮ ውስጥ ይመላለሱ እንደነበር ግልጽ ነው።

ታዲያ የሞስኮ ቆይታችንን አጠናቀን ወደ ሀገር ቤት በምንመለስበት ወቅት ብቻችንን የምንሆንበትን አጋጣሚ ጠብቆ፣ ደመቀ “አንተ ወጣት ወንድማዊ ምክሬን ልሰጥህ እሻለሁ” አለኝ።

ምክሩን ለመስማት ቀልቤን ሰብስቤ ጠበቅኩት።

“እንደምታውቀው በዛሬው ዘመን ማን እንደማይታመን ማወቁ አዳጋች ነው። ሰው ልቡ ተከፍቶ አይታይም። የሰው ልጅ በአፉ እያወራ በጭንቅላቱ ምን እንደሚያስብ አይታወቅም። በተለይም በመንግሥት ቤትና በድርጅታችን ውስጥ የትኛው አካል ለየትኛው ዓላማ እንደሚታመን ጠንቅቆ ማወቅ ያዳግታል። ስለዚህ ስለ ለውጥ ያለህን ፍላጎት ስትገልጽ ቦታ ቦታዎችን ብትመርጥ መልካም ይመስለኛል።”

ደመቀ ይሄን ሲለኝ ግር በተሰኘ ስሜት አስተዋልኩት። ዐየት አድርጎኝ ንግግሩን ቀጠለ።

“መቼም አንድ ቀን ለሀገራችን ለውጥ መምጣቱ አይቀርም። ትግሉ አንድ ዓመትም ይፍጅ ዐርባ ዓመት አንድ ቀን ለውጥ ይመጣል። ነገር ግን አንተ ለለውጡ እርሾ መሆንህ ቀርቶ ገና አንድ ርምጃ ሳትራመድ ባጭሩ ልትቀጭ ትችላለህ። ያንን የለውጥ ዕለት እንዳታይ የሚያደርጉህ አጋጣሚዎች ምን ያህል በዙሪያህ እንደበዙ ልብ ያልክ አትመስልም። በተለይ የአማራና የኦሮሞ ነገር ምን ያህል አንዳንዶችን እንደሚያበሳጫቸው፣ ምን ያህል ቀንድ እንደሚያስበቅላቸው ያወቅህ አልመሰለኝም".. ላፍታ ዐይኖቹን ቦዘዝ አድርጎ ከቆየ በኋላ ቀጠለ።

“...የሁለቱ ሕዝቦች ትብብር እንዲህ በቀላሉ የሚታይ ቢሆንማ ኖሮ ያሁሉ ሚስማር ባልተጠቀጠቀበት ነበር። ለዚያውስ በአንድ ኃይል ብቻ ሆነ እንዴ... ብዙዎች ናቸው፤ ብዙዎች! ከሀገር ውስጥም ከውጭ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሚስማሮቹን ሲመቱ ነበር... ለረጅም ዘመን... ከሰባና ሰማንያ ዓመታት ላለፈ ጊዜ። እንኳን እንደ ሕዝብ ይቅርና እንደ ሀገር ያሉን ጠላቶቻችን፣ ግብጽ ብትል _ ጣልሊያን፣ ሌላም ሌላም፣ ኢትዮጵያን ለማድከም የሚፈልጉ ሁሉ ሚስማር የሚመቱበት ነገር ቢኖር የሁለቱ ሕዝቦች ልሂቃን ትብብር ላይ እንደሆነ መቼም የሚጠፋህ አይደለም። ታዲያ አንዷን ሚስማር ለመንቀል መንቀሳቀስ ስትጀምር በዝምታ ቆመው የሚጠብቁህ ይመስልሃል? በፍጹም ዝም አይሉህም። ዓላማዬ ብለው የያዙትም፣ ለሆዳቸው ሲሉ ያደሩትም እኩል በዐይነ ቁራኛ ይከታተሉሃል። ሩቅ ሳትሄድ፣ ለግል ኪሳቸው ብለው የሚኖሩ አንዳንድ አማራና ኦሮሞ የኢሕአዴግ አመራሮችን በየዋሕነት ቀርበህ ብታወራቸው፣ በጎን ለአለቆቻችን ሹክ ብለው ሽልማት የሚያገኙበት የሎተሪ ዕጣ ሊያደርጉህ ይችላሉ።

“ይሄን የምታደርገው ለኢትዮጵያ ካለህ ፍቅር እንደሆነ ይገባኛል። የሕዝባችን ሁኔታ ምን ያህል አሳስቦህ እንደሆነ እረዳለሁ። እኔም በበኩሌ ያሳስበኛል። ነገር ግን አካሄዳችን በጥንቃቄ እስካልተገራ ድረስ ለመሰናከል እጅግ ቅርብ ነን። እንኳን እንቅስቃሴ ማድረጋችን ታውቆ ይቅርና፣ ቀድሞ ነገር  እንዴት አሰባችሁ በሚል ጭዳ ሊያደርጉን የሚቋምጡ ሰዎች ቁጥር ጥቂት አይደሉም።

“ደግሞስ... ሚስማር ተካዮቹ እንደአላየ ሆነው ዝም ቢሉ እንኳን፣ የሁለቱን ሕዝቦች ልሂቃን ወደ ትብብር ማምጣት እንዲህ ቀላል ሥራ ነው እንዴ? ሚስማሮቹን ነቅለን ብንጨርስ እንኳን፣ ሚስማሩ የገባበት ቁስል በአንዴ ሊጠግግ አይችልም ። ሚስማሮቹ የጣሉት ጠባሳ፣ ልሂቃኑ ጀርባ ላይ የተጋደመው ሰንበር በራሱ የሚፈጥረው ችግር፣ ጨርሶ ለመዳንና ትግሉን በአሸናፊነት ለመወጣት ጊዜ ወሳጅ ያደርገዋል። ለዚያ ነው

ሁሌም ጥንቃቄና ጥበብ ይጠይቃል የምለው። ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ የምንሄድ ከሆነ፡ አንድ ወደፊት ተራመድን ስንል፣ ሁለት ወደኋላ የሚመልሰን ነገር ይፈጠርና ትግሉ ባለህበት ርገጥ ይሆናል።"

ደመቀ ከተናገራቸው ውስጥ፣ ትግሉ ጥንቃቄና ጥበብ ይጠይቃል ያለውን በሙሉ ልብ የምስማማበት ጉዳይ ነው። ነገር ግን ጊዜ ሳያባክኑ ትግሉን አጠናክሮ ከመቀጠል ውጭ ሌላ አማራጭ አልታየንም። በውጭው ዓለም "ሁሉንም ሰው ማመን አደገኛ ነው፤ ሁሉንም ሰው መጠራጠር ደግሞ ይበልጥ አደገኛ ነው" ይባላል። በዚህ ትግል ውስጥ በግለሰቦች መካከል የሚፈጠር መጠራጠር ከሚያደርሰው ጉዳት በላይ በመካከላቸው የሚገነባ መተማመን ለምናልመው ለውጥ የሚፈጥረው አዎንታዊ ተጽዕኖ እጅግ ከፍ ያለ ትርጉም የሚሰጠው ነው።

በሀገራችን "ሕልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም ይባላል። ገና ለገና አንዳንዶች ወሬ ሊያቀብሉና ትግሉን ሊያሰናክሉ ይችላሉ በሚል ጥርጣሬ፣ ለትግሉ በር ከፋች የሆኑ ምክክሮችን ለመጀመር መቆጠብ ተገቢ ነው ብዬ አላስብም። እንዲህ ያለው ዕንቅፋት አንዱ የትግሉ ሂደት ፈተና እንደሆነ ቆጥሮ፣ የተጀመረውን ጉዞ መቀጠሉ ይበጃል ባይ ነበርኩ።

ያ ጊዜ ዐልፎ፣ የኦሕዴድና የብአዴን አጋርነት ተጠናክሮ፣ የሁለቱን ሕዝቦች ልሂቃን ግንኙነት ወደ መልካም ጎዳና ለማስገባት የኦሮማራ እንቅስቃሴያችንን በይፋ ባሕር ዳር ላይ ለማድረግ በቃን። በዚያ መድረክ ለቀጣዩ ትግላችን ጥሩ ግብዓት የሚሆኑ ስንቆች ተገኝተውበት ነበር። በተቃራኒ የቆመው ኃይልም በዚያ መድረክ መዘጋጀት ክፉኛ መደንገጥ መጀመሩን በይፋ አሳይቷል። ወራት ቆይቶም የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ መልቀቂያ ማስገባቱ ሲገለጽ፤ አጋጣሚውን በመልካም ለሚጠቀመው ጥሩ የመታጠፊያ ነጥብ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር አልነበረውም። በአንጻሩ ለሕወሓት ከፍተኛ አመራሮች የመርዶ ያህል አስፈሪ አጋጣሚ ሆኗል።

በዚያን ሰሞን ኃይለ ማርያም ደሳለኝን ተከትሎ ደመቀ መኮንንም መልቀቂያ ሊያስገባ መሆኑን ስሰማ ክፉኛ ተበሳጭቼ እንደነበር አስታውሳለሁ። ስለ ጉዳዩ ላነጋግረው ወደ እርሱ ስሄድ በዚያ የቁጣ እሳት ውስጥ እንደነበርኩ ያወቅኩት ዘግይቼ ነበር። ጊዜ ወስጄ ስለ ነገሩ ሰከን ብዬ ካብሰለሰልኩ በኋላ...። ደመቀም በሌላ ቀን ስለዚያ ዕለት ሁኔታዬ እንደቀልድ ሲነግረኝ የኀፍረት ነፋስ ሽው ብሎብኝ እንደነበር ትዝ ይለኛል።

"እንደዚያን ዕለት እኮ ገላምጠኸኝ አታውቅም" ነበር አለኝ ደመቀ፤ ነገሮች ከተረጋጉና እኔም ወደ ቀልቤ ከተመለስኩ በኋላ። "ምንም እንኳን ነገሮችን አንተ ባየህበት መንገድ ሳላይ ለውሳኔ መገፋፋቴ ስሕተት ቢሆንም፣ ረጋ ብለህ መጥተህ በመግለጽ ፋንታ ግልምጫው ተገቢ አልነበረም" አለኝ ፈገግታ ሳይለየው።

እንደ እውነቱ ከሆነ ደመቀ ስለሆነ እንጂ በእሱ ቦታ ሌላ ሰው ቢሆን ክፉኛ በተቀየመኝ ነበር። ለጉዳዩ የሰጠሁት ክብደት ለዚያ ያደረሰኝ ይመስለኛል። የምናስበውን ለውጥ ለማምጣትና የለውጥ ኃይሉ ተጠናክሮ ሪፎርሞችን እንዲጀምር የደመቀ እዚያው በቦታው መቆየት አስተዋጽዖው ቀላል አልነበረም። ኃይለ ማርያም

መልቀቂያ ማስገባቱ ትልቅ ዕድል የፈጠረውን ያህል፣ የደመቀ መልቀቂያ ማስገባት የተከፈተውን በር በግማሽ ይደፍነው ነበር። በኢትዮጵያ የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ለዓመታት ጡንቻውን ሲያፈረጥም የቆየውን ኃይል ለመገዳደር በፓርቲው ውስጥ የሊቀመንበርና የምክትል ሊቀመንበር ጥምረት በእጅጉ አስፈላጊ ነበር። ብዙኃኑን ሕዝብ ከጎን ያላሰለፈ የለውጥ ኃይል፥ ዘራፊው ቡድን የቆመበትን መሠረት ለመነቅነቅ፣ ብሎም እስከ ወዲያኛው ለማስወገድ ይደፍራል ማለት ዘበት ነበር። ስለዚህ ሁለቱ አመራሮች ከኦሮሞና ከአማራ ሕዝብ ወገን መሆናቸው ሰፊውን ሕዝብና ብዙኃኑን ልሂቅ አስተባብሮ ከለውጥ ጎን ለማሰለፍ በእጅጉ ስለሚረዳ፣ ደመቀ በቦታው መቆየቱን እንፈልገው ነበር።

በእርግጥ ያወቅት በኢትዮጵያ ተከታታይ አስቸኳይ ጊዜ ዐዋጆች እንዲወሰኑ የሚያስገድዱ ቀውሶች እዚህም እዚያም የተፈጠሩበት አስቀያሚ የአስተዳደር ጊዜ ነበር። ይሄንን ኢያዩ የመንግሥት ሥልጣን ጥንቅር ብሎ ይቅር ቢባል የሚደንቅ አይሆንም። ምንም ማድረግ በሚያስችልና እጆች በፖለቲካ ካቴና በታሠሩበት የመንግሥት ኃላፊነት ላይ ተቀምጦ አስከፊውን ሁኔታ ቆሞ ማየት፣ በርግጥም ቀቢጸ ተስፋ ውስጥ ሊከት ይችላል። በዚያ ስሜት ውስጥ ኃይለ ማርያም መልቀቂያ ሲያስገባ ደመቀም ተከትሎ ለመልቀቅ ቢከጅል እምብዛም አይደንቅ ይሆናል።

ዳሩ ግን አጋጣሚውን ከለውጥ ትግሉ አንጻር ሲያዩት የደመቀ ለመልቀቅ ማሰብ፣ ኢትዮጵያን ወደ መልካም የሪፎርም ጎዳና ለማሻገር የተፈጠረውን ያንን ዕድል ያመነምነዋል። ለዘራፊው ኃይልም የራሱን ሰው በምክትል ስም አስቀምጦ ዕድሜውን እንዲያረዝም በር ይከፍታል። የብስጭቱ ምክንያት ይሄ እንደነበር ከተነጋገርን በኋላ፣ አሳቡን የጋራ በማድረግ ከደመቀ ጋር የነበረን መግባባት ምንም ዓይነት ጥላ ሳያጠላበት ቀጠለ። ይሄም የተጀመረውን ትግል ወደ ቀጣይ ምዕራፍ ሊያሻግረው በቅቷል።

## “ሪፎርሙ” እንደ መንገደኛ!

ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትናፍቀው የነበረው የለውጥ ተስፋ አንዴ መጣ ሲሉት ድንገት እየተመለሰ፣ ቦግ ማለት ይጀምርና ሕዝብ ዐይኑን ከፍቶ ሲጠብቅ መልሶ እየደበዘዘ፣ ሀገራችን በተደጋጋሚ ስትሳቀቅ ቆይታለች። ያም ሆኖ ተስፋዋን አንከብክበው ከደጇ የሚያደርሱ የለውጥ መንገዶችን ተስፋ ከማድረግ ቦዝና አታውቅም። ሁሌም በተስፋ፣ ደጅ ደጁን እያየች የተመኘችውን የለውጥ እሸት ሊያቀምስዋት የቆረጡ ልጆቿን ትጠብቃለች። ከዓሥራ ዘጠኝ ሃምሣ ሦስቱ መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ጀምሮ ስድሳ ስድስት ላይ፣ ሰማኒያ ሦስት ላይ፣ ዘጠና ሰባት ላይ፣ እንዲሁም አሁን ሁለት ሺሕ ዓሥር ላይ የለውጥ በትር ያነገቡ ልጆቿ ብቅ ሲሉ ጠይም ፊቷ ፈክቷል። የብርሃን ጸዳል በደጇ ተዘርግቶ በሐሴት ፈንድቃለች።

ቀደም ያሉት የለውጥ እንቅስቃሴዎች ሲጀምሩ፣ ሀገራችን ቀና ካለች በኋላ ብዙም ሳይቆይ አንገቷ እንዲሰበር ያደረጉ አጋጣሚዎች ነበሩ። ዳግም ተስፋ እያደረገች እንድትጠብቅ የተገደደችባቸው ጊዜዎች ከአንድም ሦስትና አራት ይሆናሉ። ቢሆንም ተስፋ ሳትቆርጥ ባደረገችው ትግል ሌላ ዘመን፣ ሌላ የለውጥ ኃይል ተፀንሶ

መወለዱ አልቀረም። ብሩህ ተስፋን የሰነቀ አዲስ የለውጥ መንገድ አሁን ከደጃ ተዘርግቷል። ምን ይዞ ይመጣ ይሆን? በወቅቱ ሁሉም ኢትዮጵያዊ መልሱን በጉጉት የሚናፍቀው ወሳኝ ጥያቄ ነበረ።

እንደሚታወቀው ለረጅም ዘመናት የመንግሥት ቤት የሸረሪት ድር አድርቶበት ቆይቷል። አዲሱ ለውጥ ከተወለደ በኋላ የሪፎርሙ የመጀመሪያ ተግባር በመንግሥት ቤት ውስጥ ለዓመታት ሲከማች የቆየውን ቆሻሻው ጠርጎ ቤቱን ንጹሕ ማድረግ ነበር። ወደ ጽዳት ሲገባ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችና አጋዥ ቁሳቁሶች መሟላት ነበረባቸው። በጥንቃቄና በጥበብ እያንዳንዱ አስፈላጊ ቁሳቁስ መሰናዳት አለበት። ያለ ምንም ዝግጅት አጉል ነካክተን በምናስነሣው አቧራ ለውጡን በእንጭጩ ታፍኖ እንዲሞት መንገድ ከምንከፍት፣ እስከናካቴው መጥረግ አለመጀመሩ የተሻለ ነበር። ስለዚህ በዚሁ ጉዳይ በለውጥ ቡድኑ ውስጥ የጋራ አቋም መያዝ ግድ አለ። በመርሕ ተደረሰ።

ሪፎርሙ በዋናነት ሁለት ዓላማዎችን ያነገበ ነበር። አንደኛው፦ ሲዘረፍ፣ ሲጨቁን፣ ሲያስርና ሲገድል የነበረው ኃይል፣ ይሄም አልበቃ ብሎት የሕዝብን አንድነት በመሸርሸር ሀገር አንድትፈርስ ሌተ ቀን የሚተጋውን ኃይል ከመካከላችን ገሸሽ ማድረግ ነው። ሁለተኛው፦ ለዚች ምስኪን ባለብዙ ተስፋ ሀገር፣ በቁመቷና በወርዷ የተሸመነ፣ የሚመጥናት ፓርቲና የመንግስት አስተዳደር መፍጠር ነው።

ያም ሆኖ ሀገር አፍራሹ ኃይል ለዓመታት ጡንቻው ሲፈረጥም ስለኖረ በቀላሉ የሚወገድ አልሆነም። መረቡን በጣጥሶ ባዶ እጁን ለማስቀረት አንድ ሀገር ብዙ ሊያሰልፈን፣ብዙ ዋጋ ሊያሰከፍለን፣ጠባሳ ሳያስቀር ላይነቀል ቆርጦ ከፊታችን ቆሟል።

# የብልጽግና ውልደትና<br>የአጋጠሙ ፈተናዎች

ኢሕዴግን እንደ ድርጅት ለኢትዮጵያ የሚስማማና ዘመኑን የዋጀ አድርጎ ሪፎርም የማድረጉ እንቅስቃሴ፣ በመጨረሻ "መደመርን" እንደ መንገድ "ብልጽግናን" እንደ መዳረሻ አድርጎ ተከናውኗል። ብልጽግና ፓርቲ የተወለደበት አካሄድ ብዙ ውጣ ውረዶች የታዩበት ነበር። ፈተናዎቹ ከአንድ አቅጣጫ ብቻ አልነበሩም። ከውስጥም ከውጭም ትግል የተደረገበት ፈታኝ ሥራ ነበር። ፓርቲው የሚገጥሙት ፈተናዎች ወደፊትም ቀጣይ ስላለመሆናቸው ምንም ማስተማመኛ አልነበረም አሁንም የለም። ብቸኛው ማስተማመኛ በየጊዜው የሚገጥሙ ፈተናዎችን የሚሸከም መዋቅር ለማደራጀት ተከታታይ ሥራዎችን እየሠሩ መቀጠል ነው። አልቋል ብሎ መቀመጥ አንድ ርምጃ እንኳን እንደማያስኬደን ሳይታለም የተፈታ ሐቅ ነው። በፈተናዎች ውስጥ ሆነን

የሠራነው እንደመሆኑ መጠን ፓርቲያችን “ጨርሶ በመጀመር” መርሕ የተገነባ አልነበረም።

ጨርሶ የመጀመር መርሕ ማሳያ የሆነውን የላሊበላ ኪነ ሕንጻ እንፈትሽ። ኪነ ሕንጻውን ልብ ብሎ ለተመለከተው የታነጸበትን ዘመን ለማመን አዳጋች የሚያደርጉ አያሌ ነገሮችን ያገኝበታል። ከተራራ ውስጥ እንደዚያ ዓይነት ውበት ይወጣል ብሎ ማሰብ በራሱ እጅግ የሚደንቅ ነው። ነገር ግን ከዚህም በላቀ መልኩ አሠራሩ ምን ያህል በምናብ ተሠርቶ ያለቀ እንደሆነ የሚያመልክቱ ሕያው ምልክቶችን ይዟል።

እንደሚታወቀው የላሊበላ ቤተ ጊዮርጊስ ከአናቱ የመስቀል ቅርጽ ያለው ሲሆን መስቀሉን ተከትሎ መሐሉ ላይ ቀጫጭን ቦዮች ተበጅተውለታል። እነዚህ ቦዮች እንግዲህ ዝናብ በመጣ ሰዓት ከላይ ከአናቱ ውኃ እየተከማቸ ድንጋዩን እንዳይፈረፍረው ለማድረግ በማሰብ የተሰሩ ናቸው። ቦዮቹ ማብቂያ ላይ እንደ አሸንዳ ሆኖ እንዲያገለግሉ፤ድጋዩ ሲጠረብ ሴንቲ መተርሮችን ተረፍ እንዲል ተደረጓል።በዚህም ምክኒያት ከላይ የሚወርደው የዝናብ ውኃ አንጥፍጣፊው የሕንጻውን ግድግዳ ሳይነካው ስለሚወርድ ለአያሌ ዘመናት የደንጋይ ግድግዳው ከመፈርፈር ተጠብቋል። እጅግ የሚደነቀወ ነገረ አሸንዳዎቹ ሕንጻው ከላይ ወደ ታች ተቀርጾ ካለቀ ቡኃላ ታስበው የተቀመጠ ቅጠያዎች ሳይሆን ከመጀመሪያውም መሐንዲሶቹ ወደፊት የሚመጣውን አርጋ ክንዛቤ አስገብተው የቀረጹት የወጥ ደንጋዩ አካል የሆኑ ናቸው። ይህ ሁኔታ ጨርሶ ለመጀመር ትልቅ ማሳያ መሆን ይችላል። አንድ ነገር ሲሰሩ እያንዳንዱን ጥቃቅን ነገር አንጠርጥሮ አስቦ መጀመርን ያስተምራል።

ይሄን ሁኔታ ወደ ብልጽግና ፖለቲካችን ስናመጣው ፓርቲያችን ጨርሶ በመጀመር ያልታደለ ሆኖ እናገኘዋለን። የዚህም ዋነኛ ምክንያቱ የፓርቲ ውልደት ሂደቱ በእንቅፋቶች የተሞላ በመሆኑና አነሣሽ መንሥኤውም በወቅቱ ሀገራችን የገባችበት ፈተና በመሆኑ ነው።

እንደሚታወቀው ይሄ ለውጥ እንዲመጣ፣ ሕዝቡም ኢሕአዴግን አምርሮ እንዲታግለው መንሥኤ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል፣ የመንግሥት ሥርዓቱ በሕገ ወጦችና እጃቸው በብዙ ወንጀሎች በተጨማለቁ ሰዎች ቁጥጥር ሥር መውደቁ ነበር። ከላይ እስከ ታች ሥርዓቱን የሚያሾሩት ኃይሎች ለሀገር ልማት ከመጨነቅ ይልቅ ለግልና ለቡድን ጥቅማቸው የሚሯሯጡ፣ ሕዝቡን ከማገልገል ይልቅ በተለያዩ መንገዶች ሲጨቁኑት የነበሩ ናቸው።

ኢሕአዴግ ደርግን ገርስሶ ሥልጣን ሲረከብ ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲን፣ ልማትን፣ እኩልነትና ነጻነትን አጎናጽፋለሁ ብሎ ቃል ገብቶ ነበር። ነገር ግን የገባውን ቃል ወደ ተግባር ለመለወጥ ሲነሣ፣ ከዚያ ቀደም ያልታዩ ዐመሎች በድርጅቱ ውስጥ መታየት ጀምረዋል። በተለይም ድርጅቱን በበላይነት ለመቆጣጠር ሲጣጣር በነበረው ሕወሓት ውስጥ ቀስ በቀስ እያቆጠቆጠ በመጣው የጭቆና አዝማሚያ እና የሕገ ወጥ እንቅስቃሴ መረብ ተሳታፊ የሚሆኑ አካላት ከዕለት ወደ ዕለት ቁጥራቸው ያድግ ነበር። በዚህም ምክንያት ቀስ በቀስ ኢሕአዴግ እንደ ድርጅት ዐቅሙ እየፈረጠመ በመጣው የሕገ ወጦች ስብስብ እጅ እየወደቀ፣ በጊዜ ሂደት ለውጥ ናፋቂዎቹ ቁጥራቸው እየተመናመነ መጣ። ፓርቲውን ብቻ ሳይሆን የመንግሥት ሥርዓቱንና

ቢሮክራሲውን ሙሉ ለሙሉ ጥገኛው ኃይል በቁጥጥሩ ሥር አዋለው። በኋላም የሕዝብ ምሬት ሲገነፍልና በድርጅቱ ውስጥ የቀሩት ጥቂት ለውጥ ፈላጊዎች ከሕዝብ ጥያቄ ጎን መሰለፍ ሲጀምሩ፣ ምን እንደተከተለ ሁሉም ሰው ያውቀዋል። ወርኃ መጋቢት፣ 2010 ዓ.ም. ላይ አዲሱ የለውጥጉዞ ተበሠረ።

ብልጽግና ጨርሶ በመጀመር" መርሕ እንዳይመሠረት ያደረገው ምክንያት የሚመነጨው ከዚህ ነው። ፓርቲው በአንድ ጥላ ሥር ያሰባሰባቸው ሰዎች በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ሕገ ወጥ ኃይል የሚፈጽማቸውን ወንጀሎች ተጸይፈው ትግል ማድረግ ጀመሩ እንጂ፣ ቀጣይ ፓርቲያቸውና ቀጣዩ መንግሥታዊ ሥርዓት ምን ሊመስል እንደሚችል ጥንቅቅ አድርገው አስበው ከጻፉ በኋላ ትግላቸውን አልጀመሩትም። የለውጥ ብሥራት ከተሰማ በኋላ ኢሕአዴግ የማሻሻል ዕድል ተሰጥቶት በመንግሥት ሥልጣን ላይ ሲቆይ፣ በውስጣችን አብሮን የቆየውን ያንን አደገኛ ኃይል አስተምሮ መተው ይቻል ነበር። ነገር ግን ሕወሓት ለመማር የተዘጋጀ አልሆነም። በተቃራኒው ችግር እየፈጠረ የሕዝቦችን ተስፋ ማጨለሙን ዋነኛ ሥራው አደረገው። ቀደም ብሎ የሠራቸውን መጥፎ ተግባራት በጋራ ሆኖ ለማረምና ሕዝብን ለመካስ ምንም ፍላጎት ሊያሳይ ባለመቻሉ የለውጥ ቡድኑ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አምርሮ ሊታገለው ከውሳኔ ላይ ደረሰ። ከውሳኔው በኋላ ቡድኑን ያቆመው ምሦሶ ምን እንደሆነ ለማጥናት የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል።

የሕወሓት ሥርዓት የተቀመጠበትን መደላድል በአራት እግር ወንበር ልንመስለው እንችላለን። በርግጥ እነዚህ እግሮች ብቻቸውን የቆሙ አይደሉም። ሌሎች የሚያጠናክሯቸው ድጋፎችም አሏቸው። ነገር ግን ዋነኞቹ ምሦሶዎች አራት ስለመሆናቸው ያደረግነው ጥናት ያሳያል። ሕወሓትን ለመታገል ስንወስን ሥርዓቱ የተቀመጠባቸው አራቱ የወንበሩ እግሮች በጥንቃቄ ከተቆረጡና መሬት ላይ ከአወረድነው፣ ከኢትዮጵያ ትከሻ ላይ ብዙ ሸክም እንደሚቀል ርግጠኞች ነበርን።

የሕወሓት የዙፋኑ መሠረት የሆኑትን አራት እግሮች ምን ምን እንደሆኑ በጥናት ከለየን በኋላ እንዴት ይቆረጡ? የሚለውን ወደ ማየት ገባን። ያን ጊዜ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች ከፊታችን እንደተዘረጉ ግልጽ ይሆንልን ጀመር። እነዚያን እግሮች መነካካት በራሱ ከባድ የሆነ ነገር ነበረው። ሁሉም ሰው እንደሚያውቀው ወደ ለውጥ የመጣው ኃይል የራሱ የሆነ ወታደር አልነበረውም፤ ትጥቅ የለውም፤ የሚተማመንበት የራሱ ኃይል የለውም። ባዶ እጁን ወደ ቤተ መንግሥት የገባ ነው። ቤተ መንግሥት ሲገባም እንኳን ግቢውን የሚጠብቁ ኃይሎች ይቅርና የራሱ አጃቢዎች እንኳን የሉትም ነበር።

ሁሉም የቤተ መንግሥቱ ኃይሎች የቀደመው ሥርዓት ታማኝ ወታደሮች ነበሩ። እኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሆንኩ በኋላ የሚጠብቁኝ መቶ በመቶ ሕወሓት ያቆማቸው ጠባቂዎች ነበሩ። እነርሱን ይዞ የወንበሩን እግሮች ለመቁረጥ ማሰብ ጋዝ ይዞ ወደ እሳት የመጠጋት ያህል ነበር። ስለዚህ ሕወሓት የቆመባቸውን አራቱን የወንበር እግሮች መለየትና ለመቁረጥ መንቀሳቀስ ብቻውን በቂ አልነበረም። ወንበሩ ባዶውን ዘጭ ማለት ያለበት ብዙ አደጋ በማያደርስ መልኩ ተቆርጦ ነው።

የወንበር እግር ቆረጣው "በምን ዓይነት መንገድ ቢከናወን ይሻላል?" የሚለው የመጀመሪያው የሪፎርሙ ንድፍ

ሆነ። ያም ሆኖ ንድፉን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረ ቀላል ሥራ አልነበረም።

ሁሉም ነገር ውስብስብ በነበረበት ወቅት፣ የወንበሩን እግሮች ቀስ በቀስ በመገዝገዝ፣ በመጨረሻ ቆርጠን የምንጥለው እንዴት አድርገን ነው? በሚለው ዙሪያ ልዩ ልዩ ታክቲኮች ተጠቅመናል። ከነዚህ ታክቲኮዎች መካከል የመጀመሪያው ሕዝቡን ከጎናችን ማሰለፍ ነበረ።ሕዝቡን ከጊናችን አንዴ ማሰለፍ ከቻልን ከሕወሓት ኃይሎች የበለጠ ሕዝቡ መከታ እየሆነን ሥራችንን ለመስራት ነገሮች ቀላል ይሆኑልናል፡፡ በተቃራኒው ሕዝቡን ከማሰለፋችን በፊት ወደ ሕግ ማስከበር ኤጀንሲዎች ሪፎርም፣ ፖለቲካውና የኢኮኖሚ ተቋማቱ የምናነጣጥር ከሆነ ሪፎርሙ ውጤታማ የመሆኑ ነገር አያስተማምንም።

ስለዚህ ከሥርዓቱ ይልቅ ፊትን ወደ ሕዝብ መመለስ እንደሚበጅ ታመነበት። አፋጣኝ ምላሽ ወደ ሚያስፈልጋቸው የሕዝብ ፍላጎቶች ፊትን አዙሮ ከሕዝብ ጋር ተግባቦት መፍጠር የቅድሚያ ቅድሚያ በዚህም መሠረት ነው እስረኞችን መፍታት የጀመርነው። በቅርብም በሩቅም የሚኖሩ ተፎካካሪ ፖለቲከኞችን ወደ ሀገር ጋበዝን። ከኤርትራ ጋር ያለውን መጥፎ ግንኙነት በዕርቅ ቋጨን። የተዘጉ ሚዲያዎች ተከፈቱ፤ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ተረጋገጠ። በአሸባሪነት በተፈረጁ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ላይ የተጣለውን እገዳ አነሣን።

እነዚህን ተግባራት በተከታታይነት ስንፈጽም፣ በጥቂት ወራት ውስጥ በአንድ በኩል ሕዝቡ "ለውጡ የእኔ ነው" ብሎ ቆሞለታል፤ በሌላ በኩል መሐል ላይ ያለው ኃይል ደንዝዞ እንዲጠብቅ፣ "ወዴት ነው የምንሄደው?" እያለ ግራ እየተጋባ እንዲቆይ አድርጎታል። በዚህ መሐል በአራቱም አቅጣጫ ከሕዝብ ጋር ለመገናኘት የሚደረገው እንቅስቃሴ ይበልጥ ሕዝቡ ለለውጡ ደጀን እንዲሆን፣ በተጻራሪው የቆመው ኃይልም የጥፋት ዕቅድ ለመንደፍ በማያመቸው ሁኔታ በግራ መጋባት ውስጥ ሊቆይ ተገድዷል።

ከዚያ በኋላ ነው፤ በሀገር ውስጥም በውጭም የሚኖረው ሕዝብ በአንድ ድምፅ ለለውጡ ጋሻ መሆኑን ተገንዝበን ወደ ዋናዎቹ የወንበሩ እግሮች ትኩረታችንን ማድረግ የጀመርነው።

## እግር አንድ - የሕግ ማስከበር ተቋማት

የመጀመሪያው እግር የሕግ ማስከበር ተቋማት ናቸው። በዚህ ዘርፍ ሥር የሚሰፍሩ ተቋሞች ስምንት ገደማ ቢሆኑም ከእነዚህ መካከል ዋነኞቹና ፈታኞቹ ስድስቱ ናቸው። እነሱም፦ የሀገር መከላከያ፣ የብሔራዊ ደኅንነት ቢሮ፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ እና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ናቸው።

እንደሚታወቀው የመከላከያ ሠራዊት ከላይ እስከ ታች በዋናነት የሚመራው በሕወሓት ታጋዮች ነበር። ይሄ መከላከያ ተቋም ከዋነኛው ተልእኮው የሀገርን ዳር ድንበር ከማስጠበቅ በተጨማሪ፣ እንዳስፈላጊነቱ የሕወሓት ሥርዓት ቀጥ ብሎ በሙሉ ቁመናው እንዲቀጥል ለማድረግ ጥቅም ላይ ሲውል ነበር። አስፈላጊ ሲሆን ለማስፈራሪያነት፣ አስፈላጊ ሲሆን ለማሠር እና አስፈላጊ ሲሆን ለመግደልና ለመዝረፍ እንደ አንድ አማራጭ ሆኖ በማገልገል የሥርዓቱን ህልውና ያስጠብቅ ነበር።

የብሔራዊ ደኅንነት ቢሮንም የሚዘውረው የሕወሓት ታጋይ እንደነበር ይታወቃል። ይሄም መሥሪያ ቤት

እንደፈለገው የሚያስር፣ የሚፈታ፣ የሚገድልና የፈለገውን የሚያደርግ ከልካይ ያልነበረበት ተቋም ነበር። በተመሳሳይ በገንዘብና በልዩ ልዩ ሎጅስቲኮች ጡንቻው ፈርጥሞ የነበረውና እንዳሻው ግለሰቦችን በምስጢር የሚከታተል፣ ሳይበር ላይ የሚንቀሳቀሱ ሚዲያዎችን የሚዘጋ፣ ሌሎች በኅቡዕ የሚሠሩ የስለላና የምስጢር እስሮችን ሲያከናውን የነበረው ተቋም የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ የሚመራው በሕወሓት ሰው ለድርጅቱ የግል ጥቅም ነበር። የፌደራል ፖሊስና የአዲስ አበባ ፖሊስ ተቋማት በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚመሩት በሕውሓት ታጋዮች ነበር። እነርሱም ለድርጅታቸው ጥቅም ሲሉ አያሌ ወንጀሎችን ሲፈጽሙ ነበር። ሌላኛውና የመጨረሻው የፋይናንስ ኢንተለጀንስ ተቋም ነው። እሱም በማይታይ መልኩ ከፍተኛ የፋይናንስ ወንጀሎችን የፈጸመና አንዱ የሕወሓት ሥርዓት ምርኩዝ የነበረ ነው።

እነዚህ ስድስት ተቋማት ማፈኛ፣ ማሰሪያና መቅጫ ሲሆኑ በዋናነት በሕወሓት ቁጥጥር ሥር የነበሩ ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ ዐቃቤ ሕግ እና ከፍተኛው ፍርድ ቤቶች ውስጥ የሕወሓት ታጋዮች ቁልፍ ቦታ ይዘው ልዩ ልዩ ሕገ ወጥ ተግባራትን ሲፈጽሙ ነበር።

ሰዎች ሲያስቸግሩ ክስ ለመመሥረትና ለማስር ከደኅንነት መሥሪያ ቤት ጋር በመሆን መረጃዎችን እየተለዋወጠ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ሥር የሕግ ክፍሉን ይመራ የነበረው ኃላፊ፣ ትልቅ ተጽዕኖ ሲፈጥር ነበር። ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በተመሳሳይ በምክትሉ አማካኝነት የሕወሓትን ህልውና የማስጠበቅ ተልእኮ ተሰጥቶት ሲሠራ ቆይቷል።

በዚህ መልኩ ኢሕአዴግ ቤት ውስጥ የሕግ ማስከበርን በተመለከተ ኢትዮጵያ ውስጥ ምን እየተከናወነ እንዳለ መረጃዎች የሚፈሱለት ወደ አንድ ቋት፣ እሱም ወደ ሕወሓት ነበር። የተቀሩት የኢሕአዴግ እኅት ድርጅት ስለ ፍትሕ አካላት፣ ስለ ጸጥታ ተቋማትና ስለ ደኅንት መሥሪያ ቤቶች ምንም ዓይነት መረጃ ሳይኖራቸው፣ በጭፍን ተከታይ ሆነው ኖረዋል። በሕግ ማስከበር ተቋማት ላይ የቆመውን የሕወሓት እግር ለማሳጠር ባደረግነው እንቅስቃሴ ተቋማቱን የሚመሩ ኃላፊዎችን በሌሎች ተክተናል።

ከዚህም ባለፈ በአስተሳሰብና በአሠራር ደረጃ ተቋማቱ ሲከተሏቸው የነበሩበትን የአንድ ቡድን አመለካከት ቀይረናል። የኃላፊዎችን ስብጥርም ከተለያዩ ብሔረሰቦች የተውጣጡ በማድረግ ተከናውኗል። በዚህ ምክንያት አንድን ቡድን የሚሸተው የሕግ ማስከበር ተቋም ኢትዮጵያን ሊመስል ችሏል።

## እግር ሁለት - የፓርቲ ሥርዓት

በጣም ወሳኙ እግር፣ የሕግ አስከባሪ ተቋማቱን ጭምር እንደየ አስፈላጊነቱ በተለየ መንገድ የመምራትና የመገምገም ሥልጣን ያለው የፓርቲ ሥርዓቱ ነበር። ይሄም ሲባል ብዙ ነገሮችን ያካትታል። በዋናነት የፓርቲውን አሠራር፣ ሕግና ደንቡን፣ እንዲሁም ፓርቲው የሚመራበትን ርእዮተ ዓለም ያጠቃልላል። ይሄ የፓርቲ አሠራር ሦስት ገጾች አሉት። የመጀመሪያው ገጽ ሐሳብ ማመንጨትና ዶክመንት ማዘጋጀት ሲሆን እነዚህ በዋናነት በሕወሓት ቁጥጥር ሥር የሚገኙ ናቸው። በፓርቲው ታሪክ ውስጥ ከሕወሓት ውጪ የሚጽፉና ሐሳብ የሚያመነጩ አልነበሩም። እነርሱ ጽፈው፣ ተወያይተውና የጋራ አቋም ከያዙ በኋላ እኅት ፓርቲ የሚባሉትን

ያጠምቃሉ። አጀንዳውን ይዘው መጥተው "ይሄ ነው የምንሄድበት" ይላሉ፣ በየመድረኩ እየሄዱ ያስወስናሉ። የተቀሩት እኅት ድርጅቶች እጅ ከማውጣትና አልፎ አልፎ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ባለፈ ጽፈው፣ ሐሳብ ይዘው መጥተው፣ አጀንዳ ማስያዝ ብሎ ነገር ፈጽሞ የለም ነበር።

ከሌሎች የኢሕአዴግ አጋር ድርጅቶች አንጻር ሲተያይ ሦስቱ እኅት ድርጅቶች (ኦሕዴድ፣ ብአዴንና ደኢሕዴን) የሕወሓትን ቀጣይ ዕቅድና አቅጣጫዎችን ከሌሎች ቀድመው ይሰማሉ። ከሌሎቹ ይልቅ ቀድሞ ሰሚ የመሆን አንጻራዊ ብልጫ ነበራቸው ሊባል ይችላል። አጋር ድርጅት የሚባሉት (የጋምቤላ፣ የሱማሌ፣ የአፋር፣ የቤኒሻንጉልና የሐረሪ ድርጅቶች) ዕቅዱን የመስማት ዕድል እንኳን አልነበራቸውም።

አጋር የሚባሉት ፓርቲዎች፣ ሕወሓት ያሰበውን እና ብአዴን፣ ኦሕዴድና ደኢሕዴን በጋራ ሆነው የሰሙትን ጉዳይ ማስፈጸም እንጂ ሐሳብ ለማዋጣትም ሆነ ሰምቶ ጥያቄ ለመጠየቅ ዕድል አልነበራቸውም። በዚህ መልኩ ነበር 27 ዓመት ያለፈው። ይህ የፓርቲ ሥርዓት ቁልፍ የመንግሥት መዋቅርን በእጁ አድርጎ ሳለ ሙሉ ለሙሉ የሚመራው በአንድ ፓርቲ፣ በሕወሓት ፍጹም የበላይነት በመሆኑ፣ይሄን መቀየር የሀገር ልብ እንደመቀየር ነበር።

ነገሩን ሰፋ አድርገን ስንመለከተው በሕወሓት የበላይነት ሲመራ የነበረው የፓርቲ ሥርዓት ከፋፋይነቱ ከፓርቲው አልፎ ሀገራችን የቆመችበትን መዋቅር ጭምር ያናጋ ነበር ማለት ይቻላል። ለባለፉት ሦስት ዐሠርት ዓመታት በሀገራችን የነበረው ትርክት እጅግ ከፋፋይ ነበር። የተወሰነውን ሕዝብ እንደ ዋና፣ የተወሰነውን ሕዝብ ደግሞ እንደ አጋር ቆጥሮ የሀገር ባለቤትነትን ጥያቄ ውስጥ በሚያስገባ መልኩ የሚቃኝ ነበር። አንዱ ተወዳድሮ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን የሚችልበት፣ ሌላውን ደግሞ ፈጽሞ ጠቅላይ ሚኒስትር የመሆን እድል የሌለው የሚያደርግ እሳቤ ነበር። አንዱን እንደ ጠባብ ቆጥሮ እንደተገንጣይ የማየት፣ ሌላውን ደግሞ ትምክህተኛ ብሎ የመፈረጅ ሰፊ ዘመቻ ነበር። ይህ አላስፈላጊ የሆነ ዘመቻና መጥፎ ትርክት፣ ኢትዮጵያ የቆመችበትን የጋራ የትርክት መዋቅር የሸረሸረና ጠንካራ ሀገር እንዳይኖረን ያደረገ ነበር። የዚህ በትርክትና በጎራ የመከፋፈል እንቅስቃሴ በዋናነት የሚቀዳውም ፓርቲው (ኢሕአዴግ) ከሚከተለው እሳቤ (የአብዮታዊ ዴሞክራሲ) ነበር። ስለዚህ ኢትዮጵያ የቆመችበትን ምሦሶ መልሶ ለማጠንከር በሚደረገው ጥረት ውስጥ ፓርቲያችን የሚከተለውን እሳቤ በተገቢው መቃኘት የግድ አስፈላጊ ሆኗል።

ይሄን ለማድረግ ሕወሓት ፓርቲውን ጠቅልሎ የያዘበት አስተሳሰብ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መሥመር እና የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት, አሠራርን የሚተኩ አማራጭ መንገዶች መነደፍ ነበረባቸው። ለዚህም መደመር የተሰኘውን ሁሉን አቀፍ የሆነ የፓርቲ መንገድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆነ። አለፍ ሲልም  በአራቱም አቅጣጫ የሚኖሩ ሕዝቦችን በእኩል የሚያቅፍና ዴሞክራሲያዊ የሆነ ፓርቲ መመሥረት አለበት።

ስለዚህ የአዲሱን ፓርቲ ስያሜ፣ ዓርማ፣ ሕገ ደንብ፣ እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የፓርቲው አሠራሮች በሰነድ ደረጃ ከተዘጋጁ በኋላ ፓርቲውን በስያሜና በመዋቅር ደረጃ ኅብረ ብሔራዊ መልክ ኖሮት ሪፎርም ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ይሄ ሪፎርም በውስጣችን ያሉትን የሕገ ወጥ ቡድኑ የውስጥ ዐርበኞች ለመቀነስ እጅግ ወሳኝ ነበር። ተግባራዊ ማድረጉ ግን ከባድ ራስ ምታት ላይ የሚጥል ከመሆኑ አኳያ ስሕተት እንዳይፈጠር

በከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ ነበረበት።

የዶክመንት ዝግጅት፣ የመዋቅር ዝግጅት እና ሕገ ደንቦችና የፓርቲ የአሠራር ሒደቶች ዝግጅት ከሞላ ጎደል ሳይጠናቀቁ በፊት ወደ ፓርቲ ሪፎርም መግባት እጅግ አደገኛ መሆኑ አያጠያይቅም። በዚሁ ምክንያት ዶክመንቶችን አዘጋጅተን እስክናጠናቅቅ ድረስ ወደዚህ አጀንዳ ሳንገባ ቆይተናል። ሁሉም ከተሰናዳ በኋላ አጀንዳው መነሣት ሲጀምር ሕወሓት "ቆይ ላስብበት" ማለት ጀመረ። እነርሱ ተወያይተውበት እስኪጨርሱ ባለው ጊዜ ውስጥ በተዘጋጁት ሰነዶችና መመሪያዎች ላይ የቀረነው መወያየትና የጋራ አቋም ወደመያዝ መጣን። ሕወሓት ላስብበት› ማለቱ መፍትሔ ለማምጣት ባለመሆኑ በዚያ አጭር ጊዜ ውስጥ ብዙዎቹን የፓርቲ ውሕደት ሥራዎች ለማጠናቀቅ ቻልን። በዚህ መልኩ ብልጽግና ተወለደ።

የብልጽግና መምጣት ፓርቲውን በስያሜ ደረጃ የቀየረ ብቻ አልነበረም። ዋናው ትኩረት የነበረው የፓርቲውን ሶፍትዌር ሙሉ ለሙሉ ከመቀየር ላይ ያነጣጠረ ነበር። በእሳቤ ደረጃ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በመደመር ተተካ፤ ይሄም ፓርቲውን ሁሉን አቀፍና ኅብረ ብሔራዊ እንዲሆን አስችሏል፤ ለቡድንና ለግል መብቶች ተመጣጣኝ ትኩረት እንዲሰጥ አድርጎታል፤ በልዩነት ላይ የተመሠረተውን የፓርቲ አሠራር ወደ ትብብርና አንድነት ለውጦታል። ከብቸኝነት ጉድለት በመውጣት በትብብርና በውድድር መካከል በሚፈጠር ሚዛን፣ ሀገራችንን ወደ ብልጽግና ጎዳና እንደምናደርሳት ስምምነት ላይ ደረስን።

የፓርቲው መዋቅር ለውጥ በፓርቲው ውስጥ ዋናና አጋር የሚለውን የሚያስቀር በመሆኑ ትልቅ ለውጥ ነበር። ከፓርቲ አደረጃጀት አኳያ በሀገራችን በብልጽግና ደረጃ ኅብረ ብሔራዊ የሆነ ፓርቲ አለ ለማለት አያስደፍርም። በታሪካችን ቀደም ብሎ ኅብረ ብሔራዊ የነበሩ ፓርቲዎችን እንደ ኢሕአፓ፣ መኢሶን፣ ቅንጅትና የመሳሰሉትን ልናነሣ እንችላለን፤ ነገር ግን በብልጽግና ልክ ኅብረ ብሔራዊ አልነበሩም። እነዚያን ድርጅቶችን በአግባቡ ብንፈትሽ ምናልባትም በውስጣቸው አንድም ሱማሌ፣ አንድም ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል፣ አፋር ወይም ሐረሪ ላናገኝ እንችላለን።

ብልጽግናን ካየን ግን ከእነዚህ ክልሎች እንደ ግለሰብ ሳይሆን ፓርቲው ከእነአባላቱና ሥራ አስፈጻሚዎቹ ባንድነት ተጠቃለው የገቡበት እና በጋራ ሆነው የመሠረቱት ነው። ‹ብልጽግና እጅግ ኅብረ ብሔራዊ ነው የምንለውም ለዚህ ነው። የአባላቱን ስብጥር ብቻ ሳይሆን አሳታፊነቱን ከፍ ለማድረግ የፓርቲውን የሥራ ቋንቋ ወደ አምስት በማሳደግ ከየትኛውም የሀገራችን ፖለቲካ ድርጅት በላይ ዴሞክራሲን በተግባር ሊገልጥ ችሏል።

ይህ የፓርቲ ውሕደትና የአሠራር ለውጥ ዘራፊው ኃይል የተደገፈውን ሁለተኛ እግር የቆረጠ ነበር። ላለፉት 27 ዓመታት ዋነኛ ፈላጭ ቆራጭ የነበረውን ሕወሓት፣ በፓርቲው ውስጥ የነበረውን ሚና ከመቶ ፐርሰንት ወደ ዜሮ ያወረደ ነበር። የሕወሓትን ሕገ ወጥ ጉዞ የተፈታተነ፣ እንዴት ነው የምንቀጥለው የሚለውን ለመወሰን እንዲቸገሩ ያደረገ፣ ውሑዱን ፓርቲ በግላጭ ‹ጠላት› ብሎ እንዲፈርጅ ያስገደደ ነበር።

ይሄን ተከትሎም ብልጽግናን ለመዋጋት ሌሎች ኃይሎችን ማደራጀት የጀመረበት፣ ፓርቲዎችን ሰብስቦ እኛን ለመታገል ራሳቸውን የፌደራሊስት ኃይሎች, ብለው የሰየሙበት፣ ቀደም ብለው ጠላት አድርገው ከፈረጇቸው እንደ ኦነግ ካሉ ድርጅቶች ጋር ጭምር ድርድር የጀመሩበት አጋጣሚ ተፈጥሯል። እኛን ካላጠፉ በቀር መኖር

እንደማይችሉ በማሰብ ለጦርነት የወሰኑበት እና የረጅም ዘመናት ጉዟቸውን በአጭሩ ለማስቀረት የተገፋፉበትን ዕድል ፈጥሯል፤ የፓርቲው ሪፎርም።

## ሦስተኛው እግር – ፋይናንስ

ሦስተኛው መቆረጥ የሚገባው የወንበሩ እግር መገኛው የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ ነው። ባለፉት 27 ዓመታት ማፊያዊ በሆነ መንገድ ሕገ ወጥ ተግባራት የተፈጸመበት ዘርፍ ነው። የገንዘብ ሚኒስቴርን ጨምሮ ዋና ዋና የሆኑ የፋይናንስ ተቋማት በሕወሓት ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ቁጥጥር ውስጥ ነበሩ። የንግድ ባንክ የብድር ዘርፉ፣ ሜቴክ፣ ኢትዮ- ቴሌኮም፣ መብራት ኃይል፣ የስኳር ኮርፖሬሽን፣ የመንገዶች ባለ ሥልጣን፣ ባቡር፣ አየር መንገድ፣ ወዘተ. በሕወሓት የቅርብ ቁጥጥር እየተደረገባቸው ከፍተኛ ካፒታል ሲያንቀሳቅሱ የነበሩ ተቋማት ናቸው።

ከፍተኛ ገንዘብ ከማንቀሳቀሳቸው ባለፈ ተቋማቱ ከመንግሥት በጀት በተጨማሪ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ከፍተኛ ብድር ይገኝባቸዋል። ሀብታቸውንም እንደፈለጉ ለማድረግ ምቹዎች ነበሩ። በእነዚህና በሌሎች የፋይናንስ ተቋማት ላይ ሕገ ወጥ አሠራሮችን ለማጥራትና የአመራር ስብጥር ለመፍጠር በተወሰዱ ርምጃዎች ሕገ ወጥ ቡድኑ ቀደም ብሎ ሲያገኝ የነበረውን ጥቅም ወደ ዜሮ ለማውረድ ተችሏል።

ይህም ሲባል በእነዚህ ተቋማት ላይ የተደረገው ለውጥ ወደፊት ለሚፈጸም ዝርፊያ ተጋላጭ እንዳይሆን የሚያደርግ እንጂ ከዚህ ቀደም የተዘረፈውን ለማስመለስ የሚያስችል አይደለም። ተዘርፎ የተከማቸው ገንዘብ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ እንዲሁም በፖለቲካዊና ማኅበራዊ ኑሯችን ላይ ምን ዓይነት ሕገ ወጥ ተግባር እየተፈጸመበት እንደሆነ ሁሉም ሰው ያውቃል።

በሌላ በኩል ጥቂት የማይባሉ ግለሰቦች እና ከቀድሞ ሥርዓት ጋር የጥቅም ትስስር የነበራቸው አንዳንድ ኩባንያዎች በአንድም በሌላም መንገድ ግጭትን ፋይናንስ ሲያደርጉ ይስተዋላል። በከፍተኛ ሁኔታ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ በሀገሪቱ ይዘዋወራል። የጦር መሣሪያዎቹ ከጎረቤት ሀገራት በቀጥታ መጥተው መሐል ሀገር እና በአራቱም የሀገሪቱ አቅጣጫ ይከፋፈላል። በዩንቨርስቲዎች ብጥብጦች እንዲፈጠሩ ለማድረግ፣ በመኖሪያ መንደሮችና በአምልኮ ቤቶች የእሳት ቃጠሎችን ለማስነሣት፣ በቡድኖች መካከል እስከ ግድያ የሚያደርስ ጸብ ለመለኮስ ገንዘቡ በከፍተኛ ሁኔታ ይውላል። በጉቦ አማካኝነት ብዙ ወንጀሎች ይፈጸማሉ። ይሄንን ተከታትሎ ገንዘቡ የሚሠራውን ወንጀል ለማስቀረት ለመንግሥት ትልቅ ፈተና ሆኖ ቆይቷል። የት ታቅዶ የት ተግባራዊ እንደሚደረግ ቀድሞ ዐውቆ ወንጀሉን ለማክሸፍ ቀላል አይደለም። በመሆኑም ከፋይናንስ ጋር በተገናኘ ሌሎች ቀሪ ተግባራት መከናወን እንደሚገባቸው ግልጽ ነው።

ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ ሕገ ወጥ ተግባራትን ለመቀነስ ብሎም የፋይናንስ ሥርዓቱን ወደ ሚታወቅና ዘመናዊ ወደሆነ አሠራር ለማስገባት አዳዲስ ርምጃዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። ከእነዚህም መካከል ግለሰቦችና ኩባንያዎች በእጃቸው የሚይዙት ጥሬ ገንዘብ መጠን ላይ ገደብ ማበጀት አንደኛው ሲሆን፣ በቀን ከባንክ ማውጣት የሚችሉትን የብር መጠን በልኩ እንዲሆን ማድረግ ይገኝበታል። ግለሰቦች በቀን ከባንክ ማውጣት የሚችሉት ከ200 ሺሕ ብር እንዳይበልጥ ከተደረገ፣ በወር ደግሞ ከአንድ ሚሊየን ብር በላይ ማውጣት

ካልቻሉ የገንዘብ ዝውውሩን በባንክ ለማድረግ ስለሚገደዱ የግጭት ነጋዴዎቹ ዳናቸውን በቀላሉ ለማግኘት በእጅጉ ያግዛል። በተመሳሳይ ግለሰቦችና ኩባንያዎች ከ1.5 ሚሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብ በቤታቸው ማስቀመጥ አለመቻላቸው ለሕገ ወጥ እንቅስቃሴ የሚውለው ገንዘብ ዝቅ እንዲል ያደርጋል።

ከዚህ በተጨማሪ ዘራፊዎች በጎረቤት ሀገራት ያከማቹትን፣ ዘርፈው የቀበሩትን ማስመለሱ ከሞላ ጎደል በሕገ ወጥ ተግባራት ላይ የሚውለውን ገንዘብ በእጅጉ ስለሚቀንሰው ይሄንን ለማሳካት እጅግ ጥንቃቄ የተሞላበት እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባል። ከዚህ አኳያ ትልቅ ተጽዕኖ ሊያመጣ የሚችለው የገንዘብ ቅያሬ ሲደረግ ነው። ገንዘብ ቅያሬን በተመለከተ በሀገራችን የነበረውን አካሄድ ወደኋላ መለስ ብሎ መመልከቱ የገንዘብ ቅያሬ የማድረግ እንቅስቃሴ ምን ያህል ፈታኝ ጉዳይ እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል። በታሪካችን እስካሁን የገንዘብ ቅያሬ ካደረጉት መካከል አንዱ ደርግ ነው። በንጉሡ ዘመን የነበረውን መገበያያ ዓርማና ሌሎች ምልክቶችን በመለወጥ አዲስ ገንዘብ አትሞ ነበር።

ኢሕአዴግ ከመጣ ወዲህ እስከ ዘጠና ዓመተ ምሕረት ድረስ የገንዘብ ለውጥ አልተደረገም ነበር። ኢሕአዴግ ከሻዕቢያ ጋር ወደ ጸብ ሲገባ የገንዘብ ቅያሬ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ቀደም ብሎ የነበረውን ገንዘብ የቀለም ለውጥ በማድረግ የሀገሪቱ ገንዘብ እንዲቀየር ተደርጓል። ኢሕአዴግ የገንዘብ ለውጥ በሚያደርግበት ወቅት በሀገራችን የነበሩት የገንዘብ ኖቶች ብዛት (notes in quantity) 727 ሚሊዮን ሲሆን ባንድላይ ሲደመር የገንዘቡ መጠን (value of notes) 8 ቢሊየን ብር ገደማ ይሆናል። በአንጻሩ አሁን ያለው የገንዘብ ኖቶች ብዛት ከ2.9 ቢሊየን ከፍ ያለ ሲሆን፤ ይኽም ባንድ ላይ ተደምሮ የገንዘቡን መጠን ወደ 262.9 ቢሊየን ብር ይሆናል። የኖቶቹ ብዛት በዚህ ደረጃ ከፍ ማለት አዲስ ገንዘብ ለማሳተም የሚያስወጣውን ወጪ በብዙ እጥፍ እንዲጨምር ያደርገዋል። ከዚህ ባለፈ በዲዛይንና በጥራት ደረጃ አሁን ያለው ገንዘብ ብዙ ዓይነት ለውጦች ስለተደረጉበት ከዚህም በላይ ተጨማሪ ሀብት መፈለጉ አይቀርም።

ከዚሁ ከብር ቅያሬ ጋር በተያያዘ ልብ መባል ያለበት ሌላው ጉዳይ ለቅያሬው መነሻ የሆነው ምክንያት ነው። በሕገ ወጥ ቡድኑ ከዚህ ቀደም ተዘርፎ በጅቡቲ በኩል ድንበር ላይ፣ በሱዳን በኩል ድንበር ላይ፣ እንዲሁም በአፋር በኩል ድንበር ላይ ተከማችቶ የሚገኘው ገንዘብ በቦቴና በጭነት  መኪኖች አማካኝነት ወደ ሀገረ የሚገባ ከሆነ ቅያሬ ማድረጉ ከኪሣራ ውጭ ትርጉም አይኖረውም። ስለዚህ ያ ገንዘብ ወደ ሀገር እንዳይገባ በማድረግ የተዘረፈውን ገንዘብ ዋጋ ወደ ማያወጣ ወረቀት ለማሸጋገር በከፍተኛ ጥንቃቄ መከወን ይጠይቃል።  እንደሚታወቀው የገንዘብ ለውጥ ሦስት ወር ገደማ ይፈልጋል። ለዚያውም በዘጠናዎቹ ላይ ያደረግነውን የገንዘብ ቅያሬ መነሻ ካደረግን በሃያና ሠላሳ እጥፍ ያደገውን የገንዘብ ኖት በጥቂት ወራት እድሜ ቀይሮ ለመጨረስ ከፍተኛ ርብርብ ይጠይቃል።

የተዘረፈው ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት እንዳይገባ የጥበቃ መዋቅራችን ዓይኑን ሳይነቅል እንዲያከናውን ለረጅም ጊዜ የዐቅም ማጠናከር ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። በዚህ መልኩ አንድም የተዘረፈ ስባሪ ሳንቲም በቅያሬው ውስጥ እንዳያልፍ ሲደረግ ሁሉም እኩል ለፍቶ የላቡን ዋጋ ማግኘት ይጀምራል፤ በሀገራችንም ለሕገ ወጥ ተግባር በገፍ የሚፈሰው ገንዘብ በማያዳግም መልኩ ቱቦው ይዘጋል።

የገንዘብ ቅያሬው በድል በመጠናቀቁ ምክንያት የሕገ ወጥ ቡድኑ የተደገፈበት ዋነኛና ሦስተኛው እግሩ ሙሉ ለሙሉ ሊቆረጥ ችሏል። ከእንግዲህም፣ ሕወሓት ሕገ ወጥ ተግባራትን ለመፈጸም ተንጠልጥሎበት የሚገኘው የፋይናንስ ምንጩ በመቆረጡ ምክንያት አየር ላይ ተንሳፏል። መጨረሻውም ይፈጥናል።

ምክንያቱም የጦርነት ነጋሪት የሚጎስምበትን ሠራዊት፣ አሠለጠንኩ የሚለውን ሚሊሻ የሚቀልብበት ገንዘብ፣ የሚከፍለው ደሞዝ ስለማይኖረው ምንም ዓይነት ውጊያ ሳያደርግ አየር ላይ ተንሳፈፎ የሚገኘው ወንበሩ ሙሉ ለሙሉ መሬት ይነካል። የፋይናንስ ጉዳይ በዓይነቱ እጅግ ውስብስብ ከመሆኑ አንጻር ከብዙ ትዕግሥትና ከብዙ መጠበብ በኋላ የመጣ፣ አንድም ጥይት ሳይተኮስ የተፈጸመ፣ ኢትዮጵያን ሲገዘግዝ የነበረው ኃይል የቆመበትን ምሦሶ በመቁረጥ ሕልውናውን ከላይ ወደታች የፈጠፈጠ ትልቅ ሥራ ነው።

## አራተኛው እግር - ሌሎች ማኅበራዊ መሠረቶች

“ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል” የሚለው የፕሮፓጋንዳ ጀማሪዎች ብሂል፣ በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በብዙዎች ዘንድ ዋነኛ የፖለቲካ ተጽዕኖ መፍጠሪያ መርሕ በመሆን እያገለገለ ነው። ፖለቲካዊ የበላይነት ለመፍጠር “የፖለቲካ ተቋማትን ብቻ መያዝ በቂ አይደለም በሚል _ ሌሎች ማኅበራዊ ተቋማትም የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ እንዲሆኑ ፖለቲከኞች ሲፈልጉ ይስተዋላሉ። በዚህ ሥር የሚሠፍሩት እንደ ድጋፍ ሆነው የሚያገለግሉ ነገር ግን በአንድ ላይ ሲሰባሰቡ ትልቅ ዐቅም የሚፈጥሩ ልዩ ልዩ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ መሣሪያዎች ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ሚዲያ ነው። ሕወሓት ከሚዲያና ከሌሎች የፖለቲካ ተቋማት ባልተናነሰ ሃይማኖታዊ ተቋማትንም እንደ አንድ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያነት ሲጠቀምባቸው ቆይቷል።

### ሀ. ሚዲያ

እንደሚታወቀው በሀገራችን ሚዲያዎች በከፍተኛ ሁኔታ የመንግሥት የፕሮፓጋንዳ መሣሪያዎች ከመሆን በዘለለ ለሕዝቦች ድምጽ ለመሆን የደፈሩበት ጊዜ እምብዛም ነው። በቁጥጥር ደረጃም ካየነው ከፍተኛ ቁጥር ያላው ሚዲያዎች በመንግሥት እጅ ያሉ ናቸው። ይበልጥ አስከፊ የሚያደርገውም ሚዲያዎቻችን ከመንግሥት ባለፈ ለጥቂት ቡድኖች ፍላጎት መሣሪያ ሆነው መቆየታቸው ነው።

ከሀገር አቀፍ ሚዲያዎች ባለፈ የክልል ሚዲያዎችም ትእዛዝ ተቀባዮች ሆነው የየክልላቸውን ፍላጎት ከማራመድ ይልቅ ራሳቸውን ከሕወሓት ፍላጎት ጋር ለማስማማት ሲጣጣሩ ነበሩ። እነዚህ ተቋማት የተለየ ሐሳብ የነበራቸውን ሰዎች ገለልበማድረግ ልዩ ልዩ ርምጃዎች ሲወሰዱባቸው እንደነበር ይታወሳል።

በአንጻራዊነት የሌሎች ድምፅ የሚሰማባቸው የግልና የማኅበር ሚዲያዎችም ሲታፈኑ ነበር። በብዙ ተደራሽ የማይሆኑ ጋዜጦችና መጽሔቶችን ጭምር በመዝጋት ድምጾች ሲታፈኑ ኖረዋል። ከዋናው ሚዲያ በተጨማሪ በሳይበር ዘርፍም ማኅበራዊ ሚዲያዎችና ዌብሳይቶች እየተዘጉ ሕዝቡ ከሕወሓት አጀንዳ ውጭ ሌላ ድምፅ እንዳይሰማ ሲደረግ ነበር። የሚዲያው እንዲህ ታፍኖ መቆየት እነዚያ ከላይ የሠፈሩት ሦስት እግሮች ጠንክረው እንዲቆሙ እና የሚፈትናቸው ጠንካራ ኃይል እንዳይመጣ ለመከላከል የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ በመሆን እንዲያገለግል ረድቷል።

በሚዲያው ላይ የተደረጉት የአመራር ቅያሬዎችና አጠቃላይ የሚዲያ ሪፎርሙ ቀላል የማይባሉ ለውጦችን አስገኝቷል። ዜጎች የሚናገሩት ነገር ተጠቅሶ ወደ ቅጣት የሚመጡበት ሂደት በመቅረቱ የመናገር ነጻነት በእጅጉ ጨምሯል። የብዙ አካላት ድምፅ ስለሚሰማ የሐሳብ ብዝኃነትን የሚያስተናግድ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዐውድ ሊፈጠር ችሏል።

### ለ. ሃይማኖት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእምነቱ ቀናዒ እንደሆነ ይታወቃል። እስልምናም ይሁን ክርስትና ምእመኑ ለእምነቱ እጅግ ቀናዒ ነው። እነዚህን ሁለት ሃይማኖቶች መቆጣጠር ሕዝቡን ለመቆጣጠር አመቺ እንደሆነ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ያ ሕገ ወጥ ቡድን ችግር እንዳይገጥመው፣ የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ነድፎ በሃይማኖት ተቋማቱ ላይ እጁን ሲያስገባ ነበር። በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳትና የፓትርያርክ ምርጫ ላይ እጃቸው በመንከር መጀመሪያ የራሳቸውን ሰዎች እንዲሾሙ አደረጉ፤ ከዚያም ሁለት ቦታ በመክፈል ለማዳከምና ለመቆጣጠር ሞክረዋል።

በተመሳሳይ መጅሊሱን ለእነርሱ ታማኝ በሆኑ ሰዎች ለመሙላት ባደረጉት ጥረት ሕዝበ ሙስሊሙ ለሁለት ተከፍሎ ቆይቷል። እነዚህን ሁለት ሃይማኖቶች መቆጣጠራቸው በቀጥታ ጥቅም ባያስገኝላቸውም ሥርዓቱ የቆመባቸውን ሦስቱን ዋና ዋና እግሮች በማጠንከር በኩል ከፍተኛ ሚና ሲጫወትላቸው እንደነበር ብዙዎች የሚገነዘቡት ነው። የሃይማኖት ተቋማቱ ለእውነትና ለድኻ እንዳይቆሙ፤ መንግሥት ያላቸው ሁሉ አሜን ብለው እንዲቀበሉ፤ በተቋማቱ በኩል ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውሮች እንዲከናወኑ፤ ወደ ውጭ ሀገር ሰላዮቻቸውንና የፓርቲ ካድሬዎቻቸውን በሃይማኖት ሽፋን ለመላክ እንዲችሉ፤ ሕዝቡን ለመከፋፈል ለተደረገው እኩይ ሥራ የሃይማኖት አባቶች እንቅፋት እንዳይሆኑ የሕወሓት ሰዎች እስከ ውስጥ ዘልቀው ሠርተዋል።

ኢትዮጵያ የቆመችበት የሞራልና የእምነት መዋቅሩ› በእጅጉ ላልቶ ነበር።

ሁለት ቦታ ተከፍለው የነበሩትን የሃይማኖት ተቋማትን ችግር በዕርቅ እንዲቋጭ ማድረጋችን፣ ለሪፎርሙ ቀጥተኛ ጥቅም ባያስገኝም፣ ሀገራዊ ስሜትንና ሕዝባዊ _ አንድነትን በመፍጠር በኩል ቀላል የማይባል ሚና ተጫውቷል። ኢትዮጵያ የቆመችበትንና በፓርቲው ከፋፋይነት ምክንያት ላልቶ የነበረው የሞራልና የእምነት መዋቅሩ› ላይ ጥገና መደረጉ ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር በእጅጉ እንደሚረዳ ምንም ጥርጥር የለውም። ሕዝቡም የሚፈልገው ይሄን ስለነበር ወዲያውኑ ከለውጥ እንቅስቃሴው ጎን በመሰለፍ አጋርነቱን ለማሳየት ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም።

ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ አራት እግሮች ያሉትን የሕወሓት ወንበር መሬት እንዲነካ የተከናወነው ተግባር ለሀገራችን ብዙ ችግሮችን የቀረፈ እና በአጭር ጊዜ ለማጠናቀቅ ቀርቶ ለማሰብ የሚያዳግት ተግባር ነበር። የራሱ የሆነ የሕግ ማስከበር፣ የራሱ የሆነ ቢሮክራሲ፣ የራሱ የሆነ ግዙፍ ኢኮኖሚ ያለውን አካል በአጭር ጊዜ ውስጥ መጣል ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ መገመት አይከብድም።

ለሃያ ሰባት ዓመታት በስፋት ሲከናወን የነበረውን ውስብስብ አሻጥር ዋናውን ሰንኮፍ ውስጥ ማጠናቀቅ ከባድ ትግል ነው። ትግሉን የበለጠ ያከበደውም እኛ የተጠቀምነው ለመንቀል ዋና ዋና የሆኑትን አራት እግሮች

በመቁረጥ በሁለት ዓመት ተኩል ጊዜ በጦር መሣሪያ ላይ የተንጠለጠለ አካሄድ ባለመሆኑ ጭምር ነው። እንደዚህ ዓይነቱን በሌላ አውዳሚ መንገድ ሊያሳኩት ይችሉ ይሆናል እንጂ እኛ ባሳካነው መንገድ በጥበብ ሊያጠናቅቁት አይችሉም። ሰላማዊ ስትራቴጂዎችን የተከተለ በመሆኑ ለብዙዎች ትምህርት ሊሆን የሚችል ሪፎርም ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ለወደፊት የትግል ስትራቴጂም መነሻ በመሆን ሊያገለግል ይችላል።

# የሕወሓት ሚሳኤሎች

ሪፎርሙ በታቀደለት መንገድ ሲጓዝ ሕወሓት ጉዞውን ለማደናቀፍ ስድስት ሚሳኢሎችን ተኩሷል። ሕወሓት አንድ ሚሳኤል ባስወነጨፈብን ቁጥር የመልስ ምት ላለመተኮስ በተቻለን መጠን ስንጣጣር ቆይተናል። በውድመትና በመገዳደል ላይ ያነጣጠረ የለውጥ ጉዞ ዘላለም ሀገራችንን ከዜሮ እንድትጀምር ሲገፋት ኖሯል። የእኛም ዋነኛ ፍላጎት የነበረው እንደ ሀገር ለዘመናት የመጣንበትን የመጠፋፋት ልማድ በመቀየር አዲስ ባህል ለማኖር ካለን ጽኑ እምነት የመነጨ ነው። በዚያ ላይ ሕወሓት ራሱ የሚተኩሳቸው ሚሳኤሎች የራሱን ግብአተ መሬት እንደሚያፈጥኑት ርግጠኞች ነበርን።

የዚህ ሁለት ዓመት የሕወሓት ጉዞ የዚያን እልኸኛ እባብ አካሄድ ይመስላል። ከዕለታት አንድ ቀን አንድ የእንጨት ሠራተኛ የእንጨት ቤቱን ዘጋግቶ ከወጣ በኋላ አንድ መርዘኛ እባብ ወደዚያ እንጨት ቤት ሾልኮ ይገባል። የእባቡ አካሄድ አንዳች የሚበላ ነገር አገኝ እንደሆን በሚል ነበር። ታዲያ በረሐብ ውስጥ ሆኖ ዘወርወር እያለ ምግብ ሲፈልግ በድንገት አንድ መጋዝ ላይ ይወጣል። መጋዙም ገላውን ጫር ያደርገዋል። ጭረቱ ገላውን እንዳደማው ሲመለከት በንዴት አፉን ከፍቶ መጋዙን ነከሰው። ሌላ ጉዳት። አፉ መድማት ሲጀምር እባቡ የበለጠ እየበሸቀ መጋዙ ላይ ተጠምጥሞ ብረቱን መንከሱን ቀጠለ። ዳሩ ግን ሊያሸንፈው አልቻለም። "እልኽ ምላጭ ያስውጣል" እንዲሉ ያ መርዘኛ እባብ በእልኽ መጋዙን ለመዋጥ ያደረገው ትግል በመጨረሻ ሕይወቱን አሳጣው።

የመጀመሪያው ሚሳኤል - የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ መልቀቂያ ካስገባ በኋላ ምርጫ ተካሂዶ የአመራር መተካካት እንዳይደረግ ነገሮችን ለማጓተት ያደረገው ጥረት ነው። በወቅቱ ተደጋጋሚ የአስቸኳይ ጊዜ ዐዋጆች እንዲታወጁ በማድረግ ያለ ምንም ምርጫ ዐርባ ቀናት ገደማ እንዲቆጠር አድርጓል። በዚህ ጊዜ ውስጥ በኢሕአዴግ የእኅት ድርጅቶች እየተዘዋወረ አንዳንዴ መለማመጥ በሚመስል መልኩ ‹ድርጅታችንን እናድን... ስልጣንና ጥቅማጥቅም እንሰጣለን› በሚሉ መሸንገያዎች ከፓርቲ አባላት ጋር ሲደራደር፤ በሌላ በኩል ደግሞ በጦር መሣሪያ፣ በደኅንነትና በጸጥታ ማስከበሪያ መዋቅሩ ታግዞ ልዩ ልዩ ማስፈራሪያዎችን ሲያደርግ ነበር።

እናስራለን፣ እንገድላለን፣ ቤተሰብ ላይ ርምጃ እንወስዳለን› ዓይነት ማስፈራሪያዎች በኢሕአዴግ ቤት በስፋት ሲከናወኑ ቆይተዋል። በተለይ አዲስ የለውጥ አመራር ብቅ እንዳይል የተለያዩ የማሸማቀቅና የማጥላላት ተግባራትን አጠናክሮ ቀጥሎ ነበር። ሊመረጡ ይችላሉ የሚባሉ አመራሮችን ከሕዝብ ለመነጠል "መረጃዎች አሉን፤ መጥፎ ወንጀሎችን ሲፈጽሙ የሚያሳይ መረጃ አለን" እያሉ ያልተፈጠረውን ተፈጥሯል፣ ያልተሠራውን

ተሠርቷል ለማስባል ከፍተኛ ጥረት ተደርጎ ነበር። ሆኖም ግን ጥረታቸው ሳይሳካ ቀርቷል።

ሁለተኛው ሚሳኤል - ወደ ሪፎርም ከገባን በኋላ ሕወሓት የሚያምናቸው አመራሮች እንዳይለወጡ ለማድረግ የተወረወረ ሚሳኤል ነው። በተለይም በሕግ ማስከበር ተቋማት ላይ ያሉ አመራሮች ፈጽሞ እንዳይነኩ ለማድረግ በፓርቲ አሠራርና በሌሎች መንገዶች ሙከራዎች ተደርገዋል። ሙከራው ልዩ ልዩ ረብሻዎችን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል እስከማድረግ የዘለቀ ነበር። አዳዲስ ግጭቶችን ከመፍጠር ባለፈ በሒደት እንዲፈነዱ የተጠመዱ የጊዜ-ቦንቦችን በመቆስቆስ በመላ ሀገሪቱ አውዳሚ የሆኑ ብጥብጦችን ለማስነሣት በሠፊው ተሠርቷል። በምሥራቅ- ሶማሌ ክልል፣ ሐረርና ድሬዳዋ፤ በምዕራብ - በቤንሻንጉል እና ጋምቤላ ክልሎች፤ በደቡብ በኦሮሚያና በደቡብ ልዩ ልዩ ከተሞች፤ በሰሜን በአማራ ክልል ልዩ ልዩ ከተሞችና ዞኖች በትግራይና በአማራ የአስተዳደር ወሰኖች አካባቢ፤ እንዲሁም በአዲስ አበባ በድብቅና በይፋ ምን ምን ሲከናወን እንደነበረ ከሕዝብ ዐይን የተሰወረ አይደለም።

ሦስተኛው ሚሳኤል - ዋነኛው ሚሳኤል ሊባል የሚችል ነው። ይህም የፓርቲ ሪፎርም እንዳይደረግ የተተኮሰ ሲሆን አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንዳይቀየር፣ ከውስጥም ከውጭም ከፍተኛ ጫና ሲደረግብን ነበር። ፓርቲውን ለሁለት ለመሰንጠቅ አባላትን በጥቅማጥቅም እስከ ማባበልና አልፎ አልፎም ስብሰባዎችን ረግጦ እስከመውጣት የደረሰ የውስጥ ትግል በማድረግ በፓርቲ ሪፎርሙ ላይ ጫና ተፈጥሯል።

“ሕወሓት ከወጣ ኢሕአዴግ ይፈርሳል፣ ኢሕአዴግ ከፈረሰ ደግሞ ሀገር ይፈርሳል፣ ሕጋዊ መንግሥት አይኖርም” በሚል ልዩ ልዩ ጫናዎች ሲደረጉ ነበር። በዩንቨርስቲዎች፣ በሃይማኖት ተቋማት፣ የእርስ በእርስ ግጭት በቀላሉ ለመቆስቆስ በሚያስችሉ ቦታዎች ላይ ግጭቶችን፣ ቃጠሎዎችን፣ ግድያዎችንና በገንዘብ የተደገፉ አሰናካይ ሥራዎች ሲከናወኑብን ነበር። ነገር ግን እሱም በሰላማዊ ትግል ከሽፏል።

አራተኛው ሚሳኤል - ሕወሓት ከኢሕአዴግ እንደወጣ ሲያውቅ የፌደራሊስት ኃይሎች ያለውን ስብስብ በማደራጀት፣ ሌላ መንግሥት የሚመስል ድርጅት በማቋቋም፣ ጫና ለመፍጠር የተደረገ ሙከራ ነበር። ከፍተኛ ገንዘብ በመከስከስ ፓርቲዎቹን መቀሌ ሰብስቦ ያቋቋመው ያ ጥምረት፣ በጊዜው መክኖ ራሱ ሕወሓት ካቋቋመው ስብስብ ተባርሮ፣ ሊፈጥር ያሰበው ችግር በራሱ ጊዜ ከሽፏል።

አምስተኛው ሚሳኤል ምርጫ ነው። እኛ ምርጫውን የጨረቃ ምርጫ ብለነዋል።

እንደሚታወቀው የጨረቃ ቤቶች ሲሠሩ በጨለማ በድብቅ ነው። ምናልባት ፖሊስና የቀበሌ ሰዎች አይተው እንዳላዩ ሊያልፏቸው ይችላል። ነገር ግን የጨረቃ ቤት የጨረቃ ቤት ነው፤ አይዘልቅም። ሕጋዊነት የለውም። ሕጋዊነት ብቻ ሳይሆን በጨለማ ቶሎ ስለሚሠራ ጥራትና ጥንካሬም የለውም። የሆነ ጊዜ መፍረሱ አይቀርም። የጨረቃ ምርጫም እንደዚያው ነው፤ ለጊዜው ቢመስልም ገና ከመደረጉ በፊት የከሸፈ ሚሳኤል ነው።

ስድስተኛው ሚሳኤል - የመገንጠል ጥያቄን ማቀንቀን ነው። እጃቸው ላይ የቀረው ይሄ አማራጭ ክልሉን ለመገንጠል በሚል የሚከናወኑ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን ጎን ለጎን ይይዛል። አጀንዳውን ለማስፈጸም የጦር ሠራዊት የሚመስል ኃይል የማደራጀት እንቅስቃሴ ይደረግበታል። ከዚያም አጀንዳውን ከልክ በላይ በማቀንቀን

የፌደራል መንግሥትን ጠልፎ ወደ ውጊያ ሜዳው ለማስገባት እየተሞከረ ነው።

በርግጥ ይሄኛው ሚሳኤል በጥንቃቄ ካልተያዘ ከፍተኛ ችግሮችን ሊፈጥር ይችላል። ስለዚህ ጥሩ ስትራቴጂ በመንደፍ ሚሳኤሉ እንዲከሽፍ ማድረግ ይገባል። ጥበብ በተሞላበት አካሄድ ይሄኛው አጀንዳ ከከሸፈ ሕወሓት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በአሻጥር የሚያደርገው ጉዞ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መበጠሱ አያጠራጥርም።

# ‹ሪፎርሙ ተቀልብሷል›

# የእንቁራሪት ድምፆች…

መቸም የትኛውም ዓይነት ለውጥ ምንም ያህል ጥሩ ቢሆን ከትችት ላያመልጥ ይችላል። ወቀሳና ጣት ከመጠቆም ፍጹም ነጻ የሆነ ምድራዊ ሥራ ይኖራል ማለት ዘበት ነው። ምናልባትም ትችት የማይነካው ሥራ እስከናካቴው ያልተጀመረ ሥራ ብቻ ነው።ከዚያ ውጭ የሰው እጅ ተግባር ሁሉ ትችትና የማጥላላት ድምፆች ቢሰነዘሩበት እምብዛም ምናልባትም አያስገርምም። ባለፉት ሁለት ተኩል ዓመታት የመጣንበት የሪፎርም መንገድም ከትችት ድምፆች የጸዳ አልነበረም።

ወርኃ መጋቢት 2010 ዓ.ም ላይ ለውጡ እንዲመጣ ያነሣሱ ምክንያቶች በዋናነት ከሕዝብ ሲነሡ የነበሩ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ናቸው። ሀገራችን በዚህ ዘመን ሊኖሯት ይገባሉ የሚባሉ አንኳር አንኳር የሕዝብ ፍላጎቶች እንደነበሩ ይታወሳል። እነዚያ ጉልህ ጥያቄዎችና የሕዝብ ፍላጎቶች የለውጥ ቡድኑ አባላትን የሚያስተሣሥሩ መቀነቶች ሆነው በማገልገል የጋራ አቋም እንድንይዝ በር ከፍተዋል። ጥያቄዎቹን ለመመለስም የመጀመሪያው ተግባር በመንግሥት ሥልጣን ላይ ያለቅጥ ተንሠራፍቶ የሚገኘውን ኃይል ገለል ማድረግ የቅድሚያ ቅድሚያ ተሰጥቶት እንደነበር አይዘነጋም።

በዚህም መሠረት ለውጡ፣ በሕዝቡ ግፊትና በለውጥ ቡድኑ ሳቢነት እውን ሊሆን በቅቷል። ለውጡ እውን ከሆነና የአመራር ሽግሽግ ከተደረገ በኋላ ነበር ዝርዝር ስትራቴጂዎችን ወደ መንደፍ የገባነው። ሪፎርሙ ምን ምን ጉዳዮችን እንደሚያከናውን፣ ምን ምን ጉዳዮችን ቅድሚያ ሰጥቶ እንደሚሠራ እና የትኞቹ ጉዳዮች ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃ ይያዙ› በሚለው ዙሪያ ዝርዝር ዕቅድ የተያዘው በለውጡ ጥንስስ ወቅት ሳይሆን ጽንሱ ከተወለደ በኋላ ነበር። ያም ሆኖ ቀደም ሲል የተጀማመሩ ዕቅዶች እስከናካቴው አልነበሩም ማለት አይደለም። የመጀመሪያው የፓርላማ ንግግር ላይ የሰፈሩት ቃል ኪዳኖች ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ከለውጥ ቡድኑ አባላት ጋር በተለያዩ ጊዜያት በግልና በቡድን ሆነን ስንነጋገርባቸው ከነበሩ ሐሳቦች የመነጩ ናቸው ማለት ይቻላል።

ከዚያ ውጭ የሕወሓትን ሥርዓት ለማሻሻል፣ ለመቀየር፣ ለመለወጥ በነበረው ትግል ውስጥ መደበኛ ስብሰባዎችን አድርገን ያረቀቅነው ዕቅድና የነደፍነው ስትራቴጂ የለም። ሁላችንም በየግላችን ከያዝናቸው ዕቅዶች ባለፈ ከመካከላችን በጽሑፍ አዘጋጅቶ ‹ቀጣይ ሪፎርሙ ይሄና ያ ነው፤ እንዲህና እንዲያ መምሰል አለበት፤ በዚህና በዚያ ጊዜ ይከናወናል› ብሎ አቅርቦ የተወያየንበትና የጸደቀ ነገር መኖሩን አላስታውስም።

ትግሉን በአሸናፊነት እንወጣ ይሆን? በሚለው ዙሪያ እንኳ በመካከላችን እኩል እምነት አልነበረም። ከለውጥ በኋላ ጥገናዊ የሆነ ነገር እንጂ እንደዚህ ዓይነት መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ይመጣል የሚል እምነት የነበራቸው እጅግ ጥቂቶች ነበሩ።

እየቆየን ስንመጣ በዚህ ዙሪያ አንዳንድ ድምፆች ከውጭ ብቻ ሳይሆን ከውስጣችንም መሰማት ጀምረዋል። ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ላይም ግርታ ሲፈጥር ይስተዋላል። “ለውጡ ተቀለበሰ” የሚለው ድምፅ ሲደጋገም በጉዟችን ወቅት አብሮን ያልነበረ ሰው የእውነትም ነገሮች ተቀልብሰው ይሆን?› ብሎ ቢያስብ የሚደንቅ አይሆንም። በየሰው ጭንቅላት ውስጥ ለውጡ ተቀለበሰ ሲባል ከዚያ ቀደም ስምምነት የነበረ፣ ማኅበራዊ ኮንትራት ያለ ይመስላል።

የለውጡ አካል የነበሩ ጥቂቶች ቅጅውን ይዘው ግማሹ ተሠርቷል፤ ግማሹ ደግሞ አልተሠራም እያሉ ግምገማ ውስጥ የገቡ የሚያስመስል እንቅስቃሴ በስፋት ይስተዋላል። ምናልባት የእይታ አቅጣጫን ማስተካከል ቢቻል ነገሮች እነርሱ እንደሚያስቡት ላይሆን ይችላል። ሪፎርሙ ተቀልብሷል የሚል ድምፅ የሚያሰሙ ሰዎች፣ ቀረብ ብለው ሪፎርሙ የሚጓዝበትን ፈለግ ልብ ብለው ቢመለከቱ መሳሳታቸውን ይረዱ ይሆናል። በዚህ ሰዓት ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የሚሠራ ሰው እንጂ ከሩቅ ሆኖ ይሄ ተሠርቷል፤ ይሄኛው አልተሠራም› እያለ ደረጃ የሚመድብ ሰው አይደለም። ሀገሪቱ ዛሬ ተጨዋች እንጂ ተመልካች አትፈልግም።

ሁለት ወጣት ጥንዶች ዘወትር ማዕዳቸውን የሚቋደሱት በመስኮት አሻግረው ውጭውን እየተመለከቱ ነበር። አንድ ዕለት ሚስት ከወዲያኛው ኮንዶሚንየም ልብስ የምታሰጣ ሴት ስታይ ቆይታ፣ “አየኻት ውዴ፣ ያቺ ሴት ልብሱ ሳይጸዳ ስታሰጣው? ሰነፍ ሠራተኛ መሆን አለባት” ትለዋለች። ባል ቀና ብሎ ተመልክቷት መልስ ሳይሰጥ ተመልሶ ወደ ምግቡ አቀረቀረ። ዝምታው ከክፋት አልነበረም። ሚስቱን አንድ ቁም ነገር ሊያስተምራት ፈልጓል።

ሌላ ጊዜም ቁርሳቸውን እየበሉ ሳለ ያቺው ሴት ልብስ አጥባ ልታሰጣ ወጣች። ሚስትም አሻግራ እያየቻት “ይቺ ሴትዮ ልብስ እንዴት እንደሚታጠብ ፈጽሞ የምታውቅ አይመስለኝም” አለች በብስጭት።

በዚህ መልኩ ሚስት ዘወትር ጎረቤቷ ልብስ አጥባ ስታሰጣ ስታያት አስተያየት ከመስጠት አልቦዘነችም። ሳምንት ያህል ከቆዩም በኋላ ዘወትር ቁርስ ከሚበሉበት ጠረጴዛ ላይ እያሉ ልብስ የምታሰጣዋ ሠራተኛ ብቅ አለች። ሚስትም ከርቀት አየቻት.. ሴትዮዋ በእጇ ንጹሕ የታጠበ ልብስ ይዛለች። ንጹሑን ልብስ መያዟን ስትመለከት ሚስት እጅግ ተደንቃ ለባሏ እንዲህ አለችው፣

“ተመልከት ውዴ፣ ያቺ ሴት ዛሬ ሞልቶላታል፤ ልብስ እንዴት በትክክሉ እንደሚታጠብ ተምራለች፤ መቼም ቀጣሪዎቿ በብስጭት ተቆጥተዋት መሆን አለበት።”

ባል አሁን ተናገረ። ሚስቱ ሌሎች ሰዎችን ከመኮነኗ በፊት ነገሮችን በትክክል እንድታጤን ነገራት። ጠቋሚ ከመሆን በፊት ተመልካች፤ ተናጋሪ ከመሆን በፊት አሰላሳይ፤ ከመደምደም በፊት ደጋግማ ፈታሽ እንድትሆን መከራት፡ አሻግረው ወደ ሚመለከቱበት የመስተዋት መስኮት እጁን ይዞ እየቀረበም፣ “ይሄውልሽ ውዴ፣ ድሮም ቢሆን ሴትዬዋ የምታጥበው ልብስ ንጹሕ ነበር። መስኮቱን ዛሬ ጠዋት ነው በኦሞ የወለወልኩት! ለዚያ ነው፥

ድሮ በቆሻሻው መስተዋት አሻግረሽ እያየሻት ቆሻሻ ልብስ የምታሰጣ የመሰለሽ። እውነታው ግን እንደዚያ አልነበረም" አላት።

ሚስት ያንን ዕለት በፍጹም አትረሳውም። ለሕይወቷ እጅግ የሚጠቅማትን ምክር ያገኘችበት ድንቅ ዕለት ነበር። ከዚያን ዕለት ወዲህ አንዳች ትችት ለመሰንዘር ከመነሳቷ በፊት ስለነገሩ በጥልቀት ለመመርመር መጣጣሩን ልማድ አደረገችው።

በተለይም በፖለቲካችን፣ ነገሮችን በቅጡ ሳይመረምሩ የመተቸት መጥፎ ልማድ አለ። የራስን መነጽር ከማስተካከል ይልቅ ሙሉ ለሙሉ ችግሮችን ሌሎች ላይ መደፍደፍ ዋነኛ የፖለቲካችን መለያ ጠባይ ሆኗል። የለውጥ ጉዞ ስንጀምር ከውጭ ብዙ ትችቶች ሊገጥሙን እንደሚችሉ አስበን ትከሻችንን አስፍተን ተዘጋጅተን ነበር። ከለውጥ ቡድኑ መካከል አንዳንዶች ለውጡ ተቀልብሷል የሚል ትችት ሲያሰሙ መስማት ግን ግራ የሚያጋባ ነገር ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ በትግላችን ወቅት ከድል በፊት፣ ያንን ሕገ ወጥ ኃይል ለመቀየር መታገል እንጂ ከተቀየረ በኋላ ‹ምን ይሆናል› በሚለው ጉዳይ ዙሪያ ዝርዝር ዝግጅት አልነበረም። ትግሉን በአሸናፊነት ማጠናቀቁ በራሱ ከጥቂቶች በቀር ብዙዎችን አሳምኖ ያልነበረ ጉዳይ ነበር።

ከዚያ ውጭ ከላይ እንደተገለጸው በጽሑፍ ደረጃ የዚህ ለውጥ የመጀመሪያው ፍኖተ ካርታ ወይም ማኅበራዊ ኮንትራት ሊባል የሚችለው በበዓለ ሢመቱ ዕለት የቀረበው የፓርላማ ንግግር ነበር።

መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. የቀረበውን የፓርላማ ንግግር፣ እንደ መጀመሪያ ዕቅድ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። በንግግሩ ብዙ ጉዳዮች ተነሥተዋል። ከፍትሕ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከሚዲያ፣ ከተቃውሞ ፖለቲካ፣ ከጎረቤት ሀገራትና ከኤርትራ አንጻር፣ እንዲሁም ሌሎችም ነጥቦች ነበሩበት። እስካሁንም በዚያ ንግግር የሰፈሩት እነዚያ ጉዳዮች ከመስፋትና ከመጥበብ ውጭ በዝርዝር ሲተገበሩ ቆይተዋል። ከዚያ ንግግር ባፈነገጠ መልኩ የተደረገ ነገር የለም። ዋነኛ መሠረቱን እነዚያ ነጥቦች በማድረግ ልዩ ልዩ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል።

ሪፎርሙ የመጣበትን መንገድ፣ የለውጡን ፈለግ አይተን የምንገመግምና ተቀልብሷል› የምንል ከሆነ፣ ከዚያ የፓርላማ ንግግር ተነሥተን መሆን አለበት። የትኞቹ ተግባራት ናቸው ቃል ከገባነው ባፈነገጠ መልኩ የተፈጸሙት የትኞቹ ደግሞ በቃላችን ልክ ተፈጸሙ? በሚል የሚቀርቡ ትችቶች ውኃ ያነሣሉ። ከዚያ ውጭ ሌላው ከንቱ የምድረ በዳ ጩኸት ነው።

# ምዕራፍ አምስት

## መጋቢት እና መጋቢታውያን

“ፍጻሜ አግኝቶ እስኪታይ

ሁሌም የማይቻል ይመስላል!”

- ኔልሰን ማንዴላ

### ሰኞ፣ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም.

መጋቢት ደግሞ በተቃራኒው ቀዝቃዛ ወር ነው። ምናልባት በተደጋጋሚ ከአብዮት - ቀደም ብለን የካቲት በኢትዮጵያ የለውጥ ታሪክ ውስጥ የጋለ ወር ነው ብለናል። ስሙ ከሚነሣው ከየካቲት ቀጥሎ ስለሚመጣ ይሆናል። መስከረም ከንጉሥ ኃይል ሥላሴ መውረድ ጋር፤ ታኅሣሥ ከ1953ቱ የታኅሣሥ ግርግር ጋር፤ የካቲት 1966ቱ አብዮት፤ከሕውሓት ምስረታ ጋር፤ግንቦትም እደዚያው በ1981 ግንቦት 8ቀን ከተደረገው የጄኔራሎቹ መፈንቅለ መንግሥትና በግንቦት 13 ከተፈጸመው የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ሀገር ጥሎ መውጣት፣ በኋላም ከኢሕአዴግ ወደ አዲስ አበባ መግባት ጋር የተያያዙ ናቸው።

መጋቢት ግን ከለውጥና ነውጥ ጋር እምብዛም ታሪክ የለውም። የመጋቢት 24ቱ ክሥተት ግን የመጋቢትን ወር

ከኢትዮጵያ የለውጥ ታሪክ ጋር አያይዞታል። እንደ ስሙ ለውጥን ሊመግብ ተሰናድቷል፤ ከተሳካለት ስሙን በተግባር የሚገልጥበት ዕድል አገኘ ማለት ነው። በረጅም ሰንሰለትና መጠላለፍ ተተብትቦና ተከርችሞ ዘመናትን ያስቆጠረው የኢትዮጵያ የፖለቲካ መዋቅር ግልጥልጥ ያለበት፣ ለብዙዎች ፍንትው ብሎ የተጋለጠበት ሁኔታ ተፈጠረ። ላለፉት ሦስትና አራት ዓመታት የተቀሰቀሱት ሕዝባዊ ዐመፆች ለዘመናት ሲቀጣጠል የኖረውና ያልተቋጨው የሕዝቦች ዐመፅ ቅጥያና አካል ነበሩ። ዐመፆቹ ለአንዳንዶቹ እንደሚመስላቸው፤ ኢሕአዴግ ወለድ ወይም በኢሕአዴግ አደረጃጀት ውስጥ የተሰገሰገው ጥቅመኛ ቡድን የወለዳቸው ችግሮች የፈጠሯቸው ይበልጥ አፋፍሟቸው ሊሆን ይችላል። አይደሉም። ምናልባት የኢሕአዴግ ስሕተቶችና የጥቅመኛው ቡድን ጠለፋ ጥያቄዎችን ከዘውዳዊ አገዛዝ ወደ ፓርቲ አገዛዝ፤ ከአንድ ፓርቲ አምባገነን አገዛዝ ወደ መድብለ ፓርቲ ግንባር አምባገነናዊ አገዛዝ በተደረጉ ሽግግሮች ውስጥ ድሎች ተገኝተዋል። ነገር ግን ድሎቹ እስኪሟሉና ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስኪገነባ ድረስ ግፊቶቹ መቀጠል ነበረባቸው። የኢሕአዴግ ያልተጠበቁ፤ መጠነ ሰፊና ፈጣን እንከኖች የሕዝቦችን የነጻነት ትግል አፋጠኑት። እነርሱን ብቻ በምንጭነት መውሰድ ግን አሁንም ከአምናው አመራር ትንሽ ሻል ያለ ለውጥ በማምጣት መርካትን ያስከትላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ለሌላ ሕዝባዊ ተቃውሞ በር ይከፍታል። ስለሆነም አሁን የመጣው ለውጥ እጅግ ሰፊና ጥልቀት ያለው ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መሻሻልን በማጣት ብቻ ሊረካ የሚችል መሠረታዊ ጥያቄ እንጂ የበቀል ወይም የእልህ ፖለቲካ የወለደው አይደለም።

እኔም የለውጥ ኃይሉን በግንባር ቀደምትነትና በመሪነት ስቀላቀል ከእኔ በፊት የነበሩት አመራሮች የሠሯቸውን ስሕተቶች ለማረምና በትንሹ ሻል ብዬ ለመታየት አይደለም። ከልጅነቴ ጀምሮ በልቤ የተተከለውን የመደመርና የልቀት አስተሳሰብ ሀገሬንና ሕዝቤን ወደ ከፍታ ያሻግራል ብዬ በማመን ነው እንጂ። የለውጡ ራእይ ከፍ ብሎ የሀገራችን ኋላ ቀርነት ከማይደርስበት ሠገነት ላይ ማድረስ ነው። ራእዩ የትራንስፎርሜሽን ራእይ እንጂ የአምናን ስሕተት በማረም የሚረካ የበቀልና የመናቆር ራእይ አይደለም።

በየቦታው ተቀጣጥሎ የነደደው የሕዝቦች ዐመፅ፣ እንደ ቋያ እሳት እየተንቀለቀለ ሳይታሰብ አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ደጃፍ ደረሰ። አይደለም ሊነኩት፣ ሊቀርቡት የማይደፍሩት ‹አይደፈሬ፤ አይነኬው› አስፈሪ ቅጥር በራሱ ጉልበት ወድቆ ተደረመሰ። አርጅቶ የዛገው የብረት ደጃፍ ወለል ብሎ ተከፈተ። የሤራና የመጠላለፍ ማዕከል የነበረው የአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት የለወጡ ኃይል ማዕከል ለመሆን ራሱን ሰጠ።

ይሄንን ተከትሎ በየቦታው የተቀጣጠለው የቁጣ እሳት ጋብ ማለት ጀመረ። የፖለቲካ ቋንቋውን ተቆጣጥረውት የነበሩትና ሕዝቡ የሰለቻቸው ‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ›፣ ‹ጥልቅ ተሐድሶ›፣ ‹ኪራይ ሰብሳቢነት›፣ ‹ፀረ ሰላም ኃይሎች፣ ትምክተኞች፣ ጠባቦች፣ የቀድሞ ስርዓት ናፋቂዎች፤ሌሎችም ጨፍጋጋ ቃላት ከአየሩ ላይ ገለል አለ።በምትካቸው አቃፊና አካታች የሆኑት ይቅርታና ፍቅር፤ዕርቅና መደመር፤አንድነትና ኅብር ናኝተው ታዩ።

ከሕዝብ ጆሮ ያልራቁ፣ የሕዝብን የልብ ፍላጎት የሚፈለቅቁ፣ ሀገር ሀገር የሚሸቱና ከወቅቱ የፖለቲካ ነፋስ ጋር የሚጣጣሙ አስማሚና አቀራራቢ የሐሳብ ፈርጦች በገጠር በከተማው በፖለቲካዉ ጠፈር ላይ ገነኑ። ኢትዮጵያዊነትም ካኅነበሰበት ቀና ቀና ማለት ጀመረ። አየሩ በአንድ አፍታ ጠርቶና ተለውጦ በሰፊው

የሚተነፈስ ሆነ። የሰዉ ተስፋና የነጻነት ስሜትን ልብ ብሎ ለተመለከተ ዘመናትን ሲናፍቀው እንደኖረ ለመረዳት አፍታ አይፈጅበትም። ገና በመጀመሪያ ቀን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያደረግኩትን ንግግር ተከትሎ የብዙኃኑ ሕዝብ አመለካከት ተለውጧል። ተስፋው ንሮ ጣራ ነክቷል። ይሄ ሁሉ የሕዝብ ፈንጠዝያ በጫንቃዬ ላይ የሚጫነውን ሐላፊነት እንደሚያበዛው ምንም ጥርጥር የለውም። በመጀመሪያ ንግግር ሕዝብ በዚህ ደረጃ ከተደሰተ፣ ነገና ከነገ በስቲያ የተሻለ ሐሳብ፣ የተሻለ ተግባር፣ የተሻለ አመራር እንደሚጠብቅ እሙን ነው። በተቃራኒው ዝቅ ያለ መስሎ ከታየው እንዲያ የፈካው ፊቱ የሐምሌ ሰማይን እንደሚመስል ለመገመት ከባድ አልነበረም።

እንደ ሀገር መሪ ከሕዝብ ጋር የምተዋወቅበትን ንግግር በተቻለ መጠን በጥንቃቄ ተዘጋጅቼበታለሁ። ከሕዝብ ጋር ተፈላጊውን ዘላቂ ዝምድና እንዲያመጣልኝ፤ ልብ ለልብ እንዲያስተሳስረኝና ሰዋዊ ውጤት እንዲያመጣ በማሰብ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቼ መዘጋጀቴ በጅቶኛል። ንግግሩ ቁልፍ ከነበሩት የይቅርታና የምስጋና መልእክቶች ባሻገር በርካታ አዳዲስ ሐሳቦችንም በውስጡ አጭቆ ይዟል።

አንዲቱ የኢትዮጵያዊነት መለያ ሰንደቅ ዓላማም ቀና ብላና ከሁሉ ከፍ ብላ እንድትታይ በመልእክቴ ጉልህ ስፍራ ተሰጥቷት ነበር። የተጣላ እንዲታረቅ፣ ከሀገር የወጣ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ፣ ጥላቻ በፍቅር እንዲተካና አዲስ የመደመር ፖለቲካ እንዲጀመር ለሁሉም ጥሪ ማቅረብ የቻልኩበት ንግግር ነው። ያም ሆኖ ምክንያቱን በቅጡ ባልተረዳሁት ሁኔታ ንግግሬን ከጠበኩት በላይ ሕዝቡ ተቀብሎታል። ነገሩ አልፎ አልፎ ትዝ ባለኝ ቁጥር ምን ይሆን ምክንያቱ? እያልኩ አስባለሁ። ምናልባት ለተፈጸሙት ጥፋቶች፣ በዜጎች ላይ ለደረሰው ግፍና የከፋ መከራ በይፋ እንደ መሪ ድርጅቴንና መንግሥትን ወክዬ ይቅርታ መጠየቄ ይሆን?

"በተለያየ ጊዜ፣ መሥዋዕትነት ለከፈሉ የመብት ተከራካሪዎችና ፖለቲከኞች፤ በቅጡ ሳይቦርቁ ሕይወታቸው ለተቀጠፈ ለውጥ ፈላጊ ወጣቶች፤ ለሥነ ልቡናዊና አካላዊ ቀውስ ለተዳረጉ ቤተሰቦችና ግለሰቦች ከልብ የመነጨ ይቅርታ እጠይቃለሁ" በሚል የቀረበው ተማጽኖ አዘል ይቅርታ፤ የሁሉንም ቤት አንኳኩቶ፣ የእያንዳንዱን ዜጋ ጆሮ ያገኘና ልባቸውን እንዲከፍቱ የማስገደድ ዐቅም ኖሮት ይሁን፣ ወይም ዕድል ከእኔ ጎን ቆማ ስለነበር ለመገመት ይከብደኛል።

እርግጥ ነው፤ የእኛ ሕዝብ በመሪዎቹ ይቅርታ መጠየቅን አልለመደም። መሪዎቻችንን የፈጠረው የማኅበረሰባችን ሥሪትም ግንባርን ለጥይት ከመስጠት በላይ ይቅርታን እንድንፈራው አድርጎን ቆይቷል። ታዲያ በዚህ መልኩ ሕዝባችን ሲሸሸው የኖረውን ይቅርታ መጠየቅ ፊት ለፊት መጋፈጥ ችዬ በአደባባይና ሚሊዮኖች በቀጥታ በሚመለከቱት የሹመት ሥነ ሥርዓት ላይ ይቅርታ የማለት ድፍረት በማግኘቴ ይሆን? ለነገሩ የእኛ ሰው ደፋር ይወዳል። ደፋርና ጀግና ለመውደድ ብቻ ሳይሆን ለማምለክም የሚዳዳው ባህል ስላለን ከድፍረት አቅጣጫ ከተመለከተው እውነትም ትልቅ ድፍረት ነበር። በሌላም መልኩ ካየነው መሪዎች የቱንም ያህል ሲበድሉት ቢኖሩ "አጥፍቻለሁ ይቅርታ!" ብለው ሲጠይቁት አይቶ ስለማያውቅ ነገሩ እንግዳ ሆኖበትም ይሆናል።

ምናልባትም በዕለቱ ያቀረብኩት ንግግር ቀጥተኛና የተፍረጠረጠ በመሆኑ፣ ያለምን መከላከያና መደበቂያ ራቁቱን በቆመ እውነት ላይ የሚጨክን ኅሊና ባለመኖሩ፤ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ንግግሩ ሕዝቡ ተስፋ እንዲሰንቅ ማድረግ የሚችል መሆኑም  አስተዋጽዖው ቀላል አይሆንም። መለስ ብሎ ላስተዋለው በጊዜው ተስፋ በሀገራችን እየሞተ ነበረ ማለት ይቻላል፡፡ እንደ ሕዝብ ለእኛም ቀን የሚወጣልን መቼ ይሆን እየተባባልን ዘመናትን አሳልፈናል። ለዘመናት ደግመን ደጋግመን አንድ ቦታ ስንረግጥ ኖረናል፡፡ችግሮቻችን የሚቀረፉበትን፣ ፖለቲካችን የሚስተካከልበትን ቀን በተስፋ ሰንጠባበቅ ቆይተናል፡፡ተስፋችን ከቀቢፀ ተስፋ ጋር እኩል የተገዳደረበት ወቅት አንደ ብቻ አይደለም፤ብዙ ነው። ብዙ ተስፋ አስቆራጭ ነገሮች በበዙበት ዘመን መሪዎች ምንም እንዳልተፈጠረ ሲሰማቸው፣ በተቃራኒው ብዙ እንዳሳኩ እያጋነኑ ሲደሰኩሩ ለሰማ ሕዝብ፤ ችግሮችን የመለወጥ ትልም ሲመለከት ቢያስፈነድቀው አይገርምም። አንድነትና ኢትዮጵያዊነት ትቢያ በለበሰበት ወቅት፣ በጋራ ስለማደግ ሲነገር ሲሰማ መደሰትም ይገባዋል። በአብሮነት ስለመጠንከር፣ በኢትዮጵያዊነት ተስፋ ስለማድረግ መናገር በራሱ ተስፋ ይሰጣል።

አሁን ለደረስንበት የፖለቲካ ቀውስ ተጠያቂ የሆነውን አካል ያለ ወገንተኝነት ስለገለጥኩ፤ ችግር ፈጣሪው አንድ ወገን ብቻ እንዳልሆነ ሁሉ የመፍትሔው አካልም ከሁሉም ወገን መሆን እንደሚገባው ያለማመንታት ስለጠቆምኩ፤ የሐሳብ ልዩነት ያላቸው አካላት ሁሉ ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ፣ አንድ የሚያደርጋቸው አጀንዳ ኢትዮጵያዊነት እንደሆነና ለተለየው ሐሳባችን ሲባል ‹ኢትዮጵያዊነት ሒሳብ ማወራረጃ እንዳይሆን፣ አጽንዖት እንዲሰጠው ስላደረኩ ሊሆን ይችላል።

“በአንድ ሀገር ውስጥ የሐሳብ ልዩነቶች ይኖራሉ። የሐሳብ ልዩነት ከላይ የተሰጠን በረከት እንጂ ርግማን አይደለም። ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ መደማመጥና በመርሕ ላይ ተመሥርተን መግባባት ከቻልን፣ የሐሳብ ልዩነት በረከት ይዞልን ይመጣል።

በሐሳብ ፍጭት ውስጥ መፍትሔ ይገኛል። በመተባበር ውስጥ ኃይል አለ። ስንደመር እንጠነክራለን። አንድነት የማይፈታው ችግር አይኖርም፤ ሀገር ይገነባል። የኔ ሐሳብ ካላሸነፈ ሞቼ እገኛለሁ ማለት ግን እንኳን ሀገርን ሊያቆም ቤተሰብን ያፈርሳል። ያለችን አንዲት ኢትዮጵያ ነች። ከየትኛውም የፖለቲካ አመለካከት በላይ ሀገራዊ አንድነት ይበልጣል። አንድነት ማለት ግን አንድ ዓይነትነት ማለት እንዳልሆነ ሊሠመርበት ይገባል። አንድነታችን ልዩነቶቻችንን ያቀፈ ብዙኅነታችንን በኅብረ ብሔራዊነት ያደመቀ መሆን አለበት።

‹‹ምናልባትም በቅርብ ጊዜያት በከፍተኛ የመንግሥት ሐላፊነት ደረጃ ያለ ሰው ስለ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዚህ መንገድ ሲናገር ተደምጦ ስለማይታወቅ ሊሆን ይችላል።

“ማንነታችንን እንዳይለያይ ሆኖ የተሰናሰለ፣ እንዳይነጣጠል ሆኖ የተገመደ፣ የተዋደደና የተዋሐደ ነው! አማራው በካራማራ ለሀገሩ ሉዓላዊነት ተሠውቶ የካራማራ አፈር ሆኖ ቀርቷል። ትግራዋይ በመተማ ከሀገሬ

በፊት አንገቴን ውሰዱ ብሎ የመተማ አፈር ሆኗል። ኦሮሞው በዐድዋ ተራሮች ላይ ስለ ሀገሩ ደረቱን ሰጥቶ የሀገሩን ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ከዐድዋ አፈር ተቀላቅሏል። ሱማሌው፣ ሲዳማው፣ ቤንሻንጉል፣ ወላይታ ጋምቤላው፣ ጉራጌው፣ አፋሩ፣ ስልጤው፣ ከምባታው፣ ሐዲያው እና ሌሎቹም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁሉ በባድመ ከሀገሬ በፊት እኔን ብለው እንደ ወደቁ ከባድ አፈር ጋር ተዋሕደዋል። አንድ ኢትዮጵያዊ አባት እንዳሉት፤ እኛ ስንኖር ሰዎች፣ ስናርፈ አፈር፣ ስናልፍ ሀገር እንሆናለን። የየትኛውንም ኢትዮጵያዊ ክቡር ሥጋና በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ውስጥ አፈር ሆኖ ታገኙታላችሁ፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ደግሞ ኢትዮጵያ እንሆናለን።"

## የንግግሬ የምስጋና ክፍል...

በንግግሬ መጨረሻ ላይ በሕይወት ጉዞዬ አብረውኝ የነበሩትን የትግል ጓዶቼንና ባለቤቴን በተለይም እናቴን ማመስገኔና ዕውቅና መስጠቴ፣ ለንግግሩ ሰው ሰው መሸተት ብቻ ሳይሆን፤ በየሰዉ ውስጥ ያለውን ጥልቅና በጎ ሰብአዊ መልካምነት የኮረኮረ እውነት መሆኑ፣ የራሱ አስተዋጽዖ ሊኖረው እንደሚችል እጠረጥራለሁ። ዳሩ ግን ንግግሩን ከማቅረቤ በፊት ጠንከር ያሉ አስተያየቶች ተሰንዝረውበት፣ አንዳንድ ወዳጆቼም ቆርጬ እንዳወጣው መክረውኝ የነበረ ቢሆንም፤ ከቀረበ በኋላ በብዙዎች ዘንድ መልካም የሆነ አቀባበል ማግኘት ችሏል።

"...የሰባት ዓመት ልጅ እያለሁ እንዲህ ከፊታችሁ እንደምቆም የምታውቅና ይኼንን ሩቅ፣ ጥልቅና ረቂቅ ራእይ በውስጤ የተከለች፣ ያሳደገችና ለፍሬ ያበቃች አንዲት ኢትዮጵያዊት እናት እንዳመሰግን በትኅትና እጠይቃለሁ.

**"ይህች ሴት እምዬ ናት፤**

"እናቴ ከሌሎቹ ቅን የዋህና ጎበዝ ኢትዮጵያውያት እንደ አንዶቹ የምትቆጠር ናትና፣ ቁሳዊ ሀብት ብቻ ሳይሆን ዓለማዊ ዕውቀትም የላትም። በእናቶች ውስጥ ሁሉንም የኢትዮጵያ እናቶች ዋጋና ምስጋና እንደ መስጠት በመቁጠር ዛሬ በሕይወት ከአጠገቤ ባትኖርም፣ ውዷ እናቴ ምስጋናዬ በዐጸደ ነፍስ ይደርሳት ዘንድ በብዙ ክብር ላመሰግናት እወዳለሁ። ሌሎች ኢትዮጵያውያን እናቶቼ በልጆቻቸው የነገ ራእይ ላይ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው በመገንዘብ፣ ነገ ለሚያቅዱት መልካም ፍሬ፣ ዛሬ ላይ የሚዘሩት ዘር ዋና ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ለሚከፍሉት መሥዋዕትነት ያለኝን በምንም የማይተካ አድናቆት፣ ምስጋናና ክብር፣ በብዙ ልባዊ ፍቅር ሳቀርብ በቀጣይም ልጆቻችን የዚህችሀገር ሕዳሴ እንዲረጋገጥ፣ ዋና ተዋንያን መሆን እንዲችሉ፣እናታዊ አይተኬ ሚናችሁን እንድትወጡ አደራ በማለትም ጭምር ነው።

".. የሚስቶች ስኬት ሁለትና ሦስት ነው። ሁለት ሲሆን፣ አንዱ የራሳቸው ሌላው ስኬታቸው ከዚህም ይሻገራል። የእናቴን ራእይ ተረክባ በብዙው የደገፈችኝና የእናቴ ምትክ የሆነችልኝ ውዷ ባለቤቴ ወ/ሮ ዝናሽ ታያቸው ከነዚህ ሚስቶች ተርታ ትመደባለችና እጅግ አድርጌ ላመሰግናት እወዳለሁ።"

አዎ ይሄኛው የንግግሬ የመጨረሻው ክፍል ጠንከር ያሉ አስተያየቶች ተሰንዝሮበት ነበር።

አስታውሳለሁ... በበዓለ ሢመቱ ዕለት ወደ ፓርላማው አዳራሽ ከመግባቴ በፊት ማለዳ ላይ ሁለት ቀደምት የኦሕዴድ አመራር የሆኑ የቅርብ ወዳጆቼን አግኝቻቸው ነበር። አንዳንድ ሐሳቦችን ከተለዋወጥን በኋላ የዕለቱን ንግግሬን አነበብኩላቸው። ንግግሩን _ ሁለቱም እንደወደዱት ከፊታቸው በጉልህ ይነበብ ነበር። ለስሜቱ ቅርብ የሆነና አስተሳሰቡን የማከብርለት አንደኛው ወዳጄ በተለይ ስሜቱን ለመደበቅ አልቻለም፤ በጣም ጥሩ ንግግር እንዳዘጋጀሁ ነገረኝ። እንደ ማስተካከያ ግን መጨረሻ ላይ ያካተትኩትን ምስጋና ተመልሼ እንዳየው ጠየቀኝ። እንደዚያ ዓይነት መድረክ ላይ እናትን ማመስገን እንደ መመጻደቅ ሊያስቆጥር እንደሚችል _ ስለሠጋ ቆርጬ እንዳወጣው መከረኝ።

የእርሱ ሥጋት ትችትን ከመፍራትና ለእኔ መልካሙን ከመመኘት እንደመነጨ ባውቅም፣ አስተያየቱ ግን በጊዜው አልተዋጠልኝም። ስለዚያም የምስጋናውን ክፍል ባለበት ተውኩት። በሀገራችን፣ በተለይም በፖለቲካው መንደር የተገነባ መጥፎ ባህል አለ። ብዙዎቹ መሪዎቻችን፣ መመስገንና መደነቅን እንጂ ማመስገንና የስኬትን ዋጋ ለቤተሰብ ማካፈል ያን ያህል አያሳስባቸውም፤ ወይም ተገቢ አይመስላቸውም።

ሲቆይ ይኼ ባህል ሆኖ ቤተሰብን ማመስገን እንደ ነውር መቆጠር ጀመረ፤ ወይም የመርሳት በሽታ ትልቁ የፖለቲካችን ችግር ነው። እንደ ሮቦት ስሜት አልባ መሆን ሰው የሚያደርጉንን ሰብአዊ ባሕሪያት መተው፤ የግል ሕይወት እንዳለን መዘንጋት፣ሁሉንም ነገር ጠቅልሎ  ለራስ፣ ለድርጅትና ለፓርቲ የመስጠት አባዜ የሮቦት ፖለቲከኞች መገለጫ ጠባይ ከሆነ ሰነባብቷል። ሰው ሰው አለመሽተት ነው አንዱ  ከኢትዮጵያዊነት ተርታ ያስወጣን።  ለማኅበረሰባዊ ዕሴቶች ትልቅ ቦታ ለሚሰጠው  የኢትዮጵያ ሕዝብ የሮቦት ፖለቲከኞች አካሄድ አይዋጥለትም። እኛ ሰው ሆነን እንድንቀርበው እንጂ ግዑዝ አካል መስለን እንድንቀላቀለው አይፈልግም። ሰው መሆናችን እንደምንሳሳት ብቻ አይደለም የሚጠቁመው፤ ካጠፋን ልንታረም እንደምንችልም ጭምር እንጂ።

ጥቁር አሜሪካዊቷ ገጣሚት ማያ አንጀሎ በአንድ ወቅት ስለማልኮልም ኤክስ ተጠይቃ ስትመልስ፣ “ማልኮልም በጣም ቀልድ ዐዋቂ ነው። የታሪክ ጸሐፍት የሚሠሩት አንድ ስሕተት፤ ጀግና ሰዎችን ከሕይወት በላይ አድርገው መሣላቸው ነው። ይሄም ለወጣቶቹ ተደራሽ እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል። ወጣቶቹ እነርሱን መሆን እንደማይችሉ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል” ብላለች። በእኛ ሀገር መሪዎች ራሳቸው ሰው መሆናቸውን ለመደበቅና ከሕይወት በላይ እንደሆኑ ለማስመሰል ይሞክራሉ። ሳቃቸውን፣ ዕንባቸውን፣ ፍቅራቸውን፣ ብሶታቸውን፣ ደስታቸውን ሊደብቁ ይሞክራሉ። ከሕይወት በላይ እንደሆኑ ሊያሳዩ ይሞክራሉ። ሰው መሆናቸውን ይደብቃሉ።  ይህ የተሳሳተ መንገድ መታረም አለበት ብዬ አስባለሁ።

እውነት ለመናገር በወቅቱ ወዳጄ እናቴን የማመሰግንበትን  ክፍል  እንድቀንሰው ሲጠቁመኝ በፍጹም አይሆንም› እንድል ያደረገኝ ምክንያት ይሄ አልነበረም። እርግጥ ነው፣ ስለሮቦት ፖለቲከኝነት ከዚያ ቀደም ብዙ

ጊዜ አስብ፣ አውጠነጥን ነበር።

ሊቀር የሚገባው እንደሆነም በተለያዩ አጋጣሚዎች ተናግሪያለሁ። ሆኖም ግን፣ ወዳጄ በዚህ አመክንዮ ራሴን ስላስገዛሁ አልነበረም። አመክንዮ ከጭንቅላት የሚቀዳ ነገር _ስለሆነ እምብዛም ስሜታዊ አያደርግም። በአንጻሩ አስተያየታቸውን መቀበል በወቅቱ በእናቴ ላይ ክህደት የመፈጸም ያህል ልብን የሚከብድ ስሜት ነበረው። ውለታዋን ሁሉ አይቶ እንዳላየ በማለፍ፣ የበላሁበትን ወጭት የሰበርኩ መስሎ ታየኝ። እንዴት ተደርጎ እርሷ የሰጠችኝን ራእይ ሳልናገር አልፋለሁ? ከየት አመጣሁትስ  እላለሁ? ብዬ እንዳብሰለስል አጋጣሚው አስገድዶኛል።

በዚያን ሰዓት ከማንምና ከምንም ነገር በላይ ገዝፎ ልቡናዬን የያዘው የውዷ እናቴ ወደር የለሽ ትውስታ ነበር። ወደ ዘላለማዊ ቤቷ ተሰናብታኝ ከሄደች ገና ዓመት እንኳን ያልሞላት እማዬ፤ ይሄን የትንቢቷን መፈጸምና የምኞቷን ድምዳሜ በዓይኗ ብታየው ምንኛ ጥሩ ነበር።

የአብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ምስኪን እናቶችም ታሪክ ከዚህ የተለየ አይደለም። ዕድሜውንና ዕድሉን አግኝተው የሥራቸውን ፍሬ አይተው ተመስገን› ለማለትና ለመመስገን ቢደርሱም ባይደርሱም፣ ለልጆቻቸው ሕይወት መሻሻል ሲሉ ራሳቸውን አሳልፈው መስጠት የእናትነታቸው መገለጫ ነው። መቼም ቢሆን የሕይወትን ስጦታ በሕይወት እንጂ በሌላ መመለስ አይቻልም። ልብና ነፍሷን በልጇ ሕልም ላይ ላፈሰሰችውና የሕልሜ ፈጣሪ ለሆነችው እናቴ ይህ ቢያንሳት እንጂ የሚበዛባት አይደለም። እንደ እናቴ ምትክ የማያት ባለቤቴም በወቅቱ ምስጋና ይገባት ነበር ከአፍላ ወጣትነት ዕድሜዬ አንሥቶ እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ እንድበረታ ስላደረገች ከጥንካሬዋ ቆርሳ ዐቅም ስለጨመረችልኝ፣ ዘመም ስል ድጋፍ ስለሆነችኝ በእርግጥ መመስገን አለባት።

በሌላ ቀን አስተያየት ሰጥቶኝ ከነበረው ወዳጄ ጋር ስንገናኝ ምን ያህል የተሳሳተ ግምት ባለቤቴን ማመስገኔ በሕዝቡ ላይ የፈጠረውን አዎንታዊ ተጽዕኖ በአግራሞት ነገረኝ። ቃል በቃል ባይሆንም የሮቦት ፖለቲከኝነት ሐሳብ መቅረት እንዳለበት በቀልድ አድርጌ አንሥቼለት ነገሩን ተሳስቀን አለፍነው።

ከልጅነቴ በእናቴ በኩል የተፀነሰው ሀገርን የመምራት ሕልም እውን በሆነባት መጋቢት 24 ቀን፣ 2010 ዓ.ም. ላይ ቆሜ ወደ ኋላ በትዝታ ነጎድኩ። ወደ ምንጬ በትዝታ አዘገምሁ።

# ትንሹ ዐቢይ በበሻሻ

ገና አንድ ፍሬ ልጅ ነበርኩ፤ በትንሿ የገጠር ከተማ በሻሻ።

የመንደራችን ሕፃናት እንደ ሁልጊዜ የእሑድ ልማዳችን ከምሳ በኋላ ሜዳ ወርደን ኳስ እየተጫወትን ሳለ፣ ጀርቦሴ ወደ ምንጫወትበት ሜዳ ዘግይቶ መጣ። አቋቋሙ ወደ በኋላ ስሜን ጠርቶ እንዳስገባው ጠየቀኝ።

አንድ ተጨዋች ጎድሎን ስለነበር የእኛን ቡድን እንዲቀላቀል ተናግሬ ሳልጨርስ በደስታ ሮጦ ገባ። ጨዋታችንን አንዴ እያሸነፍን አንዴም እየተሸነፍን ቀጠልን። ጀንበር አዘቅዝቃ፣ ምሽቱ ለዐይን ይዞ፣አላጫውት እስኪለን ድረስ፣ ኳሷን ስንቀጠቀጥ ቆየን። ወደየቤታችን ስንበታተን ገላችን በላብ ተጠምቆ፣ ሰውነታችን በድካም ዝሎ ነበር።

ታዲያ እየሄድን ሳለ፣ በድንገት ጀርቦሴ “በቃ ትገለኛለች!" ብሎ ዕንባ ተናነቀው።

“ምነው? ጀርቦሴ ምን ሆንክ? ማናት የምትገድልህ?" ከብበን በጥያቄ አጣደፍነው። ጀርቦሴ በጣም ፈርቷል። ዐይናችንን እንኳን ለማየት አልቻለም። እየተርበተበተ መለሰልን።

“እናቴ... እማዬ ትገለኛለች” ብሎ እንዳቀረቀረ ቀረ።

ለካ ከቤት የወጣው እንዲጫወት ተፈቅዶለት ሳይሆን ጫካ ወርዶ ጭራሮ እንዲለቅም ተልኮ ኖሯል። ጨዋታ አዘናግቶት የተላከበትን ጉዳይ ሳይፈጽም መሸ። ጫካው ደግሞ እንኳንስ እንዲህ መሽቶ በቀንም ያስፈራልና በዚያች ደቂቃ መሄድ የሚታሰብ ነገር አይደለም። አውሬዎች ወደሚምነሸነሹበት ወደዚያ ጫካ አብሮት ለመሄድ የደፈረ ልጅም ከመካከላችን አልተገኘም። ጀርቦሴ በፍርሃት ራደ። እኛም የምናደርገው ጨነቀን።

ሰውን ለመርዳት ፍላጎት ብቻውን በቂ አልሆነም። ደፋር ልብም ይጠይቃል።

ፍርሃት ምን እንደሆነ ለመረዳት የጄርቦሴን ፊት መመልከት ወይም ወደ ጫካው ስለ መሄድ ማሰብ በቂ ነበር። ቆይቶ አንድ ሐሳብ መጣልኝ። እኛ ቤት፣ ታላላቆቼ ሰብረው የከመሩት የማገዶ እንጨት አለ። የተፈለጠ ካገኘን አገኘን፣ ካላገኘንም ሳይፈለጥ ከተከመረው ላይ አንድ ሁለት ልሰጠው ተስማማንና ወደኛ ግቢ አመራን። እንጨቶቹን በአጥር አሻግሬ ካቀበልኩት በኋላ ጀርቦሴን ተሰናብቼ ወደ ቤቴ ዞርኩ። ማንም አላየኝም ብዬ ሱክ ሱክ እያልኩ ወደ ቤት ልገባ ስል፣ ከበስተኋላዬ የእማዬን ድምፅ ሰማሁ።

“ሞቲ ከወዴት መጣህ?” ጠየቀችኝ ወደ እኔ እየቀረበች። ድምፅዋ ውስጥ ቁጣም ሆኑ ተግሣጽ አልነበረም። እኔ ግን ደንግጫለሁ። “ሞቲኮ ማልጎዳ ቱርቴ?" አለች ደገመችና እማዮ አልፍ አልፍ ካልሆነ በቀር ስትጠራኝም ሆነ ለብቻችን ሆነን ስታወራኝ በአመዛኙ “ሞቲ” ነበር የምትለኝ። እኔ ደግሞ እንደ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ልጆች እማዬ ብዬ ነው የምጠራት።

በኀፍረት አንገቴን ደፋሁ። ልዋሻት አልቻልኩም፣ ብችልም አልፈልግም። በፍርሃት ውስጥ ሆኜ እውነቱን ነገርኳት።

“ጀርቦሴ እንጨት ልቀም ተብሎ ከኛ ጋር ኳስ ሲጫወት መሸበት። እናቱ እንዳይገርፏት ስለፈራ ከኛ ክምር ላይ ሁለት እንጨት ሰጠሁት” ብዬ፣ መልሼ አቀረቀርኩ። ወደ ራሷ አቀረበችኝና ራሴኝ እያሻሸች፣

“ታዲያ… እውነትን መናገር እንጂ መስረቅን ምን አመጣው?”

“እንዳትቆጪኝ ፈርቼ ነው፣ ያልነገርኩሽ”

“ቢሆንስ! ፍርሀትን በፍቅር ማሸነፍ አትችልም? እውነቱን ተናግረህ በፍቅር ማሸነፍ ስትችል ተደብቀህ ትሰርቃለህ? ዕወቅ እሺ፣ ፍቅር ከእውነት ጋር እንጂ ከውሸት ጋር አብሮ አይሄድም። በፍቅር እውነቱን ከተናገርክ ለሁሉም ነገር መፍትሔ ይኖርሃል፤ ውሸት ወደ ትክክለኛው መንገድ ማንንም አድርሶ አያውቅም።” አለችኝ።

አሁን ሳስበው ገና በዕድሜዬ ማለዳ፣ ሁሉን በሚቀበል የጨቅላ አእምሮዬ ሰሌዳ ላይ፣ ትናንት ላይ ሆና የልጇን ዛሬ ማየት ችላ ነበር። ዛሬ ላይ ሳጤነው በፍጹም እምነትና በጽኑ መሠረት ላይ፣ የልጇን ራእይ እየተከለችና እየኮተኮተች፣ የመጻኢ ዘመኔን አቅጣጫና መዳረሻ ትገነባ እንደነበር ይሰማኛል። የዚያን ምሽት ከእናቴ ጋር ተያይዘን ወደ ቤት ስንገባ ምንም የተፈጠረ አይመስልም ነበር። የተለመደው የእናትና የልጅ ግንኙነት ቀጠለ።

እማዬ አንዳንድ ጊዜ ልጅነት አሸንፎኝ ወይም ድክም ብዬ ከምክሯ ያፈንገጥኩ ሲመስላት፣ ቃልና ምግባሬን ማስማማት እንዳቃተኝ ስታይ፤ “ልጄ፣ ንጉሥ በምግባሩና በቃሉ እንጂ በተናጠል አያስተምርም” ትለኛለች።

በቤት ውስጥ በእኔ ዕድሜ ያሉ፣ በእረኝነት አልያም በቤት ውስጥ ሥራ አገልግሎት እየሰጡ የሚኖሩ ዘመዶቻችንን ክብር የሚያጎድል አንዳች ያልተገባ አነጋገር ከተናገርኩ፣ እናቴ ከአፌ ቀለብ አድርጋ፤ “አይምሰልህ ልጄ… በሞት ምድርን የተሰናበተ ካልሆነ በቀር፣ በሌሎች ፊት እንግዳ የማይሆን ሰው ማንም የለም” በማለት፣ የግሏን ሕይወት ምሳሌ አድርጋ ታስረዳኛለች። አንደበተ ጣፋጭ፣ ንግግር ዐዋቂ፣ ትረካዋ ተሰምቶ የማይጠገብ እናት ነበረች፤ እማዬ።

አባቴ ሼህ አሕመድ ዓሊና እማዬ፤ እሷ እሱ ተብሎ ሊለይ በማይችል የወላጅ ፍቅር የልጅነት ዕድሜዬን ልዩ አድርገው ነው ያሳደጉኝ። አባቴ ሲበዛ ትጉህ ሠራተኛ የነበሩ። ንግግር ላይ እምብዛም ናቸው። ብዙ ጊዜያቸውን በሥራና በዝምታ ነበር የሚያሳልፉት። አልፎ አልፎ እንዲህ ስለአባቴ ሳወራ ‹አንቱ› ማለት ነው የሚቀናኝ።

ከእማዬ ጋር የነበረን ቅርበት ግን የአካል ብቻ ሳይሆን የነፍስ ትስስርና የመንፈስ ቁርኝትም እንደነበረው ይሰማኛል። በራእይና በሥነ ምግባር፣ በሀገርና በወገን ፍቅር፣ በክብርና በደግነት፣ በሥርዓትና በቅንነት እንዲሁም በትኅትናና በአትንኩኝ ባይነት ሚዛናዊ ሕይወት ኖሮኝ እንዳድግ በልጅነት ዕድሜዬ ማግኘት ከሚገባኝ ክብካቤ አንዱንም አላስቀረችብኝም።

አልፎ አልፎ፣ የአካባቢያችን ሰዎች በጎም ሆነ መልካም ነገር ለእናቴ ማውራት ያስደስታቸዋል እንድል የሚያደርጉኝ አጋጣሚዎች ነበሩ። እኔ ሰፈር ውስጥ ያደረግኋት ነገር ሁሉ ከመቅጽበት እናቴ ጆሮ ትደርሳለች።

"ዛሬ ልጅሽ እንደዚህ ዓይነት ግሩም ሥራ ሠራ። እንዲህ ዓይነት አስገራሚ ነገር ተናገረ። ይሄ ጉደኛ ልጅሽ የሚሠራው ሥራ ዐዋቂ እንኳን ሊያደርገው የሚከብድ ነው።" እንዲህ ዓይነት ዜናዎችን ከሰፈራችን ነዋሪዎች መስማት ለእናቴ የተለመደ ነገር ነው። እሷም የደከመችበት ፍሬዋ ከበሻሻና ከአካባቢዋ፣ ከመንደሯና ከከተማዋ ባሻገር እንደሚያልፍ እርግጠኛ በመሆን፤ "ልጄ አይስትም፣ ይነግሣል" ትላቸዋለች።

ዛሬ ላይ ሆኜ የልጅነትና የወጣትነት ዘመኔን ሳስብ፣ የድልና የሰላም አድራሻው፤ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር፣ ከመለያየት ይልቅ ትብብር፣ ከመነጣጠልም ይልቅ መደመር እንደሆነ የሚያስገነዝቡ ብዙ አጋጣሚዎች ነበሩ። የሰው ልጅ ስለ ምቀኝነትና ክፋት ማሰብን አቁሞ፣ የራሱን ወገን የማጥፋት መሠሪ ጉጉቱን ትቶ፣ ስለመደመር ቢያስብ፤ ምናልባትም ገነት ከእያንዳንዳችን ውስጥና አጠገብ ልትሆን እንደምትችል አስባለሁም፤አምናለሁም። ይህ እምነቴ የተፀነሰው በትውልድ መንደሬ በሻሻና አጋሮ ባሳለፍኩት የልጅነቴ ወራት ነበር።

ለሀገራችን ሕመም ፍቱን መድኃኒት ለማምጣት ሩቅ መጓዝ አያሻንም። ወደ ውስጣችን ብናማትርና በአጠገባችን ብንፈልገው በቀላሉ እናገኘዋለን። ይኽን በማስተማር በኩል ትንሽዋ መንደር በሻሻና እናቴ ትልቅ ቦታ አላቸው።

# መደመር በበሻሻ

በትንሿ በሻሻ እኔ ባደግሁበት መንደር የሰፈርተኛው የኑሮ ደረጃ ያልተራራቀና እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ዝቅተኛ የሚባል ነበር። ከተወለደ ጀምሮ በዚህ ዓይነት ኑሮ ውስጥ ላደገ አንድ ሕፃን፣ የወደፊት ታላቅ ጥሪው ሀገርን መምራት እንደሆነ ማሳመን የማይታሰብ ነው። ነገሩን አምኖ ለተቀበለው ታዳጊ ሕፃን ደግሞ ከዚህ ያልተናነሰው ከባድ ሥራ የዕድሜ እኩዮቹን ማሳመኑ ነው።

የጓደኞቼን እምነት ለማግኘት በአንድ በኩል ሁልጊዜም አንድ ደረጃ በዕውቀትና በክሂሎት ቀድሜ መገኘት አለብኝ። በሌላ በኩል ደግሞ አገልጋይነትና ትሕትና የጠባዬ ከፍል መሆን ነበረበት። ያለኝን የዕውቀት፣ የክሂሎትና የጠባይ ክፍተቶች በመሙላት ረገድ የእናቴ ሚና እጅግ የላቀ ነበር።

ከደጓ እናቴ መልካም አንደበት የሚወጣው ደጋፊ ምክሯ ርቆኝ አይውቅም። ለሚያደናግሩኝና ግራ ለሚያጋቡኝ ጥያቄዎቼ በወግ፣ በተረትና በምሳሌ የተከሸኑ ምላሾችን ትሰጠኛለች።

እናቴ ልስላሴና ብርታቷ፣ ተጫዋችነቷና ቆፍጣና ቁጣዋ ሚዛናቸውን ሲስቱባት አይቼ አላውቅም። ለምሳሌ ታላላቅ ወንድሞቼ አስቸግረው በምክር ፍቅር አልመለስ ሲሏት ሽመል አንሥታ ልክ ስታስገባቸው፤ እኔ አንዱ ጥግ ላይ ቆሜ አስተውላታለሁ ሲብስባት ወንድሞቼን በአርጩሜ አንቆራጥጣ ስታበቃ የያዘችውን በትር ወዲያ ወርውራ አሻግራ ወደ እኔ እየተመለከተች፤ "የጎረምሳን ጥጋብ የምታርቀው ሲቀር በምክር ሲጠም

በበትር ነው” ትለኝ ነበር።

የሰፈራችን ሰዎች “ወይዘሮ ትዝታ ኃይለኛ ሴት ናት” ሲሉ እሰማለሁ። ኃይለኛ ሲሉ መጀመሪያ ጨካኝ ናት ለማለት እንደሆነ አስብና ግራ ይገባኝ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ ስለ ደግነቷና ስለ ሩኅሩኅነቷ ሲያወሩ እሰማለሁ። የታመመን ለመጠየቅና የተቸገረን ለመርዳት የማትታክት፣ በሰርግም ሆነ በልቅሶ ፈጥና የምትደርስ የማይደክማት ፍጡር እንደሆነች የሚያውቋት ሁሉ ይመሰክራሉ።

በ1977 ዓ.ም. በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከሠተው ድርቅና ረኃብ ሳቢያ ብዙዎች ከሰሜን ወደ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ለሰፈራ ይጓጓዙ ነበር። ሰፋሪዎቹን የያዘው ትሬንታ ኳትሮ በሻሻ ከተማ ሲደርስ ይቆማል። እናቴ ስታያቸው በጣም ታዝናለች። ዐይኖቿን ዕንባ እየሞላው፤ “ሥርህ አይነቀል ልጄ” ትለኛለች። ወዲያው በበገፈጅ ድስት ወጥ ትሠራና የሚበሉት ምግብና የሚጠጡት ውኃ ይዛላቸው መኪናቸው ወደ ቆመበት ሥፍራ ትጣደፋለች።

እናቴ ስለነገ ቁልጭ ብሎ የሚታያት ነቢዪት ናት ስል ቀልድ አይደለም። በትክክል የልጅዋ የነገ ሕይወት ኮለል ብሎ የሚታያት ሴት ነበረች። በልቤ ውስጥ ባዶ ምኞትን አልተከለችም፤ ተጨባጭ ራእይን እንጂ። እናቴ ነገ ይዞልኝ ስለሚመጣው መልካም ነገር ቁጭ ብዬ በተስፋ እንድጠብቅ አላደረገችኝም። ስለነገዬ ከዛሬ ጀምሬ እንድተጋ፣ ለሚመጣው ነገር ሁሉ ሌሊትና ቀን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል እንድሠራ አስተምራኛለች። አይደለም፣ የመደመርን መርሕ የተማርኩት ከበሻሻ ገበያ እንደሆነው ሁሉ ራእይን የሰጠኝ ማንም አይለደለም ። እናቴ ናት።

# በሻሻ-ኦልማፍ ገሊን ቢላሻ...

## (በሻሻ - ውሎ መግባትም በነጻ)

ጂማን አየሁ አትበይ እንዳይቀድምሽ ቀኑ

በሻሻና አጋሮ ሄድሽ ወይ ለመሆኑ?

መደመርን ያስተማረችኝ በሻሻ ናት። ትንሽዋ በሻሻ ትልቅ የሆነ ሐሳብ ሰጥታኛለች። በሻሻ የልጅነት ትዝታዎቼ የተጠራቀመባት ቦታ ናት። ራእይ ያስታጠቀችኝና መንገዱን የመራችኝ ደግሞ እናቴ ትዝታ ወልዴ ናት።

የምዕራብ ሸዋ ዞን፣ የመናገሻዋ ፍሬ፣ ትዝታ ወልዴ፣ ብዙ የሕይወት ማግና ረጅም የኑሮ ድር ሸመናዋ

የተጀመረው ከጊቤ ማዶ ነው። በሻሻም የማይናቅ አሻራዋን አስቀምጣባታለች። ከከበቧት የጎማ ተራሮች መካከል በዝምታ የተጋደመችው ትንሿ የገጠር ከተማ በሻሻ፣ በዘመን ሐዲድ ላይ ለዘመናት አያሌ ታሪኮችን አስተናግዳለች። በበጎውም በክፉውም የምታስታውሳቸው እልፍ የታሪክ ኩነቶችን እንዴም በሳቅ፣ _ ደግሞም በእሮሮና በልቅሶ አስተናግዳ ሁሉንም እንዳመጣጣቸው አሳልፋቸዋለች። የብዙ ባህልና ዕሴት ማዕከሏ፤ የብሔርና እምነት ውብ ጥበብ መሸመኛዋ ትንሿ በሻሻ የብዙኅነት ቅይጥ ውብ መልኳ ከፊቷ ይነበባል። ከዚህች ዝም ካለች ሙዳይ ውስጥ ሕይወት በዝግታ ትፈሳለች። አረንጓዴ ለብሳ፣ አረንጓዴ ሆና ዓመትን ከዓመት የምትገጥመው በሻሻ፣ የሳምንቱን ቀናት በአርምሞና በእርጋታ ትቆይና፣ የገበያዋ ቀን ሲደርስ ከዝምታ ድባቧ በማለዳ ትነቃለች። በዝምታዋ ውስጥ ብዙ ኅብራዊ ድምፅ፣ በአርምሞዋ ውስጥ ብዙ ተመስጦ፣ በርጋታዋ ውስጥ ብዙ አስተውሎት እየደመረች መሸታ ትነጋለች።

በአዘቦቱ ቀን ወደ በሻሻ የመጣ ጥቁር እንግዳ ውኃ ጠምቶት ሊለምን፣ መድኃኒት አጥቶ ሊያቃስት ይችላል። በአዘቦቱ ቀናት በሻሻ የዝምታ ደሴት ናትና። ቤቶቿ እንጂ መንገድ ደጆቿ የማይሞቁ። የቅዳሜ ጎሕ መቅደድ ሲጀምር ግን በሻሻ መልክአ ሕይወቷ ይለወጣል። በገበያዋ ቀን ቅዳሜ ተአምር ይታያል። በየሰፈሩና በየመንደሩ ተበታተኖ የከረመው ወገን ሁሉ፣ ትናንሽ ነገሮችን ቋጥሮ ወደ በሻሻ ገበያ ይጎርፍና፣ ትልቅ ሕዝብ ይሆናል። የሚሰማው የቋንቋ ስብጥርና ሹክሹክታው እንደ ንብ መንጋ እየተመመ፣ እንደ ሐምሌ ነጎድጓድ ሲያስገመግም፣ አንዳች ኃይለኛ አርዕድ አንቀጥቅጥ ድምፅ ይፈጥራል። ግርማ ሞገስ ያለው ድምፅ። የብዙ ቋንቋዎች ውጤትና የአያሌ ሐሳብ ድምር ድምፆች በፈጠሩት ኅብረ ቅኝት፣ ከአንድ የዜማ ሊቅ አንደበት ተሰልቶ የወጣ ጣዕመ ዜማ ይመስላል።

በጣም አርቆና አድቅቆ ካለማሰብ የተነሣ ወድቀን መገኘታችን ካልሆነ በቀር፤ ከእናቴ ሕይወት የምረዳው መፍትሔ የሌለው ችግር፣ ወይም ተዘግቶ የማይከፈት በር ሊኖር አለቻሉ ነው። ገደልን የፈጠረ ፈጣሪ፣ መውረጃ አይነሳም" ይላሉ ኢትዮጵያውያን። በገደሉ መሐል መውረጃን መለየትና መተለም ግን የእኛ ድርሻ ነው። ሆኖም የችግሩ መወሳሰብ ጥልቅ ማሰብን ስለሚጠይቅ ብቻ መፍትሔውን ፍለጋ ከመድከም ይልቅ አእምሯችንን አጣጥፈን መቀመጥ ይቀለናል። የሐሳብ ሳይሆን የድርጊት ምርኮኞች ነን። የጠፉብንን ቁልፎች ሁሉ ፈልገን ለማግኘት ከመኳተን ይልቅ የሁሉን መክፈቻ የወርቁን ቁልፍ ለመፈልግ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል። የሁሉም ባይሆን የአመዛኙ ችግሮቻችን መፍትሔ የሆነው የመደመር ፅንሰ ሐሳብ በሙሉ ጥልቀቱና ደርዙ ባይሆንም መፍትሔዉን በውስጡ አቅፎ ይዟል ብዬ አምናለሁ።

ያደግኩት ብዙ ባህልና ዕሴት በተዳወረባት፤ የብሔርና እምነት ድርና ማግ የተፈተለባት፣ ውብ ጥለት ሆና በተሸመነችው በትንሿ ከተማ በበሻሻ ነው።

ለእኔ ብዙኅነትና ቅይጥነት ያለጥረትና ያለ ስብከት የተማርኩት ጥልቅ እውነት ነው። ደረታቸውን ለሰማዩ ሰጥተው የከረሙ የሸቀጥ መደቦችና አፋቸውን ከፍተው የከረሙ ይከፈታሉ። ከየቤት ከየሰፈሩ ተሸክፈው በደረሱት ትናንሽ ቋጠሮዎች ይደምቃሉ። ይሞላሉ። ዓይነቶቹ በአንድ ተደምረው፣ ብዙ ምርትና የተትረፈረፈ ሀብት ይሆናሉ። ሳንቲሞች እየተቅጨለጨሉ ተጠራቅመው ብር፣ ብሮች ተደራርበው የደረጀ ሀብት ይሆናሉ።

ግለሰቦች ተደምረው ሕዝብ፣ ቅንጣቶች ተደምረው ድልብ ይሆናሉ እዚያው በሻሻ ገበያ ላይ።

የበሻሻ ገበያ የመደመር ፍልስፍና ትእምርት ነው። ሁሉም የየራሱ ሀብት፣ ጸጋ፣ በረከት፣ አስተዋጽዖ አለው። ለየብቻው ግን ኃይል መፍጠር፤ ሕይወትን መቀየርና ወደ ልዕልና መሻገር አይቻለውም። ለዚህ ነው ሁሉም ያለውን ይዞ ገበያ የሚወጣው። እዚያ ገበያ ውስጥ ይሟላል፤ ይካፈላል፤ ይለዋወጣል። ገንዘብና ሸቀጥ ብቻ ሳይሆን ባህልና እምነት፣ አስተሳሰብና ዕውቀት ይለዋወጣል። ገበያ የሚሰጥህን እናትህ አትሰጥህም, የሚባለውን በትክክል የምናይበት ነው - የበሻሻ ገበያ።

በበሻሻ ገበያ የጠፋ ዕቃ ብቻ ሳይሆን የጠፋ ሰውም ይገኝበታል። የሩቅና የቅርብ _ዘመድ፤ የድሮና የዘንድሮ ወዳጅ ይገናኛል። ይሄን ሙላት ይሄን ኅብረት ምን _ አመጣው? ከተባለ መልሱ ገበያ የኀተተው የሰዎች መደመር፣ ሰዎች የፈጠሩት የአቅርቦትና የሀብት መደመር ነው። ውዷ እናቴ ሁልጊዜም እንደምትለው “ገበያና ትምህርት ቤት አያገናኘው ጉድ የለም።”

በበሻሻ ታሪክ ነዋሪዎቿ በክፉ ትዝታ የምናስታውሳቸው አጋጣሚዎች አሉ። ዘርንና እምነትን መሠረት አድርገው የተፈጠሩ ግጭቶች፣ በዚህም ምክንያት የጠፋ ሕይወት አለ። እነዚህን ነገሮች በሚገባ መርምሬያቸዋለሁ። ከከተማዋ ውጭ የሚመጡ እኩይ ሐሳቦች በአንዳንድ ተሸካሚዎቻቸው ላይ ተጭነው የተፈጠሩ እንጂ የበሻሻ ሐሳቦችና ድርጊቶች አይደሉም። ለዚህም ነው በእነዚያ ክፉ ገጠመኞች የሚያዝንና የሚቆጭ ነዋሪ እንጂ፣ የድል ስሜት የሚሰማው አንዳችም ሰው በከተማዋ ውስጥ የሌለው።

እናቴ ልቤ ውስጥ ያኖረችው ራእይ ሥራ ላይ የሚውልበት፣ ያለምኩት ሕልም እውን የሚሆንበት ሁነኛ መንገድ ያስፈልጋል። አዲስና ተሞክሮ ያልከሸፈ የሀገሪቱን የልብ ትርታ የሚመልስና የእኔን ማንነትና የሰብእና ደርዝ ሳያጣርስ የሚገልጥ መንገድ። ይህ አዲሱ መንገድ ምን ይሆን? ብዬ ተጠብቤና ተጨንቄ የፈጠርኩት አይደለም። ከልጅነቴ ጀምሮ በአስተዳደጌ የቀረጽኩት ነው። ነፍስ ካወቅሁም በኋላ የሕይወቴ አቅጣጫ በተቀየሰበትና በተቀረጸበት መንገድ ላይ ባጋጠሙኝ የሕይወት ልምምዶች አዳበርኩት። ቁልፍ የሆኑ የእኔ የምላቸው ሰዎች ትተውብኝ ባለፉት በጎ አሻራ በስሎ የወጣ የመደመር መንገድ ነው። ነገር ወደ ኋላ ሲያዩት ጠርቶ ይታያል› እንደሚባለው ዛሬ ላይ ቆሜ ሕይወቴን ስቃኝ የመደመርን ጭላንጭል ያየሁት ጥንት በበሻሻ ገበያ መካከል ነበር። በትንንሽ እግሮቼ ስዳክርና በሰው ባሕር ውስጥ፣ የመደመርን ጠበል በየሳምንቱ ስጠመቅ ነበር። የበሻሻ ገበያ ለእኔ የመደመር ተማሪ ቤቴ… የመደመር መቅደሴ ናት።

በርግጥ የመደመር ፅንሰ ሐሳብ እየገባኝ መጥቶ የመለያየትና የመበጣጠስ ዳፋውም ያስጨንቀኝ የጀመረው እዚያው በሻሻ ውስጥ በአዳጊነት ዕድሜዬ ነበር። በአዳጊ ልቡናዬ መለያየትና መገፈታተር የሚያስከትለው ጦስ እንደ ጥቅምት ሰማይ ቁልጭ ብሎ ይታየኝ ነበር። በሕዝቡና በመንግሥት መካከል ያለው እሰጥ አገባና በጠላትነት የጎሪጥ መተያየቱ ገና በአዳጊነቴ ይረብሸኝ ጀመር።

በነዋሪው ሕዝብና በመንግሥት መካከል የነበረው የሆድና ጀርባ ግንኙነት ጨቅላ ጭንቅላቴን ዘወትር ወጥሮ የያዘ ጉዳይ ነበር። የሃይማኖት ልዩነትና የብሔር ማንነት ጌጥና ውበት እንጂ የግጭት ምክንያት ባልሆነባት በሻሻ ለምንድነው በመንግሥትና በማኅበረሰቡ መካከል ይሄንን ያህል የጥላቻና የፍርሃት ግንብ ሊቆም

የቻለው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ላገኝለት አልቻልኩም። መንግሥት ዘወትር ሕዝቡ ልጆቹን ለብሔራዊ ውትድርና እንዲሰጥ በኃይል ያዛል። ይሄም አልበቃ ብሎት ምርቱን ለእርሻ ሰብል በርካሽ እንዲያቀርብና መንግሥት በተመነው ዋጋ መልሶ እንዲገዛ ያስገድዳል። ሕዝቡ ደግሞ ውስጡ በሚፈጠረው ቁጣና ዐመፅ መንግሥትን እንደ ጠላትና እንደ ውጭ ወራሪ እንጂ ለመብቱና ለደኅንነቱ እንደቆመለት የራሱ ኃይልና ወገን በፍጹም አያየውም ነበር።

ምንም ያህል ኃይል ቢኖራቸውና የፈለጉትን ለማድረግ ቢችሉም፣ ተቀባይነት ያላገኙ _አምባገነኖች እንዴት እንደሚረበሹና ውስጣቸው ዕረፍት እንደሚያጣ የተገነዘብኩት ያኔ ነው። ኃይል እጅና እግርን ሊያስር እንጂ ልብን ሊገዛ አይችልም። ኅብረተሰቡ የኃይል ርምጃዎችን በመፍራት ለመኖር ሲል ለይምሰል እሺታ ቢያሳይም ልቡ ግን በጽኑ ተቃውሞ እንደ ሸፈተ ነበር።

በቀድሞው ዘመንም ሕዝቡ ልቡን ለስሜቱ፣ ፊቱን ለባላባቱ ሰጥቶ ይኖር እንደነበር ባላባቶቹ አልተረዱም። እርሱ ግን፦

**"ከሀገር እኖር ብዬ**

**ልጅ አሳድግ ብዬ**

**ለባሻ ዳርኩለት ሚስቴን እቴ ብዬ!"**

ብሎ ነግሯቸው ነበር።

መንግሥት ቢያስፈራራ፣ ቢያቅራራ፣ ብዙዎችን ቢያስር፣ ቢገድል፣ የሕዝብን ልብ በጉልበት መግዛትም ሆነ ማንበርከክ የማይታሰብ ነገር መሆኑን ተረድቻለሁ።

አምባገነኖች የመንግሥት ሕዝብ ይፈጥራሉ እንጂ የሕዝብ መንግሥት አይሆኑም።ሕዝብን በመንግሥት ጉልበትና ጡጫ የተያዘ ምርኮኛ ያደርጉታል። ሕዝቡ ግን መንግሥት አልባ ነው። ቀንበር ጫኝ እንጂ መሪና አስተዳዳሪ፣ ሠራዒና መጋቢ የሆነ መንግስት እንደሌለው ያምናል። በግንብ ውስጥ ገብቶ ስንጥቅ ባገኘ ቁጥር እንደሚወጣ ውኃ፣አጋጣሚ በተፈጠረለት ቁጥር ሕዝቡም የእርሱ ባልሆነው መንግሥት ላይ ያምፃል። ሕዝብን በእውነትና በፍቅር እንጂ በማስፈራራትና በመደለል ለመግዛት መሞከር የመንግሥታት የውድቀታቸው መጀመሪያና የዘመናቸው መጨረሻ ነው። በተቃራኒው የማስፈራሪያ መሣሪያና የመደለያ ሀብት የሌላቸው የአካባቢው ሽማግሌዎች ደግሞ፣ በፍቅርና በአብሮነት ሕዝቡን በተለያየ ማኅበራዊ ሕይወት፣ በራሱ ገንዘብና ጉልበት፣ በፈቃዱ ሲያሳትፉት ማየት ተአምር ይሆንብኝ ነበር።

በመንግሥትና በዜጎች መካከል ያለው ግንኙነት እንዲሠምር ፖለቲካዊ ዐቅም ብቻውን በቂ አለመሆኑን፤ የሕዝቡን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የልብ ትርታ ማዳመጥና የመደመርን አንድነታዊና ትስስራዊ ፍልስፍና መጠቀም የላቀ ድርሻ ያለው መሆኑን በጥልቅ የተማርኩት ከዚህ ጊዜ አንሥቶ ነበር። ከጉልበት ይልቅ ፍቅር እጅግ ብርቱ መሆኗን ተምሬ ቢገባኝም፣ ወቅቱ ለእንደዚያ ዓይነቱ ተግባር ፍጹም አመቺ አልነበረም። በዚህች ዓለም ውስጥ የምንኖረው በእንግድነት ነው። ስለዚህ መኩራትና መጀነን ሳይሆን መደጋገፍና መረዳዳት

አለብን። ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ጌጥ፣ አብሮነትም ውበት እንጂ ዕንቅፋት አይደለም የሚለውን በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ኖራ እናቴ አስተምራኛለች። በጽናት ላመኑበት እስከ መጨረሻው መቆም፤ በመካከል በሚገጥሙ ዕንቅፋቶች ተምሮ ማለፍ እንጂ ተስፋ አለመቁረጥ አስገንዝባኛለች። ሊነጋ ሲል የመጨለሙን ተፈጥሯዊ እውነት አጥብቆ መያዝ ከከፋ ውድቀት ሊያድን እንደሚችል ተረድቼ እንዳድግ አድርጋኛለች።

በሻሻ የአብሮነትና የኅብረት ተምሳሌት ናት። ብቸኝነት ብሎ ሕይወት የለም። ገበያውና ዓመት በዓሉ፣ ሰርግና ሐዘኑ፣ ሶላትና ቅዳሴው፣ ምሕላውና ዱአው በአንድነት የሚደምቁበት፣ በግል የማይታሰቡ ጉዳዮች የሚከናወኑበት ቦታ ነው። ልክ እንደ ትምህርት፣ እንደ ዕድር፣ እንደ ዕቁብ ሁሉ፣ ዕርቅና ጠቡ ራሱ ሳይቀር የጋራ ነው። የእናቴ ነጻነት መውደድና ለተገፉ መቆም፣ ከበሻሻ አብሮ የመቆም አንድነት ጋር ተጣምሮ ጠባዬ ሆኖ ያደገ ይመስለኛል።

ተደራጅቶ መታገልና በሰላም ማመፅ፣ ፍጹማዊ አምባገነንነትን ለመጣል የራሱ ድርሻ እንዳለው ምንም ጥርጥር የለውም። ኢትዮጵያውያን አሁን የሚነፍሰውን የነጻነት አየር መተንፈስ የቻሉት በተለያየ መንገድ ተደራጅተው በአምባገነንነት ላይ በማመፃቸው ነው። ከዚህ በኋላ እነዚህ ለትግል ተደራጅተው የነበሩ ኃይሎች፣ ለእኩልነትና ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ዐርበኞች ሆነው ሰላማዊ በሆነ መንገድ አዲሱን የለውጥ _እንቅስቃሴ መቀላቀል ይኖርባቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ለሁላችንም የሚበጅንና ሁላችንም በደማቁ ልንጽፈው የሚገባ መፈክር ‹ዐመፅ መር› ሳይሆን ‹መደመር ተኮር ሊሆን ይገባል።

ከድህነት ማዶ አሻግሮ ወደ ብልጽግና ጎዳና የሚያስገባን ትክክለኛ መንገድ፣ መለያየት ሳይሆን መተባበር ነው፤ መበታተን ሳይሆን መሰባሰብ ነው። ሀገር ለመበልጸግ የሚያስፈልጋት ሥርዓት እንጂ አጉራ ዘለልነትና ትርምስ ሊሆን አይችልም። ወደፊት የሚያራምዱን ደግነትና ርኅሩኅነት ናቸው። የክፋትንና የጭካኔን መንገድ በሚገባ አይተነዋል። ማየት ብቻ ሳይሆን ወደ መቀመቅ ሲከተንም ኖሯል። እንደ ሞኝ የወደቅንበትን መንገድ ስንደግም መኖር የለብንም። ታላቁ ሳይንቲስት እንዳለው “ሞኝ ማለት በተለመደው መንገድ እየሄደ የተለየ ስፍራ ለመድረስ የሚጠብቅ ነውና።”

እስከዛሬ - መከፋፋቱንና መጨካከኑን፣ መገዳደሉንና : መጠፋፋቱን : ሞከረናቸው እንደማያዋጡንና የትም እንደማያደርሱን በሚገባ የተረዳን ይመስለኛል። በሀገራችን ታሪክ የተሻለ የሥልጣኔ፣ የዕድገትና የብልጽግና ዘመናት በጨረፍታም ቢሆን ያየነው በተደመርንባቸው ጊዜያት ነው። ከልዩ ልዩ ቦታ የመጡ ኢትዮጵያውያን ልዩነታቸውን ጌጥ አድርገው፤ ዕውቀትና ጸጋቸውን አዋጥተው፤ ልምድና ባህላቸውን አግባብተው የሠሯቸውን ሥራዎች ናቸው ዛሬም ኀብኝተንም አስኀብኝተንም የምንኮራባቸው በተቃራኒውም የልዩነት ምች ሲመታን፣ የመጠፋፋት ውሽንፍር ሲያለብሰን፣ የጭካኔ መዓት አውርደን የክፋት ሾተልን ስንመዝ ደግሞ በደኅናው ጊዜ የሠራነው ሁሉ እምሽክ እያደረግን አውድመነዋል። ከአሁን በኋላ መለያየትን፣ ጥላቻን፣ ጭካኔንና ጦርነትን የሚሸከም ጫንቃና የሚያራምድ ልቡና ሊኖረን አይችልም፣ አይገባምም።

አምባገነንነትን የተዋጋነውን ያህል፤ አሁን የሚታየውን ሕገ ወጥነትና ጭካኔ አምርረን መዋጋት ከሁላችንም ይጠበቃል። ጭካኔውን የሚፈጽመው ኃይል በእርሱ ላይ ግፍ ሲፈጸምበት የነበረ ኃይል መሆኑ ሕጋዊ አያደርገውም። የሞራል ልዕልናም አይሰጠውም። ጭካኔ በማንም፣ መቼም፣ የትም፣ ይፈጸም፣ ያው ያገጠጠ ክፋትና ያፈጠጠ በደል ነው።

እንዲያውም ነገሩን ከሞራል አንጻር ብናየው፣ ቀድሞ እነዚህን በደሎች ሲታገሉ የነበሩ ኃይሎች የሚፈጽሙት ጭካኔ፣ ክፋትና ግፍ በደለኛነትና ወንጀለኛነቱን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል። ሰላም በሚሰበክበት ፈታኝ ጊዜ ጦርነትና ግጭት በየቦታው መለኮስ፣ ከለውጡ ግልጽ ጠላቶች የከፋ ሰይጣናዊ ድርጊት ነው። ውሎ አድሮም በታሪክ ማኅደር ውስጥ ስምን በጥቁር ቀለም የሚያስጽፍ አስጸያፊ ተግባር ነው።

በጥንታዊ ግሪኮች አፈ ታሪክ የሆራይ እኅትማማቾች በመባል የሚታወቁ ሦስት ሴት አማልክት አሉ። እኅትማማቾቹ በዋናነት ሰላም፣ ሕግና ሥርዓትን እንዲሁም ፍትሕን በማስፈን የሰማይን ደጅ ወይም የሕዝብን በረከት ጠባቂዎች ናቸው ይላሉ። ከሦስቱ እኅትማማቾች ታላቋ ‹አይሪን› ትባል ነበር። ስሟ ሁለት ትርጉም አለው፤ አንደኛው ሰላም ማለት ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ጸደይ ማለት ነው። ሦስቱ እኅትማማቾች የጸደይ ወቅትን የሚገዙ አማልክት ቢሆኑም ወቅቱ የተሰየመው በታላቋ አይሪን ወይም ሰላም ነው። ምክንያቱም ሰላም ከሁሉም ስለምትበልጥ።

የጸደይ ወቅት የሽግግር ወቅት ነው። በግሪክ በርካታ የጦርነት ዘመቻዎች የሚደረጉበት ወቅት ነበር። ጸደይ ከሌሎች ወቅቶች የበለጠ ለጦርነት አመቺ ወቅት ነው ተብሎ ይታመናል። በአፈ ታሪኩ ታላቋ አይሪን የሰላም አምላክና ሰላም ናት። ሌላዋ እኅትዋ ኢዩኖሚያ› ትባላለች። የስሟ ትርጉም ‹ሕግና ሥርዓት› ማለት ነው። በሽግግር ወቅት ከሚያስፈልጉ ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ ሕግና ሥርዓት ነው። ሦስተኛዋ ስሟ ዲይከ› ሲባል ትርጉሙም ‹ፍትሕና ርትዕ› ማለት ነው።

እነዚህ ሦስት እኅትማማቶች በአስቸጋሪው የጸደይ ወቅት የሚገዙ አማልክት ናቸው ተብሎ ይታመን ነበር። የጸደይ ወቅት በአንድ በኩል የጦርነት ዘመቻዎች የሚደረጉበት ወቅት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ልምላሜ የሚጀምርበት የለውጥ ወቅት ነው። ወቅቱ በበጋና በክረምት መካከል ያለ የሽግግር ጊዜ ነው።

ታዲያ እኅትማማቾቹ አማልክት በዚያ አስቸጋሪ ወቅት ሰላምን፣ ሕግንና ሥርዓትን እንዲሁም ፍትሕንና ርትዕን የማስፈን ድርሻ ያላቸው አማልክት ነበሩ።

በዚህ የግሪኮች አፈ ታሪክ ውስጥ የሚገኙት አማልክት የሚወክሉት እውነት አሁን እኛ ባለንበት የሽግግር ወቅት በእጅጉ እንደሚያስፈልጉን አስባለሁ። አማልክቱ ሳይሆኑ ተግባራቸው ነው የሚያስፈልገን። እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ አማልክቱ ሰላምን፣ ሕግንና ሥርዓትን፣ ፍትሕንና ርትዕን በምድራችን የማምጣት ሐላፊነት ልንወስድ ይገባናል።

ያለንበት ወቅት በአንድ በኩል በርካታ የተስፋ ልምላሜዎች የምናይበት ወቅት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በርካታ ፈተናዎች ያሉበት ወቅት ነው። ወቅቱ እንደ ግሪኮቹ ጸደይ የሽግግር ወቅት ነው። የሽግግር ወቅት የተስፋና የሥጋት ጊዜ ነው። ይሄንን ወቅት በስኬት ልናልፈው የምንችለው በሰላም፣ በሕግና በሥርዓት፣ እንዲሁም

በፍትሕና በርትዕ ብቻ ነው። ፈጣሪ፣ ሕዝቡና የሀገሪቱ ሕግ እስከፈቀደ ድረስ በሚቆየው በዚህ ታሪካዊ የአመራር ዘመኔ፣ ለሀገራችንና ለሕዝባችን ሰላምና ፍቅር እንዲበዛ እሠራለሁ። እስካሁን በተግባር ሆኖ የማየው ግን መለያየትና መናቆር፣ መወነጃጀልና አለመተማመን ነው። ይህ መለያየትና ጥላቻ መነሻው ከሃይማኖት ልዩነት የሚመነጭ ተፈጥሯዊ ልዩነት ነው ብዬ እንዳላስብ የበቀልኩበትን ቤተሰባዊ እውነታ የሚደግፍ ሆኖ አላገኘውም። በሕዝቦች መካከል ያለን ብሔርና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ነው ብዬ እንዳላምንም እይታ ታፈርስብኛለች። የችግሩ ሰንኮፍና መርዝ ያደግኩባት በሻሻ ይሄንን የሚመነጨው ሊስተካከል ከሚገባው የመንግሥትና የሕዝብ የግንኙነት መስመር ላይ ነው ወደሚል ድምዳሜ ደርሻለሁ።

የሕዝብንና የመንግሥትን ግንኙነት የመሪና የተመሪ ማድረግ አለብን። በመረጥሸው ዳኛ ትረች፣ በቆረጥሸው ዱላ ትመች› እንደሚባለው መረታትም መቀጣትም በመረጠው መንግሥት ብቻ መሆን አለበት። ያ ከሆነ ራስን በራስ እንደመቆንጠጥ ነውና አያምም።

ያልወደድኩት ከሚያጎርሰኝ፣ የወደድኩት ይንከሰኝ› የሚል ነው ሕዝባችን። ራሱ ለመረጠው ነገር ያለውን ቦታ ሲገልጥ። ሥርዓታችንን ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ከቻልን ሌሎች ችግሮች በሁለቱ ይፈታሉ። በእኔ የአመራር ዘመን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለፍትሕና ለዴሞክራሲ የማይናወጥ መሠረት በመጣል፣ ለቀጣይ ትውልድና መሪዎች ትልሙን የማሳየት ሐላፊነት የተጫነብኝ ይመስለኛል።

ሁላችንም የቃልና የተግባራችን ውጤቶች ነን። ያለፍንበትና ያለፈብን ዘመን ማኅተምና አሻራ ተደርገን ልንወሰድም እንችላለን። በእያንዳንዳችን ሕይወት ለሚንጸባረቀው መልካምና ክፉ ምግባር፣ ምንጩ ይዘን የተወለድነው ጎሳና ቀለም ወይም በግል ምርጫችንም ይሁን በመወለድ አግኝተን እየተከተልነው ያለው እምነትና ሃይማኖት አይደለም። ከልጅነት እስከ ዕውቀት፣ ከአፍ መፍታት እስከ ከሽበት የተመገብነው ቃል፣ የሰበሰብነው ልምድ፣ ከአካባቢያችን የወሰድነው ልማድና ወግ፣ ከእነዚህም ተነሥተን የተከተልነው መንገድ እንጂ።

እዚህ ላይ የአንድ ብልህ አባትን ምክር ማንሣቱ ተገቢ ነው። አባት ለልጁ “ልጄ በውስጥህ ሁለት አውሬዎች አሉ። አንደኛው የክፋት አውሬ ሲሆን፤ መገለጫውም ምቀኝነት፣ ጥላቻ፣ ተንኮል፣ ቂም በቀል፣ ስግብግብነትና ግልፍተኝነት ነው። ሁለተኛው ደግሞ መልካም እንስሳ ነው። መገለጫውም መልካምነት፣ ለጋስነት፣ ፍቅር፣ የዋህነት፣ ይቅር ባይነት፣ ቸርነትና ታጋሽነት ነው። ታዲያ ልጄ እነዚህ አውሬዎች ሁሌም እንደተፋለሙና እንደተጣሉ የሚኖሩ ናቸው። በእኔና በአንተ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ሰዎች ውስጥ ያሉ ናቸው” ይሉታል።

ልጅም በአባቱ ገለጻ በመደነቅ “ታዲያ በመጨረሻ ማን ያሸንፋል፣ አባባ?” ሲል ይጠይቃል። አባትም የልጃቸውን ፀጉር እያሻሹ “ልጄ! የሚያሸንፈውማ አንተ አብዝተህ የመገብከው አውሬ ነው” አሉት ይባላል።

ያለንበትን ሁኔታ ለመለወጥ ቀላል ባይሆንም አማራጭ እንደሌለን ማሰብ ግን የለብንም። የቀድሞውን የሚያስረሳና የሚያስጥለንን አዲስ ተስፋ ለመቀበልና አዲስ ልምድ ለማግኘት ፈቃደኛ ብንሆን፣ ከፊታችን ባለው ዘመን አዲስ ሕዝብና አዲስ ሀገር ለመፍጠር ከዚህ የተሻለ ጊዜ የምናገኝ አይመስለኝም። የተበላሸው

ታችኛው መዋቅራችን አይደለም። "የዓሣ ግማቱ ከወደ አናቱ" እንዲሉ አበው፣ የተበላሸው ላይኛው መዋቅራችን ነው። ይህ ደግሞ ባለፉት ሃምሣና ስድሳ ዓመታት በተቀበልናቸው ትርዕክቶች በተሰበኩልን ርዕዮተ ዓለሞች በተነቀነቀልን ሐሳቦች፣ በነፈሱብን የውዥንብር ነፋሶች ምክንያት የተገነባ ነው። ችግራችን ተፈጥሯችን፣ ባህላችን፣ ቋንቋችንና ብሔራችን ያመጣው አይደለም። ያ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር ለነዚህ ሁሉ ሺሕ ዓመታት ጸንታ አትኖርም ነበር። ሀገራችንን መሠረት ሆኖ የተሸከማትና ያኖራት የታችኛው መዋቅሯ ነው። እኔም ከልጅነቴ በበሻሻ ሳየው የኖርኩት ታችኛውን መዋቅራችንን ነው። ላይኛው መዋቅራችን እንደ ተደራቢ በግድግዳው ላይ የተለሰነ ነው። በትምህርት፣ በውይይት፣ በተሻለ የፖለቲካ ሥርዓት፣ በተሻለ ሐሳብና ትርክት ልንቀይረው ግን እንችላለን።

በመሆኑም፤ አዲሱ የለውጥ ርምጃ ቀጣይ ጉዟችን ከዚህ ቀደም ባልተጓዝንበት አዲስ መንገድ፤ በሰላም በይቅርታና በፍቅር፣ በዕርቅና በመደመር፤ በተቃኘ ጠንካራ ዕሴት ሊመሠረት ይገባል። የእኔን የመደመር እሳቤ መነሻ ሆነው የፈጠሩ ሁለት ምንጮች ናቸው። የመጀመሪያው በልጅነቴ ከእናቴ የወረስኩት የማይናወጥ ራእይና የመሪነት አደራ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በትንሿ ኢትዮጵያ በበሻሻ ከልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች ጋር የኖርኩት ጣፋጭ ማኅበራዊ ኑሮ ነው። እነዚህ ሁለቱ ዛሬ ያለኝን ጥልቅና ጥብቅ የመደመር ፍልስፍና የፈጠሩ ቋሚና ማገር፣ ድርና ማግ ናቸው። መደመር ለእኔ የአንድ እስትንፋስ ነው። ሰሞን መፈክር ሳይሆን የሕይወት ዘመኔ ፍልስፍናና በደሜ ውስጥ የተሠራጨ የሕይወቴ አስትንፋስ ነው።

# ክፍል ሁለት

## ዕርቅ እና መደመር

# ምዕራፍ ስድስት

## ቁስላቸውን ያደረቁ ሀገራት

"I believe that we can heal Rwanda - and our world - by healing one heart at a time. "

“አንዲት ልብ በአንድ ጊዜ መፈወስ ከቻልን፣ ሩዋንዳን ብሎም መላውን ዓለም መፈወስ እንችላለን ብዬ አምናለሁ።”

~ ኢማኩሌ ኢሊባጊዛ

## *የይቅርታ ድልድይ*

የአንድ ሀገር ሕዝቦች በሁለት ወንድማማቾች ይመስላሉ። በወንድማማቾች መካከል ብዙ የፍቅር፣ የመረዳዳትና የደስታ ጊዜያት የመኖራቸውን ያህል ጠብ አጫሪ አጋጣሚዎችም ይፈጠራሉ። በእርግጥ የሚበዛው የፍቅርና የመተሳሰብ ጊዜ ነው። ዳሩ ግን አንዴ ጸብ ሲፈጠር እነዚያን የፍቅርና የመተሳሰብ ዘመኖች እንዳናይ የሚጋርድ ስስ መጋረጃ ይዘረጋል። ያንን መጋረጃ የመቅደድና የበደልን ቁስል የማከም ዐቅም ያለውም ይቅርታና ይቅርታ ብቻ ነው።

ከዚህ አኳያ አንድ የማስታውሰው የሰማሁት ታሪክ አለ። ዘመናትን በፍቅር ያሳለፉ ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። ቤተሰብ መሥርተው የሚኖሩትም፣ መሬት ገዝተው የሚያርሱትም አጠገብ ለአጠገብ ነው። የአንዱን ጉድለት ሌላኛው እየሞላ፣ አንዱ ለሌላው ጉልበት እየሆነ ዓመታትን በደስታና በመተሳሰብ ዘልቀው እያለ፤ አንድ ዕለት የማያግባባቸው ንግግር በመካከላቸው ተፈጠረ። ነገሩ ቀላል ነበር፤ በማንኛውም ሰው መካከል ሊያጋጥም የሚችል ተራ ጉዳይ። ዳሩ ግን ወንድማማቾቹ ሳያስቡት ንግግራቸው ወደ ጭቅጭቅ፣ ጭቅጭቃቸው ወደ እልህ ተቀይሮ እላፊ ቃላትን መወራወር ጀመሩ። ይሄም ሳይበቃ ቡጢ ተቃመሱ።

“ነገሩ ነው እንጂ ጩቤ ሰው አይጎዳም” ይላል የሀገራችን ሰው። እነዚያ ወንድማማቾች ሲጠየቁ ሁለቱም የሚመልሱት ከቡጢው ይልቅ ንግግራቸው እንደጎዳቸው ነበር።

ከኩርፊያቸው ዕለታት በአንዱ ጠዋቱን የታላቅየውን የግቢ በር አንድ ሽማግሌ አናጺ ያንኳኩ ጀመር። በሩን ከፍቶ ምን እንደፈለጉ ሲጠይቃቸው፣

“ምናልባት ሥራ ከሰጡኝ ብዬ ነው ጌታዬ። አናጺ ነኝ፤ የተሰበሩ ወንበሮችን፣ ያዘመሙ ግድዳዎችን፣ የተፍረከረኩ አጥሮችን እጠግናለሁ። በዋጋ በኩል አያስቡ፣ ብዙ አላስከፍልዎትም!” ሲሉ ሽማግሌው ተማጽኖ አዘል መልስ ሰጡ። አናጺው ሽማግሌ ቢሆኑም አቋማቸው ጠንካራ እንደሆኑ ይናገራል። የሥራ መሣሪያዎች የተቆለፉበት ሳጥናቸውን ያንጠለጠሉበት ቀኝ እጃቸው የፈርጣማ ጎረምሳ እንጂ የሽማግሌ አይመስልም።

ላፍታ ሲያስተውላቸው ከቆየ በኋላ “መልካም፣ አንድ የሚሠራ ሥራ አለ። እዚያ የሚታየው ማሳ የታናሽ ወንድሜ ነው። በድሎኝ ተጣልተናል። በማሳችን መካከለ ያለው ቦታ አረንጓዴ ነበር። በደሉ አልበቃ ብሎት ውኃ መውረጃ ቦዩን አቅጣጫ ስለቀየረው አረንጓዴ የነበረውን ያንን ቦታ እንደሚያዩት ደረቅ አድርጎታል። እንግዲህ እሱ ድንበር አይደል የፈለገው? እዚያ ቦታ ላይ ሄደው የደረቁትን ቁጥቋጦዎች ከርክመው አጥር ያቆሙልኛል። ዳግም እሱን ማየት አልፈልግም። ከጥሩ ጉርሻ ጋር እከፍልዎታለሁ፤ ገበያ ደርሼ እስክመጣ ጨርሰው ይጠብቁኝ” አላቸውና ጥሏቸው ሄደ። ከገበያ መልስ ወደ ማሳው ጎራ ሲል የሚያየውን አላመነም። በአጥሩ ፋንታ አናጺው ድልድይ ገንብተው ነበር የጠበቁት። በእርግጥ ድልድዩ እጅግ በጥበብ የተሠራ የሚያምር ድልድይ ነው። ወደ ድልድዩ እየቀረበ ሲሄድ ከድልድዩ በሌላኛው ጫፍ ታናሽ ወንድሙ አሻግሮ እየተመለከተው እንደሆነ ተረዳ።

ሁለቱ ወንድማማቾች ሳያስቡት እግራቸው እየመራቸው ድልድዩ መሐል ደርሰዋል። ታናሽዬው እጁን ከፍቶ ወንድሙን አቀፈው፤ እንባ በጉንጩ ላይ እየወረደ “ወንድሜ ይቅር በለኝ! እኔ የክፋት ድንበር ሳበጅ አንተ የፍቅር ድልድይ ገነባህ!" አለው። ታላቅዬው ወንድሙ የተናገረውን ሰምቶ እየተደነቀ ምንም ትንፍሽ ሳይል አጥብቆ ታናሹን አቀፈው። መሽቶ አናጺው ሽማግሌ ተሰናብተዋቸው ሊሄዱ ሲነሡ ወንድማማቾቹ “ቆይ አይሄዱም" ብለው እጃቸውን ያዟቸው። እየተሽቀዳደሙ “እኔ ጋር ብዙ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ሥራዎች አሉ፤ እነሱን እየሠሩ ለጥቂት ቀናት ይቆዩ?!" አሉዋቸው። ሽማግሌው አናጺ ግን በጄ የሚሉ አልሆነም።

ልጆቼ እኔም ትንሽ ብቆይ ደስ ባለኝ ነበር። ዳሩ ግን መገንባት ያሉብኝ ብዙ ድልድዮችና ስብራቶች በሌላ ስፍራ ይጠብቁኛል” ብለው የሕንጻ መሣሪያ የያዘች ሳጥናቸውን አንጠልጥለው ወጡ።

በአንድ ቤተሰብ ልጆች መካከል የሚፈጠር ቅያሜንም ይሁን በአንድ ሀገር ሕዝቦች መካከል የሚፈጠር መቋሰልን የሚያሽረው ነገር፣ ደረጃው ይለያይ ይሆናል እንጂ አንድ ነው፤ እሱም ዕርቅና ይቅርታ ይባላል። በዓለማችን ላይ በብዙ ሀገራት፣ ሕዝቦች በመበዳደል መንገድ ውስጥ አልፈው የሚያስፈራ ግንብ በመካከላቸው ገንብተው አስቀያሚ ዘመናትን ለማሳለፍ የተገደዱ አሉ። ከእነዚህ መካከል የበደልን ቁስል አከመው የማዳንን እልህ አስጨራሽ መንገድ በብልኀት የተወጡ አሉ። ሰላምና ይቅር መባባልን በማስቀደም የጠብን ገደል የናዱ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። የቁርሾን ሸለቆ፣ የመለያየትንም ባሕር የተሻገሩ ሕዝቦች በዓለማችን ሞልተዋል። እኛ ኢትዮጵያውያን ከእነሱ ብዙ ልንማር ይገባል። ትምህርት ሰጭ የሆነ የዕርቅና የይቅርታ እርምጃዎችን ለመፈጸም የቻሉ ብዙ ሀገራት ቢኖሩም ለጊዜው ሦስቱን መርጠን በአጭሩ እንይ።

## *ደቡብ አፍሪካ*

ሀገር እንደ ሀገር፣ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር እርስ በእርሱ ይቅር ተባብሎ አዲስ መንገድ ከጀመረባቸው ሀገሮች

አንዷ ደቡብ አፍሪካ ናት። በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ የአፓርታይድ መንግሥት የመጨረሻው ፕሬዚዳንት የነበሩት ኤፍ ደብሊው ዴክላርክ ሀገሪቱን እያሰመጣት ያለው የፖለቲካ ቀውስና ዐመፅ በጥልቅ አሳሰባቸው።

ችግሩን ለማርገብ ይቻል ዘንድ ተቃዋሚ ድርጅቶችንና ሌሎችንም የነጻነት እንቅስቃሴዎችን ሕጋዊ ሰውነት መስጠት ነበረባቸው። በሽብርተኞች ጥቁር መዝገብ ውስጥ ተራ ቁጥር አንድ ሆኖ የተከተበው የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ በዚያ ቀውጢ ጊዜ ሕጋዊነትን ተላበሰ። ዓለም በአድናቆት እጅ የነሣቸው የኮንግረሱ መሪ ኔልሰን ማንዴላም ከነጓዶቻቸው በድል ከእስር ተለቀቁ። በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ ያሉ ሌሎች ታጋዮችም ከሽብርተኝነት መዝገብ ተፍቀው በሰላም ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። በዘረኛው የዴክላርክ መንግሥትና በአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ መካከል ስለሽግግሩ ድርድር ሲደረግ፣ በጭንቅ የታሰበበት አንዱ ቁልፍ ጉዳይ ፍቅርንና ፍትሕን አቻችሎ የመጓዙ ጥያቄ ነበር።

ወራሪውና ዘረኛው የነጮች መንግሥት ባለሀገሮቹን ጥቁሮች እንደ ቆሻሻ እየተጠየፈ፣ ከነጮችና ከክልሶች ጋር በአጥር ተለይተው እንዲኖሩ እያደረገ፣ ሌሎች በሚበሉበት እንዳይበሉ፣ በሚጠጡበት እንዳይጠጡ፣ ከሌሎች ጋር በፍቅር እንዳይጎዳኙና ትዳር እንዳይመሠርቱ አድርጎ ከ3oo ዓመታት ለሚበልጥ ጊዜ ፍዳቸውን አሳይቷቸዋል።

እኤአ በ1949 የተለያዩ ዘሮች እንዳይጋቡ በሚከለክለው ሕግ የተጀመረው አፓርታይድን ሕጋዊ የማድረግ አካሄድ በ1950 የሀገሪቱን ሕዝቦች ጥቁር፣ ነጭ፣ ከለርድ እና ሕንዳዊ ብሎ ለአራት በመክፈል አጠናከረው። ሕጉን ተላልፈው ሲገኙም እያሰረና እያሠቃየ የግፍ ግፍ ፈጽሟል። ከ1950 እስከ 1983 ድረስ ብቻ 3.5 ሚሊዮን ደቡብ አፍሪካውያን ጥቁሮች ከነባር መንደራቸው ተገፍተው ለጥቁሮች በተከለለው ማጎሪያ መንደር ገብተዋል። በዚያ መብቶቻቸውም ተገድቧል። ይህ የግፍ ሥርዓት የተዘረጋው ከአውሮፓ በመጡ ነጮች ሲሆን፣ ገፈት ቀማሾቹ ደግሞ ብዙኃኑ ጥቁሮች ነበሩ።

በገዛ ሀገራቸው ተንቀውና ተዋርደው እንደ ትቢያ መሬት የተጣሉት ጥቁሮች፣ ከ3oo ዓመታት በላይ በግፍ ከተጫወቱባቸው ገዥዎቻቸው ጋር እንዴት ነው በሰላም ለመኖር የሚችሉት? የሽግግሩ ዘመን አንዱ ከባድ ጥያቄ ይህ ነበር። ሥልጣን ለመጋራት የወሰኑት የሽግግሩ ዘመን ተደራዳሪዎች ሌላም ቁልፍ ስምምነት ላይ ደረሱ። በዘረኛው የነጮች ዘመነ መንግሥት የደረሱ በደሎችን የሚያጣራ የእውነትና የዕርቅ ኮሚሽን እንዲቋቋም ተወሰነ።

***እ.ኢ.አ በ1995 የተቋቋመው የዚህ የእውነትና የዕርቅ ኮሚሽን ዋና ተግባራት:***

1 በዘረኛው የነጮች አገዛዝ ዘመን በሰብአዊ መብት ላይ የደረሱ ግፎችን መመርመር፤

2. ተጎጂዎችን መካስ እና ዳግም ማቋቋም፤

3. የይቅርታ አቤቱታዎችን መመልከት እና ማጽደቅ ነበሩ።

“ከትናንቱ ሕመማችን መፈወስ” የሚል መፈክር አንግቦ ትልልቅ ባለ ሥልጣኖችን ሳይቀር በአደባባይ መረመረ። ሁኔታውን በመላው ዓለም እጅግ ብዙ ሕዝብ ሲከታተለው ነበር። ኮሚሽኑ የሥራውን የመጨረሻ ሪፖርት እስካቀረበበት እስከ 2003 (እ.አ.አ.) ድረስ ባለው ጊዜ ከሰባት ሺህ የሚልቁ የምሕረት ማመልከቻዎችን ተቀብሎ፣ ለአንድ ሺሕ አምስት መቶ አመልካቾች ምሕረት ሰጥቷል። አምስት ሺሕ ለሚበልጡ አመልካቾች ምሕረት ከልክሏል። ከ22 ሺሕ ከሚበልጡ ተበዳዮች አቤቱታ ተቀብሎ ፖሊሶችን፣ የጦር አዛዦችንና የፖለቲካ መሪዎችን ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ በዓለም ሚዲያ ፊት መመርመሩን ቀጠለ።

ፈጸሙ የተባለውን ግድያ፣ ማሰቃየት (ቶርቸር)፣ አፈና፣ ስወራና የመሳሰሉትን በዝርዝር መርምሯል። ይህ የትናንቱን ሕመም የመፈወስ ታላቅ ተጋድሎ የመጨረሻውን ሪፖርት በማውጣት ብቻ አልተደመደመም። ከደቡብ አፍሪካውያንም ባለፈ የሌላውም ዓለም ሕዝብ ከፈውሱ ታሪክ እንዲማር፣ ተመራማሪዎችም ጉዳዩን በስፋት ማጥናት እንዲችሉ በሩን ክፍት አደረገ። በጊዜው ጥቅም ላይ የዋሉ የምርመራ መዝገቦች፣ ውሳኔዎች፣ የድምፅና የቪዲዮ ሪፖርቶች የተካተቱበት አንድ የመረጃ ክምችት ኢንተርኔት ላይ ለተመልካችና ለአንባቢ ክፍት ተደርጓል። የተከፈለበት ዋጋ ታላቅ ቢሆንም የተገኘው ውጤትም ድንቅ ነበር።

በ2009 ላይ የወጣው ኢንቪክተስ የተሰኘው የማንዴላንና የጓዶቹን ትግል የሚተርከው ድንቅ ፊልም ላይ፣ ማንዴላ በገጸ ባሕሪው ሞርጋን ፍሪማን በኩል ስለይቅር ባይነት እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፤
"ይቅር ባይነት ከዚሁ ነው መጀመር ያለበት። ይቅር ባይነት ነፍስን ነጻ ያወጣል። ፍርሃትን ያሸንፋል። ለዚህም ነው ትልቅ መሣሪያ የሆነው። ያለፈው አልፏል፤ ወደፊት እንመልከት።"

ማንዴላ በራሳቸው አንደበት ስለ እስር ቤት ሥቃያቸውና ስለ ቀጣይ ሕይወታቸው ሲናገሩ "የእስር ቤቱን በር አልፌ ወደ ዋናው መውጫና ወደ ነጻነት ምድር ስራመድ አንድ የተገነዘብኩት ነገር፣ ምሬቴንና ጥላቻዬን እዚሁ ጥዬው ካልወጣሁ ከእስር አለመፈታቴን ማወቄ ነበር" ማለታቸው ይታወቃል።

## *ካናዳ*

ካለፈ ሕመም የመፈወስ እንቅስቃሴን እንደ ደቡብ አፍሪካ ሁሉ ሰሜን አሜሪካዊቱ ሀገር ካናዳም አስተናግዳለች። የዕርቁ መነሻ ልክ እንደ ደቡብ አፍሪካው ሁሉ ለረጅም ዓመታት በሰው ልጆች ላይ የደረሰ ግፍና መከራ ነው። ካናዳ፣ እንደ አሜሪካና አውስትራልያ ሁሉ የጥንታዊ ነባር ሕዝቦች መኖሪያ ነበረች። በነጭ ሰፋሪዎች በጉልበትና በጦርነት ከተያዘች በኋላ ግን ነባሩ ሕዝብ በብዛት አልቆና ተሰዶ፣ የተረፈውም ተንቆና ተዋርዶ የኖረባት የግፍ ታሪክ ያላት ሀገር ነበረች። ነባሩን ሕዝብ ወርረው በማሸነፍ ካናዳን የተቆጣጠሩት ነጮች ናቸው። ወራሪ ኃይል ከራሱ ሕዝብ ውጭ ሌላ ሕዝብ፣ ከራሱ ሃይማኖት ውጭ ሌላ ሃይማኖት ያለ

አይመስለውም። ያለውንም እስኪያጠፋ ድረስ ዕረፍት አይኖረውም። በካናዳ የደረሰውም ይሄው ነበር።

ዘረኞቹ ነጮች የነባሩን ሕዝብ ባህልና ሃይማኖት ለማጥፋትና ሰዎቹንም እነርሱን የሚመስሉ አድርገው ለመለወጥ በቅድሚያ ሕፃኖቻቸውን ወደ ትምህርት ቤቶቻቸው ለማስገባት ወሰኑ። ያደጉትን ለመለወጥ ከመታገል ሕፃናቱን ከለጋ ዕድሜያቸው ጀምሮ በመኮትኮት ካናዳን በጥቂት ጊዜ ውስጥ የአንድ ሕዝብ፣ የአንድ ቋንቋና የአንድ ሃይማኖት ሀገር ማድረግ እንደሚቻል አመኑ። በመንግሥት ገንዘብ የሚንቀሳቀሱና በቤተ ክርስቲያኖች የሚተዳደሩ ትምህርት ቤቶች በየቦታው ተቋቋሙ። የነባሩን ሕዝብ ልጆች ያለ ወላጆቻቸው ፈቃድ ከየቤቱ እየወሰዱ ትምህርት አስጀመሯቸው። ለዘመቻቸው መሳካት እጅግ በመጠበብ፣ ሰላዮችን ጭምር ወደ የመንደሮቹ በመላክ፣ ለዘመቻው ያልተመለመለና ከመጠመቅ ያመለጠ ሕፃን እንዳይኖር ብዙ ደከሙ።

ዘመቻው እንደተጀመረ አካባቢ ብቻ 69 እንዲህ ዓይነት አዳሪ ትምህርት ቤቶች በካናዳ የተቋቋሙ ሲሆን፤ ከአንድ ሺሕ በላይ ሕፃናትም ከወላጆቻቸው ተነጥቀው በእነዚህ ተቋሞች ውስጥ ይማሩ ነበር። ሕፃናቱ በእንግሊዝኛ ወይም በፈረንሳይኛ ካልሆነ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዳይናገሩ ባህላቸውንም እንዳያንጸባርቁ ይገደዱ ነበር። ግዴታውን የጣለ ከፍተኛ ቅጣት ይደርስበታል።

የክፋታቸው ክፋት፣ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማሩ ወንድምና እኅት እንኳ እንዲገናኙ አይፈቀድም ነበር። ሴቶችና ወንዶች ተነጣጥለው ነበር የሚማሩት። ግፍን በግፍ የሚያስተምሩ እነዚህ አዳሪ ትምህርት ቤቶች በሕግ እስከታገዱበት ጊዜ ድረስ፣ ከ 1876 እስከ 1996 ባሉት 120 ዓመታት ውስጥ፣ ወደ 50 ሺሕ የተጠጉ ሕፃናት እንዲህ ዓይነት አዋራጅ ሥቃይ ደርሶባቸዋል። ወደ ስድስት ሺሕ የሚደርሱ ሕፃናት ለሞት ተዳርገዋል። ሴቶች ተደፍረዋል፣ ታፍነው ተወስደዋል። ብዙዎቹ ተደብድበዋል፤ አካላቸውን አጥተዋል።

በ2007 እኤአ ይህ የግፍና የዐመፅ ታሪክ መለወጥ ጀመረ። አዳሪ ትምህርት ቤቶች በነባሩ ሕዝብ ላይ ላደረሱት በደል ሕጋዊ ድምዳሜ የሚሰጥ ስምምነት በይፋ ተዘጋጅቶ ተፈረመ። በእነዚያ የጨለማ ዘመናት የደረሰውን ግፍና በደል በዝርዝር አጥንቶ ሪፖርት የሚያቀርብና ሕዝቡንና ሀገሪቱን በብሔራዊ ይቅርታ ወደፊት የሚያሻግር የእውነትና የዕርቅ ኮሚሽን በካናዳ ተቋቋመ። ልክ እንደ ደቡብ አፍሪካው ኮሚሽን፣ ባለሥልጣኖችንና የትምህርት ቤቶቹ አስተዳዳሪዎች የነበሩትን ቄሶች እንዲሁም ሌሎች ሐላፊዎችን በአደባባይ መረመረ። የበዳይና ተበዳይን ቃል እየተቀበለ ሥራ ላይ በቆየባቸው ስድስት ዓመታት ውስጥ የ6.500 ምስክሮችን ቃል ተቀብሏል። ሕዝቡ ካለፈ ታሪኩ እንዲማርና ከሕመሙ እንዲፈወስ ሰባት ብሔራዊ ትዕይንቶችን በተለያዩ የካናዳ ግዛቶች አደራጅቷል። የካናዳ መንግሥት የምርመራ ሥራውን ለማገዝ ከ5 ሚሊዮን የሚልቁ መዝገቦችን አስረክቧል። ለኮሚሽኑ ሥራ የሚሆን 72 ሚሊዮን ዶላር በጀት መድቧል።
በመጨረሻም በ2015 ኢ.አ.አ የካናዳው የእውነትና እርቅ ኮሚሽን ስድስት ቅፆች ያሉትን የማጠቃለያ ሪፖርት ይፋ አደረገ።ነባሩ ህዝብ ለከፍትኛ ትምህርት የሚያገኘው ዕድል እንዲሰፋ፡ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት እንዲሻሻልና ሌሎችም 94 የሚደርሱ የ መፍትሔ ርምጃዎችን ለሕዝብና ለመንግሥት አቀረበ። የካናዳው

ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ አጠቃላይ ሪፖርቱን በካናዳው ሕዝብ ስም ሙሉ ለሙሉ ተቀበሉ፡፡ በምክር ቤት ቀርበውም ባለፉት መንግሥታት ለተፈጸሙት በደሎችንና ደባዎች ሁሉ በይፋ ይቅርታ ጠየቁ፡፡ ኮሚሽኑ ያቀረባቸውን የመፍትሔ ርምጃዎች ተግባራዊ ለማድረግ መንግስታቸው ፍቃደኛ መሆኑን በመግለፅ ተጎጂዎችን ሁሉ ይቅርታ ጠየቁ፡፡ዕርቁ ዘላቂ እንዲሆንም ከነባር ሕዝቦች መሪዎች ጋር በየዓመቱ እየተገናኙ በሕዝቦች ሰላማዊ ግንኙነት ላይ ውይይት እንደሚያደርጉ ቃል ገቡ፡፡

የክርስትና ሃይማኖት መሪዎችም፡አንዱ አንዱን እየተከተለ ፡ባፈው ለደረሰው ግፍ እና ሰቆቃ ነባሩን የካናዳ ሕዝብ  በሃየወማኖት ስም ለተፈፀመው ግፍና በደል በይፋ ይቅርታ ጠየቁ፡፡ በደቡብ አፍሪካ እንደተደረገው ሁሉ ዓመታትን የፈጀው የምርመራ ኮሚሽኑ ሥራ የማጠቃለያ ሪፖርት በማውጣት ብቻ አልተደመደመም ፡፡ የካናዳ ሕዝብና ሌሎችም ተመራማሪዎች ከተፈፀመው ዘመናትን ያስቆጠረ የግፍ ታሪክና ከተካሄደው የይቅርታ ሂደት መማሩን እንዲቀጥል ፣ የተሰበሰበውን መረጃዎችና እማኞች ሁሉ ለሕዝብ ክፍት በሆነ መንገድ እንዲቀመጥ ተደርጎል፡፡

## ሩዋንዳ

በይቅርታ የመሻገርን ጥበብ ለዓለም ያሳየች ሌላዋ አፍሪካዊት ሀገር ሩዋንዳ ናት፡፡ሩዋንዳ እ。 አ。 አበ1994 በተደረገ ፍጅት ወደ አንድ ሚሊዩን የሚጠጉ ዜጎች ተጨፍጭፈውባታል፡፡እንግሊዝ/አሜሪካዊው ደራሲ ክርስቶፈር ሂችንስበግል ታሪክ ማስታወሻው ላይ ከፍጅቱ የተረፈች አንዲት ሩዋንዳዊት አግኝቶ እንዳወራ ይናገራል፡፡

በዚህ ዓለም ላይ እሷን የሚያውቃት አንድም ሰው እንዳልተረፈ እንደነገረችው ሂችንስ ይገልጻል፡፡ አንድም ሰው፡፡ ልጅነቷን የሚያውቅ፣ አብሯት የተጫወተ፣ በፍቅር አብሯት የኖረ፣ ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ የት/ቤት ጓደኛ ማንም እሷን የሚያውቅ ሰው የለም፡፡ ምንም ሆናለች፡፡ የኖረችው ሕይወት ሁሉ ከባዶ ሊጀምር ነው፡፡

ይሄ ታሪክ ሁሌም ውስጤን ሰርስሮ ገብቶ አጥንቴን ሲፍቀው ይሰማኛል፡፡ በዓለም ላይ ምንም የሚያውቀን ሰው ሳይኖር እንዴት መኖር እንደሚቻል ራሱ ለማሰብ ይከብዳል፡፡ “ሕይወቷ ተርፏል፤ ነገር ግን የዕለት ማስታዎሻዋና ካላንደሯ ባዶ ነው” ይላል ሂችንስ በሐዘን፡፡ በሀገሪቷ ከሚኖሩ ሁለት ዋና ዋና ጎሳዎች ውስጥ የሚበዙት ሁቱዎች ሲሆኑ በቁጥር አነስተኛዎቹ ደግሞ ቱትሲዎች ናቸው፡፡

ቤልጂየምንና ጀርመንን የመሰሉ ቅኝ ገዥዎች መጥተው፣ ለመግዛት እንዲመቻቸው ከፋፍለው እና አቀያይመው እስኪለያይዋቸው ድረስ፣ በአንድ ላይ በፍቅር የሚኖሩ ሕዝቦች ነበሩ፡፡ አንድ ሃይማኖትና አንድ ባህል ያላቸው፤ አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡

በፍጅቱ ዋዜማ ላይ ቤልጅየሞቹ ከፋፍሎ ለመግዛት ያመቻቸው ዘንድ ቱትሲዎችን በኢኮኖሚ ማጠናከራቸውና ቱትሲዎቹ በሀገሪቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የበላይነት እየያዙ መምጣታቸው፣ በሁቱዎቹ ዘንድ በብሶት

ይነገር ነበር። ይሄን ብሶትም በሚዲያ በማራገብና በተለይም በቱትሲዎች ላይ ጥላቻ እንዲያድግ ከፍተኛ የሆነ ቅስቀሳና ማነወር ይካሄድ ነበር። እ.አ.አ በ1994 ሚያዝያ ውስጥ የሁቱ ጎሳ አባል የሆኑት የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ዡቬናል ሃብያሪማና አውሮፕላናቸው ተመትቶ ተገደሉ።

አውሮፕላኑን ያጋዩት ቱትሲዎች ናቸው ተብሎ በስፋት ተወራ። ሁቱዎች ይሄንን ለመበቀል ገጀራቸውን እየወዘወዙ አደባባይ ወጡ። የገሃነም ቀናት ተብለው በሚጠሩት በተከታዮቹ ሦስት ወራት ውስጥ ወደ ስምንት መቶ ሺሕ የሚጠጉ ቱትሲዎችና ከእነርሱ ወግናችኋል የተባሉ ሁቱዎች ያለምሕረት ተጨፈጨፉ። በዚህ አሰቃቂ ፍጅት የሀገሪቷ 20 ከመቶ ሕዝብ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሲያልቅ፣ ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ ደግሞ ነፍሱን ለማትረፍ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ተሰደደ። በነዚያ ቀናት 250,0oo ሴቶች ተደፍረዋል። የሀገሪቱ የልማት አውታሮች ፈራርሰዋል። ሀገሪቱም ወደ እርስ በርስ ጦርነት ተማግዳለች። በትግሉ ሂደት ጨፍጫፊዎቹ ሁቱዎች ተሸንፈው ከሀገር ተሰደዱ። በተራቸው ተጨፍጫፊዎቹና ተበዳዮቹ ቱትሲዎች ሥልጣን ያዙ። በዚህ ጊዜ ሀገርን መልሶ ከመገንባቱ ጎን ለጎን ሩዋንዳ የተደቀነባት ሌላው ትልቁ ጉዳይ ወንጀለኞቹ እንዴት ይዳኙ የሚለው ጥያቄ ነበር።

እንደ አብዛኞቹ ድኅረ እልቂት ሀገራት ሩዋንዳም በመጀመሪያ የታያት ተጠርጣሪዎችን እየጎተቱ እስር ቤት መክተትና ወንጀለኞችን መቅጣት ብቻ ነበር። ሩዋንዳ አያሌ በፍጅቱ የተጠረጠሩ ሰዎችን አሰረች። 22 ሰዎችን የዘር ማጥፋት ቀንደኛ ወንጀለኞች ብላ በሞት ፍርድ ቀጣች። ሆኖም ግን አንድ ሚሊዮን ሕዝብ ባለቀበት የወንጀል ባሕር ውስጥ ስንቱን አስሮ ስንቱንስ ገድሎ መዝለቅ ይቻላል? ቱትሲዎች ሥልጣን በያዙ በሁለተኛው ዓመት ውስጥ የእስረኞቹ ቁጥር 80,000 ደረሰ። እስረኞችን ማጎሪያ በቂ ቦታ ጠፍቶ ጠባብ ክፍል ባላቸው ቤቶች ውስጥ ሺዎች ተፋፍገው ለመኖር ተገደዱ። የሚበሉት አጥተው በሕመምና በችጋር ተጠበሱ።

ይኼን ጊዜ የዓለም ሚዲያዎች እሪ አሉ። ሩዋንዳ ያን ሁሉ ሕዝብ አጉራ ማቆየቷንና ለመደበኛ ፍርድ ማቅረቧን ችላ በማለት - ትታ፣ ጋቻቻ በመባል የሚታወቀውን ባህላዊና ማኅበረሰባዊ የፍርድ ሥርዓት እንደ አዲስ ዘረጋች።

በየመንደሩና በየአካባቢው ወደ 12 ሺሕ የሚጠጉ ማኅበረሰባዊ የፍርድ ሸንጎዎች በመላ ሀገሪቱ ተቋቋሙ። ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚደርሱ ጉዳዮች በሕዝቦች መካከል ሰላምና ዕርቅ የሚያወርድ ውሳኔ አገኙ። ጥፋታቸውን በሕዝብ ፊት አምነው ይቅርታ የጠየቁ በደለኞች አንዳንዶቹ እዚያው በነጻ ተለቀቁ። ሌሎች ደግሞ ለበደላቸው እንደ ካሳ እንዲሆን ለኅብረተሰቡ ማኅበራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ እየተደረገ በሰላም ወደ ቤታቸው ተሸኙ። ሩዋንዳም ያለፈ ጠባሳዋን በዕርቅና በፍቅር አከመችው።

በሩዋንዳ የጽልመት ቀናት በቦታው ተገኝቼ የሆነውን የማየት ዕድሉ ገጥሞኛል። ጦርነቱን አሸንፌያለሁ ብሎ የመጣ ታጋይ፣ ወደ ቀዬው ሲመለስ ሁሉም ወገኖቹ አልቀውበት በማግኘቱ፣ በበቀል ስሜት ሰፈሩን በቦንብ

እስከማጋየት የደረሰ ርምጃ ሲወስድ አይቻለሁ። ይሄም ማሸነፍና መሸነፍ፣ ሰላምና ጦርነት የሚባሉትን ጉዳዮች በተለየ መንገድ እንዳያቸው አድርገውኛል።

# ምዕራፍ ሰባት

*የኢትዮጵያን ዕርቅ ፍለጋ*

*"የነገር ራስ አጥፍቻለሁ ልካስ"*

## *በይቅርታ እንድንሻገር...*

በካናዳ፣ ሩዋንዳና ደቡብ አፍሪካ ውስጥ የተፈጸሙት ያለፈውን በይቅርታ ዘግቶ መጪውን በፍቅር የመክፈት ሀገር አቀፍ የፈውስና የሰላም ሥራዎች ቀላል አለመሆናቸውን እንገነዘባለን። በአጭር ጊዜ ለተፈጸመ ዘግናኝ ጭፍጨፋም ሆነ በብዙ መቶ ዓመታት ለተከናወኑ የግፍ ድርጊቶች መልሱ ያው ይቅርታ፣ ዕርቀ ሰላምና ፍቅር ብቻ ነው። በተለይ ለኛ ለኢትዮጵያውያን የቅርቡም ሆነ የሩቁ ታሪካችን ከበደልና ከደም የነጻ አይደለም። ጥፋተኛውን ወንጅሎ ለመቅጣትና የዘር ዘሩን ለመበቀል የምናደርገው ጥረት ሁሉ እሳት ሆኖ የሚያቃጥለው ሁላችንንም ነው። ይልቁንም ቆም ብለን ልናስብ ይገባል። ጅል ቤቱን አንድዶ ሲሞቅ <አሁን ገና በራልኝ> አለ ይባላል። በሁላችንም ውስጥ ያለው መልካምነት ሊወጣ የሚችለው በይቅርታ ስንፈወስ፣ በዕርቀ ሰላም ስንቀራረብና በፍቅር አንድ ስንሆን ብቻ ነው። ለዚህም ነው ነጋ ጠባ "በይቅርታ እንሻገር፣ በፍቅር እንደመር' የምንለው።

አዲሱ የለውጥ ምዕራፍ የትኩረት አጀንዳ፣ በውርደት ድባብ ውስጥ የወደቀውን ኢትዮጵያዊነት በሚገባው ልክ ከፍ ማድረግ ነው። ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ማድረግ እያንዳንዳችንን ከፍ ያደርገናል። ስለዚህም ሕልማችን እርስ በእርስ በመቆራቆስ የሸረሸርነውን አብሮነትና ሰብአዊ ክብር ወደቦታው መመለስና ጠንካራ ሀገር መፍጠር ነው። ለዚህ ደግሞ ቀዳሚው ተግባርና የጉዟችን መጀመሪያ መለያየት የፈጠረው ግንብ አፍርሶ የግንኙነት ድልድይ በማነጽ፣ በይቅርታና በፍቅር ልብ ለልብ መገናኘ የሚያስችል ዐውድ ማመቻቸት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ካለፈው ጥፋት ተምር የተበላሸውን አስተካክሎ፣ ቀና ታሪክ በመሥራት ለአዲስ ኢትዮጵያዊ ዐርበኝነት በር መክፈት ያስፈልጋል።

አንድ ሰው በልጅነት ዘመኑ የደረሰበትን በደልና መከራ እያሰበና እየቆዘመ፣ አዘውትሮም ያንን ለመበቀል እያቀደ መኖር ይችላል። ውጤቱ ግን ዕድገትና ብልጽግና አይሆንም፤ ወደ ትናንት እየሄዱ ማደግ ስለማይቻል። ብልኅ ከሆነ ከትናንቱ ይማራል፤ ችግሮቹን ይለያል። ከዚያም ዛሬ ባገኘው ዕውቀት፣ ገንዘብ፣ የአስተሳሰብ ደረጃና ልቦና ልክ ያርማቸዋል። ሁሉም የትናንት ነገሮች ግን ሊታረሙ አይችሉም። የዕርቅና የይቅርታ አስፈላጊነቱ እዚህ ላይ ነው። ያለፉትን ሁሉ ይቅር ብሎ፣ ዳግም እንዳይደገም በዕርቅ እልባት ሰጥቶ፣ በፍቅር ወደፊት መሻገር ያስፈልጋል።

***ምሬትና እህህ' እያሉ ስለ ራስ መቆዘም ለማንም በጅቶ አያውቅም።***
***"እህህ ነው እንጂ ያከሳው ደረቴን፣***
***ሳልበላ አላድርም አንድ እንጀራ ራቴን!?"***

እንዳለው እረኛ፣ ውስጥ ውስጡን መብሰክሰክ ፍሬ የሌለው የትካዜ ዛፍ ነው። ቁጭት የሚጠቅመው ለአንድ ነገር ብቻ ነው። ለነገ ሥራ መነሻ። ያለበለዚያ ግን የትናንትን ቂም መቋጠሪያ ይሆናል።ብሶት አዲስ ሕይወት

ካልወለደ የበቀል ሽክርክሪት ውስጥ ይነክራል። ለዚህ ነው ፍቅርና ይቅርታ የተሻሉ የታሪክን ስብራት መፈወሻ መድኃኒቶች የሚሆኑት። መጭውን ዘመን በሰላምና በፍቅር ለመጀመር ይቅርታን ሊያመጡ የሚችሉ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ አሠራሮች፣ አደረጃጀቶችና ሕዝባዊ ትስስሮችን በየደረጃው መጀመሩ አማራጭ የለውም። ሕዝቦችና የፖለቲካ ኃይሎች በመካከላቸው የነገሠውን በጥርጣሬና በጎሪጥ የመተያየት ክፉ አመል ለማሸነፍ የጠፋውን ፍቅርና መደማመጥ መመለስ አለብን።

ሁላችንንም ደስተኛና ተጠቃሚ ወደሚያደርገን ቅርርብና የግንኙነት ደረጃ እንደግ። ጥፋት የውድቀት መጨረሻ ስኬትም የአሸናፊነት ማረጋገጫ አይደለም። ለድርጊታችንና ለንግግራችን ሐላፊነትን ወስደን ለዕድገትና ለሥልጣኔ በር ከፋቾች እንሁን።

ለተተኪው ትውልድ ቂም በቀልንና ጥላቻን ከማውረስ እንቆጠብ። በቀልና ቂም የውድቀት እንጂ የሥልጣኔ መነሻ ሆነው አያውቁም። ቁርሾና ግጭት የድህነት እንጂ የብልጽግና ማዕከላት ሆነው አያውቁም። በበዓለ ሢመቱ ያደረግኩትን ንግግር ተከትሎ በሳምንታት ዕድሜ ውስጥ ትልልቅ የድጋፍ ሰልፎች በየስፍራው ተካሂደዋል። ቁጥሩ ከፍተኛ የሆነ ሕዝብ በአንድም በሌላ መንገድ ከለውጡ ጎን መሰለፉን አረጋገጠ። ፈገግ በሚያስብል መልኩ የድጋፍ ሰልፎች ላይ የባንዲራ ርዝመት ውድድሩ በሜትሮች ተጀምሮ ኪሎ ሜትሮች ላይ ደረሰ። ሙዚቀኞች በነጠላ ዜማ፣ ወግ ጸሐፊዎች በወጎቻቸው የወቅቱን ስሜት ገለጹ። ከሰብአዊ መብት አቀንቃኞች እስከ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ ከሀገር ውስጥ እስከ ውጭ ጋዜጠኞች የወቅቱ ስሜት ምን ይመስል እንደነበር የየበኩላቸውን አንጸባርቀዋል።

በጣም አስደናቂውና ተስፋ ሰጪው እውነታ ደግሞ ይህ ሁሉ የሆነው ሕዝብን በወጣቶችና በሴቶች ማኅበር ተደራጅተው፣ ወይም በፓርቲ ጥሪና በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ድለላና ስውር ማስፈራሪያ ተጎትተው አልነበረም። የለውጡ የመጀመሪያ ምዕራፍ ልጅ ዐዋቂውን፣ ወዳጅ ጠላቱን፣ የቅርብ የሩቁን፣ የውስጥ የውጭውን ሁሉ አስደምሟል ማለት ይቻላል። ለለውጥ ቡድኑም ተዝቆ የማያልቅ ብርታትን አጎናጽፏል።
ኢትዮጵያዊነት ሲበርደን የምንደርበው፣ ሲሞቀን አውልቀን የምንወረውረው ድርብ ልብስ ወደ መሆን ተሸጋግሮ ነበር። በደምና በአጥንት የተገነባ የነጻነት ጉልላት መሆኑ ቀርቶ እንደ ዕዳ መቆጠርም ተጀምሮ ነበር። ይህ እንዲሆን ያደረገው እከሌ ነው፣ እከሊት ናት ብሎ እጅ መጠቋቆም _ አያሻም። በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የእያንዳንዳችን አስተዋጽዖ ስላለበት ሁላችንም ሀገርንና ሕዝቧን ይቅርታ መጠየቅ ይኖርብናል። ሁላችንም ይቅርታ ተቀባይም ሰጭም በመሆን አዲሱን ምዕራፍ በፍቅር መጀመር ተገቢ ነው። <የውሾን ነገር ያነሣ> በማለት፣ ያለፈው አልፏል ብሎ የቀደመውን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በእውነተኛ በፍቅር፣ በይቅርታና በዕርቅ መዝጋቱ ለሁሉም ይበጃል። በሕዝቦች መካከል ቂምና በቀልን፣ ቁርሾንና ጠብን፣ ጥላቻና ጠላትነትን ለሚዘሩ ኃይሎች ዕድልን ላለመስጠት ንግግሮቻችን ከዚህ የተቆጠቡ ሊሆኑ ይገባል። በሕዝቦችና በፖለቲካ ኃይሎች መካከል ይቅርታና ፍቅር እንዲኖር የሚሠሩ ቡድኖችንና ሥራዎችን ማበረታታት አለብን። ሕዝቦች የሚያስፈልጋቸው ተጋግዘው አንዳቸው ስለሌላቸው የሚማሩበትን መንገድ መቀየስ ነው። አብረው መኖርና

መብላት ብቻ ሳይሆን አብረውም እየሠሩ ወደጋራ ብልጽግናና ስኬት የሚያሳድጉበትን መንገድ መትለም አንዱ የመደመር ሂደት ነው።

ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ሰዎች የጋራ ኩባንያዎችን እንዲመሠርቱና አብሮ የመሥራትን ባህል እንዲያዳብሩ፤ የስፖርት ማኅበራት ከየማኅበረሰቡ በሚመጡ ሰዎች እንዲቋቋሙ፤ የጋራ ዕሴቶቻችንን የሚያሳዩ ሥነ ቃሎች፣ ተረቶች፣ አፈ ታሪኮች፣ ወደሌላው ቦታ በመሄድ ክዋኔዎች፣ እንዲሰባሰቡና እንዲታወቁ፤ ከአንዱ እንድንተዋወቅና እንድንግባባ የሚያደርጉን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ጉዞዎች እንዲጠናከሩ ልናደርግ ይገባል።

ከሌላ ቦታ መጥቶ ያልተወለደበትን አካባቢ የሚያለማ ሰው ለሕዝቦች መስተጋብር እሴት ስለሚጨምር እንዲበረታታ ማድረግ አለብን። አንዱን እምነት ሌላው እንዲያውቀውና እንዲያከብረው የሚያደርጉ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል። በትምህርት ቤቶቻችን ልዩ ልዩ ሃይማኖቶቻችን ያሏቸው ዕሴቶች በትምህርት መልክ እንዲሰጡና መፈራራት እንዲቆም ማድረግ አለብን።

በጋራ ለዚህች ሀገር ያደረግናቸው ተጋድሎዎች፣ የሠራናቸው የጀግንነት ሥራዎች፣ የዋልንባቸው የጦር ዐውድማዎች ጎልተው ሊነገሩ ይገባቸዋል። በክልሎች መካከል የሚገኙ ወሰኖች የጠብ ሳይሆን የጥምረት መነሻዎች እንዲሆኑ ማስቻል አለብን።

ከውጭ ሀገር የሚመጡ ኢንቨስተሮችን ለመቀበል የምንጥረውን ያህል፣ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል የሚመጣን ባለሀብት ለመሳብና ለመንከባከብም መትጋት አለብን። የምንተርከው የኢትዮጵያ ታሪክ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ የሁላችንንም ታሪኮች እንዲያትት እንሥራ። ብዙ የሀገራችንን ቋንቋዎች መማር፣ መናገርና በብዙ የሀገራችን ቋንቋዎች መጻፍን እናበረታታ። የየብሔረሰቡ ምግቦች፣ የወግ ዕቃዎችና የጥበብ ሥራዎች ወደ መሐል ገበያው እንዲመጡና በሁላችንም ታውቀው ጥቅም ላይ እንዲውሉ እናድርግ። የሁላችንንም ታሪክና ባህል የሚያሳዩ የኢትዮጵያ ሙዝየሞችን በየአካባቢው እናቋቁም። በዚህም ኢትዮጵያን እንዴት በጋራ እንዳቆምናት ትውልዱ እንዲረዳ እናድርግ። መደመርን እንዲህ ነው ማቀላጠፍ የምንችለው።

በተለይ መጪው ትውልድ እርስ በርሱ እንዲተዋወቅና የጋራ ሕልም እንዲያዳብር እናብቃው። ያለመውን ሕልም ከዕለታዊ የባህልና የእምነት ውርርሱ ጋር አዋሕዶ እንዲያበለጽግ እናግዘው። አንዱ የሌላው ጸጋና ሀብት ባለቤት ነውና በግልም ይሁን በጋራ ያላቸውን ጸጋና ሀብት እንደራሳቸው አድርገው እንዲንከባከቡና እንዲኮሩበት እናበረታታ። ይህ የሚሆነው ደግሞ አንዱ ለሌላው መብት፣ ታሪክ፣ ባህልና ቅርስ ጥብቅና እንዲቆም ማድረግ ከተቻለ ብቻ ነው። የሞትነው በጋራ ነውና የምንነሣውም በጋራ ነው። የአንዱ ቁስል የሁላችንም ነውና አንዱ ካልዳነ ሁላችን አንድንም።

ሁሉንም ተጠቃሚና የለውጡ አካል ለማድረግ እንዲቻል በቅደም ተከተል ለተለያዩ የኅብረተሰባችን ክፍሎች፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመጓዝ ይሄንን ያልተለመደ መንገድ፣ አዲስ አቅጣጫና ፋና ወጊ ፍልስፍና መግለጥ እጅግ አስፈላጊ ነበር። ለምሳሌ በምሥራቃዊው የሀገራችን ክፍል ጅግጅጋ በመሄድ የመደመርን ፍልስፍና መሠረት በማድረግ፣ በሶማሌዎችና በኦሮሞዎች መካከል ዕርቅ እንዲወርድ ሠራን። በበደል የተጨማለቀውን የወቅቱን የክልሉን መሪም በይቅርታና በፍቅር ለማቀፍ ሞከርን።

በክልሉ ተወላጆችና ከሌላ ክልል መጥተው በዚያ በሚኖሩ የሀገራችን ዜጎች ላይ ጭካኔ የተላበሰ ዘግናኝ ስቃይና ለመንገር የሚከብድ ኢሰብአዊ ክፋት ተፈጽመው ነበር። ይህን በማድረጉ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ጭምር የተከሰሰውን የክልሉን መሪ እንደ ወንድም በማቀፍ፣ የሠላም እጃችንን ዘርግተን ልባዊ የዕርቅ ጥሪ አቅርበን ነበር።

እንደዚያ ያለው ርምጃ ያስከፋቸው በርካታ ሰዎች እንዳሉ ዐውቃለሁ። ዳሩ ግን ዕርቅ በጠላትነት ለራቀ፣ ይቅርታም ለበደለ እንጂ ለመልካምና ለበጎ ወዳጆቻችን የምንሰጠው ችሮታ አይደለም። በዚያው ሰሞን በሕዝባዊ ትግሉ ጊዜ በእምቢ ባይ ዐመፅዋና በጽኑ ታጋይ ወጣቶቿ ወደምትታወቀው አምቦ አቅንቼአለሁ። ከዐመፅ ወደ ሰላም፣ ከትግል ወደ ሀገር ግንባታ እንዲሸጋገር ለሕዝቡ ልባዊ ተማጽኖ አቅርቤ ነበር። በተመሳሳይ በመቐለ፣ በጎንደር፣ በባሕር ዳር፣ በሐዋሳ፣ በአሶሳ፣ በሠመራና በጋምቤላ በተደረጉ ጉዞዎች የይቅርታና የመደመር ጥሪ አስተላልፌያለሁ።

በሹመቴ ማግሥት ከቦታ ቦታ ስዘዋወር የነበርኩት ራሳችን በራሳችን ላይ የጫነነውን የጥላቻ ርግማን ለማለዘብ ነበር። በመቐለ የመጀመሪያ ጉዞዬ ተመሳሳይ የመደመር ጥሪዬን በትግርኛ ያደረኩት ያለምክንያት አልነበረም። በታሪክ አጋጣሚ ባለፉት በርካታ ዓመታት ቁንጮ የሀገራችን የፖለቲካ ተዋናዮች የሕወሓት ሰዎች ነበሩ። በአንድ በኩል የሕወሓት ነባር አመራሮች ከነበራቸው ቁልፍ ሚና አንጻር የመገለል ስሜት ሊፈጠርባቸው ይችላል የሚል ግምት ነበረኝ። በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይ ሕዝብ እንደ ሌላው ወገኑ በለውጡ ተጠቃሚ እንጂ በምንም መልኩ ተጠቂ እንደማይሆንና ከዚህ ጋር ተያይዘው ሲነዙ የነበሩ ወሬዎች ተገቢ እንዳልሆኑ ለማስረዳት ነበር።

ለውጡ የመደመርና የማቀፍ እንጂ አግላይ እንዳልሆነ በሩቁ ሳይሆን ፊት ለፊት ተገናኝተን ከሕዝቡም፣ ከየክልሉ ባለ ሥልጣናትም ጋር መክረናል። ይህ ከመልካም ምኞት የመነጨ ርምጃ ሙሉ ለሙሉ ግቡን የመታና ሁሉንም ጮቤ ያስረገጠ ነው ባይባልም፤ የለውጥ ቡድኑ የተለመውን ሰላማዊ ርምጃ ያለ እክል ማድረግ የቻለበትን አንጻራዊ ነጻነት እንዳስገኘ እሙን ነው። ከሕዝብ የምናገኘው መልካም ምላሽ፣ የቤት ሥራችንን እንደሚያበረታው የታመነ ነው። ርምጃችን ትንፋሽ የማይሰጥ ቢሆንም መፍጠን እንዳለብን ነጋሪ አላስፈለገንም። ቀጥለን ያመራነው ወደ አማራ ክልል ነበር። ወደ አማራ ክልል ያደረኩት ጉብኝት ከመንፈቅ በፊት ካደረኩት ጋር ሲነጻጸር ፍጹም የተለየ ነበር።

ከወራት በፊት በኦሮሞና በአማራ ሕዝቦች መካከል ለዓመታት የተዘራውን የጥላቻ አሜኬላ ለመንቀል ጉዞ

አድርገናል። ጉዞው አንድነትንና እውነተኛ ወንድማማችነትን ወልዷል። በመካከል ላይ ተገንብቶ የቆየውን ያንን የልዩነት ግንብ አፍርሶ በጋራ ለኢትዮጵያዊነት የሚተጋ ሕዝብ ለመፍጠር ችሏል። በእርግጥ ከኛ በፊት ብዙ ደራሲዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎችና ይመለከተኛል የሚሉ ሰዎች፣ መንገድ የሚጠርግ ሥራ መሥራታቸው ይታወቃል።
ባሕር ዳር በተገኘንበት በዚያች ቅጽበት በመላው አመራርና በአጠቃላይም በሕዝቡ የተደረገልን አቀባበልና የተቸረን ድንቅ ፍቅር ልዩ ስሜት ፈጥሮብን ነበር። ይህ ስሜት የእኔና ባሕር ዳር ላይ የተገኙት ጓዶቼ ስሜት ብቻ አልነበረም። የአማራ ክልል ከፍተኛ አመራሮችም ከመገለጽ በላይ የሆነ የመደመም ስሜት ውስጥ እንደነበሩ ለመታዘብ ችያለሁ።

ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ገዱ ነበር። አንድ መርሐ ግብር ላይ የገዱን ተመስጦ ያረበበበት ገጽታ አይቼ በፈገግታ ተጠጋሁት። ቃል ከአፌ ሳላወጣ በዐይኔ ብቻ አወራሁት። ስሜቴ ገብቶታል። አሁን ለምናየው አብሮነትም ሆነ ለተፈጠረው ክፍተት ተጠያቂዎቹ እኛው አመራሮቹ መሆናችን ነጋሪ አያሻውም። “በሚሆን በማይሆን ከመናቆር ወጥቶ ይህ ሕዝብ አብሮነቱን ካጸና በእውነቱ ትልቅ ታሪክ ነው” አለኝ።እኔም ከአፉ ቀበል አድርጌ፣ “ኦሮማራ ዛሬ የኦሮሞና የአማራ ጥምረት ቢሆንም ነገ ግን የመላ ኢትዮጵያውያን የአንድነት ኪዳን ነው” አልኩት። ትክ ብሎ አየኝ። ምክንያቱም ኦሮሞና አማራ ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በጋብቻ በመተሳሰርና በመዋለድ ትልቅ ታሪክ ያላቸው ሕዝቦች ናቸው። በአንድም ይሁን በሌላ መልኩ ኦሮማራ ፍቅሩንና አብሮነቱን እንደያዘ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቤት ይገባል" አልኩና፣ ፈገግ ብዬ አየሁት። እሱም ፈገግ አለ።

እኛ ባሕር ዳር ተገኝተን ከክልሉ አመራሮችና ከአካባቢ ሽማግሌዎች ጋር ስንነጋገር ጉዟችን ግቡን እንደሚመታ ቅንጣት ታህል አልተጠራጠርንም ነበር። በወቅቱ ብዙ ሕዝብ ከጎናችን ነበር። የአማራ ሕዝብም ልቡን ከፍቶ ነበር የተቀበለን። በተመሳሳይ ዓመት ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አማራ ክልል ማቅናቴ ነው። የአሁኑ ግን እንደ ቀደመው ጊዜ አልጋ በአልጋ አልሆነልኝም።
በትግራይና በአማራ ክልሎች መካከል የተፈጠረው ውጥረት የጎንደርና የባሕር ዳር ጉብኝቴን ፈታኝ አድርጎታል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በመቐለ ጉብኝቴ ወቅት ስለወልቃይት ተጠይቄ የሰጠሁት ምላሽ በተሳሳተ መንገድ ትርጉም ተሰጠው። ይኼም የሚዲያ አፍ ማሟሻ ከመሆኑም በላይ ዓባይን ስሻገር በግማሽ የተዘጋ ልብ እንዲገጥመኝ ምክንያት ሆኗል። ወቅቱ ወደ ኋላ ማፈግፈግን የሚጠይቅ አልነበረም። ጥንቃቄ ሳይለየኝ ወደፊት መጓዝ ብቸኛ አማራጬ ነበር።

ደግነቱ የአማራ ክልል ሕዝብ አላሳፈረኝም። ኦቦ ለማና አቶ ገዱ የለኮሱትን የኦሮማራ ችቦ ዳግም በማቀጣጠል ሕይወት እንዲዘራ በማድረግ፣ የጣና ዙሪያ ገብ ሕዝብ ፍቅሩን አጎናጸፈኝ። በእርግጥ ኦሮማራ በማንም የተፈጠረ የሕዝቦች ጥምረት ሳይሆን የአማራና የኦሮሞ ሕዝቦች ዘመን ተሻጋሪ የአብሮነት ኪዳን ነው። ባይሆን ባይሆን ሕዝቡን ለመለያየት ከልሂቃኑ በኩል ብዙ ድንጋይ ተወርውሯል ማለት ይቻላል።

ባለፉት ዓመታት በሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች መካከል መቃቃርን ለመፍጠር ፖለቲካዊ ሥልጣንን ተገን በማድረግ የተሠራ ሤራ ነበር። የተፈጠረው ቁስል ሳያመረቅዝ እንዲያሽር፤ ለማ መገርሳና ገዱ አንዳርጋቸው ከነጓዶቻቸው የነበራቸው ሚና እጅጉን ከፍ ያለ ነው። እኔና ዶክተር አምባቸውም ለረጅም ጊዜ የኦሮማራ ወዳጅነት እንዲጠናከር ስንመክር ብንቆይም፣ የውጤታማነቱ መሠረቶች ግን ሁለቱ ሕዝቦችና በታሪክ አጋጣሚ ሕዝቦቹን የማገልገል ዕድል የገጠማቸው ሁሉም አመራሮች ናቸው።

በተቀሩት አራት የክልል ከተሞች በሐዋሳ፣ በአሶሳ፣ በጋምቤላ፣ በሠመራ በአካል በመገኘት የአዲሱን ለውጥ ዕድልና ትግል ለሕዝብ፣ ለሀገር ሽማግሌዎችና ለተሰሚ መሪዎች ለማብሠር ሞከርኩ። ሁሉን አቀፍ ለውጥ ለማምጣት ተደምረው ሀገራዊ ኃይል እንዲሆኑ ጥሪዬን አቀረብኩ። በበደል ስሜት የተወጠሩ ልቦች እንዲረግቡ የይቅርታና የፍቅር ቃሌን አጉልቼ ተናገርኩ። ሕዝቡ በየቦታው ያደረገልኝ ደማቅ አቀባበልም ሥጋት በፈጠረው የነፍሴ ስንጥቅ ውስጥ የተስፋ ነፋስ እንዲነፍስ አድርጓል።
በአሸባሪነት ተፈርጀው በሌሉበት የሞት ፍርድ የተበየነባቸው የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና ታዋቂ የመብት አቀንቃኞች ወደ ሀገር ቤት ለመመለስ ፊታቸውን አዞሩ። ትኬታቸውን ለመቁረጥ መዋል ማደር ወይም ሌላ ድርድር ውስጥ መግባት አላስፈለጋቸውም። ሻንጣቸውን ሸክፈው ደጋፊዎቻቸውን አስከትለው ወደ ሀገር ቤት ጎረፉ። ስደት ቤታቸው የሆነ፣ ዘመድ ቤተሰቦቻቸውን ካዩ ዓመታት የከረሙ፣ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና የጦር አዛዦች ወደ ሀገር በተመለሱ ቁጥር፣ የፖለቲካ ትኩሳቱ እየበረደና ውጥረቱ እየቀነሰ መጣ። ይሄም የለውጥ ተስፋውና የሰላም ውጋጋኑ እየፈካ እንዲመጣ አደረገው። በአንድ ክፍል ውስጥ አብረው መቀመጥ የማይችሉ ሰዎች ከአንድ ገበታ ላይ በፍቅር እንዲበሉ ለውጡ ምክንያት ሆነ።

ብርሃኑ ነጋና ሌንጮ ለታን፣ ዲማ ነገኦና ታማኝ በየነን፣ ከማል ገልቹና አረጋዊ በርሄን፣ ግደይ ዘርዐ ጽዮንና ዳውድ ኢብሳን እንዲሁም አንዳርጋቸው ጽጌንና ጃዋር መሐመድን የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሄደው ተቀበሏቸው። ትናንት ለሕይወት ሲፈለጉ የነበሩ ሰዎች ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ቪ.አይ.ፒ. ሳሎን ሶፋ ላይ ቁጭ ብለው ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጡ ማየት የተለየ ስሜት ይፈጥር ነበር። የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎቹም ሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያን በአጭር ጊዜ እውን ይሆናል ብለው የማይጠብቁት ትዕይንት ነበር። የኢትዮጵያ መንግሥት ኦነግና ግንቦት ሰባትን እንዴት ያያቸው እንደነበር ለመረዳት ማንንም መጠየቅ አያስፈልግም።

አስታዋሽ አጥተው በየባዕድ ምድሩ ወኅኒ ቤት የሚማቅቁ ወገኖቻችን ጉዳይም ሌላው አሳዛኝ የሀገራችን ገጽታ ነው። ሁሉንም ማስለቀቅና ለእናት ምድራቸው ማብቃት የልባችን ፍላጎትና የዘውትር ጸሎታችን ነበር። ወደ ግብጽ ለሥራ ጉብኝት በሄድኩበት ጊዜ አንዱ ልቤን የያዘው ጉዳይ የነዚሁ ወገኖቻችን ጉዳይ ነበር። በዚያ ባዕድ ምድር ያለምንም ተስፋ በእስር ቤት ታጉረው ከነበሩ ወገኖቻችን ጋር በአውሮፕላን መመለስ ተአምር እንደሚፈጥር አየሁ። ወገንን ‹አለሁልህ› ማለት ዕቅፍ ሙሉ ደስታ እንደሚሰጥ ከእስር በተፈቱት ወገኖቻችን ፊት ላይ በጉልህ ተጽፎ አነበብኩ።

ከሳዑዲ ዓረቢያ ኢትዮጵያውያንን አስፈትተን አብረን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰናል። ለዜግነት የሚሰጥ ክብር ከገንዘብ በላይ ሐሴትን እንደሚገዛ በአውሮፕላኑ ውስጥ ከነበርነው ሰዎች በላይ የሚረዳ ሰው መኖሩ ያጠራጥራል። በኬንያና በሱዳን ቁጥራቸው የበዙ እስረኛ ወገኖቻችንን ከባዕድ ሀገር ወኅኒ እንዲወጡ ማድረግ ከተፈቺዎቹ በላይ እኔን ሲያስደስተኝ ነበር። ከዓመታት በፊት አንዳርጋቸው ጽጌ ከየመን አውሮፕላን ጣቢያ ተይዞ ወደ እስር ቤት ሲገባ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ተፈጥሮ እንደነበር አስታውሳለሁ። ብዙ ሰዎች ተረብሸው ነበር።

አንዳርጋቸውን ከየመን አየር ማረፊያ ለመያዝ የተካሄደው ኦፕሬሽን እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ የፈሰሰበት እንደነበር መነጋገሪያ ሆኖ ነበር። ከዚያም ባለፈ በእስር ቤት ውስጥ የደረሰበት መንገላታት በተከታታይነት ሲገለጽ ቆይቷል። እንደዚህ ያሉ ነገሮችን መስማት ስሜትን ከመረበሽ ባሻገር አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ወደ ውስጡ እንዲያነባ ያደርገዋል።

አሜሪካ ቢን ላደንን ከምትፈልገው በላይ የኢሕአዴግ መንግሥት የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችን በአሸባሪነት ይፈልጋቸው ነበር። እነዚህ ሲታደኑ የኖሩ የፖለቲካ መሪዎች ናቸው በቦሌ በኩል ዕቅፍ አበባ እየተበረከተላቸው በቀይ ምንጣፍ ላይ ተራምደው፣ በጠራራ ፀሐይ ወደ ሀገራቸው የገቡት። ይሄን ማየት ብዙዎች ወደ ውስጣቸው ሲያነቡት የነበሩትን ዕንባ በደስታ ወደውጭ እንዲያነቡት አድርጓቸዋል።

በሐምሌ ወር መጨረሻ ላይ በአሜሪካ ልዩ ልዩ ከተሞች አዲሱን የኢትዮጵያ የለውጥ አመራርና ሂደት የሚደግፉ ታላላቅ ሰልፎችና ስብሰባዎች በተከታታይነት ተካሄዱ። በዚህ ወቅት ነበር የተፈጠረውን የለውጥ ማዕበል ለማስፋፋት፣ የተገኙትን አስደሳች ዕድሎች ለማጋራትና ከናፈቁን የሀገራችን ውድ ልጆች ጋር በአንድ ጣራ ሥር ለመጨዋወት ከለውጥ አመራሩ የተወሰኑትን ይዤ ወደ አሜሪካ ያቀናሁት።

በሰሜን አሜሪካ በነበረኝ ቆይታ ኢትዮጵያዊነት የሚል የጋራ አጀንዳ ያላቸውን ሰዎች ለማነጋገር ችዬ ነበረ። ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገብረ ማርያምን፣ አርቲስት ታማኝ በየነን፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌን፣ ኮሎኔል ጎሹ ወልዴን፣ የኢሳትና የኦ.ኤም.ኤን ሚዲያ ጣቢያ መሥራቾችና ጋዜጠኞችን፣ ሌሎችንም ውድ የሀገራችን ልጆች አግኝቻለሁ። ከብዙዎች ጋር ኢትዮጵያዊነትና መደመር አስተቃቅፎን መልካም የሆኑ ሐሳቦችን ለመለዋወጥ በቅተናል።

ግንቡን እናፍርስ፣ ድልድዩን እንገንባ የሚል መሪ ቃል በተሰጠው ይህ ጉዞ ላይ ያገኘነው ጠንካራ ምላሽ የጥላቻ ግንብ እየፈረሰ የፍቅር ድልድይ በየቦታው ሲገነባ በዐይናችን ለማየት ቻልን። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የሀገራችን ልጆችም አዲሱን ዓመት በሀገር ቤት ተገኝተው ዘመን መለወጫን አብረውን ለማክበር ቀጠሮ ተያዘ።

ከዳያስፖራው ማኅበረሰብ ጋር ያደረግነው ምክክር ከወለዳቸው መልካም ነገሮች መካከል አንዱ የዳያስፖራ ትረስት ፈንድን መመሥረት ነው። ኢትዮጵያዊው ለሀገሩ ልማት በየቀኑ አንድ አንድ ዶላር ለማዋጣት ፍላጎቱን በደስታ አሳይቶናል። ይሄን ፍላጎቱን በተግባር እንደሚገልጠው ቅንጣት ታህል አልተጠራጠርንም ነበር።

የሸኘነው 2010 ዓ.ም. የመገባደጃው ሰሞንና ከኤርትራ ዕርቅ አውርደን የጀመርነው አዲሱ 201 ዓመት የመጀመሪያዎቹ ወራት፣ ስሜትና ግለት የበዛበት እንደነበር ትዝ ይለኛል። በተከታታይ ከውጭ ሀገራት ወደ ሀገር ቤት የሚገቡትን የተለያዩ ፓርቲዎች መሪዎችና አክቲቪስቶችን በመቀበልና በማስተናገድ አዲስ አበባ ጦዛለች። ከሚሊኒየም አዳራሽ እስከ አዲስ አበባ ስታድየም ያለው ሰፊ ጎዳና ተጨናንቆ ከረመ። ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ እስከ መስቀል አደባባይ ሌሊትና ቀን ሕዝቡ የትግል ጀግናዬ ነው ያለውን በድምቀትና በስሜት ይቀበላል። ሁሉም ይወክለኛል፣ ይገልጸኛል ያለውን ባንዲራና ዓርማ እንደ ፍላጎቱ በደረቱ፣ በካናቴራው፣ በመኪናው፣ በየስልክ እንጨቱና በየግድግዳው ላይ መስቀልና መለጠፍ የተለመደ ክሥተት ሆኖ ሰነበተ። ከተማይቱ ይሄንን ሁሉ ጽንፍ የያዘ ልዩነት በሰላም እያስተናገደች መክረሟ፣ ሁላችንንም እያስደሰተ የቆየ ጉዳይ ነበር። ያው የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደሚባለው እየቆዩ የተገለጡ አመሎች ቢኖሩም በወቅቱ የነበረው ዐውድ ከሚገባው በላይ አስደሳች ነበር። ኦነግ ሰላማዊ ትግሉን ለመቀላቀል ትጥቁን አስረከቦ፣ ሠራዊቱን ከኤርትራ በትግራይ በኩል አስገባ። በመንገዱ የሞቀ አቀባበል በመቐለ ከተማ ተደርጎለት ነበር። ይህ ከጥቂት ወራት በፊት የማይታሰብ ብቻ ሳይሆን የማይታለምም ነበር።

የኦነግን አመራር በመስቀል አደባባይ ለመቀበል የሚደረገው ዝግጅት ደግሞ በአዲስ አበባ ተጧጡፏል። ከሳምንት በፊት ለገቡት የግንቦት ሰባት መሪዎች አቀባበል ለማድረግ ከተማዋ ሰርግ ስትሰርግ ነበር የከረመችው። በእንደዚህ ዓይነት የሽግግር ሰሞን በተለያዩ ድርጅቶች ደጋፊዎችና ተከታዮች መካከል እዚህና እዚያ ግጭት መፈጠሩ የተጠበቀና አይቀሬ ጉዳይ ነበር። ምክንያቱም ለረጅም ጊዜ፣ እንኳን እንደዚህ በተለያዩ ጽንፍ ያሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ያለገደብ ሐሳባቸውን ገልጸው ይቅርና አንድ ፓርቲ ውስጥ ያሉ ሰዎችም ትንሽ ዝንፍ ካሉ ቁጣና ጦርነቱ መያዣ አይኖረውም ነበር።

ዘመናዊው የፖለቲካ ባህላችን የተመሠረተው አሳደህ በለው, በሚለው ቅኝት ላይ ነው። መምታት፣ መደምሰስ፣ መቅበር፣ ማንኮታኮት፣ ማሠርና ማሳደድ የፖለቲካ መዛግብተ ቃላታችንን ሞልተዉታል። አብሮ መኖርን ሳይሆን በሌላው መቃብር ላይ በትረ መንግሥታችንን ለማቆም ነው ስንፎክር የኖርነው። ማኅበረሰቡ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ በዚህ የተንሻፈፈ የፖለቲካ መሥመር በመቃኘቱ የፖለቲካ ባህሉ፣ ሥርዓቱና ልማዱ በዚሁ ላይ የተመሠረተ ነበር።

አሁን የጀመርነው አዲስ ክሥተት ነው። ለአዲስ ክሥተት የሚሆን ልማድ፣ ባህልና ሥርዓት ገና አላዘጋጀንም። ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ለአጋም ሲዘጋጅ በኖረ መሬት ላይ ጤፍ ዘርተንበት የናፈቅነው ጤፍ በዋዛ ይገኛል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። አዲስ እየዘራን ላለነው የመቻቻል፣ የመግባባትና የመደመር ጉዞ የሚሆን አባባል፣ ተረት፣ ምሳሌ፣ ሙዚቃና ሥነ ቃል ገና አላዘጋጀንም። የተከሠቱትን አሳዛኝ ክሥተቶች የፈጠራቸውም

ይሄው ነው። የማኅበረሰባችን የፖለቲካ ባህልና እየመጣ ያለው የለውጥ ማዕበል በእኩል ፍጥነት ጎን ለጎን እየሄዱ አልነበሩም። ስለዚህም አልፎ አልፎ ችግሮች ማጋጠማቸው አልቀረም። በምንገኝበት የዘመን ምዕራፍ እየተጓዝንበት ያለው የሀገር ግንባታ ሂደት ወደ ሰላም፣ ዕድገትና ልማት እንዲያመራ ብቸኛ መሣሪያው ኃይል ሳይሆን ዴሞክራሲ ነው።

ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባት የመጨዋቻ ሜዳውን ከመቼውም ይልቅ ማስፋትና ሁሉም በእኩልነት የሚሳተፍበትን ግልጽና ፍትሐዊ የጨዋታ ሕግና ዕድልን ማመቻቸት ይጠይቃል። ኢትዮጵያውያን በመረጡት መንገድ ተሰባስበውና ተደራጅተው ፓርቲ፣ ንቅናቄ ወይም የሲቪል ማኅበር በማቋቋም፣ ያለፍራቻ በነጻነት መንቀሳቀስ እንዲችሉ፣ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ርምጃ ወስደናል። በእኔ እምነት ከዚህም በላይ ሊደረግ ይገባል።
ምሁራን፣ ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ተንታኞች፣ ማኅበራዊ አቀንቃኞች (አክቲቪስቶች)፣ ደራስያን፣ ጦማርያንና ሌሎችም ሐሳብ አመንጪዎች በሀገራቸው ላይ በነጻነት ሐሳባቸውን እንዲገልጹ መንገድ ጠርገናል። ኅሊናቸው ሳይገደብና ሳይሸበብ እያሰቡ እንዲኖሩ ዕንቅፋቶችን ሁሉ ማንሣት ጀምረናል።

በወቅቱ የተነሣው ፖለቲካዊ ፍትጊያ የሰው ሕይወት እስከ ማጥፋት ደርሷል። በአዲስ አበባ ዙሪያ፣ በተለይም በቡራዩ አካባቢ ውጥረት ነግሦ ነበር። አላስፈላጊ ግጭት ተቀሰቀሰ። ግጭቱ እየተባባሰ ሲሄድ የነበረው ሰላምና ፖለቲካዊ ተስፋ በዐመፅና በተስፋ መቁረጥ ተተካ። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰላማዊ ሰዎች መኖሪያቸውንና ንብረታቸውን ጥለው እግሬ አውጪኝ _ አሉ። ንብረታቸውን አንጠልጥለው፣ ልጆቻቸውን አዝለው ከአካባቢው ሸሹ። በየትምህርት ቤቱና በየእምነት ተቋማቱ የጦርነት ተፈናቃዮች ይመስል ተጠልለው በገዛ ሀገራቸው ስደተኞች ሆኑ።

የተፈጠረው ጥላቻና ምሬት፣ ተስፋ መቁረጥና የልብ መውረድ በዚህ አካባቢ ብቻ ተወስኖ የቀረ አልነበረም። በተፈጠረው ጣፋጭ የለውጥ እሸት ተደስቶና ተስፋው አብቦ የቆየው አብዛኛው ሕዝባችን ከመቼውም ይልቅ በቀቢጸ ተስፋ ጨለማ ውስጥ ተዋጠ። የለውጡ መሪዎች ንግግሮች በፈነጠቁት የተስፋ አቅጣጫዎች ሕዝቡ ተደሰቶ ነበረ። ከአሁን በኋላ የትም ሄጄ፣ ያሻኝን ሠርቼ በነጻነት መኖር እችላለሁ የሚል ተስፋ ውስጡን ሞልቶት ነበር።

በቡራዩ የተፈጠረው ሁከት ግን በአንድ ጊዜ ብዥታ ፈጠረበት። ጭራሽ <የት ሄጄ ብኖርና ብሠራ ነው ሕይወቴ ከአደጋ የምትጠበቀውን?> የት ብኖር ነው ንብረቴን የማልዘረፈው? ልጆቼንስ በሰላም የማሳድገው? ከሚል ቀቢጸ ተስፋ ውስጥ እንዲወድቅ አደረገው።

የተፈጠረውን አደጋ የሰማሁት ሳዑዲ ዓረቢያ እያለሁ ነበር። አደጋውን በሰማሁበት ቅፅበት ተስፋ የማጣት ስሜት ውስጤን ክፉኛ ወጋኝ። ይህ ዓይነት ስሜት ከዚህ ቀደም የተሰማኝ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ተጠናቆ

ወደ አዲስ አበባ ስመለስ ነበር። ብሶት ነፍሴን ሲዳብሳት፣ በጥልቅ መብሰክሰክ ውስጥ ተዘፈቅሁ። እንዲያ የደግነትና የሥነ ምግባር አምላኪዎች የነበርን ሕዝቦች፣ ዛሬ በተራ አጀንዳዎች ክቡር የሰው ሕይወትን እስክንቀጥፍ የወረድነው እንዴት ብንሆን ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተሳነኝ።

በእርግጥ እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ማኅበረሰብ ከታመምን ቆይተናል። ከዕውቀት እጦት የተነሣ የነፍሳችን አከርካሪ እንክትክት ብሎ ተሰባብሯል። ችግራችን በድብብቆሽና በመሸፋፈን ወይም ጤነኛ መስሎ በመታየት፣ ሳንታከም መዳን፣ ወጌሻ ሳያየን ከስብራት መጠገን እንጠብቃለን። ነፍስ ኄር፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም እንዳሉት ጠብና ጥላቻችን ከጨቋኙ ጋር እንጂ ከጭቆናው አይደለም ብሎ ለመደምደም የማስረጃው ክምር ምስክር ለምኔ ያስብላል። መነጋገርና ተቀራርቦ መመካከር የምርጫና የቅንጦት ጉዳይ አይደለም። ሀገራችን ረጅም ታሪክና ቱባ የሃይማኖትና የብሔር ብዝኃነት አላት። ደግሞም በአሁኑ ወቅት ዋልታ ረገጥ የልዩነት አተካሮ ውስጥ ገብተናል። ከእነዚህ ነጥቦች አንጻር ተቀራርቦ ከመመካከር ውጭ መድኃኒት የለንም። እያደር እየኮሰሱ የመጡትን ግጭትና ልዩነትን የመፍቻ መንገዶቻችንን ከመጠቀም ይልቅ ውረድ እንውረድ' እናበዛለን። በውይይት ልዩነትን ከመፍታት ይልቅ ዘራፍ› የማለት ልማድ ሥር ሰድዷል። የመደማመጥና በሌላው ጫማ ውስጥ ሆኖ ነገሮችን የመመልከት ልማዳችን እንደ ቀይ ቀበሮና ዋልያ ተመናምኗል።

እስከ ዛሬ እንደ ሀገርና ሕዝብ አንድነትን ልንፈጥር የሞከርንባቸው ብዙ ምክንያቶች ነበሩን። አንዱ ለሌላው ውበቱና ህልውናው እንደሆነ በመረዳት በፍቅር ተደምረን የመኖራችን ባህል ግን ሳስቶ ኖሯል። ለብዙ ዘመናት ብሔርን፣ ሃይማኖትን፣ አካባቢን፣ ባህልንና ርእዮተ ዓለማዊ አቋምን ያማከለ መቃቃር በሀገራችን ነበር፤ አሁንም አለ። ድህነትና ችግር፣ ጥላቻና ዐመፅ በገነነበት ሁኔታ ስለኖርን በፍቅር ጉዳይ እጅግ ብዙ ከስረናል። ብዙ በማጣት ለዘመናት ስንጎዳ ኖረናል። ብቸኛው መድኃኒት ፍቅር ስለሆነ ነው፤ በቶሎ በፍቅር አንድ መሆን የሚያስፈልገው። በችግርና በችጋር ለብዙ ዘመን የተፈተነ ሕዝብ፣ ስለይቅርታ ለማሰብ ፍላጎቱ እንኳን ቢኖረው የውስጥ ዐቅሙ አይኖረውም።

ግለሰብም ሆነ ማኅበረሰብ በመልካም ሕይወትና በተደላደለ ሰላም ለመኖር፣ ፍቅርና ይቅር ባይነት አስፈላጊዎቹ እንጂ ቅንጦቶቹ አይደሉም። “በፍቅር እንደመር፣ በይቅርታ እንሻገር” የሚለውን መሪ ሐሳብ አምጦ የወለደውም ኢትዮጵያን ወደዚህ መልካም ሕይወትና የተደላደለ ሰላም ለመምራት ያለው ጽኑ ፍላጎት ነው። ይቅር ማለት ከማፍቀር በብዙ እጅ ይከብዳል። ብዙ ልፋትና ጥረት የሚጠይቀውም ማፍቀር ሳይሆን ከልብ ይቅር ማለት ነው። በተለይ በደሉ ለረጅም ጊዜ የቆየና የከፋ በሆነ መጠን ይቅር ማለቱ የዚያኑ ያህል ይከብዳል።

“እኛ በታሪክ አንኖርም፤ ታሪክ ግን በውስጣችን ይኖራል” የሚለው አባባል አንድ ጠንካራ እውነትን አጉልቶ ያሳያል። የሩቅ ዘመናት ታሪክ በውስጣችን እየኖረ ባልኖርነው ሕይወት፤ ባልወሰንነው ውሳኔና ባላጠፋነው ጥፋት ዙሪያ እየተጨቃጨቅንና እየተነታረክን ከአፈር ሳንነሣ ወደ አፈር እንመለሳለን። እስካሁን ፊታችን ወደ

ኋላ እንደዞረ ነው። በማናስተካክለው ትናንት ላይ ጉልበታችንን ሁሉ እያጠፋን ነው። ትናንትን የማስተካከያ መንገድ ግን አንድ ብቻ ነው። እርሱም ዛሬና ነገን ከትናንት የተሻለ ማድረግ።

ምጡን እርሺው፤ ልጁን አንሺው ይላሉ እናቶቻችን። የቅድሙን ምጥ የሚያስረሳው የአሁኑ ልጅ ነው። እናት ልጇን ባየች ቁጥር ምጡ አያብሰከስካትም፣ አያናድዳትም፣ አያስተክዛትም። እኛም ዛሬን የተሻለ ማድረግ ከቻልን በትናንቱ መብሰክሰካችን፣ መቆራቆሳችንና መነታረካችን ያበቃል። በታሪክ እንደታየው ሰው በዛሬው ነገር ካልረካ አንድም ከቀድሞ ጋር በፍቅር ይወድቃል፣ አልያም በቀድሞ ነገር ይብሰከሰካል።

በአሁኑ ወቅት የአብዛኛው ጭቅጭቅና ጠብ ምክንያት የታሪክ እይታችን ነው። ታሪክን እኛንና ልጆቻችንን ሊያገለግል በሚችል መልኩ ማንበብ እንችላለን። ታሪክን ልንማርበትና ሠናዩን ልናዳብርበት እንደሚያስችል መሣሪያ ልናስበው እንችላለን። ከሁሉም በላይ ደግሞ ታሪክ ለአብዛኞቹ ችግሮቻችን መልስ ሊኖረው እንደማይችል መገንዘብ ይኖርብናል። ታሪክ ሚናው ለቀጣይ ጉዞ ስንቅና የተስተካከለ የእይታ አድማስ እንጂ ለኗሪ የዕለት ተዕለት ቀለብና የተበዳይነት እሮሮ ወይም የበላይነት ቀረርቶ ግጥም ማቀበል አይደለም።

ከፋም ለማ ያለፈ ታሪክ አልፏል። ትርጉማችንንና ትምህርታችንን እንጂ ሂደቱን መቀየር አንችልም። የሆነው ሆኗል። የምንችለው መዘከር ብቻ ነው። ለምን እንዘክረዋለን? ያልን እንደሆነ መልሱ ሁለት ነው። ክፉውን ለማረምና በጎውን ለማጎልበት። የአዲሱ ለውጥ ርምጃዎችና አመለካከቶች በዝርዝር እንዲታወቁና እንዲጨበጡ ለማድረግ ሰፊና ቀጣይ ሥራ መሠራት አለበት። ሚዲያዎቻችን በትናንት ላይ ተጠምደው መጪውን ተስፋ ለማጨለም ነጋ ጠባ መራወጣቸው ጠቃሚ አይደለም። ስለትናንት ስናወራ ሁሌም ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። ከትናንቱ እንድንማር፣ ስሕተታችንን እንዳንደግም ለማድረግ በሚያስችል መንገድ መሆን አለበት። ጉዟችን መንታ ትልሞች ያቀፈ ነው። በአንድ በኩል አዲስ ሥርዓት መዘርጋት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት የሚሆን አዲስ የፖለቲካ ባህል መፍጠር።

ባህሉ አስቀድሞ ቢዘጋጅ ኖሮ መንገዱን ቀና ባደረገው ነበር። ልክ በለሰለሰ እርሻ እንደሚዘራ ምርጥ ዘር ይሆንልን ነበር። የሆነነው ግን እርሻውንም ማስተካከል፣ ምርጥ ዘሩንም ማምጣት እንደተገደደው ገበሬ ነው። ይህ ገበሬ በተስተካከለ እርሻ ላይ ቢዘራ ኖሮ መሬቱን በማስተካከል የሚወስደውን ጊዜና፣ ከመሬቱ ጋር የሚያደርገው ትግል የሚፈጥረውን ውጣ ውረድ ይቀንስለት ነበር። አማራጩ እያስተካከሉ መዝራት ነው።

በማኅበረሰቡ ዘንድ ሰፊ መሠረት ያልጣለ የለውጥ አቅጣጫና አስተሳሰብ የለውጥ እንቅፋቶችን በሙሉ ዐቅሙ ሊያስወግድ አይችልም። የማይታለፉ ቀይ መሥመሮችን በጉልህ ማሥመርም በራሱ በቂ አይደለም። አዲሱ ለውጥ እውን ሊሆን የሚችለው በሁሉም መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የጠራ የለውጥ አመለካከትና አስተሳሰብ ስንይዝ ብቻ ነው። በዚያን ጊዜ በአዲሱ የለውጥ አራማጆችና በትናንት ላይ ተቸንክረው በቀሩት ቡድኖች መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት እንዲሠመርበትና ነጥሮ እንዲወጣ ማድረግ ይቻላል። የተለያዩ

አመለካከቶችን በሐሳብ ልዕልና፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አሟግቶ በመርታትና በመረታት ራስን ወደ ለውጥ አቅጣጫ መመለስ፣ ሀገርንም ወደ ተፈለገው የለውጥ ምኅዳር ማስገባት ይቻላል። ያኔ ነው አፋችንን ሞልተን “እኛ የአባቶቻችንና የእናቶቻችን ልጆች ነን፤ ጠቢብነታችን ድንጋይ በድንጋይ ላይ ከማስተዛዘል አልፎ ሀገርን ከመበታተን በርግጠኝነት ያድናል” የምንለው። ያኔ ነው በፍቅር ተደምረን፣ በይቅርታ የምንሻገረው።

## *ብረሳሽ ቀኜ...*

## *የመደመር ቀንና የሰኔ 16ቱ አደጋ ትውስታ*

በመኖሪያ ቤቴ የጥናት ክፍል ውስጥ ቆም ብዬ በቀጣዩ ቀን የአዲስ አበባ ሕዝብ ባዘጋጀው ሕዝባዊ ሰልፍ ላይ ስለማደርገው ንግግር አብሰለስላለሁ። የጥናት ክፍሌ በር በቀስታ ተከፈተ። የመጨረሻ ልጄ ወደ ክፍሉ ዘለቀች። በቀጥታ ወደቆምኩበት በመምጣት እግሬ ላይ ተጠመጠመች። እርሷ በተማጽኖ እግሬን አቅፋ ሽቅብ ስትመለከተኝ እኔ ደግሞ በመገረም ቁልቁል በስስት ሳያት ዐይኖቻችን ተገጣጠሙ:: አቅፌ ግንባሯን ሳምኳት። የያዝኩትን ወረቀት ጠረጴዛው ላይ ጣል አድረግኩት። እጄን እየጎተተችኝ እሷ ከፊት እኔ ከኋላ ሆነን ባለቤቴ ወደተቀመጠችበት ሳሎን አመራን። ከባለቤቴ ጎን ሶፋው ላይ ከመቀመጤ፤"አባቢ ምን እየሠራህ ነው?" አለችኝ። ፀጉሯን ዳበስ ዳበስ እያደረግሁ "ነገ ብዙ ሰዎች የሚሰበሰቡበት ትልቅ ሰልፍ አለ… እዚያ ላይ ለሰዎቹ የምናገረውን ንግግር እያዘጋጀሁ ነው።"

"እንዴ… ንግግር ይዘጋጃል እንዴ?… ለምን ዝም ብለህ አትነግራቸውም?" ግራ በመጋባት ቆንጆዬ ዐይኖቿን ጠበብ ሰፋ እያደረገች አስተዋለችኝ። "ቆይ ደሞ ለምን ሌላ ሰው አይነግራቸውም?… አንተ ሁል ጊዜ መሥራት ብቻ ነው እንዴ? መቼ ነው ከኛ ጋር የምትጫወተው?" ስትል ቅሬታ አዘል አስተያየቷን አከለች። ከጎበዝ ጋዜጠኛ ጥያቄዎች የበለጠ የሚያስጨንቁኝ የእርሷ ጥያቄዎች ናቸው። ምን ብዬ እንደምመልስ? እንዴት ብዬ እንደማስረዳት? እቸገራለሁ። ደግነቱ ጥያቄውን አጠንክራ አትገፋበትም። መለስ ብላ ብርታት የሚሆነኝን ፍቅር አስታጥቃኝ ትሄዳለች። አንገቴ ውስጥ ተወሽቃ እንደምትወደኝ ስትነግረኝ በአዲስ ጉልበት እሞላለሁ።

በዚህም ዕለት የተደገመው ትዕይንት ይሄው ነበር። ልጄን አስተኝቼ ከተመለስኩ በኋላ ከባለቤቴ ጋር ስለየውሏችን ስናወራ ጥቂት ቆየን። አጭር ጸሎት ካደረስን በኋላ ባለቤቴ ወደ መኝታ ክፍል እኔ ደግሞ ወደ ጥናት ክፍሌ ተመለስኩ።

ልጄ የናፈቀችኝን ያህል ልታገኘኝ ሳትችል ቀርታ ተሰናብታኛለች። ባለቤቴም ቢሆን የተለየ ቸርነትና ልግስና አልገጠማትም። ውስብስብና ሥር የሰደዱ ችግሮች እጅ ተወርች ያሰሯት ድኻ ሀገር መሪ መሆን ፈተና ነው። ለችግሮቹ መፍትሔ ለማስገኘት ቅን ልቡና ብቻ በቂ አይደለም። ሰፊ ጥናትና ትንተና ብሎም ሀብት ማሰባሰብን ይሻል። ከዚህ የተሻለ ሌላ አማራጭ የለም። እንደ ቀድሞዎቹ መሪዎቻችን ከዙፋን ይልቅ ኮርቻ ላይ የምንቀመጥበትን ቀናት ማብዛት መፍትሔ አያስገኝም። ይልቁንም በዙሪያ ያለውን ሀብት አሟጦ ከማሰባሰብ በተጨማሪ ጥቂት ከጓደኛ፣ ከልጅ፣ ጥቂት ከሚስትና ከወላጅ ጊዜ መቀነስንም ይጠይቃል።

በጠረጴዛው ላይ ተደራርበው የተቀመጡትን ወረቀቶች ሳገላብጥ መቼ እንደጫርኩት የማላስታውሰው አንስድ ማስታወሻ ዓይኔን ሳበው። በወረቀቱ አናት ላይ እንዲህ የሚል ጥያቄ ደምቆ ተጽፏል።

## *"ሀገር ምንድን ነው?"*

ከጥያቄው ሥር ደግሞ፤ "ሀገሬ ለኔ፡- በትናንት ውስጥ የወገንና የቤተሰቦቼ መኖሪያ ነበረች። በዛሬ ውስጥ ደግሞ የልጆቼ ቤት ናት። ሀገሬ ትናንትና ዛሬ ብቻ አይደለችም። ነገ ልጆቼን የምታቅፈውና ፍቅር የምትመግባቸው ኢትዮጵያ ነች። ወገኖቼም ልክ እንደኔ የኔን ደስታና ተስፋ በእኩልነት ይጋራሉ ብዬ አምናለሁ።" የሚል ማብራሪያ ታክሎበታል።

በጥያቄ የታጀበና እንደ ባቡር ፉርጎ የተቀጣጠለ የሐሳብ መንኮራኩር በቆምኩበት ለአፍታ ይዞኝ ጭልጥ አለ። ደራሲ ከበደ ሚካኤል ታሪክና ምሳሌ በሚሉት መጽሐፎቻቸው የመጀመሪያ ገጾች አካባቢ ላይ ‹‹ሀገር በታሪክ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በልማድ፣ በተስፋ፣ በደስታና በመከራ ተሳስሮ የሚኖር አንድ ወገን የሆነ ሕዝብ የሚኖርበት የዓለም ክፍል ነው በማለት አስፍረዋል። በእኔ እምነት ደግሞ ሀገሬን የማየው ልክ እንደ አንድ ትልቅ ቤተሰብ ነው። ብዙ ሕፃናትና ወጣቶች፣ ጎልማሳዎችና አዛውንቶች ያሉባት። ድኾች ከሀብታሞች በዝተው የሚኖሩባት። ገጠሬው ከተሜውን ከብቦ የሚያድርባት። ወታደሩ ዳር ድንበር ለማስከበር ሕይወቱን፣ ገበሬው ምድሪቱ እህል እንድትሰጠው ጉልበቱን የሚያፈስባት። ሀገር ትልቅ ቤተሰብ ሆና ነው የምትታየኝ። ይሄንን እያሰብኩ አንድ የቆየ መዝሙር በውስጤ አንቃጨለ፡-

***"ውብ ሀገሬ... ውብ ሀገሬ... ውብ ሀገሬ...***
***ባንቺ እኮ ነው፣ መከበሬ... መከበሬ...***
***እናት አባት ቢሞት፣ በሀገር ይለቀሳል***
***እኅት ወንድም ቢሞት፣ በሀገር ይለቀሳል***
***ሀገር የሞተ እንደሁ ወዴት ይደረሳል?***
***ውብ ሀገሬ... ውብ ሀገሬ... ውብ ሀገሬ...***
***ባንቺ እኮ ነው፣ መከበሬ... መከበሬ..."***

በዘመን መካከል እንደ ሀገርና ሕዝብ ያስተናገድናቸው ታሪካዊ ክሥተቶች በግልጽ እንደሚያረጋግጡት ውዲቱ ሀገራችን በተወሳሰበ ችግርና መከራ፣ ሥር በሰደደ ድህነትና ኋላቀርነት ታጥራ የተተበተበች ምድር ናት። ይህን እውነት መረዳት በራሱ የሚፈጥረው ሕመም ጥልቅ ነው። ነገር ግን ለመሪ መታመም ብቻ በቂ አይደለም። ሕመሙን ወደ መፍትሔ አማራጮች በመቀየር ውጤታማ የሆኑትን ለይቶ መረዳትን ይጠይቃል።

ዋናው የመሪነት ሐላፊነት ደግሞ በቅድሚያ ቅደም ተከተል መሠረት ሕዝብን አስተባብሮ፣ አነቃንቆና መርቶ

መፍትሔዎቹን ወደ ተግባር በመቀየርና በማስቀየር ወደ ውጤት ማምራት ነው። የሀገርን ሕመም ከመታመም በላይ ማከሙ ይከብዳል። ይህ ሀገርን የማከም ሐላፊነት የማስተባበርና የመምራት ሸክም በዋናነት በመሪዎች ትከሻ ላይ እንደሚወድቅ የታወቀ ነው። በማከምም መሪው ተሳትፎ ያደርጋል። መሪው ከደከመ ወይ ችላ ካለ ሕመሙ ይባባሳል ወይም ቁስሉ አመርቅዞ በዘላቂነት የማይሽር ነቀርሳ ሊፈጥርም ይችላል። መሪው ከጠነከረና በዙሪያው ያሉት ሰዎች መልካም ትብብራቸው ካልጎደለበት ሕመሙን ወደ ጤና፣ ስቃዩን ወደ ደስታ፣ ፈተናውን ወደ ድል በመለወጥ መልካም ውጤት ሊያስመዘግብ ይችላል። ሕክምናው ቤተሰብን፣ ሕዝብንና ሀገርን ሁሉ የሚያካትት በመሆኑ ውስብስብነቱ ከፍተኛ፣ ተግዳሮቱም ጠንካራ ይሆንበታል።

ሀገርን አክሞ በማዳን ሂደት ውስጥ አልጋ በአልጋ የሆነ ነገር የለም። ይልቁንም መፍትሔ የሌለው ችግር፣ የማይታለፍ መከራም እንደሌለ በጥልቅ ማመንን ይጠይቃል። በትኩረት ቅደም ተከተል መሠረት እየወጋ የሚያድን መርፌ፣ እየቆረጠ የሚያሽር ቀዶ ሕክምና ማካሄድ ይጠበቅበታል። በዚህ ውስጥ ሁሉ ግን የሚሰራውን ሥራ ሁሉ መዳንን ግብ አድርጎ፣ ትኩረትን አሰባብስቦ ሕክምናውን መምራት ይገባል። በሕክምናው ሂደትም የራስን ግላዊ ሕመም ዋጥ አድርጎ በመያዝ ቅድሚያን ለሀገር መስጠት ያሻል። መሪው በሀገሩ ስቃይ አብሮ ቢታመምም ችሎ የሚቀደደውን ለመቅደድ፣ የሚቆረጠውን ለመቁረጥ፣ የሚጣለውን ለመጣልና የሚሰፋውን ለመስፋት ድፍረት ብቻ ሳይሆን ጥበብንም መላበስ ያስፈልገዋል። በአንድ ጀንበር ተነሥቶ ሰማይ መንካት፣ በአንድ ሌት ወርዶ መቀመቅ መርገጥ አይቻልም። መነሣትም ሆነ መውደቅ፣ መታመምም ሆነ መዳን የአንድ ዕለት ክንውን ሳይሆን የጊዜ፣ የሂደትና የተግባር ድምር ውጤት ነው። በጡብ ላይ ጡብ በመደረብ ግንብ መፍጠር እንደሚቻል ማመንን ይጠይቃል። የማያቋርጥ የውኃ ጠብታ ድንጋይ መቆርቆሩን መረዳትና መቀበል ያስፈልጋል።

መደመርን የአዲሱ ሀገራዊ ለውጥ መሪ እሳቤ በማድረግ፣ እኔም የታመመች ሀገሬን ለማከም ፈጣሪ ብልኀትን ከልበ ሙሉነት ጋር አጣምሮ እንዲሰጠኝ ካለማቋረጥ ጸሎት አደርሳለሁ። ስለ እኔና አብረውኝ በዚህ ሥራ ስለተጠመዱ ብዙ ሀገር ወዳድ ወገኖቻችን ለሚጸልዩልንም ትልቅ ክብርና ምስጋና አለኝ። በዚህ ምሽት ብርታት ሰጥቶ፣ ካለአንዳች መሰላቸትና ድካም በነገው ሕዝባዊ ሰልፍ ላይ የማደርገውን ንግግር አዘጋጅቼ እንዳጠናቀቅ ያስቻለኝ ይህ በውስጤ የተፈጠረው መነሣሣት ነበር።

በሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በመስቀል አደባባይ ሊደረግ የታሰበው ሕዝባዊ ሰልፍ ዓላማው ማበርታት ነበር። ከአዘጋጆቹ እንደተገለጠው በእኔና በሥራ ባልደረቦቼ በሀገር ደረጃ ተግባራዊ መደረግ የተጀመረው የለውጥ ጉዞ፣ በአጭር ጊዜያት ውስጥ ላመጧቸው መልካም ለውጦች፣ ዕውቅና ለመስጠትና ድጋፍንና አጋርነትን ለማረጋገጥ ያሰበ ነበር። ይሄን የተቀደሰ ዓላማ ለመደገፍና ከጎኑ ለመቆም ከስሜት ባሻገር እንደ ፖለቲካ ሰው በቂ ምክንያቶችም ነበሩ ብዬ አስባለሁ።

በሀገራችን የፖለቲካ ተቃውሞ ሰልፍ ካልሆነ በቀር የፖለቲካ ድጋፍ ሰልፍ በሕዝብ አዘጋጅነት ማካሄድ

የተለመደ አይደለም። ሕዝብ መንግሥቱን በግዳጅ ሲደግፍ ነው የኖረው። ከዚያም ካለፈ በጉርሻና ማባበያ ካልሆነ በቀር በራስ ነጻ ፈቃድና ተነሣሽነት የድጋፍ ሰላማዊ ሰልፍ የተከናወነበት ወቅትና ጊዜ ነበር ብሎ ለማለት ይቸግራል።

መንግሥታዊ ወኪሎች የሚገኙበት ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፎች ይደረጋሉ። የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጡ አካላት እንወክልሃለን የሚሉትን ሕዝብ አስገድደው ያስወጡታል። ይወጣል። ይህ ነው የኖረው ወግና ልማድ። ሊያደምጡት ሳይሆን ሊነግሩት። ፕሮፓጋንዳቸውን ሊሰብኩት፣ ሊደነፉበትና ሊያስፈራሩት። ለዚህ ደግሞ በየአደባባዩ አየር ላይ ሰፍፈው የሚኖሩት የ<ይውደም> መፈክሮች ምስክሮች ናቸው።

ሰኔ ዓስራ ዓምስት ምሽቱን ብዙ ነገሮች በዓእምሮዬ ሲመላለሱ ነበር።ገና ሶስት ወር ያልሞላው የኃላፊነት ወንበር ሀገሪቱን ከዳር እስከ ዳር እንዲህ ማንቀሳቀሱ እንግዳ ነገር ነው።በውጭ የሚገሩ ወገኖቻችንን ማነቃቃቱና ከአፍሪካና ከዓለም አቀፍ መሪዎችና ሚዲያዎች ያገኘው ትኩረት ዕጹብ የሚያሰኝ ነው።ይህ ሁሉ ወደ አንዳች ታሪካዊ ምዕራፍ መሸጋገራችንን ያረጋገጠልኝ ማስረጃ ነበር።
ነገ አጋጣሚውን ተጠቅሞ ሕዝብን ለማድመጥ መገኘት ታሪክን የሚገለብጥ ነው። ይህ ምሽት እያንዳንዱ ሰዓት የዓመት ያህል በውስጡ ብዙ ክስተቶችና ዜናዎችን እየተሸከመ ያልፋል።በዚህ መሀል በደርግ ዘመን በግዳጂ ይከናወኑ ከነበሩ ሰልፎች ጋር በተያያዘ የሰማሁት አንድ አስገራሚ ፖለቲካዊ ቀልድ ታውሶኝ ፈገግ አልኩ።
መስከረም 2 ቀን 1969ዓ/ም የአብዮቱ በዓል በመስቀል አደባባይ ላይ በታላቅ ሕዝባዊ ሰልፍ እየተከበረ ነበር። በዋዜማው መስከረም አንድ ቀን የዘመን መለወጫ ቢሆንም።
የአዲስ አበባ ቀበሌዎቻቸውና ተመራጮቻቸው ግን ቀኑን ያሳለፉት በድምፅ ማጉያ ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ ለአቢዮቱ ያለውን ድጋፍ በሰልፍ እንዲያረጋግጥ በመቀስቀስና በዚህ ሕዝባዊ ሰልፍ ላይ ያልተገኘ ነዋሪ የአቢዮቱ ግንባር ቀደም ጠላትና የአድኅሮት ኃይላት ተባባሪ መሆኑ ታውቆ ርምጃ እንደሚወሰድበት በማስጠንቀቅ ነበር። በዚህ መሰረት በዓሥራ ዓንድ ሰዓት የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በየቀበሌዎቻቸው ቅጥር ግቢ ተገኙ። ስማቸውን በማስመዝገብ ለዕለቱ የተዘጋጀውን መፈክር በማንገብ ወደ አቢዮት አደባባይ አመሩ።በዚህ መሀል አንድ የሰከረ ጎልማሳ የመንግስት ሠራተኛ ለመሄድና ላለመሄድ አመነታ። ጠዋት ሊነጋጋ አካባቢ ከነስካሩ ከተቀመጠበት ወነወበር ተነስቶ ወደ ቀበሌው ጋር ያመራል።ለዕለቱ አስተባባሪ ስሙን አስመዝግቦ ምን ማድረግ እንደሚጠበቅበት ጠየቀ። ከቀበሌው ዓጥር ግቢ ውጭ በkሚ ዘንግና በሰሌዳ ላይ ተጽፈው ከተቀመጡት ወቅታዊ መፈክሮች መካከል አንዱን አንግቦ ሰልፈኞቹን መቀላቀል እንደሚች ተነገረው።
ሰካራሙ መፈክሩ ከተቀመጠበት ክምር አንድ መፈክር ማንሣት ትቶ ዞር ዞር እያለ ማማተር ጀመረ። ድንገትም ከመንገድ ባሻገር ካለው አጥር ግቢ አጠገብ ‹እዚህ ቤት ተናካሽ ውሻ በመኖሩ ተጠንቀቁ› የሚል ጹሑፍ የሠፈረበት ባለዘንግ ሰሌዳ አየ። ወደዚያው ራመድ አለና ማስታወቂያውን ነቅሎ ሰልፈኛውን ተቀላቀለ። አንዳንዶች እንዲያውም ሰሌዳው ላይ የሰፈረው ጹሑፍ 'መሸናት ክልክል ነው የሚል እንደነበር የሚገልጹም

አሉ።

ሰካራሙ ከቀበሌው ነዋሪ ሰልፈኛ ጋር በመሆን የነቀለውን መፈክር እንዳነገበ አብዮት አደባባይ ይደርሳል። አብዮት አደባባይ በተንቀሳቃሽ የመኪና ስቱዲዮ ፕሮግራሙን የሚያስተላልፈው የማስታወቂያ ሚኒስቴር ጋዜጠኛ፣ የአዲስ አበባ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ በአራቱም አቅጣጫ ወደ መስቀል አደባባይ እየገባ መሆኑን ይለፍፋል። በተጨማሪም ሰልፈኛው ካነገባቸው መፈክሮች መካከል ጥቂቶቹን በማተት፤ አስታጥቁን አታስጨርሱን! ዲሞን በዲሞትፎር! እዚህ ቤት ተናካሽ ውሻ በመኖሩ*.....

በዘመን መካከል ሕዝብ ተገዶ መውጣቱ ሳይበቃው ይፎከርበት ነበር። ሰልፈኛውን ማንም ላድምጥህ የሚለው አልነበረም። የነገው ሰልፍ ከዚህ የተለየ ነው። መንግሥት መናገር ብቻ ሳይሆን ሕዝብን የሚያደምጥበትና የሚሰማበት ነው። ይኽን አዲስ መንገድ ለሕዝብ ማሳወቅና ማረጋገጥ ለአዲሱ የለውጥ ኃይል እጅግ አስፈላጊ ነው። ጋንዲ ልታይ የምትሻውን ለውጥ ለማየት መጀመሪያ ራስህ ተለወጥ ይላል።

በሁለተኛ ደረጃ ሕዝባችን ወቀሳን ብቻ ሳይሆን የማመስገን ባህልን እንዲያጎለብት የነገው ሰልፍ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በተለይም የመደመር እሳቤ ዋና መርሕ የሆኑትን ማካተትና ማሳተፍ፣ የሐሳብ ልዩነትን በሰላማዊ መንገድ ለማስተናገድና መቻቻልን ለመፍጠር የራሱ ሚና ይኖረዋል።

በሦስተኛ ደረጃ ሊቀመጥ የሚችለው ዓላማና ግብ ለተሠራጨው መርዝ ማርከሻ መስጠት ነው። ለውጡ የአንድ አካባቢ ሕዝብና ብሔር ስብስብ ነው በማለት የመለያየት መርዙን ለሚያሠራጨው ቡድን ለውጡ ሕዝባዊ ድጋፍ ያለው መሆኑን የሚያረጋገጥ ነው። ሰልፉ የተደረገበት የሰኔ 16 ማለዳ ፍንትው ያለ ፀሐያማ ማለዳ ነበር። ሕዝቡ በቡድን በመሆን እየጨፈረና ራሱ የፈጠራቸውን መፈክሮች እየፈከረ ከየአቅጣጫው ወደ መስቀል አደባባይ መጉረፍ የጀመረው ገና ሰማዩ የአህያ ሆድ ሊመስል ነበር። ገና ከሰልፉ ቀን ቀድሞ የኔን ምስል ከመደመር ሐሳብ ጋር አጣምረው ያየዙ ቲሸርቶችን በየመንገዱ እየገዛ ሲዘጋጅ እንደ ነበር ሚዲያዎች ሲቀባበሉት ተመልክቼ ጥልቅ መገረም ፈጥሮብኛል። በዕለቱ ምን ለብሼ መውጣት እንዳለብኝ እስከ መጨረሻዋ ምሽት ድረስ ርግጠኛ አልነበርኩም።

በመጨረሻዋ ሰዓት የታላቁን የነጻነትና የዕርቀ ሰላም ምሳሌ የኔልሰን ማንዴላን ምስል መረጥኩ። የመጨረሻው ሰው ነጻ እስኪሆን ድረስ ማንም ሰው ነጻ አይደለም' የሚለው ተጠቃሽ ንግግራቸው የተከተበበትን ብሩህ አረንጓዴ ካናቴራ ቀለል ካለ አለባበስ ጋር አዋሕጄ ለመልበስ ወሰንኩ።

የሰኔ 16 ቀን 2010 ዓ.ም. ሰልፍ ሁላችንም ከጠበቅነው በላይ የሰዎችን ትኩረት የሳበ ነበር። የሰልፉ ጥሪ ከተደረገበትና ለዝግጅት ከተወሰደው ጊዜ አንጻር ይሄንን ያህል ሰው ይመጣል ብሎ የጠበቀ አልነበረም። ሰልፉ በዋናነት የተደረገው አዲሱን ለውጥና አመራር ለመደገፍ ቢሆንም በዘመናት የተከማቸውን ግፍ፣ በደልና አምባገነናዊ ጨቋኝ አገዛዝ ለመቃወም ወደ መሆን ያደላ ይመስል ነበር። መደመር የሚለው ፅንሰ ሐሳብ

ከልሂቅ እስከ ደቂቅ፣ ከከተማ እስከ ገጠር እንዲህ በየሰዉ ልብ ያቃጨለው፤ የመቀነስና የመከፋፈል፣ የመፈረካከስና የማነስ አደጋና ያስከተለው ዳፋ የታከተው ሕዝብ በመብዛቱ ይመስለኛል። አይደለም ዛሬ በከፍተኛው የሀገሪቱ መንበር ላይ ተቀምጬና የኢትዮጵያን ከባድ ሐላፊነት ተቀብዬ ይቅርና፣ ያኔ በወጣትነቴ ተራ ወታደር ሆኜም እኒህ ሁለቱን ጸጋዎች (ብልኀትና ልበ ሙሉነት) እንዳይጓደሉብኝ፣ ሀብት ንብረቶቼ እንዲሆኑ እፈልግ፣ ቀን ከሌትም እታገል ነበር።

ሰው በተሠማራበት ቦታ ሁሉ ነገሮችን የሚያከናውንበት ጥበብና ጥንቃቄ የተሞላበት ድፍረት ከሌለው፣ መልካም ነገሮችን ለመሥራት አይችልም ብዬ አምናለሁ:: በተቃራኒው በራሱና በሌሎች ላይ ታላቅ አደጋን ሊጋብዝ መቻሉንም ተጠራጥሬ አላውቅም። በአዲሱ የለውጥ ጎዳና ወደ ሐላፊነት ከመጣሁ ወዲህ ተግባራዊ ለማድረግ የጣርኳቸው ነገሮች ሁሉ ከዚህ የሰርክ እምነት ቃል ኪዳኔ የተቀዳ እንጂ ወቅቱ በድንገት የፈጠረው አልነበረም። ደግሞም ሕዝባችን ሐሳቤን ተረድቶ ከጎኔ ስለቆመልኝ እንጂ እንደ ቀደምት ገዢዎቻችን ፈቃዴን በተከሻው ላይ በጉልበት ለመጫን እንደምሞክር አስቦ ቢሸሽኝ ኖሮ አንዳችም ቁም ነገር ለመሥራት አይቻለኝም ነበር:: ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎኔ መሆኑን የገለጸበት የሰኔ 16ቱ ሰልፍ በሕይወቴ ትልቅ ስፍራ እንደያዘ እንደሚኖር አልጠራጠርም።

በሰልፉ ላይ የነበረው የሕዝቡ ስሜትና ከፊታቸው ላይ የሚረጨው ኃያል አዎንታዊ ኃይል የመደመርን ብርቱ ጉልበት ያረጋገጠልኝ ነበር። ሕዝባችን ሊያመሰግነንና አድናቆቱን ሊገልጽልን የወደደው ምንም አድርገንለት ሳይሆን ስላከበርነውና ስቃዩን ተረድተን የነጻነት ተስፋን ስለፈነጠቅንለት ብቻ ነበር። ንግግሬንም በዚሁ አቅጣጫ በመቃኘት ምስጋናውንና አድናቆቱን መልሼ ለሕዝቡ ለመስጠት በመወሰን የበለጠ ለመሥራት ቃል በመግባት ላይ ነበር ያተኮርኩት። ከጥቂት ሳምንታት በፊት ሕዝቡ በተስፋ መቁረጥና በቁጣ የተሞላ ነበረ። ዛሬ በተስፋና በብሩህ ልብ ወደፊት እየተለመ፣ ለታላቅ ሀገራዊ ራእይ እንዲህ በአንድ ተደምሮ አየሁት። ይህ በራሱ ለእኔ የኢትዮጵያን ትንሣኤ በዐይኔ በብሌኑ የማየት ያህል ነው። ይህ ትዕይንት ለዚህች ቀን ስንታገል ያሳለፍናቸውን ዕንቅልፍ አልባ ሌሊቶችና ማለቂያ የሌላቸው የትንቅንቅ ቀናት ፍሬ ቢስ ሆነው እንዳልቀሩ ምስክር ነበር።

በኃይልና በጉልበት ተገዶና ተረግጦ በመሸማቀቅ፣ በገዢዎቹ የተጣለበትን የግዴታ ቀንበር ለመሸከም ሊወጣ ከሚውተረተር ሕዝብ ይልቅ፣ በነጻ ፈቃዱ ተመርቶ ወደ ኅብረት የሚመጣ ሕዝብ በወራት ዕድሜ ውስጥ ተአምር ሊፈጥር መቻሉን ደጋግመን አይተናል። በታሪክ የምናውቃቸው የዐድዋ ዘመቻና ድል፤ የካራማራ አንጸባራቂ ተጋድሎና አሸናፊነት እንዲሁም በቅርቡ በ2009 ዓ.ም. የእሬቻ በዓል ሕዝባዊ ዐመፅ ላይ አይተን ያረጋገጥነው እውነት ይህ ነው። አሁንም ይህ የሰኔ ዓሥራ ስድስቱ ሰልፍ የዚሁ እውነት ታሪካዊ ነጸብራቅ ነው። ነጻነት የሚፈጥረውን ሕዝባዊ ኃይልና መነቃቃት ሌላ ምንም ነገር ሊፈጥረው አይችልም።

በሕይወት መንገዴ ሁሉ የዜጎችን መብትና ነጻነት ለማረጋገጥ ከመጣር አልቦዘንኩም። ሙሉ መብቱን ከእጁ ያስገባና ነጻነቱን የተቀዳጀ ሕዝብ፣ ወሰን የሌለው ዐቅምና ኃይል ባለቤት መሆኑ ግልጽ ነው። ከነጻነት በላይ

ለሰው ልጅ ሊኖረው የሚችል ጸጋ፤ ታግለንም ልናጎናጽፈው የምንችለው ምንም ሀብት የለም። ይህ ከልጅነቴ ጀምሮ ይዤው የመጣሁት ጠንካራ እምነቴ ብቻ ሳይሆን፣ ስታገልለትም የኖርኩት የሕይወቴ አንኳር መርሕም ነው።

ይኸ መርሕና እምነት በንድፈ ሐሳብ ብቻ ተቀብዬ የማልፈው አይደለም። በተግባርም ትክክለኛ መሆኑን ያረጋገጥኩት ሐቅ ነው።ሰው ነጻነት ካለው፣ በውስጡ የያዛቸውን ረቂቅ የሐሳብ ሀብቶችም ይሁን በዙሪያው ያሉትን ማኅበራዊና ቁሳዊ ጥሪቶች ባለቤት ለመሆን የሚያግደው አንዳች ኃይል የለም። በሰልፉ ላይ የተገኙ ሕፃናትና አዛውንት፣ ሴቶችና ወንዶች፣ ወጣቶችና ጎልማሶች በአንድነት ድምፅ የመደመርን ስሌት በተግባራዊ ኅብር ለትዕይንት አበቁት። ቋንቋና ዘር፣ ሃይማኖትና የፖለቲካ አመለካከት ሰዎችን የመለያየት ዐቅም አልነበረውም። የትምህርት ደረጃውንና የኢኮኖሚ ከፍታውን የሚያስብ ከቶ አልነበረም። በመደመር ሰዎች ራሳቸውን በመሆን ከሌላው ጋር ተጋምደው፣ በአንድነት ዜማ እየተመሩ ይተሙ ነበር።

“እናት ሀገር... ኢትዮጵያ" የሚለው ዜማ ከግለሰቦችና ከቡድኖች ፍላጎትና መፈክር ይልቅ ጎልቶ ያስተጋባ ነበር። አምስቱ ወይም ስድስቱ የክራር ጅማቶች እያንዳንዳቸው በተናጠል የየራሳቸው የተቃኘ ልዩ ድምፅ ቢኖራቸውም፣ ከሌሎቹ ተነጥለው የሚያወጡት ድምፅ ግን ከተደጋጋሚ ባዶ ጩኸትነት የዘለለ ሊሆን አይችልም: "በክራር አናጋሪ ጣቶች ሲነካኩ ግን ቀልብን መስለብ የሚችል ኅብረ ዜማ ይፈጥራሉ። ከፍ ካለው በገና ድርድር ክሮች የሚወጣው ድምፀት ደግሞ መንፈስን በአርምሞ የሚሞላ ዜማ ያመነጫል። በባለሞያ ተከሽኖ ሲቀርብ እጅ አስቆርጣሚ የተባለው ወጥ፣ የተወጠወጠበትን ንጥረ ነገሮች በተናጠል ብንቀምሳቸው ጣዕም የለሽ፣ መራርና ጎምዛዥ፣ ወይም ደግሞ አቃጣይና አንገሽጋሽ መሆናቸው አይቀርም። ልዩ ልዩ ጣዕም፣ ድምፅ፣ ቅላጼ፣ መልክና ደርዝ ብንይዝም ስንደመር ውብ ኅብረ ማንነት ልንፈጥር እንችላለን። በዕለቱ ሕዝቡ ሁሉ በአንድ ተደምሮ ሲተምና ሲያዜምም እንዲሁ ነበር።

መደመር መለያየትን የማይሰብክ፣ ልዩነትና አንድ ዓይነትነትን የማያስገድድ አንድነት ነው። በሁሉም ነገራቸው አንድ ዓይነት የሆኑ አንድ ሺሕ ጡቦች በአንድ ስፍራ ቢቆለሉ የማንንም ቀልብ አይስቡም፤ ለማንም መኖሪያ ሊሆኑ አይችሉም። ተሰናስለውና ተሰድረው ቤት ካልሆኑ በቀር፣ ጡቦች ፋይዳ አይኖራቸውም። አንድ ሺሕ ልዩ ልዩ ነገሮች ሥምረትና ፍሰት ፈጥረው ሲታዩ ግን የሚኖራቸው ኅብርና ተግባር፣ ልዩነትና ተግባቦት የተመልካች ቀልብን ሰቅዞ፣ ስሜትን አፍዝዞ የሚይዝ ውበት ይሆናል።

በሺሕ የሚቆጠሩ ሰዎች በተሰበሰቡበት ሥፍራ ብዙ ጊዜ ንግግር አድርጌ ዐውቃለሁ። የሰኔ ዓሥራ ስድስቱ ግን ፍርሃትና ተስፋ፣ ጭንቀትና ደስታ የተቀየጡበት ድብልቅልቅ ስሜት አጭሮብኝ ነበር። ይሄንን ድብልቅልቅ ስሜት ይዤ ንግግር ለማድረግ መድረክ ላይ መውጣት ነበረብኝ። ጠጠር ቢጣል መሬት አያርፍም። ሰልፈኛው እንደ ጤፍ ነዶ ችምችም ብሎ መስቀል አደባባይ ላይ ከትሟል።

ለለዉጡ ኃይል፤ የወደፊቷን ኢትዮጵያ የሚያሳይ ትንታግ ስሜት ያወጣ ነበር። ለጸሎት እንደቆመ አስቀዳሽ ጸጥ ብሎ ንግግሩን ሲያዳምጥ፣ ከተናጋሪ ይልቅ ሕዝቡ በዝምታው ውስጥ ይናገር ነበር። የእኔን ንግግር ሕዝቡ፤ የሕዝቡንም ዝምታ እኔ እያዳመጥን ንግግሩ አለቀ። ንግግሬን ጨርሼ ከመድረክ ከወረድኩ በኋላ በተዘጋጀልን ወንበር ላይ ተቀምጠን የዝግጅቱ አጋፋሪ የመሸጋገሪያ ሐሳቦችን እያስተላለፈ እያለ ነበር፤ 'ደ--ግ--ው… ፍንዳታ' የሚል ድምፅ የሰማነው።

በብዙ ምክንያቶች ፍንዳታ ይሆናል ብሎ ያሰበ ማንም አልነበረም። አብዛኞቻችን ድምፁ ወደተሰማበት አቅጣጫ ዞርን። ፍንዳታው በፍጹም ቦምብ አይመስልም ነበር። እሸት በቆሎ ሲጠበስ የሚያወጣውን ዓይነት የታፈነ <ዱሽ!> የሚል ድምፅ ነበረው። ቦምብ መሆኑን በፍጹም ማናችንም አልጠረጠርንም። ከመቀመጫችን ተነሥተን ነገሩን ለማየት ስንሞክር፣ ወዲያው ከግራና ከቀኝ የመጡት የደኅንነት ሠራተኞች አፋፍሰው ከመድረኩ ላይ ይዘውን ወረዱ። መሆን የሌለበት አሳዛኝ ነገር መፈጠሩን ተረዳሁ፡ በውስጤ የተፈጠረውን ስሜት አሁንም ቢሆን ስም ልሰጠው መቻሌ ያጠራጥረኛል። የሚልዮኖች ተስፋ ድንገት ፊቴ ላይ ሲከለበስ፣ ከአፍታ በፊት አየሩን ሞልቶ የነበረው ተስፋ በቅፅበት ወደ ድንጋጤ ፈጣሪ ባሩድ ጢስ ሲለወጥ ምን ማለት እንዳለብኝ በሰዓቱ ሊከሠትልኝ አልቻለም።

ምን ያህል ሰው ተጎድቶ ይሆን? በእንደዚህ ዓይነት ውብ ትዕይንተ ሕዝብ፣ በሰላማዊ ወገን ላይ እንዴት ያለ ጨካኝ ልብ ነው ጥፋት ለመፈጸም እጁን የዘረጋው? ለምን? በርግጥ ይህ ነገር እውነት ነው? በማለት ብዙ ጥያቄዎችን በውስጤ ለራሴ ማቅረብ ቀጠልኩ። የውጭ ኃይል ሊሆን ይችላል የሚል ሐሳብ ድንገት ብልጭ ቢልብኝም አልመሰልህ አለኝ። ማን ሊሆን ይችላል? ለሚለው ጥያቄ መልሱን ለጊዜው ተወት በማድረግ ልቤን መለስ አደረግኩት። ከዚያ ይልቅ ክሥተቱ በሕዝቡ ላይ የሚፈጥረው የመሸበርና የቁጣ ስሜት የበለጠ ጥፋት እንዳያደርስ ታላቅ ሥጋት ገባኝ። <ማንኛውም ድርጊት እኩልና ተቃራኒ የሆነ ምላሽ አለው> እንደሚባለው።

ሕዝቡን ማረጋጋትና ከደረሰው የክፋትና የጥፋት አፍራሽ መልእክት በላይ መሆናችንን ማሳየት ነበረብኝ። ውስጤ በበርካታ ጥያቄዎች እንደተሞላ ቢሆንም፣ ሕዝቡ በድንጋጤው ውስጥም ሆኖም የእኔ ደኅንነት አሥግቶት በተለያዩ መንገዶች እየጠየቀ ነበር። ሙሉ መርሐ ግብሩ በተለያዩ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች በቀጥታ እየተላላፈ ሳለ የተፈጸመ በመሆኑ፣ በትዕይንተ ሕዝቡ ለነበረው ታዳሚ ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያውያን መልእክት ማስተላለፍ ነበረብኝ።

በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች በተሰባሰቡበት መሐል የፈነዳ ቦምብ ምን ያህል ሰው ሕይወት ቀጥፎ፣ አካል አጉድሎ ይሆን? ምን ያክሉስ በድንጋጤ ብዛት በመገፋፋት ተረጋግጦ ይሆን? ገና የለውጥ ተስፋ አየን ብለው ደስታቸውን ሊገልጹ በመውጣታቸው በእሳት ይቀጡ? በጥያቄ ትርምስምስ ውስጤ ተጉላላ። ለራሴ ተረጋግቼ ሕዝቡን ማረጋጋት ነበረብኝ። የመሪነት አንዱ ሐላፊነት የግል ስሜትን ዋጥ አድርጎ ሕዝብን ማረጋጋት ነው።

በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብዬ በደረሰው አደጋ የተሰማኝን የልብ ስብራት ገለጽኩኝ። ሕዝቡ ባለበት እንዲረጋጋ፣ አስፈላጊውን ድጋፍ በጸሎትና በሌሎችም መንገዶች እንዲገልጽ፣ በየኩርባው የሚያጋጥሙን ዕንቅፋቶች ቢኖሩም እንኳ ከጉዟችን እንደማያደናቅፉንና የለውጡን ከፍታ ወደ ታች ለመጎተት የሚሹ ኃይሎች የእነሱን ስልት እንድንከተል ሊያደርጉን እንደማይገባ ገለጽኩ።

በቀጣይ ማጣራት የሚደረስበት ቢሆንም፣ ወንጀሉ የተፈጸመው በተደራጀና ልምድ ባለው ቡድን መሆኑን ከግምት በማስገባት፣ ምርመራው በጥንቃቄ መካሄድ አለበት። ለዚህም በአሜሪካ የፌዴራል ምርመራ ቢሮ /FBI/ ባለሞያዎች በመታገዝ ጭምር ምርመራው እንዲካሄድ ድጋፍ መጠየቅ ተገቢ አቅጣጫ መሆኑ ተሰምቶኛል። በደረሰው ፍንዳታ የተጎዱ ሰዎች መኖራቸውን ስሰማ ልቤ በሐዘን ተሰበረ። የጠፋ የሰው ሕይወት መኖሩ ደግሞ የማይጠፋ ጠባሳን በልቤ ላይ መተዉ አልቀረም። ሰላምን ብሎ ለሰላም እየዘመረ በሰላም ከቤቱ የወጣ ሰው በወጣበት ሲቀር ከምንም በላይ ልብን ያደማል።
ፍንዳታው ሊያደርስ ይችል የነበረውን የአደጋ ግዝፈት ሳስበው ይበልጥ ዘገነነኝ። በኋላ የተገኘ መረጃ እንዳረጋገጠው፣ በአጠቃላይ 2 ሰው መሞቱን እና ከ63 ሰው በላይ ከባድ እና ቀላል የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን የጤና ሚኒስቴር ገለጠ።

ክሥተቱ የመደመርን ሁለት ገጽታዎች በጉልህ አስተምሮኝ አልፏል። የነጻነትን ጣፋጭ ጣዕምና መራራ ዋጋ በአንድ ቀን በአንድ መድረክ ላይ ያየሁባት ቀን ነበረች። እያንዳንዱ ቀን በውስጡ በብርሃን የታጀበን ቀንና በጽልመት የተዋጠን ሌሊት እንደሚይዝ፣ ይህችም ቀን የተስፋ ብርሃንና የጥፋት ጽልመት ፊት ለፊት አንገት ላንገት ተናንቀው ያለፉባት ዕለት ናትና ሁልጊዜም በውስጤ ትኖራለች።

ከምንም በላይ ቦምብ ሊወረወር መሆኑን ተመልክቶ ለሕይወቱ ሳይሳሳ የሚቀልብ ደፋር ወጣት ያየሁበትን ያንን ቅጽበት መቼም አልረሳውም። ይህንን አስደናቂ ጀግንነት ፈጽሞ የተሰዋው ወጣት ቡሳ ጋዲሳ ሩዳ የሚባል ሲሆን የምዕራብ ወለጋ ልጅ ነው። ሰዎችን ከሞት ሊያድን ሞትን በጸጋ በመቀበል ክርስቶስ ቀዳሚ ተጠቃሽ እንደሆነ ይታወቃል። ወጣቱ ቡሳ ያን ክርስቶሳዊ ቤዛነት በአደባባይ አሳየ። ለካስ ይህችም ሀገር የሕዝብን ሕይወት በሕይወቱ የሚታደግ ጀግና መውለዷን አላቆመችም። ራሱን ለሀገሩና ለወገኑ አሳልፎ የሚሰጥ ቤዛ። መደመር ለማይዋጥላቸው የነጻነት ጠላቶች የሰው ሕይወት ርካሽ ነው። ለእነርሱ ያልሆነ ነገር ሁሉ ቢወድም ግድ የላቸውም። ውድ ከሆነው የሰው ክቡር ሕይወት ይልቅ ጥቅማቸውን ያስቀድማሉ። ያቺ ቀን ራሳቸውን ለሀገራቸውን የሚሠዉ ብቻ ሳይሆኑ፤ ሀገራቸውን ለራሳቸው ጥቅም የሚሠዉ መኖራቸውንም አይተንበታል።

ትልቁ ቁም ነገር እውነተኛ ነጻነት ማንም ለማንም በችሮታ የሚሰጠውና ሲፈልግ ደግሞ የሚወርሰው ሸቀጥ አለመሆኑ ነው።እውነተኛ ነጻነት ፈጣሪ በእያንዳንዱ ሰው ልቡና ውስጥ ያስቀመጠው፣ ሰው በመሆናችን ብቻ የታደልነው፣ በማን ሊገሰስ የማይችል ጸጋና መብት ነው።

ሕዝባችን ጥንታዊና ዘመናትን የዘለቀ የነጻነትና የሥልጣኔ ባለቤት ተደርጎ በሌሎች ይቀናበታል። የተስፋ ጎሕና የነጻነት ትንሣኤ ፋና ተደርጎ ይታያል። ከውጭ መጥተው በወረሩት በሌሎች ኃይላት ሳይሆን፣ በላዩ በተሸከማቸው ገዥዎቹ ነጻነቱን ተቀምቶ የብልጽግና ተስፋው ተገፍፎ መኖሩ፣ እንደ እግር እሳት የሚያንገበግብ በደል ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሰው በፊት ድንጋይ ወቅሮ ዐለት ሰርስሮ ታሪኩን አኑሯል። ብራና ዳምጦ ቀለም በጥብጦ ጽፏል። በዐለትና በድንጋይ ላይ ታሪኩን ከትቧል። ውስጣዊ ነጻነቱና ሰብአዊ መብቱ ግን ሲረገጥ ኖሯል። የሀገሬ ሕዝብ፣ ጥንታዊ ጨቋኝ ገዢዎቹ ከጫኑበት የባርነት ቀንበር ለመላቀቅ ታግሎ እፎይ አልኩ ሲል፣ ዘመን ዕድል የሰጣቸው አዲሶቹ ገዥዎቹ ሌላ ዘመናዊ ባርነት ጭነውበት ቆይቷል።

ከድንጋይ እስከ ብራና፤ ከብራና እስከ ወረቀት ታሪኩንና ሐሳቡን በጽሑፍ ያስቀመጠ ጀግናው ኢትዮጵያዊ፤ በዘመነ ኢንተርኔት እንዳይጽፍ እጁ ታሰረ። እንዳይናገር አፉ ተለጎመ። መሄጃ እንዳጣ ውኃ በቀደዱለት ቦይ ብቻ እንዲነጉድ ተገደደ። ራሱን ወደ ሥልጣኔና ወደ ብልጽግና እንዳይወስድ በነጂ-መሪዎቹ እንደ እንስሳ ሲነዳ ማየት ልብን የሚያደማ ውጋት ነው። ከየትኛም ሕዝብ በፊት በዋርካ ሥር ተሰብስቦ የራሱን ጉዳይ በራሱ ሲወስን የነበረ ሕዝብ ነው። ነገር ግን ስለ ራሱና ስለቀየው እንኳን ተሰብስቦ መመካከርና መነጋገር እንዳይችል ተደረገ። ይህ ታላቅ ሕዝብ በዴሞክራሲና በሀገር ደኅንነት ስም በአፈና መረብ ተሸብቦና ተለጉሞ ሲኖር ከማየት የከፋ ስቃይና ክፉ ሕመም ሊኖር አይችልም። ይሄንን ለዘመናት ተጭኖ የኖረ የባርነት ቀንበር ከሕዝቡ ትከሻ በማውረድ፣ የግል ነጻነቱን ማረጋገጥ፣ ከማንም ኅሊና ያለው መሪ የሚጠበቅ ፍትሐዊ ቅን ርምጃ እንጂ እንደ ልዩ ችሮታ ተደርጎ ሊወሰድ ፈጽሞ አይገባም።

ሰኔ 16 ይህ ሕዝብ አዳማጭ መሪና አክባሪ አገልጋይ ካገኘ የሚፈልገውን ብቻ ሳይሆን የሚያስፈልገውንም የሚያውቅ መሆኑን ያስመሰከረባት ቀን ነበረች። በዕለቱ ሕይወታቸውንና አካላቸውን ያጡ ዜጎች መቼውንም ልንረሳቸው አንችልም። ቆስለው በየሆስፒታል የተኙ ወገኖቻችን ከደረሰባቸው ጉዳት ይልቅ የሀገራቸው ደኅንነትና እኔ ጉዳይ አስጨንቋቸው ሳይ፣ የተሸከምኩት ሐላፊነት ክብደት እስከ አጥንቴ ዘልቆ ተሰማኝ። በየሆስፒታሉ እነርሱን መጎብኘትና ተገቢውን ሕክምና እንዲያገኙ መደረጉን መከታተል ብቻ ሳይሆን እኔም ደም መስጠት ነበረብኝ። ሕዝብን ለማዳን እነርሱ ካፈሰሱት ደምና ከገበሩት ሕይወት አንጻር ሲመዘን ይሄን ማድረግ ከቁጥር የማይገባ ተግባር ቢሆንም፣ ሕዝብ እንደ ክብር ሲቆጥረው መመልከት በራሱ ትንግርት ሆኖብኛል።

ሰኔ 16 የመደመር ኅብረ ዝማሬ ያስደነበረውና የነጻነት ጮራ እብሪተኛ ዐይኑን ያጭበረበረው አውሬ በቀላሉ እጅ እንደማይሰጥ ፍንጭ የሰጠ ቀን ነው። አውሬው ቆስሏል፤ ግን ጨርሶ አልሞተም። ደግሞም በቀላሉም አይሞትም። ለዘመናት አፍኖ ያቆየው ፖለቲካዊ በደልና መረገጥ ድንገት ከላዩ ላይ ሲነሣለት፣ ልክ እንደ

በደሉ፣ ፍጹማዊ የሆነ ጭካኔና ሥርዓት አልበኝነት፣ እዚህም እዚያም ሊፈነዳ እንደሚችል መጠርጠሬ አልቀረም። ይዞ የኖረ ሰይጣን ሲለቅ አንዘፍዝፎ ነው እንዲሉ። የዘመናት ጨቋኝ አገዛዝና ለከት የለሽ በደል፣ በሕዝቡም ዘንድ ተመጣጣኝ ጥርጣሬን፣ ጥላቻን፣ ሲከፋም መገዳደልን ሊያስከትል እንደሚችል የሌሎች ሀገሮችም ያለፈ ተሞክሮ ያሳየናል። ከልክ በላይ የተወጠረ ጎማ ሲፈነዳና ታምቆና ታፍኖ የቆየ ክፍል ሲከፈት ከሚፈጠረው ውጥረት የሚወጣው ኃይል ጎጂ መሆኑ የሚጠበቅ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የአምባገነንነት ኢፍትሐዊ አየር ገለል ሲል በደቦ ፍርድ መተካቱ አስፈሪው ሐቅ ነው። ዓለም በሙሉ እያየ ሰው በቢላ ሲታረድ፣ በእሳት ነድዶ ወደ አመድነት ሲለወጥ፣ ከነነፍሱ ጭልጥ ካለ ገደል ሲወረወር፣ ሕግና ሥርዓት ያልያዘውን የሰው ልጅ ጭካኔና የግብተኝነት ፖለቲካ በየቦታው ሲፈለፈል ለማየት ችለናል።

አሰቃቂው የአፓርታይድ ሥርዓት ሲገረሰስ በኢንካታና በኤኤን.ሲ. መካከል የነበረው ጥላቻ አገረሸ። ደቡብ አፍሪካውያን ጎማ በአንገታቸው እየጠለቀ ከነ ነፍሳቸው በእሳት ተቃጠሉ። ለመቶ ዓመታት በአፓርታይድ ታስሮ የኖረው ሕዝብ ሽግግሩ በከፋ ጭካኔ ውስጥ እንዲያልፍ አስገድዶት ነበር።

ከሰኔ ዓሥራ ስድስቱ ትዕይንት በኋላ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እዚህም እዚያም የታዩት ከሥተቶችና ጥፋቶች አሳዛኝ ቢሆኑም የማይጠበቁ ግን አልነበሩም። ቢያንስ በቅርብ ዘመናት በሀገራችን የተፈጠረው መታፈንና ፍጹም አምባገነናዊ አመራር የፈጠረው ጫናና ብሶት ቀላል አልነበረም። የታፈነ ቁጣና ምሬት ራሱን የሚገልጽበትን ዕድል እየጠበቀ ነበር። በሕዝቦች ተጋድሎ አዲሱ አስተዳደር ከመጣ በኋላ እዚህም እዚያም የታዩት መጨካከንና መገዳደሎች፣ የዚህ ችግር ሁነኛ መገለጫዎች ናቸው:: በመራራ ጥላቻ የተነሣ ዜጎች በጭካኔ ተገድለዋል። ፈጣሪን የማያውቁና የማይፈሩ፣ እንስሳዊ ባሕርያቸውን ያላሸነፉ፣ ኋላ ቀርና ያልሠለጠኑ ሕዝቦች ከፈጸሙት የባሱ ጭካኔዎችን በአጭሩ ዕድሜያችን አይተናል።

የሰኔ አሥራ ስድስቱን ክሥተት በተመለከተ የቀረቡ የመጀመሪያ ደረጃ የምርመራ ሪፖርቶች እንዳመለከተቱት፣ ወንጀሉን ለመፈጸም በምክንያትነት የቀረቡት ሦስት ነበሩ። በኦሮሚያ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ አልመጣም (የሕዝቡ ጥያቄ አልተመለሰም)፣ ሰልፉን የጠራው ኢሕአዴግ ነው፣ እንዲሁም HR-128 የተባለውና በአሜሪካን ኮንግረስ የቀረበውን የውሳኔ ሐሳብ (Resolution) ሊያስቀር ስለሚችል ሰልፍ መካሄድ የለበትም፤ ስለዚህም በሕዝቡ መካከል ቦንብ በመወርወር ሰልፉ መበተን አለበት የሚሉ ነበሩ። በሌላም በኩል የኦሮሞ ተወላጆችን እጅ በመጠቀም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ጥቃት እንዲፈጸም በማድረግ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኦሮሞ ቢሆንም በኦሮሞ አይወደድም ለማስባል የታሰበ ነበር። በወንጀሉ የተሳተፉት ሁሉ እዚያ ምድብ ውስጥ መውደቃቸው ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የተዘራው ክፉ የጥላቻ በሽታ በየቦታው የቆሰቆሰው ግጭት፣ በመቶ ሺሕዎችና

በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወገኖቻችንን አፈናቅሎ በገዛ ሀገራቸው ባይተዋርና ስደተኛ አድርጓቸዋል። ሲዘራ የኖረው ዘረኝነትና ሌላውን የመፍራትና የመጥላት አባዜ፣ አፍርቶና ጎምዛዛ ፍሬ አጎምርቶ በተጨባጭ ልናየው በቅተናል። የሆነው ሁሉ ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳል እንደሚባለው ነው።

የተፈጠረውን እውነታ አምኖና ክፋቱን አውግዞ የተሻለውን ለመፍጠር ደፋ ቀና ከማለት ይልቅ፤ በዓለም ታሪክ ተፈጥሮ እንደማያውቅ ዱብ ዕዳ ክሥተት በመቁጠር መርበትበት ግን ተገቢ አይደለም። ከቀዶ ጥገና ሰመመን ሲነቃ ቁስሉ አመመኝ ያላቸውን ሕመምተኛ ቀዶ ጥገና ባታደርግ ኖሮኮ አያምህም ነበር ያሉትን ዓይነት ምክር የመከሩንም ነበሩ። የችግሮቹ የመነሻ ምክንያት ለውጡ እንዲመጣ ያደረጉት የተከማቹ የጥላቻና የግፍ ክምችቶች ናቸው። ነገሩን ከላይ ከላይ እያዩ ለውጡ የፈጠረው ዳፋ ነው ማለት ግን ከለውጡ በፊት ፍትሕና ሰላም፣ ፍቅርና እኩልነት የነበረ ለማስመሰል የሚሯሯጡ ኃይሎች ቅዠት ነው። ከእነርሱም በተጨማሪ የቅርቡንና የአሁኑን እንጂ የሩቁንና የኋላውን የዘነጉ ተላላ ሰዎች ሽውራራ እይታ ነው።

በዕለቱ በፖሊስ የጸጥታ አጠባበቅና ቁጥጥር ብሎም በፍተሻ ላይ ክፍተት እንደነበረ በምርመራ ተረጋግጧል። ፍተሻን አልፎ የገባ አንድ ቦንብ ፈንድቶ ጉዳት አድርሷል። አንድ ሌላ ቦንብ ደግሞ ሳይፈነዳ ተገኝቶ እንዲመክን ተደርጓል። ይህም በተለይ ቦንቦቹ በገቡበት አቅጣጫ ሐላፊነታቸውን ያልተወጡ የፖሊስ አባላት መኖራቸውን አመልክቷል። በአጠቃላይ የወንጀሉ አፈጻጸም ቀድሞ ታስቦ በዕቅድና በረቀቀ ሁኔታ የተፈጸመ በመሆኑ፣ ምርመራው ረጅም ጊዜ ወስዷል። በዚህ ሂደት የወንጀሉ ዋና አቀናባሪና መሪ አልተያዘም። ይህም በምርመራ ሥራው ላይ ዕንቅፋት ፈጥሯል።

ዐውቆ አጥፊዎቹን መከራ ያስተምራቸው። ባለማወቅና በስሜታዊነት በጥፋት ለተጠመዱት ግን አንገት የተሠራው አዙሮ ለማየት ነውና፣ የመጣንበትን ዘንግተን ወደ ባለ መቀመቅ መንደርደሩ _ አይገባም፤ _ ተመለሱ የሚል፤ የወዳጅ ምክራችንን እንለግሳለን። እንደዚህ ዓይነት ጥፋት ሁለት ተሸናፊዎችን እንጂ ማንንም አሸናፊ አድርጎ መፍጠር አይችልም። በሶሪያ፣ በሊቢያና በየመን የተከሠቱት የእርስ በርስ ጦርነቶች ለላይኛው አባባል ሁነኛ ማስረጃ ይሆናሉ። ከተፋላሚ ኃይሎቹ ጋር ሀገርና ሕዝብ ወድሟል፣ አብሮም ከሽፏል። በታሪክ አጋጣሚ ወርቃማ ዕድል በእጃችን መዳፍ ወስጥ ሲገባ ከሚያጠፋን ጽንፍ የረገጠ ጥላቻና ልዩነት ይልቅ፣ በፍቅር መደመርን በመምረጥ ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግን መንገድ መከተል ይኖርብናል። ሰው ዕድል ሲያገኝ ጥረት እንጂ ጥፋት ሊጨምር አይገባውም። በዕድሉ ላይ ጥፋት የሚጨምር ሁሉ የመጨረሻ ውጤቱ አጥፍቶ መጥፋት ነው። በዕድሉ ላይ ጥረት የሚጨምር ግን ውጤቱ ከብሮ ማክበር ይሆናል። የሀገራችን የመጀመሪያውን የመደመር ቀንና በዕለቱ የደረሰውን የሽብር ጥቃት ሲታሰብ፣ በቁጥር የላቅነውና የበዛነው ምርጫችን ፍቅርና ሰላም እንደ ነበር ታሪክ ምስክርነቱን ይሰጣል።

*“የቸገረው ዱቄት፣ ከንፋስ ይጋባል”*

*ርጥብ ሲጤስብን፣*

*ደረቅ ሲነድብን፣*

*በታላቅ ዝምታ፣ አይቻልን ችለን*

*ሳንበርድ ወይ ሳንፈላ፣ ለጉድ ተወዝተን*

*ጥንቱ ምድጃ ሥር፣ ይኼው ዛሬም አለን።*

በሕይወት ውስጥ ከፍላጎታችን ውጭ በኑሮ ተገፍተን የምንከውናቸው ተግባራት አሉ። ያለፈቃዱና ያለፍላጎቱ ከአዋራ ጋር የሚነፍስ ዱቄት፣ አፍ ኖሮት ስሜቱን መግለጽ ቢችል፣ እንዲህ ወይም እንዲያ ማለቱ አይቀርም። አንደኛውን ባሕሪውን ቀይሮ ከአዋራ አይደባለቅ ነገር፣ ተፈጥሮው የእህል ዘር ነው። አይለይ ነገር ነፋሱ ያለፈቃዱ ከአዋራ ደባልቆ ይገፋዋል። እኔም ልክ እንደዚህ ዱቄት በሁለት ጠንካራ የስሜት ጫፎች የመወጠር ክረት በውስጤ ይመላለስ ጀምሯል።

አዲሱ ለውጥ ከሱማሌ ክልል ከፍተኛ አመራሮችና አጫፋሪ ጓዶቻቸው የገጠመው ግድድር አፋጣኝ መፍትሔ እንደሚሻ ከተረዳን ውለን አድረናል። በሌላ በኩል ደግሞ ፈጥነን ያያያዝነው፣ ተረባርበን ያቀጣጠልነው ለውጥ ተመልሶ እንዳይዳፈን፣ በወጣነው ልክ እንዳንወርድ፣ በገነባነው ልክ እንዳናፈርስ፣ ጥንቃቄ የተሞላው ብልኀትና ዘዴ አስፈላጊ መሆኑንም ተገንዝበናል። በዚህም የተነሣ ተገደን ካልሆነ በቀር በምንም መልኩ ክልሉን ወደ ሁሉን አቀፍ ግጭት ሊመራ በሚችል አካሄድ ላለመምራት ለራሳችን ቃል ገብተናል። የተከተልነው አቅጣጫ ሁሉንም የሀገራችን ሕዝቦች የለውጡ ተጠቃሚና አካል ማድረግ ነበር።

በነደፍነው የግንኙነት ቅደም ተከተል መሠረት ወደተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመጓዝ የፍቅርና የይቅርታ ቃል መስበክ ስንጀምር፣ የመደመር ፍልስፍና ፋና ወጊ መሐንዲሶች ሆነን ስናስተምር ታላቅ ትኩረትና ቅድሚያ የሰጠነው ለዚሁ ለሱማሌ ብሔራዊ ክልል ነበር። በእርግጥ በወቅቱ የነበረው የክልሉ ርእሰ መስተዳደር የይቅርታን መንገድ ማየት የሚሻ ባለመሆኑ ምክንያት ለይቅርታ ሆነ ለመደመር ጥሪያችን ጆሮውን ከመስጠት ይልቅ በእኩይ ተግባሩ ገፋበት። ያም ሆኖ የሶማሌ ክልል ጉዳይን በተለየ እይታና የመፍትሔ መንገድ ማስተናገድ የሚጠይቅ ጂኦ ፖለቲካዊ እውነታና ልዩ ታሪካዊ መሠረት ከመሆኑ አኳያ፣ የላቀ ጥንቃቄ ማድረጋችን ግድ ይል ነበር።

በሀገራችን ምሥራቃዊ ክፍል በኩል ከጂቡቲ፣ ከሱማልያና ከኬንያ ጋር የሚዋሰነው የሶማሌ ክልላዊ መስተዳደር የበርካታ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መኖሪያ ነው። ከኦሮሚያና ከአፋር ክልል ሕዝቦች፣ ጋር

በመልከአ ምድር ጭምር ይዋሰናል። ክልሉና በውስጡ የሚኖሩ ሕዝቦች ላለፉት መቶ ዓመታት ምናልባትም ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ከጦርነት ተለይተው አያውቁም። በዚህ አካባቢ በየዓሥርና ሃያ ዓመታቱ እየተመላለሰ ሕዝቡን ከፍተኛ ችግር ይገጥመዋል። በወልወል በኩል ትንኮሳ ካደረገው የጣልያን ወራሪ ሠራዊት ጋር የተደረገውን ጦርነት ማንሣት እንችላለን። በ1969 ዓ.ም. ከጎረቤት ሀገር ሱማልያ በዚያድባሬ መንግሥት የተሰነዘረው የወረራ ጥቃት የፈጠረው ጥፋትና ያፈሰሰው ደም፣ አካባቢውን ምን ያህል ጎድቶት እንዳለፈ ለመገመት አስቸጋሪ አይሆንም።

በዚያ ላይ ከዐፄዎቹና ከደርግ  መንግሥት ወኪሎችም የተሰነዘሩ ተደጋጋሚ እንግልቶች ነበሩ። የኢሕአዴግ መግባትን ተከትሎ ክልሉ አንጻራዊ ሰላም ያገኘ ቢመስልም፣ የኋላ ኋላ ግን የክልሉን ሰላም የሚነሡ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ተከሥተዋል።

አንደኛው የፌዴራል መንግሥት በክልሉ ፖለቲከኞች ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ የክልሉን ሰላም በእጅጉ የተፈታተነ መሆኑ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከአጎራባች ሀገሮች ጋር የተያያዘ ነው። በአጎራባች ሀገሮች ውስጥ ነዋሪ የነበሩ የሱማሊያ ዜጎች በሀገራቸው የመንግሥት መዋቅር ስለፈረሰና ጽንፈኞች ስለተበራከቱ፣ ወደ ክልሉ ያለ ፈቃድ ገቡ። ይሄም በክልሉ ላይ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ ከፍተኛ ጫናን አሳድሯል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በቀይ ባሕር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከረ የመጣው ዓለም አቀፍ የኃያላን  ፉክክርና የሽብር ተጋላጭነት በማዕከላዊው  መንግሥት ዘንድ የሚፈጥረው ሥጋት አለ። ይህም ሥጋት በክልሉ አስተዳደር ላይ የሚከተለው አካሄድ ከሌሎች አካባቢዎች ለየት ያለና ጭቆና የተቀላቀለበት እንዲሆን አድርጎታል። ለዚህም የቀድሞው የክልሉ ፕሬዝዳንት አብዲ መሐመድ ዑመርና ቡድናቸው ወደፊት ገፍተው መምጣት በሕዝቡ ላይ የነበረውን የጭቆና ቀንበር አክብዶታል።

በሌላ አገላለጽ በአካባቢው የተንሰራፋው የመገንጠልና የሽብርተኝነት አደጋ፣ ከመደበኛ የመብት ጥያቄ ጋር ተሳስሮ መምጣቱ፣ የፌደራል መንግሥቱን ሥጋት እንዲጨምር ምክንያት ሆኗል። እንዲሁም በትጥቅ ትግል ጭምር የሚፋለመው የሶማሌ ነጻ አውጭ ግንባርና ሌሎች የመንግሥት ተቃዋሚዎች በተነጻጻሪ በዚያ አካባቢ እየተጠናከሩ መጥተዋል። በወቅቱ የፌደራል መንግሥቱን እያስተዳደረ ያለው አካል፣ የሀገሩን ሠርዶ ባገሩ በሬ› በሚል ፈሊጥ፣ በክልሉ የሚንቀሳቀሱትን እነዚህን ኃይሎች ለመጨፍለቅና በእጅ አዙር ለማስገበር በማሰብ፣ ፈላጭ ቆራጭ መሪዎችን ወደ ሥልጣን አመጣቸው።

በዚህ ሂደት በሕገ ወጥ የሥልጣን የበላይነትና ጠያቂ ባጣ አምባ ገነንነት የክልሉ ፕሬዝዳንት አብዲ መሐመድ ዑመር ቡድን ገንኖ ለመውጣት ቻለ። በዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ ‹በርታ! አበጀህ! ግፋበት የሚል እንጂ አንድም ሃይ ባይ አልነበረውም። አመራሩም ከላይ እስከታች በጥቅም መረብ ተሳሰረ። የክልሉ መሪም ለወታደራዊና ለደኅንነት አዛዦቹ ያለውን ፍጹም ታዛዥነት ለማሳየት በገዛ ሕዝቦቹ ላይ ጨከነ።

ለዘመናት አብረው የኖሩ የአጎራባች ሕዝቦችን ወደ ግጭት በመግፋት ቁጥራቸው ከአንድ ሚልዮን በላይ የሆኑ ዜጎች ያፈሩትን ሀብትና ንብረት ተቀሙ። ዜጎችን ከሚኖሩበት የሶማሌ ክልል በማፈናቀል ታሪክ ይቅር የማይለውን የግፍ ግፍ ተፈጸመ። ይህ በአመራሩ ይከናወን የነበረው ፀረ ሕዝብ ተግባር፣ አዲሱ የለውጥ አመራር ወደ ሥልጣን ከመጣ ወዲህ በተነጻጻሪ ቀንሶ ወደ ዕርቅና ሰላም ይሸጋገራል የሚል ተስፋ ነበር። ከክልሉ ይወጡ የነበሩ አስተማማኝ የሲቪልና ወታደራዊ ማስረጃዎች ግን እውነታው የተለየ መንገድና አቅጣጫ ተከትሎ መጓዙን ማመላከት ጀመሩ።

በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል በጅግጅጋ ከተማና በተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች የተፈጠሩትን የዐመፅ ተግባራት በመምራት ረገድ፣ የክልሉ የቀድሞ ፕሬዚዳንትና ቡድናቸው በቀጥታ እጃቸው ነበረበት። ከዚህም ባሻገር ዋነኛ አቀናባሪ በመሆንም በክልሉ ውስጥ የተለያዩ ወንጀሎችንና የሽብር ሥራዎችን ለማካሄድ የሚያስችሉ አደረጃጀትና ዕቅድ ማዘጋጀታቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎች በስፋት ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ።

ዕቅዱ የሚፈጸመው በተደራጀውና በዋናነት በክልሉ በጀት በሚተዳደረው ሄጎ› በሚል ስያሜ በሚጠራው ሕገ ወጥ የወጣት ቡድን ነበር። ቡድኑ ለጉዳትና ለዝርፊያ የሚያግዘውን ዐቅም እንዴት መገንባት እንደሚችል አማራጮች ተተንትነው ተቀምጠውለት ነበር። በትግበራ ወቅትም ተጎጂዎች ራሳቸውን መከላከል እንዳይችሉ በሚያስችል መልኩ ተወጥኖ፣ የጥፋት ቡድኑ ሕገ ወጥ ድርጊቱን ሲፈጽም የተሻለ ትጥቅ እንዲያገኝም ተደርጓል። ከዚህም በላይ የክልሉ ልዩ ኃይል ሽፋን እንዲሰጥ ተመቻችቷል። በክልሉ የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዋና አቀናባሪነት ተመርቶ ለሽብር ሥራ በመዘጋጀት ላይ የነበረው የሽብር ቡድን፣ ለዓላማው ማስፈጸሚያነት የተለያዩ የወንጀል ዓይነቶችን እንዲፈጽም አቅጣጫ ተቀምጦለታል። ይህም ብሔርንና ሃይማኖትን መሠረት ያደረገ የዘር ማጥፋት፣ አስገድዶ መድፈር፣ ከባድ ውንብድናና ዘረፋ ማካሄድ፣ የንብረት ማውደምና ማቃጠልን ያጠቃልላል።

በሰዓቱ መጠነ ሰፊና አስከፊ በሆነ ደረጃ ወንጀሎችን ለመፈጸም ዕቅድና የተግባር ልምምዶችን ማድረግ ተጀምሮም ነበር። በዚህ መልኩ ተደራጅቶ ለጥፋት በዝግጅት ላይ የነበረው ሄጎ የተባለው ሕገ ወጥ ቡድን፣ ሊያወድማቸው በዕቅድ የያዛቸውን ተቋማትና ኩባንያዎች ከሚገልጹ ጠቋሚ መረጃዎች ጋር፣ በወሳኝ ሰዓት በመንግሥት እጅ ውስጥ ወደቁ። ጉዳዩን ተከታትሎ ለፍርድ ለማብቃት፣ ከክልሉ የለውጥ ኃይሎች ጋር በመሆን፣ መንግሥት ከፍተኛ ምስጢራዊ ክትትሎችን ሌት ከቀን መሥራት ቀጠለ። ያም ሆኖ በምሥራቁ የሀገራችን ሰማይ ላይ ያንዣበበው የጥፋት ደመና እጅግ አስፈሪና አሳሳቢ ነበር።

በአዲሱ የለውጥ ጉዞ መቶ ቀናት ከመቆጠሩ በፊት፣ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ሰላምን ለማረጋገጥ ያደረግነው ርምጃ፣ ተስፋ ሰጪ ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ክብርና ሞገስን ያስገኘልን ነበር። ጎረቤት ከሆነው የኤርትራ ሕዝብ ጋር ማንም ያደነቀውን ዕርቅ ፈጥረናል። ይህንን ማድረግ የቻልን ሰዎች እኛው ራሳችን እዚሁ እርስ በርሳችን ብንጋጭና ጦርነት ብንጀምር ምን ያባላል? ደም የተፋሰሱ ደቡብ ሱዳናውያንን ሸምግለን

በሀገራቸው ዕርቅ ለማውረድ የቻልን ሰዎች፣ እርስ በርሳችን ደም ብንፋሰስ ያስታረቅናቸው ጎረቤቶቻችን ብቻ ሳይሆኑ የገዛ ሕዝባችንም ክፉኛ ይታዘበናል። የመንንና ኤርትራን ወደ ሰላሙ ጠረጴዛ ለማምጣት የቻልን ሰዎች፣ ዛሬ እርስ በርሳችን ብንታኮስ አፍሪካ ይንቀናል፤ ዓለምም ይሳለቅብናል።

በሆነ ባልሆነው ግጭት መጫርና ጦርነት መለኮስ ቀላል ነው። ከባዱ ጠብን አብርዶ፣ ተጋጪዎችን ከግጭት አፋፍ መልሶ፣ ወደ ሰላም ጠረጴዛ ማቅረብ ነው። መተኮስና መውረር ቀላል ነው። ፈተናው ተኩስ ከመከፈቱ በፊት ቆም ብሎ ማሰብ፣ ጦርነት ሊቀር የሚችልበትን ብልኀት መዘየዱ ላይ ነው።

በባድመና በዛላንበሳ በድንገት የተጀመረውን የሞት፣ የጥፋትና የጥላቻ ዝናብ አስቁመን በሰላም ጠረጴዛ ለመሰባሰብና ለዐይን ለመተያየት ከሃያ ዓመት በላይ ወስዶብናል።

አያት ቅድም አያቶቻችን የለኮሱትን እሳት እኛ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ዛሬም በማንደድና በመንደድ ላይ ነን። ዛሬ የምንተኩሰው ጥይት ለልጅ ልጆቻችን የመተላለቂያ ጦርነት ዘር እንደሚሆን እንዴት አልታየንም? ጦርነት ሁሉን ሊጎዳ እንጂ ከቶ ማንን ሊጠቀም ይችላል? በጦርነት ነጥብ ማስቆጠር ይቻል ይሆናል እንጂ ማንንም አሸናፊ አያደርግም። የለውጥ ጉዟችን በከፍተኛ የብልጽግና ግብ የተቃኘ፣ በመደመር መርሕ የተፈተነ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቅኝት ነው።

ይህ ሀገራዊ አጀንዳ በግል ጥቅም ከታወረና በዘረኝነት ከተጋረደ ወገን ጋር ከዚህ በላይ በአይጥና ድመት ድብብቆሽ ሊቀጥል አለመቻሉን ተረድቷል። በተለይም በከፍተኛው አመራር አስተባባሪነት፣ ከፍተኛ ግምት ያለውን በሚልዮን የሚቆጠር ብርና የመደለያ መሬት በመስጠት፣ ክልሉን ከኢትዮጵያ የመገንጠል ዓላማም እንደተያዘ ታወቋል። ይህ እየታወቀ አደጋውን በዝምታ መመልከት የሚቻል አልሆነም። ሀገርን በመካድ በታሪክ ፊት የሚያስጠይቅ ወንጀል ነው።

በሥልጣን ዙፋን ተቀምጦ ካለጠያቂ መዝረፍና መግፈፍ የለመደ አምባገነን፣ በሥልጣኑ ለመቀጠል ሲል እስከምን ሊወርድና ምን ያህል ውድመት ሊፈጽም እንደሚችል፣ የቀድሞ የሱማሌ ክልል አመራሮች ርምጃ ግልጽ ማሳያ ይሆናል። ወታደራዊ ግጭቱ ከመፈጸሙ በፊትና በኋላ የተሰባሰቡትና ተአማኒነት ያላቸው መረጃዎች በግልጽ እንደሚያሳዩት ከሆነ፣ ቡድኑ ዓላማውን በተቀናጀ አግባብ ለማስፈጸም በቂ ቅድመ ዝግጅት አድርጓል። በዚህ ረገድ አመራሩ የአጥፊ ቡድኑን አባላት ከመመልመል አንሥቶ የተለያዩ ሥልጠናዎችን እስከ መስጠት ተሳትፎ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን፤ የአጥፊ ቡድኑን የተለያዩ መሥፈርቶችን አውጥቶ ምልመላ አካሂዷል።

ለዚህም አብረው ዘመናት በኖሩ ሕዝቦች መካከል የታቀደ ግጭት በመፍጠር፣ የአጥፊ ቡድኑን ለማረጋገጥ መጠቀማቸው፣ በታሪክ የማይረሳ ጥቁር አሻራ ጥሎ አልፏል። አመራሩና አጥፊው ቡድን በምስጢር በቀጥታ

ለመገናኘት እንዲያስችላቸው፣ ከዱባይ ዋጋቸው እያንዳንዳቸው ሠላሳ ሺህ ብር የሆነና ብዛታቸው 40 የሚደርስ በጠቅላላው ዋጋቸው 1.2 ሚልዮን ብር የሚያወጡ S8+ (ኤስ.8 ፕላስ) ሞባይሎችን አስመጥተው ለቡድኑ እንዲከፋፈል አድርገዋል። ሄጎ እና ዋ ሄገን የተባለ የፌስቡክ ገጽ አስቀድሞ በመክፈት፣ የጥፋት ፈጻሚውን ቡድን እንዲሁም ሌሎች የበላይ አመራሮችን በቀጥታ ሲያገኙና የተለያዩ ሕገ ወጥ ቅስቀሳዎችን ሲያስተላልፉ እንደነበረ በመረጃ ተረጋግጧል።

በዚህ የፌስቡክ ገጽ አማካኝነት ከተሠራጩት የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳዎች መካከል፣ የፌዴራል መንግሥት በክልሉ ላይ የጦርነት ክተት ዐዋጅ ማወጁና ወረራ መፈጸሙ ተነግሯል። ወንድማማች ሕዝቦችን በጠላትነት ፈርጆ ስም ያጠፋል። በተጨማሪም ነዳጃችንን ሊወስዱብን ነው፤ ነዳጃችንን ይዘን ታላቋን ሶማሊያ እንቀላቀላለን፤ የሶማሌ ሕዝብ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ይነሣ፣ ሀገሩንም ነጻ ያውጣ፤› የሚሉ ጥሪዎችም ተላልፈዋል። የጥቃት ቡድኑ በመከላከያ ሠራዊት ካምፕ ላይ አደጋ እንዲጥል የቃጠሎ አደጋ እንዲያደርስ ታቅዷል። አብያተ ክርስቲያናትን ለማቃጠል ተዘጋጅቷል። በባንኮች ላይ የማቃጠልና የዝርፊያ ተግባር እንዲፈጸም ቅስቀሳ ተደርጓል። እነዚህን ሁሉ ከተገኙ የሰውና የሰነድ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል።

ወንጀሉ በተቀናጀና በተደራጀ መልክ ዝግጅት ተደርጎበት የተፈጸመ መሆኑን የሚያመላክቱ ሌሎች ማስረጃዎችን ማግኘት፣ ለጉዳዩ ከተሰጠው ትኩረትና ክትትል አንጻር አስቸጋሪ አልነበረም። የጥቃቱ ዒላማ ባልሆኑ ቤቶች፣ ባንኮችና ሌሎች ድርጅቶች ላይ “CMC” (አብዲ መሐመድ ዑመር ማለት ነው)፣ “ONLF” (የአጋዴ ነጻ አውጭ ግምባር)፣ “የሱማሌ ሞቃዲሾ” የሚል ምልክት ወይም ጽሑፍ ተደርጎበት ነበር።

ታሳቢውም ይህ ምልክት ወይም ጽሑፍ ያለበት ተቋም አይቃጠልም ወይም አይዘረፍም ለማለት ነው። የጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ቤቶች፣ ባንኮችና ሆቴሎች ላይ ይህ ምልክት አልተደረገባቸውም። ይህ ጥቃት አድራሽ ቡድን የታሰበውን የወንጀል ድርጊት እጅግ ስልታዊና ፈጣን በሆነ መንገድ እንዲፈጽም ለማስቻል የታሰበ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል።

የሚዘርፉ ቡድኖች ከላይ የተጠቀሰው ምልክት ያላረፈባቸውን የግለሰብ ቤቶች, የመንግሥትና የግል ድርጅቶች፣ ባንኮች፣ የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቆች፣ የልብስ ቡቲኮች፣ የሕንጻ መሣሪያዎች፣ አነስተኛ ምግብ ቤቶችና መጠጥ ቤቶች፣ ተሽከርካሪዎችና የመሳሰሉትን በመለየት የዘረፋና የማቃጠል ተግባር ፈጽመዋል። እንዲሁም አልከፈት ያሉ ቤቶችን፣ ሱቆችንና ድርጅቶችን በሱማሌ ክልል ልዩ ኃይል ፖሊስ አባላት በጥይት እየተመቱ እንዲከፈቱ ያደርጉ ነበር። በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ፈርሐን ጣሂር አማካይነት የጅግጅጋ ስፖንጅ ፋብሪካ ሙሉ በሙሉ ሊወድም ችሏል። በዚህም ወደ 59 ሚሊየን ብር የወደመ መሆኑን በምስክሮችና በሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል።

በዋናነት በምሽት በተካሄደው የሁከትና የረብሻ ርምጃ የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ሐላፊና ሠራተኞችን

በማስገደድ የከተማዋ መብራት እንዲቋረጥ ተደርጓል። ጨለማውን ተገን በማድረግም በርካታ መንግሥታዊ ተቋማት፣ የግል ድርጅቶችና መኖሪያ ቤቶች ሳይቀሩ ዝርፊያ ተካሂዶባቸዋል። ብዙ ድርጅቶች ተቃጥለዋል። ይባስ ብሎ የተዘረፉ ንብረቶች ከተሰበሰቡ በኋላ የሚጭን መኪና ተዘጋጅቶ ነበር። የት እንደሚወሰዱ ያልታወቀ ቢሆንም፣ ንብረቱ ተጭኖ ሲወሰድ ነበር። ለንብረታቸው መዳን ጥረት ሲያደርጉ በነበሩ ባለንብረቶችና በቦታው ተገኝተው ይሄንን አሳዛኝና አሳፋሪ ድርጊት በመቃወም ሲከላከሉ የነበሩ ግለሰቦች፣ የሶማሌ ክልልን ልዩ የፖሊስ ኃይል ዩኒፎርም በለበሱ አካላት በጥይት እየተመቱ እንደነበር፣ በተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል። በዚህም ወቅት የክልሉን ልዩ ኃይል ዩኒፎርም በለበሱ ኃይሎች፣ በጥይት የተመቱ ግለሰቦችን አስከሬን የሚጭን መኪና አዘጋጅተው ነበረ። ብዙዎቹ ሟቾች በዚህ መኪና ተጭነው ወደ ተለያዩ የጅምላ መቃብር ቦታዎች ተወስደው መቀበራቸውን ከተሰበሰቡት ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል።

በዚያ ወቅት በቀጥታና በተዘዋዋሪ የተሰበሰቡትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ መከላከያ ሠራዊታችን እንዲንቀሳቀስና ክልሉን እንዲያረጋጋ ማድረግ አስፈላጊ ነበር። ያለማወላወልም ትዕዛዙን አስተላለፌያለሁ። መከላከያ ሠራዊታችን ያን መሰል የተቀነባበረ ሕገ ወጥ ተግባር በቁጥጥር ሥር ለማዋል ያሳየው ቁርጠኝነትና የከፈለው መሥዕዋትነት እጅግ የሚያኮራ ነበር። ያ ሠራዊት የጥፋት ኃይሎች ይመኙት እንደነበረው እርስ በርሱ ሳይከፋፈል ከሕዝብ ጎን ቆሞ የተለኮሰውን እሳት ባያጠፋው ኖሮ፣ ጉዳቱ ምንኛ የከፋ ሊሆን እንደሚችል በዚያ አጭር ጊዜ የደረሰው የሕይወትና የንብረት ጥፋት ምስክር ይሆናል። ከሃምሣ ዘጠኝ ሰዎች በላይ ሕይወት ሲጠፋ፣ ከ266 ሰው በላይ ቀላልና ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶበታል። ሴቶችና ሕፃናት በሄጎ ቡድንና በክልሉ ልዩ ኃይል ፖሊስ አባላት ሲሰቃዩ ሲደፈሩ ነበር። ግምቱ ከ42 ሚሊየን ብር የሚበልጥ ንብረት (ከቤተ ክርስቲያን፣ ከመንግሥት፣ ከግለሰብ መኖሪያ ቤት፤ ከንግድ ድርጅቶች) ተቃጥለዋል፤ ተዘርፈዋል፤ ወድመዋል። ብዛታቸው በውል ተለይተው ያልታወቁ የከተማው ነዋሪዎች ከቤትና ከንብረታቸው እንዲፈናቀሉ ተደርጓል።

ይሄን ችግር ማለፍ እጅግ ፈታኝ የአመራር ሥራ የሚጠይቅ ነበር። በአንድ በኩል የክልሉ ፕሬዚዳንትና ጀሌዎቹ እንደሚሰብኩት ዓላማችን ሕዝቡን በተጽዕኖ ሥር ማስገባት ሳይሆን፤ በተቃራኒው ሕዝቡን ከተጫነበት ቀንበር ማላቀቅ እንደሆነ ማሳየት ያስፈልጋል። የክልሉ ሚዲያ በአጭር ጊዜ ነዝቶት የነበረው “ተወረራችሁ” የሚለውን ሰበካ መስበር እጅግ አስፈላጊ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ የመከላከያን እንቅስቃሴና የክልሉን ልዩ ፖሊስ ለአንድ ዓላማ እንዲሰለፉ ማድረግ አንገብጋቢ ጉዳይ ነበር።

የክልሉ ልዩ ፖሊስ ከላይ በተገለጸው የተወረርን ስሜት ሙሉ በሙሉ ቢሳብና ከሀገር መከላከያና ከፌደራል ፖሊስ ኃይል ጋር የለየለት ግጭት ውስጥ ቢገባ፣ ጥፋቱ እጅግ የገዘፈ ይሆናል። የክልሉ ልዩ ኃይል እስከ አየር መቃወሚያ ድረስ የታጠቀና እስከ አምስት መደበኛ ክፍለ ጦር ሊገመት የሚችል ኃይል ያለው በመሆኑ፣ ጥፋቱ ከባድ እንደሚሆን መገመት ቀላል ነው። በአንድ በኩል የጥፋት ተልእኮ የያዘውን ኃይል መነጠል፣ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛውን ልዩ ኃይል ማሳመን ያስፈልግ ነበር።

በመጨረሻም ለውጡ የጉልቻ መቀያየር እንዳልሆነና አንድን በፌደራል የተሾመን ሰው በሌላ ከፌደራል በሚሾም ሰው የመተካት ሂደት እንዳልሆነ ለማሳየት፤ ቀጣዩ የክልሉ አስተዳዳሪ በምክር ቤቱ የሚሾምና ሙሉ ዐቅም ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነበር። እነዚህ ሁሉ ተግባራት በተገቢው መልኩ በመከናወናቸው ከተደገሰው ጥፋት አንጻር እጅግ ባነሰ መሥዋዕትነት አመርቂ ውጤት ለማምጣት ተችሏል። መሥዕዋዕትነት ያስከብራል፤ ሁሌም ደግሞ ይዘከራል። ርምጃችንን ግን አሸናፊ ድሉን እያሰበ የሚፎክርበትና የሚያቅራራበት፣ ተሸናፊ አንገቱን ሰብሮ የሚያዝንበትና የሚቆጭበት ዓይነት አይደለም። ይልቁንም የአንድ ሀገር ልጆች በፖለቲካ እምነት ሳቢያ ጎራ ለይተው፣ መሣሪያ መዘው፣ የባሩድ እርሳስ አጢሰው እርስ በርስ የተዋጉበት ነው። የቆሰሉበት፣ አካላቸውን ያጡበትና ለሞት የተዳረጉበት ነው። በተመሳሳይ ክሥተት ቁጭት ውስጥ የገባ የሚመስለው አንድ የድሮ ገጣሚ፣

*የገደለው ባልሽ፣*
*የሞተው ወንድምሽ፣*
*ሐዘንሽ ቅጥ አጣ፣*
*ከቤትሽም አልወጣ!*
*ሲል እንደገለፀው፤ በቁጭት ከማለፍ ባሻገር ፈንጠዝያ ውስጥ መግባት የሚቻልበት አልነበረም።*

በዚህም የተነሣ ዛሬ ካለችውና ለወደፊቱም እንገነባታለን ብለን ከምናስባት ኢትዮጵያ አንጻር መሠረታዊ ጥያቄ ማንሣት የተሻለና ጠቃሚ ይሆናል። በአንድ ጀንበር የለውጡ ንፋስ በእጃችን ያስያዘንን የሰላም ርግብ ለቅቀን የጦርነትን እሳት እንድንጨብጥ የሚያደርግ ምን ምክንያት ይኖራል? ለዛሬው ሕይወታችን የዳረገችንንና የተረከብናትን ኢትየጵያን ተጠያቂ በማድረግ አለመውደድ መብታችን ነው። ነገ ለልጆቻችን የምናስረክባትን ኢትዮጵያ ግን ውብ አድርገን የመሥራት ዜግነታዊ ሐላፊነትና ግዴታ አለብን።

የምንጠራበት ስም በጣም ያማረውን ቀዳሚ ትርጉም የሚሰጡት ላወጡልን፣ ወደዚህ ዓለም ላመጡን ለወላጆቻችን ነው። በትክክልም ስማችን የእኛ ሳይሆን የነርሱ ሕልም ነው። ምናልባት የሚወዱትንና የተሰማቸውን ማስታወሻቸው፣ የተስፋቸው መልሕቅና የሚወዱት መንፈሳዊ ወይም ሀገራዊ ጀግና መጠሪያ ስም ሊሆን ይችላል። ይህ መጠየቅና መልስም ልንፈልግለት የሚገባን እውነታ ነው።

በተለያየ ምክንያት ስማችንን ላንወደው እንችላለን። በልካችን የተሰፋ ላይመስለን፣ ሕልማችንንና ማንነታችንን፣ ተስፋና እምነታችንን፣ ዘመናችንንና ሰብእናችንን የማይገልጽ፣ በወላጆቻችን ፍቃድ ብቻ ተበጅቶ እኛን ያገለለ፣ ራሳችንን የማናይበት የቀደምቶቻችን መገለጫ ሆኖ ሊሰማን ይችላል። ወደ ኋላ ተመልሰን ይሄን የታሪክ እውነታ መቀየር አንችልም። መፍትሔው አንድም ተቀብሎና ተላምዶ መኖር ነው፤ አልያም ደግሞ ይወክለናልና ተስፋና ትውስታችንን ያኖርልናል ያልነውን ስም ለራሳችን በማውጣት በእርሱ መገልገል ነው። በማያጠራጥር

መልኩ ሀገርም ልክ እንደ ስማችን ናት። የወረስነውን ላንወደው እንችላለን። ባህልና ሙዚቃው፣ ምግብና መጠጡ፣ ታሪክና ትውፊቱ፣ ግብረገቡና ሥርዓቱ፣ ገዢዎቹና ሊቃውንቱ፣ የሃይማኖት አባቶቹና አስታራቂ ሽማግሌዎቹ፣ ቋንቋውና ሰንደቅ ዓላማው፣ ቀደምት

መፍትሔው የመገንጠል ፖለቲካ ማራመድ _ አለበለዚያም መሰደድ አይደለም። የእስልምና እምነት ቃለ ነቢ፣ መሰደድ ከመጥፎ ተግባራት እንጂ ከሀገርና ከራስ እንዳልሆነ ይነግሩናል። በሀገራችን የምናያቸው ጥፋቶች፣ ስሕተቶችና ጉድለቶች፣ ለምን እንደዚህ ሆኑ? ብሎ መጠየቅ ይቻላል። ዘለዓለም ግን ጥያቄውን አንሥተን አናለቅስም፣ አናላዝንም። ሙሾም አናወርድም፣ ስደትም አንገባም። ቀደምቶቻችን ጊዜና ዐቅም ዕውቀትና ሀብት በፈቀደላቸው መልኩ የሚያልሟትን ሀገር ወይም የሀገር ጅማሮ አውርሰውናል።

እነርሱ ዓለምን በሚረዱበት፣ ሃይማኖትና መንግሥትን በሚያዩበት፣ የሕግንና የአብሮነትን ልክ በሚገነዘቡበት ልክ፣ ሀገር ሰፍተው አወረሱን። በሰፉት ልክ ባለቤት ነን ብለው በማይቀረው ሞት አልፈዋል። በዓሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን (መክዘ) እንደ ዓሥራ ስድስተኛው መክዘ ማሰብ ነውር አይደለም። ነውር የሚሆነው በሃያ አንደኛው መክዘ እንደ ዓሥራ ስድስተኛው መክዘ ማሰብ ነው። ተተኪ ትውልድ የመሆን አንዱ ዕድል ሁለት ነው። ትናንት የተሳተውን ለማረምና ትናንት የጎደለውን ለመሙላት። ከእኛ በኋላ የሚመጣው ትውልድም እኛ የተሳተውን የሚያርመው፣ እኛ ያጎደልነውን የሚሞላው ብዙ ይኖረዋል።

ዛሬ የሀገር ባለቤቷ እኛ ነን። ከእኛ ውጭ ማንም ባለቤት ነኝ ብሎ ሊመጣ አይችልም። ባለቤት እንደ መሆናችን መጠን ወደ ፊት ወደ ኋላ ተብሎ ሐላፊነት የሚላከክበት፣ ብንወድቅ ለውድቀታችን ጣት የምንቀስርበት፣ ብናንሠራራ ለምጥቀታችን ኒሻን የምናጋራው ማንም ሌላ ኃይል ሊኖር አይችልም። በዘመናችን የወረስናት ሀገር የሁላችንም ቤት በምትሆንበት መልኩ ማደስና ማበጀት፣ ማቃናትና ማዘመን መብታችን ብቻ ሳይሆን ግዴታችንም ጭምር ነው። ልክ ወላጆቻችን ያወጡልን ስም የእነርሱ ሕልም እንደሆነው ሁሉ፤ እኛም ነገ ለልጆቻችን የምንሰጠው ስም ለእኛ ሕልማችን ሊሆን ይገባል።

ለልጆቻችን የምናወርሰው ሀገር ከወረስነው እኩል ከሆነማ ምኑን የተሻለ ትውልድ ሆንነው? ከወረስነው የምናወርሰው ከኮሰመነ ምኑን ኖርነው? መጥተን መሄዳችን፣ ማንበብ ማወቃችን፣ ማለፍ መውደቃችን በምን ይታወቃል?

*"ጨንግፎ ካልሆነ ትውልድ ተሰፋው ነጥፎ፣*
*አይሞትም የሰው ዘር፣ ያባት ስም ታቅፎ"*

ሀገራችን ትናንት የተሠራችው በትናንት እይታ ነው። ቀደምቶቹ አያቶቻችን ዘመናቸው ባሳያቸውና ሕልማችን ነው, ባሉት በዘውዳዊው ሥርዓት ሀገር አስተዳደሩ። ይህ ክሥተት በሰሜንም፣ በደቡብም፣ በምዕራብም፣ በምሥራቅም የነበሩት መንግሥቶቻችን ባሕርይ ነበር። የዘመኑ እሳቤ መሆኑን የምንረዳው በዚያ ነው።

በአያቶቻችን ትከሻ ላይ ቆመው፣ የተሻለ አሻግረው ማየት የቻሉት አባቶቻችን፤ የአያቶቻችን ሀገር ለሁሉም የምትበቃ ሆና አልታየቻቸውም። ገና በተማሪነታቸው በሰልፍ፣ በትጥቅ፣ በውይይት፣ በምርምር ሕልሞቻቸውን የምታካትትና የምታቻችል ሀገር ለመፍጠር ታገሉ። ዛሬ የምናያት ሀገርም እነርሱ ያስረከቡንን ነው። ለዚህም ወቀሳና ሙገሳ አይቀርላቸውም።

እኛስ ዛሬ በአባቶቻችን ትክሻ ላይ ሆነን በልካችን የተሰፋ ሀገር የለንም ብለን ማልቀስ ይኖርብናል? ወይስ ታሪክና አጋጣሚ የቸረንን አድማስ ተመልካችነት፣ ሉላዊነት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ተጠቅመን፤ በሕግና በሥርዓት የምትመራ ሀገር ገንብተን ማውረስ አለብን? መልሱ ያለው ከሁላችን ጋር፣ በእያንዳንዳችን እጅ ውስጥ ነው።

## *“ልዩነትን በመደመር ለመርታት፣*
## *ዕጣ ፈንታን በእጅ ማስገባት”*

በጃፓን የተፈጸመ ታሪክ እንደሆነ ይነገራል። አንድ የጦር ጀኔራል ሠራዊቱን ይዞ ወደ ጦርነት ይሄዳል። ጀኔራሉ የያዘው የሠራዊት ብዛት ከጠላት ጦር ጋር ሲወዳደር በዓሥር እጥፍ ያነሰ ነበር። ቢሆንም ጀኔራሉ በጥሩ ስትራቴጂ ጠላትን እንደሚያሸንፍ ያውቃል። ሠራዊቱ ግን ጥርጣሬ ላይ ነው። ወደ ጦር ሜዳው እየተጓዙ ሳለ አንድ የጸሎት ቦታ ሲደርስ ወታደሮቹን አስቆማቸውና እንዲህ አላቸው።

“ጸሎት ቤቱ ገብቼ ስመለስ ዕጣ ፈንታችን ምን እንደሚሆን ሳንቲም ወደ ላይ ወርውረን እናረጋግጣለን። ሳንቲሙ በጎፈር በኩል ካረፈ መሸነፋችንን ከወዲሁ እናውቃለን። በተቃራኒው በሰው በኩል ካረፈ ደግሞ እናሸንፋለን። ዕጣ ፈንታችን በእጃችን ነው" አላቸው። እንዳለውም ጀኔራሉ ጸሎቱን አድርሶ ሲመለስ ወታደሮቹ እያዩ ሳንቲም ወደ ላይ ሲወረውር ሳንቲሙ በሰው በኩል ዐረፈ። ሠራዊቱም በራስ መተማመን ስሜት ውስጡን አጠንክሮ ወደ ጦር ሜዳው አቀና። ድልም ተቀዳጁ።

በመልስ ጉዞ ወቅት ከሠራዊቱ አንዱ ወደ ጀኔራሉ ቀርቦ እንዲህ ሲል ተናገረ። “ዕጣ ፈንታን የመቀየር ሥልጣን ለማንም የለውም።”

ይኸን ጊዜ ጀኔራሉ ቀስ ብሎ ሳንቲሙን ለወታደሩ እያሳየው፤ “ዕጣ ፈንታችን በእጃችን ነው። እኛ እንደፈለገን አድርገን መቀየር እንችላለን፤ ዋናው የእኛ ከልብ መፍቀድ ነው” ሲል መለሰለት። ወታደሩ ሳንቲሙን ሲያይ በእጅጉ ተደነቀ፤ በሁለቱም በኩል ሰው እንጂ ጎፈር አልነበረውም።

ያለንበት ዘመን በትሩፋት የተሞላ ነው። አይነጋላቸውም ከተባሉት "የሦስተኛው ዓለም ሀገራት ውስጥ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ አንዲት ጥይት ሳትተኮስ ሥልጣን የሚረካከቡ መሪዎች ተፈጥረዋል። ከአውሮጳ

ሀገራት ጋር የሚወዳደር ኢኮኖሚ የገነቡ ሀገራት "ኋላ ቀር" ከሚሏት ከአፍሪቃ አህጉር ተገኝተዋል። የሕግ የበላይነት ፈልቆ ያረሰረሳቸው፣ የሃይማኖት ልዩነታቸውን አቻችለው በሴኪዩላር መንግሥት መተዳደር የጀመሩ፣ ሙስና እንደ ርኩሰት የሚቆጠርባቸው፣ ሰላማቸው ከእነርሱ አልፎ ለጎረቤቶቻቸው የሚተርፍ፣ የፖለቲካ ተደማጭነታቸው በአህጉራዊና በዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ እየዳበረ የመጣ ሀገራት፣ ከዚህችው ከአፍሪቃ ውስጥ ተፈጥረዋል።

ትናንቶቻቸው በእርስ በርስ ጦርነትና በጠመንጃ የበላይነት፣ በዘረኝነትና በሙስና የተበጠበጠ፣ በአምባገነንነትና በረኃብ የሚታወስ ሀገራት ነበሩ። እነዚህ ሀገራት፣ የወረሱትን ለልጆቻቸው ላለማውረስ ወሰኑ። ወቅትና ዘመናቸው በፈቀደላቸው ዐቅም ሁሉ ተንፈራገጡ። ዕጣ ፈንታቸውን በእጃቸው አድርገው፣ ከልብ ተማክረው፣ በእውነት ተደመሩ። በዚህም ከወደቁበት ትቢያ ለመነሣት ቻሉ። አቧራቸውን ከላያቸው አራግፈው ዳግም ጥንታዊ የሥልጣኔ ጉዟቸውን የተቀላቀሉ ጥቂቶች በዙሪያችን አሉ። ወደፊትም በዝተው መኖር ይቀጥላሉ።

ኢትዮጵያዊነትን ከፍ ደመቅ ማድረግ የጀመርነው ስሙ አፋችን ላይ ስለሚጣፍጠንና በታሪኩ ርዝመት ተማርከን አይደለም። ይልቁንም እኛ ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳችን የተሳሰርን፣ እንዳንለያይ ሆነን የተጋመድን፤ ከዚያም በላይ እንዳለፈው ዘመን ሁሉ ቀጣይ ዕጣ ፈንታችንም በጥብቅ የተቆራኘ፣ በአጥንት በሥጋችን ውስጥ ድርና ማግ ሆኖ የተሸመነ፣ ድንቅ የአንድነት ጥበብ በመኖሩ ነው።

- ከሁሉም የላቁ የዓለማችን ሥልጣኔዎች የጀርባ አጥንት ሆኖ የያዛቸው መርሕና ዓምድ አንድነት ነው።

- በኅብረ ብሔራዊ የአንድነት እንቅስቃሴ እንጂ፤ በነጠላ ጉዞ ኅብረተሰባዊ ለውጥን ያረጋገጠ አንድም ሀገር የለም።

- አንድነት የሁሉም ተፈጥሯዊ ሕይወት መገለጫ እውነት ነው። አንድነት ሲባልም የአቋም እንጂ የቁመና አይደለም። የአቋም ድማሮ የዐቅም ድማሮ ይፈጥራል። ልዩነት ግን ፍቅርን ሳይሆን ፍርሃትን መሠረት ያደረገ፣ በምትሐት የሚፈጠር የአርቴፊሻል እውነታ ውጤት ነው።

በ920ዎቹ በችካጎ አሜሪካ የሚኖር ደብሊው አይ ቶማስ የተባለ የሥነ ማኅበረሰብ ሊቅ (ሶሲዮሎጂስት) “ሰዎች እውነት ናቸው ብለው የተቀበሏቸው ሁነቶች እውነተኛ የሆነ ውጤት ያመጣሉ” ሲል መናገሩ ተዘግቧል። እኛ እውነት ብለን የምንቀበላቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? ይሁነኝ ብለን የምንናገራቸው፣ የምንሠራቸውና የምንፈጽማቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? አሁን ባለንበት ተጨባጭ ነባራዊ ሕይወት ተጨባጭ ያልሆኑ ሐሳባዊ ነገሮች ተደርገው ሊታዩ ይችሉ ይሆናል። ነገ አዝመራ ሆነው የምናጭዳቸው ጥሩም ይሁን መጥፎ ነገሮች፣

ዛሬ እውነት ናቸው ብለን በሐሳብ ማሳ ላይ የዘራናቸው ናቸው።

ባለፉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት በሀገራችን በዘራናቸው የብሔር ልዩነት አጀንዳዎች ሳቢያ፤ ዛሬ በማጨድ ላይ ያለነው የልዩነትን አዝመራ እንጂ የአንድነትን ምርት አይደለም። ራስን በብሔር ማንነት መግለጽ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ሆኖ አይደለም። በራስ ቋንቋ፣ ባህልና ብሔራዊ ማንነት መገለጫዎች መኩራት ተገቢ ነው። ሀገራችንም በኅብረ ብሔራዊ መሠረት ላይ የቆመች ሀገር መሆኗን በምንም መልኩ መካድ አይቻልም።

ያም ሆኖ በሀገራችን በብሔር ማንነት ራስን የመግለጫው መንገድ በተካረረ ፉክክር የተሞላና ሌላ ብሔርን እንደ አጋር ሳይሆን እንደ ተቀናቃኝ የሚያይ ነው። «አንድነት›› ተብሎ የሚቀነቀነውም ብዙኅነትን የማያስተናግድ፣ አንድ ዓይነትነትን የሚያቀነቅን ነው። ነገሮች በተቃርኖ የተሞሉ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

መደመር በመርሕ ደረጃ "የዐቅም ድማሮን ያመጣል" የሚል ሐሳብን ያቀነቅናል። ስለሆነም በሀገር ውስጥ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን እንጂ መለያየትንና መገንጠልን አያራምድም። በሕዝቦች መካከል ፍርሃትን ሳይሆን ፍቅርን ዘርቶ ያበቅላል። ኅብረ ብሔራዊ አንድነት በስፋት ያብብ ዘንድ የእሳቤው የማዕዘን ድንጋይ በማድረግ ይቀበላል። "ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ለኢትዮጵያ እኛ የፈጠርንላት እውነት አይደለም። በአንድ ላይ አስተሳስሮ ሊያቆያት የሚችል ጽኑ እውነት ነው። ይሄን ሐቅ መቀበል እንጂ መቃወም አይቻልም።

ኅብረ ብሔራዊ አንድነት አጥር ሳይሆን ድልድይ የሚገነባበት ሕልም ነው። በጀት ባይኖርህም ዶማና አካፋ ሆኖ ልማትን ለማምጣት መቆፈሪያ ሆኖ ያገለግልሃል። መደመር በፖለቲካ ፕሮግራሙ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት ዘብ የሚቆም፣ በማንነት ትንተናው ደግሞ በኅብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ መሠረቱን የሚያንጽ አቋም ነው። የወዳጅ ጠላት ትንታኔ የለውም። አካታችና አሳታፊ የሆነ ሰፊ ወርቃማ አማካይ ያለው ነው። ውግንናውንም ለዚህ ወይም ለዚያ ብሔርና ብሔረሰብ ብቻ በማለት አይለያይም። ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ያለ ልዩነትና የያለ አድልዎ በእኩል ለዴሞክራሲ፣ ለሰላምና ለብልጽግና ይሠራል። መደመር ከአንድነትና ከኢትዮጵያዊነት ጋር እርስ በርሱ የተሳሰረ፣ እንዳይለያይ ሆኖ የተጋመደ ነው። እንዳለፈው ዘመን ሁሉ የቀጣይ ዘመን ዕጣ ፈንታችንም፣ በጥብቅ ከተቆራኘ ድርና ማግ የተገኘ ውብ የጥበብ ሸማ ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል። መሬታችን ያልዘራንበትን አያበቅልም፤ አላበቀለምም።

ለጸደቀው መልካም አዝመራ ድርሻችን እንዳለንበት ሁሉ ለደረቀውም ቡቃያ እኩል ተጠያቂ እንሆናለን። ትውልድ ሲሄድ ትውልድ ይመጣል። መሪና መንግሥታት አልፈው ሌላ ይተካል። ሥርዓትና ርእዮት ይቀያየራሉ። ዘመን የፈቀደለት ሲተከል ያልፈቀደለት ይነቀላል። በዚህ ሁሉ ለውጥ ውስጥ አጠቃላይ ሽግግርን ማረጋገጥ የሚችል ባህልና ትውፊት ይፈጠራል። ትናንት የነበረው ትውልድ በዘመኑ መልካም የመሰለውን ዘራ። ከእርሱ በኋላ የመጣው ትውልድ ማሳውን ሲመለከት ስንዴውና እንክርዳዱ አብሮ በቅሎ አገኘው። እንክርዳዱን ነቅሎ

ስንዴውን ለማሳደግ ሞከረ። እርሱም በተራው መልካም የመሰለውን ዘር ዘራ። እኛም በዘመናችን ስናየው ስንዴውና እንክርዳዱ በቅሎ አገኘነው። እኛም በዘመናችን እንክርዳዱን ለመንቀልና ስንዴው ለማሳደግ እየሞከርን ነው።

የትውልዳችንን ዘር በሀገራችን ላይ ስንዘራ ግን በዕውቀትና በጥበብ የተሻለውን ዘር መምረጥና መዝራት ይኖርብናል። ያለፈው ዘመን መልካም ጊዜ ብቻ ሳይሆን የፈተናም ጊዜ ነበር። ቁርጠኝነትን የሚያስታጥቅ ወኔ፣ ትሕትናን የሚያላብስ ቅንነት ይኖረን ዘንድ ወቅቱ የግድ ይለናል። መለያየት ሳይሆን አብሮነት፣ መገፋፋት ሳይሆን መረዳዳት፣ መነጣጠቅ ሳይሆን መተባበር የምናሰፍንበት ዘመን መሆን አለበት።

በዓለማችን ዛሬ ታላላቅ የሚባሉ የአውሮፓና የአሜሪካ ሀገሮች ከኛ የባሱ ችግሮች ነበሩባቸው። ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም ከፊሉን ችግራቸውን አሸንፈው ነው ለዛሬ ታላቅነትና ልዕልና የበቁት። በመነጋገር፣ በመግባባት፣ በመደመርና ሰጥቶ በመቀበል መርሕ ከተመራን ችግራችንን ለመፍታት አስቸጋሪ አይደለም።

እነርሱ እንደተከናወነላቸው ሁሉ ለእኛም ይሳካልናል። ያን ጊዜ በተቀመጥንበት እርጥብ የማይጨስብን፣ ደረቅ የማይነድብን መካከለኞች መሆን እንችላለን።

## *"የማን ዘር ጎመን ዘር"*

የምንፈልገውን ሙዚቃ ለመጨዋት መጀመሪያ ቅኝታችንን ማስተካከል አለብን። በትዝታ ቅኝት አንቺ ሆዬ ዜማን መጫወት አይቻልም፣ በምንገኝበት የለውጥ ርምጃ ውስጥ በሕግ መግዛት ወይም የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ሂደት፣ ከመልካም ምኞትና ፍላጎት ባሻገር የእያንዳንዳችንን ተሳትፎ ይሻል። መጽሐፍ ጥበብን መሻት መልካም መሆኑን ይነግረናል። እውነትን መፈለግና ማድረግ ደግሞ የጥበብ ምንጭና ውጤት ነው። ተወደደም ተጠላ በዙሪያችን የከበበንን የሀገራችንን ለምለም እንይ፤ እሾህና አሜከላውን እንመልከት፤ በአያት ቅድመ አያቶቻችን ብሎም በአባት በእናቶቻችን ዘመን የተዘራ ደግና ክፉ አዝመራ ውጤት ነው። በእኔና በአንተ፣ በወንድምና በእኅቶቻችን ያልተኮተኮተ፣ በልጆቻችን ውኃ ሳይጠጣ የበቀለ አንድም ችግኝ በጓሯችን አይገኝም። በሀገር ደረጃ ሲደርስ እያየን የምንደነግጠው እንግዳ ነገር ሁሉ በጓሯችን ያሳደግነው ችግኝ መሆኑን ፈጽሞ መጠራጠር አይገባንም። እኛ ሳንዘራው አልፎ አልፎ የሚበቅል ወፍ ዘራሽ ችግኝ የለም ወይ? ብለንም ብንጠይቅም መልሱ "አለ" ነው። ዳሩ ግን የኛ ጥፋት የሚሆነው ወፍ ዘራሹን መጥፎ ዘር እንዴት ተከታትለን ሳንነቅለው ቀረን? ለምን እንዲፋፋና እንዲስፋፋ ዕድል ፈጠርንለት? የሚለው ነው።

ለዚህ ነው ዛሬ ላለንበትና ለገባንበት የችግር አረንቋ የስንፍናውን ያህል ያላዋጣ የለም ለማለት የሚያስደፍረው። ልጆቻችንን ያጫወትንባቸው ተረቶች፣ እረኞቻችን በዱር በገደሉ ያንጎራጎሯቸው ዜማዎች፣ ምርቃቶቻችንና ርግማኖቻችን፣ የሰርግ ዘፈኖቻችንና ሙሾዎቻችን፣ በፉከራና በሽለላ የሚወዘውዙን

ቀረርቶዎቻችን፣ በአርምሞና በተመስጦ የሚነጥቁን መዝሙሮቻችንና መንዙማዎቻችን፤ ሁሉም በጥልቅ የሚመጋገቡና የሚወራረሱ ሆነው እናገኛቸዋለን።

በማኅበረሰባችን ውስጥ ሥጋና ነፍስ ዘርተው የሚመላለሱት ሥነ ቃሎቻችን ምን ይላሉ? ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ነው። ይሄን ሳንመልስና ሳንረዳ የሕግ የበላይነት ብሎ መንጫጫቱ ከምኞት የዘለለ ተጨባጭ ውጤት ማስገኘት አይችልም። ከእምነታችን የሚመነጨው ሕግ ነው፣ ሥርዓትን ከባህል ወግና ልማድን ከአኗኗር አሰናስሎ የሚመራን። "ለወትሮው በጨቋኝነትና በሸብር ሥራው የሚያስፈራን መንግሥት ነበር፤ አሁን አሁን ሕዝብንና መንግሥትን የሚያስፈራራው ራሱ ሕዝብ ሆኗል" ስትል አንድ የማኅበራዊ ሚዲያ ታዛቢ ተናግራለች። በበሽታችንና በመፍትሔው መካከል ሊኖር የሚገባውን ትስስር ስሜታዊነታችንና እልከኝነታችን እንዳይሰወርብን መጠንቀቅ ይኖርብናል። ስሜታዊነት በልኩ መልካም ነው፤ ሰው ያደርጋልና። በዝቶም ይሁን አንሶ ልኬታውን ካለፈ ግን ለምንም ለማንም አይበጅም።

ጀግንነትን በምን ሣልነው? ኃይልና ሥልጣንን ለልጆቻችን እንዴት ተረክነው? እነርሱስ እንዴት ተቀበሉን? በእውነት ስለ እውነት ትሑት ሰው ይከበራልን? ሕግና ሥርዓት ጠብቆ ሊኖር የሚወድን ሰው እናወድሰዋለንን? ርኅራኄና የዋህነት ማሳየት እንደ ፈሪነት ይወሰዳል ወይንስ እንደ ጀግንነት? በሰርግና በልቅሶ፣ በበዓልና በጦርነት ወቅት ስለ እነዚህ ዕሴቶች ግጥሞቻችን የሚሉት ነገር አለን? በሰርክ ሕይወታችን ለአዝማሪ የሚወረወሩት ግጥሞቻችን ዛሬ ስለገባንበት ምስቅልቅል ምን ያስተምሩናል? አባባሎቻችን ምን ይነግሩናል? ተረቶቻችንስ ምን ይገልጡልናል?

### *"ሀገራቸው ወዲያ፣ ዳርቻ ቀበሌ*
### *ተበድሮ ገዳይ፣ ጥይት እንደ ጥሬ"*

በችግር ውስጥ ሆኖ፣ እንኳን የሚዘራ የሚበላ ጥቂት ጥራጥሬ ለነሣው ድኻ ገበሬያችን ምንድን ነው የመከርነው? ክንዱን ማፈርጠሚያ፣ ጠኔን መጠየፊያ ወኔ እንደማስታጠቅ፤ ጭራሽ የድህነት ብጤውን ደም እንዲያፈስ "ተበድሮ ገዳይ" የተሰኘ ስንኝ እንቋጥራለን።

ትክክለኛ የዝንተ ዓለም ጠላቱን ኋላ ቀርነትና ድህነቱን እየሸሸግን፣ የድህነትን ቀንበር አብሮ የሚያሸካክመውን ድኻ ወንድሙን እንዲገድል በስውር እናነሣሣዋለን።

ምክራችንን አላደምጥ ብሎ ከድህነትና ከበሬዎቹ ጋር ሲታገል ዘመኑን የፈጀ ገበሬ የሰው ነፍስ ለማጥፋት ኅሊናው አልፈቅድ ሲለው እንኳን፣ ለእምነቱ ልንተወው ፈቃደኛ አልነበርንም፡ አባቱ በእርጅናው ዘመን ይጦረኛል፣ ቤተሰቦቹ መጠለያ ዋርካ ይሆነናል፣ ዘመድ አዝማድና የቀዬው ሰው ለሀገርና ለወገኑ አምባ

መጠጊያ ይሆናል ብሎ ተስፋ የጣለበትን ወጣት ወደ ሻትነው ዐመፅ፣ ጸብና መገዳደል ለመምራት አዲስ ስንኝ ቋጥረን መርዛችንን እንዘራለን።

*"አባቱ ነበር ቀንበር አንጠልጣይ*
*ልጁ ደረሰ በጩቤ ዘንጣይ፤*
*አባቱ ነበር ዳዊት ደጋሚ*
*ልጁ ደረሰ በእርሳስ ለቃሚ፤*
*አባቱ ነበር ከብት አባራሪ*
*ልጁ ደረሰ ቅልጥም ሰባሪ፤"*

ቀንበር "አንጠልጠሎ" ሺሕዎችን በመመገብ የሰው ልጆችን ሕይወት ማስቀጠልን የቂል ግብር አድርገን ሣልነው። በእርሱ ምትክ በጩቤ ዘንጥሎ ሕይወት ማጥፋት የብልህ ሥራ ሆነ። ዳዊት ደግሞ፣ ሶላት ሰግዶ "ኃይል የፈጣሪ" እንደሆነ ከሚያምን አባት ይልቅ፤ በገዛ ነፍጡ የሚያደላድል ፈላጭ ቆራጭ በእርሳስ ለቃሚ ልጅ ብልጥ ተደረገ። ከብት አባሮ እያረሰ እየወቃ እያበራየ ኑሮውን ከሚገፋ ገበሬ ይልቅ፤ ቅልጥም እየሰበረ፣ ቋንጃ እየቆረጠ በሽፍትነት የሚፎንን የበለጠ ትልቅ ተደርጎ ታየ። ወጣቱን ገበሬ ለጠብ ቆስቁሰነው ካልተሳካ፣ ወደ እኅቱ መዞራችን አይቀሬ ነው። መግደል የሚጠየፉ አባትና ወንድም ያሏት ኮረዳ፣ በቤተሰቦቿ ጨዋነት እንዳትኮራና አንገቷን ቀና አድርጋ እንዳትሄድ ትወቀሳለች። ሰላም ወዳድነታቸው ከሞኝነት፣ ጨዋነታቸው ከፍርሃት ተቆጥሮ በትሕትናቸው እንድታፍር በቅኔ በትር ትሸነቆጣለች።

*"ገዳይ ገዳይ ያልሺው፣*
*ጀግኔ ጀግኔ ያልሺው፣*
*አባትሽ አይገድል፣ ወንድምሽ አይገድል፣*
*አርሶ ያብላሽ እንጂ፣ ሆድሽ እንዳይጎድል"*

መግደል የኮረዶቻችንና የጎረምሶቻችን የፍቅር መስፈሪያ፣ የውበት መለኪያ እስኪሆን አጎልምሰነዋል። የከንፈር ወዳጆች መሞጋገሻና የብቃት መለኪያ እስኪመስል እየደጋገምን በዜማና ግጥም አሸሞንሙነነዋል። ጭራሽ መሣሪያ ማንገት እንደ ባህል ተቆጥሮ ከአልባስ በላይ እንደ ኩታ የሚጎናጸፉት ማኅበረሰቦች ብዙ ናቸው። በዚህም የተነሣ ጭምት የገበሬ ልጅ ዐይኑን ያሳረፈባት ኮረዳ፣ የፍቅር ምርጫዋን እንዲህ በማለት ትገልጻለች።

*"ገዳይ እወዳለሁ፣ መራዥም አልጠላ፣*
*ሲደክመኝ ዐርፋለሁ፣ በጎፈሬው ጥላ"*

ሰው ከሰው ሲኖር ሁሌ ፌሽታና ደስታ የለም። አንዳንዴ ጠብ ይከሠታል። በተረትና ምሳሌው "እንኳን ሰው ከሰው፣ ብርሌ ከብርሌ ይጋጫል" የተባለው ካለ ምክንያት መቼ ሆነና? ይህን መሠረት አድርገው የተፈጠሩት ሥነ ቃሎቻችንስ? በተጣሉ ሰዎች መካከል ዕርቅን ጋበዙ ወይስ ጠብን?

*"ጀግኔ ለጠላው ሰው፣ አያውቅም መሳሳት*
*ሚስቱን ባንድ ጥይት፣ ቤቱን በገል እሳት"*

ከተጣዮች መካከል ጀግና መሰኘት የወደደ ከሽምግልና ይልቅ ጠመንጃውን ይታመናል። ጠመንጃውን ደግኖ በጠላው ሰው የሕይወት ክፋይ በሚስቱ ላይ ይተኩሳል። አጋር ይነጥቀዋል። በዚህም አይቆምም፤ ዞሮ ማረፊያውን ጎጆውን ያነድበታል። ግን በቅሬታ ወይ በሐዘኔታ አይደለም። እንዲያ ከሆነ ጀግንነቱ ጥያቄ ውስጥ ይገባል። ይሄን ሁሉ ጭካኔ ያለስስት መፈጸም አለበት። የምክሩ ጭካኔ አሳቆት አንገቱን የደፋ ሰው ካለስ?

*"ማመንታቱን ትተህ፣ በለው ሳትቀደም*
*ገላጋይ አያጣም፣ በኋላ ያለደም"*

አንተ ብትራራ እንኳ ባላንጣህ አይራራልህም። ያለህ ምርጫ መሞት ወይም መግደል ብቻ ነው›› ለማለት መሆኑ ነው። እርሱ ብቻም አይደል ዋናው ‹‹አንተ ቅደም እንጂ ሽማግሌዎቹ በኋላ በቀል እንዳይፈጸምብህ ይመክቱልሃል›› የምትል እጅግ ተቀጣጣይ ሐሳብ አለች። እንዲያም ሆኖ ጸብ ከሁለቱም ወገን በቶሎ አልቀሰቀስ ቢለን ወደ መነዝነዝና መጨቅጭቅ እንሄዳለን። ሁለቱን ጠበኞች እየዞርን ለጠብ እንለማመጣለን።

*"ጎበዝ ሰው ግደሉ፣ ሰው መግደል ይበጃል*
*ይዋል ይደር ማለት፣ ጠላት ያደረጃል"*

ይሄን ያክል ነፍስ መጥፋት የሚለመንበትና የሚበረታታበት ልማድ አለን። ይዞ በሚመጣው መዘዝ እየተስፈራራ፣ ሞት እየተቀጠረ ‹‹ለምሳ ያሰበህን ለቁርስ አድርገው›› በሚል ፈሊጥ የሚበጀው ቀድሞ መግደል መሆኑን ይሰብካል። በእርሱ አድማጭ ካጣን ምክራችን ወደ ተፈጥሯዊ እውነታ ይዞርና ለገዳዩ ከተፈጥሮ ምሳሌ እናመጣለታለን።

*"አወይ ዋርካ ሞኙ፣ አወይ ሾላ ሞኙ፣*
*ሳያብብ ያፈራል፤*
*አንዱን ካልገደሉት መች ሌላው ይፈራል?"*

በዕውቀት ራስን ማጎልመስ፣ በሽምግልና መጠበብና በሞያ መካን ክብርና መፈራትን ኢያጎናጽፉም።

ለመፈራት መግደል ግድ ነው ይላል ሥነ ቃሉ። የሚመራን ከሰማይ የወረደ ወይም ከሌላ ሩቅ የመጣ አይደለም። ሥልጣን የሚይዙትም ሆነ ሕዝብ የሚሆኑት የኛው የራሳችን ልጆች ናቸው። ልጆቻችንን ዕድል፣ አጋጣሚና ጥረት ረድቷቸው የመሪነትን ዘውድ ቢቆናጠጡ የሚመሩን በምን ባህል ነው? በልጅነት አእምሯቸው ላይ የቀረጽናቸው ስንኞች ምን ዓይነት ገዢ ሊሆኑ እንደሚገባቸው የሚያመላክቱ ናቸው።

*"በደም ካልነከሩት እንደ እመጫት አልጋ፣*
*ሀገሩ ሀገር አይሆን፤ አልጋውም አይረጋ"*

ብዙ ሀገራት በብረትና በደም ተመሥርተዋል። ይህ የማይካድ የታሪክ እውነት ነው። ተመሥርተዋል ማለት ግን በጥሩ ተመርተዋል ማለት አይደለም። ሕግና ሥርዓት ያልሰፈነበት ሀገር ናፋቂዎች በመሆናችን፣ ሥልጣን ደም ካልፈሰሰበት አይረጋም የሚል ድምዳሜ በፖለቲካ ባህላችን ላይ እንዲያጠላ አድርጓል። ነገ ሥልጣን የሚጨብጡ ልጆቻችን የሚመሩትን ሕዝብ በምን ዓይነት መንገድ ይምሩት? በፍርሃት ወይስ በፍቅር? በፍትሕ ወይስ በጭካኔ? ሥነ ቃላችን መልስ አለው።

*"በሬውን እረደው!*
*ሚስቱንም አግባበት!..*
*ቤቱንም አቃጥለህ አድርግለት አመድ፣*
*ሲጨንቀው፣ ሲጠብበው ያረግሃል ዘመድ"*

በሬ በእርሻ ለሚተዳደር ሰው ያለውን ትርጉም እያወቅን፣ የትዳርን ክቡርነትና የሀገር መሠረትነት እየተረዳን፣ የቤትን ዞሮ መግቢያነት እየተገነዘብን ይሄን ምክር እናስበው። በሬውን አርዶ፣ ሚስቱን አግብቶ፣ ቤቱን አቃጥሎ ተስፋ አሳጥቶ፣ የመዛመድ "ጥበብ" በሙዚቃዎቻችንና በስንኞቻችን እየታዘለ በምድራችን ላይ ይዘራል።

እንዲህም ተሁኖ ክብርና መፈራትን የጨበጠው አካል የምትገጥመውን እያንዳንዷን ተቃውሞ፣ ችግርና ፈተና፣ በመንገዱ የሚቆሙትን ተግዳሮቶች ሁሉ እንደ ጉድፍ እየጠረገና እየከላ ይጓዛል፤ የሚቋቋመውና የሚጋፈጠው ቢኖር እንኳ መልሱ ስለት ነው፣ ለምን? በስንኝ ያኖርንለት የአመራር ጥበብ ነዋ!

*"ከአፎቱ ይውጣ ጎራዴ ሳንጃው*
*ደም በደም ይሁን መረማመጃው"*

በሥነ ቃሎቻችን ውስጥ ጀግንነት የተሳለበት አጠቃላይ ገጽታ በሁሉም የሕይወት ዘርፍ ላይ ያለው ተጽዕኖ ጥልቅና ሰፊ ጥናትን ይጠይቃል። ግን ደግሞ ፊታችን ላይ ገደል ተንዶ ሲወድቅ፣ በድቅድቅ ጨለማ ሰማይ በአብሪ ኮኮብ መታረሱን እያየን፣ ሳናፍርና አንገታችንን ሳንደፋ፣ ለውጥ የለም የምንል ከሆነ፣ በትክክል

ለድምዳሜያችን መሠረት የሚሆን ምክንያት ማቅረብ ይኖርብናል። ሁልጊዜ ጽንፍ ላይ መንጠልጠል እንጂ ወርቃማውን መካከል ላለማወቃችን አሳማኝ ምክንያት ሊቀርብ ይገባል።

ፈሪ አለበለዚያም ጀግና ብቻ ሆነን የምንገኘው በምን የተነሣ ነው? በአንድ ጀንበር የለውጥ ንፋስ መንግሥትን ተክተን የምናስፈራ አውሬ የሚያደርገን የሞራል መሠረት ከምን የመነጨ ነው? በውጊያ ላይ ድል አድራጊነትን የሚያጎናጽፍ ጀግንነት የመታደላችንን ያህል በአንዲት የጥይት ድምፅ እንደ ደነበረ የከብት መንጋ ሸሸት ውስጥ የሚያስገባን ጉዳይ ምንድር ነው? ሙሉ በሙሉም ባይሆን የሥነ ቃሎቻችን አስተዋጽዖ አንድ ምክንያት ሊሆን መቻሉን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

***የከረረ ይበጠሳል፣***

***የበደለ ይወቀሳል!***

*ስለታም ሰይፉን ባናትህ - እንደ ፍላፃ አንባርቆ*

*መሬት የሰፋህ ወደታች - በግሩ ተረክዝ ጨፍልቆ*

*በሸንፈት ገደልህ መሐል - ተማጽኖህ ሲላወስ በዕንባ*

*ባዝራ እንደሚገራ ጋላቢ - ልጓሙን መዳፍ ያስገባ*

*ቁጣውን ዋጥ ያደረገ - ጠላት መሆንህን ሳይፈራ*

*ሰይፉን አፎት መልሶ - እግሩን ከላይህ ያነሣ*

*ከመግደል ራሱን ያራቀ - በምሕረት ነፍሱን ያጸና*

*ሀገር ያሻውን ይበል - ለኔ ግን እርሱ ነው ጀግና።*

እሑድ፣ ጳጉሜን 4 ቀን 2011 ዓ.ም. እና መስከረም 5 ቀን 2011 ዓ.ም.! ታሪክ የማይዘነጋቸው ደማቅ ቀናት ነበሩ። ነፍጥ አንግበው መንግሥትን በጠብመንጃ ሲታገሉ የነበሩ የዐርበኞች ግንቦት ሰባት እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አመራሮች የተደረገላቸውን ጥሪ ተከትለው ወደ ሀገራቸው ገቡ፡ ከቦሌ ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ ጀምሮ እስከ መስቀል አደባባይ ጠጠር መጣያ እንኳ የሚገኝ አይመስልም። ከመላ ሀገሪቱ ተጓጉዘው ዋና ከተማ የደረሱት ደጋፊዎች ፊት ላይ የነበረው የደስታ፣ የተስፋና የናፍቆት ፊት ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም መገናኛ ብዙኃንን ትኩረት የሳበ ነበር።

በመሪዎቹ ገጽታ ላይ የሚነበበው ስሜት ያለፉበትን መንገድ ቁልጭ አድርጎ ይናገራል። በወቅቱ እነዚህ ኃይሎች ወደ ሀገራቸው ሲገቡ መንግሥት ባደረገው ጥሪ መሠረት ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ያደርጋሉ ተብሎ ታስቦ ነበር። በአንዳንድ ተከታዮቻቸው ልብ ውስጥ ይመላለስ የነበረው ሐሳብ ግን ወጥ አልነበረም። ጥቂት የማይባሉት ደጋፊዎቻቸው ሕጋዊዉ የመንግሥት መዋቅር በታጋዮቹ የሚተካ ይመስላቸው ነበር። በመደጋገም የሚሰማው “የሽግግር መንግሥት” የተባለ ሐውልት ይተከላል ብሎ የሚያምን ደጋፊም ነበር። እናም ያ

በቀጥታ መሆን ሳይችል ሲቀር ከመሪዎቹ መግባት ብዙም ባልራቀ ጊዜ ውስጥ ግጭቶች እዚህም እዚያም በየማዕዘኑ መፍላት ጀመሩ። በጋለ ብረት ምጣድ ላይ እንደተዘረገፈ ፈንዲሻ እዚህም እዛም መንጣጣትና መስፈንጠር ጀመረ።

በሽግግሩ ዘመን፣ ከዕለታት በአንዱ ቀን፣ የኦነግ መሪዎች ወደ አዲስ አበባ መምጣታቸውን ተከትሎ የተነሣው ፖለቲካዊ ቁርቁስ ሰላም የሚነሳ ሆነ። በዚህም ሳቢያ ንግድ ተቀዛቀዘ፣ ኢንቨስትመንት ባለበት ከመርገጥ አልፎ የቁልቁለት ጉዞ ሆነ። ጥርጣሬና አለመተማመን በነገሠበት አካባቢ ሁሉ እንደሚሆነው ንብረት የሚሸጥም ሆነ የሚገዛ ጠፋ። የሚመጣው ስለማይታወቅ፣ ሁሉም ያለችውን የሙጥኝ ብሎ ባለበት ተንጠልጥሎ ቀረ። ሌላ ሌላው ነገ ሀገር ሰላም ሲሆን ይደረስበታል ተባለ። በየትኛውም ሀገር ቢሆን በመንግሥትና ባለው የፖለቲካ ሥርዓት ያልተማመነ ማኅበረሰብ እንዲህ ነው የሚያስበውና የሚኖረው።

በአሮጌው ተደስተንና ረክተን በምቾት መኖራችንን በማቆም በእያንዳንዱ ዕለት የላቀውንና ከፍ ያለውን ዓለም በመመኘት ለእርሱም እውን መሆን መታገል ይገባን ነበር። እኛ ግን እንደምንም ራሳችንን ወደኋላ ለመመለስ እንፈቅዳለን። ወደ ላቀው የከፍታ ስፍራ መውጫው መንገድ የእኛ ፈቃድና ከትናንት የመላቀቅ ፍላጎት እንጂ ሁሌም አብዮት ሊሆን አይገባም። መግደል መሸነፍ ነው።

አዲሱ የለውጥ መንገድ ያልተጓዝንበትና ያልሞከርነው አዲስ መንገድ ነው። በዕለት ተዕለት ርምጃችን ብንችል ለሕዝባችን የምሥራች እንጂ መርዶ ነጋሪ ሟርተኞች እንዳንሆን መጠንቀቅ ይገባን ነበር። በሁኔታዎች መወሳሰብ ግን ከራሳችን አልፈን ለሕዝብ የገባነውን ቃል በተግባር ማረጋገጥ በየዕለቱ ከባድ ፈተና እየሆነ መጣ

በጊዜው በቡራዩ የነበረው ረብሻ ቆይቶ በቪዲዮ ሲታይ አሳዛኝ ነበረ። ዱላ የያዙ ለጋ ወጣቶች በቡድን በቡድን ሆነው፣ ሌሎች ወጣቶችን ያባርራሉ። ደብድበው በሞትና በሕይወት መካከል ጥለዋቸው ይሄዳሉ። የአካባቢውን ሱቆችና የንግድ ድርጅቶች ይዘርፋሉ። የዘረፉትን ተሸክመው ይሮጣሉ። ከመጣደፋቸው የተነሣ በሸሸቱ ወቅት እርስ በእርስ እየተገጫጩ ይወድቃሉ። ከወደቁበት ተነሥተው የዘረፉትን ንብረት ተሸክመው እንደገና ይሮጣሉ። እንደ መሪ ይህንን ማየት የሚያሰቅቅ ነበር።

በርግጥም ያ ትዕይንት ሀገራዊ ሕግና ደንብ ተንዶ ኃይል በጥቂት ጉልበተኛ የሰፈር አለቆች መዳፍ ውስጥ ሲወድቅ፣ ማኅበረሰብ ሊደርስ የሚችልበትን የሥርዓተ አልበኝነት ጥግ ማሳያ ነበር። በቡራዩ የረብሻ ሰሞን፣ ኋላም በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተስተዋለው ትዕይንት፣ ሰዎች ፖለቲካን በተሳሳተ መንገድ ተርጉመውና አጉብጠው ለራሳቸው ጥቅም ማስፈጸሚያ ሲሉ የሚጓዙትን ርቀት በዐይናችን በብረቱ የታዘብንበት ነበር። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የአፍሪካ መዲና በሆነች ከተማ፣ በአንድ መንደር በተከሠተ አሳፋሪ ትዕይንት፣ ሀገርን ወደ ሩዋንዳ ዓይነት እልቂት ሊከትት የሚችል ፖለቲካ እንዴት በቀላሉ ሊያቆጠቁጥ እንደሚችል በዐይናችን

አይተናል፡፡ በቅጡ ያልተደራጀና ይህ ነው የሚባል ጦር የሌለው የተቆጡ ወጣቶች ስብስብ ይሄን ማድረግ ከቻለ፣ የተደራጀ ቡድንና በደንብ የታጠቀ ጦር ምን ሊያደርግ እንደሚችል አስደንጋጭ ፍንጭ ሰጥቶናል፡፡

በቡራዩ ተጀምሮ ያስደነገጠን ክሥተት፣ በምዕራባዊው የሀገራችን ክፍል ደግሞ ጭራሹኑ ወደ ሙሉ ትዕይንት ተቀየረ፡፡ በቦሌ የገቡት ታጋዮች ተከታይ ነን የሚሉ ታጣቂዎች የመንግሥት መዋቅር አፍርሰው የኃይል አስተዳደር የመትከል አዝማሚያ አሳዩ፡፡ መንግሥት “የከረረ ይበጠሳል፣ የበደለ _ ይወቀሳል” በሚል ሆደ ሰፊነት የከፈተውን የሰላም በር ተጠቅመው ወደ ሀገር የገቡ ቡድኖች ተአማኒነቱንና የሕዝቡን ተስፋ የሚያከስም ተግባር መፈጸሙን ተያያዙት፡፡

ጭራሽ ከመሥመር በወጣና ሐላፊነት በጎደለው አካሄድ ታጣቂዎቹ ትጥቃቸውን የመፍታት ስምምነታቸውን ዘነጉት፡፡ ይባስ ብሎ የጥሪ ቀጣናዬን አትድፈሩብኝ እስከ ማለትም ደረሱ፡፡ ዝርፊያና አፈና፣ ሞትና መፈናቀልም በየክልሉ በረታ፡፡ ብዙዎች ይሄንን ድርጊት በአንድ በኩል ከገቡት ኃይሎች ክህደት ጋር አያያዙት፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት የሕግ የበላይነት ለማረጋገጥ ያሳየው ዳተኝነት መገለጫ ተድርጎ ተወሰደ፡፡ አንዳንድ ከለውጡ በተጻራሪ የቆሙ ፖለቲከኞችም የመንግሥትን ዐቅመ ደካማነት ማሳያ አድርገው በማቅረብ ድጋፍ ማሰባሰቢያ ሊያደርጉት መሞከራቸው ተስተውሏል፡፡

የበለጠ በቅርበት ተጠግቶ ለሚመረምር አስተዋይ፣ መንግሥት የተከተለው መንገድ በጥበብ የተከናወነ ብቻም ሳይሆን ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታንም ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ይረዳል፡፡ የትጥቅ ትግል ጉዞ ረዥም ነው፡፡ ትጥቅን ከትከሻ ላይ ማስጣልና ከአእምሮ ላይ ማስፈታት ፈጽሞ ይለያያሉ፡፡ አእምሮን ትጥቅ ማስፈታት የሥነ ልቡናና የሥነ ማኅበረሰብ ዕውቀቶችንና ለውጦችን የሚፈልግ ነው፡፡ አጠቃላይ ማንነትን መለወጥን ይጠይቃል፡፡ የሀገራችን ፖለቲካ ባለፈበት እጅግ ጥልፍልፍና የመካካድ ፍኖት የቆሰሉ፣ የተጎዱና ተገድደው ወደ ትግል የገቡ ኃይሎች አሉ፡፡ እነዚህን ኃይሎች ወደ መተማመን ማምጣት ከባድ ነው፡፡ በሰላም አብሮ ወደ መኖር ማሸጋገርም አስቸጋሪ ነው፡፡ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ሥራውን ቋጭቶ ያስገኘውን የተትረፈረፈ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ተቋዳሽ እንዲሆኑ የጠራቸው ይመስላቸዋል፡፡

ጥሪው “አብረን እንግዛ ሳይሆን “አብረን እንገንባ የሚል መሆኑን የተረዱት አይመስሉም ምናልባት ብንከዳ በሚል በስንት መከራ የሰበሰቡትን መሣሪያ ለመፍታትና አሳልፈው ለመስጠት ይቸግራቸዋል፡፡ የዚህ ሁሉ ጥርጣሬያቸው መነሾ ግን በምንም መልኩ ከራሳቸው ጋር ብቻ የሚያያዝ ነው ብሎ መደምደም አዳጋች ነው፡፡ እነርሱም ቢሆኑ ያለፈው የፖለቲካና የማኅበረሰብ ታሪካችን የቀረጸባቸው ባሕርያት ውጤቶች ናቸው፡፡ የሀገራችን የፖለቲካ ትግል በጭካኔና በመጠላለፍ የተሞላ መሆኑን የሚያሳዩትን እኒህን ስንኞች እየሰሙ ያደጉ ናቸው፤

*ገሥግስን ና በለው፣ ገሥግስን ና በለው*

*ጠላትክን እንደ በሬ አጋድመህ እረደው፣*

የሰው ልጅ ጠላት በመሆኑ ብቻ እንደ በሬ አጋድሞ እስከማረድ የሚጓዝ ጭከናን ታቅፈን፣ ሰላማዊ ፉክክር እንዴት ሊታሰብ ይችላል? የጠፋንና ያልተረዳነው ነገር አለ ወይስ የአያያዝ ስሕተትና ወጣ ገብነት አለ? ለእነዚህ ብርቱ ጥያቄዎች በቀላሉ መልስ ማግኘት እንደማይቻል ግልጽ ነው።

አንድ ጥንታዊ የፈረንጅ ተምሳሌት በማከል ሐሳቤን ላስረዳ። በአንዲት መርከብ ተጭነው ወደ ተስፋይቱ ምድር በሰው ልጆች መሪነት ይጓዙ የነበሩ ድመቶች ነበሩ። በኃይለኛ የውቅያኖስ ማዕበል ሳቢያ መርከበኞቹ ራሳቸውን ለማትረፍ መርከቡንና ድመቶቹን ትተው በትንሽ ጀልባ ተለይተው ያመልጣሉ። ድመቶቹን የጫነችው መርከብ ግን በማዕበል ተገፍታ ማንም ካልጠበቀው ከአንድ ያልታሰበ ወደብና የምድር ዳርቻ ላይ ታርፋለች። በመርከቢቱ የተጫኑት ድመቶች ምንም እንኳን ከማዕበሉ አደጋ በሕይወት በመትረፋቸው ደስታ በውስጣቸው ቢፈጠርም፣ ካሰቡት ቀርቶ ካላሰቡት ዳርቻ በመድረሳቸው ሥጋትና ፍርሃት በውስጣቸው መፈጠሩ አልቀረም።

ከምንም በላይ ተስፋቸውን ያጨለመው በዚያ የባሕር ዳርቻ የሚላስ የሚቀመስ ነገር አለመኖሩ ነው። በነፋሱ ከወዲያ ወዲህ የሚርገበገቡ ጥንዚዛዎች እና በጭቃማ አፈር ውስጥ ገላቸውን የቀበሩ ቅንቡርሶች ከመኖራቸው በቀር ምንም የሚበላ ነገር የለም። እናም ድመቶቹ በዚህ የሕይወት መንታ አማራጭ መሐል ሆነው ከመርከባቸው ሳይወርዱ በሐሳብ በመዋለል ላይ ሳሉ አንድ የድመቶች የጎበዝ አለቃ ጉሮሮውን ጠራርጎ እንዲህ አለ፡-

"በማንም በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ድመታዊ ማንነታችሁን ለመካድና ለመለወጥ የማትደራደሩ ድመታውያን ሆይ! እኛን ድመቶችን ድመት ያደረገን ምግባችንና የዕለት እንጀራችን ቀርቦልን ሳይሆን አድነንና ጥረን ግረን የምንበላ መሆናችን ነው። ከአደን ውጭ ድመታዊ ማንነት የለም፤ ሊኖርም አይችልም። እኛ የኑሯችን ሳይሆን የማንነታችን ውጤቶች ነን። በመሆኑም በዚህ ባሕር ዳርቻ የምንከተለው የሕይወት መንገድ መራራ ቢሆንም በአየሩ ላይ ውር ውር ባዮቹን ጢንዚዛዎች አድኖ በመመገብ ብቻ ሊሆን ይገባል። ከዚያ ውጭ ሆዳችንን ለመሙላት ስንል የምናደርገው ሽር ጉድ በድመታዊ ማንነታችን ላይ ክህደት መፈጸም በመሆኑ ዛሬ በሥጋ ነገም በነፍስ የምንጠየቅበትና በታሪክም የምንወቀስበት ምግባር ነው" በመርከቡ ላይ ካሉት ድመቶች መካከል በቁጥር ጥቂት የማይባሉ ድመቶች የጎበዝ አለቃውን ድመት ንግግር ተከትለው ከኋላው ተሰለፉ።

"ድመታዊ ማንነት ብሎ ነገር የሥራ ፈት ከንቱ ፍልስፍና ነው። ድመቶች መኖራቸው እንጂ የማንነት መሠረታቸው አይደለም የመኖር ምንጫቸው" አለ ሌላኛው፡ አስከትሎም "ዝንጀሮስ ብትሆን ምንድር ነው ያለችው፣ መጀመሪያ የመቀመጫዬን አይደለምን? አያ ጅቦም ቢሆን ሽኮናው ድፍን የሆነውን መብላት ያረክሳል› ቢሉት ብልቼው ልቀደስ አላለም? እኛ ድመቶች አዳኝ ማንነት አለን ብለን ራሳችንን በረሐብ የምንቀጣ መሆን አይኖርብንም። ምንም እንኳ አናቱን መረሬ ጭቃ ውስጥ ቀብሮ የማይሸሽና የማይንፈራገጥ

ቅምቡርስ ሆዳችን እስኪተረተር ድረስ መብላት አጓጊና አስደሳች ባይሆንም ከረኃብ መሻሉን ማንም መካድ አይቻለውም። ስለዚህ አንዳንድ ጽንፈኞች በሚያቀርቡት ከንቱ ምክር ሳንዘናጋ መኖርን እናስቀድም” ሲል ተናገረ። የቀድመውን የኀበዝ አለቃ ከተከተሉት የበለጠ ቁጥር ያላቸው ድመቶች፣ ሁለተኛውን የኀበዝ አለቃ ተከትለው ወደ ረግረጉ ጭቃ ተሠማሩ።

“ኧረ ጥቂት እንረጋጋ!” ሲል ድምፁን ከፍ አድርጎ መናገር የጀመረው ሦስተኛ ድመት በሁለት ጽንፍ በቆሙት የኀበዝ አለቆችና ተከታዮቻቸው የመደመጥ ዕድል ማግኘት አልተቻለውም ነበር። እንዲያም ሆኖ ሐሳቡን ከመግለጽ አልተመለሰም። “ውድ የትግል አጋሮቼ ድመቶች! ከባድ ቢሆንም በርጋታ ለማሰብ እንሞክር። ከፊታችን ያለው አማራጭ ሁለት ብቻ ወይም ግራና ቀኝ ብቻ አይደለም። ድመታዊ ማንነታችን እንዳይጠፋ ጢንዚዛዎችን በማደን መመገብ እንችላለን። ግን ደግሞ እርሱ ብቻውን በሕይወት ለመቆየት በቂ ስለማይሆን ወደ ረግረጉ ወርደን ቅንቡርስ ብንበላም ችግር የለውም። በሁለቱም አማራጭ መኖርና ማንነታችንን በእኩል ማቆየት እንችላለን” አለ ሦስተኛው ድመት።

በመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ወደ ሁለቱ ጽንፍ ራሳቸውን ያቆራኙት ድመቶች ቁጥራቸው የላቀ ነበር። በተለይም ድመታዊ ማንነት የሚቀነቀንበት ካምፕ በቁጥር በርካታ አባላት ነበሩት። ይሁንና ምግቡ በቂ ባለመሆኑና ረኃቡም በማየሉ ጥቂት የማይባሉ ድመቶች አቋማቸውን ቀይረው ወደ ረግረጉ አቀኑ። ከእነርሱ ተለይተው የቀሩት የስድብና የርግማን ናዳ ያወርዱባቸው ጀመር። መሳደብ ብቻ አይደለም፤ ያስፈራሯቸውም ጀመር። ይሄ በእንዲህ እንዳለ፣ አንድ ትንቢት ጎልቶ መደመጥ ጀመረ። ይሄውም፣ ድመታዊ ማንነታቸውን ጠብቀው እስከሞት የዘለቁ የድመት ነፍሶች የሰው ልጆች ማዕበሉ አልፎ ወደ ዳርቻው ሲመጡ በክብር ሥጋና ነፍሳቸው ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚወሰድ መሆኑ በሰፊው መነገር ጀመረ። ይህም ጥቂት ጽንፍ ይዘው የነበሩትን ሊያበረታ ቢችልም አብዛኞቹ ድመቶች ግን መካከለኛውን መንገድ መርጠው ማዕበሉ እስኪቀንስና መርከበኞችም መጥተው እስኪያድኗቸው በጽናት መጠባበቅ ቀጠሉ።

ጊዜው ቢቆይም በትንቢት እንደተነገረው ማዕበሉ ሲረጋ መርከበኞቹ መጡ። መካከለኛውን መንገድ ይዘው የተጓዙት ተመልሰው ወደ መርከቡ ወጡ። ከባሕሩ ዳርቻ ሲደርሱ፣ ከአዳኝ ማንነታችን አንወጣም ብለው ጢንዚዛ ብቻ ሲመገቡ የቆዩት ድመቶች በምግብ እጦት ሞተው ነበር። በስሜት ተገፍተው ማንነታቸውን ፍጹም ረስተው በጭቃ ውስጥ መኖር የጀመሩት ድመቶችም ዳግም ወደ ቀድሞው ማንነታቸው ለመመለስ አልፈቀዱም። በዚህም የተነሣ መርከበኞቹ እዚያው የጭቃ ማጥ ውስጥ ጥለዋቸው ወደ ተስፋይቱ ምድር አቀኑ። ወርቃማውን አማካይ የተከተሉት ድመቶችም የተስፋዪቱን ምድር ለመመልከት በቁ።

በመከራ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ዘወትር ወርቃማውን አማካይ መከተል ከጉዳቱ ትርፉ እንደሚያመዝን ርግጥ ነው። ወርቃማው አማካይ ነጠላ መሥመር አይደለም፤ ሰፊ አማካይ መንገድ ነው። እንደ ነገሮች ነባራዊ ሁኔታ ቦታን መቀያየር ያስችላል፤ ስትራቴጂን ለመለወጥ ሰፊ ዕድል ይፈጥራል። ወርቃማው አማካይ ነቢር ነበብ

(Realistic) ብቻ ሳይሆን ገቢር ነበብ (pragmatic) አካሄድም ነው፤ ነቢራዊ ሁኔታን እያነበቡ ገቢራዊ ሆኖ የመኖር ጥበብ። የትኛውንም ጽንፍ መያዝ ከተፈጥሮ፣ ከሰውና ከራስ ጋር የተካረረ ግጭት ውስጥ ከትቶ ያላትማል። መጥፊያችንም ሊሆን ይችላል። በታሪክ ሰፍሮ እንደሚነበበው አብዛኞቹ ግጭቶች፣ ጦርነቶችና አተካሮዎች መነሻቸው ጽንፈኛ ችኮነት ነው።

ዓለም ላይ እየተከሠቱ የሰውን ልጅ አብሮ የመኖር ተስፋ ያመናመኑ ግጭቶች ትናንት ነበሩ። ዛሬም በየአቅጣጫው አሉ፣ ከፈቀድንላቸው ነገም ይኖራሉ። ፈሊጠኞቹ "የጉድ ቀን አይመሽም" እንዲሉ ያስገደዳቸው፣ መውጫ የሌላቸው የሚመስሉ የጠብ ገደሎች፣ ንጋት የተጠየፋቸው የመሰሉ የግጭት ጨለማዎች በሰው ልጆች መካከል ተከሥተው "አያልፉም!" ሲባሉ እንደ ጤዛ አልፈዋል። በትጥቅ ትግል ውስጥ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ትጥቅ ትግል ያመሩት ለሰላማዊ ትግል ቦታ በማጣታቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ሁልጊዜም ትክክል አይደለም።ይልቁንም እነዚህ ኃይሎች በሰላምም ሆነ በጦርነት ሐሳባቸውን ገዢ አድርገው መጫን እንጂ ለምርጫ ማቅረብ የሚሆንላቸው አይደለም ብሎ መገመቱ ለእውነታው ሊቀርብ ይችላል፡፡ ከዚሁ በተቃራኒና በትይዩ በቡድን ስም ጥቂቶች የሚጠቀሙበት ሀብት በግልጽ መታወቅ አለመቻሉ የችግሩ አንዱ ምንጭ ነው። በእነዚህ ቡድኖች ውስጥ ቡድኑንና ሀገርን ከውስጥ የሚቦጠቡጡ የተለያዩ ነቀርሳዊ ችግሮች ይኖራሉ። እነዚህም በልዩ ልዩ መልኩ የተፈጸመ የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ በሕገ ወጥ ንግድ ተሳትፎ የተፈጸመ ወንጀል፣ በቡድኑ ውስጥ የተፈጠረ አንጃ ደጋፊነትና፣ ከሥልጣን ከተገለለው አካል ጋር ሆኖ ተደማጭነትን ከፍ ለማድረግ የሚሠራ ሤራና የመሳሰሉ ናቸው።

በዚህ ውስጥ የተገደሉ፣ የጠፉ፣ የተኮላሹ፣ ስቃይ የተፈጸመባቸው ዜጎች ጥቂት አይደሉም። እታገልለታለሁ ብሎ የወጣው ዓላማና በመጨረሻ የደረሰበት ግብ ሐር አምባና ቆቦ ሆኖ የተገኝ ጥቂት አይደለም። ለሕዝብ ብሎ ወጥቶ ለግሉ አትርፎ ተመልሷል። ይህ ደግሞ እታገልለታለሁ ከሚለው ሕዝብ ይነጥለዋል። በዚህ ንቅዘት ውስጥ ወደ ሰላማዊ አየር ሲመለስ የገንዘብ፣ የሐሳብና የመረጃ እጥረት ይገጥመዋል። እነዚህን እጥረቶች ለመቅረፍ የተለያዩ የመፍትሔ አማራጮችን ይማትራል።

የትጥቅ ትግል አድራጊው ብዙ ጊዜ ለጥቃትና ለምልመላ እንዲመቸው በአብዛኛው ጎረቤት ሀገሮቻችን ተቀዳሚ ምርጫዎቹ ናቸው። በተለይ ከሀገሩ ጋር ኩርፊያ ወይም ታሪካዊ ተቀናቃኝነት ወይም ጠብ ያላቸው ጎረቤት ሀገራት ይመቻሉ። ሀገራቱም በበኩላቸው ለታጋዩ ቡድን መንቀሳቀሻ ቀጣና በሀገራቸው ሲፈቅዱ በምላሹ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስጠብቅ አቋምና ተልእኮ ለቡድኑ ያሸክማሉ። ነጻ ምሳ የለምና! ይህ የተገኘ ገንዘብ ለሁሉም አባላት በፍትሐዊነት ይከፋፈላል ወይ? መልሱ ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ነው።

በሀገራዊው የትጥቅ ትግል የሚካሄድ የሀብትና የሥልጣን ድልደላ ትግሉን በመቀላቀያ ዘመንና ዕድሜ፣ በተፈጸመ ጀብድ ወይም ደግሞ በሀገር ቤት በሕዝብ ዘንድ ባለ ዕውቅና መሠረት የሚፈጸም ነው። ይሄም በጫካው ቡድን ውስጥ ከፍተኛ አመራርን ያካተተ የጥቂቶች አምባገነናዊ አንጃን ይፈጥራል። አንጃዉ

በደጓሚዎች የሚለገሰውን ገንዘብ አጥልሎ ለራሱ ያስቀራል። የትግሉ ዕድሜ ሲራዘም የአንጃው የገቢ መጠን ይጨምራል። ይህንን በደም ሸያጭ የተገኘ ገቢ ቢቻል የታጋዮችን ጉልበትና ዕውቀት በመጠቀም ጭምር በተለያዩ የንግድና የአገልግሎት ዘርፎች ላይ በመሠማራት ተጨማሪ ሀብት ለማካበት ይሞክራል። ባይቻል ደግሞ ከአበዳሪዎች ጋር የተሻለ ድርድር በማድረግ ተጨማሪ ርዳታ ለማግኘት ያቅዳል።

ይህ ነቀርሳዊ አንጃ መረጃ ለማግኘት የተለያዩ ሰላዮችን አሥርጎ ወደ ሀገሩ ማስገባቱ አይቀርም። የመታገያ ቀጣና የሰጡት ጎረቤትና የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለት የተለያዩ አካላት፣ ከሠርጎ ገቦቹ ሰላዮች ጋር ደርበው ዓላማቸውን የሚያሳኩበት ዘዴ ይወጥናሉ። በተቻለ መጠንም የሌላ ሀገር ዓላማ ፈጻሚዎች አንጃው ሳያውቅ ወደ ሀገር እንዲገቡ ይሞከራል። ይህ ከተሳካ የገዛ ወገኖቻቸውን በባዕድ ያስጨርሳሉ። ነገሩ ከሸፎ የሚታገሉት ሥርዓት ከደረሰባቸው ያገኘውን መረጃ ለሕዝቡ በማጋለጥ ደጋፊያቸውን ያመናምንባቸዋል።

የትጥቅ ትግል የተራዘመ ጦርነት እንደሆነ ለአፍታ መዘናጋት ጉዳቱ ተመን የለሽ ነው። ምናልባትም አንዲት ዘለላ መረጃ በበረሐና በጫካ የሚደርስበትን መከራና ችግር ተቋቁሞ የኖረ ሙሉ ብርጌድ ጦር በሰዓታት ያለወሬ ነጋሪ ልታስጨርስ ትችላለች። የሚፋለሙት መንግሥት በታጋዮቹ ጦር ውስጥ አሥርጎ ያስገባቸው ሰላዮች ሊኖሩት ይችላሉ። በጫካው ኢፍትሐዊ አያያዝ፣ በፍትሕ መጓደል ወይም ተስፋ በመቁረጥ ከጦሩ ብዙዎች ሊከዱና ለመንግሥት መረጃ ሊሰጡ ይቻላሉ። ምናልባትም በከለላ ሰጪው ሀገር የመንግሥት ሥርዓት ተቀይሮ የሚቃወሙት መንግሥት ደጋፊ ሥልጣን ሊጨብጥ ይችላል። በሌላም በኩል አበዳሪዎች ሊመናመኑ ይችላሉ። የገዛ ሕዝባቸው በጊዜ ብዛት ተስፋ ይቆርጥባቸዋል። ከነአካቴው ሊዘነጋቸውም ይችላል።

ይህ ሁሉ ሥጋት አስቀድሞ ከሀገር ወጥተው ወደ ትጥቅ ትግል እንዲገቡ ካነሣሣቸው በደል፣ እልህና ቁጭት ጋር ተጣምሮ ሲበዛ ተጠራጣሪ፣ ጨካኝና ምሕረት የለሽ ያደርጋቸዋል። ከወጡበት ማኅበረሰብ ዕሴትና ግብረ ገብነት የወጣ ተበቃይና ጠላፊ
የሆነ ሰብእና ይላበሳሉ።

ግባቸው ሥልጣን መያዝና መያዝ ብቻ ይሆናል። የችግር ሁሉ መፍትሔ እነርሱ፣ የችግር ሁሉ መድኀኒት ነፍጣቸው እንደሆነ ውስጣቸው ያምናል። እያንዳንዱ የቆሰሉት ቁስልና የፈሰሳቸው ደም፣ በትግል የተሠዉ ጓዶቻቸው፣ የባከነ ዕድሜያቸውና የረገፈ ወጣትነታቸው ሁሉ እንደ ዕዳ ተከማችቶ በእነርሱ በሚመጣ ለውጥ ብቻ ይወራረዳል የሚል ጽኑ እምነት ይይዛሉ።

በጊዜ ብዛት በመካከላቸው የሚፈጠሩት አለመግባባቶችና ግላዊ ጠቦች ይሰፋሉ። በሂደት ያበቀሏቸው ልዩነቶች እንደ ማኒፌስቶ ተቆጥረው ከዋናው ቡድን በአንጃነት ለመሰንጠቅ ያበቃሉ። ልዩነቶች በሐሳብ መሸናነፍ ወይም በሰላማዊ ልዩነት አይፈቱም። በጫካ ሕግ መሠረት የልዩነቶች ሁሉ መፍትሔያቸው ነፍጥ

ነው። ለትግል የተወጣበት ዋነኛው ተገዳዳሪ አካል ይዘነጋና የእርስ በርስ ጦርነት ሊነሣ ይችላል። የሚቃወሙት መንግሥት ይሄን ከተረዳ አንደኛውን ቡድን ነጥሎ ለመርዳት የሚቀድመው የለም።

በሀገር ደረጃ የሚታወቀው ውስብስብ ችግር ድንገት ታሪክና አጋጣሚ ፈቅዶለት ሊፈታ መንገድ ጀመረ እንበል። ሲታገሉት የነበረው ሥርዓት ተወግዶ በሌላ ተተካ። የተተካው ሥርዓት በሰላም ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ፈቀደላቸው፤ ጥያቄም አቀረበላቸው እንበል። ይቀበሉታል? ወይስ ይበቀሉታል? በርግጥ ይህ ጫካ ውስጥ የዳበረ አጉራ ጠናኝ እሳቤ ወደ ጠረጴዛ ሲጋበዝ ከታጋዮቹ መካከል ወረቀትና ብዕር የያዙ አንዳንድ ታዳሚዎችን ማግኘቱ አይቀርም። እነዚህ ታዳሚዎች የተነሡበትን ጥያቄ ያልረሱት ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ የተነሡበትን ጥያቄ፣ የተጓዙበት መንገድ ያስጣላቸው አሉ። እነዚህ ትከሻቸውም አእምሯቸውም የታጠቀ ነው። ስለዚህም ያነገቡት ጠመንጃ ከሚወርድ እሳት ከሰማይ ቢወርድ ይቀላቸዋል። የከፈሉት መሥዋዕትነት ያለ ደም የሚጠራ፣ ያለ ሬሳ የሚካስ አይመስላቸውም።

አንዳንዶቹ በረሐና ጫካ የበላውን ዕድሜያቸውን ከተማ ውስጥ ቢኖርና ቢሠራ ሊያገኘው ይችል ከነበረ ቁሳዊ፣ ክሂሎታዊና ቤተሰባዊ ዕድገት አንጻር ይመዝኑታል። በዚህ ሚዛን የከሰሩ ስለሚመስላቸው የትግላቸውን ስኬት ብቻ እንደ ስኬት ለመቀበል ይከብዳቸዋል። ግላዊ ጥቅም ካላመጣ በቀር። በደንባራ በቅሎ እንደ ተጨመረ ቃጭል፣ ደግሞ የታገሉለት ማኅበረሰብ ደግሞ "ገድሎ መፎከርን" እንደ ጀግንነት ይቆጥረዋል። ከዚህ ባህል አንጻር ሰላማዊ ጥሪን መቀበል በድካምና በተሸናፊነት ተተርጎሞ ክብር እንዳያሳጣቸው ይሠጋሉ። በጫካና በበረሐ ያገኙት የነበረውን ስም፣ ገድልና ጥቅም ላለማጣት ሲሉም ድኅረ ሰላም የነውጥ ትግላቸውን ይቀጥሉታል።

በድፍን ሀገራችን የተፈጸሙት ብጥብጦች፣ ግጭቶችና ወንጀሎች ይሄን ያረጋግጣሉ። መንግሥታዊ ለውጥን ተከትሎ አካባቢያዊ ግጭቶች፣ ዝርፊያዎች፣ ቅሚያዎች፣ የጅምላ ፍርዶች ሲፈጠሩ በታሪካችን የመጀመሪያ አይደለም። ለውጥን ተከትሎ የመንግሥት መዋቅር መዳከም ዛሬ አልተጀመረም። የልጅ ኢያሱ መንግሥት በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ሲተካ፣ የዐፄ ኃይለ ሥላሴ በደርግ ሲተካ፣ ደርግም በተራው በኢሕአዴግ ሲተካ በሽግግሮቹ ምዕራፍ ላይ ብዙ ጆሮን ጭው የሚያደርግ ነገር ተከሥቷል።

በእነዚህ ጊዜያት የተፈጸመው ነውር በስፋትም በጥልቀትም እንዳሁኑ ሥር የሰደደ አልነበረም። ለምን የአሁኑ ባሰ? ብሎ መጠየቅ ይገባል። ነገሩን በሁለት አንጓ ልናየው እንችላለን። በተደጋጋሚ በለውጥ ዘመን እየፈጸምናቸው ያለፍናቸው አስነዋሪ ተግባራት አልታረሙም። አንዱ የቀደመውን የክፋት ሪከርድ እየሰበረ ነው የተጓዘው። ስለዚህም እየባሰ እንጂ እየተሻሻለ አይሄድም። በሌላም በኩል በዜጎች መሐል እየተዘራ የመጣው የጥላቻ ዘር ፍሬ እየሰጠ መጥቷል ማለት ነው። በሀገር ደረጃ የሞራል መሠረት ወርዳ ወለል ላይ ቁጭ እስከምትል ተጥላ ነበር። በድፍን ሀገር በዕድሜም ሆነ በሃይማኖት፣ በሀብትም ሆነ በዕውቀት የሚከበር ፍጡር ጠፍቶ ነበር። ጥሎ ማለፍና መተላለፍ እንደ መልካም ዕሴት ይቀነቀን ጀምሮ ነበር።

ተቋማዊ በሆነ መልኩ ዐቅም ተሰጥቶት ሲሰበክ የከረመው መለያየት እንጂ አንድነት አልነበረም። ‹በቡሓ ላይ ቆረቆር› ይባላል። እነዚህ ሁሉ እየተሸረሸሩ በመጡበት ጊዜ ብረት ታጥቀው በትጥቅ መንግሥትን ይታገሉ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሀገር ገብተው እንዲንቀሳቀሱ ተፈቀደ። ይህም ያለጥርጥር የጎራ መደበላለቅ ፈጠረ። በመንግሥትና በተፎካካሪ ድርጅቶች መካከል የጠራ ርእዮት ጠንክሮ አለመውጣቱ ታጋዮች በነባሩና በአዲሱ ርእዮት መካከል እንዲዋልሉና ማረፊያ ቦታ እንዲያጡ አደረጋቸው። ይህ ሁሉ ሀገራዊ ሕመም የፖለቲካውን ምኅዳር ወደዚህ ምስቅልቅል ከተተው።

ከዚህም በተጨማሪ ቀድሞ ያልነበሩና ነገሩን ከሆነው በላይ ሊያጦዙ የሚችሉ፣ ግለሰቦችንና ትናንሽ ቡድኖችን ከሆኑት በላይ ኃይለኛ የሚያስመስሉ ዓለም አቀፋዊ እውነታዎችንም ማየት ያስፈልጋል። ኢንተርኔትና ማኅበራዊ ሚዲያ ተፈጥሮ ተስፋፍቷል። በእጅ በሚያዙ ስልኮች ሳይቀር ቅጽበታዊ መልእክት ብቻ ሳይሆን በምስል፣ በድምፅና በጽሑፍ ማንኛውንም መልእክት ማስተላለፍ ተችሏል። የተሳሳተ መረጃና ዜናን ያለተጠያቂነት ለማስተላለፍና ሕዝብን ለማወክ መቻሉም ሌላው የችግሩ አንጓ ነው።

በቅርቡ ለንባብ የበቁ ሥነ ልቦናዊ የጥናት ጽሑፎች አንድ ዕውቀት ጨምረውልናል። ግለሰባዊም ሆነ ማኅበረሰባዊ የሽብር ሥራዎች ልክ እንደ አየር ንብረት ትንበያ ሳይንስ በጥናት ለመተንበይ ይቻላል ይላሉ። በሀገር ደረጃ የሽብርና የሁከቱን መባባስ አንዳንዶች አብዝተው ይፈልጉታል።

የመንግሥት ትኩረት ከሌሎች ነገሮች ይልቅ ሽብርና ሁከትን በመከታተል ላይ እንጂ በእነርሱ ላይ እንዳይሆን ያግደዋል ብለው ያምናሉ። ትናንት ያመለጠንን ዕድል ዛሬ ልናስመልስ ይገባል የሚል ከንቱ ምኞትም አለ። በየዘመኑ ከሁከትና ከግርግር የሚያተርፉ፣ ለማትረፍም ተግተው የሚሠሩ በርካታ አካላት መኖራቸው፣ የግንባር ላይ ምልክት ነው። የለውጥ ቡድኑ የችግሮቹን መጠንና ስፋት በዚህ ደረጃ ተረድቶ መፍትሔ የማስቀመጥ ውሱንነቶች ነበሩበት።

ፈረንጆቹ ‹‹አስቀድሞ ለጤንነቱ ጊዜ ሊሰጥ የማይፈቅድ ለበሽታው ጊዜ ይሰጣል›› ይላሉ። የግጭትን ጊዜያዊነት፣ የሰላምን ዘለዓለማዊነት ያልተረዳ ሚዲያ በሕዝቦች መካከል ባለች የክብሪት እሳት ላይ ቤንዚን ያርከፈክፋል። ዘመን የማይነጋ መስሎት በጨለማ ይሻሻጣል። እንኳንና ሕዝቡን ሊያሻግር እሱ ራሱ በጨለማ እየዳከረ በዕውር ድንብር ዕቃ ይፈጃል። በመፍትሔዎች ፍለጋ ላይ ሳይሆን በችግር ሐሰሳ ላይ ብቻ ይበረታል። ቁስል እየቆጠረ የፈውስን ቀን ያዘገያል። በእኛነት ጭንብል ተሸሽጎ ሌሎችን እያጠቆረ ለፍጅትና ለበቀል፣ ለቂምና ለጥላቻ ዐቅሙን፣ ጊዜውንና ጉልበቱን ይፈጃል። በዘመነ ማኅበራዊ ሚዲያና በዘመነ ቴክኖሎጂ መኖራችን ሁሉም ሰው የዜናና የመረጃ ተቀባይ ብቻ ሳይሆን ሰጪም አድርጎታል። ከሀገር ርቀው በብዙ ሺሕ ማይል የሚኖሩትም ግጭቱ ውስጥ ያሉትም እኩል ተንታኞች ናቸው።

ሰዉም እጁ ላይ የደረሰውን የሐሰት ዜናና የተሳሳተ ፎቶግራፍ ሁሉ ሳያጣራና ሳይመርጥ ይውጣል። ይህም ያለንበትን ለውጥና ሁኔታ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽዖ ሳያደርግ አልቀረም።

የማያልቅ የሚመስል የመከራ ዘመን ያዩ ሁሉ በቁስል ነጋዴዎቻቸው አልተፈወሱም፤ በአሻጋሪዎቻቸውና በሩቅ ተመልካቾቻቸው እንጂ። የተናጉት የሚጠገኑት በብርቱ ወጌሻ እንጂ፣ ስብራቶቻቸውን እያወዳደረ የማን አጥንት ይበልጥ ደቀቀ በሚል ሕመም አወዳዳሪ አይደለም። ሰላም ረዥሙ የታሪክ ጊዜ ነው። ግጭት አይፈጠር አይባልም። “ወፍ በላዬ ላይ አይብረር አይባልም፣ ጭንቅላት ላይ ጎጆውን አይቀልስ እንጂ" እንዲሉ፣ ጸብና ግጭት አይከሠት አይባልም። የጠብን ዘመን ማርዘም ግን የግጭት አፈታትና የሰላም አከባበር ዕውቀት ጉድለት ነው። ሰላም ከሁሉም በፊት የነበረንና ከሁሉም በኋላ የሚኖረን ሀብታችን ነውና።

*እባብ ስለ ሆዱ፣*
*ይሄዳል በሆዱ!*

*በአፍኝ ያለ ጥሬ፣*
*በጉንጭ ያለ ወሬ፣*
*መበተን ወዳፈር፣ እንዳገኙ አፍሶ*
*እንደ ትርፍ ኪሳራ፣ ባያጣም ጨርሶ፣*
*ማሳ አገኘሁ ብሎ፣*
*አይበትንም ዘሩን፣ ያገሬ ገበሬ፣*
*ጦር ከፈታው ይልቅ፣*
*ያውቃልና ሀገር፣ መፍረሷን በወሬ።*

በእንግዳ መቆያ ክፍል ውስጥ ሆኜ አሻግሬ ማዶውን በመስኮት እመለከታለሁ። በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤትና በፓርላማው አጥሮች መካከል ያለው ሰፊ የአስፓልት መንገድ ጭርታ ተጭኖታል። ከአቧሬ ድልድይ የተነሣው ጎዳና በቀኝ የበዓለ ወልድን፣ በግራ የጥይት ቤትን አጥር እየታከከ መጥቶ የመስቀለኛ መንገዱን መብራት ያልፍና ወደ እሪ በከንቱ ይሻገራል። ወደ ቀኝ ከታጠፉ አራት ኪሎ ወደ ግራ ከዞሩ ወደ መስቀል አደባባይና ካዛንቺስ ያመራል። በእነዚህ ጎዳናዎች ላይ የመኪናም ሆነ የሰው እንቅስቃሴ ጸጥ እረጭ ብሎበታል።

የልዩ ጥበቃ አባላት መኖሪያ ከሆነው አካባቢ ተነሥቶ የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት አጥርን ታኮ የሚያልፈው

የአስፋልት መንገድ በቀይ እምቡጥ ጽጌረዳ የተሸፈነ ዐጸድ ይመስላል። ሁሉም ወታደሮች ቡራቡሬ ፋቲጋቸውን ለብሰዋል፤ አናታቸውም ላይ ቀዩን ክብ የሱፍ ቆብ ደፍተዋል። በሰባት ወይም በስምንት የሰልፍ ረድፍ ቆመው ነበር። በግምት ወደ ስምንት መቶ አካባቢ የሚጠጉ የደቡብ እዝ ልዩ ጥበቃ ኮማንዶ ሠራዊት አባላት ናቸው።

እነዚያ ኮማንዶዎች መሣሪያ እንደታጠቁ የቤተ መንግሥቱን ዙሪያ ግንብ በጎን እያዩ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሲመጡ የአዲስ አበባ ሕዝብ በአግራሞት ያያቸው ነበር። ይህንን እጅግ አደገኛ የሆነ ድርጊት ቢቻል ምንም ዋጋ ሳያስከፍል ባይቻል በአነስተኛ ዋጋ ማክሸፍ አለብኝ። ድንገት ወደ አእምሮዬ የጥቁሮች መብት ታጋይ የማልኮም ኤክስ ተጠቃሽ ንግግር መጣ።

*"You're not to be so blind* with *patriotism that you can't face reality. Wrong is wrong, no matter who does it or says it."*
*Malcolm X, By Any Means Necessary*

*"ያፈጠጠውን እውነታ ለመረዳትና ለመጋፈጥ እስከማትችል ድረስ በሀገር ፍቅር ልትታወር አይገባም። ማንም ይናገረው ማንም ያድርገው፣ ስሕተት ሁልጊዜም ስሕተት ነው።"*
*ማልኮም ኤክስ፣ ባይ ኤኒ ሚንስ ነሰሳርይ*

በግልጽ ዐይናችንን አናይም በማለት ካልጨፈንን፣ ጆሯችንንም አንሰማም ብለን ካልደፈነው በቀር፣ አድማው ምን ተፈልጎ እንደተከናወነ ግልጽ ነበር። በአዲስ የለውጥ ርምጃ መገሥገሥ በጀመረችው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ፖለቲካዊ እምነትን በግሉ አልያም ተደራጅቶ በሰላማዊ መንገድ ለማራመድ እንደ ቀደሙት ዘመናት መግደል ወይም መሞት አያስፈልግም። ያን መሰሉን የኃይል፣ የጉልበት፣ የጭካኔ ፖለቲካዊ መንገድ ከበቂ በላይ ሞክረነዋል። ወደፊት አላራምድ ከማለት አልፎ እዚያው የነበርንበት ቦታ ለመቆም እንኳን ከልክሎናል። እንዲያውም ወደ ኋላ አንደርድሮ ቁልቁል ሊደፋን ሲል ሕዝብ በአንድ ድምፅ ተነሥቶ በቃ አለ።

በአሮጌው ማፍያ ቡድን ከሚመራው አጥፊ አካሄድ በሕግ ተፋተን አዲስ አቅጣጫ ከጀመርን ገና መንፈቅ እንኳን አልሞላንም። ጊዜው አጭር ቢሆንም ለውጡ የሕዝብ ቅቡልነት ማግኘቱ በተደጋጋሚ በአደባባይ ተረጋግጧል። አድመኞቹና ከኋላ የሚያስተባበሩት የጥፋት ኃይሎች ግን ይሄን የአደባባይ እውነታ ከፊታቸው እያዩ መቀበል አልሆነላቸውም። ከዚያም አልፈው ከታሪክ ጉዞና ከሕዝብ ፍላጎት በተፃራሪ በመቆም ጥፋታቸውን ቀጠሉበት።

መደበኛውን ዕለታዊ ተግባር ለመከወን በማለዳ ቢሮዬ ገብቼ በዝግጅት ላይ ሳለሁ አስደንጋጩ የአድማ ዜና ቢሮዬ ደረሰ።

እንደ አጋጣሚ ዕለቱ አዲሱ የመንግሥት አደረጃጀት በካቢኔ ውይይት ሊደረግበት ቀጠሮ የተያዘበት ነበር። እኔና ምክትል ጠቅላይ ሚነስትሩ በትንሿ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ነበርን። የቤተ መንግሥት የውስጥ ጥበቃ መኮንኑ ባልተለመደ ሁኔታ ወደ አለሁበት ጠረጴዛ ቀርቦ በተጣደፈ ወታደራዊ አነጋገር፣ በቁጥር 800 የሚሆኑ የልዩ ጥበቃ አባላት ወደ ምድብ ሲያቸው ከመመለሳቸው በፊት "ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይን ማነጋገር እንፈልጋለን በማለት ከነሙሉ ትጥቃቸው በጽ ቤቱ ዙሪያ ጥይት ቤት አካባቢ መሰባሰባቸውን ገለጸልኝ።

በቀጣይ ዘመን አሻራ የማያኖር ኣንድም ታሪካዊ ክሥተት የለም። በሀገር ደረጃ እንደ መንግሥት የምናከናውናቸው የአሠራርና የአደረጃጀት መፍትሔዎች ዘረው ተዟዙረው በኣሻራቸው ይገለጣሉ። ይህን የኮማንዶዎች ሁኔታ፣ የአራዳ ዘበኞችን ጉዳይ፣ ኋላም ወታደራዊ ደርግን ማሰብ ተገቢ ነው። ልጅ ኢያሱ ከመንበረ ሥልጣናቸው በኃይል የተገፉት በሸዋ መኳንንት ሤራ ብቻ ሳይሆን በተፈራ አስተባባሪነት የተደራጁትን የአራዳ ዘበኞች በመጠቀም ነበር።

ተፈሪ መኮንን በቀጥታ ወደፊት መተው ለጊዜው ፖለቲከኞች ሐሳባቸውን ከመሸጥ ከመለወጥ ይልቅ በረቂቅ ሤራ ከኋላ መሸጉ። መሐል ሠፋሪ ጦር እንዲህ ካልተደረገኝ እንዲህ ዓይነት ርምጃ እወስዳለሁ ብሎ እንዲዝትና እንዲያስፈራራ አደረጉት። በዚያ መንገድም ሥልጣናቸውን ተቆናጠጡ። እቴጌ ጣይቱ በዚያ ወቅት ለዚህ ጦር ክፉ ትምህርት አስተማራችሁት ብለው ነበር።

ታሪክ ራሱን ሲደግም፣ ለሠራዊቱ ያስተማሩት የተንኮልና ሤራ ለራሳቸው መከራ አመጣባቸው በ1953 ዓ.ም. የንጉሠ ነገሥቱ አካሄድ ያልተስማማቸው መኮንኖች የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ አደረጉባቸው። ይሄው ጦር በኋላ የሕዝቡን አብዮት ቀምቶ ዐፂውን ገድሎ መቃብራቸውን አጠፋው። እቴጌ ጣይቱንና ሚኒስትሮችን ከሥልጣን በማውረድ የተጀመረው የወታደሩ ዐመዕ፣ ራሱን ዘውዱን ገርስሶ በት መንግሥቱን በመያዝ ተጠናቀቀ። ይህ መንገድም ሀገሪቱን ለማያባራ የእርስ በርስ ጦርነትና እልቂት ዳረጋት። ዳፋውም እስከ ዛሬ አልለቀቀም።

በመሆኑም ይሄንን የሠራዊት አድማ በተሳካ መልኩ ማክሸፍ ብቻ በቂ አልነበረም። ሠራዊቱ ዓላማው ከፖለቲካው ገለልተኛ ሆኖ የሀገሩን ሉዓላዊነት ከጠላት መጠበቅ እንደሆነ ማረጋገጥ በሚችል አካሄድ ችግሩ መፈታት አለበት። ይህ ጽኑ አቋሜ ነበር።

ወታደሮቹ ቤተ መንግሥት በተገኙበት ሰዓት አቶ ደመቀ መኮንን ወደ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በማምራት ላይ ነበር። የደመቀ መኪና ጽቤት እንደደረሰ የእሱ መኪና መሆኑን ገምተው ወታደሮቹ አስቆሙት። ከዚያም ከመኪናው ወርዶ እንዲያናግራቸው ባቅራቢያ ወደሚገኝ ግቢ ወሰዱት።

ነገሩ ምን ያህል ግራ አጋቢ እንደሚሆን ለመገመት ቀላል ነው። በዚያ ደረጃ ቁጥር ያላቸው ወታደሮች ባልታሰበ ሰዓት እዚያ ተገኝተው ‹‹ጥያቄዎች ይዘን መጥተናል፣ እናግረን›› ሲባል እንኳን በሀገር መሪ ደረጃ ማንም ሰው ግራ ቢጋባ እምብዛም _አይደንቅም። ምንም ችግር ባላስከተለ መንገድ ወታደሮቹን አነጋግሮና ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ ዐውቆ፣ የመጣውን ወታደር አረጋግቶ፣ ጉዳዩን በሰላም ለመፍታት ስምምነት ላይ መድረስ ፈታኝ ቢሆንም ደመቀ በብቃት ተወጣው።

አራት ኪሎ በዘመን ሂደት ወጥነትን የተላበሰ አካባቢ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት የፖለቲካ ነርቭ የማዘዣ ጣቢያ ነው። የገዥዎችና የመሪዎች መቀመጫ ነው። የሕዝብ ተወካይና እንደራሴዎች መሰብሰቢያ ነው። የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ መቀመጫ ነው። የአንድ መቶ ሠላሳ አምስት ዓመታት የዘመናዊ ኢትዮጵያ የአመራርና የፖለቲካ ሐሳብ ማፍለቂያ ነው። አንድ ኃይል ሀገሪቱን መግዛት ወይም ማስተዳደር ጀመረ የሚባለው አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ገብቶ መኖር ሲጀምር ነው። በምኒልክ፣ በኢያሱ፣ በዘውዲቱ፣ በኃይለ ሥላሴ፣ በጣልያንም ሆነ በደርግ ወግ ልማዱ ያው እንደቀድሞው ነው። መሪ የሆነ ሁሉ ቤተ መንግሥቱን መያዝና መቆጣጠር ይኖርበታል።

በምሥራቅ በመኖሪያ መንደር፣ በግቢ ገብርኤልና በታዕካ ነገሥት በኣታ፣ በሰሜን ምሥራቅ በጥይት ቤት፣ በሰሜን በፓርላማ ሕንፃ፣ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራልና በበዓለ ወልድ የተከበበ ሥፍራ ነው። ወሌ መስጊድ፣ የኢሕአዴግ ጽ/ቤት፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የዐርበኞች ሕንፃና የፈረሰው የአራት ኪሎ መንደር በአካባቢው አሉ።

በአራት ኪሎው ቤተ መንግሥት ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እቴጌ ጣይቱ፣ ልጅ ኢያሱ፣ ንግሥት ዘውዲቱ፣ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ፣ ኮሎኔል መንግሥቱ፣ አቶ መለስ፣ አቶ ኃይለ ማርያም ኖረውበታል። አንዳንዶቹ መሪዎቻችን በኖሩበትና በመሩበት ግቢ ውስጥ ታመው፣ አልጋ ይዘው በክብር ዐርፈውበታል። አንዳንዶች ደግሞ በከበሩበት ተዋርደው፣ በሰጡበት ለምነው የመከራ ሞት ሞተውበታል። ሌሎች በኃይል ተወግደው፣ በቁም ታስረው፣ በድብቅ ሞተው፣ በድብቅ ተቀብረውበታል። ሌሎችም በስደት ተሸኝተውበታል።

መቼም ለዚህ የኮማንዶዎች አድማ አንድ አስተባባሪ ከበላይ ይኖራል። በዚህ ረገድ ጦሩ ተመስጋኝ ነው። ፖለቲካው መሐል ልግባ አላለም። አሁን ታዲያ ይሄን መሰል ሁኔታ ለምን ተፈጠረ? እንደ በታች ሹማምንቱ ሁሉ የበላዮች የሉበትምን? በሰኔ 16ቱ ሙከራ የተረዳነው ታላቅ ነገር ነበር። በዚያ ሤራ ውስጥ ማን ምን ሐላፊነት እንደሚወስድ ዝርዝር ሥርዓት ተመቻችቶ ነበር። አሁንም ያው ትዕይንት መልሶ ተደግሞ መጥቷል። ዛሬስ አዛዡ ማነው? አቀናባሪው ማነው? ዝርዝር ሐላፊነት የወሰዱት እነማን ናቸው? እነዚህ ጥያቄዎች መመለስ ይኖርባቸዋል። አሁን ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው አንዳች መርገምት ሀገሪቱ ላይ ወርዶ ይሆን እንዴ ብዬ አስባለሁ።

በአንድ ፊት መከላከያ እዚያ ለመሥዋዕትነት ተሰልፎ ይሠዋል። ሀገሩን ሊያድንና ሊጠብቅ። በሞቱ ሰላም ሊያስገኝ። እዚህ ደግሞ መፈንቀለ መንግሥት ያካሂዳሉ።

*አንዱ ሲገነባ ሌላው ካፈረሰ፣*
*የተዘራ ማሳን ገልብጦ ካረሰ፣*
*አንዱ የተከለውን ሌላኛው ሲነቅል፣*
*ሸቅብ መውጣት ቀርቶ ቁልቁል መንከባለል።*

በዚህ መልኩ እስከመቼ እንቀጥላለን? መልስ አልነበረኝም። በእርግጥ እንዲኖረኝም አልጠበቅኩም። በምንገኝበት የዘመን ምዕራፍ የሀገር ምሥረታም ሆነ የሀገር ግንባታ ሂደት ወደ ሰላም፣ ዕድገትና ልማት እንዲያመራ መሣሪያው ኃይል ሳይሆን ዴሞክራሲ ነው። እኔን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ማካተትን፣ ማሳተፍን፣ ልዩነትን ማክበርን፣ ብዝኃነትን መቀበልን ይጠይቃል። በሕግ የበላይነት ማመንና በሕግ ብቻ መሥራትን ተግባራዊ ማድረግ ይሻል። ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባት የፖለቲካ ሜዳውን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ማስፋትን ይፈልጋል። ሁሉም በእኩልነት የሚሳተፉበትን ዕድል ማመቻቸትን የግድ ይላል።

ኢትዮጵያውያን በግልም ይሁን በቡድን ተሰባስበው፣ እንደ ፓርቲ፣ ንቅናቄ፣ ሲቪል ማኅበረሰብ፣ ወዘተ. ያለ ፍራቻ በነጻነት መንቀሳቀስ የሚችሉበት ሥርዓት ተፈጥሯል። በቃል ብቻም ሳይሆን የሕግ ማሻሻያ በማድረግ የተግባር ርምጃ ተወስዷል። ምሁራን፣ ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ተንታኞች፣ ማኅበራዊ አቀንቃኞች (አክቲቪስቶች)፣ ደራስያን፣ ብሎገሮችና ሌሎችም ሐሳብ አመንጪዎች ሕጋዊ የመጫዎቻ ሜዳ ተፈጥሮላቸዋል። መሣሪያ አንግተው መንግሥትን ይፋለሙ ለነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶችና አባሎቻቸው ምሕረት ተደርጓል። ውጤቱ ግን ከታሰበው ውጭ ብቻ ሳይሆን ከሚጠበቀውም የተለየ አቅጣጫ ይዞ ብቅ አለ።

ድርጊቱን አደገኛ የሚያደርገው የጥያቄው ተገቢ መሆን አለመሆን አይደለም። የመከላከያ ሠራዊት አባላት እንደማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል ጥያቄ ሊኖራቸው ይችላል። ይሄን ጥያቄም የማቅረብ መብት አላቸው።

ጥያቄውን ለማቅረብ ግን ሕጋዊና ተገቢ የሆነ አካሄድ አለው። ወታደራዊ ዲስፕሊንንና ደንብን ያከበረ መሆን አለበት። በተቋማዊ ተዋረድ መሠረት ደረጃውን ጠብቆ የሚሄድ መሆን አለበት።

የተከሠተው ድርጊት እንኳን ጥብቅ ዲሲፕሊንና የእዝ ቁጥጥር ከሚጠበቅበት ወታደር፣ ከሲቪል እንኳ የሚጠበቅ አይደለም። ሲቪልም ቢሆን ጥያቄውን በተደራጀ መልኩ መግለጽ ሲፈልግ የሕግንና የመመሪያን ጠገግ አክብሮ ነው። መጀመሪያ በቅርቡ ላለው አመራር አስታውቆ፣ ካልተመለሰለት እንደገና ጠይቆ፣ ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት ካለበት እንኳ በደብዳቤ አሳውቆ ነው።

በሕገ መንግሥቱ በግልጽ እንደተቀመጠው ማንኛውም ሰላማዊ ትዕይንት አድራጊ ኃይል፣ ምንም ዓይነት መሣሪያ መያዝ አይችልም። ትጥቅ ተይዞ “ሰላማዊ” ሰልፍ ወይም ጥያቄ የሚባል ነገር የለም። በመከላከያ ሠራዊት አባል ደግሞ ጉዳዩ ከዚህም ያልፋል። ከወታደራዊ ዲስፕሊን ዋነኛ መገለጫዎች አንዱ ጥብቅ የእዝና የቁጥጥር ሥርዓትን መከተል ነው። አንድን የወታደሮች ስብስብ ሠራዊት' የሚያሰኘው በእዝና በቁጥጥር፣ በሥርዓትና በደንብ የተቀናጀና የተሰደረ ሲሆን ነው። ይህ ካልሆነ ግን ውጊያን የሚያስቀርና ሲከሠትም በአጭር የሚፈጽም ሊሆን አይችልም። በመሠረቱ ጠንካራ የእዝና የቁጥጥር ሥርዓት የሌለውና የማይተገብር ሠራዊት እንዲሁ ከመንገድ ተጠራርተው ከተሰባሰቡ የሽፍቶች ስብስብ በምንም የተሻለ አይደለም።

በአንድ ሠራዊት የእዝና ቁጥጥር መሠረት ማንኛውም አሐድ ከበላዩ ያለው አመራር ዕውቅና ሳይሰጠው ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ አይችልም፤ አይገባምም። አንድ ሻምበል ያለ ሻለቃው ዕውቅና ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ አይችልም።

ባየነው ክሥተት ግን ከሻለቃም፣ ከብርጌድም፣ ከክፍለ ጦርም፣ ከኤታማዦር ሹምም፣ አልፎ የሀገሪቱ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዡን ካላገኘሁ የሚል የሠራዊት አሐድ እንዳለ ሕዝቡ ተገንዝቧል። ወታደር የቅርብ አለቃውን አምኖ ዝመት ከተባለበት የሚዘምት እንጂ ለሠራው ሥራ ዕውቅና ስጡኝ አይልም። እንዴት ስኬታማ ሥራ እንዳከናወንኩ ተመልከትልኝ ብሎ አጀብና ዐዋጅ የሚፈልግም አይደለም።

ዛሬ እኛ በነጻነት እንድንኖር ብዙ አባት አያቶቻችን ዋጋ ከፍለዋል። በባዶ እግራቸው፣ በተራብ ሆዳቸው ከሀገር ሀገር ተንከራተዋል። እኛም የእነርሱ ታሪክ አስቀጣዮች በመሆናችን ኩራት ሊሰማን ይገባል እንጂ “ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ይጨመርልን” የሚል ቅሬታ አቀረቡ መባል ለሠራዊቱ ክብር አይመጥንም።

ይህ ማለት ግን ሠራዊቱ ችግር የለበትም ማለት አይደለም። እንኳን እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት ገና ለማደግ ዳዴ እያለች ያለች ሀገር ቀርቶ፣ በየትኛም የዓለማችን ክፍል የሚኖር ወታደር ችግርን እየተጋፈጠ የሚኖር ነው። ምቹ የሀገራቸውን አየርና ከባቢ ትተው በረሐ ለበረሐ የሚኳትኑት ወታደር የትም ሀገር ቢሆን ግዳጅ ለመወጣት ቆርጦ የሚነሣ ስለሆነ ነው። ወቅቱ ሁሉም በሀገሪቱ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ ያገባኛል የሚል በሙሉ ጦሩን አውርዶ አማራጭ ሐሳብ እንዲያመጣ ጥሪ የተላለፈበት ነው። በርካቶችም ፖለቲካዊ አጀንዳን በትጥቅ የማስፈጸም ውጥናቸውን ርግፍ አድርገው ትተው መሣሪያቸውን ፈትተዋል። በዚህ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመገርሰስ መሣሪያ ያነሡ እንኳ መሣሪያቸውን በጣሉበት ወቅት፣ ለሕገ መንግሥቱ የመጨረሻ ዘብ እንዲቆም የሚጠበቅበት፣ ሕዝብና መንግሥት እምነት የጣለበት አካል የመንግሥትን ትጥቅ አንግቶ መንግሥትን ካልሰማኸኝ ለማለት መምጣቱ ከባድ ጥፋት ነው።

ወቅቱ በብዙ መልኩ ተስፋ ሰጪ ቢሆንም በተቃራኒው ደግሞ ብዙ የጥፋት ክሥተቶች በየቦታው የሚከሠቱበት ነበር። በዚህም ምክንያት ሕዝቡ ጭንቀት ላይ ነበር። ይሄን ደግሞ ከመከላከያ ኃይላቸው በላይ ሊገነዘብላቸውና ሊያረጋጋላቸው የሚችል የለም። ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ምን ያህል ሀገራችንን እንደጎዳት የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። ድርጊቱ ያለፉትን ጥፋቶች የሚያስቀጥል፣ ሕዝቡን እንዲሸበርና እንዲርድ ያደረገ፣ እጅግ አሳፋሪ ድርጊት ነበር።

ከተቋማዊ አሠራር አንጻር ክሥተቱ ሁለት ነገሮች አሳይቶን አልፏል። የመጀመሪያው “ለምን ጥያቄያቸውን በተገቢው መንገድ አላቀረቡም?” የሚለው ነው። በዚህ ረገድ ወይ ጥያቄያቸውን አቅርበው ሰሚ አላገኙም፤ አልያም ጥያቄያችንን አመራሮቻችን ሊመልሱት አይችሉም የሚል እምነት አድሮባቸዋል ማለት ነው። በሁለቱም ረገድ የመከላከያን ተቋማዊ አሠራርና አመራር ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነበር። በዚያም አለ  በዚህ በመደበኛው የመከላከያ ሠራዊት መዋቅር ላይ ወታደሮች አለፍ ሲልም ሕዝቡ ያለውን አመኔታ የሚሸረሽር ተግባር ነው።

ሁለተኛው ደግሞ “ቤተ መንግሥት እስኪደርሱ ድረስ እንዴት አልታወቀም" የሚለው ነው። በዚህም የመከላከያን የእዝና የቁጥጥር ሥርዓትን ብቻ ሳይሆን የብሔራዊ ደኅንነት እና የፌደራል ፖሊስ እንዲሁም በሌሎች የመረጃ ተቋማት ላይም ሕዝቡ ያለውን እምነት የሚሸረሽር ተግባር ነው። ወቅቱ ያልተረጋጋና ለውጡም ገና ሥር ያልሰደደ በመሆኑ ሕዝቡ በቀላሉ ይረበሻል። ይሄን ሊያሰክን የሚችለው ደግሞ በተቋማት በተለይም በደኅንነት፣ በፖሊስና በመከላከያ ላይ እምነት ሲያድርበት ነው። አሁን በታየው ሁኔታ ግን የታጠቁ ወታደሮች ቤተ መንግሥት ደረሱ እየተባለ፤ ሊረጋጋ አይቻለውም። በአጠቃላይ ድርጊቱ ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም አንጻሮች ቢታይ የሀገሩን ዳር ድንበር ለመጠበቅ ሌት ተቀን ደፋ ቀና የሚለውን፣ በረሐ ለበረሐ የሚንከራተተውን፣ ብዙ ችግሮች ቢኖሩበትም ተቋቁሞ ለሕዝቡ ዘብ የሆነውን የመከላከያ ሠራዊት ትክክለኛ መልክ የማያሳይ ሕገ ወጥ ድርጊት ነው። መሠረታዊው ጉዳይ ችግሩ “እንዴት ይታለፍ?” የሚለው ነው። በአዲሱ የለውጥ ርምጃ ጥቅማቸው የሚጎዳ ክፍሎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እናውቃለን። ግን ደግሞ ብዙኃንን በማሰብ ዘላቂ የሀገርና የራስንም ጥቅም ማመዛዘን ያስፈልጋል። በአሮጌው ተደስተንና ረክተን በምቾት መኖራችንን በማቆም በእያንዳንዱ ዕለት የላቀውንና ከፍ ያለውን ዓለም በመመኘት፣ ለእርሱም እውን መሆን መታገል ያስፈልጋል።

ወደላቀው የከፍታ ሥፍራ መውጫው መንገድ የእኛ ፈቃድና ከትናንት የመላቀቅ ፍላጎት እንጂ ሁሌም አብዮት ሊሆን አይገባም። መግደል መሸነፍ ነው።

አዲሱ የለውጥ ጎዳና ያልተጓዝንበትና ያልሞከርነው አዲስ መንገድ ነው። በዕለት ተዕለት ርምጃችን የምሥራች አብሣሪ እንጂ መርዶ ነጋሪ ሟርተኞች እንዳንሆን በጽናት መሥራት ይኖርብናል። በቅርብ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መፈንቅለ መንግሥት እንግዳና የማይታወቅ ክሥተት አይደለም። በልጅ ኢያሱ፡ በቀዳማዊ ኃይለ

ሥላሴም ሆነ በኮሎኔል መንግሥቱ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ተሞክሯል። ብዙዎቹ ፍንቀላዎች የተሞከሩት መሪዎቹ ከቤተ መንግሥት ውጭ እያሉ ነበር።

በልጅ ኢያሱ መንግሥት ላይ ተፈሪ መኮንን ከሸዋ መኳንንት ጋር አሢረው መፈንቅለ መንግሥት ሲያደርጉና ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት፣ ተፈሪም አልጋ ወራሽ ሲሆኑ፣ ልጅ ኢያሱ ከምኒልክ ቤተ መንግሥት ውጭ በሀገራችን ምሥራቃዊ ክፍል በጉብኝት ላይ ነበሩ። በ1953 ዓ.ም. የታኅሣሡ ግርግር በመባል የሚታወቀው የእነ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ መፈንቅለ መንግሥት ሲሞከር፣ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ብራዚል በጉብኝት ላይ ነበሩ። በ1981 ዓ.ም የደርግ ጀኔራሎች መፈንቅለ መንግሥት ሲያካሂዱ፣ ኮሎኔል መንግሥቱ በምሥራቅ ጀርመን በጉብኝት ላይ ነበሩ። በእርግጥ በ1966 ዓም የተካሄደውን **የመፈንቅለ** መንግሥት ሙከራ የንጉሡ የበታች መኮንኖች በአራተኛ ክፍለ ጦር ግቢ ውስጥ በመሆን ሲዶልቱ፤ ከዚያም የተጋጋለውን ሕዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ መስከረም ላይ 1967 ዓ.ም የደርግ የበታች መኮንኖች የዐፄውን ሥርዓት ከዙፋን ሲያወርዱ፣ አዛውንቱ ንጉሥ በኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥታቸው ውስጥ ነበሩ።

የልዩ ጥየቃ ጦር አባላቱ የመጡት ከሐዋሳ ነበር። ግዳጃቸውም በአዲስ አበባ ዙሪ በቡራዩ ከተማ አካባቢ ተከሥቶ የነበረውን ረብሻ ለማረጋጋት ነው። ለዚህ ተልእኮ በቡራዩና በኮልፌ አካባቢ ሠፍረው ነበር። እነዚህ የልዩ ጥበቃ ጦር አባላት እንዴትና በፓኑ መሪነት ለዚህ ዓመፅ ሊነሳሱ ቻሉ፣ ጦሩ ዩኒፎርሙን ለብሶና ሙሉ መሣሪያውን ታጥቆ ወደ አራት ኪሎ የምኒልከ ቤተ መንግሥት፤ ወደ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ሲያመራ አንፎ ላይ፡ ዊንጌት ላይ፣ ኮልፌ ላይ፣ ፓስተር ላይ፡ ፒያሳ ላይ ማስቋም እንዴት አልተቻለም እንዴትስ ስለ እንቅስቃሴው መረጃ ለወታደራዊ ደኅንነት፤ ለበላይ አመራር አካላት፣ ሳይደርሳቸው ቀረ?

በማንኛውም ወቅትና ጊዜ ሁሉ መፈንቅለ መንግሥት ሊካሄድ እንደሚችል መገመት ከመንግሥታት ሁሉ የሚጠበቅ ተግባር ነው። በተለይም በለውጥ ጊዜ። እንዳሁ የፖለቲካና የደኅንነት ተመራማሪና ጠበብት የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግሥታዊ ሥልጣን ባሻገር በኢኮኖሚ ባለቤትነት ውስጥ እጁን ሲያስገባ ለመፈንቀለ መንግሥት በር እንደሚከፍት ይገልጣሉ። ፖለቲካዊ ሥልጣኑን ለኢኮኖሚ ጥቅሙ ማስጠበቂያ ያደረገው ኃይል፣ ጥቅሙን ሊያስከብርለት የማይችል መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ መፈንቅለ መንግሥት ሊያደርግ የሚችልበት ሰፊ ዕድል አለ። በቅርቡ በግብፅ ወታደራዊ ጄኔራል አልሲሲ የተካሄደው መፈንቅለ መንግሥትና የተቀለበሰውን ሕዝባዊ ኣብዮት ሰማንነት ያስረዳሉ።

ከዚያም በላይ በቱርክ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ወደ ሥልጣን በመጣው በአርዱጋን መንግሥት ላይ የተሞከረውን መፈንቅለ መንግሥት አስረጂ አድርገው ያቀርባሉ። ከዚህና ከነባር ምክንያቶች በመነሣት ነበር የለውጥ ቡድኑ ከማንኛውም ተቋም በፊት የሪፎርም እንቅስቃሴውን በመከላከያና በደኅንነት ተቋማት ላይ ያካሄደው። የመከላከያ ኃይሉ፣ የጸጥታ አካላቱና ደኅንነቱ ታማኝነታቸውን ለሀገር እንጂ ለፖለቲካ ድርጅቶች እንዳይሆን የማስተካከያ ሥራዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሠርተዋል።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ከባድ መከፋፈል አለ። ሞልቶ ተረፈ ሊባል በሚችል መጠን ስሜታዊ ነን። ከምክንያታዊነት ጋር ተጣልተናል፤ ታመናል። ጤና መሆን የምንሻው ግን ሳንታከም ነው።

ወጌሻ ሳያየን ስብራታችን እንዲጠገን እንጠብቃለን። ሕመማችንን በግላጭና በድፍረት ማየትና ማሳየት አልተላመድንም። ድብብቆሽንና መሸፋፈንን ነው የምንመርጠው። ነፍስ ኄር፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ጥላቻችን ጨቋኙን እንጂ ጭቆናን አይደለም, _የሚሉት እውነትነቱ ሊካድ አይችልም። የጥላቻ ዘር ከሚገባውና ከሚያስፈልገው በላይ ተረጭቷል። መንግሥታዊ ሥርዓት መፍረስ አይደለም ለሰዓታት ቢስተጓጎል ከዚህ በፊት እንደነበረው ሕዝብ ራሱን በራሱ እያስተዳደረ፣ አካባቢውን እየጠበቀ፣ አጥፊን እየገሰጸና እየቀጣ መንግሥት እስኪ መሠረት በትዕግሥት ይጠባበቃል ብሎ ለማሰብ አስቸጋሪ ነው። እልቂት፣ ዝርፊያና ውድመት ይመጣል።

መፈንቅለ መንግሥቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ርቆ ሊጓዝ የሚችል አፍራሽ ተጽዕኖ እንደነበረው መገመት ቀላል አይደለም። አዲሱ የለውጥ ርምጃ በሰላማዊ ትግል በአፍሪካ ምድር መንግሥት ሊለወጥ መቻሉን በገሐድ የፈነጠቀ ጮራ ነበር። አዲሱ ለውጥና አዲሱ ትውልድ ከቀደሙት አባቶቹና ታላላቆቹ የተለየ መንገድ ተከትሏል። ፖለቲካዊ ልዩነትን በኃይል ሳይሆን በሐሳብ ሊሞግትበት የሚችልበትን ዕውቀትና የሞራል ዕሴት አዳብሯል።

ሐሳብንና አሳቢውን በመግደል አብዮት የማካሄድን ታሪክ ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናብቶ ተሻግሯል ማለት ተጀምሮ ነበር። የሆነ ሆኖ ወታደሮች መሣሪያ ታጥቀው በድንገት ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ማምራታቸው አስደንጋጭ ነበር። የምዕራባውያን ዴሞክራሲ በድኻ አፍሪካ ሀገራት ሊያፈራና ሊጸድቅ አይችልም ለሚሉ ወገኖች ሰርግና ምላሽ ሆነላቸው።

ብረት አንግበው እስከ መገንጠል ጽንፍ ለረገጡ ጥራኝ ዱሩ ባዮች ጥሩ ሰበብ ሰጣቸው። የዚህ መፈንቅለ መንግሥት ጠንሳሾችና አቀነባባሪዎች ይሄን ጠንቅቀው ያውቃሉ። ግን ግለኞችና ራስ ወዳድ ናቸው። መንግሥት ራሱን ለመጠበቅ የማይችል አድርጎ የማቅረብ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው። ቢቻል ወደ መንበሩ ለመውጣት፣ ባይቻል እጅን ለመጠምዘዝና ፍርሃትን ለመፍጠር የታለመ ነበር። በኋላ ተጠናቆ የቀረበው የምርመራ ሪፖርትም ይሄንኑ ሐሳብ የሚደግፍ ነው።

### *ዓምድ ጥገና*

### ዋልታና ተራዳው ዓምዱ እየፈረሰ

# ሀገሬ ምን ቀራት ግንቡ ከተማሰ።

ለጥንታውያኑ ቻይናውያን ከፍተኛው ራስ ምታት ከአጎራባች ሕዝቦች የሚሰነዘርባቸው ወረራ ስለነበር ችግራቸውን እስከ ወዲያኛው ለማሰናበት ይወስናሉ። በሰላም ለመኖር ካላቸው ፍላጎት የተነሣም ብዙ ሺሕ ኪሎ ሜትሮችን የሚያካልለውን ታላቁን ግንብ ለመገንባት በቁ።

ዳሩ ግን ለሰላማችን ዘብ ይቆማል፣ ያለስጋት እንድንኖር ያስችለናል› ብለው የገነቡት ያ ግንብ ከወረራ አላዳናቸውም። በመቶ ዓመት ውስጥ ሦስት ጊዜ ያህል ተወረሩ። ይህ ሁኔታ ጥያቄ ማጫሩ አይቀርም። አንድም ሰው አይዘለውም የተባለውን ግንብ የጠላት እግረኛ ጦር እንዴት ሊያልፈው ቻለ? ያስብላል።

ቀላል ነው! የጠላት ጦር የግንቡን የተለያዩ በሮች ለሚጠብቁት የቻይና ወታደሮች ማባበያ በመስጠት ያልፋሉ። ቻይናውያኑ ምንም ያህል አጥራቸውን አጠንክረው ቢገነቡም አጥሩን የሚጠብቁ ሰዎችን ጠባይ በጥሩ መገንባት እንዳለባቸው ረስተዋል። እናም የራሳቸው ሰዎች ሰላማቸውን በቀላል ማባበያ ሸጡባቸው።

ጠንካራ ተቋም የሌላት ሀገር በዚያ ላይ የሕዝቧ ሥነ ምግባር ጠንካራ ካልሆነ እንደ ቡትርፍ ወንፊት የተባለውን ትቶ ያልተባለውን እያሾለከ ረፍት ይነሳል። ጠንካራ ሥነ _ምግባር ያለው ትውልድ እንዲመናመን በትልቁ አስተዋጽዖ የሚያበረክተው የሃይማኖት ተቋማት ጥንካሬያቸውን እያጡና እየተፍረከረኩ ሲመጡ ነው።

በተለይም ለማኅበራዊ ጉዳዮች ትልቅ ቦታ በሚሰጥ ሀገር ውስጥ እነዚህ ሰብሮ መጽናት ይከብዳል። በቀላል ግፊት መንሸራተት ይከተላል። በዚህ፣ ከመንግሥት የሚጠበቀው ሀገርን የሚመጥናት ተጨማሪ ዓምዶች እየገነባች፣ እርስ በርስ እንዲተሳሰሩና እንዲተባበሩ እያደረጉት፣ የበለጠ ዐቅም መፍጠር ነበር። ያም ቢቀር ያለውን ጠብቃ ማቆየት እንጂ መስበር ቀና አካሄድ ሊሆን አይችልም። ዓምዶቿን መስበር የጀመረች ሀገር ፍጻሜዋ ያስከፋል። በእኛም ሀገር በመንግሥት እየተደረገ የነበረው አካሄድ የሀገርን ዓምዶች መስበር እንጂ ማጽናት እንልነበረ በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ የአደባባይ እውነት ነበር። ግን ለምን? መጠየቅ ይኖርበታል።

በተለያየ ጊዜ ስለ ለውጥ በጋራ ከማዋያቸው ጓዶች ጋር ይሄንን ጉዳይ አብዝተን አናነሳው ነበር። ለምን የስብራት ምክንያት እንሆናለን ሀገር ጠንካራ ተቋማት ያስፈልጓታል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስና የኢትዮጵያ እስልምና ደግሞ ከእኛው ጋር የኖሩ፤ የተሳሰሩ፤ ከፉውን ደጉንም ከዚህች ሀገር ጋር የተካፈሉ ተቋሞቻችን ናቸው። የፖለቲካ አካሄዱ የስብራቱ አንዱ ምክንያት ነው። ስለዚህም የመፍትሔውም ምክንያ መሆን አለበት እንል ነበር።

ለሦስተኛ ዲግሪ ሟሟያ እንዲሆን ባካሄድኩት ጥናት የደረስኩበት አንድ እውነታ ቢኖር፣ የአንዲት ሀገር

ማኅበራዊ ካፒታል ድርና ማግ ሆኖ ማስተሳሰሩን ዓምድና ምሰሶ ሆኖ በአንድነት ማቆሙን ያረጋገጠ ነበር። በእምነትና ባህል ዙሪያ ያቆምናቸው ማኅበራዊ ሀብቶች አዕማድ በመሆን ከሺሕ ዘመናት በላይ ሀገራችንን የተሸከሙ ቅርሶች ናቸው። ታሪካችንን፣ ዕሴታችንን፣ ባህላችንን፣ ጀግንነታችን ነጻነታችንንና በአጠቃላይ እኛነታችንን ገንብተዋል። አንዳቸው ከሌላው ጋር ተሳስረዋል፤ አንዱ ሌላውን እኑሯል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዚህች ሀገር ታሪክ ውስጥ ቁልፍ ሚና ነበራት። በሀገሪቱ ታሪክ ለረዥም ዘመናት የቆየች ተቋም ናት። ከሀገረ መንግሥት ግንባታ፣ ከሥነ ትምህርት፣ ከሕግ፣ ከባህል፣ ከሥነ ጽሑፍ፣ ከኪነ ሕንጻ፣ ከዘመን አቆጣጠር፣ ከውጭ ግንኙነት ጋር የተያያዘ የሺሕ ዘመናት ታሪክ አላት።

እስልምናም በተመሳሳይ የሀገሪቱ መገለጫ ነው፤ ከኢትዮጵያ ስም ጋር ሁሌም ከፍ ብሎ የሚታይ። ሀገራችን እስልምና በዓለም ከመስፋፋቱ በፊት በክብር የተቀበለች ሀገር ናት። ለሰሀቦች መጠጊያና መሸሸጊያ የሆነች ናት። ሃይማኖቱ የሀገራችን ዕሴቶችን የቀረጸ ነው። ከሀገረ መንግሥት ግንባታ፣ ከትምህርት፣ ከውጭ ግንኙነት፣ ከሥነ ጽሑፍ፣ ከሞራል ግንባታና ሕዝቦችን ከማስተሳሰር ጋር የተያያዘ የሺሕ ዘመናት ታሪክ አለው።

እስልምና ሀገሪቱ የቆመችበት አንደኛው ዓምድ ነው።

እነዚህ ሁለት ዓምዶች ሀገሪቱን ደግፈው መቆም ሲገባቸው ያ ዘመን እነርሱ ራሳቸውን እክል ውስጥ ከቷቸው ነበር። መፈንቅለ ሲኖዶስ ተደርጎ ሲኖዶሱ ለሁለት ተከፍሏል። ይህም 24 ዓመታት አልፎታል። ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በስደት አሜሪካ ተቀምጠዋል። እዚያም ሲኖዶስ አለ።

እዚህ ሀገር ውስጥ ደግሞ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዐርፈው ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ በመንበር ላይ ነበሩ። እዚህም እዚያም ሲኖዶስ አለ።

ውዝግቡ ሕዝቡንም፣ ቤተ ክርስቲያኒቱንም ሀገሪቱንም ጎድቷል። ሁለቱ ወገን ለተለያየ ፖለቲካ ምሽግ እየሆነ ሀገረ መንግሥቱን ይበልጥ አዳክሟል። ሕዝቡም የተዋለደ የተዛመደ በመሆኑ ደጋፊና ተቃዋሚ ሆኖ ቤተሰባዊነቱን ከወዲያ ወዲህ ያንገላታዋል። በመካከል ግራ የገባቸው ኢትዮጵያውያን ገለልተኛ የሚባል አካሄድን መርጠዋል መስሏል። አንድ ሆና ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ ያለባት ቤተ ክርስቲያን እርሷ ራሷ በሁለት መዋቅር ተሰንቅራ በአደጋ አፋፍ ላይ መገኘት ዕጣ ፈንታዋ ሆነ።

የሀገራችን ሌላኛው ዓምድ የሆነው እስልምና፣ ተቋማዊ ዐቅሙ ዳብሮ መገንባቱ ለሙስሊሙ መንፈሳዊነት ማበብ ብቻ ሳይሆን ለሀገረ መንግሥት ግንባታችን መጠናከር አይተኬ ሚና አለው ብዬ አምናለሁ። ሆኖም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝበ ሙስሊሙ ከፖለቲካዊና ትእምርታዊ ማዕከል ተገሎ እንዲቆይ ያደረገው ፖለቲካችን ለሙስሊሙ መጨቆን ብቻ ሳይሆን ለሀገረ መንግሥታችን መማሰን ምክንያት ሆኗል።

የመገለሉ ሁኔታን በማስተካከል በውሱን ደረጃም ቢሆን እስልምናና ሙስሊሙ የውጭ ሳይሆን የውስጥ፣ መጤ ሳይሆን ነባር ኢትዮጵያዊ መሆኑን እንዲታወቅና ሀገራዊ ተቋም እንዲኖረው በማድረግ የ66ቱ አብዩት ጉልህ አስተዋጽዖ አድርጓል። ሆኖም ሙስሊሙን ዕውቅና አግኝቶ የእምነት ነጻነቱን ከማጎናጸፍ በዘለለ፣ ሙስሊሙን አንድ አድርጎ ለሀገረ መንግሥቱ ጥንካሬ አስተዋጽዖ እንዲያደርግ አስቻይ ሁኔታዎች አልተመቻቹም ነበር።

ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላም የሙስሊሙ ተቋማዊ ሁኔታ መሻሻል የታየበት አልነበረም። ይልቁንም ሲንከባለል የመጣው ተቋማዊ ድክመት እንዲባባስ በማድረግ የእስልምና ምክር ቤት የገዥው ፖለቲካ ማስፈጸሚያ እንዲሆን ተደረገ። ይሄም "በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖ መጅሊሱ እወክለዋለሁ ከሚለው ሙዕሚን እንዲነጠል አደረገው። ይባስ ብሎ ሳር ቅጠሉ አብዮታዊ ዴሞክራሲን ይዘምር የሚለው የተለጠጠ ፖለቲካዊ መታበይ፣ መጅሊሱንም እንዲጫነው ተፈለገ፡ ለሙዕሚኑ የምትከተለውን አስተምሮ ልምረጥልህ ተባለ። እንኳንም ዘንቦብሽ፣ እንዲያውም ጤዛ ነሽ እንዲሉ የሕዝበ ሙስሊሙ ብቸኛ የጋራ ማኅበራዊ ተቋም፣ በሕዝበ ሙስሊሙ ውስጥ ያለውን እንጥፍጣፊ ቅቡልነት እንዲያጣ አደረገው።

ድምጻችን ይሰማ የሚለው የሕዝበ ሙስሊሙ ጩኸት በየጁምዓው የሀገራችን መስጂዶችን ሞላ።

የሕዝበ ሙስሊሙን የፍትሕ ጥያቄ በአፈናና በመከፋፈል ለመመለስ ተፈለገ። በዚህም የተነሣ የእስልምና ምክር ቤት ለስድስት ዓመታት ለሁለት ተከፍሎ ቆየ። ጥያቄ ከሚያነሡ የእምነቱ ተከታዮች መካከል አንዳንዶቹ ለእሥር ተዳረጉ። አንዳንዶችም ወደ ባሕር ማዶ ተሰደዱ። ሥልጣን በያዙትና ጥያቄ በሚጠይቁት መካከል ሁለት ጎራ ተፈጠረ። አንዱ ሌላውን ያወግዛል፤ ይተቻል። አንድ ሆነው የሀገሪቱን ችግሮች መፍታት ያለባቸው የእስልምና አባቶችና ሊቃውንት፣ እነርሱ ራሳቸው ተከፋፍለው ለሀገሪቱ ፈተና ሆኑባት።

በሀገራችን የነጻነት ታሪክ ውስጥ ሃይማኖት የተጫወተው ሚና እጅግ ሲበዛ ከፍተኛ ነው። በዚህም የተነሣ መንግሥት እነዚህን ማኅበራዊ መሠረቶች መነካካት ቀርቶ እንዳይናዱ መከላከል ነበረበት።

እኔም ባገኘሁት አጋጣሚ ለወዳጆቼ ስለጉዳዩ ከማንሣት አልቦዘንኩም ነበር። እንደውም በአንድ አጋጣሚ ለጊዜው ስሙን የማልጠቅሰው የቀድሞ ባለሥልጣን ስለዚህ ጉዳይ ሳነሣበት የሰጠኝ መልስ እጅግ ነበር ያስደነገጠኝ። አስታውሳለሁ "አታስብ! ኢትዮጵያ እንኳንስ ያለ ፈጣሪ ያለ መንግሥትም የኖረች ሀገር ናት" ሲል ነበር የመለሰልኝ።

በዚያ ደረጃ ያለ ከፍተኛ ባለሥልጣን እንዲህ ዓይነት አቋም መያዙ በወቅቱ እጅግ አሳዝኖኛል። ማዘን ብቻውን በቂ ስላልሆነ ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ ነገሮችን ለመቀየር ጥረት ሳደርግ ቆይቼ የተሻለ ተጽዕኖ ማሳረፍ

የምችልበት ቦታ ላይ ተገኘሁ።

ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት በመጣሁ አጭር ጊዜ ውስጥ ነበር የሀገር ሽማግሌዎች ሁለቱን ሲኖዶሶች ለማስታረቅ እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን የሰማሁት። ይህ እንቅስቃሴ በተለያየ ጊዜ ተጀምሮ እየተሰናከለ ቢቆምም፣ የተስፋ ብርሃን ፈጠረልኝ:: በጉዳዩ ላይ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስን አናገርኳቸው። ቢሳካ ደስተኛ መሆናቸውን ገለጹልኝ። ይሄን በመያዝ የአስታራቂ ኮሚቴውን አባላት በጽ/ቤቴ አገኘኋቸው::

የኮሚቴ አባላት ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ የተደረጉት ሙከራዎች ለምን እንደከሸፉ፣ አሁን ደግሞ የተሳካ እንዲሆን ከመንግሥት ምን እንደሚፈልጉ በስፋት ውይይት አደረግን። በመንግሥትም ይሁን በግሌ ሥራቸው እንዲሳካ የሚቻለኝን ሁሉ እንደማደርግ ቃል ገባሁላቸው።

በአሜሪካ ያሉት አባቶች የኮሚቴው አባላት ከእኔ ጋር መነጋገራቸውን ሲሰሙ በደስታ ተቀበሉት። ለዕርቀ ሰላሙ ዝግጁ መሆናቸውንም ገለጡ። ሕዝቡም ተስፋው ለመለመ። የኮሚቴው አባላትም ወደ አሜሪካ አቀኑ።

የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤትን ችግር ለመፍታት ከሁለቱም ወገን ጋር መነጋገር ነበረብኝ። መጀመሪያ ሁለቱን ወገኖች በየተራ አነጋገርኩ። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች አንድ ጠንካራ ሀገራዊ ተቋም እንደሚያስፈልጋቸው እምነቴን ነገርኳቸው። የዝሆኖቹ መጣላት የሚጎዳው ሣሩን መሆኑን አሳሰብኳቸው ያለፈውን ትቶ በቀጣይ አካሄድ ላይ ተነጋግሮ ጠንካራ ተቋም መገንባቱ እንደሚሻል ሐሳቤን ገለጥኩ፡፡ እነርሱም ተቀበሉት።

ከሁለቱም ወገን ያሉበት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መዋቅራዊ የሽግግር ኮሚቴ ተቋቋመ። ኮሚቴውንም ተቀዳሚ ሙፍቲ ሐጂ እድሪስ እንዲመሩት ስምምነት ላይ ተደረሰ።

ኮሚቴው የልዩነት ሐሳቦቹን ዘርዝሮ፣ የመስማሚያ ሐሳብ አዘጋጅቶ፤ አንድ ጠንካራ መጅሊስ የሚቋቋምበትን ሁነኛ መንገድ እንዲያመጣ ሐላፊነት ተሰጠው። በሐምሌ ወር ወደ አሜሪካ ስሄድ የሲኖዶሱ የዕርቅ ሂደት በመልካም ሁኔታ ላይ መሆኑን ሰምቼ ነበር። የማያሳፍረን የኢትዮጵያ አምላክ ዕርቁን እንደሚያሳካውና ስብራታችንን እንደሚጠግነው ርግጠኛ ነበርኩ።

አሜሪካ እንደ ደረስኩ የዕርቀ ሰላሙ ኮሚቴ የደረሰበትን ሪፖርት አቀረበ። አባቶች ችግሩን በዕርቅ ለመፍታት ወሰኑ። የዕርቀ ሰላሙን ሐሳብ ሁለቱም ሲኖዶሶች ተቀበሉት። እኛም በአሜሪካ ያሉት አባቶች በተገኙበት ዕርቀ ሰላሙን በዋሽንግተን ዲሲ አከበርን።

ወደ አዲስ አበባ ሐምሌ 24 ቀን ስንመለስ ጉዳዩ የጉዞ ጉዳይ ብቻ አልነበረም። ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስና ከ6 በላይ ጳጳሳት ወደ ኢትዮጵያ አብረውን መጡ። ፓትርያርኩ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ከ24

ዓመታት በኋላ ነው። አንዳንድ አባቶች ይሄንን ሳያዩ ሞት ቀድሟቸዋል። ሌሎቹ በእርጅና ምክንያት ሊከተሉን አልቻሉም። ዕድል የገጠማቸው አባቶች ግን ይሄው ታሪክ ሲቀየር ሊያዩ ነው። ጉዟችን የተሰበረውን የኢትዮጵያ ዓምድ የሚጠግን ነበር።

አዲስ አበባ ስንደርስ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ በፈገግታ በተሞሉ ፊቶች ተጥለቅልቋል። ነጋሪት ይጎሰማል፤ መለከት ይነፋል፤ ዕጣን ይታጠናል፤ መስቀል ተደርድሯል፤ ድባብ ተዘርግቷል። ለፈጣሪ ምስጋናና ዕልልታ ይቀርባል። ከአውሮፕላን ማረፊያው እስከ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አቀባበሉ ልዩ ነበር። ሕዝባችን ዕርቅና ሰላምን ምን ያህል _ እንደሚፈልግ አደባባይ ወጥቶ የተናገረበት ቀን ነው። የተመኘሁትን በተግባር አሳይቶኛልና ፈጣሪዬን አመሰገንኩት። ሀገራችን በአዲስ መንፈስ በአዲስ ምዕራፍ ላይ መሆኗን ማንም አይቶ ይመሰክር ነበር።

ከእስልምና የመዋቅራዊ ሽግግር ኮሚቴ ጋር በተደጋጋሚ ውይይት አድርገናል። የኮሚቴ አባላት ያልተፈቱ ችግሮችን እየለዩ በጥንቃቄ ይሠሩ ነበር። የሁሉም ፍላጎት ዕርቀ ሰላሙ ነው። ከመከፋፈሉ የተገኘ ጥቅም የለም፤ ከመዳከም በቀር። ነባሩ መጅሊስ ሐላፊነቱን ለማስረከብ፣ ሁለቱም ወገኖች በአንድነት ለመሥራት፤ ከሁለቱም ወገኖች የሚሳተፉበት ጊዜያዊ ምርጫ ለማድረግ፤ የዑለማዎችን ጉባኤ ለማካሄድ፤ በተለያዩ ቦታዎች ተከፋፍለው ያሉ ወገኖችን ወደ አንድ ለማምጣት ስምምነት ላይ ተደረሰ።

በመንግሥት በኩል መወሰድ የነበረባቸውን ርምጃዎችም በሕግና በሥርዓት ለመመለስ ቃል ገባን። የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤትን በዐዋጅ ለማቋቋም፤ የእስላማዊ ባንክን ለማቋቋም፣ መንግሥት የሚቻለውን ሁሉ እንደሚያደርግ ቃል ከገባንባቸው መካከል ይገኙበታል።

ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም. ልዩ ቀን ነበረች። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የዕርቀ ሰላም ቀን። ሚሊኒየም አዳራሽ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች ተሞልቷል። አያሌ ታዋቂ ክርስቲያኖች በሙስሊም ወገኖቻችን ደስታ ለመካፈል በሚሊኒየም አዳራሽ ከትመዋል። ኢትዮጵያ የቆመችበትን አንደኛውን ዓምድ አምና ጠግነናል። ዛሬ ደግሞ ሌላኛውን ዓምድ እንጠግናለን። ኢትዮጵያችን ሁለቱን ዓምዶች ስታገኝ ብርቱ ትሆናለች።

በርትተን ሌሎችን ዓምዶችም እንጨምራለን፡ ሕዝበ ሙስሊሙ ያለፈውን ሁሉ ለታሪክ ትቶ በኅብረት ወደፊት ይራመዳል። በእምነቱ ላይ ቆሞ ያለፈውን ቁስል ይሽራል። ፍቅር ምን ያህል ፈዋሽና ጠጋኝ ዐቅም እንደሆነ በዚያን ዕለት የሚሊኒየም የሕዝበ ሙስሊሙ ጉባኤ ማሳያ ሆኖኛል። በእውነት በእውነት እዚህ ቦታ መገኘት ተአምር ማየት ነው። ሀገር በልጆቿ እንደገና ስትጠገን አየሁ። ኢትዮጵያን ለመታደግ መለያየት እንደማይበጅ ልጆቿ ከራሳቸው ተሞክሮ ተምረው ወደ ቀልባቸው ሲመለሱ መመልከት ጥልቅ ደስታ ይፈጥራል።

ደግሞስ ዑለማዎች፣ ዒማሞች፣ ዑስታዞች፣ ታላላቅ የሙስሊም ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች እንደ አበባ

ፈክተው፣ እንደ ኮከብ አብርተው ኢትዮጵያን ሊታደጉ ሲነሡ ከማየት በላይ ምን አስደሳች ነገር አለ?

ሐምሌ 25 ቀን 2010 እና ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የዓምድ መጠገኛ ቀናት ተብለው እንደሚታወሱ አምናለሁ። የነገው ትውልድ ኢትዮጵያ እንዴት ወደ ብልጽግና እንደተጓዘች ሲያስብ እነዚህን ቀናት በመነሻነት ያስታውሳቸዋል። እኛም የታሪኩ አካል ሆነን በጆሯችን የሰማነውን የተስፋ ቃል አካል ለብሶ ሲመላለስ በዐይናችን አይተናል። ለዚህ ሁሉ የኢትዮጵያ አምላክ የተመሰገነ ይሁን።

# ምዕራፍ ስምንት

## ወንዝ ተሻጋሪ ዕርቅ

ሓፍቲ ሀገር ኤርትራ!

## “ተኳርፈን እንዳንቀር”

“ሰላም ናፈቀኝ። ጦርነት በሕይወትና በቁስ ላይ ከሚያስከትለው ጥፋት የበለጠ የሚያስጠላኝ ነገር በዚህ ዓለም ያለ አይመስለኝም። የሰው ልጅ በመካከሉ የሚፈጠሩትን ልዩነቶች በውይይትና በሰላም የሚፈታበት ቀን መቼ ይመጣ ይሆን? ያ ቀን ናፈቀኝ።”

ይሄን የሚለው ደራሲ በዓሉ ግርማ “ኦሮማይ” በተሰኘው መጽሐፉ ነው። በዓሉ ስለጦርነት የተንገፈገፈው የዛሬ ሠላሳ ዓመት ገደማ በኤርትራ በነበረው ጦርነት ወቅት ነበር። እርሱን ካንገፈገፈው ጦርነት በኋላ በድጋሚ ሌላ ጦርነት ማድረጋችንን ቢያውቅ ምን ይሰማው ይሆን? በዓሉ ከሚናፍቀው በላይ እኔም ለዓመታት ሰላም ይናፍቀኝ ነበር።

ቃል መሬት ይዞ ሲበቅል መመልከት የጀመረው ሕዝብ ድጋፉን በየአቅጣጫው እየገለጸ እንዲቆይና እኔም እንደመሪ ብርታት እንድሰንቅ አድርጎኛል። የለውጥ ጉዟችን ከሀገር አልፎ ቀጣናውን ይዞ መጓዝ እንዳለበት ቀድሞም እምነት ነበረኝ። እርግጥ ነው ገና ከመጀመሪያው የለውጥ ወጋገኑ አድማስን ተሻግሮ መታየት ጀምሮ ነበር።

የኢትዮጵያ ሰላምና ብልጽግና ከድንበር መልስ ያለ ውስጣዊ ጉዳይ ብቻ አይደለም። በጎረቤቶቿና ቀጣናውን ካለው ሰላምና ብልጽግና ጋር የተሳሰረ እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ከዚህ አኳያ ሀገረ ኤርትራ ከሁሉ በፊት ትኩረት ማግኘት ነበረባት።

በበዓለ ሢመት ንግግር ወቅት ከተላለፈው የሰላም ጥሪ በተጨማሪ፤ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ መግለጫ የሰላም ጥሪ ቢቀርብም፤ በኤርትራ መንግሥት በኩል ኦፊሴላዊ ምላሽ ሳይገኝ ቀናት መቆጠራቸው መጀመሪያ ላይ ግርታን ፈጥሮብኝ ነበር። 'ነገሩ እንዴት ነው? ሰላምን ለማምጣት የሰላም ጥሪ ከማድረግ በዘለለ ኢትዮጵያ ምን ማድረግ ይገባታል?' ብዬ እንዳስብ አስገድዶኛል። ደግነቱ የኤርትራ ምላሽ ዘገየ እንጂ ጨርሶ አልቀረም።

ሃያ ዓመታትን ያስቆጠረ ኩርፊያ፣ በርካታ ክሶችና ጣት መጠቋቆሞች፣ ቁስልና ጠባሳ ነበረ። ይህ ሁሉ ግን ልኡካኖቻቸውን በመላክ እና እኛም እጃችንን ዘርግተን በመቀበል ተጠናቀቀ። የኤርትራ ከፍተኛ ባለሥልጣናት አዲስ አበባ ሲገቡ የሕዝቡ ስሜት ልዩ ነበር። አንዳች የተረሳ፣ አንዳች የተናፈቀ፣ አንዳች እንግዳ የሆነ ስሜት ፈጥሯል። ይህ ስሜት በእንጭጩ ሊቀዘቅዝ አይገባውም። ድፍረት የተሞላበት ሞኛሞኝ ውሳኔ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ለሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦች ግንኙነት መጠናከር አስፈላጊነቱ አጠያያቂ ስላልሆነ ፈጥኜ ወደ አሥመራ ለማቅናት ወሰንኩ።

አሥመራ ስንደርስ በኤርትራ ሕዝብና መንግሥት የተደረገልን ቤተሰባዊ አቀባበልና መስተንግዶ እጅግ ልዩ ነበር። ለካ ሕዝቡ እንደዚህ ተነፋፍቋል? በአጉል ግትርነት ስንቱን ነው ከወንድምና ከእኅቱ፣ ከአባትና ከእናቱ፣ ከዘመድ አዝማዱ ያቆራረጥነው? ከገመትኩት በላይ የናፍቆት ወላፈን በሕዝቡ ፊት ላይ አነበብኩኝ። ይሄንን ሕዝብ ነው ለዓመታት የፕሮፓጋንዳችን ሰለባ ያደረግነው!

ከዚያ ቀደም አሥመራን የማየት ጉጉት እንደነበረኝ ያወቅሁት እዚያ ስደርስ ነበር። በልብ ወለድ መጽሐፎች፣ በታሪካዊ ማስታወሻዎች፣ በሙዚቃ ግጥሞች እና በየሰው ጉጉት ሲፈጥሩብኝ ኖረዋል? ንግግር መሐል ስለአሥመራ የሰማኋቸው ታሪኮች ለካ በውስጤ የተደበቀ የመጎብኘት ጉጉት ሲፈጥሩብኝ ኖረዋል?

የአሥመራን መሬት ሲረግጥ፣ አየሩን መተንፈስ ስጀምር፣ ኪነ ሕንጻዎቹን ስመለከት... በውስጤ መሸጎ የቆየው ኤርትራን የመጎብኘት ጉጉት ነፍስ ዘርቶ አየሁት! በጣም ደነቀኝ!! በኤርትራ በነበረኝ ቆይታ ከፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር ለዓመታት እንጂ ደቂቃዎች ዕድሜ ትውውቅ ያለን አይመስልም ነበር። ፕሬዝዳንቱና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት እንደአንድ ቤተሰብ ተቀብለው አስተናገዱን። ሕዝቡም እግዜር ይስጠው መልካም ፊት አሳየን።

በአጭር ጊዜ ቀድሞ ከነበረው አካሄድ በተለየ መልኩ አዲሱ መንገድ ብርሃን መፈንጠቅ እንደቻለ ሁሉም ዜጋ በተጨባጭ አይቶ ማረጋገጥ ከሚችልበት ምዕራፍ ላይ ደረስን። በእርግጥ ሁልጊዜም ኢትዮጵያውያን ሰላምን የምንሻ ሕዝቦች ነን እንላለን። እንደ መንግሥትም ጦርነት የሚሸከም ትከሻ የለንም የሚል ዲስኩር በተደጋጋሚ ይሰማል። በተግባር ግን ጠብና ጦርነትን የሚያስቀር እርምጃ ስንወስድ እምብዛም አይስተዋልም። ከኤርትራ ጋር ያደረግነው ዕርቅ ለውጡ ሀገራዊ መሠረቱን ሳይለቅ በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ ባሉ ተጎራባች ሀገሮችና ሕዝቦች መካከል አንዳች የመቀራረብና የመፈላለግን ድባብ እንደፈጠረ ማሳያ ሆነ። በዚህም ሳቢያ በኬንያ፣ በሶማልያ፣ በጂቡቲ፣ በሁለቱ ሱዳኖች መንግሥታትና ሕዝቦች ውስጥ ሰላምን የማስፈንና ብልጽግናን የመጋራት ጉጉቶችና ጥረቶች ተንቦገቦጉ።

ከዚያም ተሻግሮ መንፈሱ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ዘልቋል። ኢትዮጵያ ከመካከለኛው ምሥራቅ ጋር ከመልክዐ ምድራዊ ቅርርብ በላይ የፖለቲካ፣ የታሪክ እና የእምነት ትስስርና ዝምድና አላት። ይህ ነባር ትስስር በቀላሉ የሚበጠስ ባይሆንም ያለ ጥበብና ልበ ሰፊነት ግን ለፍሬ የሚበቃ አይደለም። ቀጣናውን የእስልምና አክራሪነት መነሻ ነው በማለት ሀገራቱን ከማራቅና በጥርጣሬ ከማየት ይልቅ ተቀራርቦ በጋራ የማደግ ትልምን መቋጠር እንደሚያስፈልግ አስባለሁ።

ግንኙነቶቻችን ማተኮር ያለባቸው ለጋራ ጥቅም በሚውሉ በተመረጡ ሐሳቦት ላይ ብቻ ነው ብዬ በጥብቅ አምናለሁ። ስለዚህም ከተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች፣ ከሳዑዲ ዓረቢያና ከመሳሰሉት የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር ጠንካራ ቅርርብ በመፍጠር፣ በሂደት ተግባራዊ ለሚደረጉ የጋራ ፕሮጀክቶች መንገድ ተጠርጓል።

የኢትዮጵያና ኤርትራን ዕርቅ ተከትሎ የመጣውን የመጀመሪያውን አዲስ ዓመት በሀገራቱ ድንበር ላይ ከሚገኙ ሠራዊቶቻችን ጋር ለማክበር ቀጠሮ ይዘን ቀኑን መጠበቅ ጀመርን። መስከረም በባተበት ጀምበር፣ በዓሥር ሺዎች ወጣቶቻችን በተቀጠፉበት ስፍራ ስንገናኝ የነበረው ስሜት ድብልቅልቅ ያለ ነበር። ቁጭት፣ ሐዘን፣ ደስታ፣ ንዴት፣ ሳቅ፣ እንባ፣ ፀፀት... ጥልቅና ብውዝ ስሜት። ወታደሮቻችን እየተቃቀፉ ሲያለቅሱ፣ አብረውን የነበሩ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን በናፍቆትና በሰቀቀን ሲሳሳሙ ሁላችንም እንግዳ የስሜት ማዕበል ውስጥ ሰጥመን ጠፋን።

ጓድ ደመቀ መኮንን በሐሳብ ጭልጥ ብሎ የሚሆነውን ይታዘባል። ከኢሳይያስ ጋር የጀመርኩትን ወሬ

በመግታት ለአፍታ ካስተዋልኩት በኋላ ጠጋ ብዬ በእጆቼ ትከሻውን መታ መታ ሳደርገው፣ ላመል እንኳ ዐይኑን ከተከለበት አቅጣጫ ሳይመልስ፣ “ይሄ ሕዝብ እኮ አልተጣላም፤ ተመልከት ወታደሩን! እኛ እኮ ነን የተጣላነው፤ እኛ መሪዎቹ… ተናቆርን፣ ቂም ተያያዝን፣ ጸብ ቆሰቆስን ከዚያ ተቋሰልን። የተሳበው ቃታም፣ የተተኮሰው ጥይትም የመሪዎቹ ነበር፤ በጣም ያሳዝናል” ሲል ተናገረ።

ጭንቅላቴን በአዎንታ ከመወዝወዝ በቀር የምሰጠው መልስ አልነበረኝም…

## እማማ አፍሪካ

ወቅቱ ከፍ ብለን የምናስብበት ነው። በነጠላ ሳይሆን በጋራ፣ በግል ሳይሆን በቡድን እንደ አንድ ሆነን የምንንቀሳቀስበት ወቅት ላይ ነን። ችግሮቻችን የጋራ እስከሆኑ ድረስ ባለን ሳይሆን ተባብረን መፍታት ይኖርብናል።

‹ኑ! እንደ አፍሪካ እናስብ… ኑ! በሰፈር ሳይሆን እንደ አህጉር እናቅድ… ኑ! አብረን አንሥራ ችግሮቻችን የጋራ ናቸውና በጋራ እንለፋቸው› የማለት ልበ ሰፊነትና ተሰባሪነት በሁላችንም ውስጥ ሊያቆጠቁጥና በተግባርም ሊገለጥ ይገባል። ከፊታችን ያለው ዘመን ብሩህና ተስፋ ሰጭ ሆኖ የሚታየው ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን፣ ለመላው አህጉራችንም ጭምር ነው። በአስከፊ ድህነትና በእርስ በእርስ ጦርነት የምትታወቀው አህጉራችን ለብልጽግና ባላት ምቹ ሁኔታ ሁሉም በጉጉት የሚመኛት አህጉር እየሆነች ነው። ከቅርብ ዓመታት በፊት በእርስ በርስ ጦርነትና ግጭት የማይናጡ የአፍሪካ ሀገራት በጣት የሚቆጠሩ ነበሩ። ዛሬ ነገሩ ተገልብጦ ጦርነት ያለባቸው ሀገሮች ጥቂት ናቸው።

እውነተኛ ዴሞክራሲ ለአፍሪካ ብርቅና ድንቅ መሆኑ እየቀረ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት በእውነተኛና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የተመሠረተ መንግሥት በብዙ የአፍሪካ ሀገራት አልነበረም። ዛሬ ይህ የሥልጡን ሕዝቦች ባህል በብዙ የአፍሪካ ሀገሮች በገሐድ እየታየ ነው። በሥልጣን ላይ ያለ አፍሪካዊ መንግሥት ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ተወዳድሮና ተሸንፎ ሥልጣኑን በሰላም ሲያስረክብ ማየት በአፍሪካ ውስጥ ሰበር ዜና መሆኑ እየቀረ ነው።

የበርካታ ሀገሮች የኢኮኖሚ ግሥጋሤ ተስፋ የሚሰጥ እንጂ የሚያስቆዝም አይደለም። ባለፉት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ ብቻ አፍሪካ ያስመዘገበችው ኢኮኖሚያዊ እመርታ በዓለም ከተደነቁ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቶች በታላላቆቹ ተርታ ተመዝግቧል። የቻይናና የአንዳንድ የእስያ ሀገሮች ብቻ መለያ የነበረው የሁለት አሐዝ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሪኮርድ የተሰበረው በአፍሪካውያን ነው።

ይህ አስደናቂ ግሥጋሤም ለዓመታት የዘለቀና ለሌሎች ሀገሮችም በአርአያነት የሚጠቀስ ነው። ነገር ግን በቂና ዘላቂ ሊባል ወደሚችልበት ደረጃ ገና አልደረሰም። ልንመልሰው የሚገባው ቁልፍ ጥያቄ እኛ አፍሪካውያን በምን ምክንያት ከእስያና ከላቲን አሜሪካ ሀገራት አንሰን የሀገረ መንግሥት ግንባታችንና የብልጽግና ጉዟችን አመርቂና ዘላቂ መሆን ተሣነው? የመጻኢ ዘመን ጉዟችንስ ከቀደምት አካሄዳችን ተነጣጥሎና ተበታትኖ ይቀራል ወይስ በጋራና በኅብረት ተደምሮ ይበልጥ ለፍሬ ይበቃል?

በታሪክ አጋጣሚ ያገኘነውን ዕድል ተጠቅመን በአዲስ መንገድ ወደፊት ለመጓዝ፣ ከሁሉ አስቀድሞ የአዲስ አስተሳሰብ ባለቤት መሆን ያሻል። አፍሪካውያኑ በገዛ ሀገራቸው ብሎም በባርነት በተጋዙበት ሀገር ከአውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች ነጻ ለመውጣት የመረጡት የአስተሳሰብና የርእዮተ ዓለም _ መንገድ በዋነኛነት ፓን-አፍሪካኒዝም እንደነበር ይታወቃል። በዚህ መንገድ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት በ960ዎቹ ከቅኝ ግዛት ወጥተው የነጻነትና የብልጽግና ብርሃን በአህጉሪቱ መፈንጠቅ ጀምሯል።

የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ፋና ወጊና ፈር ቀዳጅ መሪዎች ከሆኑት መካከል የእኛው ዐፄ ኃይለ ሥላሴ፣ የጋናው ክዋሜ ኑክሩማህ፣ የኮንጎው ፓትሪስ ሉሙምባ፣ የታንዛኒያው ጁሊየስ ኔሬሬ፣ የዛምቢያው ኬኔት ካውንዳና የግብጹ ጋማል አብደል ናስር ተጠቃሽ ናቸው። ለዚያ ዘመን ችግር የዚያ ዘመን ጀግኖች መፍትሔ አምጥተዋል።

ለዚህ ምን ችግር ዘመኑን የሚዋጅ መፍትሔ መፈለግ ደግሞ የማንም ሳይሆን የእኛ የዛሬዎቹ ሐላፊነት ነው። ፓን አፍሪካኒዝም በአፍሪካ አህጉር የሚኖሩ አፍሪካውያንንና አትላንቲክ ማዶ የሚኖሩ ትውልደ አፍሪካውያንን ያስተባበረ ሉዓላዊ ሐሳብ ነበር። አማርኛ ለመውጣት እንደማትችል ታይቷቸው ነበር። ያኔ ይህ ሐሳብ መሬት ወርዶ እነዚያ ቀደምት አበው አፍሪካ ካልተባበረችና ካላበረች በፍጥነትና በጥራት ከዘመናት ሲተገበር ኖሮ ዛሬ የምሥራቅ እስያ ሀገሮች የያዙትን ቦታ የምትይዘው አፍሪካ ነበረች። ለየብቻ የሚቀመጡ ፊደላት ተደምረው ቃላት… ለየብቻ የሚኖሩ ቃላት ተደምረው ፀረፍተ ነገር ለየብቻው ያሉ ዐረፍተ ነገሮች ተደምረው ዐንቀጽ… ከዚያ ድርሰት እያለ ይፈስሳል። ያ ጉዞ ነው ዛሬ የምናደንቃቸውን ታላላቅ ድርሳናት ያበረከተልን። ፓን-አፍሪካኒዝምም እንደዚሁ ተባብሮና አብሮ በመደመር ማደግ ነው።

ዛሬ በአህጉራችን ድህነትና ችግር፣ አምባገነንነትና ኢዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ፈተናዎቻችን ናቸው። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የዛሬ ጀግኖች ያስፈልጉናል። ጀግኖች ስንል ጀብደኞች ለማለት አይደለም። ጀብደኞች ዛሬን ብቻ እየተመለከቱ የነገውን ዘመን የሚያጨልሙ ቅርብ አዳሪዎች ናቸው። በእነርሱ በኩል ጉዟችን ወደ ልዕልና ሳይሆን ወደ እንጦሮጦስ ነው። እውነተኛ ጀግኖች ሩቅ የሚያዩና የሚያሳዩ ናቸው። ለዛሬ መፍትሔ ሲሰጡ ለነገም መሠረት የሚሆን ነገር ይሠራሉ። በዕብሪት የተሞሉና ከክንዳቸው ርዝመት አርቀው መመልከት የማይችሉ ጀብደኛ መሪዎች፤ የመንደር ፖለቲካቸውንና ጀብደኝነታቸውን ተሻግረው ኅብረትና አንድነትን ሊፈጥሩ አይችሉም። ከራሳቸው ምስኪን ዜጋ ይልቅ ለራቀው ባለጠጋ ዓለም ዐይናቸው ይገለጣል። ድጋፍ እገዛቸው፣ ብልጽግና ክብራቸው ከራሳቸው ድኻ ሕዝብ ይልቅ ለራቀው ባለጠጋ ባዕድ የተመቸ ነው። አፍሪካውያን ከሌሎች አፍሪካውያን ጋር ከመነገድ ይልቅ በሩቅ ያለው የአውሮጳና የአሜሪካ ገበያ፣ አሁን አሁን ደግሞ የእስያውያን ገበያ ያማልላቸዋል።

በመከራ የተገኘች ጥሬ ሀብትን በኪሳራ ሸጠው ባገኟት ጥቂት ፍራንክ፣ ርካሽ የባሪያ ምርቶች ማራገፊያ ለመሆን መንገዶቻቸው ሁሉ ወደ ወደቦታቸው እንዲፈሰሱ የተቃኙ ናቸው። አውሮፓውያኑ በድፍን አፍሪካ ከካይሮ እስከ ኬፕታውን፣ ከጂቡቲ እስከ ዳካር ያለ ፓስፖርትና ቪዛ ሲምነሸነሹ ኖረዋል። አፍሪካውያን ግን ለራሳቸው ሀገር ባዕድ ሆነው በነነት የመንቀሳቀስ መብታቸውን ተነፍገው፣ የገዛ ሀገራቸው እስር ቤት ሆኖባቸው፣ ከትናንቱ ባልተናነሰ ዛሬም በእናት አህጉራቸው ባዕድና የበዪ ተመልካች ሆነው ይማቅቃሉ።

ሥልጣኔም ሆነ ዕድገት ያለ ኅብረት የማይሆንና የማይታሰብ ሕልም ነው። ለሥልጣኔና ለብልጽግና ግብዐትና ሙዓለ ንዋይ ወይም ሌላ አንጡራ ሀብት የመጀመሪያም ዋነኛም አይደለም። አፍሪካውያን ተለውጠው ወደ ዕድገትና ወደ ብልጽግና ለማምራት ያላቸው ከሁሉ የተሻለና ፈጣኑ መንገድ በፍቅር በመደመር በአንድነት እጅ ለእጅ ተያይዘው መሻገር ብቻ ነው። ሳይጀምር የሠለጠነና የበለጸገ ሀገር፣ ሳይያዝና ሳይተጋገዝ ያደገ ሕዝብ ትላንትም ሆነ ዛሬ አልታየም።

ልንሄድበት የተገባው መንገድ ማንም ሰው በቀላሉ ሊረዳው ይችላል። ነገር ግን አፍሪካውያን ያላቸው የጋራ ራእይም ሆነ ወቅቱን ያገናዘበ ርእዮተ ዓለም ከውስጣቸው ጠንክሮና ነጥሮ ወጥታ ለማለት ያዳግታል። ስግብግብነትና ንፍገት ሥር በመስደዱ ያለንን ተፈጥራዊ ሀብት እንኳን በአግባቡ እንዳንጠቀምበት አድርጎናል። ተሻምተን ልንቀራመተው ይገባል ብለን በአእምሯችን ደምድመናልና አብሮ ከማሸነፍና ከመበልፀግ ይልቅ መራኮት ውስጥ ገብተን እንተላለቃለን። እርስ በእርስ እንፋጃለን። እና አፍሪካውያን ስለብሶታችን እያነሳን ጊዜያችንንና ጉልበታችንን የምናባክንበት ወቅት አልፏል። የጥንት ቅኝ ገዢዎች አውሮፓውያን በአባቶቻችን ዘመን ስላደረሱት በደል እያነሳንና እያመነዠክን ዕድሜያችንን የምንፈጅ ከሆነ ውድ ሀብታችን ዛሬም የሌሎች ሲሳይ ሆኖ፤ እሮሮው ብቻ ይተርፈናል።

ቅኝ አገዛዙ ትቶብን የሄደውን ጠባሳና ክፉ አሻራ፣ ዛሬም እንደትኩስ ቁስል የምናስታምም ከሆነ፣ ነጻነትና ብልጽግና የሩቅ ሕልም እንጂ የዛሬ እውነታችን ሊሆን አይችልም። እንደ ሌሎቹ ነጻ ሕዝቦች ያለንን በማወቅ ከቀድሞ አሳዳሪዎቻችንና ከሌሎች እኅት የዓለም ሕዝቦች ጋር እኩያ ተወዳዳሪና በራሳችን ጉዳይ ወሳኝ ልንሆን ይገባል። ለዚህም ቆም ብለን ማሰብና የችግሩን ምንጭ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መፍትሔ ሰጥተን ማለፍ ይኖርብናል።

ወደ ፊት እያዩ ወደ ኋላ መሄድ መደናገር ነው። ወደ ፊት እየሄድን አልፎ አልፎ ወደኋላ መመልከቱ ግን ብልህነት ነው።የፊቱ ላይ አትኩሮ የኋላውን መቃኘቱ መንገዳችንን ፈጣን፣ ጤናማና ከግጭት የጸዳ ያደርግልናል። አፍሪካውያን በፍጥነትና በጥንቃቄ ልንሄደው የሚገባ ብዙ የፊት መንገድ ይጠብቀናል። መንገዱ በጋራና በትብብር የምንሄደው እንጂ በተናጥል ሆነን የምንወጣው አይደለም። ለየብቻ መሄዱ ለብዙ አደጋና በታሰበው ጊዜ ላለመድረስ ሊያጋልጠን ይችላል። ዓለም በጋራ በሚጓዝበት ዘመን ለብቻ መንገታገት ለመንኮታኮትና የመንገድ ሲሳይ ከመሆን ውጭ ምንም ፋይዳ የለውም።

በጊዜ ውስጥ ወደ ትናንት የሚጓዙ ሞኞች ብቻ ናቸው፣ ጊዜ የኋልዮሽ መንገድ የለውምና። ቆሞ መቆዘምም ወደ ኋላ ከመጓዝ የተሻለ አይደለም። በፈጣን ዓለም ውስጥ ቆሞ ማደግ የሚችለው ዛፍ እንጂ ሰው አይደለም። አፍሪካ ከመቆምና ስለትናንቱ ከመቆዘም፣ በሌሎች ላይ ጥገኛ ሆኖ ከመኖር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልትላቀቅ ይገባል። አንቆዝም የምለው ለዚህ ነው። ትኩረታችንን በወደፊቱ ላይ እናድርግ። ትናንትን ማየት የሚጠቅመን ለጥንቃቄ ብቻ ነው።

ያለነው በአዲስ ዘመን ላይ ነው። በራችንን ዘግተን ማንቀላፋታችንን ከቀጠልን ምን እንዳመለጠን እንኳን ማወቅ አንችልም። ስንባንን ከቀድሞ በከፋ ሌላ ባርነት ውስጥ ራሳችንን ማግኘታችን አይቀርም። ከተለወጠ

ዓለም ጋር አብሮ መለወጥ ይኖርብናል። ዳግም ንቃት አማራጭ ሳይሆን የመኖርና የህልውናም ጉዳይ ነው::

ለክፉ ዘሮች መብቀያ ምቹና ለም መሬት መሆን ይበቃናል። በተቃራኒው ለመልካም ዘሮች የተከፈተ ልብ ሊኖረን ግድ ይላል። ለሰላም፣ ለዕርቅ፣ አብሮ ለመሥራት፣ በጋራ ለማደግ፣ በአንድነትና በመደመር ችግሮችን ለመሻገር ከቻልን፣ አዲስ የለውጥና የነጻነት ብርሃን መፈንጠቅ ይጀምራል። ከተደመርን፣ ዛሬ ለእኛ፣ ነገ ለልጆቻችን የምትሆንና የምታኅኅ አፍሪካን መፍጠር እንችላለን። ይህንን የአፍሪካን አንድነትና የመደመር አርአያነት ለመምራት ሐላፊነቱን ለመረከብ ከአፍሪካ ቀንድ የተሻለ አማራጭ የለም:: ኢኮኖሚያዊ ተአምር በመሥራት ያሳየነውን መልካም ጅማሬ ወደ ሁለንተናዊ አንድነትና ዕድገት በመቀየር መጪውን የአፍሪካን አዲስ ጉዞ ፈር መቅደድ እንችላለን። በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2017 የምሥራቅ አፍሪካ አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት 5.9% ሲሆን፣ ይህ ዕድገት በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታትም ጸንቶ እንደሚቆይ ጥናቶች ተንብየዋል። የፖለቲካ ውጥረት ባለባቸው አንዳንድ የቀጣናው ሀገሮች ውስጥ ያለው አለመረጋጋት ባይታሰብ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ከዚህም የበለጠ ሊሆን እንደሚችል ጥናቱ በተጨማሪ ይጠቁማል። በግብርና ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ የቆየው የቀጣናው ሀገሮች ኢኮኖሚ፣ አሁን ቅርጹ ተቀይሮ፣ የአገልግሎት ዘርፉ የኢኮኖሚው ዋና አንቀሳቃሽ እየሆነ ነው።

በምሥራቅ አፍሪካ እየመጣ ያለው መረጋጋትና ሰላም፣ የገበያውን ያህል ተስፋ ሰጭና የሚያጓጓ ነው። በአንድ ወቅት የጦርነትና የግጭት ቀጣና የነበረው ክልል፣ በአሁኑ ጊዜ፣ የሰላምና የሥራ ቀጣና ሆኗል። አሁን ያለው ትልቁ ዜና፣ በአገሌና አገሌ መካከል ጦርነት ተከፈተ ሳይሆን፣ በአገሌና አገሌ መካከል ዕርቅ ወረደ የሚል ሆኗል።

በደቡብ ሱዳን ተፋላሚዎች መካከል ዕርቅ ወርዶ፣ የሰላም ስምምነት ተፈርሞ፣ አዲሲቷ አፍሪካዊት ሀገር፣ ፊቷን ወደ ሰላምና ዕድገት ጎዳና መልሳለች። ሚልዮኖችን አፈናቅሎ፣ ለረሃብና ለመከራ ዳርጎ፣ የሃያ አንደኛውን መቶ ክፍለ ዘመን ትልቁን ሰብአዊ ቀውስና ትራጀዲ ሊያስከትል ቋፍ ደርሶ የነበረው የእርስ በእርስ ጦርነት በሚያስገርም ፍጥነት ተወግዶ፣ ደቡብ ሱዳን ዛሬ የሰላም አየር የምትተነፍስ ሀገር ሆናለች።

ከሃያ ዓመት በላይ ባልተቋጨ ጦርነት ውስጥ የነበሩት ኢትዮጵያና ኤርትራ፣ ጦርነት የፉራ ነው, ብለው የሰላምና የፍቅርን መንገድ ከተያያዙት ሰንብተዋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከሃያ ዓመት በኋላ እንደገና ወደ አሥመራ በረራ ጀምሯል። ለሁለት አስርት ዓመታት ተለያይተው የቆዩ ቤተሰቦች አሥመራና አዲስ አበባ ላይ ሲገናኙ የነበረው ስሜት፣ ለሁለት ተከፍለው ቆይተው ከዘመናት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተገናኙ ኮሪያውያን ቤተሰቦች ላይ ከሚታየው ስሜት የተለየ አልነበረም። ኢትዮጵያና ኤርትራ ለሃያ ዓመታት ተፈራርተን ማዶና ማዶ እየተያየን ቆምን። በመጨረሻ ግን እግራችን ተፈታ።

**"አትንኩት ያን ቋጥኝ ካለበት ይቀመጥ፣**

**ብዙ ሰው ይጎዳል እስከሚገላበጥ"**

እንዲሉ፣ ከኮረብታ አናት ቁልቁል የሚንከባለል ቋጥኝ አንዴ መገልበጥ ይጀምር እንጂ፣ በመንገዱ ጉልበት እያገኘና መንከባለሉ ብርታት እያስታጠቀው በቅልጥፍና የቁልቁለት መንገድ ይሄዳል። ዕርቀ ሰላሙ ወርዶ

ጠላትነቱ ፀሐይ እንደ ወጣበት በረዶ ቀለጠ። ከዚያም የሁለቱ ሀገራት ሕዝቦችና መሪዎቹ የኢትዮጵያውያንን አዲስ ዓመት በሁለቱ ሀገሮች ድንበር ላይ በሚገኙ ከተሞች በአንድ ላይ አከበርን። የኢትዮ ኤርትራን ጦርነት የሚያስታውስ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዛላንበሳና ቡሬ የተባሉትን የድንበር ከተሞች አሣምሮ ያውቃቸዋል። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የሁለቱ ሀገር ዜጎች በጦርነት እሳት ተዋል። የብዙ ምስኪኖች ደም እንደዋዛ በከንቱ የፈሰሰው እዚህ ነበረ።

እልቂቱ ከደረሰ ሃያ ዓመት አልፎታል። ዛሬ ያ ሁሉ አልፎ አዲስ ዓመትን በጋራ ለማክበር በቃን። ምንም እንኳን ሐዘኑ ጥልቅ ቢሆንም፣ ጉዳቱ ካደረሰው ጠባሳ በላይ ሁለቱን ሕዝቦች አንድ የሚያደርገው ፍቅር ያይል ነበር። ይህች ቀን የሥቃዩ ገፈት ቀማሽ ለሆኑት የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች ልዩ ነበረች። በተንጣለለው በረሐ ለሀገሮቻቸው ፍቅርና ክብር ወድቀው የቀሩ ወገኖቻችን ዕድሉ ኖሯቸው ለዘላለም ከተንተራሱት ክንዳቸው ቀና ብለው ይሄንን ቀን ለአንድ አፍታ ቢያዩ ምን ይሉ ይሆን? ዓይናችንን ጨፍነን በተጓዝነው የዕብደት ጉዞ የማያዝን ማን ይኖራል?

እምነቱን በሌሎች ላይ በግድ በመጫን ማንነቱን ለዓለም ለማሳየት የተነሣው አዶልፍ ሂትለር፣ በሁለተኛው የዓለም _ ጦርነት ወደ 2 ሚልዮን የሚጠጉ ምስኪኖችን ጨፍጭፏል፣ አስጨፍጭፏል። በኮንጎ ውስጥ በተደረገው አሰቃቂ ወረራ፣ የቤልጅየሙ ሊዮፖልድ ዳግማዊ፣ ስምንት ሚልዮን አፍሪካውያንን በጭካኔ ፈጅቷል። አገዛዙ ሥጋት ላይ የወደቀበት መስሎ ሲሰማው፣ ሌላው ግልፍተኛ የዓለማችን ፖለቲከኛ ዮሴፍ ስታሊን ሰባት ሚልዮን ወገኖቹን ፈጅቷል። እስማኤል ኤንቨር በኦቶማን ቱርክ፣ ፖል ፖት በካምቦዲያ፣ ያኩቡ ጋዋን በናይጄሪያ እያንዳንዳቸው በየሀገራቸው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ምስኪን ሲቪሎችን በጭካኔ ገድለዋል፤ አስገድለዋል። በኢትዮጵያና በኤርትራም ከዚህ የተለየ ነገር አልሆነም። የጦርነት መጋዝ ሕዝብን ገዝግዟል፤ አቁስሏል፤ ገድሏል። ግፍን የሚያጥብ፣ ቁስሉን የሚያደርቅ ነገር ቢኖር ሌላ አይደለም ይቅርታ ነው፤ ሰላም ነው፤ ፍቅር ነው።

<ከዐይን በቀር በውኃ የማይጸዳ አንድም የሰውነት ክፍል የለም> ይላሉ። ዐይን ውኃ አይነካውም። ሊታጠብና በውኃ ሊጸዳ አይችልም።

“ታዲያ ዐይን በምን ይጸዳል?” ሲል ወጣቱ አንድ የተከበሩ ዐዋቂን ይጠይቃል።

“አንድም በእንባ፣ አንድም በማየት” አሉት።

“ምን በማየት?”

“የሚወደውን”

“የሚወደድ በምን ይታወቃል?”

“በልብ... በእንባ..... በፍቅር” አሉት። በዚህ መልክ ወጣቱን ወደ ልቡ መለሱት።

ታላቅነት ለአሮጌ ችግር አዲስ መፍትሔ ማስገኘት ነው። በቤተሰብና በጎረቤት፣ በኅብረተሰብና በማኅብረሰብ፣ በሀገርና በቀጣና ብሎም በአህጉር ደረጃ ችግር ሊፈጠር ይችላል። ችግር ሁሉ መፍትሔ አለው። ከአውራ

መፍትሔ ቁልፎቹ አንዱ መደመር ነው። በመደመር ስሌት ሁሉም ያሸንፋል፤ ሁሉም ይጠቀማል። አንዱ ሁሉን ይጠቅማል፣ ሁሉም አንዱን ይጠቅማል። አህጉራችን አፍሪካ በሰላምና በብልጽግና እንድትጥለቀለቅ ሁላችንም ከሌሎች ሳንጠብቅ የየራሳችንን ድርሻ እንወጣ።

በመደመር ውስጥ ከሌላ ከመጠበቅ ይልቅ የድርሻን ማበርከት የተከበረና ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። ሁሉም የበኩሉን መልካም ነገር ሲያደርግ ክፋት ቦታውን ይለቃል። ለዚህ ነው በፍቅር መደመር፣ በይቅርታ መሻገር፣ የአዲሱን ዘመን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍልስፍና ሊቃኝ ይገባል የምንለው።

ሰላም ሰላምን ያበዛል። ከኢትዮጵያና ኤርትራ ዕርቀ ሰላም በማስከተለ ኤርትራ ጂቡቲም ወደ ሰላም ገበታ መምጣታቸው ምንኛ ደስ የሚያሰኝ አጋጣሚ ነው። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ በአውዳሚ ጦርነት ከገጠመቻት ከኤርትራ ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከሁሉም ጎረቤቶቿ (ከሶማልያ፣ ከጂቡቲ፣ ከሱዳን፣ ከደቡብ ሱዳን እና ከቅርብ አጋሮቿ (ኡጋንዳና ሩዋንዳ) ጋር በመምከርና ከመሪዎቻቸው ጋር በመወያየት፣ ቀጣናው የሰላም ቀጣና ሆኖ በኢኮኖሚ እንዲበለጽግ የጋራ ስምምነት ላይ ተደርሷል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሶማልያ፣ አሰቃቂ የቦንብ ፍንዳታና እልቂት በየጊዜው የሚሰማባት ከክፉ ዜናዎች የማትርቅ ሀገር ነበረች። የሞቃዲሾ መደበኛ መኖሪያዎች ቀርቶ ከቤተ መንግሥት እስከ አውሮፕላን ማረፊያው ያለው ዋና መንገድ እንኳ፣ ለመሪዎቿ ጭምር አስፈሪና ሥጋት የተሞላ ነበር። የአጥፍቶ መጥፋትና የፍንዳታ ወሬ ተቀይሮ፣ ይሄው ሞቃዲሾም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሳምንት ሦስት ቀን በረራ የሚያደርግባት ሰላማዊ ከተማ ሆናለች።

እምብዛም በመልካም ስሙ የማይነሣውን የአፍሪካን ቀንድ ትእምርተ ብልጽግና እናድርገው። አየር ላንድ ከዛሬ መቶ ሃምሣ ዓመታት በፊት ለአምስት ዓመት የቆየ (845-49 እ.ኤአ) ከባድ የሆነ ረኃብ ገጥሟት ነበር። የድንች ድርቅ ይሉታል። በተከታታይ ዓመታት በድንች ላይ በደረሰው ችግር ምክንያት የተከሠተ ነበር። አየር ላንዳውያን በብርቱ ታግለው ዛሬ ለሌሎች የሚተርፉ ሆነዋል። ይሄው የድንች ድርቅ ወደ ኖርዌይም ተዛምቶ የሃምሣ ሺሕ ኖርዌያውያንን ሕይወት ቀጥፏል። ከዐርባ ሺሕ በላይ ኖርዌያውያንም በስደት አሜሪካ ገብተዋል። ያውም ብዙዎቹ ለማለፊያ የሚበቃ ገንዘብ ስለሌላቸው ያለ ክፍያ እስከ ሰባት ዓመት ለማገልገል እየፈረሙ ነው የገቡት። ኖርዌይ ዛሬ የት ነው ያለችው?

ቻይናውያን ከሃምሳ ዓመታት በፊት ምን ነበሩ? ኤምሬቶች ከዐርባ ዓመታት በፊት የት ነበሩ? ቬትናማውንያንና ሲንጋፖራውያን ከዐርባ ዓመታት በፊት ማን ነበሩ? በርትቶ በመስራት የማይለወጥ ሀገር የለም። የማይቀየርም ክፉ ስም የለም። ይሄን ቀጣናዊ ሰላምና የተረጋጋ ሁኔታ ይበልጥ ልናሳድገው፣ ድንበሮቻችንን ክፍት አድርገን ገበያዎቻችንን በመቀላቀል፤ ሕዝቦቻችን የትም ሄደው በነጻነት ሊሠሩ ይገባል። ምሥራቅ አፍሪካ ነጻ ገበያ እና ‹‹ኮሜሳ›› ተጠናክሮ፣ መተሳሰርና ኢኮኖሚያዊ ትስስሩ ለፍቶና ተጠናክሮ መላውን አፍሪካ ቢያካትት፤ የመደመር ፖለቲካ ከአፍሪካ አልፎ ገበያችንን እስከ መካከለኛው ምሥራቅ ድረስ ሊያሰፋው ይችላል። አፍሪካዊ የኢኮኖሚ ውሕደት ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ትርፍና ብልጽግና ታላቅ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። በምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ያለው እምቅ ዐቅም አፍሪካን የብልጽግና ተአምር የሚሠራባት አህጉር

ሊያደርጋት ይችላል።

በሀገር ውስጥ የተጀመረውን የመደመር እንቅስቃሴ አጠናክረን በቀጣና ደረጃ ካቀጣጠልነው፣ ሰንሰለት ያለው የዕድገት ሰደድ እሳት መፍጠር እንችላለን። በዚህ መንገድ አፍሪካን የገዥዎቿ መፈንጫ መስክ ከመሆን የሕዝቦቿ ፍሬያማ ገነት ማድረግ እንችላለን። ለሀገራችንም ሆነ ለአህጉራችን አዲስ ታሪክ የመሥራት ዕድል ከፊታችን ይጠብቀናል። ምርጫው ይሄን ትልቅ ዕድል በሐላፊነት ተቀብሎ ወደፊት መጓዝ ወይም ፊትን የኋልዮሽ አዙሮ ማፈግፈግ ብቻ ነው።

በፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴና በፀረ ቅኝ አገዛዝ ትግል የተጀመሩት የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነጻነት ትግሎች ተደምረው ዳር ያልደረሱባት አህጉር አፍሪካ ነች። እንደ አህጉር መደመርን በአግባቡ ልንተገብረው ከቻልን ወደ ሁለንተናዊ ብልጽግና የሚያሸጋግር መሠረት ይሆነናል። መደመርን እንደ አስተሳሰብ በሕዝቦቻችን ዘንድ ማሥረጽ ከቻልን፣ ለተግባራዊነቱ ከተጋን ያለ ጥርጥር ከሀገር አልፈን፣ ቀጣናችንን ብሎም አህጉራችንን ለመለወጥ የሚያስችል ጉልበት ይኖረናል።

ብርቅዬ ዕሴቶቻችንን በመደመር መርሕ እንደ ሰንሰለት በማስተሳሰር፣ ያለፉትን ጥፋቶችና ክፍተቶች በማረም፣ በደልና ግፍን በፍትሕና በይቅርታ ሚዛን ላይ በማኖር፤ የወደፊቷን ብሩህ ሀገር መገንባት እንችላለን። በተለወጠ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ወደ አፍሪካ ቀንድ እንዝለቅ። ፍቅርና ይቅርታን፣ አንድነትና ሰላምን አማካዩ ባደረገ የመደመር ስሌት ውስጥ ገብተን ለላቀ ድል ወደ መላዋ አፍሪካ፣ ብሎም ወደ ዓለም እንትመም።

# ክፍል ሦስት

## የመደመር እሳቤዎች

# ምዕራፍ ዘጠኝ

'ፍሪልዮን'

**ከአክሱም ጫፍ አቁማዳ**

ትግራይ ላከ፣ ወሎጋ፣ አበድረኝ ብሎ አንድ ቁና ጤፍ

ወሎም አፈረና የለኝም ማለቱን ባህሉን መዝለፍ

ቆሌውን መንቀፍ

ላከ ወደ ሸዋ ምናልባት ቢሰጠው ለሰው እሚተርፍ።

ሸዋም አፈረና የለኝም ማለቱን ወደ ሐረር ዞረ

ሐረርም መልሶ ባሌን አተኮረ

ባሌም ወደ አርሲ፣ አርሲ ሲዳሞን

ሲዳሞም ተክዞ፣ ግን የለኝም ብልስ ማን ያምነኛል ብሎ

ወደ ጋሞ ላከ አቁማዳ ጠቅሎ።

ጋሞን ብርድ መታው ሐዘን ገባውና

የራሱን ምንዳቤ የግል ሥቅየቱን ችሎት በጥሞና

በጋቢ ጀቡኖ የልቡን ጠባሳ ሲኖር እንደ ደኅና

ዛሬ የወንድሙን የእርዳኝ አቤቱታ መስማት አልቻለና።

አውጥቶና አውርዶ ላከ ወደ ከፋ እጅግ አስተዛዝኖ

ካፍረት ያድነኛል ከራብ ያወጣኛል ሲል በአያሌው አምኖ።

ከፋ እንደ ደረሰው በድንገት አቁማዳው በነብሱ ዋይታ

ሐራራው ተሰማው የሥጋው ድንፋታ

ብልኅት አዛጋ ቆይቶ ቆይቶ የተስፋ ጠል ቀዳ

ሊልክ ከኢሉባቦር አበድረኝ ብሎ እህል በአቁማዳ።

ጭምት ኢሉባቦር ይኖር የነበረ የቤቱን ጉድ ጓዳ

በሞኛሞኝ ገላው ቆዳው ውስጥ ወሽቆ

ጠየቀ ወሊጋን ሃፍረቱን ደብቆ ኩራቱን ዘቅዝቆ

ኬት አመጣ ብሎ ወደኔ ላከብኝ እያለ ወለ እጅጉን ተደሞ

ሄደ ወደ ጎጃም ዛሬን ሁነኝ ብሎ ሊማጸነው ቆሞ።

ጎጃምም ተሰምቶት ሰቀቀን ሐዘኑ ደረት እየመታ፣ ቅኔ እያወረደ፣ እንባ እያፈሰሰ

ወግና ኩራቱን በየቦዳው መሐል እየነሰነሰ

ዓባይን ተሻግሮ ከጎንደር ደረሰ።

ፋሲል ላይ ተነጥፎ ጎንደርም ሐዘን ላይ ነበረ ተቀምጦ

ተድላ ልጁ ሞቶ ገናን ክንዱ ታጥፎ በዘመን ተድጦ

ጎጃም መጣ ሲሉት የእዝን የተመኘን ልቡን በታዘበ

የኩራት ካባውን ሲጥል ባንጓበበ

የወንድሙ መምጣት እቅጩ መንሥኤ መሆኑን ሲረዳ ረኃብ አበሳ

ጥንትም አልሆነኝም ከእንግዲህ ይበቃኛል ለይሉኝታ አልሳሳ

ብሎ ከኤርትራ እህል ለመበደር በርትቶ ተነሣ።

የዘመዱ እጦት ነበርና እጦቱ በዝቶ ሰቀቀኑ

ኤርትራ ታመመ ደም ጎረፈ ከዐይኑ።

ወደ ትግራይ ላከ መላ ባገኝ ብሎ ከአደራ ደብዳቤ

እባክህ ላክልኝ አንድ አቁማዳ እህል ልሞት ነው ተርቤ።››

ትግራይ አስተውሎ አቁማዳው የራሱ መሆኑን ለይቶ

ረኃብ ዕጣቸው የሁል ወንድሞቹ መሆኑን አካቶ

ሐዘኑ አነቀው፤ ትንፋሹ መረረው፣ ትካዝ ሆዱ ገብቶ።

እኔና ወንድሞቼ” አለ በለዘብታ

ለራሱ እንዲያወራ የራሱን ስሞታ፤

“እኔና ወንድሞቼ ሁላችን . . . ሁላችን

ከባዶ አቁማዳ ነው እሚዛቅ ፍቅራችን

ይኸ ነው አንድነታችን፣ ይኸ ነው ባህላችን

ዘመን ማዛጋቱ በያንደበታችን።

ለኋላ ትውልዶች ተረት እንዳይመስል ይኸ ብካይ እሮሮ

ይኸ ጠፍ ሰብእና ይኸ ሥቁይ አእምሮ

እንዳኖር ያሻኛል ይኸንን አቁማዳ ከፍ ካለ ስፍራ

መጥቆ እንደ ባንዲራ

ምንም ባዶ ቢሆን በውስጡ አይጠፋና የታሪክ አዝመራ።”

ይኸንን ተናግሮ ከአክሱም ሐውልት ዘንድ ትግራይ ተጠግቶ

አንዴ እየጸለየ አንዴ እየዘመረ ያለመጠን ተግቶ

ጫፉ ላይ ሰቀለው ያን አቁማዳ አውጥቶ።

**ደበበ ሰይፉ**

(ለራስ የተጻፈ  ደብዳቤ) ፣

1967

ጥር ወር በአውሮጳ በረዷማ የክረምት ወቅት በመሆኑ ከአፍሪቃ ለሚሄድ ሰው ቅዝቃዜው ከአጥንት ዘልቆ ይገባል። በዚህ በረዶውና ብርዱ ባየሉበት ወቅት፣ በጣልያን ታላቋ የሮም ከተማና የዓለም የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መንበር በሆነትዋ ውቧ ቫቲካን የነበረን ይፋዊ ጉብኝት የማይረሳ ነበር። ከጣልያን መሪዎች፣ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳትና ከታላላቅ መንፈሳዊ መሪዎች ጋር በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ውይይቶችን በማድረግ ወዳጅነታችንን ያጠናከርንበት ጊዜ ነበር። የፖፑ የቅርብ አማካሪና በቤተ ክርስቲያኒቱ አንቱ ከተባሉ መንፈሳዊ መሪዎች አንዱ የሆኑት የኛው ካርዲናል አባ ብርሃነ ኢየሱስ፣ የነበረንን ጉብኝት ልዩ ከማድረጋቸውም ባሻገር ሀገራችን በሮም ያላትን ውክልናና ቦታ ከፍ ያደረጉ አባት መሆናቸውን አይቻለሁ።

በዓለማችን ባሉ ዋነኛ የሥልጣኔና የታሪክ ማዕከላት ውስጥ ያደረግናቸው ጉብኝቶች የክረምቱን ቅዝቃዜ ያስረሱን ነበሩ። ጥበብና ፍልስፍና፣ ታሪክና ፖለቲካ እንዲሁም እምነትና ኪነ ሕንጻ ጎልተው የሚታዩባት ጥንታዊቷ ሮምና ዘመናዊዋ ጣልያን አንድም ሁለትም ናቸው። ከዓለም ዙሪያ የሚጎርፉትን በሚልዮን የሚቆጠሩ ጎብኚዎች እያማለሉ ተቀብለው ይሸኛሉ። ሮምን ከነሙሉ ግርማዋና ውብቷ ያየ ሰው፣ በዐድዋና በማይጨው አባቶቻችንና እናቶቻችን ተጋጥመው ያሸነፉት ኃይል የመንደር ጉልበተኛን ሳይሆን የኃይለኞችን ኃይለኛ መሆኑን ተገንዝቦ የላቀ ክብር ሊሰጣቸው ይገደዳል።

በታላቋ ሮም የነበረውን ጉብኝታችንን እንደ ጨረስን የጉዟችን ኮምፓስ የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም ስብሰባ ወደሚካሄድባት የአውሮጳ ውበት መገለጫ ወደምትባለው ስዊዘርላንድ አነጣጠርን። ከጥቂት ሰዓት በረራ በኋላ ነጭ የበረዶ ሸማዋን ተከናንባ ዙሪያዋን በከበቡዋት ታላላቅ የአልቡላ አልፐስ ተራሮች  መካከል ወደተደበቀችው ትንሷ_የዳቮስ ከተማ ገባን።

ዓሥራ ሁለት ሺሕ የማይሞሉ ነዋሪዎች ያሏት ዳቮስ ከዚህ ታዋቂ ዓመታዊ ስብሰባ በተጨማሪ የበረዶ ተንሸራታቾች የሚያዘወትሯት ስመ ጥር የአውሮጳ የመዝናኛ ከተማ ናት፡ ይህ ዓመታዊ ስብሰባ ብዙ ታዋቂ የሀገር መሪዎች፣ ሳይንቲስቶችና ባለጠጎች የሚሳተፉበት እስከ ሦስት ሺሕ ታዳሚዎችን የሚያስተናግድ የዓለማችንን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስስ ታላቅ ጉባኤ ነው። ከዋናው ጉባኤ በተጨማሪ ብዙ የጎንዮሽ ስብሰባዎችን በማድረግ ስለተጠመድን የነበረው ድካም ቀላል አልነበረም። ብዙ መሪዎችና ታዋቂ ሰዎች በሀገራችን እየታየ ያለውን የለውጥ ማዕበል ምን ያህል በአድናቆት እንደሚያዩት ስረዳ ለእኛ ያልታየን ነገር ይኖር ይሆን? ብዬ መጠየቁ አልቀረም። ስብሰባው በአናት ባናቱ ስለነበረ ከተማይቱን ለመጎብኘት በቂ ጊዜ አልነበረንም። በአገኘሁዋት ጥቂት ጊዜ በጉባኤው ላይ የቀረቡ ሐሳቦችና ሚዛን የደፉ ሥራዎች ወደሚታዩበት ሰፊ የኤግዚብሽን አዳራሽ በመሄድ ወዲያ ወዲህ እያልኩ አንዳንድ ሥራዎችን ሳይ ቆየሁ።

ግራና ቀኝ እያማተርኩና ውስጤ የሚመላለሰውን ብዙ ሐሳብ መልክ እያስያዝኩ ሳዘግም ድንገት ቀልቤን የሚይዝ ጽሑፍ ከባሻገር ተመለከትኩ። A Frillion dollar worth idea' ይላል ጽሑፉ። ፍሪልዮን' የሚባል ቁጥር መኖሩንም ከዚያ ቀደም ሰምቼ ስለማላውቅ፣ ይህ ደግሞ ስንት ነው? በሚል ጉጉት ወደ ኤግዚብሽኑ ጎጆ ቀረብ አልኩኝ። ለከዋክብትና ለአሸዋ ስንት እንደሆን ባላውቅም፣ ለገንዘብ ግን እስከ አሁን ትልቁ ቁጥር “ትሪልዮን' መሆኑን ነው የማውቀው። እሱም ቢሆን ወይ የአሜሪካ ጥቅል ሀገራዊ ምርት ወይም የተሸከመችው ትልቅ ዕዳ አልያም በቅርብ ጊዜ እንደ አፕልና አማዞን ያሉ ኩባንያዎች ከብዙ አስደናቂ የስኬት ጉዞ በኋላ የነኩት የሀብት ግምት መሆኑን ሁላችንም ሰምተናል። በርግጥ ከፍተኛ የገንዘብ ግሽበት የደረሰባቸው ሀገራት ትልቅ ቁጥር ያላቸው የገንዘብ ኖቶችን በማተም ችግራቸውን ለመቅረፍ ሲሞክሩ

ታይተዋል።

የዙምባቡዌው መቶ ትሪልዮን ዶላር ኖት (30 የአሜሪካን ዶላር ብቻ ዋጋ ያለው) እንዲሁም ሐንጋሪ በ946 ያሳተመችው የሴክስቲልዮን (1 ከ24 ዜሮዎች ጋር) ፔንጎ ሊረሱ ሊረሱ አይችሉም። እነዚህን ቁጥሮች እንኳን ለመጠቀም ምን ያህል እንደሆኑም ለመረዳት አስቸጋሪ ነው።

የሰው ልጅ ዘመኑን ሁሉ ሲቆጥር የኖረ ቢሆንም፣ መጠን በጣም እያነሰ ሲሄድ ወይም እጅግ እየገዘፈ ሲመጣ የቁጥር መጠንን ለማገናዘብና ትርጉም ለመስጠት እጅግ ይቸገራል። ሚልዮን፣ ቢልዮን፣ ትሪልዮን የሚባሉ ቁጥሮችን ከመላመዳችን በፊት መጠኑ የበዛ ቁጥርን የምንጠራው እልፍ፣ አእላፍ፣ ትእልፊት፣ ወዘተ እያለ በሚቀጥል አቆጣጠር ነበር። በጊዜ ሂደት ግን ሚልዮን፣ ቢልዮን፣ ትሪልዮን፣ ኳትሪልዮን... እያለ የሚቀጥለውን ማለቂያና ማብቂያ የሌለው የአሐዝ ክምር እየተላመድን ነው። ይሄንን እያሰብኩ ነበር በዚህ የቁጥር መሰላል ላይ የፍሪልዮን ማረፊያው የት እንደሆነ ያልተመለሰ ጥያቄዬን ይዤ ከሩቅ ካየሁት ጽሑፍ አጠገብ የደረስኩት።

ከሩቁ ‘ፍሪልዮን’ ብዬ ባነበብኩት ሰሌዳ ላይ ያለው ጽሑፍ ቀረብ ብዬ ሳየው የትሪልዮን ዶላር ሐሳብ' ነበር የሚለው። በማላውቀው ምክንያት ለውትሮ የሰማይ ጥግ ሆኖ የሚታየኝ ትሪልዮን ከማውቃቸው ትንንሽ

ቁጥሮች አንዱ ሆኖ ታየኝ። 'ፍሪልዮን' ከሚባለው ቁጥር አንጻር ሁሉም ቁጥሮች ደቃቅና ድንክዬ ሆነው ታዩኝ። ፍሪልዮን የቁጥሮች ንጉሥ ሆኖ ታየኝ፤ ቁጥሮች ሁሉ ቁጥራቸውን የሚያገኙበት የቁጥሮች ምንጭና ልኬት። ከሰሌዳው ላይ የተገለጸውን የትሪልዮን ዶላር ሐሳብ ምንነት እንኳን በቅጡ ሳላጣራ ውስጤን ካነቃቃው የፍሪልዮን ሐሳብ ጋር እየተጫወትኩ ወዲያ ወዲህ ማለቴን ቀጠልኩ።

ከሚሊዮን ጀምሮ ያሉ ትልልቅ ቁጥሮች የጋራ መለያቸውና ድንበራቸው llion' - ሊዮን' የሚለው ድኅረ ቅጥያ ሲሆን ትክክለኛ ትርጉሙ ይህ ነው ለማለት ባይቻልም የግዙፍ ቁጥሮች መለያ ሆኖ ያገለግላል። በእርግጥ መጨረሻው ላይ "ዮን የሚለው ድምፀት በጣልያንኛ የብዛት አመልካች ቅጽል ነው።

ከትሪልዮን ወደ ዜሮ ከዚያም ተመልሼ ወደ ፍሪልዮን ስመጣ ብዙ ጥያቄዎች በፍጥነት ወደ አእምሮዬ እንደ ጅረት ሲፈሱ ቆዩ። ይህ ሁሉ የሆነው በአጭር ጊዜ ውስጥ ነበር። ሓሳብና ምናብ ከጊዜ ውጭ የሚሠሩ የሌላ ዓለም ክፋዮች ሳይሆኑ አይቀሩም። "Free" ነጻ፣ "llion" ደግሞ የቁጥር ታርጋ። "ፍሪልዮን" ነጻ ቁጥር፤ ነጻን የሚያክል ቁጥር፤ ወሰን የሌለው ነጻ ቁጥር። ለሀገር፣ ለወገን፣ ለፈጣሪ የሚሰጥ ተመን አልባ ስጦታ። የፍሪልዮን ዶላር ኢንቨስትመንት፣ በነጻ የመስጠት ኢንቨስትመንት፣ በነጻ በመስጠት መክበር። መስጠት - መስጠት - መስጠት።

መስጠት ደማቅ አሻራን አትሞ የማለፍ ትልቅ ምስጢር ነው። በነጻ መስጠት ደግሞ የፍሪልዮን ዶላር ኢንቨስትመንት ነው። ለዘመናት በገዳ ሥርዓት ራሱን ሲያስተዳድር የኖረው የቦረና አርብቶ አደር በነጻ መስጠትን በተመለከተ አንድ አስደናቂ ልማድ አለው። የቦረና አካባቢ ቆላማ በመሆኑ ክረምት ከበጋ የሚፈሱ ወንዞችና ምንጮች እምብዛም የሉትም። ከብቶቹን እና ግመሎቹን ውኃ ለማጠጣት ኤላ ተብሎ የሚታወቅ ጉድጓድ ቆፍሮ ማዘጋጀት ግድ ይለዋል። ኤላ አጠገብ ለእንስሳት የውኃ መጠጫ ገንዳ ይኖራል። የቦረና አርብቶ አደር ውኃውን ከኤላ አውጥቶ እንስሳቱን አጠጥቶ ዝም ብሎ አይሄድም። እንስሳቱን አጠጥቶ እንደጨረሰ ገንዳውን በውኃ ሞልቶ መሄድ ለዘመናት የቆየ ልማዱ ነው። እንስሳቱ ጠጥተው ከጨረሱ በኋላ ገንዳውን ውኃ ሞልቶ የመሄዱ ምስጢር ሌላ አይደለም። ውኃ የተጠሙ የዱር እንስሳትና አዕዋፍ በውኃ ጥም እንዳይቸገሩ፣ ውኃን ለዱር ፍጥረታት በነጻ የመስጠት ባህል ነው።

ትልልቆቹ የሰው ልጅ በረከቶች በዋጋ የሚተመኑ አይደሉም። ፍቅር፣ ውበት፣ እውነት፣ እምነት፣ ምስጋና፣… በገንዘብ የምናገኛቸው ነገሮች አይደሉም። ማንም በገንዘብ ድኻ የሆነ ሰው እነዚህን መስጠት ይችላል። ተፈጥሮ እነዚህን ሁብ ቶች ለሁሉም ሰው የሰጠችው ሁሉም ሰው እነዚህን ኢንቨስት አድርጎ በረከት እንዲሰበስብ ነው::

ሰላምታንና ፈገግታን እንውሰድ። አንድ ሰው ሰላምታና ፈገግታ በመስጠት ብቻ የዓለምን ቋጥኞች መናድ ይችላል። ለመስጠት እስከ ፈለግን ድረስ የምንሰጠው አናጣም። እኛም በነጻ የተሰጠን አለና። ሁሌም መስጠታችንን ለማብዛት እንሞክር። ዓለም ለማይሰጥ ሰው ክብር የላትም። ያለውን ካልሰጠ የሰጠችውን ትነጥቀዋለች።

መስጠት በሌለበት መቀበል ከየት ይመጣል? ከይቅርታ ውጪ ፍቅር፣ ከሰላም ውጭ ደስታ ይኖራል ብለን

ማሰብ አንችልም። እርግጥ ነው ዛሬም ቢሆን መግደል ማሸነፍ፣ መጣል መብለጥ በሚመስላቸው አእምሮዎች ውስጥ መስጠትና ማካፈል፣ ፍቅርና ይቅርታ፣ መጨመርና መሙላት ሳይሆን መቀነስና መጉደል ተደርጎ ይቆጠራል። መስጠት ዞሮና በዝቶ የሚመለስልን ብድር ሳይሆን፣ ላይታፈስ ፈሰሶ እንደ ቀረ ውኃ፣ ተቃጥሎ አመድ እንደሆነ ማገዶ ይታሰባል።

አጢኖ ለተመለከተው ግን እውነታው ከዚህ የራቀ ለመሆኑ ተፈጥሮ እንኳን በዑደቷ ታስተምረናለች። ከቶም ዛሬ ቀጥፈን የምንበላው ፍሬ ትናንት የተተከለ ችግኝ ትሩፋት አይደለምን? ከዕጽዋት ጋርስ በመመጋገብና በመለዋወጥ የምንጋራውን አየር ዛሬ የፈጠርነው ነውን? እህል ውኃችን የሚቀዳበትን ኢኮኖሚ እኛ ብቻ የመሠረትነው ነውን? ዛሬ የምንመገባቸውን አዝርዕት ያለማመድናቸው እኛ ነንን? የዛሬዎቹን የቤት እንስሳት ያላመድናቸው እኛ ነንን? የሚያንቀሳቅሰውም ሆነ መሠረቱ የተጣለበት ፍልስፍና ሳይቀር ሁሉም በትናንት ድካም የተገኙ፣ የትናንት መስጠትና የመደመር ትሩፋቶች አይደሉምን? ቢገባንማ አንጠፍጥፎ በመስጠት እንጂ ነጥቆ በመጎሰር ሰዋዊ ሙላት አይገኝም። መሰብሰብ ሸክም ያበዛል። ጥጋብ እንጂ ርካታ አይሆንም።

ዘመኑ እንዴትም ይሁን እንዴት፣ የሰዉ ጠባይ እንደ ምንም ይሁን እንደ ምን፤  የላቀውን ለመስጠት ብቻ ሳይሆን የላቀውንም ለመቀበል ዝግጁ መሆን የተሻለ ምርጫ ነው። መስጠትና መቀበል አይቀሬ ብቻ ሳይሆን ውብ የሕይወት ምስጢር ነው።

ሁላችንም ከተቀባይነት የማናመልጥ ከመስጠት ውጪም ሕይወታችንን ሙሉ ማድረግ የማንችል ተቀባባዮች ነን። የመደመር እሳቤ የጸጋና የምስጋና ተቀባዮች፣ የደስታና የልግስና ሰጪዎች በመሆን የሚደመደም የትስስር ስሌት ነው። ሰጭነትና ተቀባይነትን ዐውቀን ከተጠቀምንበት በውጤቱ ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ሀገርንም ልንለውጥበት እንችላለን። ለዚህ ከተቀበለው አልቆ በመስጠት የከፍታው ጫፍ ላይ በክብር ዐርፎ የሚገኘውን ጀግናውን አትሌት አበበ ቢቂላን ማስታወስ እንችላለን።

ይህ የኦሎምፒክ ጀግና የሩጫን እና የድሉን ታላቅነት ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላ አፍሪካውያን የቀደደ ነው። ‹ጨለማ› ተብሎ ይወቀስ የነበረው አህጉር ፋናው በኦሎምፒክ አደባባይ እንዲበራ እንደ ተወርዋሪ ኮኮብ መንገዱን መርቷል። በባዶ እግር፣ በተቃጠለ ጥቁር ድንጋይ ላይ 42 ኪሎ ሜትር ሮጦ አንደኛ ሲወጣ ለሀገሩና ለሕዝቡ ምን ያልሰጠው ነገር ነበር? ክብሩን፣ ምቾቱን፣ ዐቅሙንና ሁለንተናውን። በመስጠቱስ ምን ያላገኘው ነገር አለ? የሀገርን ክብርና ዝና ከፍ ከማድረግ በተጨማሪ በትውልድ ልብ ውስጥ የሚንቦገቦግ ዘላለማዊ ችቦ፣ የማያንቀላፋ እሳትም ለኩሷል። ሞቶ ተቀብሮና ዓመታት አልፈው እንኳን የጀግኖች ጀግና ነውና ዛሬም ስሙ በልባችን ውስጥ አበበ እንጂ መች ሞተ? እንኳን እኛ ወገኖቹ ጃፓኖች እንኳን አበበ ያሸነፈበትን ጊዜና ቦታ በክብር ያስቡታል።

ቁጥር አልባ ቁጥር የሆነውን ፍሪልዮንን ‹‹ፍሪልዮን›› የሚያደርገው ከኋላው የደረደራቸው የዜሮዎች ብዛት ነው? ከሆነስ ፍሪልዮን ባለ ስንት ዜሮ ቁጥር ነው? አሰብኩ፡፡ ለመሆኑ እስከ ዛሬ የመጨረሻው ትልቁ ቁጥር ስንት ነው? ብዬ ኢንተርኔት መፈተሽ ጀመርኩ፡፡ ‹‹ጉግልፕሌክስ» የሚባል ቁጥር አገኘሁ … ጉግልፕሌክስ እነትሪልዮንን ጫጩት ያሳክላቸዋል። ስንት መሆኑን ግን የሚያውቅ ማንም የለም።

ሌሎችም ከጉግልፕሌክስ በላይ የሆኑ ቁጥሮችን አገኘሁ… ሁሉም ግን ከቁጥር በላይ ቁጥር ለመሆን የሚታገሉ ፅንሰ ሐሳቦች ሆነው ታዩኝ። እኔ ግን ፍሪልዮን የሚባል ከቁጥር በላይ ያለ ቁጥር ሳይሆን ቁጥር አልባ ቁጥር ፍለጋ ላይ ነኝ።

ዓለም አብዝተው የሰጧትን አብዝታ ትሰጣለች። ጥላሁን ገሠሠ ድምፁን አብዝቶ ያለስስት ሰጠን። ራሱ እንኳን ስንት እንደ ሆኑ በትክክል ቆጥሮ የማይዘልቃቸውን የዜማ ጅረቶች አወረደልን። ስለ ሁሉም ጉዳያችን በሚስረቀረቅ ድምፁ አንጎራጎረልን። እኛም ከሰጠን በላይ በድምፃዊነቱ ወደድነው። አከበርነው። ተፈጥሮ ያደለችውን ድምፁን ለመሳል ውኃ ውስጥ እየጠለቀ በሚያደርገው የትንፋሽ ልምምድ ይበልጥ ድምፁን እያራቀቀው ሲሄድ፣ እሱንም ያለ ስስት ሲለግስ እኛም ፍቅራችንን ያለስስት ሰጥተን ከዘመን ወደ ዘመን አሻገርነው።

ጥላሁን ዘፈኖቹን የሰጠን እሱም ከገጣምያን ግጥም፣ ከዜማ ደራስያን ደግሞ ዜማን ተቀበሎ ነው። የመሣሪያ አጃቢዎች፣ አቀናባሪዎች፣ አታሚዎችና አሠራጮች ሁሉ ድርሻ አላቸው። በእያንዳንዷ የጥላሁን ሙዚቃ ውስጥ የብዙ ሰዎች አሻራ አለበት። ለብቻ በመሮጥ የሚገኝ ድል የለም። የዜማ ደራሲው፣ ገጣሚው፣ አቀናባሪው፣ ሙዚቃ ቤቱ፣ ካሴት አዟሪው፣ የሙዚቃ ሃያሲው፣ የሙዚቃ አስተማሪው፣ የማስታወቂያ ባለሞያው… ቁጥር ስፍር የሌለው መሰጠት ይከተላል። ተቀብሎ መስጠትን የሚያውቅ ሰው እሱ የፍሪልዮን ኢንቨስትመንት ባለቤት ነው። መደመር ማለትም ይህ ነው።

እያንዳንዳችን የያዝነውን አካልና አእምሮ በመስጠትና መቀበል ሂደት ውስጥ የገነባነው ነው። ስናድግ የእናትና አባት ብቻ ሳይሆን የመላው ኅብረተሰብ ክትትል፣ ምክርና ተግሳጽ ስላልተለየን ነው አሁን የያዝነውን ሰብእና የያዝነው። ጠዋት ወደ ሥራ ስትገቡ ከፈግግታ ይልቅ ጨፍጋጋ ፊት የሚያሳያችሁ ቢኖር ቢሮ ገብታችሁ በውጤታማነት አትሰሩም። ወኔና ብርታታችሁን ይገድለዋል። ስለዚህ ጠዋት ፈገግታ የሰጣችሁ ሰው በቀናችሁ ላይ ሥልጣን አለው ማለት ነው። ማንም ብቻውን አይጓዝም።

መብራቱን፣ ስልኩን፣ ራዲዮውን፣ ቴሌቪዥኑን፣ መኪናውን፣ ወዘተ የሰጠን ሌላ ሰው ነው። ያለሰው ብቻችንን አንድ ቀን እንኳን መዋል አንችልም። በምድር ላይ ሰው ሁሉ ጠፍቶ ብቻችንን ብንቀር ምን የምንሆን ይመስለናል? እንደ አዲስ ድንጋይና ድንጋይ አፋጭተን እሳት እንለኩስ ካልሆነ በስተቀር አሁን ያሉን በረከቶች ሁሉ አይኖሩንም። ሥጋ ጠብሰን የምንበላበትን እሳት እንኳን ማግኘት ጭንቅ ነው፤ ክብሪትን ተቀብለነው እንጅ ራሳችን ፈጥረነው አይደለምና። ስለዚህ ካለቅብብሎሽ እኛ ሰው ልንሆን አንችልም። ድንጋይ ከማፋጨት የገላገለን አብሮነት ነው፤ መስጠትና መቀበል ነው። ምሉዕ ሰው መሆን የሚቻለው በመደመር ብቻ ነው። ለብቻ ሰው መሆን የለም። ግለሰብ ሆኖ የቀረ በሞት ይቀጫል፣ ያበቃለታል። ‹‹ግለሰብ›› ቤተሰብ፣ ከዚያም ኅብረተሰብ፣ ማኅበረሰብና ሀገረሰብ እያለ ሲበዛ ሞት የማያቆመው ችግር የማይረታው የሰውነት ምስጢር ይገለጣል፤ ምሉዕ ሕይወት በፍሪልዮን ብቻ ትለካለች።

ከላይ የሰፈረው የደበበ ሰይፉ ግጥም እኛ ኢትዮጵያውያን በችግርና በመከራችን ውስጥ ሆነን እንኳን መስጠትን የለመድን ሕዝቦች እንደሆንን ያሳየናል። የደበበ አቁማዳ ትእምርቱ ብዙ ነው። ባዶው አቁማዳ

ባዶውን አልነበረም ሲዞር የነበረው፤ ፍቅር ተሞልቶበት እንጂ። አቁማዳው የኢትዮጵያውያን ማንነት ምልክት ሲሆን ታሳቢ ያደረገው በውስጡ የያዘውን ተዝቆ የማያልቅ ፍሪልዮን ፍቅርን ነው። ለዚያም ነው ደበበ አቁማዳው እንደ ባንዲራ ይውለበለብ ዘንድ ከአክሱም ጫፍ ላይ ይሰቀል ብሎ ግጥሙን የሚደመድመው። እኔ ሁሌም ይሄንን የደበበ አቁማዳ አክሱም ጫፍ ላይ ሲውለበለብ በዓይነ ኅሊናዬ አየዋለሁ።

ጓዳችን ባዶ ሆኖ እንኳን ብድር የጠየቀንን ሰው እምቢ ላለማለት እኛ ራሳችን ብድር ውስጥ የምንገባ ሕዝቦች ነን። ከመስጠት ጋር የዚህን ያክል እንተዋወቃለን። ጉርሻና ዳረጎት የመስጠት ባህላችን ህያው ቅርሶች ናቸው። ከችግራችን በላይ አይሞቱት ሞት የምንሞተው መስጠትን አቁመን መቀበልን ብቻ ስንናፍቅ ነው። ሁሉም የእኔ ብቻ ይሁን ስንል ነው። የእኛ ባህል ራስ ተርቦ ስለሌላው ረኃብ መጨነቅ እንጅ እየነጠቁ ሌላውን ጦም ማሳደር አይደለም። ረኃብም ቁንጣንም እንደሚያሠቃዩ ማስተዋል ይገባናል። ለዚህም ነው ከተራብ ይልቅ ለጠገበ አዝናለሁ የሚባለው። ‹‹ስስት›› የቁንጣን ሕመም ነው። የሚሰስት ሰው ሆዱ ቢሞላም ኅሊናው ተርቧልና ይሰስታል። ብዙ ሀብት ቢያካብትም ከአእምሮው ግን አሁንም የሳንቲም ድምፅ የሚያስስ ጎደሎ ነው።

ከአክሱም ጫፍ ላይ የተሰቀለው የደበበ አቁማዳ የመደመር ባህላችን ምልከት ነው። ዘመናችንን የሚዋጅ የፍቅር ባንዲራ ነው።

# ምዕራፍ ዓሥር

## ርእዮተ ዓለም

## ወይስ

## ርእዮተ ኢትዮጵያ?

“በገብስማ ዶሮ እየተመኻኘ

የኔስ በሽታዬ ሰው ሆኖ ተገኘ።”

~ ሕዝባዊ ግጥም

**የእይታ መነጽርን መቃኘት**

ደስተኛ ሕይወትን የታደሉ ጥንዶች ነበሩ። ለዓመታት ሲቆዩ በትዳራቸው ችግር ገጥሟቸው አያውቁም። አንድ ወቅት ግን ባል የሚስቱ ጤንነት ያስጨንቀው ይጠብበው ጀመር። ቢቸግረው ወደ ሐኪም ዘንድ ሄዶ "እረ ዶክተር፣ የባለቤቴ የመስማት ችሎታ ቀንሷል። ጆሮ ላይ የሚገጠም መሣሪያ ሳያስፈልጋት አይቀርም፤ ግን ምን ብዬ እንደምጠይቃት ቸገረኝ። እስኪ መላ ምታ?" ሲል ይጠይቀዋል።

ዶክተሩም ጥቂት አሰብ አድርጎ፣ "አታስብ ቀላል ነው። ባለቤትህን ዐርባ ርምጃ ርቀሃት ጮክ ብለህ አናግራት። ካልሰማች ዓሥር ርምጃ ቀርበህ ድጋሚ አናግራት። አሁንም ካልሰማችህ ድጋሚ ዓሥር ርምጃ ቅረብ፤ እንዲህ እንዲህ እያልክ መልስ እስክትሰጥህ ድረስ አናግራት። የመስማት ችሎታዋ በዚያ ይረጋገጣል። ከምን ያህል ርቀት ላይ እንደሚሰማት ለማረጋገጥና ምን ዓይነት መሣሪያ እንደሚያስፈልጋት ከዚያ በኋላ እንወስናለን" አለው።

ባልም በሚቀጥለው ቀን እንደተባለው አደረገ። ባለቤቱ ማዕድ ቤት ሆና ምግብ ስታበስል ጠብቆ "ውዴ፣ ዛሬ ምሳ ምንድን ነው?" ሲል ይጠይቃል። መልስ ግን የለም። ዓሥር ርምጃ ደረጃ ጠጋ ብሎ ድጋሚ ይጠይቃል። አሁንም መልስ የለም። እያለ እያለ፣ ዓሥር ርምጃ ያህል ብቻ ርቋት "ውዴ፣ የዛሬው ምሳ ምንድን ነው?" ብሎ ጠየቀ።

ምንም መልስ የለም። አሁን የባለቤቱ ጤንነት ሁኔታ በጣም አሳሰበው። "በቃ ጆሮዋ መስማት አቁሟል ማለት ነው" እያለ አጠገቧ ሲደርስ "ውዴ፣ የዛሬው ምሳ ምንድን ነው?" አለ፣ በጀርባዋ በኩል እንደቆመ። ሚስት ካቀረቀረችበት ቀና ብላ አንባረቀች ። "ዛሬ ምን ሆነሃል? ይሄው ለአምስተኛ ጊዜ ‹ዶሮ ነው ምሳችን› አልኩህ። ፍላጎትህ እኔን ማስጮኽ ከሆነ ቁርጡን ንገረኝ!" አለችው። ለካስ የማይሰማው እርሱ ነበረ። የራስን ዕውቀት እንደ መጨረሻ እውነት ይዞ ጭቅጭቅና ንትርክ ማድረግ የተለመደ ነገር ነው። በተለይ ከግል እይታ የዘለለ ሳይንሳዊ ማረጋገጫ በሌለው ፖለቲካዊ የርእዮተ ዓለም ጉዳዮች ዙሪያ የሚካሄዱ ሙግቶች፣ ዛሬ መለስ ብለን ስናስባቸው አንዳንዶቹ ፈገግታን፣ ሌሎቹ ደግሞ ንዴትንና ግርምትን ያጭራሉ። አልፎ አልፎ ቃላት በመወራወር የተጀመረው ንትርክ በጠብመንጃ አፈሙዝ የሚቋጭበት አሳዛኝ አጋጣሚ ፈጥሮ ማለፉም ይታወሳል።

ታላቅ ሐሳብ የታላቅ ለውጥ መሠረት ነው። የፖለቲካ ተመራማሪዎች እንደሚያስቀምጡት ‹‹ርእዮተ ዓለም» የሐሳቦች፣ የአካሄዶች፣ የእሳቤዎች፣ ወዘተ... ሥርዓት ሲሆን በዋናነት የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ንድፈ ሐሳቦችን ለማርቀቅ መነሻ መሆኑ የአስተሳሰብ ማሕቀፎች ናቸው። ፖለቲካና ኢኮኖሚን በማማከል ያሉንን ገዢ አመለካከቶችና እምነቶች በመቀመር የምንኖርበትን ዓለም መመልከቻ ልዩ መነጽር ነው። የፖለቲካ ቡድን ወይም ድርጅት የሚመራበትን መርሕ፣ የሚያቀነቅነውን አጀንዳ፣ የሚታገልለትን የማኅበረሰብ ክፍል ምን እንደሆነ የሚተነትንበት፤ አቋሙን የሚበይንበት ኅብረተሰብን አደራጅቶ ምን ዓይነት ኅብረተሰባዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚዊ ለውጦችን እንደሚያመጣ ቅርጽ የሚያስይዝበት የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ መመሪያ ነው። ከመነሻ ታላቅ ሐሳብና ትክክለኛነት ባልተናነሰ ደረጃ ርእዮት ዓለማዊ ቅኝት ለሐሳብ የተፈጻሚነት ደረጃን ያጠናክራል። ከሐሳብ ጥልቀትና ርቀት፣ ከሚያማልል ውበትና እውነት ይልቅ ሐሳብ በተግባር ዕቅድ ተመንዝሮ መሬት እንዲወርድ ማድረግ፣ በተጨባጭ ሕይወት ውስጥ ለውጥ እንዲያመጣ ሲደረግ የተፈጻሚነት ደረጃው ከፍተኛ ይሆናል። በዚህም የአቅጣጫ ጠቋሚነት ሚና ይኖረዋል ።

ከዚህ አኳያ “ርእዮተ ዓለ›› ምን ጉዳዮች ላይ ትኩረት መደረግ እንዳለበትና እንደሌለበት በፈርጅ በፈርጁ ለማስቀመጥ ይረዳል። በዚህም ምክንያት በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ አካላት ወጥ የሆነ ግብ ይዘው ለለውጥ እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በተደጋጋሚ በታሪክ ውስጥ ሲፈጸምና ሲረጋገጥ የተስተዋለውም ይኸው እውነታ ነው።

ለምሳሌ የኅብረተሰብን ዕጣ ፈንታ በመወሰን ረገድ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ወሳኝ ሚና ይጫወታል የሚለው ፅንሰ ሐሳብ መነሻ ጀርመናዊው ፈላስፋ ሄግል ነው። የሄግልን ዲያሌክቲክ ንድፈ ሐሳብ መነሻ በማድረግ ካርል ማርክስ የራሱን የዳያሌክታዊ ቁሳካላዊነት ንድፈ ሐሳብ በማርቀቅ  የኅብረተሰብን ዕጣ ፈንታ በመወሰን ረገድ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት የገለጸበትን የማርክሲዝምን ርእዮተ ዓለም ፈጠሯል። ሚልዮኖችንም ከጎኑ አሰልፏል። በማርክሲዝም ርእዮት ዓለም ላይ አዲስ ቀንድና ጭራ በመቀጠል ቭላድሚር ኢሊች ኢሊያኖቭ ሌኒን ካፒታሊስታዊ ሥርዓትን ሳይሆን ፊውዳላዊ የዐፄ ሥርዓትን ከኋላቀሯ ሩሲያ በማስወገድ ሶሻሊስታዊ ሥርዓትን ሊመሠርት ችሏል።

የቻይናው አብዮተኛ ማኦ ሴቱንግ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን በቻይና ተግባራዊ ያደረገው ከሩሲያም በተለየ ለገበሬ ዜጎችና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ልዩ ትኩረት በመስጠት መሆኑ ይታወቃል። ቬትናሞች በአሜሪካ የሚደገፉትን የሰሜን ቬትናሞችን ከአሜሪካ ጋር ጨምረው ማሸነፍ ያስቻላቸው በቻይና ቅኝት ተግባራዊ የተደረገውን ማኦኢዝም በቀጥታ በማውረድ ሳይሆን በጎላ ብሔራዊ ዐርበኝነትም ጭምር በመደገፍ ነበር። በትክክል በርእዮተ ዓለምነት ሊፈረጅ መቻሉ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ቢሆንም አሜሪካውያን ለነፃነትና ራስን በራስ ለማስተዳደር በሰጡት ታላቅ ዋጋ ከእነርሱ የበለጠ ቁጥር እና የተሻለ መሣሪያ የታጠቁትን እንግሊዞች ከውጊያ ውጭ በማድረግ ነፃነታቸውን ማረጋገጥ ችለዋል።

በዚህ ሚዛን ማኅበረሰባዊ ለውጥን ለሚሰፍር በእርግጥም ርእዮተ ዓለም በሙሉ እውነታዊ መሠረት ባይኖረውም፣ ኅብረተሰባዊ ለውጥን በማረጋገጥ ረገድ ጉልህ ሚና መጫውቱን ይገነዘባል።

በኢትዮጵያ በራስ የርእዮተ ዓለም ምሽግ ውስጥ ተሸሽጎ የሌላውን ካምፕ ለማጥፋት ባለመ አቋም የሚደረግ የፖለቲካ ሤራ፣ ከ1960ዎቹ ጀምሮ ባህል እየሆነ የመጣ ነገር ነው። በተለይም ደግሞ ከተማሪዎች እንቅስቃሴ በኋላ በሀገራችን ሰፊ ተቀባይነት ያገኘው የማርክሲዝም/ሌኒኒዝም እሳቤ፣ የዘመኑ ተራማጅ ኢትዮጵያውያንን በብዙ ጎራዎች ከፋፍሎ ሲያፋትግና ሲያጋጭ ቆይቷል። ሁሉም በሚባል ደረጃ የሶሻሊዝም ርእዮተ ዓለም ተከታይ ቢሆኑም፣ “የኔ ሶሻሊዝም ይሻላል፤ ያንተ ሶሻሊዝም ችግር አለበት” በሚል ጥራዝ ነጠቅነት ከጋዜጣና ከበራሪ ወረቀቶች ክርክር እስከ ከተማ ዐመፅና የበረሐ የትጥቅ ትግል የደረሰ የብዙ ሺሕ ወጣቶችን ሕይወት የቀጠፈ አሳዛኝ ፍሬ ቢስ መጠፋፋት ተካሂዶበታል።

ያ ትውልድ በደርግ ተቃዋሚነትም ሆነ በደጋፊነት ፈርጀን ዛሬ የምናስባቸው አባላቱ ከሚለያዩበት ገጽታ ይልቅ የሚመሳሰሉበት መልክ ሚዛን ይደፋ ነበር ማለት ይቻላል። በቅድሚያና በዋናነት ሁለቱም ቡድኖች ታላቁን የሀገራዊ ተቃርኖ መሠረት፣ የመደብና የብሔር ጭቆናን አምነው የተቀበሉ ነበሩ። መሬት ለአራሹና የራስን

ዕድል በራስ የመወሰን መብት መረጋገጥ ግንባር ቀደም መፈክራቸውና ማዕከላዊ ማታገያ ነጥቦቻቸው ነበሩ። ኋላ በተፃራሪ ጎራ መቆም ዕጣ ፈንታቸው ቢሆንም ሁለቱም በአስከፊነቱ የፈረጁት ኋላቀር የፊውዳል ሥርዓት በሕዝባዊ ተቃውሞ ሲገረሰስ አይተዋል። ነገር ግን አንደኛው ወገን ወደ ሥልጣን የመጣውን ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግን ደግፎ አብሮት ለመሥራት መፍቀድ ብቻ ሳይሆን በተግባርም ከጎኑ ተሰልፎ ሲሠራ፤ ሌላው ወገን ደግሞ "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትና ዴሞክራሲን ያለገደብ አሁኑኑ" በማለት በተፃራሪ ጎራ ተሰለፈ።

ትዕግሥትና መቻቻልን የማያውቀው የርእዮተ ዓለም ሰባኪነት፣ ሁለቱን ሶሻሊስቶች እርስ በርሳቸው አፋጃቸው። ምንም እንኳ እነዚህ ሁለት ወገኖች የጠመዝማዛ ትግላቸው መዳረሻ ሶሻሊዝም መሆኑን ርእዮተ ዓለም ግባቸው አድርገው የተቀበሉ ቢሆንም፤ በሚያስማማቸው ነገር ላይ  አብረው እየሠሩ ሌላውን ጉዳይ በሂደት እየተወያዩ ለመፍታት ተስማምተው መዝለቅን አልመረጡም። ይልቅስ በጥቃቅን ነገሮች ተኳርፈው ወደ እርስ በርስ ፍጅት እንደተሸጋገሩ የቅርብ ዘመን ሀገራዊ ታሪካችን ይመሰክርልናል። በእርግጥም ደግሞ የርእዮተ ዓለም ሰባኪነት ከፉከራና ሽለላ፣ ከውረድ እንውረድ ሰባኪነት ባሻገር ርጋታና አርቆ አስተዋይነትን አያውቅም።

ያ ትውልድ ራሱ በግልጽ ባላወቀው ሀገራዊ ሕልም ውስጥ ተነክሮ ከሚጨበጠው ሕልም በእጅጉ ርቆ ነበር። በዚያ የሀገር ፍቅር ትኩሳት ውስጥ ከርእዮተ ዓለም ዳንኪራ ተሻግሮ የሚጨበጥ ሕልም ቢኖረው ኖሮ ዐለት እንደ ብረት አቅልጦ ሀገር ይሠራ እንደነበር ለመገመት ነቢይ መሆን አይጠይቅም። ያ እስከሞት ደጅ ድረስ የዘለቀ የሀገር ፍቅር፣ ያ እንደ ሳምቡሳ በዘይት ለመጠበስ የቆረጠ ኮስታራ ልብ፣ ያ ተረከዝን ከሞት ለሚመር ቁስል የዳረገ ሀገራዊ ወኔ፣ ነባራዊና ሀገራዊ ሁኔታን የመረዳት ዐቅም አዳብሮ የሚጨበጥ ሕልም ቢኖረው ኖሮ አሁን ትዝታችን በዋሸንት የእንጉርጉሮ ዜማ የታጀበ አይሆንም ነበር። ለሀገራችን ራእይ ከመሰነቃችን በፊት ሀገር ምን እንደሆነች በጥልቅ መረዳት አለብን።

ርእዮተ ዓለም ማኅበረሰባዊ ለውጥን ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ባይካድም ዓለምን በነጻነት ከተለያዩ አማራጮች አንጻር እንዳንመለከት የሚገድብ ግርግዳ በመሆን ቀኖናዊነትን መፍጠሩም ይታወቃል። በመሠረቱ ርእዮተ ዓለም የሰው ልጆችን የሐሳብ አድማስ የሚገድብ አቋማዊ ግንብ ነው ማለት እንችላለን። በአንድ ዓይነት ርእዮተ ዓለም ጎራ ውስጥ ያሉ ሰዎች አስቀድመው የደረሱበትን ድምዳሜ ላለማስነካት በዙሪያቸው የሚያንጹት የፖለቲካ ግንብ እና የምልከታ አጥር በጊዜ ሂደት ራሳቸውንም ጠፍሮ  የሚይዝ እስር ቤት ይሆንባቸዋል። እንደነዚህ ያሉት የርእዮተ ዓለም እስረኞች የገዛ ወኅኒያቸውን በገዛ ራሳቸው ፈቃድ ይገነባሉ። በገዛ እጃቸው ስለታሰሩ ራሳቸውን እንደ እስረኛ አያዩም። ሌሎችን እነርሱ ወደ ገቡበት ወኅኒ ለመጨመር በትጋት ይሰብካሉ።

የርእዮተ ዓለም እስረኞች እንደፈለጉ ማሰብና ማንበብ አይችሉም፤ ከፈለጉት ጋር በነጻነት አይመክሩም። ንባባቸውም ሆነ ውይይታቸው፤ ጥናታቸውም ሆነ መፈክራቸው ከዚያው ከትንሿ የርእዮተ ዓለም ኪሳቸው አይወጣም። በሌላ አገላለጽ ከአንድ ምርት ውጪ የሸቀጥ አልባ ኪዮስክ ባለቤቶች ናቸው። የሚሸጡትም ሆነ የሚገዙት የላቸውም። ቀስ በቀስ ነባራዊውን ዓለም እየዘነጉ፣ ራሳቸው በፈጠሩት ምናባዊ ዓለም ውስጥ ተከርችመው፣ አዲስ የወጣችውን ፀሐይ ለማየት ዕድሉንም ፍላጎቱንም አጥተው፣ በራሳቸው ጨለማ ውስጥ

መኖር ዕጣ ፈንታቸው ይሆናል። ምክንያቱም ራሳቸውን አስቀድመው በቸነከሩት የአቋም ችካል ላይ እንደ ቴዘር መጨዋቻ ኳስ ላይፈታ ጠምጥመውታልና።

በዕውቀት ሳይሆን በጥምቀት የርእዮተ ዓለም እስረኛ ለመሆን የፈቀዱ ግለሰቦች፣ አልጋውን ማንጠፍ በማይወድ ሰነፍ ወንደላጤ ልንመስላቸው እንችላለን። አንዳንድ ወንደላጤዎች አልጋቸውን ለማንጠፍ ስለሚሰንፉ አንዴ ባነጠፉት አልጋ ውስጥ ቀስ ብለው ተንሸራተው ገብተው ይተኛሉ። ከአልጋቸው ሾልከው እንደገቡት ሾልከው ይወጣሉ። አንሶላው እንዳይፈላለስባቸው ተጠንቅቀው ስለሚተኙ ዕንቅልፋቸውን በነጻነት አያጣጥሙም። ከተገላበጡ ያነጠፉት አልጋ ስለሚፋለስባቸው የገዛ ነጻነታቸውን ለስንፍናቸው ባሪያ አድርገውት ይኖራሉ። ዕንቅልፋቸው የተረበሸና በሰቀቀን የተሞላ ነው። የርእዮተ ዓለም ምርኮኞችም እንዲሁ ናቸው። አስቀድመው ያሠመሩትን የሐሳብ መሥመር ላለመነካካት ሲሉ የማሰብ ነጻነታቸውን አጥተው በሰቀቀን ውስጥ ይኖራሉ። ርእዮተ ዓለማቸው እንዳይፋለስባቸው አለማሰብን መፍትሔ ያደርጉታል። መገላበጥም ሆነ መለወጥ አይችሉም። ማርክሲስታዊ ርእዮተ ዓለም መሠረታዊ ተቃርኖን መነሻ በማድረግ የሚነሣ በመሆኑ በኃይል አሰላለፍ ወዳጅ ጠላት፣ እኛ እነሱ የሚል ፍረጃን መከተሉ የተለመደ ነው።

በተደጋጋሚ እንደተስተዋለው የርእዮተ ዓለም ክርክሮቻችን መነሻና መድረሻ አንዱና መለያ ችግር ፍረጃ ነው። በተለየ ቦታ የተለየ ሐሳብ ሊቀርብና ሊፈልቅ ይችላል ብሎ ለማመን እንቸገራለን። ከእኛ ሐሳብ የተለየን ሰው ሁሉ ለማብጠልጠል በአንድ ጎራ ውስጥ እንከተዋለን። ከዚያም አልፎ ለወቀጣ እና ቅጥቀጣ እንዲያመቸን በማለም በአንድ ከረጢት፣ በአንድ ሙቀጫ ውስጥ እናጭቀዋለን። ደርግ ተቃዋሚዎቹን ወንበዴ፣ አድኃሪ፣ አቆርቋዥ፣ ፊውዳል፣ ገንጣይ፣ አስገንጣይ፣ የአረብ ደላላ፣ አናርኪስት ወዘተ… እያለ ይፈርጅ ነበር። ተቃዋሚዎቹም ደርግን ፋሽስት፣ ባንዳ፣ ጨፍጫፊ፣ የሥልጣን ጥመኛ እያሉ ይፈርጁት ነበር። አሁንም ይህ መፈራረጅ እንደቀጠለ ነው።

ስንፈርጅ እኛም እንደምንፈረጅ ማወቅ አለብን። መፈረጅ የሰዎችን ሐሳብ ለመረዳት አለመፈለግን ወይም አለመቻልን አመልካች ነው። ፍረጃ የሐሳብ እጦትንና የማስረዳት ዐቅም ውሱንነትን ያሳያል። ለፍረጃ መቸኮል ባዶነትን፣ ግልብነትን ነው የሚያሳብቀው። ሰዎችን ለመረዳት ከመጣር ይልቅ በአንድ ከረጢት ውስጥ ከትተን ለመሳደብ ወይም ለማውገዝ ሲባል ብቻ ለፍረጃ መጣደፍ በጥልቁ አለመብሰል፣ የአርቆ ማስተዋል ጉድለት መገለጫ ነው። የሰዎችን ሐሳብ ለመረዳት ከፈለግን ያቀረቡትን ሐሳብ በአግባቡ አድምጠንና ተረድተን መፍትሔው በምላሹ ሐሳባችንን ማቅረብ ነው። ለመግባባት ክፍት የሆነ ልብ ይጠይቃል፤ የሚሰማ ጆሮ ይፈልጋል። መጀመሪያ የማያወላውል አቋም ይዞ በዚያ ላይ ለመስማት ፈቃደኛ ካልተሆነ ተነጋግሮ መግባባት፤ ተወያይቶና መክሮ መርታትና መረታት የሚባሉ ነገሮች አይኖሩም። ድሮ ከመነሻው ነው ያከተመላቸው።

በሐሳብ ዙሪያ የመጨረሻ የሚባል አቋም፣ የመጨረሻ የሚባል ድምዳሜ የለም፡፡ አቋም የተያዘበት ሐሳብ “የላቀ ሐሳብ” የሚሆነው ለጊዜው ነው። እኛ ሰዎቹ ዝግ ካልሆንን በቀር ሐሳብ በሌላ የተሻለ ሐሳብ ለመረታት ዝግጁ ነው።

በሐሳብ ተከራክረው መርታትና መረታት ከማይፈልጉ ሰዎች ጋር ብንወያይም ለውጥ አናመጣም። ለይምሰል

ሐሳባችንን የሚሰሙን ቢመስለን እንኳን እንዴት አድርገው እንደሚጥሉት ዘዴ ይቀይሳሉ እንጂ በምክንያታዊነት አይመረምሩትም። በተስተካከለ የሐሳብና የአመለካከት ሚዛን ለሚጓዝ ዜጋ፣ የሀገርና ሕዝብን ነገ ማየት የሚቻለው ከእኛው ዛሬ ላይ ቆመን እንጂ፣ በሌሎች ዛሬ ላይ ቆመን እንዳልሆነ የሚሰወር እውነታ አይደለም። የእኛ ሀገር የወቅቱ ተራማጅ ምሁራን ግን በተቃራኒው መንገድ በመጓዝ በትናንቷ አውሮጳ ላይ ቆመው የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ማለም ያዙ። በሌላ አገላለጽ በዛሬይቱ አሜሪካ ደፍ ላይ ሆነን የነገይቱን ኢትዮጵያ እንደማለም ነው። መነሻቸው በአመዛኙ በነዲድ የሀገር ፍቅር ስሜትና የለውጥ ጉጉት የተቃኘ ቢሆንም የጉዟቸው ውልግድና አንዱ ትልቅ ስሕተት ይህ ነው። ዒላማ ከቆምክበት ቦታ አንጻር የምታስቀምጠው እንጂ የትም ቦታ ላይ ቆመህ የምታነጣጥረው አይደለም። ኢትዮጵያን በዛሬዋ ላይ ቆመን ነው ነገዋን ልናነጣጥር የምንችለው። ይሁን እንጂ የማርክሲዝምና ሌኒኒዝም ርእዮተ ዓለም የዚያ ወቅት አማላይነትና ፋሽንነት ተዳምሮ፣ ተራማጆቻችን ከሰው ማሳ መሐል ቆሞው የራስን ጎተራ ለመሙላት የማለም ጥረትና ጭንቅ ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል።

ሮኒንግ ባልስቪክ የተባለች የታሪክ ጸሐፊ፣ በተማሪዎች ንቅናቄ ዘመን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስለነበሩት የተማሪዎች ርእዮተ ዓለማዊ ጥያቄዎች ስታነሣ፣ አንዳንዶች ከማስገረም አልፈው የሚያስቁ ዓይነት መሆናቸውን ትገልጻለች። "የፋሽን ዝግጅት በዩኒቨርሲቲው መዘጋጀት የለበትም … የኢምፔሪያሊስቶች ሥራ ነው› ብለው ከፍተኛ ሁከት ሲያስነሡ እንደነበር ታወሳለች። እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎች በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቻችን አጀንዳ ሆነው ተነሥተው የቀናት መከራከሪያ ሲደረጉ በነበረበት ወቅት፣ ሀገሪቱ ዜጎቿን እንኳን በቅጡ መመገብ ያልቻለች መሆኗን በአመዛኙ መዘንጋቱ ወይም ለጊዜውም ቢሆን ወደጎን መገፋቱ አይቀሬ ነው።

እነዚያ የዕውቀት ብርሃን የፈካላቸው የዚያ ዘመን ወጣቶች፣ ለትምህርት የላካቸውን ድኻ ገበሬ ቤተሰብና ማኅበረሰብ ችግር ረስተው፣ በጥቃቅን ርእዮተ ዓለማዊ ክርክር ጉልበታቸውን ይፈጁ ነበር። ስለፋሽን ርእዮተ ዓለማዊ ተጽዕኖ ያነበነቡበትንና የተመራመሩበትን ጊዜ በከፊልም ቢሆን መሥዋዕት አድርገው በተጨባጩ እውነታ ላይ በማተኮር‹ የገበሬ ወገኔን ማረሻ እንዴት ላሻሽልለት?' ብለው ቢመራመሩ ኑሮ በውሱን ደረጃም ቢሆን ምናልባት ዛሬ ከችግራችን ልንወጣ እንችል ነበር።

አውሮጳውያን ዴሞክራሲ፣ ዕድገትና የጸና ጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታን ማረጋገጥ የቻሉት፤ በራሳቸው መንገድ ከመካከለኛው ዘመን እስከ ሕዳሴ (ሬነሳንስ)፣ ከግብርና እስከ ኢንዱስትሪ ሕዝባዊ አብዮቶችን አካሂደውና በሁለት ታላላቅ የእልቂት ጦርነቶች ውስጥ አልፈው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በጃፓን የዕድገት ጉዞ ውስጥ ቁልፍ ድርሻ መያዙ የሚነገርለት የልማታዊ መንግሥት ፅንሰ ሐሳብ ተግባራዊ የተደረገው ጃፓናዊ መልክና ባሕሪ ተላብሶ ነው። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ በግሉ ዘርፍ የተካሄዱ የባለቤትነት ይዞታ ለውጥ መደረጉ ባይቀርም፤ የንብረቶቹ ባለቤቶችን ከማግለልና ከማራቅ ይልቅ በሥራ አመራር ድጋፍ እንዲያደርጉ ምቹ መደላደል የመፍጠር ርምጃ ተወስዷል።

የኢትዮጵያን ችግር ለመረዳት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ቀርቦ ማጥናት ያስፈልጋል። በአንድ አጋጣሚ ፈረንጅ ሀገር ለትምህርት እንደወጣ የቀረ ምሁር፣ ምዕራባዊውን ዕውቀት በመቅሰሙ የተነሣ ብቻ፣

ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ችግር ከኔ በላይ መፍትሔ ሰጪ ላሳር! ሲል ማድመጥ አሳዛኝም አሳፋሪም ነው። ከአንዲቷ የገጠር ቀበሌ እንኳን በተግባር ትውውቅ የሌለውና ወርዶም ያላየ ሰው፣ የኢትዮጵያን ችግሮች በድፍረት ተንታኝ ሆኖ መቅረብ ግብዝነት ነው። በአራቱም ማዕዘን ለሕዝብ እንታገላለን የሚሉ የፖለቲካ ልሂቃን የራሳቸውን የሥነ ልቦና ችግር በሕዝቡ ላይ ከማራገፍ በፊት፣ ወደ ሕዝቡ ጠጋ ብለው ተግባራዊ ዝምድናን በመፍጠር ማዳመጥና የአገልጋይነትን ልማድ ማዳበር ይኖርባቸዋል።

ርእዮተ ዓለማቸውንም የሩቁን ባለጠጋ ዓለም ሳይሆን መጀመሪያ የቅርቡን ሀገራዊ የብዙኃኑን ኑሮና የራሳቸውን ውስጠ ልቦና ለማየት ሊጠቀሙበት ይገባል። መሠረታዊው ጉዳይ መሬት ላይ ያለውን ችግር አጥንቶ የሚጨበጥ መፍትሔ ማቅረብ ነው። ወሳኙና ፈታኙም ነገር ከርሱ የሚርቅ አይደለም። የአስተዋጽዖዋችንን ልክ ያለብን ላነገብነው መርሕ ባለን ታማኝነት ሳይሆን፣ መለካትና መመዘን በምናስመዘግበው ውጤት ልክ ሊሆን ይገባል። ትኩረታችንን በተጨባጭ ችግሮች ላይ እስካደረግን ድረስ ተጋግዘን ሀገራችንን ወደፊት ማራመድ አይሳነንም። በተቃራኒው በመለወጥ ላይ ባለ ዓለም ውስጥ፣ እያንዳንዷን ነጥብ እየመዘዝን ጠብ ያለሽ በዳቦ ብለን በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ ለግብግብ እጅጌያችንን የምንሰበስብ ከሆነ ግን፣ ለሥራ የሚውለው ጉልበታችን ለብጥብጥ ይውልና ትርፋችን ሰቀቀንና ምሬት ብቻ ይሆናል።

አንድ ጠዋት ናስሩዲን የቤቱ በር በከፍተኛ ድምፅ ሲንኳኳ ይሰማል። እየተበሳጨ ተነሥቶ በሩን ሲከፍት ከደጅ ጎረቤቱ ቆሟል። "መልካም ፈቃድህ ቢሆንና አህያህን ለአንድ ቀን ብታውሰኝ በማለት ጎረቤት ጥያቄውን ያቀርባል። "ለአንተ ለጎረቤቴ ደስ እያለኝ ላውስህ እፈቅድ ነበር። ችግሩ ግን አህያውን ሌላ ሰው በውሰት ወስዶታል" ሲል በትሕትና ናስሩዲን ምላሽ ይሰጣል።

ታዲያ ያ ጎረቤት ተሰናብቶ ሊሄድ ሲል ከናስሩዲን ቤት ጓሮ አቅጣጫ የሚያናፋ የአህያ ድምፅ ይሰማል። ከዚያ ናስሩዲንን ትኩር ብሎ እያየ፣ "የአህያህን ድምፅ ከጓሮ ሰማሁ ልበል?" ሲል ይጠይቃል።

ናስሩዲን ለጎረቤቱ ምላሽ ለመስጠት ሳይጨነቅ ፈጥኖ በሩን በመዝጋት ለራሱ እንዲህ ሲል አሰበ፣ "ምን ዓይነት ጎረቤት ነው… ከእኔ ቃል ይልቅ የአህያዬን ድምፅ ያምናል እንዴ? ለዚህስ እንኳንም አህያዬን አላዋስኩት! ኧረ ንብረቴን ለመዋስ እምነት የሚጣልበትም አይደል!!"

በሀገራችን፣ ርእዮተ ዓለም ሳታውቀው የምታውቀው፣ ሳይገባህ የምትሞትለት ክፉ መንፈስ ሆኖ ቆይቷል። በቃል ከማነብነብና መፈክሮችን በጉልህ ድምፅ ከማሰማት በዘለለ በስክነት ቁም ነገራቸውን ለመውሰድ ያደረግነው ሙከራ ብዙ የሚያስመካ አይደለም። ርእዮተ ዓለም ከሀገር በታች እንጅ ከሀገር በላይ አለመሆኑ ገና ሙሉ በሙሉ አልገባንም። መሥመራችን መዳኛ መሞቻችን ብለን እናቀነቅላለን። በየትኛውም ሚዛን ቢሆን ሀገርን አፍርሶ ርእዮተ ዓለምን ማንበር ኪሳራ ነው። ሁሉም የያዘውን ሐሳብ ቅዱስና ፍጹም አስመስሎ ማነብነቡ ያለ ቢሆንም ፍጹም እንዳይከፈት አድርጎ ለእውነታ በርን መዝጋት የዕድገት ሳይሆን የውድቀት መንገድ ነው።

ኢትዮጵያ አሁን ባላት ዐቅምና ሁኔታ የነጻነትና የእኩልነት ጥያቄዎችን እንዴት ትፈታለች? የሚለውን ጥያቄ ከነባራዊ ሁኔታችን አንጻር ተንትነን ምላሽ መስጠት ይጠበቅብናል። የዜጎችን እኩልነትና ነጻነት ሳይሸራርፉ

በሚዛናቸው ለማስጠበቅ ኢትዮጵያ ያለባት ችግርና ያካበተችው ዐቅም ምንድነው? የሚለውን መፈተሽ ያስፈልጋል።

ከራሳችን ውስጥ ራሳችንን በጥልቀት መፈለግ፣ የተዛባ ታሪካችንን ለማስተካከል ተግባራዊ የምናደርግበት መንገድ ፍቅርና ዕርቀ ሠላም ወይስ ጥላቻና ኃይል? በኢኮኖሚ ልናረጋግጥ የምንሻውን ፍትሐዊነት በማምጣት ረገድ ተመራጩ አቅጣጫ ውርስና ምጽዋት ወይስ የጋራ ባለቤትና ሥራ? ከድህነት እና ድንቁርና ሕዝባችንን ለማውጣት ሕዝብ ለዘመናት ሲያምንበት ከነበረው እምነት ጋር በማፋታት ከአዳዲስ ነቢዮች ጋር ማስተዋወቅ፣ ወይስ በነባሩ ላይ ተመሥርቶ አዲስ መንገድ መተለም? የጋራ ድሎቻችንን በማስፋት የተሳሰርንበትን ሸማ ማጠናከር፣ ወይስ በአዲስ መሠረት አዲስ ውብ ሸማ ለመሸመን ጥረት ማድረግ? ወደኋላ በቀረንበት ልክ ወደፊት ፈጥነን ለመስፈንጠርና ከአንገታችንም ቀና ለማለት የምንሰበስበው እንጂ በትነን የምንዘራው ወረት ሊኖር እንደማይገባ አያጠያይቅም።

ከሁሉም በፊት እኛ ኢትዮጵያውያን እርስ በርሳችን የተሳሰርን፣ እንዳንለያይ ሆነን የተጋመድን፣ ከዚያም በላይ እንዳለፈው ዘመን ሁሉ ቀጣይ ዕጣ ፈንታችንም በጥብቅ የተቆራኘ፣ በአብሮነታችን ድርና ማግ ውብ ሆኖ የተሸመነ ድንቅ ጥበብ በመሆኑ ነው። ተደምረን ለሀገር መቆም ስንችል ብቻ ርእዮተ ዓለማዊ ውይይታችን ፍሬ ሊያፈራ መቻሉን ማመን ይኖርብናል።

በማያጨቃጭቅ መልኩ ርእዮተ ዓለም የነገ አቅጣጫችንን ለመተለም ጠቃሚ አስተዋጽዖ ያደርጋል። መዳረሻችንን በማመላከት ጉዟችንን ከመዳረሻችን አንጻር እያስተካከልን እንድንሄድ አጋዥ መሆኑም አያጠያይቅም። ነገር ግን ሀገራዊ መፍትሔያችን ሀገራዊ መልክና ባሕርይ የራቀው፣ በአየር ላይ የተንሳፈፈ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል። በራሳችን መልክ በራሳችን ልዩ ባሕርይ መሬት መርገጥ ይኖርበታል። እንዲያም ሲባል ዕጣ ፈንታችን በብዙ ውጫዊና ውስጣዊ ኃይሎች እጅ ውስጥ ባለ ሀገር ይቅርና ሉዓላዊነታቸው እጅግ በጠነከረ ኃያላን ሀገራትም እንኳን ዕጣ ፈንታን በአንዲት አቅጣጫ ብቻ ወስኖ መጓዝ የማያዋጣ ከንቱ ሙከራ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ይሆናል። ርእዮተ ዓለም ጥቅል መንገድን ከማመላከት በዘለለ የሰው ልጆች ነባራዊ ሕይወታቸውን እያጤኑ፣ እያስተካከሉና እያረሙ እንዳይሄዱ የሚያደርግ መሰናክል ከሆነ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።

አንድ ሀብታም ሰው በድንገት ዓይኑን ይታመምና ማየት ሲያዳግተው ለመታከም ወደ አንድ የግል ሆስፒታል ያመራል። ከሆስፒታል የሰማው ዜና ግን አስደንጋጭ ነበረ:: ዶክተሮቹ ዐይኑ እንዳበቃለትና ድጋሚ ማየት እንደማይችል ይነግሩታል። ሰውዬውም ሁሉ የሞላለት ሀብታም ስለሆነ በፍጥነት ዐይን ፈልገው የሚተኩለት ከሆነ የሀብቱን ግማሽ እንደሚሰጣቸው ቃል ይገባል። ይሄን ጊዜ ዶክተሮቹ በገንዘቡ ብዛት ልባቸው መማለል ይጀምራል። ችግሩ ግን ዓይን የሚለግስ ሰው ተፈልጎ ታጣ። የዐይን ባንክ ሲሄዱም ምንም የለም።

ዐይን የሚለግስ ሰው በማጣታቸው ዶክተሮቹ በመቆጨት ላይ ሳሉ ድንገት አንዲት ድመት ባጠገባቸው ስታልፍ አንድ ሐሳብ ብልጭ ይልባቸዋል። "ለምን ከድመቷ ላይ ወስደን አንገጥምለትም" ተባባሉ። እንዳሉት የድመቷን ዐይን ነቅለው ለሰውዬው ገጠሙለት። ከቀዶ ጥገናው በኋላ ማየት መቻል አለመቻሉን ለማረጋገጥ

ቸኩለው ከሰውዬው ፊት ላይ ፋሻውን አነሡና ጠየቁት።

“አንተ ሰው እንዴት ነው፣ ማየት ቻልክ?”

“አዎ ማየት ጀምሬያለሁ ሲል ይመልሳል።

በጣም ጥሩ!” አሉ ተደስተው።

“ለመሆኑ ምን ይታይሃል?” በጋራ ዙሪያውን እንደከበቡት።

ሰውዬውም “አይጥ ነዋ ሌላ ምን ይታየኛል?

ብዙ አይጦች በዙሪያዬ  ከበውኛል!” አላቸው ይባላል።

የምናየው  ነገር በመመልከቻችን ይወሰናል።

የርእዕዮተ ዓለም ትክክለኝነት የሚለካው ነባራዊ እውነታን ቁልጭ አድርጎ ሲያሳይ ነው። የሚስፈልገን ኢትዮጵያን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ፣ የራሳችንን ችግር እያየን ራሳችን ምናርመውና  በሂደት የሚጎለብት ርእዮተ ኢትዮጵያ ነው።

# ምዕራፍ ዓሥራ አንድ

## "ኢትዮጵያ"

ከዳንኢዴስ እንስራነት ወደ
ተስፋ አድማስነት !

### "ተስፋ መቀነት ነው መቼም"

**ጸጋዬ ገብረ መድኅን**

ሃምሣ እኅትማማቾች ነበሩ። ካለፍላጎቱ ልጆቹን የዳረው አባትም ሴት ልጆቹ በሰርጋቸው ቀን ባሎቻቸውን ገድለው እንዲያድሩ መከራቸው። አንዷ በስተቀር ሁሉም የአባታቸውን ምክር ፈጸሙ። ባሎቻቸውን ገድለዋቸው አደሩ። ይህ ኃጢአታቸው በአማልክቱ ዘንድ ከሞት በኋላ አስገራሚ ቅጣት እንዲበየንባቸው አድርጓል። ቅጣቱም ወንዝ ወርደው ውኃ በማሰሮ እያመላለሱ ሸንቁር ያለበት ትልቅ እንስራ መሙላት ነው። ሴቶቹ ከቅጣት የሚያርፉት እንስራውን ሲሞሉ ብቻ መሆኑ ተነገራቸው። እንስራው ደግሞ ሸንቁር ነው። በዚህ ሁኔታ ከሥር የሚያፈሰውን ሸንቁር እንስራ ለመሙላት ዘለዓለም ውኃ በማሰሮ ካለ ዕረፍት ያመላልሳሉ።

አንዳንዴ ኢትዮጵያ እንደ ዳናኢዴስ ልጆች እንስራ ትሆንብኛለች። ልጆቿ የማይሞላ ጉድለቷን ለመሙላት መትጋታቸው አልቀረም። ወንዝ ወርደው፣ ዳገት ቁልቁለቱን አቆራርጠው ጉድለቷ ይሞላል በማለት ይባዝናሉ። ነገር ግን 'ሞላች' ሲሉ ታጎድልባቸዋለች፤ ጨበጥናት ሲሉ ታፈተልክባቸዋለች፤ 'አለፈላት' ሲሉ ፤ ታልፍባቸዋለች፤ 'ቀን ወጣላት' ሲሉ ትጨልምባቸዋለች። እንደ ዳናኢዴሶች ሸንቁር እንስራ እንድንሞላ የተረገምን ይመስል ልፋታችን ሁሉ በዜሮ ይባዛል። ሞላናት ያልናት ኢትዮጵያ ተመልሳ ያው ትሆናለች። እኛም በእልህ ውኃ ከማመላለስ ባሻገር እንስራችን ለምን አልሞላችም ብለን አልጠየቅንም።

ብልህነት ስለጎደለን በየጊዜው እሷን ይሞላልናል ያልነውን ውኃ ከማመላለስ በዘለለ ቆም ብለን እንስራችን ስለምን አልሞላችም ብለን አልጠየቅንም። የማትሞላበትን ሸንቁሯን ዐውቆ ሊደፍንላት የሞከረ የለም። በ1960ዎቹ አብዮት አካሂደናል፤ እንስራው ግን ይባስ ጎደለ እንጂ አልሞላም። በ1980ዎቹም ሌላ ለውጥ ሞክረናል፤ አሁንም እንስራው ውኃ እንዳልተጨመረበት ጎዶሎ ነው። የ1997 ምርጫ ደግሞ ይሞላዋል ያልነው ቀርቶ ያለውንም አንጥፍጥፎ እንስራውን ጭራሽ ባዶ አደረገው። ኢትዮጵያን ለመገንባት፣ ይህችን ለዘመናት የጎደለች እንስራችንን ለመሙላት ብዙ ሙከራዎች ተደርገዋል። ያደረግናቸው ሙከራዎቻችን ሁሉ ግን እንደ አፈ ታሪኩ ሸንቁር እንስራ መሙላት ሆኖብናል።

አስተካከልነው ያልነው መልሶ ያው ይሆናል። ገነባነው ብለን የተማመንበት ፈርሶ ይቆየናል። ብዙ ገንብተናል፤ በቀያችን ግን ፍርስራሽ እንጅ ሕንጻ የለም። ሁልጊዜም ተመልሰን ከዜሮ እንጀምራለን። ከ'ሀ' የመጀመር አባዜ ይዞን “T” ላይ ሳንደርስ ዘመንና ትውልድ ተፈራረቀብን። “ሀ” ን ብቻ እንደሚያውቅ ሕፃን ዘላለም “ሀ” እንላለን። ይህ ሁሉንም አፍርሶ እንደ አዲስ የመጀመር ልማዳችን ውጤት ነው።

ሕጋዊነት፣ ሞያተኝነትና ተቋማዊ አሠራር ሥር ይዘው በተቋቋሙባቸው ሀገሮች የፖለቲካ መዋቅሩ፣ ሥርዓቱ፣ ደንቡ፣ መዓርጉና የመሳሰሉት አሠራሮች ቋሚና እንደ መሬት ዘላቂ ናቸው። የባንዲራቸው ዕድሜ በመቶና በሺሕ ለሚቆጠር ዓመታት ሊዘልቅ ይችላል። የሕዝብ መዝሙሩ አያሌ ትውልድ አገልግሎ ገና የልጅ ልጅ ልጆች ሊዘምሩት ይችላሉ። የከተሞች፣ የመንገዶች፣ የትምህርት ቤቶች፣ የሆስፒታሎች ስምና ባለቤትነት በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የጀመረ ሊሆን ይችላል። ባልታሰቡ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሳቢያ የሚለወጡ አንዳንድ ጉዳዮች ሊኖሩ ቢችሉም፣ አብዛኛው ነገር ትውልድን በቋሚነት እንዲያገለግል ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

የቺካጎው የሥነ ማኅበረሰብ (ሶሺዮሎጂ) ሊቅ ባሰፈረው መላ ምት መሠረት፣ ሕዝቦች ሁኔታዎች መገጣጠምን እውነት አድርገው መቀበል ከፈቀዱ በሂደት እውነታ መሆኑ አይቀሬ ነው። ኢትዮጵያ የፈጠርናት

እንጂ ተፈጥራ አልቆየችንም። ማንነትም ይፈራል፤ ስለዚህም ይሰፋል ይጠባል፤ ይጠፋል ይኖራል። የነገር ዳር ድንበሩን በዓለም መጀመሪያ ከምድር ጋር እንደተፈጠረና ለዘለዓለም መነካካት የማይቻል አስርን ከመውሰድ መቆጠብ ይኖርብናል። የታሪክና የተፈጥሮ ግጥምጥሞሽ ያስገኙዋቸውን ነባራዊ ሁኔታዎች በየት መልኩ እውነት ሆነው ቢቃኙ መልካም ይሆናል ብሎ መተርጎም መልካም ነው። በአንድነት እንደ መኖር ሁሉ መለያየትም ስምምነት እንደሚያሻው አይጥፉን።

ከግማሽ ምእተ ዓመታት በላይ  ተገንብቶና ተደራጅቶ የቆየውን የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት፣ ፖሊስና የአየር ኃይል ኢሕአዴግ በአንድ ቀን አፈራርሶ እንደ ቆሻሻ ዕቃ ጥሏቸዋል። ከምኒልክ ዘመን ጀምሮ የተቋቋመው ሠራዊት ‹የደርግ ሠራዊት› ተባለ። ለውጡ ለሀገር ይጥቀም አይጥቀም ማንም አያውቅም። ይህ ሁሉን የመለወጥና በራስ መልክ የመትከል አባዜ ጉዞችንን ቁልቁል እንጂ ሽቅብ እንዲሆን አላደረገም። ለውጣችንን የሚመራው ስሜት ሳይሆን ሳይንሳዊ ጥናትና ፍልስፍና መሆን አለበት።

እኛ ኢትዮጵያውያን ባለፉት ተከታታይ ትውልዶች በቻልነው ዐቅም ሀገራችንን ለመለወጥ ለፍተናል፤ ልፋታችን ግን ሁሌም ከአዲስ ስለሚጀምር እንስራውን አይሞላም። ሀገር በልፋትና በድካም ብቻ አይገነባም፤ ብልኀትም ያስፈልጋል። ዘለዓለም ውኃ በመጎተት ብቻ እንስራዋ አትሞላም፡ ሽንቁሯን ፈልጎ መድፈን ያስፈልጋል። የእንስራችን ሽንቁር፤ የልባችን ሽንቁር ነጸብራቅ ነው። የኢትዮጵያ ሽንቁር በፍቅር አለመደመር ነው። እንደ እሳትማማቾቹ ከመግደል ልማዳችን የሚመነጭ ርግማን ነው። ሽንቁር ልባችንን ለይቅርታና ለፍቅር ካላዘጋጀነው በስተቀር የኢትዮጵያ ሽንቁር አይደፈንም።

እንስራችን ኢትዮጵያ እንድትሞላ ሽንተሯን በፍቅር መድፈን ያስፈልጋል። የመሙላት ተስፋዋ እውን የሚሆነው ሽንቁሯን ስናድስ ብቻ ነው። እንደማትሞላ እያወቅን በተስፋ ቢስነት ዘለዓለም እንደ ባተሌ ሠራተኛ ንብ ውኃ እናመላልሳለን እንጅ ኢትዮጵያ ልትሞላ አትችልም። የሙላቷ ተስፋ የሚወሰደው፤ አዲስ የተሰፋ አድማስ የምትሆነው፣ ጥላቻ የነደለውን ጎኗን ስንጠግንላት ብቻ ነው። ይህ እድሳት ግን ቀላል ሥራ ኣይደለም። እንስራዋን ማደስ የገዛ ልብን ከማደስ ይጀምራልና። የገዛ ልብን ሳያድሱ፣ ነፍስን ከጥላቻ ጉድፍ ሳያጸዱ፣ የተስፋ አድማስን አሻግሮ ማየት አይቻልም። ተስፋን ማየት የሚችሉት ንጹሕ ልቦች ናቸው።

ሀገር ያለልፋት አይገነባም። ልፋት የተስፋ ምልክት ነው። ተስፋ ያላቸው ሰዎች ወደቅን ብለው አይንከባለሉም፤ ቆሸሽን ብለው አይላቁጡም። ሰባት ቢወድቁ ሰባቴ ለመነሣት ይሞክራሉ። መውደቅን አምኖ ተቀብሎ የሚንከባለል ሰው እንዴትም ይንከባለል፣ በጭቃ ከመነከር አይወጣም። የሚለፋ ሰው ግን አንድ ቀን ከጭቃው ይወጣል። ስለዚህ ሀገራችንን የመገንባት ሙከራችን በመሰናክል የማይገታ፣ በወጥመድ የማይማረከ፣ በዕንቅፋት የማይረታ ነው። የኢትዮጵያን የተስፋ አድማስነት የምናረጋግጠው በብርታት በቆሙ እግሮቻችን፣ ብልኀት በሚያስሱ ልቦቻችንና የኢትዮጵያን ታላቅነት በሚያልመው አእምሯችን ነው። ይህ የሁሉም ኢትዮጵያውያን የቤት ሥራ ነው። እንደ ዳናኢዴሶች በብርታት ውኃ እናመላልስ፤ ግን ደግሞ የእንስራችንን ሽንቁር እንድፈን። ሽንቁርን መድፈን ብልኅነት፣ በትጋት ውኃ መቅዳት ደግሞ ታታሪነት ነው። ተስፋችን የሚቀዳውም ከኒህ ከሁለቱ ነው፤ ከብልኅነትና ከታታሪነት።

ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን "አብረን ዝም እንበል" በተሰኘው ግጥሙ ውስጥ፤

"ተስፋ መቀነት ነው መቼም

የሰው ልብ አይችለው የለም-- " ይላል።

መቀነት እናቶች ቀሚሳቸውን አጥብቀው የሚያስሩበት ብቻ ሳይሆን ብሶት ፈተናቸውን ለመቋቋም ወገባቸውን የሚደግፉበት ነው። ተስፋ እንደ መቀነት ፈተናን መቋቋሚያና መሻገሪያ ስንቅ ነው። ተስፋ ካለን ዳገቱን መውጣታችን አይቀርም። ከተራራው ጫፍ ላይ ቆመን ድላችንን ማብሠራችን አይቀርም። ኢትዮጵያውያን እንደ ሲሲፈስ ወደ ተራራ አናት ድንጋይ ሲገፉ መኖር ብቻ ሳይሆን፤ ከተራራው አናት ደርሰን በድንጋይ ቤታችንን መገንባት አለብን። ተስፋ ሲመነምን ምኞትም ድኩም ይሆናል።

ተስፋ ቢስ ሰው ምኞቱ የመንደሩ አለቃ ከመሆን አይዘልም። የመንደሩ አለቃ መሆን ሲያቅተው ደግሞ የቤት ጎረቤቶቹ አለቃ ለመሆን ይመኛል። ምኞቱ እየጠበበ እንጅ እየሰፋ አይመጣም። ተስፋ ስለሌለው ምኞቱን እያጠበበ ይመጣል። ሆኖም ምኞቱን ቢያጠበውም ያ የጠበበው ምኞቱ አይሳካም። ምክንያቱም ጠባቧንም ምኞት ለማሳካት ተስፋ ይፈልጋልና። ተስፋ ያለው ሰው ግን ምኞቱም ያድጋል፤ ምኞቱን የማሳካት ዕድሉም ያድጋል። ተስፋ ችግሮችን ሁሉ የመሻገሪያ ብርታትን ይሰጣል። ተስፋ ውስጥ እጅ መስጠት የለም። "ኢትዮጵያ፡ - አዲሲቷ የተስፋ አድማስ" ስንል የምታድገዋንና ገናና የምትሆነዋን የወደፊቷን ኢትዮጵያ በምናባችን አስቀምጠን ነው።

ኢትዮጵያውያን ተስፋ ቢስነት ተጭኖን፣ ትልቁን ራእይ ዘንግተን፣ በተስፋ ቢስነት በየመንደራችን እንድንጠለል ያደረገን ምንድነው? ሐሞታችንን ያፈሰሰው፣ ወኔያችንን የሰለበው፣ ብርታታችንን የወሰደው ምንድን ይሆን? ጣልያንን አሸንፋለሁ ብሎ በተስፋ ከቤቱ የወጣ ያ የዓድዋ ድል ባለቤት እንዴት ለጥቃቅን ነገሮች ተሸንፎና እጅ ሰጥቶ ምኞትና ሕልሙን በመቀስ ቆራረጠ? ምኞትና ሕልሙን ለማሳካት በትጋት መንቀሳቀሱን ትቶ ምኞቱን መከርከምና ማሳነስ ውስጥ እንዴት ገባ? ኢትዮጵያውያን ትልቅ የምናልምና ሕልማችንን እውን ለማድረግ በብርታት የምንቆም መሆናችንን አስመስክረናል። አሁን ግን ሕልምን በማሳነስ የተስፋ ቢስነታችንን ሕመም ለማስታገሥ እንራወጣለን። ስኬት የሚመጣው ሕልምን በመከርከምና ምኞትን በማሳነስ ሳይሆን ትልቅ ህልም ይዞ በብርታት በመንቀሳቀስ ። ኢትዮጵያ ትላንት በአድዋ ድል የጥቁር ህዝቦች ሁሉ መከታና ኩራት እንደሆነችው ሁሉ ይሄን ስሟን የሚያድስና የሚሰፋ ጉዞ መጀመር አለባት ። ለዚህም ስንቃችንንና ትጥቃችን ተስፋ ነው ። ተስፋ መቀነት ነውና ። ፈተናዎችን ሁሉ ጥርሳችንን ነክሰን ፣ወገባችንን አጥብቀን እንሻገራቸዋለን ።

በተለይም በፖለቲካ ውስጥ ሕዝብ እንመራለን የምንል ሰዎች እንዴት የተሰፋ ቢስ መንገድ እየተከተልን መሪ ለመሆን እንደምንሞክር ይገርመኛል። ተስፋ የሌለው ሰው እንዴት መሪ ሊሆን ይችላል? አንድ መሪ ከሁሉም ነገር በፊት ተስፋ ሊኖረው ይገባል። የመሪነት መነሻና ገፊው ምክንያትም ብዙሃንን ከከበበው የጨለማ ድባብ ባሻገር ብርሃንን ለማማተር ማማተር መቻሉ ነው ። ጨለማውንማ ሁሉም ያየዋል ። መሪ ከጨለማው ባሻገር ያለችውን የብርሃን ጭላጭል ተመለክቶ፣በጭላንጭሏ ተመርቶ፣ተከታዮቹን ከጨለማው ነጻ የሚያወጣ ነው ።

መሪ ከዝናብ መሃል እንደምትወጣ ጸሃይ ለህዝብ ተስፋን ይዞ መምጣት አለበት ።

መሪነት ድሎት ለማግኘት የሚመረጥ ቦታ አይደለም። በመሪነት ውስጥ የሥራ ርካታ ሊኖር ይችላል፤ ምንቾትን ፈልገው የሚገቡበት ሥራ ግን አይደለም። የትግል ቦታ ነው ። ችግሩን፣ፈተናውን፣እንቅፋቱን ተጋፍጦ ማለፍን ይጠይቃል ። በሰው ብቻ ሳይሆን በሌሎች እንስሳትም መሪነት ከፊት የሚመጣውን ተጋፍጦ፣ መሥዋዕት ሆኖ ከተራራው ጀርባ ያለውን ድል ማጣጣም ነው።

ያን መሰል ተጋድሎ ሞቀኝ በረደኝ፣ ጠማኝ አቃጠለኝ ከሚል የእኔነት ውስጣዊ ጩኸት ራስን በማላቀቅ ራስን ለሕዝብ፣ ለሀገርና ለጋራ ጥቅም ማስገዛትና አሳልፎ መስጠትን ይጠይቃሩ። የራስን ማንነትንና ክርሱ የሚመነጨውን ሥጋዊ ፍላጎት ለእምነታችን፣ለተልዕኮና ግባችን በማስገዛት ከርሱ ከፍ ላለውና ለላቀው ተስፋ መኖር ስንጀምር ከፍ ያለ ርካታ ማግኘት እንችላለን ።

ተስፋ የትናንትን ቁምና የዛሬን ብሶት ረስተን ነጋችንን ለማሣመር የምንተጋበት ስሜት ነው። ትናንትን እያስታወሰ የሚቆዝምና ዛሬን እያየ የሚያማርር ብዙ ሰው አለ። አሁን የጠፋው ነገን በተስፋ አሻግሮ እየተመለከተ ነገውን ለመሥራት የሚተጋ ነው። እርግጥ ነው ትናንትም ሆነ ዛሬ ችላ ሊባሉ አይችሉም፤ ነገር ግን ሁለንተናችንን እንዲቆጣጠሩት መፍቀድ የለብንም። ወደ ፊት እየሄዱ የኋላን መቃኘት ማለትና ወደፊት እየሄዱ ፊጽሞ ወደ ኋላ መመልከት ይለያያሉ። አንድ ሰው መኪና ሲነዳ ወደፊት እየሄደ ወደ ኋላ በስፖኪዮ መቃኘት ይችላል። ይህ የሚጠቅመው ለጥንቃቄ ነው። ወደ ፊት እየነዱ ወደ ኋላ ሙሉ ለሙሉ ዞሮ መመልከት ለግጭት ይዳርጋል። እንዲሁ ታሪክ ላይ ሙሉ ዐይናችንን ስናደርግ ዛሬያችንን ልንነጠቅ እንችላለን። ዛሬን እያማረሩና እየወቀሱ መኖርም ትርጉም የለውም። አሻግረን ከጨለማ መውጫ መንገዳችንን ማማተር ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ ተስፋ አስፈላጊ ነው። ሆኖም ተስፋ ብቻውን የሚቆም ባዶ ሕልም እንዳይሆን በብርታታችን ሊታገዝ ይገባዋል።

አንዳንድ ሰዎች ፍቅርና ይቅርታን ብዙ ጊዜ በንግግሮቼ ሳነሣ “ይሄ ነገር አልበዛም እንዴ?” ይሉኛል። ፍቅርን መትከል እንዲህ በአንድ ቀን ንግግር ብቻ የሚቻል ይመስላቸዋል። ለዓመታት ስለጥላቻ ሲወራ በዛ ያላሉ ሰዎች፤ በዚች አጭር ጊዜ ስለ ፍቅር ሲወራ በዛ ይላሉ። ለዓመታት ጥላቻን በየቀኑ ሲጠጣ የኖረ አእምሮ ከጥላቻ ስካር በአንድ ጊዜ ሊላቀቅ አይችልም። ፍቅር ስንዘራ ዝም ብለን ለአንድ ሰሞን የወግ ማድመቂያ አይደለም።

ፍቅርን ስንዘራ እየተከታተልን ውኃ ልናጠጣው፣ አረም ሲወርሰው ልናርመው፣ ተባይ እንዳይበላው መድኃኒት ልንረጨው የግድ ነው። ድግግሞሽ ይፈልጋል። ትጋት ይፈልጋል። በድግግሞሽ ኃይል ጥላቻ እንደበቀለብን ሁሉ፣ በድግግሞሽ ኃይል ነው በጥላቻው ምትክ ፍቅርን ተክለን የምናበቅለው። ድግግሞሽ አዲስ ባሕርይን የመፍጠሪያ ምስጢር ነው። ብዙ ክሂሎቻችን በድግግሞሽ ምክንያት የመጡ ናቸው።

የተከልነው ሥር እየያዘ እንዲሄድ ድግግሞሽ ያስፈልጋል። ጥላቻ ልክ እንደ ባሕር ዛፍ ነው። በዙሪያው ያሉትን የፍቅርና የተስፋ ችግኞች ሁሉ ውኃቸውን ለራሱ ወስዶ ያደርቃቸዋል። ፍቅርን ተክያለሁ ብለህ ከተውከው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጥላቻ አድርቆት ታገኘዋለህ። ፍቅር እስኪያድግና ጥላቻ እስኪደርቅ ተግቶ መሥራት ያስፈልጋል።

የጥላቻን ሥሮች በይቅርታ መበጣጠስና የፍቅርን ሥሮች ደጋግሞ የአብሮነትን ውኃ ማጠጣት የግድ ነው። መደመርን ለማሥረጽ የጥሩ አትክልተኛ ጠባይ ወሳኝ ነው። ገና በአግባቡ ካላደገ ችግኝ ጥላ ሥር ለመተኛት የሚቸኩል አትክልተኛ መሆን የለብንም። ከጥላው ሥር ለማረፍ መጀመሪያ ችግኙ እንዲያድግ በታታሪነት መሥራት ይኖርብናል።

ሀገራችን አሁን አንድ ዓይነት ጠባይ የላትም። በአንድ በኩል ትንፋሽ በሚያሳጣው ፈጣን አዲስ የለውጥ ርምጃ ተደስተውና ብሩህ ተስፋ ተሞልተው ለላቀ ዘላቂ ድል ሌት ተቀን ደፋ ቀና የሚሉ እልፍ አእላፍ ዜጎች አሉ። በዚያው መጠን አዲሱ የለውጥ መንገድ በዕንቅፋት የተሞላ እንዲሆን የሞት ጥላ ይዘው የሚባክኑ አሉ። እዚህና እዚያ የሚጫሩ ጦር አማዛዥ የግጭት እሳቶች፣ መፈናቀሎች፣ ጉስቁልናዎች፣ ቅያሜዎችና የመጠፋፋት ዝንባሌዎች አሉ። እነዚህ ፈተናዎች ጨርሰው ሕዝቡን ፈጽመው ተስፋ ባያስቆርጡትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሰለሉት፣ በተስፋ ሰናቂዎች ምትክ ሟርት ጠሪዎችን አበርክቶብናል። አንድ የሃይማኖት አባት ወይዘሮዋን ‹‹ፈጣሪሽን ትወጂያለሽን?› ሲሉ ይጠይቋታል።

ወይዘሮዋም ሳታቅማማ በሙሉ ልቤ፣ ኃይል እና ሐሳቤ ነዋ» በማለት ትመልሳለች

"ሰይጣንንስ ትጠይዋለሽ?››

"አይ አባቴ፣ ሰይጣን እንኳ ትዝ ብሎኝ አያውቅም፣ ፈጣሪዬን ከምወድበት ጊዜ ተርፎኝ አለማያውቅ ሰይጣንን ለመጥላት ጊዜ አላገኘሁም›› ስትል መለሰችላቸው ይባላል። መውደድ ሸጋ ነው። አፍቃሪ ልብ ለጥላቻ የሚተርፍ ቦታም ሆነ ጊዜ አይኖረውም። ፍትሕን በፍቅር ጭምር እንጂ በሕግ ብቻ አናመጣውም። ሕግ ፍትሕን ያሰፍናል። ፍርድ በተሸናፊው ላይ የሚያመጣውን የሽንፈት ቁስል ግን አያከምም። ቁስሉን የሚያክመው ፍቅር ነው። ፍቅር ደግሞ አሸናፊም ተሸናፊም አይፈጥርም። ያለ ፍቅር እውነት አይሠምርም፣ እኩልነትም ይደነቃቀፋል። ፍትሕን ለማረጋገጥ ሌሎችን እንደ ራሳችን መውደድና ማፍቀር የሚገባን በዚህ የተነሣ ነው። መሪዎች የሚመሩትን ሕዝብ ሲያፈቅሩ የፍቅራቸውን ልክ የሚገልጹበት ዋና መንገድ አለ። እርሱም ዋናው ቀሪ ዘመናቸውን ለራሳቸው ሳይሆን ለሕዝባቸው በመኖር ማሳለፍ ነው። ለሕዝብ ራስን መስጠት ማለት የራሳቸውን ፍላጎት ያዝ አድርገው የሕዝባቸውን ፍላጎት በማስቀደም ነው ።

አንድ ሼህ ለወዳጃቸው፤" ዐይኖቼ በጨለማ ውስጥ እንደ ቀን ማየት ይችላሉ" ብለው ሲናገሩ የሰማ አንድ የሚያውቃቸው አልፎ ሂያጅ ቆም አለና፤

"አጀብ ነው!' ብሎ መደነቁን ከገለጸ በኋላ፣ "ታዲያ ግን ስለምን ማታ ማታ ሲጓዙ ባትሪ ያበራሉ? አልፎ አልፎ ባትሪ ይዘው ሲጓዙ አይቼዎት ዐውቃለሁ// ሲል ዐይን

ዐይናቸውን እያየ ጥያቄውን በአክብሮት አቀረበ።

ሼሁ ሊመልሱ "ትክክል ነው፤ ባትሪ እይዛለሁ። እንደምታውቀው እኔ መሪ ነኝ፤ መሪ ስትሆን ለአንተ ሳይሆን ለሌሎች ነው የምትኖረው። እኔ ባትሪ የምይዘው በጨለማ ወቅት ማየት ስለማልችል ሳይሆን፣ ሌሎች እኔን ማየት እንዲችሉ ነው" አሉት።

# የብልጽግና ተረክ

## ነፃነት ለሕዝባችን፤ ብልጽግና ለሀገራችን

በጥቁር አባያ ቀሚስ ከራስ ፀጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ተሸፍናለች። ለጋ አዳጊ ሕፃን ናት። የተነጠረ ማር የሚመስለው አለንጋ ጣቷን ለምጽዋት ስትዘረጋ _ አንጀት ታላውሳለች። ፀሐይ ማዘቅዘቅ በመጀመሯ ይሁን ወይም ምጽዋት መጠየቁ አድክሟቸው፤ ለይቼ ልረዳው ባልችልም፤ የአዳጊዋ እናት የምትመስል፣ ሙሉ ጥቁር አባያ ቀሚስ የለበሰች ሴት ከትራፊክ መብራቱ አጠገብ አስፓልቱ ጠርዝ ላይ ተቀምጣለች። አብሯት አንድ ድምቡሼ አዳጊ ሕፃን ተቀምጧል። ድምቡሼው ሕፃን እናቱን፣ አልፎ አልፎም ወደ እኅቱ ዐይኖቹን በመላክ ይመለከታል። ሶሪያዊ ስደተኞች ሳይሆኑ አይቀሩም። የመናዊም ሊሆኑ ይችላሉ። ጥልቅ የሐዘን ስሜት ልቤን ከብዶ ተጫነው።

‹‹የጨው ገደል ሲናድ፣ ሞኝ ይስቃል፣ ብልኅ ያለቅሳል›› ይባላል። በእርስ በርስ ጦርነት፣ እነ ሶሪያ፣ እነ ሊቢያ፣ እነ የመን ዐይናችን እያየ ሲፈርሱ እና እንደ ጨው ሲናዱ ማልቀስ ብቻ ሳይሆን፣ ቆም ብሎ ማሰብም፣ ትምህርት መውሰድም ብልኅነት ነው። መነሾው ምንም ይሁን ምን፣ በወንድማማቾች መሐል የሚደረግ ውጊያ፣ ውሎ አድሮ፣ ሀገርን ያፈርሳል። ሚልዮኖችን ስደተኛ፣ ሚልዮኖችን አካል ጉዳተኛ ሊያደርግ ይችላል። አምባ ገነንነትን ለመጣል፣ ወይም ነጻነትን ለማግኘት፣ በጥቂት ሰዎች የተጀመረው ተቃውሞ፣ እንዴት ባለ ፍጥነት አድጎ እና ተባብሶ፣ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሀገርን ወደ መናድ እንደ ደረሰ ስናስብ፣ መውደቂያው ሜዳ መነሻው ቀዳዳ ያሰኛል።

የ15 ሶሪያውያን ወጣቶች መታሰር እና የአንዱ መሞት ያስነሣው ተቃውሞ፣ መጨረሻው የሶሪያ መፍረስ እንደሚሆን ያሰበ ሰው የለም። ግን ሊሆን ይችላል። ሆኖም አይተነዋል። ሶሪያም፣ ሊቢያም፣ የመንም ሕያው ምስክሮቻችን ናቸው።

እኔ ለሀገሬ ሰላም ምን ሠራሁ? ምንስ መሥራት ይኖርብኛል? እኛስ ለሀገራችን ሰላም ምን እየሠራን ነው? ብለን በነጠላም ሆነ በጋራ መጠየቅ ይኖርብናል። መጠየቅ ብቻ አይደለም፤ የዐቅማችንን ያህል ስለ ነገዋ ሀገራችን ሰላም ዛሬ ላይ ጠንክረን መሥራት ይገባናል። አለበለዚያ የሶሪያ፣ የሊቢያና የየመን ዕጣ ፈንታ ሊገጥምን የማይችልበት አንዳችም ምክንያት የለም።

በሀገር ደረጃ የመጣው ለውጥ እንዲጸና አንዱ መንገድ፤ ጠንካራ የፖለቲካ ፓርቲ ሚቋቋም መሆኑ ግልጽ እየሆነ ከመጣ ቆይቷል። እንዲያውም ከቅርብ ወዳጅ፣ ጓዶቼ ጋር በተገናኘን ቁጥር ከለውጡ ጋር በተያያዘ ደጋግመን የምናነሣው አንዱ ጉዳይ የኢሕአዴግን እርጅና ነበር። ኢሕአዴግ አርጅቷል። የማዳን ጊዜውን እንደጨረሰ መድኃኒት እርሱ ራሱ ሕመም ወደ መሆን እየተሸጋገረ ነው። ስለዚህ ፈጥኖ ራሱን መለወጥ ይኖርበታል። ይህ በአመራር ደረጃም ሆነ በአባላትም ሰፊ አጠቃላይ ስምምነት የተደረሰበት ጉዳይ ቢሆንም፤ ተኪው ፓርቲ በምን ርእዮተ ዓለም? የቱን ዓላማና ፕሮግራም አንግቦ? በምን ስያሜ? እንዴት ይመሠረታል? የሚለው ጥያቄ ግን ገና ያልጠራና ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነበር።ሰላምን ማስቀደም ዐበይት አጀንዳ

መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

ኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ያጣችውና የምትመኘውን ያህል ያላገኘችው ሰላምን ነው። ሀገሪቱ ያለ ሰላም እንኳን ዴሞክራሲን ማስፈን፣ በሕይወት መቆየትም ላይሆንላት ይችላል። ኢትዮጵያ ያለ ዲሞክራሲ፣ ያለ ልማት እና ያለ ዘመናዊ ሥልጣኔ መኖር ትችላለች። ይኸው እስከ ዛሬም ኖራለች።

ይህን ያህል የኖረችው ግን፣ በማያባሩ ጦርነቶቿ እና የእርስ በእርስ ግጭቶቿ መሐል በነበሩት ሰላሞቿ የተነሣ ነው፤ ሌላ ምስጢር የለውም። እስከ ዛሬ የነበረው ባህላችን ብቻ ሳይሆን፣ አሁን ያለውም የተፋፈገ የፖለቲካ አየር፣ ሰላም ከምን ጊዜውም በላይ ለኢትዮጵያ የህልውና ጥያቄ እንደሆነ ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ያለፈውም ሆነ የዛሬ ታሪካችንና ባህላችን የሚያስተምሩን ሌላው ቁልፍ ነገር፤ ልዩነቶቻችንን በሰላም የመፍታት ባህል እስካላዳበርን ድረስ፤ የጦርነት እና የግጭት ታሪካችን ማባሪያ ሊኖረው የማይችል መሆኑንም ጭምር ነው።

እንደ አለመታደል ሆኖ ግጭትና ዐመፅ እስከዛሬ የነበረ ያለፈው ረጅም ታሪካችን ብቻ ሳይሆን፣ የሁለተኛ ዓመት ዕድሜውን ሻማ ሊያበራ የተቃረበው የሽግግር ዘመን ታሪካችንም አንዱ መገለጫ ሆኗል። የሚገርመው ነገር በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ የታዩት አስደናቂ ለውጦችም የተወለዱት፤ በግጭቶቹ መሐል በነበሩ የሰላም ፋታዎች ነው:: እነዚህን የሰላም ፋታዎች አስፍቶ፤ የታሪካችን መገለጫዎች ማድረግ፣ ሰላሙን ፡ ወደ ዲሞክራሲ፣ ሰላሙን ወደ ብልጽግና እየለወጡ ወደ ፊት መሻገር፣ ለአንድ ቀን እንኳ ማደር የሌለበት የቤት ሥራችን ሊሆን ይገባል። ሰላም መሠረት ነውና ከአለማደጋችን በበለጠ፤ ሰላም ማጣታችን በብርቱ ሊያሳስበን ይገባል። ዘላቂ እድገትን ከማምጣት፤ ዘላቂ ሰላምን ማምጣት መክበዱ በዚህ የተነሣ ነው። እርግጥ ነው፤ ሌሎቹም ያስፈልጉናል። ዐበይት አጀንዳዎቻችን ናቸው። ሰላም ግን ከሁሉም በላይ የሚያስፈልግ እና በሌሎቹም ሊተካ የማይችል የህልውናችን ምሰሶ ነው።

በሁሉም አቅጣጫ የሰላም ጥያቄ ጎልቶ ይሰማል። ሀገራችን በፓርቲ ፕሮግራም መመራት ከጀመረች ጊዜ አንሥቶ አንድም ጊዜ በሀገር በቀል እሳቤ ላይ የተመሠረተ መፍትሔ ገዢ የሆነበት አጋጣሚ ተፈጥሮ አያውቅም። እስከ አሁን የተቀረጹ መፍትሔያዊ ፕሮግራሞች ሁሉም ለማለት በሚያስደፍር መልኩ የውጭ ቅጅና ካርቦን ኮፒዎች ናቸው።

የሁሉም ፓርቲዎች ርእዮተ ዓለማዊ መሠረት ከአውሮጳ የማርክሲዝም፤ ሊበራሊዝም ወይም ሶሻል ዴሞክራሲ ፅንሰ ሐሳቦችና ሀልዮቶች፤ አለበለዚያም ከቻይና፣ ከሰሜን ኮሪያና ከአልባኒያ ሶሻሊስቶች በቀጥታ የተቀዱ ናቸው። ጥቂት እንኳ ኢትዮጵያዊ መልክና ባሕርይ እንዲንጸባረቅባቸው ጥረት አልተደረገም። ይልቅስ የሀገራችንን ሁኔታ በአውሮፓውያኑ ሀልዮቶችና ፅንሰ ሐሳቦች ልክ ለመስፋት ሲባል በተከተልነው ባዕድና ገታራ አቋም ሳቢያ፤ የተወሳሰቡ ፅንሰ ሐሳቦች፣ ወደ ፖለቲካ ቋንቋችን ገብተው፤ ይኸው ዛሬም ድረስ ሲያነታርኩን ብቻ ሳይሆን ሲያናቁሩን እና ሲያፋጁን ኖረዋል።

አንድ ምሳሌ ልጥቀስ። ምንም እንኳን ሀገራችን የገበሬ ሀገር መሆኗ ግልፅ ቢሆንም፤ የተከተልነው ርእዮተ ዓለም የተነሣ አንድም ካፒታሊስት በሌለበት ሀገር፣ ካፒታሊስትን እንደ ጠላት ፈርጀን ስናወግዝ ኖረናል። በሌላ በኩልም እዚህ ግባ የሚባል የወዝ አደር መደብ ወይም የፋብሪካ ሠራተኛ በሌለበት የገበሬ ሀገር፣

የወዝአድሩን አምባገነንነት ለማረጋገጥ ፓርቲ ከመመሥረት ባሻገር፣ ለወዝ አደር መብት የቆመ አንድ ፓርቲ እንጂ ስለ አያስፈልግም በማለት፣ ዓሥራ ሰባት ዓመት ሙሉ በመኮነን ዘልቀናል። ሦስተኛ ምሳሌ መጥቀስም ይቻላል። በጣት የሚቆጠሩ ከፍተኛ ባለሀብቶችን ይዘን ‹‹ኢኮኖሚውን ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ

እንተውለት ወይስ በቅይጥ ኢኮኖሚ አቅጣጫ እንምራው›› በሚሉ ጉንጭ አልፋ ክርክሮች ጊዜያችንን ገደልን።

ከ1983ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ያለው የኢሕአዴግ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፕሮግራም አግላይ ነበረ። በሚከተለው ስትራቴጂ በፊት ከነበሩት አብዮታዊ ፕሮግራሞች ብዙም የተባለ ነበር ለማለት አያስደፍርም። እሱም እንደ ቀደምቶቹ መደባዊ ፕሮግራም ነበረው። ምንም እንኳ በጠቅላላ ዓመታዊ ምርት መጠን ላይ ከፍተኛ ጭማሪ ማምጣት የቻለ ቢሆንም፤ ድርጅቱ ሲከተለው የነበረው መሥመር የተወሰነውን የኅብረተሰብ ክፍል አግላይ፤ ዜጎችን ባለቤት ወይም ወዳጅ፤ በመሐል ሰፋሪ እና በጠላትነት የሚፈርጅ ነበር። ወዳጅ የተባለው አርሶ አደር ነበር። ከመሐል ሰፋሪነት የተፈረጀው ደግሞ የከተማው ንኡስ ከበርቴና የመንግሥት ሠራተኛው ነበር። ከፍተኛ ባለሀብቱ በኪራይ ሰብሳቢነት፣ ምሁሩ ደግሞ በወላዋይነት ተፈርጇል። በተውሶ ርእዮቶች ተመርተን አርብቶ አደሩን ለሐሳብ ትግል አይጠቅምም ብሎ የሚፈርጅ ሥርዓት ዘርግተን 28 ዓመታትን ተጉዘናል።

መደባዊ ፕሮግራሞች ዞሮ ዞሮ ዜጎችን በጠላትና ወዳጅ መፈረጃቸው አይቀርም። በጠላትነት የተፈረጀው አካል የራሱን ጥቅም ለማስጠበቅ መታገሉ የማይቀር ስለሆነ በመደባዊ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፕሮግራሞች ግጭት የማይቀር ጉዳይ ነው:: በተጨማሪም በመሐል ሰፋሪነትና በጠላትነት የተፈረጀው ኃይል በዋናነት የፖለቲካ ማዕከል በሆኑ ከተሞች የሚገኝና እያደገ የሚሄድ የኅብረተሰብ አካል ስለሆነ ተቃርኖው በዚያው ልክ ከፍ እያለ ይሄዳል። መደባዊ ፕሮግራሞች በባሕርያቸው እኛና እነሱ፣ በወዳጅ ጠላት ፍረጃ አዙሪት ውስጥ የሚሽከረከሩ በመሆኑ፤ ዴሞክራሲያዊ ባሕርይን ሊጎናጸፉ አይችሉም። በስያሜና ከአንገት በላይ በሆነ ስሜት ዴሞክራሲያዊ ነኝ ማለት ብቻ ዴሞክራሲያዊ አያደርግም። በዚህም የተነሣ ፓርቲዎቻችን ለሀገር ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማትን ከማስገኘት ይልቅ ራሳቸው የተቃርኖ ምንጭ በመሆን የከፋ ግጭትና ጥፋት ፈልፋዮች ሆነው ዐረፉ::

ሰላምን ፍቅር እንጂ ጥላቻ ወልዶት አያውቅም። መራራቅ፣መለያየትና መገፋፋት´ የሚፈጥር ርምጃ በሚከተል ርእዮት ዓለም ዘላቂ ሰላምን ማረጋገጥ አይቻልም። በልዩ ልዩ ታሪካዊ መሠረቶች የእኔ ብሔር፣ የእኔ ሃይማኖት፣ የእኔ መደብ፣ ታሪካዊ በደል ተፈጽሞበታልና ታሪካዊ ስሕተቱን ለማረምና ለማስተካከል ተረኛነቱን ልውሰድ ማለት አደገኛ ነው። እንዲህ ያሉ ሐሳቦች በተግባር ተሞክረውም አለመሥራታቸ ተረጋግጧል። ምድሩ ላይ ካለው ወቅታዊ እውነታና ከሰውነት ጋር በተጣላ መንገድ ሰላምን ማረጋገጥ አይቻልም::

እንደ አለመታደል ሆኖ በዘመናዊው የፖለቲካ መሥመር ለሀገራችን መፍትሔ እንዲሰጥ ምርኩዝ ያደረግነው ርእዮተ ዓለም በራሳችን ሀገር በቀል ዕሴት ላይ ተመሥርቶ ሳይሆን አውሮፓዊ መንገድን የተከተለ ነበር። ይኽ ደግሞ ችግራችንን ከመፍታት ይልቅ አዳዲስ ችግሮችን እየፈጠረብን መጣ።

መደመርን ፀንሶ የወለደው ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታ ይህ ነው። ምንድን ነው የሚጎድለን? ከሚል የተነሣ እና ለችግሮቻችን መፍትሔ ለመስጠት የሚተጋ እሳቤ ነው። የይዋጣልን እና የሁከት መንገድ ሳይሆን የይቅርታና ዕርቀ ሰላምን ጎዳና ተከትሎ ብልጽግናን መዳረሻው የሚያደርግ፣ ለሀገር በቀል ችግር የተዘጋጀ ሀገር በቀል መፍትሔ ነው። ኢትዮጵያዊ መልክና ባሕርይ የተላበሰ ዴሞክራሲያዊ ገቢር ተኮርነት (ፕራግማቲዝም) ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ሀገራዊ ትብብርና ውድድሩ ሕዝብን ቀዳሚ ተጠቃሚ የሚያድርግ ውሳኔና በበረከት ተአምራት ሥራ ዙሪያ እንጂ በመርገምት እና ራስ ወዳድነት እሽቅድድም አይደለም።

መደመር ምክንያትና መንገድ ፈልጎ ዐቅምን፣ ዕውቀትን፣ ገበያን ለማስፋት ኀብረተሰብን ለትብብር ይደምራል እንጂ፤ ሰበብና ምክንያት ፈልጎ አይገፋም፤ አይቀንስም። ይደግፋል እንጂ ገፍቶ አይጥልም። መደመር በደልን፣ የተሰበረ ልብን፣ በፍቅር ያክም ይጠግናል እንጂ፤ መልሶ መላልሶ በመቆፈር አያደማም። መደመር ወደ ከፍታ ከሚወስድ ጎዳና ጋር እንጂ፤ ‹‹ከባለህበት እርገጥ›› ጋር አይተዋወቁም። መኪናን ከጎማው አንሥቶ ወደ ላይ ማጠብ፣ ቤታችንን ከምድር ቤት ጀምሮ ወደ ፎቅ ማጽዳት፣ ገንብቶ ማፍረስ፣ ለፍቶ ደክሞ መና መቅረት፣ ታጥቦ ጸድቶ ተመልሶ ጭቃ መሆን! የመደመር እሳቤ መርሕ አይደለም። መደመር ስለትናንት ሲል ነገን በሁከትና ጠብ ሊሞላ የሚፈቅድ ሳይሆን፤ ለነገ ውጤት ሲል የትናንት በደልን በይቅርታ፣ በዕርቀ ሰላምና ፍቅር ማሳለፍን የሚያስቀድም እሳቤ ነው።

አዲሱ ፓርቲ በእርግጥም ሃገር በቀሉ እሳቤ ወይም መደመር ወደ መሬት የሚወርድበት የተግባር ርምጃ ሊሆን ይገባል። መደመር የተግባር ሐሳብ ነው ስንል፣ ወደ ፓርቲ ፕሮግራም፣ ወደ ሥርዓትና ፖሊሲ በመቀየር የሕዝብን ፍላጎት የሚመለስ ነው ማለታችን እንደሆነ ሊሠመርበት ይገባል።

አዲሱ ፓርቲ ከየትኛውም ነገር በፊት ሦስት ታሪክ ለዋጭ ነገሮችን ከግምት ያስገባ ወይም ማስገባት ይኖርበታል። የተለመደውን መንገድ የሚሻገር፣ በተስፋችን ላይ እንጂ በችግራችን ላይ የማይንተራስና አድማሰ ሰፊ የሆነ፣ ታሪክ ለዋጭ ነው ስንል፣ ‹የኢትዮጵያ የብልጽግና ፓርቲ› በፓርቲው መካከለኛ ዓላማና ተግባር፣ በሀገርና በትውልድ ላይ ሊፈጥር ለሚያስበው ለውጥና ልዩ አስተዋጽዖ ላይ የተመሠረተ ስም ነው። ፓርቲው የሚቋቋመውም፣ የሚኖረውም፣ የሚሠራውም ለሀገራችንና ለሕዝባችን ሁለንተናዊ ብልጽግና በመሆኑ፤ አሁን ባሉ ችግሮችና ከቀደመ ታሪካችን ጋር በተያያዘ ገድል ላይ የተንጠለጠለ አይደለም። በሀገሪቱ ላይ አዲስ ገዢ ተርክን በመፍጠር ነገን ባማከለ መልኩ አሸናፊነትን የሚፈጥር ፓርቲ መሆን ይጠበቅበታል። ያለፈውን አኩሪ ታሪካችንና የዛሬውን ልዩ ዕድላችንን እንደሀብት ተጠቅሞ ዓለም አቀፍ ቁመናና የመጪው ዘመን ተወዳዳሪ አፍሪካን የምትመራ በዓለም አቀፉ መድረክ ላይ ተሰሚ የሆነች ኢትዮጵያን መሠረት የሚጥል አድማሰ ሰፊ ፓርቲ ሊሆን ይገባል።

አዲሱ ፓርቲ በስሙም ሆነ በግብሩ ከመነሻ አንሥቶ እስከ መድረሻ ግቡ ድረስ የመደመር እሳቤን የሚያረጋግጥ መሆን ይኖርበታል። በቀደመው ጊዜ አብዮታዊ ዴሞክራሲ እያልን የተውሶ እና ያረጀ፣ የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ባላነበበ መሥመር የአውር ድንብር ጉዞ መከራ ተቀብለናል። አሁን ውግንናችንን ማስተካከል አለብን። የፓርቲያችን የአካሄድ መርሕ መሆን ያለበት፤ የሀገርና ሕዝብ ተጠቃሚነትን ምን ያህል ማረጋገጥ እንችላለን? የሚል ነው። የምናመጣው መፍትሔ ምን ያህል መሬት ላይ ያሉ ችግሮችን መፍታት

ያስችላል የሚል ነው።

በሌላ አነጋገር ገቢራዊነትን (ፕራግማቲዝም) እናስቀድማለን ማለት ነው። በየትኛውም መስቀለኛ መንገድ እና አጣብቂኝ ውስጥ በምንገባበት ሰዓት የምርጫና የውሳኔያችን ውጤት አስቀድሞ ሕዝብና ሀገርን የሚጠቅም ውጤት ያመጣል? ወይስ አያመጣም? ብለን እንጠይቃለን እንጂ፤ የፓርቲውን ጥቅም ያስጠብቃል? ወይስ አያስጠብቅም? የሚል ሙግት ውስጥ አንገባም፤ እንደማለትም ነው። ታላቁ የፍልስፍና መምህር ዊሊያም ጀምስ፣ ገቢር ተኮርነት በርእዮተ ዓለም ታስሮ ከመቀመጥ ይልቅ ወቅቱ የሚጠይቀውን በመረዳት ወደ ድል ደጅ የምንዳረስበት አማራጭ ማለት እንደሆነ ይገልጻል። በዚህ የገቢር ተኮርነት እይታ መሠረት፣ ከቀደምት የሀገራችን ፓርቲዎች፣ አካሄዳችን የሚለይ ይሆናል።

በሀገር ደረጃ ሰብአዊ ክብር፣ ፍትሕና እኩልነት፣ ነፃነትና የሕግ የበላይነት ተረግጠው፤ ጭርሱኑ እንዲጠፉ ሲደረግ ቆይቷል። በሴቶች ላይ የሚደርስ ዘመናትን ያስቆጠረ በደል እና የመብት ጥሰት፣ የወጣቶች ስደት፣ የተደራጀና በሥልጣን ጉያ ውስጥ የመሸገ ሌብነት፣ የመሠረተ ልማት አውታሮች በበቂ አለመዘርጋት፣ የአካባቢ መራቆት እና ሌሎችም ፈተናዎች ቀስፈው ይዘው በሚያንገላቷት ኢትዮጵያ ውስጥ፤ ከሰላም ይልቅ ጦርነት ሠልጥኖ ማየት በእውነት ያሳዝናል።

ንጹሕ የመጠጥ ውኃ ማግኘት፣ መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ተደራሽነት፣ የመጠለያ ቤት መቀለስ ዛሬም ለብዙዎች የቀን ሕልም በሆነባት ሀገራችን ውስጥ አንድ ብርም ቢሆን ለጦርነት ሲወጣ ማየት ኅሊናን ይረብሻል። ይሄን የመቀየር ዕድሉ በእጃችን ነው። በታሪክ ስም፣ በክብር ስም፣ በጥቅም ስም እና በሌላም ስሜታዊ ምክንያቶች፤ የሌለ ሀብታችንን አልባሌ ጉዳዮች ላይ መከስከስ ቀርቶ፤ ሰላምን እና የሀገሩን ሀብት ለባለቤቱ ሕዝብ ለመመለስ፣ መጠለያ እንዲያገኝ፣ ጤናው እንዲጠበቅ እና እንዲበለጽግ ማድረግ ያሻል።

በመሰላልም ሆነ በደረጃ ወደ ላይ መውጫ ምስጢሩ ተመሳሳይ ነው። ወደ ከፍታ የሚያሻግረን ማንቀላፋት ሳይሆን መንቃት፣ መታቀፍ ሳይሆን መልቀቅ ነው፤ አዲስ ዐቅም፣ አዲስ መንገድ መኖሩን መረዳትና ተግባራዊ ማድረግ፤ በትክክልም ራሳችንን ከችግሮቻችን በላይ እንድናቆም፣ አልፈናቸውም ወደ መፍትሔ እንድናመራ ያስችሉናል። ከዚህ አንጻር ሦስት ትላልቅ ወቅታዊ ፈተናዎችንን በመንቀስ የመፍትሔ

እርምጃዎችን ለማመላከት አዲሱ ፓርቲ ትኩረት ሰጥቷል።

ብዙ ዘመን ስለ ድህነት ዘምረናል። በተደጋጋሚ ድህነትን እናጠፋለን ብለን ጮኸናል። በዚህም ምክንያት ድህነት የልቡናችንን ትልቅ ስፍራ ይዞ ቆይቷል። አዲስ የሚቋቋመው ፓርቲ ግን በዚህ ችግር ላይ የሚያጠነጥን ጦር አስመዛዥና አብዮታዊ ትግል ቀስቃሽ ፖለቲካን በመቅበር፣ እንደ ሀገርና እንደ ሕዝብ ልንሆን የምንችለውን የመሆንና የማድረግ ፓርቲ ነው።

ለምን በችግራችን ላይ እንቆዝማለን? ለምን በግባችን ላይ አናተኩርም? ከእኛ የተለየ ሐሳብና ታሪክ ያላቸውን ወገኖቻችን እንደ ጠላት በመፈረጅ የ‹ፀር› ትርክት ያለው ፓርቲ ሳይሆን፤ በአንድነት፣ በፍቅር፣ በእኩልነት ላይ የሚያተኩር ዓላማ መር፣ ችግርን ወደ ዕድል በመቀየር የሚያምን፣ ዕድገትን በቁጥርና በመቶኛ ብቻ ሳይሆን በሰዎች የሕይወት ጥራት ለውጥ የሚለካ ፓርቲ ነው። ድህነትን ለቅቀን ብልጽግናን እናልም። ፈተናን ረግጦ

በማቅናትና በመጓዝ እንጂ፤ ታቅፎ ቆሞ በማንቀላፋት ከድህነት መላቀቅ አይቻልም። በአንድ ሐሳብ ተሸፍኖና ታቅፎ ማንቀላፋት መቸከልን እንጂ መሻገርን አያጎናጽፈም። እንዲያውም የባሰውን ድህነት ተባዝቶ እንዲፈለፈል ያደርጋል።

አዲሱ ፓርቲ በኢትዮጵያ የፓርቲዎች ታሪክ እና ተረክ አዲስ ሐሳብ ብቻ ሳይሆን አዲስ አቀራረብና አዲስ የሰላማዊ ትግል ስትራቴጂ ይዞ መብቀል ይኖርበታል። ለዚህም በሁሉም አቅጣጫ የበለጸገ አስተሳሰብ ይዞ መጥቷል።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ በበርካታ ተቃርኖዎች የተሞላ ነው። ፓርቲዎች ፕሮግራሞቻቸውን ተቃርኖዎችን ሊያሰፋ በሚችል መልኩ ቀርጸዋቸዋል። በዚህም የሀገራችንን ፖለቲካ ወደ ባሰ ዋልታ ረገጥነት እያዘመመ መጓዙ ይስተዋላል። በሌላ አባባል ፓርቲዎች ዋልታ የረገጥነትን ተቋማዊ የማድረግ ሚናቸው ከፍ እያለ መንጸባረቅ ጀምሯል።

በእርግጥ አዲሱ ፓርቲ የዛሬና የብሩህ ነገ ፓርቲ ነው። ፓርቲው ትናንትን ለዛሬና ለነገ ካለው ጥቅም አንጻር ይመለከታል። ታሪክ ዛሬንና ነገን ካላገለገለ ከአካዳሚ አልፎ የፖለቲካ ጉዳይ መሆን አለበት ብሎ አያምንም።

ስለሆነም የሕዝቦችን የጋራ ኅብራዊ ታሪክ፣ የሀገረ መንግሥቱን በጎ በጎውን ታሪክ ወስዶ ለትምህርት ይጠቀማል። በዋናነት ግን ብልጽግና በሁለንተናዊ መልክ የበለጸጉ ዜጎችና የበለጸገች ኢትዮጵያን ነገ እውን ሆና ለማየት ይሠራል። በዚህ ረገድ እንደ አሳዳጊ ወላጅ እናት አዲሱ ፓርቲም በተግዳሮት ውስጥ ማለፉ የማይቀር ነው። ፓርቲው አዲስ ሐሳብ ይዞ ወደ ፖለቲካው ምኅዳር የሚቀላቀል በመሆኑ በርካታ ተግዳሮቶች ሊጋረጡበት መቻላቸው አያጠያይቅም። የሚጠበቅም ነው።

አብዮት ከትርፉ ይልቅ ኪሳራው በእጅጉ ይጎላል። ፈረንሳይ ከሪፎርም እንጂ ከአብዮት አላተረፈችም። ሩሲያም እንዲሁ። ቻይናም ቢሆን ዛሬ የምትገኝበትን ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ያስገኘላት በዴንግ ሻኦ ፒንግ መሪነት ያካሄደችው የሪፎርም ርምጃ እንጂ በረጅሙ ጉዞ የተጠናቀቀው አብዮት እንዳልሆነ በሕይወት ቆመን ያረጋገጡት እውነታ ነው። እርግጥ ነው ሪፎርም ከአብዮት በላይ የሚያደክም ከባድ የዳገት መንገድ ነው። ዘለግ ያለ ጊዜም ሊወስድ ይችላል። ነገር ግን ሐላፊነትና ተጠያቂነትን ያገናዘበ ነፃነትን ለማረጋገጥ አስቀድሞ የዴሞክራሲ ባህልን መገንባት ይኖርበታል። ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ከማረጋገጥ በፊት ሀብት ለመፍጠር መትጋትን ማስቀደም ተገቢ ይሆናል።

የባህልና የቋንቋ ነፃነትን የማረጋገጥ ርምጃ በሕግ የተደገፈ ዐዋጅ ከማውጣት በዘለለ፤ ተጨባጭ ዐቅምን የሚጠይቅ ውዝፍ ሥራ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በመሆኑም አዲሱ ለውጥ የተከተለው አቅጣጫ ሪፎርም እንጂ አብዮትን አይደለም። ሪፎርም በባሕርይው ተቃዋሚና ተቺ የሚበዛው መንገድ መሆኑን እንረዳለን። መረዳታችን ታጋሽ እና ሆደ ሰፊ ቢያደርገንም ከምንጓዝበት ሐዲድ በማውጣት፣ ለውጡን ውጠው፣ ሀገርን ወደ ትርምስ ለመምራት፣ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት፣ የሚመርጡ የታጠቁ ኃይሎችን የምንታገስበት ትከሻ እንደሌለን ሊያውቁ ይገባል። የሕግን የበላይነት የማስከበር መንግሥታዊ ሐላፊነታችንን በሁሉም መንገድ እንወጣለን።

ኢትዮጵያ በያዘችው ፍጥነት ብልጽግናዋን ቀጥላ፤ በ2030 በአፍሪካ ከፍተኛ ኢኮኖሚ ባለቤት ከሆኑ ሀገራት መካከል አንዷ ለመሆን አቅዳ በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች። እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ብቻ ሳይሆን እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይኽ ዕቅድ እንደሚሳካ ሙሉ እምነት አለኝ።

አሁን ከዳር እስከ ዳር ሕዝባችን ለመበልጸግ ትልቅ ፍላጎት ያሳየበት ወቅት ላይ ነው ያለነው። የፖለቲካና የኢኮኖሚ ንቃቱ ከመቼውም ጊዜ በላይ የጨመረበት ጊዜ ነው። የትግራይ ሕዝብ፣ በፖለቲከኞቹ መካከል ያለውን ልዩነት በምክክር አልፎ፣ በጋራ መበልጸግ ስለሚቻልባቸው መንገዶች ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር መክሮ፣ ሀገር ለመለወጥ ቆርጦ ተነሥቷል። የአማራና አፋር ሕዝቦች፣ የኦሮሚያና የሶማሌ፣ የደቡብና የጋምቤላ፣ የሐረርና የቤንሻንጉል ሕዝቦች በጋራ ሆነው፤ ዴሞክራሲ የሰፈነባት፣ ዜጎች በእኩልነት የሚኖሩባት፣ ኅብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ከፍላጎት የዘለለ እንቅስቃሴ ውስጥ ናቸው። ሁሉም ኢትዮጵያዊ፤ በዓለም ፈጣኑ የኢኮኖሚ ግሥጋሤ የሚታይባት ኢትዮጵያን ማለም ብቻ ሳይሆን፤ የዓለም ሀብታሞች መናኸሪያ እንድትሆንላቸው ከፍ ያለ ጉጉት ፈጥረዋል። ይህ ሁሉ የሕዝባችን ዕቅድ እና ምኞት እውን ሊሆን የሚችለው ሰላም እስከ አለ ድረስ ብቻ ነው። ሰላም ከሌለ ምኞታቸው ምኞት ብቻ ሆኖ ይቀራል።

እነዚህንና መሰል በጎ ምኞቶችን ማሳካት ለሀገራችንም ለአፍሪካም ትልቅ የቤት ሥራ ነው። በየትኛውም የዓለም ክፍል ባልታየ ሁኔታ፣ ከአራት ሰዎች አንዱ በሚራብባት አህጉራችን ውስጥ፣ ከሰላም ይልቅ ጦርነትን መምረጥ፣ በእነዚህ ረኃብተኛ ወገኖቻችን _አይወት መጫወት ነው። በዓመት ብቻ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ምስኪኖች በወባና ኤችአይቪ ኤድስ በሚያልቁባት አፍሪካ ውስጥ በጦርነት መነገድ እነዚህን ሕመምተኞች ከመግደል የማይተናነስ ወንጀል ነው።

ሀገር በልጆቿ ትፈርሳለችም፤ ትገነባለችም። እነ ሶሪያ፣ የመን፣ ሊቢያ የፈረሱትና እየፈረሱም ያሉት በፈጣሪ ቁጣና ርግማን ሳይሆን በልጆቻቸው ተግባር ነው። የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ልጆች እያንዳንዳችን የምንመርጠው መንገድ ይለያይ ይሆናል እንጂ፤ መድረሻችን ሁለንተናዊ ብልጽግና ያላት ሀገር ለመገንባት ነው፤ መሆንም አለበት። መቼም ማንም ኢትዮጵያዊ ልጁን ሀገር አልባ የማድረግ ፍላጎት አይኖረውም። ሀገራችንን ወደ ብልጽግና ጎዳና ለመውሰድ ኢሕአዴግ መለወጥ እንዳለበት ከወሰንን ቆይተናል። ዳሩ ግን ለመለወጥ ረጅም ጊዜ ወስዶብናል። ራሱ ያልተለወጠ ለውጥን ሊያመጣ እንደማይችል በመርሕ ደረጃ ሁላችንም ተግባብተን የነበረ ቢሆንም፤ ወሳኙ ጊዜ ሲደርስ ከመካከላችን የእናቴ ቀሚስ አደናቀፈኝ የሚሉ ሰዎች በይፋ መታየት ጀመሩ። መንገዱ አንዴ ተጀምሯል። ለዚያም ነው፤ በመለወጣችን ላይ ቁርጥ አቋም ይዘን የተነሳነው፤ ሀገሪቱ እንድትለወጥ የእውነት ስለምንሻ ነው መሐል መንገድ ላይ ወገቤን ያሉትን የቀድሞ ጓዶቻችንን አምርረን ወደመታገል የገባነው። በዚህም ምክንያት የማታ ማታ መንገዳችን ለየቅል ሆኗል።

የሆነው ሆኖ ኢሕአዴግ ታሪክ ከመሆኑ በፊት በለውጥ ታሪክ መሥራቱ ምንም ጥርጥር የለውም። ብልጽግና እንዲወለድ ቀናውን መንገድ በመከተሉ ለሀገራችን የለውጥ ጉዞ የተጫወተው ሚና ጥፋት ሳይሆን ልማት መሆኑን አረጋግጧል።

መድረሻውን ብልጽግና፣ መንገዱን መደመር ያደረገው ፓርቲያችን ‹‹ብልጽግና ሁሉንም የሀገራችን ዜጎች

ሊያካትት የሚችል የነገ ፓርቲ ሆኗል። እኛም ጊዜያችን ደርሶ፣ የተወሰነ ምዕራፍ ተጉዘን፤ ሰላምን ለሀገራችን፣ ብልጽግናን ለሕዝባችን ለማስገኘት የበኩላችንን ካደረግን በኋላ የተሻለ መንገድ ይዘው ለሚመጡት ለነገዎቹ በክብር እናሻግራለን። ምክንያቱም ብልጽግና ያለ ትውልድ ቅብብሎሽ እንደማይሳካ ጠንቅቀን እናውቃለን። ቸር ያድርሰን!!

**"የኮሮና ፈተና" በመደመር ጎዳና**

**መዳፌ**

የአምስት ጣቶቼ ሥር፣

ሰው የመሆኔ ምስጢር፤

አወይ ይህ መዳፌ - ተጭኖ በአፌ፣

በዘመን ብያኔ - ከማንነት ርቆ፣

በአርምሞ መቀመጥ - ተጠቦ ተጨንቆ ፤

መኖር እዚያና እዚህ - ይመስል ያልበቃው፣

የሌላ መዳፍ ራብ - ናፍቆት እያጠቃው፤

በመታጠብ ሰበብ - ራሱን ይጨብጣል፣

አለመማር ለካ - ከመማር ይከብዳል።

**የዘመን ቅኔ**

የሰው ልጅ ለዓለም

መዳፉ ወጌሻ፣ አንደበቱ ሐኪም፤

የወንድሙን ቁስል፣ ቀርቦ የሚዳብስ

ሲወድቅ የሚያነሣ፣ ለተራበ 'ሚያጎርስ፤

የወገኑ ጧሪ፣

የሞተን ቀባሪ፤

ለሰው መዳኒቱ፣ ሰው እንዳልነበረ

ሁሉንም በሩቁ፣ ዘመን ተቀየረ

ወራሪ ሲመጣ፣ መሸሸ ተጀመረ፤

ሰው መቅረብ አስፈራው፣ የማይሆነው ሆነ

ጠላቱን ሊያሸንፍ በሩቅ ተወሰነ።

የሰው ልጆች ሕይወት ቅጽበታዊ፣ በፈተና የተከበበ የሰልፍ ሜዳና የውጊያ ዐውድ ትንቅንቅ ነው። የሰው ሕይወት ራሱ በሚፈጥራቸው ግጭቶችና ከተፈጥሮ በሚመጡ ጦርነቶች የተሞላ ነው። ታሪክ መመዝገብ ከተጀመረበት ጊዜያት ቀድሞም ቢሆን የሰው ልጅ በብዙ ሰልፎች ውስጥ አልፏል። አጭር ምድራዊ ሕይወቱ በበሽታ፣ በጦርነት፣ በሽብርና በተፈጥሮ አደጋ የተሞላ ነው። በየትኛውም ዘመንና የዓለም ክፍል የተከሠቱ ወረርሽኞችን ታሪክ በጥሞና ስንቃኝ፣ ማለፍ ከማንችለው አንድ እውነታ ጋር ፊት ለፊት መፋጠጣችን አይቀርም። ይኸውም የመቅሰፍቱ ሰለባ የሚሆኑትና በዋናነት የሚጠቁት የኅብረተሰብ ክፍሎች በአመዛኙ የኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ ድኻ ወገኖች ናቸው። በሀገራትም ደረጃ ከአየነው ያልበለጸጉት አዳጊ ሀገራት የፍዳው ዋነኛ ገፈት ቀማሽ ሆነው እናገኛቸዋለን።

እንደምሳሌ ከቅርብ ዘመናት ትዝታቸን ውስጥ እንደ ኤች ኣይ ቪ ኤድስና ኢቦላ ያሉ አሰቃቂ ወረረሰኞችን ማንሣት ይቻላል። የዓለምን ገጽታና የሰው ልጆችን የአኗኗር ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ለውጠው ያለፉ እንደ ተስቦ፣ ኮሌራ፣ ወባ፣ ፈንጣጣና ኢንፍሉዌንዛ ያሉ ታላላቅ ወረርሽኞችም ቢሆኑ ከዚህ የተለየ ታሪክ የላቸውም። አንድ ወረርሽኝ ተጋግሎ የዜጎችን ሕይወት እንደቅጠል ካረገፈ በኋላ የሚፈጠረው ድንጋጤ ወዲያው ተዘንግቶ ትኩረት የሚያጣበት መሠረታዊ ምክንያት ከዚህ እውነታ ጋር የሚተሳሰርበት ፖለቲካዊ ክር ጠንካራ ነው።

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሁኔታ ግን የተለየ ይመሰላል። እስከ አሁን ባለው ሁኔታ የወረርሽኙ ወረራና ጥፋት እየተስፋፋ ያለው በበለጸጉት ሀገራት ዘንድ ነው። በበሽታው በመያዝም ሆነ ዜጎችን በሞት በመቀማት ረገድ የፊት ረድፍ ተሰላፊዎች የበለጸጉት ሀገራት ሆነዋል። ለምሳሌ በታላቋ ብሪታንያ ብቻ ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የጤና ሚኒስትሩና ልዑል ቻርልስ የዚህ አደጋ ሰለባ መሆናቸው አስደንጋጭ ዜና ነው። የካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትርና የስፔን ንጉሣዊ ቤተሰቦችም ከቫይረሱ መዳፍ አላመለጡም። የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕም የለም ባሉት ኮሮና ተይዘዋል። እንዲሁም በዓለማችን ላይ ዕውቅ የሆኑ የስፖርትና የጥበብ ከዋክብትና ባለጠጎችንም ጭምር ወረርሽኙ ጎብኝቷቸዋል። ምናልባትም ዓለማችን ካየቻቸውና በአስከፊነታቸው በታሪክ መዝገብ ላይ ካሰፈረቻቸው ገዳይ ወረርሾች ከእነ ስፓኒሽ ፍሉ (የኅዳር በሽ)) እና ከ ‹ጥቁር ሞት (black death)› ተርታ ሊሰለፍ እንደሚችል የመጀመሪያ ጥቂት ወራት ሰለባዎቹ ጠቋሚዎች ናቸው።

በዚሁ ሁኔታ ከቀጠለ በድኻ ሀገራት ላይ የሚኖረው የኢኮኖሚ ፈተና ከጤና ቀውሱ ቢብስ እንጂ አያንስም። ቀድሞ ነገር አሜሪካ ስታስነጥስ ዓለም ሁሉ ክፉኛ እንደሚያስለው ሁሉ፤ በድኅረ ኮቪድ-19 ማኅበረ ኢኮኖሚዊና ፖለቲካዊ ጫናው በተለይ በአዳጊ ሀገራት ላይ ሊከፋ እንደሚችል መገመት የሚያስቸግር አይደለም።

ቫይረሱ መላው ዓለምን ለማዳረስ፣ እያንዳንዱን ጓዳና ጎድጓዳውን ሊነካ አፍላ ግሥጋሤ ላይ እያለ ገና

የፖለቲካ አየሩን መነካካት ጀምሯል። መንግሥታት ሲንገዳገዱ፣ መሪዎች ሲጨነቁና የሚያደርጉት ሲጠፋቸው፣ ድሮ ድሮ አደጋን ለመከላከል ይመኩባቸው የነበሩት ተቋማት ጨርሰው እንደማያድኗቸው አስበው ዐይናቸውን ወደ ፈጣሪ ሲወረውሩ ተመልክተናል። የፖለቲካ ፓርቲዎች እርስ በእርስ መካሰስ አልተቆጠቡም። ፖለቲከኞች የተፈጠረው የጤና ቀውስ ለሌላ ጉዳይ ፋታ ስለማይሰጥ፣ የታቀዱ ምርጫዎች ለወደፊት እንዲተላለፉ ወስነዋል።

በሽታውን ፈርቶ ለአንድ ሰሞን በየቤቱ ሲከተት የነበረው ሕዝብ በአንድ በኩላ ከበሽታው ባልተናነሰ ሥራ ማጣቱ የሆድ ርኃቡን ቀስቅሶበት ግር ብሎ ወደ አደባባይ እንዲወጣ ተገዷል። በዚህም ጥቂት የማይባሉ ዜጎች አስገዳጅ የቤት ውስጥ ቆይታ ዐዋጆችን በመተላለፋቸው በጸጥታ ኃይሎች ርምጃ እስከ መቁሰል፣ መታሰርና ሕይወታቸውን እስከ ማጣት ደርሰዋል። ለመንግሥታትም በአንድ በኩል ለወረርሽኝ መስፋፋት ዕድል የሚፈጥሩ ወሳኒ ቤቶችን ባዶ ለማድረግ ታራሚዎችን በይቅርታ ሲለቅቁ በሌላ በኩል ርኃብ ገፍትሮት ከቤቱ የወጣውን ሰው በማሰር የሁለት አጣብቂኞች ሥቃይ ሰለባ ሆነዋል።

ቫይረሱ ዲፕሎማሲውን በማመስ፣ በሀገራት ግንኙነት ላይ ብርቱ ተጽዕኖውን ከማሳረፍ አልተመለሰም። ቫይረሱን በመፍጠርና በማስፋፋት አንዱ ሀገር ሌላውን ይወነጅላል።

የአሜሪካ መሪዎች በተደጋጋሚ ቫይረሱን የቻይና ቫይረስ' ወይም ሁዋን ቫይረስ' ብለው በአደባባይ እስከመጥራት ሲደርሱ፤ ቻይናም በበኩሏ ቫይረሱ የአሜሪካ ወታደሮች ወደ ሀገሯ ሳያስገቡት እንዳልቀሩ እየጠቀሰች አሜሪካን ከመኮነን አልተመለሰችም። የቫይረሱ ምንጭ ናት በሚል ቻይና ካሳ እንድትከፍላቸው እስከ መጠየቅ የደረሱ ሀገራትም አሉ።የዚህ ውዝግብ አካል የሆነችው ኢራን በቫይረሱ ሥርጭት የመጀመሪያ ሰሞን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎቿ መጠቃታቸውን ስታይ ታሪካዊ ጠላቶቼ በምትላቸው ቫይረሱ ሆን ተብሎ እሷን ለማጥፋት እንደተሠራጨ በአደባባይ እስከመናገር ደርሳ ነበር። የበሽታውን መዛመት ለመግታት በሚል ሀገራት ጉዞ ለማገድና ድንበራቸውን ለመዝጋት ሲያመነቱ በቆዩበት ወቅት፤ ሀገረ አሜሪካ ከማንም አብልጣ የምታቀርባቸው ወዳጆቿን እንግሊዝን ጨምሮ በድፍን አውሮጳውያን ላይ የጉዞ እግድ የጣለች ሰሞን፤ ከፍተኛ ወቀሳ ሲሰነዘርባት ቆይቷል። ወረርሽኙ ውዝግብ ከአስከተለባቸው አካላት መካከል ሌላኛው የዓለም የጤና ድርጅት ነው።

እርግጥ  ነው ዓለም አቀፋዊ ጤና ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ ትልቅ ሐላፊነት የተጣለበትና ሰፊ ትኩረት የሚያገኝ ተቋም እንደመሆኑ መጠን፤ አንዳንድ ውዝግቦች ሊገጥሙት እንደሚችሉ መገመት አይከብድ ይሆናል። ዳሩ ግን ብዙዎች ሊያዳላላቸው ይችላል ብለው ከሚገምቱት ከምዕራባውያን ዘንድ ኩነኔ ሲወርድበት ታዝበናል። ምዕራባውያን በተለይም አሜሪካ፤ ድርጅቱ በቻይና መዳፍ ውስጥ ወድቋል፤ በሚል ሰበብ ወረርሽኙ የዓለም ሥጋት መሆኑን ይፋ ለማድረግ ዘግይቷል ብላ ስትከስ ተደምጧል። በዚህም የተነሣ ዳይሬክተር ጀኔራሉ ሥልጣናቸውን እንዲለቅቁ ከምዕራባያውያን ግፊት ሲደረግ ነበር። ይህ ሁሉ ውዝግብ በድኅረ ኮሮና ወራት፣ በዓለማችን የሚከሠቱ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች ቀላል እንደማይሆኑ ጠቋሚ ነው።

እስከ ዛሬ ድረስ በወረርሽኞች ሳቢያ ዓለማችን የከፈለችውን ከፍተኛ የሕይወት ግብር ማሰብ ያሳምማል። የጄስቲያን ወረርሽኝ በመባል የሚታወቀውና በ6ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ ተከሥቶ የነበረው በሽታ፤ በወቅቱ ከነበረው ጠቅላላው የዓለም ሕዝብ መካከል ከግማሽ የሚልቀውን ሕዝብ ሳይቀጥፍ እንዳልቀረ ይገመታል። በ14 ኛው ክፍለ ዘመን የተከሠተው 'ጥቁር ሞት' በመባል የሚታወቀው ገዳይ ወረርሽኝ፤ ‹ከ75 -125 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎችን ፈጅቷል› ተብሎ ይገመታል። ምንም እንኳን በመጨረሻ ውጤታማ ክትባት ቢፈጠርለትም ፈንጣጣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ብቻ ወደ 300 ሚሊዮን ያህል ሰዎችን እንደቀጠፈ ይገመታል።

የዛሬ መቶ ዓመት አካባቢ 'ስፓኒሽ ፍሉ' ወይም በእኛ ሀገር 'የኅዳር በሽታ' በሚል የሚታወቀው የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ፤ በዓለም ዙሪያ ከ50 እስከ 100 ሚሊዮን ያህል ሰዎችን እንደ ቅጠል አርግፏል። ይህም በክፍለ ዘመኑ የተካሄዱ ጦርነቶች ሁሉ ከጨረሱት ሰዎች ቁጥር ሳይቀር በእጅጉ ይልቃል። የቅርብ ጊዜ ትዝታችን በሆነው ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ እንኳን ከ75 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ተጠቂ እንደሆኑ የሚገለጽ ሲሆን፤ ግማሽ የሚጠጉት በዚያው ሰበብ ሕይወታቸውን እንዳጡ ተያይዞ ይነገራል።

እስከ አሁን ድረስ መድኃኒትም ሆነ ክትባት ያልተገኘለት የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በሀገራችን፣ በአህጉራችንና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ ምን ሊሆን ይችላል? የሚለው ጥያቄ የሁሉንም መሪ ልቦና ቀስፎ የያዘ ጉዳይ ነው:: ዓለማችን ባላት የቅርብ ትስስር ምክንያት ኮቪድ 19 ከዚህ በፊት ከነበሩ መሰል ቫይረሶች በተለየ ሁኔታ በፍጥነት በመላ ዓለም ተዛምቷል። 'ስፓኒሽ ፍሉ / የኅዳር በሽታ' እንኳን በዘመኑ በሀገራችን ወደ ብዙ አካባቢዎች ለመስፋፋት በርካታ ጊዜያትን የወሰደ ሲሆን፤ ኮሮና ቫይረስ ግን በሦስት ወራት ዕድሜ ውስጥ መላ ዓለምን አዳርሷል። ይህ የሰውን ዘር ህልውና እየተፈታተነ ያለ ወረርሽኝ ለጊዜው በሕክምና ሳይንሱ መፍትሔ የለሽ ብቻ ሳይሆን አስከትሎት የሚያልፈውን ጦስና ዓለም አቀፋዊ ጫና ለመገመትም አዳጋች ነው። አሁን ከህልውና በመለስ ባሉ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ተጠምደን፣ የወረርሽኙ መዛመት እንዲባባስ በምንም መንገድ መፍቀድ አይገባንም።

ለጊዜው የዚህ ቀውስ ቀዳሚ መፍትሔ ሊሆንና ከእያንዳንዳችን የሚጠበቀው ችግሩ ጊዜያዊና አላፊ መሆኑን በመገንዘብ፣ ነገሩን በእርጋታና በሰከነ ልብ ማየት የሚችል አስተዋይ መሪ ሆኖ መገኘት ነው።

በእንደዚህ ዓይነት ወቅት ሀገርን መምራት፣ ሀገርን በጦርነት ጊዜ ከመምራት በላይ ትዕግሥትንና አርቆ ማሰብን ይጠይቃል። አርቆ ማሰቡ ፊት ለፊት መንበረ ሥልጣኑ ላይ ከተቀመጡት ብቻ ሳይሆን፤ በአንድም በሌላ መንገድ ሕዝብን ከሚመሩ አካላትም የሚጠበቅ ነው። የሐሳብ መሪዎችም ሆኑ የፖለቲካ መሪዎች ቅንጅት ያለውና የተናበበ አካሄድ ተከትለው ወደፊት መራመድ ይገባቸዋል፡፡

ሀገርንና ሕዝብን ያለብዙ ጥፋት ወደ ፊት የሚያሻግረው መካሰስና ጣት መጠቋቆም ሳይሆን፤ ለሕዝብና ለሀገር ሲሉ መደጋገፍና መተባበር ብቻ ነው። መጨረሻ ከሌለው ችግር ተንታኝነት ወጥተን፣ እንደ መሪዎች መፍትሔውን ማሰብና ነገን አሻግሮ ለማየት መቻል ይጠበቅብናል። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ፖለቲካውንና ሀገርን ማረጋጋት ያስፈልጋል። ጽንፍ ይዞ መታኮስና ጎራ ከፍሎ መናቆር የቫይረሱን ሥርጭት እንጂ ማንንም

አይጠቅምም። በዚህ ሰዓት ሀገርን እንደ አንድ ቤተሰብ አይቶ በማቀራረብ በአንድነት መምራት ይገባል።

ይህ ቫይረስ በተከሠተበት በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን በከፍተኛ የለውጥ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። በታሪካችን ከገጠሙን የለውጥ አጋጣሚዎችና ለውጥን እየመራን ካለንበት ሁኔታ አንጻር ሲታይ፤ በእርግጥም ይህ ለሀገራችን ወደ ፊት ለመወንጨፍና ወደ ላይ ለመስፈንጠር ልዩ ዕድል ያገኘችበት ወቅት ነው። ነገር ግን የለውጥ ታሪኮቻችን በፈተና የተሞሉና አስፈሪ የመሆናቸውን ያህል፤ ታሪክን ለመቀየር ከፍተኛ ሥራ ላይ በተጠመድንበት ወቅት ያጋጠመን ፈተና መሆኑ ይህንን ወረርሽኝ የከበደ አድርጎታል።

በኢትዮጵያ የፖለቲካው ጉዞ ውስጥ የመሪዎች አላስፈላጊ ነጥብ መጣል የኢትዮጵያን የፖለቲካ ምኅዳርና ሕዝብን ዋጋ ሲያስከፍል ኖሯል። ይህም ከነገሥታቱ ዘመን ጀምሮ በተሞከሩ መፈንቅለ መንግሥቶች፣ በደረሱ ረኃቦችና ቀውሶች፣ ለእነዚህ ፈተናዎችም በተሰጡ ምላሾች ሳቢያ በሕዝብና በመንግሥት፣ በመሪና በተፎካካሪ መሐል ጠባሳ እየጣለ አልፏል። በአለፉት ሁለት ዓመታትም የዴሞክራሲን መሠረት ጣልን እንጂ የቤቱን ግርግዳና ጣራ ገና አላጠናቀቅንም። እንግዲህ በዚህ ጅማሮ ምዕራፍ እየተጋን ባለንበት ሁኔታ የቫይረሱ መከሠት ፖለቲካዊ ጫናውን ከፍ ያለ ያደርገዋል።

ሌላው ተጨማሪ ጉዳይ ሀገራችን ይህንን ታሪካዊ የለውጥ አጋጣሚ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ እልባት ለመስጠት በዝግጅት ላይ ባለችበት ሁኔታ ወረርሽኙ መምጣቱ ነው። በእርግጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ ካለው ነባራዊ ሁኔታና ዝግጅት አንጻር፤ ሕዝባችን እየተካሄደ ላለው ለውጥ ባለው ድጋፍ፣ ምርጫው ቢካሄድ፤ የብልጽግና ፓርቲ በውድድር አሸንፎ በሥልጣን ለመቀጠል ከየትኛውም ሀገራዊ ፓርቲ በላይ የተሻለ ዕድል ያለው መሆኑን በሚገባ ያውቃል። ስለሆነም የምርጫውን መራዛም ከየትኛውም ፓርቲ በላይ ብልጽግና የማይፈልገው ጉዳይ ነው። ፓርቲያችን ከዚህ በላይ የሚያሠጋው ነገር ቢኖር፤ የጀመርነው ሰላማዊ የዴሞክራሲያ ሂደት በቫይረሱ ምክንያት መጓተቱና፣ ያለችን ጥቂት ጥሪትና ዐቅም ቀውሱን ለማርገብና ጥፋትን ለመቀነስ በመዋሏ፣ የተፈጠረውን ጉጉትና ግለት እንዳይገታው ነው። የሆነው ቢሆን የተጀመረው ለውጥ ከመሥመር ሳይወጣ ወደ ግቡ እንዲደርስ ቀን ከሌት በመሥራት፣ ከወረርሽኙ ባሻገር መልካም ፍጻሜ እንደምንፈጥር ጠንካራ ተስፋ አለኝ።

ቫይረሱ በቻይና ተከሥቶ በዓለም ዙሪያ ዳር እስከ ዳር በፍጥነት በመሠራጨት፣ ይህን ጽሑፍ እስከጻፍኩበት ሰዓት ድረስ ብቻ፤ ከሰላሳ ሚሊየን በላይ ሰዎች በቫይረሱ መያዛቸው ተረጋግጧል። ከሁለት መቶ ወደሚበልጡ ሀገሮች በመዳረስ ወደ ሚልየን የሚጠጉ ሰዎችን ሕይወት ቀጥፏል። አደጋው በእነዚህ ቁጥሮች እንደማያበቃ ማንም ያውቃል። ተውሳኩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን በመያዝ ቀላል ቁጥር የሌላቸውን ሰዎች ሊገድል እንደሚችል የማኅበረሰብ ጤና ሳይንቲስቶች ሲወተውቱ ቆይተዋል። የዓለም ጤና ድርጅትም ወረርሽኙን አስቸኳይ የጤና አደጋ በማለት ሀገራት ተባብረውና ታጥቀው እንዲፋለሙ ጩኸቱን ማሰማት ከጀመረ ውሎ አድሯል። የብዙ ሀገሮች የጤና አገልግሎትና የሕክምና መስጫ ተቋማት በወረርሽኙ ተጥለቅልቀው የእርዳታ ያለህ እያሉ ነው። የችግሩ አስቸኳይነትና አደገኛነቱ ለማንም ግልጽ ነው።

ገና በወረርሽኙ ጅማሬ ላይ ዓለማችን በትሪልዮን ዶላሮች የሚቆጠር ሀብቷን አጥታለች። የንግድ ዘርፉ

የተዳፈነ እሳት ሆኗል። ከተሞች በየሀገሩ እንደ ወኅኒ ቤት ተከርችመው እየታጠሩ ነው፤ ድንበሮችም እንደዚሁ። ዓለም አቀፍ ጉዞዎች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ከቆሙ ሰነበቱ። ብዙ ሀገሮች ለአስቸኳይ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ማንም ከቤቱ እንዳይወጣ አግደዋል። በመቶ ሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች ኑሯቸውን ቤታቸው ውስጥ ካደረጉ ሳምንታት እየተቆጠሩ ነው። እጅግ በለጸጉ በሚባሉ አንዳንድ ሀገሮችም በአንድ ቀን ብቻ በሺሕ የሚቆጠሩ ዜጎቻቸው ሞተውባቸው ያድራሉ። የዚህን ሁሉ ሕዝብ ሕመም መርምሮ በማከም፣ ታማሚዎችን ሲከባከቡና ሲያጽናኑ ውለው የሚያድሩ፣ በዕውቀትና በልምድ የተካኑ ሐኪሞችም በቫይረሱ ተይዘው በበሽታው እየወደቁ ነው። በአንዳንድ ሀገሮች ከአጠቃላይ ሟቾች ውስጥ ቀላል የማይባሉ የሕክምና ባለሞያዎች ይገኙበታል።

የኮሮና ቫይረስ በሽታ ካደረሰብንና እያደረሰብንም ካሉት ጉዳቶች አንዱ ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ነው። በበሽታው ሥርጭት የተነሣም ንግዱና ኢንዱስትሪው በመቀዛቀዙ የሸቀጣ ሸቀጦች ዝውውርም ተገቷል። ኢንቨስትመንቱና የቱሪስቶች ጉብኝት ሙሉ በሙሉ ስለቆመ፤ ኢኮኖሚዎች ማደንዘዣ እንደተወጋ ሕመምተኛ ሰመመን ውስጥ ገብተዋል። በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሥራ አጥ እየሆኑ ነው።ሥራ ሲቆም ገቢም ስለሚቆም፣ ለረጅም ጊዜ ራሳቸውን ችለው መኖር የተሳናቸው ሰዎች ሲበዙ የሚፈጠረውን ቀውስ ለመገመት ይከብዳል።

የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል፤ እንዲሉ የወረርሽኙ ኢኮኖሚያዊ ጫና ከባዱ ፈተና ሆኖ ይቀጥላል። በዚህም ምክንያት ዓለም ቢያንስ በአራት የወደፊት የኢኮኖሚ ገጽታ አማራጮች ውስጥ ልትገባ ትችላለች ተብሎ ይጠበቃል። አንደኛው በበዛ ስግብግብነት ኢኮኖሚያዊ ሥርዓቱ ዐይን ወደ አወጣ ዘራፊነት ሊለወጥ ይችላል። ሌላው ጠንካራ የመንግሥት ካፒታሊዝም ሊሰፍን የሚችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። ሦስተኛው ጭራሽ ከዚህ በተቃራኒ አክራሪነት የተላበሰ፣ አምባገነን የሆነ ሶሻሊስታዊ ሥርዓትም ሊበቅል ይችላል። የመጨረሻው ደግሞ በአርቆ አስተዋይነትና ነባራዊ ሁኔታን በአግባቡ ከመረዳት፣ የኢኮኖሚ ገጽታው በመደመር እሳቤ የተቃኘ ጤናማ ፉክክርን ከገንቢ ትብብር ጋር አጣጥሞ የቆመ፣ ዴሞክራሲንና ልማትን ያማከለ ካፒታሊዝም ሊገነባ ይችላል። እነዚህ አማራጮች ቀጣይ የወደፊት ዕጣ ፈንታዎች የመሆን ዕድላቸው እኩል ባይሆንም፤ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ወረርሽኙን ለመከላከል ተግባራዊ የምናደርጋቸውን ርምጃዎች ግን ይህን ታሳቢ በማድረግ መተንተን ግዴታ ነው።

እንደ መንግሥት ከቢሆን አጋጣሚዎች በመነሣት አሁን ካለው በከፋ ደረጃ ወረርሽኙ ጫና ቢያሳድር፣ ከቀውሱ ለመውጣትና በየደረጃው ኢኮኖሚው እንዲያገግም ልንወስዳቸው የሚገቡ ርምጃዎችን በዝርዝር ለይተናል። ሁኔታው አሁን ባለው ሁኔታ ከቀጠለ ነጻ የገበያ ኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት የሚከተሉ ሀገራት ክፉኛ ሊጎዱ ይችላሉ። ነገሮች በዚሁ ከቀጠሉ የግራ አክራሪነት መልሶ የመስፋፋት ዕድሉ ሰፊ ነው። በእኛ በኩል አስቀድመን እንዳልነውና በስትራቴጂያችን እንዳስቀመጥነው፤ ዓለማችን እያላት እንደሌላት እንድትሆን እያደረጋት ያለው ዋልታ ረገጥነት ነው። ስለሆነም የድኅረ ኮሮና የፖለቲካ ኢኮኖሚ ፖሊሲያችን በመደመር እሳቤ ላይ የተመሠረተውን ሚዛናዊ የመንግሥት ሚና በወሳኝነት ተግባራዊ ያደርጋል። ያ ማለት ማንኛውም መንግሥታዊ ድጋፍ ሚዛን ጠብቆ መተግበር ይኖርበታል። በሁሉም የወረርሽኙ የቢሆን አጋጣሚዎችና ደራሽ

አማራጮች፣ የመንግሥት የድጋፍ ርምጃዎች መሥመር የተከተሉ ሊሆኑ ይገባል። በትላልቅና በአነስተኛ የንግድ ተቋማት፣ ሥራ ባላቸውና ከሥራ ውጪ በሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለውን የጉዳት ደረጃ በሚዛኑ ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የንግድ ማኅበረሰባችን የሚያጋጥማቸውን ውድድር መቋቋም እንዲችሉና ያላቸውን የሥራ ልምድና የአሠራር ጥበቦቻቸውን መሠረት አድርገው በማገገም፣ ዳግም ተወዳዳሪ ሆነው ሠራተኞችን መቅጠር እንዲጀምሩ በሚዛን አቅማቸውን መደገፍ ግድ ነው። አለበለዚያ ነጋዴዎቻችን ይጎዳሉ። እንደ ሀገር መገንባት የምንሻው ካፒታሊስታዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ሳይናጋ ተጠናክሮ መቀጠሉ ወቅቱ የሚጠይቀው ዐቢይ ጉዳይ ነው። በአንድ በኩል ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና ማኅበራዊ ፍትሕን የማረጋገጥ ፖሊሲያዊ ቅኝት በኢኮኖሚ ማገገሚያ ርምጃዎቻችን እንዲንጸባረቁ አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት የሚያሻ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከድጋፍ ዐቅም ጋር አስተሳስሮ ፈጠራንና ነጻ ውድድርን ተግባራዊ ማድረግን የሚጠይቅ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ወደ ብልጽግና ለማምራት የመረጥነው ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሥርዓታችን ካፒታሊስታዊ ነፃ የውድድር መንገድ ነው። በዚህ ማሕቀፍ መሠረት የመንግሥት ሚና በአመዛኙ ፖሊሲ የማመቻቸት እንጂ እንደግለሰቦች ቢዝነስ ውድድር ውስጥ ገብቶ የገበያ ሥርዓቱን መረበሽም ሆነ እንደ ተራድኦ ድርጅት ለዜጎች መቆሚያ የሌለው ድጎማ መስጠት አይደለም። ዜጎች ተወዳዳሪነታቸውን እንዲያሳድጉ በማስቻል ዘላቂ የሆነ የእድገት መንገድ መከተል ለኢኮኖሚያችን አዋጭ መንገድ ነው ብለን እናምንም።

በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉንም ነገር መንግሥት እንዲቆጣጠርና የኢኮኖሚ መዘውሩ ሙሉ ለሙሉ ከግል ከፍለ ኢኮኖሚው እጅ መውጣት አለበት የሚሉ ኢኮኖሚስቶች መኖራቸውም ይታወቃል። ይኼም ሌላ ጽንፍ ነው ብለን እናምናለን። መንገዳችን ሶሻሊስታዊ ባለመሆኑ መንግሥት በሁሉም ሀገራዊ ኩባንያዎች ውስጥ የሼር ድርሻ ተካፋይ ለመሆን አይታገልም፤ መታግልም አይኖርበትም።

ቀድመው ዐቅም የፈጠሩ የግል ባለሀብቶች፣ ኋላም ሥራ ፈጣሪ ናቸውና መንግሥት ወይም ኅብረተሰብ በዚህ ወቅት ሊደግፋቸው ይገባል ብለን እናምናለን። ይህ አጋጣሚ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥ መልካም አጋጣሚ በመሆኑ ትላልቆቹን ብቻ ሳይሆን ትናንሾችንም በመደገፍ፣ ሌሎችም ወደ መድረኩ የሚመጡበትን ምቹ ሁኔታ በማመቻቸት፣ በጥቂቶች ብቻ ተይዞ የሚገኘውን የንግድ እንቅስቃሴ ለሌሎችም ማመቻቸት ያስፈልጋል የሚሉም አሉ፡፡ ለምሳሌ የቤትና የንብረት አከራዮች ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ። መጠቀምን ብቻ ሳይሆን መርዳትና መደገፍንም እንዲማሩ ማስተማር ተገቢ ነው። መሠረታዊ የሆነ የትምህርት፣ የጤና፣ የምግብና የመጠለያ አገልግሎት ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚደርሱ አገልግሎቶች እንዲሆኑ፣ የፖሊሲ ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ ቀጥተኛ የመንግሥት ተሳትፎ እንዲኖር ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ይሆናል።

ገበያ ለሁሉም ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት የሚችሉ እጆች አሉት፤ በሚል ግትር አመለካከት የመንግሥትን ድርሻ መገደብ ታላቋን አሜሪካንን እንኳን ያስከፈላት ዋጋ ቀላል አይደለም። በዚህ የቀውስ ወቅት ሀብታሟና በቴክኖሎጂ ምጡቅ የሆነችው ሀገር ቀላል የጨርቅ ማስክና የፕላስቲክ ጭምብልም ሆነ ሕይወት አዳኝ

የሆነውን የአየር ማስተላለፊያ ቬንትለተር ማቅረብ እንደተሳናት ታዝበናል። በዚህ ረገድ እንደ ሀገር ልንከተለው የሚገባን አቅጣጫ በመደመር እሳቤ የተቃኘ፣ የእርስ በርስ ፉክክርን ከጋራ ትብብርና መደጋገፍ በማጣመር የቆመ፣ ዴሞክራሲን ያማከለ ልማታዊ ካፒታሊዝም መሆኑን አስረግጦ ማለፍ ቀላል ፈተና አልነበረም።

ሀገራዊ ኢኮኖሚውን የማሳደግ መሠረት የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ዋነኛ ድርሻ መሆኑን የብልጽግና ፓርቲ ያምናል። ላለፈው አንድ ዓመት ይህንኑ ሲያበረታታና ተስፋ ሲሰጥ መቆየቱ ይታወቃል። በዚህ ከወረርሽኙ ጋር በተያያዘው ቀውስ የተነሣም በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ገና ከጅምሩ ጫና ማሳደር አይሻም። ከዚያው ጎን ለጎን ደግሞ በኑሮ

ደረጃው ዝቅተኛ የሆነው የማኅበረሰብ ክፍል ማኅበራዊ ፍትሕ እንዲረጋገጥለት ይፈልጋል። ውሱን ዐቅም ባለበት ሁኔታ ይህን ሚዛን አስጠብቆ መቀጠል አዳጋች ቢሆንም ተደጋግፎ ችግሩን ከማለፍ ውጪ አማራጭ የለም። ዕውቁ የታሪክ ተመራማሪ ዋሻል ሃራሪ ሰሞኑን እንደጻፈው በድኅረ ኮሮና የምንኖርባት ዓለም በቅድመ ኮረና ከምናውቃት በጣም የተለየች ትሆናለች። የቀኝም ይሁን የግራ ዋልታ ረገጥነት በድኅረ ኮሮና ቦታ ያለው አይመስልም። ዓለም በፖለቲካዊው፣ በኢኮኖሚያውና በዲፕሎማሲያዊ አቅጣጫዎች በመደመር እሳቤ (ከዋልታዎቹ መሐል) ሚዛኗን ጠብቃ ካልቆመች እንደገና መውደቋ አይቀርም።

ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በቶሎ ቫይረሱን በማሸነፍ መረጋጋትና ሰላም መፍጠር ነው። የችግሩ የማያዳግም መፍትሔ መንግሥታትና ሕዝቦች ሀብታቸውን፣ ዐቅማቸውንና ጊዜያቸውን፣ ሳይንሳዊ ዕውቀታቸውንና ቴክኖሎጂያዊ ክሂሎታቸውን አስተባብረው፣ ወረርሽኙን ለማሸነፍ እንደ አንድ ሆነው መነሣታቸው ብቻ ነው። እንደ ማኅበራዊው ሕይወታችን ሁሉ ኢኮኖሚያዊ ዋስትናችንም በመተጋገዝና በመተሳሰብ መደመርን ግድ ይላል። ይህ ዓለም አቀፋዊ ወረርሽኝ የፈጠረውን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውስ፣ አንድ ሀገርና ሕዝብ ተነጥሎ ሊያሸንፈው አይችልም። ሉላዊ ችግር ሉላዊ መፍትሔን ይሻል። የኮሮና ፈተናን በመደመር ቀመር ከገጠምነው ወደ ቀውሱ ስንገባ ከነበረን ማንነት ጠንክረንና ተቀራርበን፣ በሁለንተናዊ ማንነታችን በልጽገንና ማኅበራዊ ካፒታላችንም ዐድጎ መውጣት እንችላለን። የመደመር እሳቤና ተግባራዊ መፍትሔ ለብልጽግና ብቻ ሳይሆን ለህልውና ማስጠበቂያም የላቀ መንገድ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችንም ከዚህ አሳሳቢ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ተነጥላ የምትገኝ ሀገር አይደለችም። በሽታው በእኛም ሀገር አጣዳፊና አደገኛም ሁኔታን ፈጥሯል። ቫይረሱ ወደ ሀገራችን መግባቱ ከተረጋገጠ ገና ወር አካባቢ ቢሆንም ወረርሽኙ የፈጠረው ዓለም አቀፍ መዘጋጋት የንግድ ሥራችንን ከፉኛ በማወኩ ኢኮኖሚያችንን እየጎዳ ነው።

በቅድመ ኮሮና 'ብቻ መሆን' ምነው ብቻህ/ሽን እንዳላስባለ ሁሉ፤ በዘመነ ኮሮና ደግሞ ሰብሰብ ብሎ አንድ ላይ ሆኖ መገኘት አደገኛ ሆኗል። ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ሕፃናትና ልጆች በቤት ተቆልፈው መዋል ከጀመሩ ሰንብተዋል። ሰዎችን የሚያሰባስቡ እንደ ስፖርት ፕሮግራሞች፣ ኮንሰርቶችና ኢግዚቢሽኖች ተዘግተዋል። በየአራት ዓመት የዓለምን ሕዝቦች ከየሀገሩ የሚሰበስበው የኦሎምፒክ ጨዋታዎችም ለሚቀጥለው ዓመት ተላልፏል። ቤተ እምነቶችና የፖለቲካ ስብሰባዎች ጨምሮ ሕዝብ በብዛት

የሚሰበሰቡባቸው ቦታዎች ሁሉ ጸጥ ረጭ ብለዋል።

**መገፋፋት በዛ መራራቅ ከበደን**

**ልንገባ ነው መሰል ገደል ተያይዘን።**

ይህ ወረርሽኝ የማናውቀውን ቫይረስ ምንነት ብቻ ሳይሆን በሩቅና በቅርብ ያለነውን የሰው ልጆችን፣ የራሳችንን ማንነት አይተነው በማናውቀው መንገድ የገለጸ ነው። ቫይረሱ ከሌሊት ወፍ ተነሥቶ በአሳማ ሥጋ በኩል ተዛምቶ ወይም ከሌሎች እንሰሳት ወደ ሰዎች የተሸጋገረ ነው ይባላል። አንዳንዶች ደግሞ ከረቀቁ ላብራቶሪዎች በሆነ መንገድ አምልጦ የወጣ "ሥነ ሕይወታዊ አጥፊ መሣሪያ ነው" ብለው ይተነትናሉ። ከዚህ ውጪ ደግሞ የወረርሽኙን ምንነት፣ የተከሠተበትን ምክንያትና ማን እንደቀሰቀሰው የሚነገሩ ወሬዎች ለብዛታቸው ቁጥር የለውም። የኮሮና ቫይረስ ዝርያዎች ብዙ ዓይነት ሲሆኑ በዋናነት በእንስሳት ላይ የሚገኝ ወደ ሰው ሲሸጋገር ከፍ ያለ ጉዳት በማድረስ የታወቀ ረቂቅ ፍጡር ነው። ምንም እንኳን ከዚህ በፊት አነስተኛ ወረርሽኞች ተከሥተው ቢያውቁም የዘንድሮው ኮቪድ9 ቫይረስ የቀሰቀሰው ሉላዊ ወረርሽኝ በብዙ መልኩ የተለየ ነው።

ከመደመር ፅንሰ ሐሳብ አንጻር እጅግ አስገራሚው እውነታ ያለው ከቫይረሱና ከተቀነቀነው ወረርሽኝ አንጻር የታየው አስገራሚ ባሕርይ ነው። ኮቪድ 19 እንደማንኛውም ቫይረስ ከፍጥረታት ሁሉ ረቂቅና ከእንሰሳትና ከሰው ሕዋሳት ውጪ ሊራባም ሆነ ለረጅም ጊዜ ሊኖር የሚችል አይደለም። እንደዚህ በአጭር ጊዜ ራሱን አባዝቶና አሠራጭቶ የዓለምን ኃያላን መንግሥታት ሳይቀር፣ ዕውቅ ልሂቃንና እንደሰው ያለን ግዙፍ ፍጥረት ማንበርከኩ አስደማሚ እውነት ነው። ከሕዋስ/ሴል ወደ ሕዋስ፣ ከሰው ወደ ሰውና ከሀገር ወደ ሀገር የተሠራጨበትን ፍጥነትና ብርታት የሰውን ልጅ ትንሽነት ያጋለጠ ነው። ነጋሪት ሳይጎስምና ኒዩክሊየር ሳይስፈልገው ዓለምን ያንበረከከ ብቸኛ ልዕለ ኃያል መንግሥት ለመሆን ምን ቀረው? አሁን ኮሮና ሲባል የማይደነግጥ ማነው? ሳይንሳዊ ጥናቶች እንደሚያሳዩን ቫይረሱ ራሱን የሚያባዛበትና ከሰውነት ተከላካይ ነጭ ሴሎች ጥቃት የሚድንበት መንገድ የረቀቀ ነው።

የመጀመሪያውና አስቸጋሪ ባሕርይው የሚዛመትበት ፍጥነት ሲሆን ሌላው ደግሞ ሴሎቻችንን የሚወርርበትና የራሳችንን ዐቅም ተጠቅሞ ራሱን እያባዛ የኛን ሰውነት በራሳችን ወታደር ሴሎች የሚያፈራርስበት ሁኔታ ነው።

በመጀመሪያ የተያዙ ሁሉ ስለማይታመሙ፣ ብዙኃን ቫይረስ ተሸካሚ እንደሆኑ በማናውቃቸው ሰዎች፣ ከሀገር ሀገር በልዩ ልዩ መጓጓዣዎች አማካኝነት ወደ ሀገሮች ሁሉ መሠራጨቱ ነው። ሁለተኛው በተለያዩ ሕመሞች የተጠቁና በዕድሜያቸው የገፉ ሰዎችን በኃይል በማጥቃት ለሞት በመዳረግ የሚፈጥረው ሽብር ነው። ይህም ያለንን ሀብትና ዐቅም ሁሉ በሕክምናና የበሽታውን ሥርጭት ለመግታት በምናደርገው ግርግር፣ ዐቅማችንን ያጣን፤ በፍርሃት የታሰርን፣ ፍጡራን እንደሆንን እንዲሰማን ማድረጉ ነው። የሚተላለፍበት መንገድ አሳሳች በመሆኑም እርስ በርስ ተራርቀን፣ በቤታችን ተዘግተን፣ አፍና አፍንጫችንን አጨንበለንና ተገልለን እንድንቆይ ሲያደርገን፤ ሁሉን ለራሱ ጥቅም የደመረ፣ የመደመርን ስሌት ከሰው ልጆች መሐል ለማጥፋት ታጥቆ የተነሣ ተንኮለኛ ጋኔን እንጂ፤ ራሱን እንኳ ችሎ መኖር የማይችል ድቃቂ ፍጡር አይመስልም።

የኮቪድን የመደመር ስሌት ለመርታት ሁነኛው መንገድ ኮቪድ የወሰደብንን የላቀ የመደመር እሳቤ መተግበር ነው። የኮቪድ የመደመር ስሌት የራሱ ባልሆነ የሰው ሕዋስ ተደምሮ መራባትና ከሰው ሰው መዛመት ነው። የኮቪድ የመደመር ስሌት ብዙ አዳዲስ ሰዎችን በመያዝ የኮቪድ ታማሚዎችንና ተሸካሚ አማቾችን ማብዛት ነው። የኮቪድ የመደመር ስሌት ፍርሃትንና ሽብርን በመፍጠር በሰዎች መካከል ያለውን ማኅበራዊ ዐቅምና መንፈሳዊ ጉልበት በማጥፋት፣ ሰዎችንና ሀገሮችን በታትኖ ማንበርከክ ነው።

የኮቪድ የመደመር ስሌት ሰዎች መሥራትና መማር እንዳይችሉ፣ መገበያየትና ተሰባስበው ጸሎት ማድረስ እንዳይችሉ ማራራቅና አንዱ ለሌላው እንዳይደርስ መለያየት ነው። የኮቪድ የመደመር ስልት ዓለምን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ በመክተት፣ ከቫይረሱ ይልቅ በረኃብና በሌሎች ሕመሞች፣ በጦርነትና በማኅበራዊ ቀውሶች የፈራረሱ ሰዎችን ፈጥሮ መንገሥ ነው። ኮቪድ ይህንን ሁሉ ሊያስብ አእምሮ እንደሌለው ሁላችንም እናውቃለን። ነገር ግን ኮቭድ የሚሠራበትና ወረርሽኙ እየተባዛበት ያለው መርሕ በመደመር ስሌት ሲታይ ይሄንን ይመስላል።

የኮቪድ ወረርሽኝ ከሚሠራበት የላቀና ብልኅ የሆነ የመደመር ስልትና ስሌት ከተጠቀምን፣ ኮቪድን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተግዳሮቶቻችንን እንደ ሀገርም፣ እንደ ሰው ልጅችም ማሸነፍ እንችላለን። መደመር ስልትም ስሌትም ነው። መደመር መርሕም መንገድም ነውና። ኮቪድን ለሰው ልጆች ሁሉ እንደተደቀነ አደጋና ፈተና ከአየነው፣ መደመርን ደግሞ ይህንን ተፋልመን ልናሸንፍበት እንደምንችል ሁነኛ ጎዳና ልናየው እንችላለን።

# “በጊዜ መደንገጥ”

# የመጀመሪያው ጥበብ

በሀገራችን “ሳይቃጠል በቅጠል” የሚሉት አባባል አለ። ትልቅ አባባል ነው። መነሻ ላይ ከደረስክበት እሳትንም ቢሆን መቃጠል ከጀመረው ጫካ ከራሱ ዛፍ ቅርንጫፍ ገንጥለህ፣ ሲግለበለብ የነበረው ነበልባሉን ልታጠፋው ትችላለህ። ያን አጋጣሚና ዕድል መጠቀም አቅቶህ ከዘገየህ ግን እሳቱን ለማጥፊያ ያገለግልህ የነበረ ቅጠል ከእሳቱ ጋር ተባብሮ አንተኑ መልሶ ያጠፋሃል። ‹ሳይርቅ በቅርቡ፣ ሳይደርቅ በእርጥቡ› ማለትም ይሄው ነው። ዛሬ መሥራት ያለብህን ለነገ ካልከው የምታሸንፈው ያሸንፍሃል፤ የምትጨብጠው ይጨብጥሃል። በጊዜ ደንግጠህ ውሳኔ አለመስጠትህ የሚያስከትለው ጉዳት እጅግ የከፋ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ጋር በተገናኘ ፈረንጆች አንድ አባባል አላቸው፤ ‹‹boiling frog syndrome›› ይሉታል።

እንቁራሪት፣ በውኃ የተሞላ ድስት ውስጥ እያለች ውኃው እሳት ላይ ቢጣድ የሰውነት ሙቀቷን ከውኃው ጋር አስማምታ የመቆየት ዐቅም አላት ይባላል። በዚህ መልኩ ሙቀቱ እየጨመረ ሲሄድ እንቁራሪቷም ከሙቀቱ ጋር ራሷን ማስማማቷን ትቀጥላለች። ልክ ውኃው መንተክተክ ሲጀምር ግን (የመፍላት ነጥብ ላይ ሲደርስ) እንቁራሪቷ ቃጠሎውን መቋቋም ያቅታታል፤ ያኔ ከድስቱ ውስጥ ለመውጣት ትወስናለች። ዳሩ ግን የመዝለል ዐቅም አይኖራትም። ከሙቀቱ ጋር ራሷን ለማለማመድ ባደረገችው ጥረት ሙሉ በሙሉ ጉልበቷን ጨርሳለች።

ታዲያ ያቺን እንቁራሪት የገደላት የውኃው መፍላት ነው ብለን ካሰብን ተሳስተናል ይላሉ ፈረንጆች። እንቁራሪቷ የሞተችው በትክክለኛው ጊዜ ዐቅሟን ትክክለኛ ቦታ ላይ ለማዋል አለመወሰኗ ነው። በተመሳሳይ ከኮሮና ጋር የሚደረገው ፍልሚያ በጥበብ የተሞላ ካልሆነ በኋላ ማጣፊያው እንደሚያጥር ግልጽ ነው። ለዚህም የመጀመሪያው ጥበብ በጊዜ መደንገጥ ነው።

ኮሮና በድፍን ሀገር ከመዛመቱ በፊት በመመርመር ለይተን ልንገድበው ይገባል። አንድ ሰው ለኮቪድ ወረርሽኝ መነሻም መከሰሚያም ሊሆን ይችላል። በደቡብ ኮሪያ "ሕመምተኛ 3 Patient-3 የሚል ስያሜ የተሰጣት ሴት በሀገሪቱ ወረርሽኙ ሲም ለተያዙት 60 በመቶ ታማሚዎች መንሥኤ ነበረች። በሄደችባቸው የገበያ ስፍራ፣ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎች ሰፍራዎች ሁሉ ቫይረሱን ያለ ዕውቀቷና ፍላጎቷ በመርጨት ብዙ ሺሕ ሰዎችን ወደ ወረርሽኙ ስትጨምር ነበር። የአንድ ሰው ኃይል። በዚህ ወረርሽኝ ውስጥ ገና ማን እንደሆነ ያላወቅነው ሕመምተኛ ዜሮ የሚባልም አለ። ሕመምተኛ ዜርን (Patient zero) በጊዜው ዐውቀን ብንለይ ኖሮ ዛሬ የተፈጠረው ቀውስ ሁሉ ባልተፈጠረም ነበር። እሳቱን ልናጠፋበት የምንችለው ቅጠል ጫካውን ሲያቃጥል መቻሉ አስገራሚ የመደመር ስሌት መሠረታዊ እሳቤ ነው።

በርግጥ ወረርሽኝ ሲያጋጥም በድንጋጤ መራድና ሲያልፍ ደግሞ አቅልሎ ማየት ልማድ ሆኗል። ፍርሃት መፈረካከስን ይፈጥራል። ከልክ ያለፈ ፍርሃት የውስጥ ሥነ ልቦናንና በሽታ የመከላከል ዐቅማችንን ማዳከሙ ብቻ ሳይሆን፤ እንደ ማኅበረሰብም ያለንን አንድነትና በትክክል የማሰብ ዐቅም ይነሳናል። በፍርሃት መሸነፍ እንጂ ማሸነፍ የለም። ሌላው የፍርሃት ችግሩ ከቫይረሱ በላይ የሚጋባና በፍጥነት የሚዛመት መሆኑ ነው።

ፍርሃት ባለበት ቦታ የመደመር ስሌትን ለመተግበር አዳጋች ነው። ፍርሃት በታታኝ ነውና። ፍርሃት አስፈሪውን በመደመር ሲያገዝፍ፣ ፈሪውን ደግሞ በመበታተን ያኮስሳል። ዕውቀት፣ ተስፋ፣ ተግባቦትና ጠንካራ አመራር ፍርሃትን ወደ ድፍረትና ጠንካራ አንድነት የመለወጥ ዐቅም አለው። ፍርሃት ረግቦ በሰዎች መካከል ለአንድነት መተማመንና መቀራረብ ሲፈጠር፣ የመደመር ቀመሩ መሥራት ይጀመራል። ጤና ግለሰባዊ ጉዳይ ተደርጎ የሚታይበት ጥንታዊ ዘመን አልፎ ጤናን ኅብረተሰባዊ ከዚያም ባሻገር ዓለም አቀፋዊ የህልውና ጉዳይ እየሆነ መምጣቱን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በአንድ ጊዜ በሁለት ግንባር የሚፈጠርበትን ጦርነት መግጠምና መቋቋም የሚችል ጠንካራ የጤና ሥርዓትና አደረጃጀት መፍጠር ሀገራት በመደመር እንጂ ለብቻቸው ሊያረጋግጡት አለመቻሉን ከምን ጊዜውም በላይ በኮቪድ ግልፅ ሆኗል። በመደመር የሚፈጠር አንድነት የትናንትን ጥበብና የዛሬን ዐቅም ተጠቅሞ የተጋረጠውን ተግዳሮት ለመርታትና የተሻለ ነገን ለመፍጠር መነሻ ነው። ያለፈውን ዘመን አተያይ ሳትወያይ፣ ሳትተችና ሳትነቅፍ አዲስ የእይታ መነጽር መፍጠር ፈጽሞ የሚሞከር አይደለም። ይህም ሲባል ያለፈው ሁሉ አንዳችም ሊመሰገን የሚገባው ገጽታ የለውም ማለት እንዳልሆነ መረዳት ያሻል። ያለፈው በራሱ የሚመሰገን በጎ ገጽታ ባይኖረው እንኳን፣ ለአዲሱ እይታ መፈጠር መሠረት በመሆኑ ተገቢውን ምስጋና መቸር፣ በቀጣይ ሌሎች አዳዲስ የእይታ ችግኞች ሳይበቅሉ እንዳይደርቁ፣ ሳያፈሩ እንዳይረግፉ ያደርጋል። ስለሆነም ኮሮና ቫይረስ በሽታውን ከመከላከልና ከማሸነፍ ባሻገር ተጋላጭነታችንን ያሳየና ለአኗኗራችንን መልስን እንድንጠይቅ ማድረግ አለበት።

ጥቁር ሞት የተባለው የ4ኛው ክፍለ ዘመን ገዳይ ወረርሽኝ ለአውሮጳ ሥልጣኔ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ማድረጉ ይጠቀሳል ከወረርሽኙ በኋላ የአውሮጳ የአኗኗር ዘይቤ በከፍተኛ ደረጃ ተቀይሯል። ሕዝቦች በአኗኗራቸው ላይ ጥያቄ እንዲያነሡና እንዲመረምሩ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል።

ከወረርሽኙ በፊት የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራውን የደነዘዘ ዘመን አልፈው ወደ ተነቃቃው የተሐድሶ ወርቃማ ዓመታት እንዲሸጋገሩ ምክንያት ሆኗል። የአውሮፓ ዩኒቨርስቲዎች ለሳይንስ፣ ለቴክኖሎጂና ምርምር ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት አብዛኛዎቹን በሽታዎች የሚፈውሱ መድኃኒቶችን ለማግኘት ምክንያት ሆኗል። ይሄው ጥቁር ሞት› የተሰኘ ወረርሽኝ በአውሮፓ በተለይም በምድረ እንግሊዝ ገብቶ ብዙ ሕይወት ባጠፋበት ጊዜ ልክ እንደ አሁኑ የኮሮና ዘመን ከሰው ተለይቶ በቤት የመዘጋት ርምጃዎች ተወስደው ነበረ።

በዚህ የተነሣ ቴአትር ቤቱ የተዘጋበትና ከመድረክ እንዲርቅም የተፈረደበት ዊልያም ሼክስፒር ከተውኔት ሥራዎቹ ባሻገር ታላላቅ ሥነ ግጥሞቹን በዚያ ወቅት እንደጻፈ ይነገርለታል። በሌላም በኩል ታላቁ የፊዚክስ ሊቅና የካልኩለስ ፈጣሪ መሆኑ የሚነገርለት አይዛክ ኒውተን ያስተምርበት የነበረው ኬምብሪጅ ዩንቨርሲቲ ተዘግቶ ወደ ቤቱ እንዲሄድ ተደርጎ ነበር። ታዲያ በቤቱ ግቢ ውስጥ ካለው ትልቅ የሾላ ዛፍ ስር ተቀምጦ ሳለ፣ ከገጠመው የፍሬ ዱብታ ትዕይንት በመነሣት አስገራሚውን የስበት (ግራቪቲ) መርሕ መቀመሩ ይተረካል።

በቀደሙት ዘመናት ሀገራችን ባሳለፈቻቸው ወረርሽኞችና ድርቅ የተነሣ የተፈጠረው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጥ ምን ገጽታ ነበረው? የሚለው ጥያቄ ሰፊ ጥናት የሚያሻው መሆኑ እሙን ነው። የ1966 ዓ.ም ድርቅና በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ብዙ ሕዝብ የጨረሰውን ረኃብ በጨረፍታ ስናስብ፣ መንግሥታዊ ለውጥ ከማምጣቱ ባሻገር በኪነ ጥበብ ዘርፍ የሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድኅን፣ ‹‹ረኃብ ስንት ቀን ይሰጣል›› የሚለውን ግጥም፣ የድምፃዊ ጥላሁን ገሰሰን ‹‹ዋይ ዋይ ሲሉ››ን አብቅሏል። ወደ ባሕር ማዶም ስንሻገር We are the World' የሚለውን ታዋቂ የጥበብ ሰዎች የተሳተፉበትን ክወና መፍጠሩ ሌላ ምልከታ ነው።

ወረርሽኝ ውርሱ ጥፋት እንጂ ፍካት ሊሆን አይችልም ብሎ መደምደምን ከባድ የሚያደርገውም ይኸው እውነታ ነው። ወረርሽኝ ሊፈጥረው ከሚችለው የኪነ ጥበብ፣ የባህልና የፈጠራ መነቃቃት ባሻገር ራሳችንን፣ ቤተሰባችንና ማኅበረሰባችንን የምንመለከትበትን የእይታ መነጽር ሊቀይረው እንደሚችል ይታመናል። ዓለምን ያለውድ በግድ ከማቀራረቡም ባሻገር፣ የእምነታችንን ዕለታዊ ተዛምዶና ጥልቀትም ፈትኖ ማለፉ አይቀርም። ለብቻ መትረፍ እንደሌለና የሌላው ሕይወትና መኖር ለመኖራችን ዋስትና መሆኑንም ሳያሳየን አይቀርም።

የወረርሽኙ አስፈሪነትና የቫይረሱ ምስጢራዊነት ለሁሉም እንግዳ በመሆኑ የሰው ልጆች እንደቤተሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ ሀገርና ዓለም አቀፋዊ ትብብሮችንና መናበቦችን በመፍጠር የመደመርን እሳቤና ተግባራዊ ልምምድ ሊያጎላው እንደሚችል ምንም ጥርጣሬ የለውም። ከወረርሽኙ ቀድማ ያገገመችው ቻይና ያላትን ልምምድና ዐቅም ከሌሎች ጋር በመካፈል ላይ ትገኛለች። ከያኒው በጥበቡ፣ ሐኪሙ በሙያው፣ ባለሀብቷ በገንዘቧ፣ ባለሆቴሉ በንብረቱ ሁሉም ባለው ያለውን በመደመር ችግሩን በጋራ ለማለፍ የሚያሳየው መሰጠት ማኅበረሰብን ከግለኝነትና ከጽንፈኝነት ሊታደግ የሚችል አጋጣሚን መፍጠሩ አይቀርም።

ዘረኛነትንና አክራሪነትን ተላብሰው ጠብንና ነውጥን የሚዘሩ ድምፆች ጋብ ብለው ሁሉም በጎነትንና አንድነትን

የሚያራምዱ ድምፆችን ሲያስተጋባ ማየት፣ ምናልባትም ይህ ወረርሽኝ የጥፋት ብቻ ሳይሆን እንደ ሀገር ተደምረን የምንሻገርበት እመርታ ውስጥ ይከተን ይሆን፤ የሚል ተስፋን ያጭራል። እንደ ጃክማ ያሉ ባለጠጎች የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ እንደ ቤተሰብ በመቁጠር የማካፈልን ጉልበትና ከችግር በላይ ሆኖ በመፍትሔነት የመደመርን ታላቅነት ያሳየ ነው።

ወረርሽኙን ተከትሎ ብዙ ቀልዶች ተፈጥረዋል፡፡ ከሰማኋቸው ውስጥ አንዷ ይኽን ትመስላለች። ሰውየው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ናቸው። ማኅበራዊ መራራቅን ለመፍጠር ቤት ሆነው እንዲሠሩ ገደብ ከተጣለባቸው የመንግሥት ሠራተኞች መካከል አንዱ ናቸው። ዳኛው ይሆን መሠረት አድርገው፤ ማጠቃለያ ስለሚሰጥበት አንድ የፍርድ ጉዳይ፤ በሌላ ጫፍ በኢንተርኔት ከተገናኙ የግራና የቀኝ ዳኞች ጋር በመወያየት ላይ ነበሩ። እንደርሳቸው ትምህርት ቤት ተዘግቶ ቤት መዋል የጀመሩ የ5 እና የ7 ዓመት ልጆቻቸው እናታቸውን አልታዘዝ ብለው በፈጠሩት ረብሻ ለፍርድ ወደ እርሳቸው ችሎት ቀረቡ።

ጭራሽ አባትዬው ይመሩት የነበረውን ችሎት በመረበሽና በመድፈር ጥፋት የወንጀለኛ ሙት ሕግ አንቀፅ ተጠቅሶባቸው በየክፍላቸው ተዘግቶባቸው እንዲቀመጡ የተፈረደባቸውን ውሳኔ አስመልክቶ የሰማሁት ቀልድ፣ በሥራ ውጥረት ውስጥ ሆኜ ስሰማው ፈገግ ከአሰኙኝ ቀልዶች አንዱ ነው። ነገሩ በወረርሽኙ ፡ ምክንያት የተስተናገደውን አዲስ ዓይነት የሕይወት ዘይቤ በዚያውም ለመወረፍ የተነገረ መሆኑ አያጠያይቅም።

ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያጋጥመው ፈተና መልከ ብዙ ነው። ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን በተመለከተ እንደ ማኅበረሰብ ዛሬም ድረስ ያልተቀየሩ አልፎ አልፎም የተሳሳቱ አመለካከቶች በስፋት ይንጸባረቃሉ። በአብዛኛው የማኅበረሰቡ ክፍል ዘንድ፤ ወረርሽኙን በግለሰቦች ኃጢአት ሳቢያ በቁጣ የወረደባቸው መቅሰፍት ፡ አድርጎ መመልከት አሁንም በስፋት ይስተዋላል።

እንደ ሀገር ባሳለፍናቸው ታላላቅ ድርቆችና ወረርሽኞች ታሪክ ላይ የተደረገ በቂ ጥናት የለም ማለት ይቻላል። ከፖለቲካ ሕይወታችን የራቀውን ታሪክ በተመክሮነት ያደራጀነውና ያስተማርነው ጥቂት እንደሆን ሁሉ። ሀገር በባዕድ ሲወረር የእምነት ተቋማት ምእመናቸውን በማስተባበር ያደረጉትን ተጋድሎ ያህል ወረርሽኝን ለመከላከል የፈሉትን ተጋድሎ አጉልተው አልተረኩልንም። ያኔ የሆነውን ዛሬ ልናነጻጽረው በምንችል መንገድ በጥበብ ከሽነው በምስልና በሥነ ጽሑፍ አቀናብረው ብዙም አላልንም። ከብቶች አልቀው ሀገር በመጥረቢያ ሳይቀር እስኪያርስ ያደረሰውን ደስታ የተሰኘ የከብቶች በሽታ፣ የኅዳር ወረርሽኝ፣ የፈንጣጣና የወባን ብቻ ሳይሆን የቅርብ ጊዜ ትዝታችን የሆነውን የኤችአይቪ / ኤድስ ወረርሽኝን ልምምድና ትዝታ ኪነ ጥበባዊም ሆነ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለታሪክ ያስቀመጡ በቂ መዛግብት ማግኘት የማይታሰብ ነው። በየትኛውም አቅጣጫ ተጉዘን ተለቅሞ የወጣ የተደራጀ እውነተኛ ትሮ ማግኘት እጅግ ሲበዛ ከባድ ነው። ከሺ ዓመታት በላይ ቸነፈር፣ ተስቦ፣ ረሐብና ወረርሽኝ ሲፈራረቁብን እንደነበር ጥንታዊ መዛግብት ይነግሩናል፡፡ እንዴት አንድ ዕንቅፋት ደጋግሞ መታን?

ከታሪክ ወቀሳ መለስ ብለን አሁን ያለንበትን ሁኔታ ስንቃኝም ያንኑ ፈዛዛ ምስል ነው የምናገኘው። ብሔራዊ

የአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ ሥርዓታችን ቢሆን፣ ተስፋ ሊሰጥ የሚችል ዓይነት አልነበረም። በአየር መዛባት ሳቢያ የሚከሠተውን ድርቅና እርሱን ተከትሎ የሚቀጥለውን ረኃብና ችጋር እንጂ ተስቦና ቸነፈር መመከት ላይ ያተኮረ ወቅቱን በሚመጥን ዐቅም የተደራጀ አይደለም። በመምጣት ላይ ካለው አደጋና ከሕዝባችን አኗኗርና ብዛት ጋር ከተነጻጸረ ግን የምላሽ ዐቅሙ እጅግ ሲበዛ ደካማ ነው። በአመዛኙ በራሱ የታጠረና የምላሽ ብቃቱም በባለሙያ፣ በመሣሪያና በመሠረተ መዋቅር ያልተጠናከረ ነው።

በዓለም ደረጃ አዳዲስ በሽታ አምጪ ቫይረሶችን ከአሁን በፈጠነና መከላከልን በአረጋገጠ ደረጃ መለየትና በተገኘበት ወስኖ ማስቀመጥ የሚያስችል ጠንካራ ሥርዓት ያስፈልገናል። ከስም በላይ በሥራው የሚለይ፣ ከሂደት ይልቅ በውጤት መለካት የሚችል መሆን ይኖርበታል።

በባለጠጋ ሀገራት ከሚገኝ አንድ ሆስፒታል ያልበለጠ ዓመታዊ በጀት ይዞ የዓለም ጤና ድርጅት በሚል ስያሜ የዓለምን ጤና አስጠብቃለሁ ማለት የሚሠራ እንዳይደለ፣ የዘርፉ ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ እኛም ከተግባር ተመክሯችን የተገነዘብነው እውነታ ነው። ዓለም ባለመደመሩና በከፍተኛ ኅብረት ባለመሥራቱ እንደትናንት ሁሉ ዛሬም ከፍተኛ የሕይወትና የሀብት ጉዳትና ኪሳራ ማስተናገድ ዕጣ ፈንታችን ሆኗል።

ጀልባችን ቢለያይም በአንድ ባሕር ላይ የምንቀዝፍ ባሕረኞች ነን። የመቀመጫችን ምቾቱና ደረጃው ቢለያይም የተሳፈርነው ግን በአንዲት ትልቅ መርከብ ላይ ነው:: አይመለከተኝም አያገባኝም የሚል ሽሽት እንደማይሠራ የኮሮና ወረርሽኝ አድምቆ አሳይቶናል። በበሽታው ላለመጠቃት ዘር፣ ቀለም፣ ሀገር፣ ሀብት፣ ሥልጣን መደበቂያ ምሽጎች አይሆኑም። በጋራም ዓለም ተረባርቦ ፋሺዝምንና ናዚዝምን እንዳጠፋው ሁሉ በተናጠልም በጋራም ተቀናጅተን መቆም ይኖርብናል።

ጭው ካለ ምድረ በዳ መካከል፣ ከስንት አንዴ እንደሚገኝ በምንጭ የተከበበ ለምለም ስፍራ፤ በኮቪድ ወረርሽኝ መካከልም አልፎ አልፎ ቢሆንም ተስፋ የሚያነሣሡ ትብብርና ድጋፎችም ተስተውለዋል። ወረርሽኙ በመጀመሪያ የተከሠተባት ቻይና በዓለም የጤና ድርጅትና በሁለትዮሽ ግንኙነቶች ልምዷንና ድጋፏን አካፍላለች። በሚጠበቀው መጠንና ደረጃ ባይሆንም በተናጠል ከሚካሄድ የብቻ ትግል ይልቅ፤ በመደመር የሚፈጠር ኅብረት ታላቅ ዋጋ ያለው መሆኑን ዓለም ወረርሽኙን ለመከላከል ትምህርት የወሰደባቸው የቻይናና የኮሪያ ተሞክሮዎች ምስክር ናቸው። በዓለም የጤና ድርጅት አማካኝነት በኢኮኖሚ የገፉት ሀገራት ብቻ ሳይሆኑ በኢኮኖሚ ወደኋላ የቀሩትም ሀገራት፣ ስለወረርሽኙ ወቅታዊና ወጥነት ያለው መረጃ፣ ሞያዊ ምክርና መመርመሪያ መሣሪያ አግኝተዋል። ለጊዜውም ቢሆን በአጋጣሚ አፍሪካ በበሽታው በከፋ ደረጃ የተጠቃች አለመሆኑ በጅቷታል። በጣልያን፣ በስፔንና በአሜሪካ ያጋጠመውን ያህል ወረርሽኙ በአፍሪካ ጉዳት ቢያስከትል ኖሮ ቀውሱ ከዚያም በላይ የከፋ ይሆን ነበር።

ለስፔንና ለጣሊያን የደረሱላቸው በድንበር የተሣሠሯቸው አውሮፓውያንና ምዕራባውያን ሳይሆኑ የሩቅ ምሥራቋ

ሀገር ቻይና ነበረች። በአውሮፓ እምብዛም ያልተነዱ ብዙ ሀገራት ነበር። ሆኖም የቻይናውያን ሐኪሞች ቀድመው ሞት ወዳጠላበት መንደር በድፍረት መዝመታቸው ግርምትንና ትዝብትን የፈጠረ ክሥተት ነው ቻይና ለኒውዮርክም ተርፋለች። ታላቋ አሜሪካ የመሣሪያና የግብዓት ድጋፍ ከሶሻሊስቷ ሩሲያ ሲቀርብላት ከምስጋና ይልቅ ብዙ ማብጠልጠል ተሰምቷል። በቅኝ ግዛት ታሪካቸው በቋንቋና ባህል ከተሣሠሩን አውሮጳውያን ይልቅ ለአፍሪካውያን እገዛ ይዞ ቀድሞ የደረሰው፣ በኢትዮጵያ መንግሥትና በአሊባባው ባለቤት መካከል በተፈጠረው ትብብር የበቀለው የድጋፍ እጅ ነበር።

ይህ ወረርሽኝ የእውነተኛ ወዳጆች መፈተኛ ብቻ ሳይሆን ሀገራትና ሰዎች ልዩነታቸውንና የቀደመ ቁርሿቸውን ወደ ጎን በመተው ከሁሉ የከበረውን የሰውን ልጅ ሕይወት ለማትረፍ ታላቅነታቸውን የሚያሳዩበት ልዩ ዕድል መሆኑም ነው። የሚደረገው ነገር ትልቅነት ብቻ ሳይሆን ለማድረግና ከጎናችሁ አለን ለማለት የምናሳየው በጎ ፈቃደኝነት የሚፈተንበት ጊዜ ነው። የሀገራችንን በጎ ፈቃድና የተጽዕኖ ፈጣሪነት ሚና ለአፍሪካ ወንድሞቿ የክፉ ቀን ድምፅና ፈጥኖ ደራሽ በመሆን፣ በችግር ውስጥ እንኳ ሚናዋን የማትረሳ መሆኗን ዳግም አስመስክራለች። ይህ ሚናዋ ቫይረሱ እስኪሸነፍም ሆነ በድኅረ ኮሮና የመልሶ መቋቋሚያ ወቅት ተጠናክሮ የሚቀጠል ይሆናል። በመደመር ስሌት ውስጥ እንደማገርና ምሰሶ የሚቆም እንደ ጠረጴዛና ወንበር ቤት የሚያደምቅ ብቻ ሳይሆን፤ እንደ ሚስማርና ሙጫ የተበታተነውንና የተፍረከረከውን የሚያያይዝ ስውር ተደምሮ ደማሪ እጅ ያስፈልጋል።

መጪው ትውልድ የሚረከባት ዓለም ሰላሟ የተጠበቀ፣ አየሯ ለኑሮ የተመቸ፣ በወረረሽኝ የማትናጥና የማትሸበር እንድትሆን ሀገራት በየግላቸው ሊገነቡት የሚገባ ጠንካራ ሥርዓት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሠመረ የጤና ሥርዓት ለመፍጠር፣ የመደመርን እሳቤና ስሌት የግድ ከሚል ምዕራፍ ደርሰናል። የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ማንቂያ ደወልና ሁነኛ ዕድል ሊሆን ይገባል።

ኢትዮጵያውያን ከኮቪድ በከፋ ፈተና ውስጥም አልፈው የማሸነፍና የመሻገር ልምዱም ዐቅሙም እንዳላቸው ተጠራጥሬ አላውቅም። የዓለም አቀፉ የጤና ድርጅት ዳይሬክተር ጀኔራል ወንድሜ ዶክተር ቴዎድሮስ አድኃኖም እንዳለው፤ "ኮሮና ቫይረስን በብልኀት ከመጋፈጥ ይልቅ በፍርሃት መሸሹ የበሽታውን ያህል አደገኛ ነገር ነው። የእኔም እምነት ይኸው ነው። በበሽታው ሳንሸበርና ሳንሸነፍ፣ መሥራት ያለብንን ሥራ ሁሉ ተባብረን እንደ አንድ ሀገርና አንድ ሕዝብ ሆነን፣ በመደመር ስሌት በደካማ ጎናችን ተደጋግፈን፣

በጠንካራ ጎናችን ሌሎችን እያገዝን፣ ታሪካችንን የሚመጥን ሥራ መሥራት ይኖርብናል። እንደማንኛውም ያለፉ ታላላቅ ወረርሽኞችና የሰው ልጆችን በጨለመ ዘመን የከተቱ ዓለም አቀፍ ችግሮች ኮቪድ 19ም ጊዜውን ጠብቆ መሄዱና ታሪክ መሆኑ አይቀርም። ምናልባት በጥቂት ወራት ወይም ከዚያ በላይ። ምናልባትም ከቻይና፣ ከጣልያንና ከአሜሪካ ተመጣጣኝ፣ የከፋ ወይም ያነሰ ጉዳት አድርሶብን ሊሄድ ይችላል። ወረርሽኙ ከመከሠቱ በፊት ቅድመ ቀውስ፣ ሙሉ ወረርሽኙ ሲከሠት ደግሞ በቀውስ ውስጥ፣ በመጨረሻም ከቀውሱ በኋላ በድኅረ ቀውስ የማገገም ሂደት ውስጥ ማለፋችን አይቀርም። በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ ትብብር፣ መተሳሰብ፣ ማካፈል፣ ለራስና ለሌሎች መጠንቀቅ ይገባናል። ይህ ወረርሽኝ አብረን ተደምረን የገባንበት የሰው ልጆች ችግር መሆኑን በመረዳት፤ ከቀውሱ ወጥተን እንደገና በተሻለ ጥንካሬና ብልጽግና ሀገርና

ሕይወት እንዲቀጥል ከመደመር ስሌትና መንገድ ውጪ የተሻለ የስኬት ጎዳና አይታየኝም።

በኢኮኖሚ ድህነታችንና በቴክኖሎጂ ኋላ ቀርነታችን ዋናው ዕንቅፋት ሊሆን አይችልም። ዕንቅፋት ሊሆን የሚችለው ያለንና የሆነውን ደምረን ኮቪድ ዓለምን ያንበረከከበትን የመደመር መንገድ በላቀና ቫይረሱን ሊረታ በሚችል መንገድ ለመደመር አለመቻላችን ነው። የዓለም ሕዝቦች ከተባበርን በቂ ሀብት፣ የተትረፈረፈ ዕውቀትና መላ፣ ሁሉን የሚችል ፈጣሪን ከጎናችን ማሰለፍ እንችላለን። ሀገራችንም ይህ ችግር መነሻዋ እንጂ መውደቂያዋ ሊሆን አይችልም። ከራሳችን አልፈን ለሌሎች መትረፍን የምንማርበት፣ በዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ከተለመደው ውጪ ከበጎነትና ከማካፈል፣ ከጠንክሮ መሥራትና ከመተባበር የሚመነጭ አዲስ የብልጽግና መንገድ እንዳለ ማሳየት እንችላለን። የቫይረሱ ጥንካሬ ያለው በእኛ ድካም ውስጥ ሲሆን፣ መፍትሔውም የሚገኘው ተደምረን በምንፈጥረው አብሮ የመቆምና የማሸነፍ ስሌት ውስጥ ነው።

# በእጅ ያለ አረንጓዴ ወርቅ!

በአንዲት ይጀመራል የሺሕ ማይል ጉዞ ፣

ወደ ኋላ የለም ዕርፍን በእጅ ይዞ፤

የዋህ ማዶ ያያል ዐይኑ እየማለለ፣

ወርቅ፣ ብር፣ አልማዙ እግሩ ሥር እያለ፤

ግን ... ተደበላልቆብህ ሜዳው ከገደሉ፣

የመለወጥ ምስጢር ከጠፋብህ ውሉ፣

ባዶ መዋተት ነው፣ ከንቱ ምኞት ሁሉ።

ላገር ለሰፈርህ ቢታጣለት አቻ፣

ጎጆህን ብትቀልስ ከባሕር ዳርቻ፣

ዓሣ ሳታሠግር መረብ ሳትዘረጋ፣

ልመና ጸሎትህ ቢመሽም ቢነጋ፣

መብላት ብቻ ሆኖ መሥራቱ ካቃተህ፣

ጠጠር ትለቅማለህ፣ አልማዝ ላይ ተኝተህ።

ተፈጥሮን እያደነቅሁ በእግር መጓዝ እወዳለሁ። እንጦጦና ዙሪያ ገባው ወትሮም ደስ ይለኛል። ጫካውን ሰንጥቄ በእግሬ መሄድና ከተራራው አናት ላይ ወጥቼ የአዲስ አበባን ዙሪያ ገባ ቁልቁል ማማተር የሚፈጥርብኝን ስሜት ልረዳው እንጂ በቃላት ልገልጸው ይከብደኛል። በአዕዋፉ ዝማሬ ተከብቤ ቀዝቃዛውን ንጹሕ አየር እያጣጣምኩ ጥቂት ደቂቃዎችን ሳሳልፍ ነፍሴ በሐሴት ትሞላለች። ተከማችቶ የተጫነኝን ውጥረት ሰብሬ ለመውጣትና መንፈሴን እንደገና ለማደስ ሲያምረኝ፣ ከአዲስ አበባ አፋፍ ላይ አረንጓዴ ሸማውን ተከናንቦ በጸጥታና በርጋታ ወደ ተቀመጠው ወደ ሸማግሌው የእንጦጦ ተራራ እወጣለሁ።

አንድ ቀን ታዲያ ይህ ፍላጐ ጠንክሮ ሲመጣብኝ ብድግ ብዬ እንጦጦ አናት ላይ ፡ ሁሉም እንዳለ ነው፤ ልክ እንደ ድሮው። የከተማው ጩኸት ያላወከው ረጭ ሰለ ጫካ በማስኖች ጭስ ያልተበከለ አየር፣ ሣር ቅጠሉ፣ የአዕዋፉ ዝማሬ ምርጥ በዚቃ ተማሪዎችን ያስንቃል። ቆዳን የሚሸነቁጠው ቅዝቃዜ ዛሬም ሞቃቱን ከተማ አቀዘቅዛለሁ ብሎ ይደክማል። ማለዳ ላይ ያ ሸማግሌ ተራራ የነጭ ጉም ጋቢ ይለብስና አዳሩን ወደ የካ አቅጣጫ ዘርግቶ፣ከተማውን ይታዘባል። ምሽት ላይ ደግሞ በውርጩ እየተጋረፈ አካባቢውን ጸጥ ያደርገዋል።

በቅዝቃዜ የተሞላውና የምንጮች መፍለቂያ የሆነው እንጦጦ፣ ንጹሕ የመጠጥ ውኃ እጥረቱ እንዳለ ነው። ለዚህም ሳይሆን አይቀር አዲስ አበቤው ከእንጦጦ ራስጌ አፈግፍጎ፣ ጎጆ ኑሮውን ከግርጌው ፍል ውኃውን ከብቦ የከተመው። ሰዎች ስንባል ራስን ከተፈጥሮ ጋር ከማስማማት ይልቅ፣ ምቾትን ወደሚሰጠን መጠጋቱን እንመርጣለን። ችግሮቻችንን ራሳችን ከመፍታት ይልቅ በተፈጥሮ ኃይል ተቀርፈው የሚጠፉበትን መንገድ ማማተራችን የቆየ ልማዳችን ይመስለኛል።

ቴክኖሎጂንና ልዩ ልዩ ችግር ፈቺ አሠራሮችን በመፍጠር ከትውልድ ወደ ትውልድ እያሻሻሉ አሳድጎ መጠቀም ላይ እምብዛም ነን። ከሦስት ሺህ ዘመን ጀምሮ ዛሬም የምንጠቀምበት የግብርና አሠራራችን ለዚህ ጥሩ ማሳያ መሆን ይችላል። ሩቅ ሳንሄድ እዚሁ ከእንጦጦ ወረድ ብለን ሽሮ ሜዳ የሚሸጡት የሚያማምሩት ውብ አልባሳትን እንይ። ዛሬም ድረስ የሚዘጋጁት ጥንት ቅድመ አያቶቻችን በጀመሩት ማዳወሪያና የሸመና መሣሪያዎች ነው። ምንም ያህል የአሠራር ማሻሻያ ሳይደረግበት፣ ዛሬም በእኛ ዘመን ሚልዮን ዜጎቻችን ለዕለት ጉርሳቸው የሚዳክሩበት የሥራ ዘርፍ ሆኖ ቀጥሏል።

የቀደምት አያቶቻችን ጥበብ የተገለጠበት በመሆኑ ሊያስደስተንና ሊያኩራራን ይችል ይሆናል። ነገር ግን

ያለምንም መሻሻል ዘመናትን መሻገሩ ለእኔ ትውልድ ሰዎች፣ በተለይም ዐውቀናል ተምረናል ለምንለው አንገታችንን አስደፍቶ የሚጎትት ቋጥኝ መሆኑ አይካድም። አያቶቻችን ተመልሰው ቢመጡ ምነው ትንሽ እንኳን ሳታሻሽሉት? ከእኛ በኋላ ሥራም አልሠራችሁ? ሳይሉን አይቀርም።

የእንጦጦ ተራራ እኛ ሀገር በመገኘቱ ሳይበደል _ አልቀረም ብዬ እንዳስብ የተገደድኩባቸው አጋጣሚዎች ቀላል አልነበሩም። በሌሎች ሀገራት ቢሆን ከትልቅ ከተማ አጠገብ ያለ እንደ እንጦጦ ያለ ውብ ተራራ እንዲህ ችላ ሊባል አይችልም። ከፍተኛ ሙዓለ ንዋይ ፈሰስ ተደርጎበት፣ ቀን ከሌት የብዙዎች ቀልብ የሚያርፍበት መናፈሻ ወይም ጎብኝዎች የሚያዘወትሩት ሪዞርት፤ ሕዝብ የሚተራመስበት ስፍራ ይሆን ነበር። ብስክሌትና ስኩተር የሚነዱ፣ በእግራቸው የጤና ጉዞ የሚጓዙ፣ ሶምሶማ የሚሮጡ፣ ዛፎቹ ሥር ዐረፍ ብለው የሚዝናኑ አያሌዎች እንደ ጉንዳን እንጦጦ ሥር ውር ውር ይሉ ነበር።

በተለያዩ ጊዜያት በጎበኘኋቸው ሀገሮች ልዩ ልዩ ፓርኮችን አይቻለሁ። በእነርሱና በእንጦጦ መካከል በምናቤ ቀዘፍኩ፤ አነጻጸርኳቸው። እዚህ ተቀብሮ ያልወጣው እምቅ ሀብታችን አለ፤ ከማዶ ደግሞ በተንጣለለው አድማስ ላይ የተካነ ሠዓሊ የከተባት የምትመስለው አዲስ አበባችን ትንፏለላለች። እዚህ በሸማግሌው ተራራ ውስጥ ሀብት ብሉኝ ብሉኝ ይላል። እዚያ በደመቀችው ከተማ ውስጥ ድህነት ዙፋኑን አንሰራፍቶ ብዙዎችን አንገት ያስደፋል። በቁጭት እያነጻጸርኩ አጤንኩት። ከቆጠቆጠኝ የውስጥ ስቃይ ለመላቀቅ እየሞከርኩ፤ “መቼም ትናንትን መመለስ አይቻልም” በማለት ወደ ኋላ ማምረሬን ተዉኩ። ትኩረቴን ወለል ብሎ ወደ ተከፈተ የዛሬና የነገ ዕድል ለማዞር ሞከርኩ። “አዎን! የፈሰሰ ውኃም መልሶ አይታፈስም።

ከኢጅ ያመለጠ ጊዜ ዳግም አይመለስም። ያልተሰፈረ ሀብታችንንና ዛሬያችንን በሙሉ ዐቅም መጠቀም እንጂ የባከነው ዕድልና ትናንትናችንማ ላይመልስ ሄዷል። ነገም ካልሠራንበት ባዶ ሕልም ነው። ነገ ፣ ነገ ስለሆነ ብቻ አያስተማምንም። ብቸኛው የሚጨበጥ ሀብት በእጃችን ያለው ዛሬና የተሸከመው ዕድል ብቻ ነው” ብዬ ቆም _አልኩ። ከበላዬ የሚንጫጩት ወፎች በሐሳቤ ሳይስማሙ አይቀሩም፤ ግር ብለው አንድ ላይ ተነሡና ወደ ሰማያት መጠቁ። በዚህ መሐል ልጅ ሆኜ የሰማኋት አንዲት ታሪክ ትዝ አለችኝ።

አንድ ገበሬ እጅግ የምታምር ወፍ በእጁ ይዞ ጨፍልቆ ሊገድላት ጨመቃት። ከመግደልህ በፊት ሦስት ነገሮች ልንገርህ አለቺው። ሰማት። “አንደኛ በእጅህ ያለውን ሀብት በአግባቡ ሳትጠቀምበት በከንቱ አትልቀቀው። ሁለተኛ ስለአለፈው ነገር ሁሉ እየተበሳጨህ ጊዜህን በከንቱ አታባክነው፤ ኪሳራ እንጂ ትርፍ የለውምና” አለችና ዝም አለች። ገበሬውም የመጨረሻውን ምክር እንድትነግረው ሲጠይቃት፤ ሦስተኛው ከራሱ አልፎ ለልጆቹ የሚጠቅም ምክር በመሆኑ እስከ አልለቀቃት ድረስ እንደማትነግረው ገለጸችለት። ገበሬው ለመስማት ጓጉቶ ሲለቃት የመጀመሪያዎቹን ሁለት ምክሮች እንዲያስታውሳት ጠየቀችው። በፍጥነት መልሶ ነገራት። ከዚያም “በእውነቱ አልተሳሳትክም። ነገር ግን ገና ምንም ለአልጨበጥከው ምክር ስትል የጨበጥካቸውን ጠቃሚ ምክሮች በአግባቡ አልተጠቀምክባቸውም። ለማንኛውም ሆዴ ውስጥ ለልጅ ልጆችህ ጭምር የሚበቁ እጅግ የከበሩ ዕንቁዎች ያሉ ሲሆን ምክሬን ባለመጠቀምህ አመለጠህ። የመጨረሻው ምክር ላልከኝ

አዎ! ሦስተኛው ምክር የሁለተኛው ድጋሚ ነው። በል ስላለፈው ነገር በመቆጨት ጊዜህን በከንቱ አታባክን" ብላው ከዐይኑ ተሰወረች። እርሱም ድህነቱን እንደታቀፈ ቀረ። እጅግ ከፍተኛ ገቢ ልናገኝባቸው የሚያስችሉን እያሌ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ሀብቶች አሉን። የቱሪዝም ዐቅማችንን ብቻ ብናይ በዓመት በብዙ ቢሊየን ዶላሮች የሚቆጠር ገቢ ማግኘት የሚያስችለን ነው።

በተለይ በሰው ሠራሽ ታሪካዊ ቅርሶች በኩል ከግብጽ በስተቀር የትኛውም አፍሪካዊ ሀገር አጠገባችን ሊደርስ አይችልም። ዳሩ ግን በቱሪዝም ገቢ ከአፍሪካ እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሚመደቡ ሀገራት ውስጥ ነን። ከቅርሶቻችን ባለፈ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ተፈጥሯዊ እልፍ ሀብቶች እያሉን መቸገራችን ይደንቃል። ድህነታችን ቅንጡ ድህነት የሚያሰኘውም ይሄ ነው። ሀብት ላይ ተኝተን የደኸየን ነንና።

ነዳጅ በበቂ ላይኖረን ይችላል። የከበሩና ለጥሬ ዕቃነት የሚውሉ ማዕድናትን ወደ ምርት ማስገባት የሚያስችል የኢኮኖሚ ዐቅም ገና በመገንባት ላይ መሆናችን ይታወቃል። አምራች ኢንዱስትሪውና በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የሚታገዘው ግብርናችን ያን ያህል ጠንካራ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ሆኖም ግን ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ሀብቶቻችን ሞልተውና ተርፈው በየሰፈራችን አሉ። አመለካከታችንን ከቀየርን፣ አሠራራችንን ካስተካከልን፣ ጥቂት ዕሴቶችን ከጨመርን፣ በማንኪያ አውጥተን በጭልፋ ማፈስ በቻልን ነበር።

ሀብቶቻችንን ማጥናትና ማልማት ከቻልን ያለን ሀብት ከነዳጅና ከወርቅ ቢበልጥ እንጂ አያንስም። አሉን እያልን ከመኩራት በዘለለ ጥቅም እንዲሰጡ ወገባችንን ታጥቀን ከሠራን፣ ያለ ጥርጥር ጢስ የማይለቁ ግዙፍ ኢንዱስትሪዎች መሆናቸው አይቀርም።

"ቤት ሲሠሩ በቅድሚያ መሠረቱን መጣል፤ ወደ ቤት ሲዘልቁ በቅድሚያ በሩን መክፈት" ተገቢ ነው። ለመላው ሀገራችን የቱሪዝም መስሕቦች መሠረትና በር በመሆን የምታገለግለዋ አዲስ አበባችን በመሆኗ እርሷን የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ ማበጃጀት እንደሚገባ ከበፊቱ ይልቅ ጎልቶ ታየኝ። ይሄንና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን እያብሰለሰልኩ እንደተለመደው በእንጦጦ ተራራ ላይ ታች እላለሁ። አወጣለሁ፤ አወርዳለሁ። ከራሴ ጋር እወያያለሁ፤ እሟገታለሁ፤ እለካለሁ እቆርጣለሁ።

እንጦጦ ላይ የተከማቹትን ዕንቁ ዕድሎች በእደ ልቦናዬ ጨብጬ ተራራውን ቀስ እያልኩ ወረድኩ። ይህ ሐሳብ ዘር ሆኖ ለመብቀል፣ ችግኙም ትክክለኛ መሬት አግኝቶ _ አበባና ፍሬ እስኪያወጣ ጊዜ አለፈ። ጊዜ በጊዜ ተተክቶ ብዙ ነገር ተቀያየረ። እኔም _ ሕልሜን እንደያዝኩ ወደ ሐላፊነት መጣሁ። የቀደሙ ሐሳቦችን ወደ ግብር የመለወጫው ጊዜ መጣ። እንጦጦም ከተደበቀበት የአእምሮዬ ጓዳ ብቅ አለ። የለውጡ ወላፈን ግለቱ መልክ መልክ እየያዘ ሲመጣ ለውጡ የፖለቲካ ከመሆን የኢኮኖሚ ወደ መሆን መሻገር እንዳለበት ግልጽ ነበር። ለውጡ ደግሞ የሚጀምረው ከመንግሥታችን መቀመጫ ቢሮ፣ የአራት ኪሎ ግቢ እስከ እንጦጦ ተራራ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ዳር፤ ከኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ በኩል እስከ ሰሜን፣ ምዕራብና ደቡብ አፍሪካ መሆኑን ተረድተን ነበር። ነገሩ መጀመሪያ ሲታሰብ መያዣና መጨበጫ የሌለው ይመስል ነበር። አስቀድሞ በምናቤ የተሣለውና ደጋግሞ ሳወጣውና ሳወርደው በኖርኩት ሐሳብ ላይ የፈጣሪ እገዛና የባልንጀሮቼ አብሮነት ተጨመረበት። ያን ጊዜ ወደ ተግባር ለመግባት መዋልና ማደር አላስፈለገንም።

እንጦንጦን ጨምሮ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ አካባቢዎችን ስለመቀየር ተነጋገርን። ከተማችን የሀገራችን እምብርት በመሆኗ በሌሎች የክልል ከተሞች ላይ የምትፈጥረው አዎንታዊ መነቃቃት ቀላል እንዳልሆነ አሰብንበት። በእርግጥ ፕሮጀክቱን እውን ለማድረግ የገንዘብ ጉዳይ ትልቁ ራስ ምታት መሆኑ አልቀረም። ያም ሆኖ በበቂ ከታሰበበት ለእርሱም መፍትሔ ለመስጠት የተለያዩ መንገዶች አይጠፉም። በሀገራችን ለፕሮጀክቶች የሚመደብ ገንዘብ ከማጣት በላይ ችግራችን የፕሮጀክት ዝርክርክነትና ጀምሮ ያለመጨረስ አባዜያችን ነው። ገንዘብ ከማግኘታችን በላይ ዝርክርክነትን እንዴት እንደምናስቀርና ባልነው ጊዜ ጀምረን እንዴት እንደምንጨርስ ይበልጡን አሰብኩበት።

ብዙ ምራቅ የሚያስውጡ የፕርጅት ሐሳቦች ከተነደፉ በኋላ በታቀደላቸው ጊዜ ያለመጠናቀቃቸውና ለዝርፊያ አመቺ መንገድ መፍጠራቸው ሀገራችንን ሀብ አክስሯታል። ብክነትና ዝርዝርክነትን እናስወግድ፤ በጊዜና በጥራት እንጨርስ፤ እነዚህ ነገሮች ዋና የሥራ መርሖቻችን እንደሚሆኑ ተግባባን። የአንድነት ፓርም በሊህ መንፈስ ነበር የተጀመረው። ይህ ቤተ መንግሥት ከተቆረቆረ አንድ መቶ ሃምሣ ዓመት ያህል ሆኖታል። ከዐፄ ምኒልክ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ድረስ መሪዎች ኖረውበታል። ሠርተውበታል፣ መርተውበታል። ግቢው የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ዋና መናኸሪያ ሆኗል። የሀገሪቱን ገጽታ የቀየሩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ወታደራዊ ውሳኔዎች ተወስነውበታል። በዚህ ብቻ እንኳን ግቢው የተለየ ትኩረት ሊያገኝ ይገባል።

ከአርባ ሄክታር በላይ ስፋት ያለው ይኸ ግቢ፣ በአፍሪካ እጅግ ጥቂት ከሆኑ ከመቶ ዓመታት በላይ በአንድ ቦታ የተለያዩ መሪዎች ከመሩባቸው አብያተ መንግሥታት አንዱ ነው። ያውም ብዙዎቹ አብያተ መንግሥታት በቅኝ ገዥዎች በተሠሩባት አፍሪካ የእኛው ቤተ መንግሥት ልዩ ትርጉም ማግኘቱ ምንም አያጠያይቅም። ቢያንስ ቢያንስ ከመቶ ሃያ ዓመት በላይ የተከማቸ የመንግሥት መዝገብ ያለበት ታሪካዊ ቦታ ነው። ያልተሰረዙና ያልተደለዙ የሀገርን ታሪክ እንዳለች የሚያስቀምጡ ብዙ መዛግብት በግቢው ይገኛሉ። ቀደምቶቻችን ሲገለገሉባቸው የነበሩት ዕቃዎች፣ ልዩ ልዩ መሣሪያዎችና የቤቶቹ አሠራር በየራሳቸው የሚናገሩት ጥበብ ቀላል አይደለም። ብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገራት እንኳንስ ቤተ መንግሥቶቻቸው ይቅርና መላ ታሪካቸውም ከቅኝ ግዛት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ በመሆኑ እነርሱነታቸውን ከአውሮፓውያን የቅኝ ግዛት ትርከት ለመፈልቀቅ ኢያሌ የቤት ሥራ ይጠይቃቸዋል። በዚህ በኩል እኛ ዕድለኞች ነን ለማለት ይቻላል። ስለማንነታችን ለማወቅ ብቻ ሳይሆን ከስሕተቶቻችንም ለመማር የሚያስችሉ ሕያው ምስክሮች ቤተ መንግሥታችን ውስጥ ተቀምጠው የእኛን ቀልብ ይጣራሉ።

እስር ቤቱ፣ ግርፋትና ግድያ የተፈጸመባቸው ስፍራዎች፣ ሀገር ያጠፉ ውሳኔዎች የተወሰኑባቸው ወንበርና ጠረጴዛዎች የታሪካችንን ብጉርና ማድያት እንዳለች ይዘዋት ይገኛሉ። ግቢው ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥት ሲሞከር ታዝቧል፤ የባለ ሥልጣናት ድግስና ፌሽታ ብቻ ሳይሆን የባለሥልጣናቱ ተኩስና ዋይታ የሚሰማበት

አስፈሪ ማዕከል ሆኖም ያውቃል። የአብዮቱ ሰዎች ምሳና ቁርስ ሆነውበታል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ጨምሮ ብዙ የፖለቲካ ሰዎች አዛዥ ናዛዥ እንዳልሆኑበት መልሰው ታስረውበታል። በተለምዶ ስድሳዎቹ የሚባሉት የቀድሞ ባለሥልጣናት ከሰባት ዓመታት በላይ ታስረውበት ነበር። በነገሥታቱ ዘመን የምግብና የመጠጥ ማቀዝቀዣ የነበረው ስፍራ በአብዮቱ ዘመን የእስረኞች ማሠቃያ ሆኖ ያውቃል። ግብር እንደተበላበት ሁሉ ብዙዎች ተበልተዉበታል።

ተራማጅ ነኝ ባዩ የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂዎችን፣ ዴሞክራት ነኝ የሚለው የቀድሞ አምባገነኖችን መቀጣጫ አድርጎበታል፤ በዚሁ በአራት ኪሎው ቤተ መንግሥት። ግቢው ሲገቡበት ከውጭ እንደሚፈሩት ዓይነት አይደለም። ውስጡ አሳዛኝ ነው። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ፣ ከሁለቱ የጉባኤ አዳራሾችና ከዙፋን ቤቱ ውጭ ያለው ስፍራ እንኳንስ ሌላውን ሊያስፈራራ ራሱ ቁዘማ ላይ ነበር። የሰዎችን ዐይን መናፈቁን ገና ሲገቡበት ጮኾ ይናገራል። ዋና ከተማ ላይ የተተከለ፣ ለዚያውም የሀገሪቱ ቁንጮዎች የኖሩበት አካባቢ አይመስልም። በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ቤተ መንግሥትን ያህል ግቢ ወና ወና እየሸተተ ዞር ብሎ ለማየት አለመድፈር ከማስተዛዘብ በላይ ነው። ባለቤቶቹ ሸሽተዉት፣ ነዋሪዎቹ ከድተዉት፤ አስተዳዳሪዎቹ ረስተዉት፤ ሀብት ሲጠፋ ምን እንደሚመስል ማሳያ ሆኗል።

የቀድሞው ቤተ መንግሥት፣ ዙፋን ቤቱ፣ የግብር አዳራሹ፣ ዕንቁላል ቤቱና ሌሎችም ለዐርባ ዓመታት ያህል ሸረሪት ድሩን እያደራባቸው ቆይተዋል። የሕዝብ ዐይን እስከ አልዳበሳቸው ድረስ በጉያቸው ምን ታሪክ ቢያዝሉ ግርማ ሞገስ ብሎ ነገር የለም።

ነዋሪዎቻቸው በችግር ምክንያት ጥለዋቸው የተሰደዱ የጥንት ከተሞች መስለዋል። ሰፊው ግቢ በሆድ ዕቃው ይዟቸው የነበሩት ጉዶች እንኳንስ ለመግለጽ ለማየትም ይከብዳሉ። በዳዋ የተዋጡ፣ እርስ በርሳቸው ተዛዝለው ከዛሬ ነገ እንውደቅ አንውደቅ የሚባባሉ፣ በቆሻሻና በፍራሽ የተሞሉ የቆርቆሮና የጭቃ ቤቶች ሞልተውታል። ቤቶች በጨረቃ የተሠሩ የድኾች መጠለያዎች እንጂ በቤተ መንግሥት ግቢ ውስጥ የሚገኙ አይመስሉም። አንዳንዱ የግቢው ክፍል የሰው እግር ከረገጠው ሃያና ሠላሳ ዓመት አልፎት ነበር። ሌላው ቀርቶ በቅጡ የተሠራ የፍሳሽ ማስወገጃና የውኃ መውረጃ እንኳን አልነበረውም። ሽንት ቤት ውስጥ ተወልዶ እዚያው የሚያድግ ልጅ መጥፎ ጠረኑ መቼም ላይሰነፍጠው እንደሚችለው ሁሉ፤ እንዲህ በድሪቶ ከተሞላ ግቢ ውስጥ የሚፈልቅ ድሪቶ አስተሳሰብ ሀገርን ወደፊት ያራምዳል ማለት ዘበት ነው።

የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ዋና ከተማ ውስጥ ኑሯቸውን እንደማድረጋቸው በመላ ሀገሪቱ ከሚኖሩ ሕዝቦች በተሻለ ለብዙ መሠረተ ልማቶች ቅርብ ናቸው። አብዝቶ ይቸግራቸዋል ከተባለም በዋናነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ችግሮች መካከል ከነዋሪዎች ቁጥር ማሻቀብ ጋር ተያይዞ የድምፅ ብክለት እና ፍሳሾች የሚፈጥሩት መጥፎ ጠረን ከግንባር ቀደም ችግሮች ተርታ መመደባቸው አይቀርም። ልጆችና ወላጆች አብረው የሚሄዱበት፣ ዕውቀት ከተዝናኖት የሚያገኙበት ስፍራ የለም ማለት ይቻላል። ገንዘብ ያላቸው የውጭ ምንዛሬ አውጥተው ዱባይና ሞምባሳ ይሄዳሉ። በከተማዋ ውስጥ የተረፈችው ጥቂት መተንፈሻ ስፍራ ቤት ተሠርቶበት ወይም

ወንዙ በመጥፎ ጠረን ተበክሎበት መሄጃ የሚያጣውን ነዋሪ ብዛት ቤት ይቁጠረው፡፡

መጠነኛ ማስተካከያዎች ቢደረጉበት ዐይነ ግቡ መሆን የሚችል ግዙፍ ግቢ በቤተ መንግሥት ስም መሐል አዲስ አበባ ተንጣሎ ይገኛል፡፡ ከግርጌው መስቀል አደባባይ አለ፡፡ መሐል ላይ የአፍሪካ አባቶች አፍሪካን ነጻ ለማውጣትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ለመመሥረት የተሰበሰቡበት ታሪካዊ አዳራሽ ይገኛል፡፡

ከአፍሪካ አዳራሽ ማዶ በአስደናቂ ታሪካዊ ቅርሶች የተሞላው ኢዩቤልዩ ቤተ መንግሥት አለ፡፡ በመንገዱ መካከል እነዚያ የአፍሪካ ቀደምት መሪዎች የተከሏቸው ዛፎች አሉ፡፡ ሕዝባዊ መናፈሻዎች ሞልቶ የተረፈን ይመስል ዛፎቹ ያሉበት ሥፍራ ታጥሮ ተቀምጧል፡፡ ከቤተ መንግሥቱ ራስጌ አብያተ ክርስቲያናት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ሙዝየሞች፣ የባህል ልብስ መሸጫዎች እና በመጨረሻም ባለ ግርማ ሞገሱ እንጦጦ አለ፡፡

ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት የመጣሁ ሰሞን ያው በእግር መዘዋወር ስለለመደብኝ በግቢው ውስጥ ዞወርወር እያልኩ እንድመለከተው አደረገኝ፡፡ ከባልደረቦቼ ጋር ገደሉን እየዘለልን፣ ጥሻውን እየጣስን፣ የፈራረሱትን ግድግዳዎች እየታከክን፣ ተዘግተው የኖሩ ሕንጻዎችን እያስከፈትን፣ ከነባር የግቢው ጠባቂዎችና ሠራተኞች ስለምንነታቸው እየጠየቅን መረዳት ቻልን፡፡ በዚያ ያለውን ሀብት ማወቅ ያስደስታልም፤ ያሳዝናልም፡፡ ስፍራው በቤተ መንግሥት ስም ታጥሮ በመቀመጡ ተሸንሽኖ በግለሰቦች እጅ ከመግባት አትርፎታል፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ታሪካዊ ሕንጻዎች ክብካቤ ቢጎድላቸውም ህልውናቸው ጨርሶ እንዳይጠፋ ዕድል ፈጥሯል፡፡ በሌላ በኩል ምንም ዓይነት አገልግሎት አለመስጠቱ ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን ምንም ዕሴት ሳያክሉባቸው ይዞ ብቻ ማኖር እንደ መልካም ባህል ተቆጥሮ ወደ ቀጣይ ትውልድ መተላለፍ የለበትም፡፡ ቅርሶቻችንን ከመጠበቅ ባሻገር ዕሴት ጨምሮ የማልማትን አዲስ ባህል ለመፍጠር ተንቀሳቀስን፡፡ ደግሞም ተሳካልን፡፡

ሥራውን የጀመርነው ከቢሮ ነው፡፡ መርሐችንም ከቢሮ እስከ ሀገር የሚል ነበር፡፡ የትምህርት ባለሞያዎች የሚመክሩት አንድ ነገር አለ፡፡ ይኼውም ማንኛውም ነገር ከትንሽ ወደ ትልቅ፣ ከቅርብ ወደ ሩቅ፣ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከተራ ወደ ውስብስብ ሲጓዝ ቀና ይሆናል፡፡ ደግሞ እኛ በተደጋጋሚ የምንታማው ጀምሮ ባለመጨረስ ነው፡፡

ጀምረን በተገቢው መንገድ ፕሮጀክቶቻችንን ባለመጨረሳችን ምክንያት ሀገራችንን የጅምር ፕሮጀክቶች ዐውደ ርእይ _ አድርገናታል፡፡ ይህ በእኛ ላይ በፈጠረው የተነሣ ጠባሳ ፕሮጀክት ለመጀመር ባሰብን ቁጥር አብዝተን እንድንጨነቅ አድርጎናል፡፡

ይኽንን አዙሪት ለመስበር በብርሃን ፍጥነት ከምንለካው ርቀት መጀመር የለብንም፡፡ በክንድና በስንዝር ከምንለካው ነገር መጀመሩ የተሻለ ነው፡፡ መጀመሪያ የመቀመጫዬን እንደተባለው፡፡ ቀጥሎም ስለዘላቂነት ማሰብ እንጀምራለን፡፡ የምንሠራው ለእኛ ብቻ አይደለም፡፡ ከእኔ ትውልድ በኋላ የሚመጡ መሪዎች ያለ ሐሳብ ሊገለገሉበት እንዲችሉ ጭምር እንጂ፡፡ ቢሯችን በሕንጻ ሥራው ጥንካሬ የሚደነቅ ነው፡፡ ለዘመናዊ የመንግሥት አሠራር ግን ምቹ አልነበረም፡፡ ቢሮዎች እንጂ የመገልገያ ምቹ ሁኔታዎች አልነበሩትም:: ሌላው

ቀርቶ የመረጃና የግንኙነት መሥመር _ አዘረጋጉ ለዛሬው ዘመን በፍጹም አይመጥንም። ዝግ ልቦናን የሚፈጥር ዝግ ቢሮ ነው። የመንግሥትን ሥራ በተቀላጠፈ መንገድ ለማከናወን የሚያስችሉ ክፍሎች የሉትም።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤቱን ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ እንዲሆን አድርጎ ማስተካከል ተጀመረ። ድጋፍ ያደረጉልን አካላት ከአራት ወር በኋላ መጥተው አይተው ገንዘባቸው መልካም ነገር ላይ እንዳረፈ አምነው ተደሰቱ። በተገቢው ጥራት፣ ያለ ብክነትና ዝርክርክነት፣ በአጭር ጊዜ ማጠናቀቅ እንደምንችል ሠርተን አሳየን። አንዱ አዙሪት ተሰበረ። ይህ አጋጣሚ ለእኛም በቀጣይ ላቀረብናቸው የድጋፍ ጥያቄዎች መልካም ዕድልን ፈጠረልን። በአማረ መልኩ ቢሮው ዳግም መዘጋጀቱ የፈጠረው አዎንታዊ የሥራ መነቃቃት ደግሞ የበለጠው ትርፍ ሆነልን።

በትምህርት በኩል ከአየነው የጽሕፈት ቤቱን ሥራ በአራት ወራት ማጠናቀቃችን ብዙ ትምህርቶችን አስገኝቶልናል። ፕሮጀክቶቻችንን በተገቢው ደረጃና ጊዜ ለማጠናቀቅ ውሳኔ ብቻ አይበቃም። እንደ ሰጎን ዕንቁላል የቅርብ ክትትል ይፈልጋል። ሥራውን

እንደ ገቢ ማስገኛቸው ብቻ ሳይሆን እንደ ልጃቸው ሊያዩ የሚችሉ የሥራ ሐላፊዎች፣ ባለሞያዎችና ሠራተኞችን ከየአሉበት አፈላልጎ ማሰለፍ ይጠይቃል። ካልተከታተሉት የተፈረመ ሁሉ አይሠራም፤ የተመራ ሁሉ አይፈጸምም። ጽሕፈት ቤታችንን ባልነው ጊዜ፣ በሚጠበቅበት ደረጃ ስንፈጽም ቀጣዩ ሥራችንን ለማገዝ በሙሉ ልብ የሚነሡ ደጋፊዎች አገኘን። ለአንድነት ፓርክ ፕሮጀክት ጅማሮም በር ከፈተ።

የአንድነት ፓርክ ፕሮጀክት ተጀመረ።

መጀመሪያ ሥራውን ከነፍሳቸው የሚወዱ የሥራ ሐላፊዎችን በመብራት አፈላለግን። ቀጥለን የታሪክ አሻራ መተዉ የሚፈልጉ፣ የሞያቸውን መቅኔ ለሀገራቸው ለማፍሰስ የተዘጋጁ፣ ባለሞያዎችን አመጣን። በመጨረሻም ሰዓታቸው አልቆ ከዚያ ገለል ለማለት የማይጣደፉትን በተቃራኒው የሥራው ማለቅ የሚያሳስባቸውን ሠራተኞችን አሰባሰብን። ለወደፊት ትምህርት እንዲሆን፣ ድሮና ዘንድሮን ማሳየት እንዲችል፣ ግቢውን በበራሪ ማሽኖች (በድሮን) ታግዘን ቪዲዮ ቀረጽነው። የታሪክና የቅርስ ባለሞያዎች ታሪካዊ ነገሮችን ከሌሎች እንዲለዩ አደረግን። ታሪካዊ ሀብቶቻችንን መዝግበን ያዝን። ስለ እነርሱ አሠራር፣ አጠጋገን፣ ታሪክና አጠቃቀም ጥናቶችን አደረግን።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቤተሰቦች፣ ባለሟሎችና አገልጋዮችን አነጋግረናል። በደርግ ጊዜ እዚያ ግቢ የሠሩ ባለ ሥልጣናት፣ መኮንኖች፣ ሠራተኞችና ወታደሮችን አስተያየት ተቀብለናል። ከ60ዎቹ ግድያ የተረፉ እስረኞች የታሠሩበትን ቦታ አይተው ታሪካቸውን ነግረውናል። በኢሕአዴግ ዘመን በቦታው የነበሩ፣ የሠሩ፣ ባለሥልጣናትና ሠራተኞችን አማክረናል። መዛግብቱንና መጻሕፍቱን አገላብጠናል። የቀድሞ የድምፅና የቪዲዮ መረጃዎችን መርምረናል። በሀገሪቱ የታወቁ የታሪክ ምሁራንን አስተያየት ወስደናል። ከመላ ሀገሪቱ የተውጣጡ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጎብኝተው አስተያየታቸውን እንዲሰጡ አድርገናል። በዚህ መልኩ ሥራዎች እየተከናወኑ ሲመጡ ግቢው መጽዳት ጀመረ። በሥራው ወቅት አንዳንድ አስገራሚ አጋጣሚዎች

ይፈጠሩ ነበር። እዚህም እዚያም የሰው ዐጽሞች ይገኙ ነበር። ሕግ ያላወቃቸውና ታሪክ ያልመዘገባቸው የግፍ ድርጊቶች በግቢው መፈጸማቸውን ጮኸው መናገር የሚችሉ ሕያው ማስረጃዎች ናቸው፡

የግቢው ገደላገደል መሆን ምናልባትም በአመሠራረቱ ወቅት ስትራቴጂያዊ ጠቃሚነቱ ትልቅ ግምት እንደተሰጠው ይጠቁማል፤ ያም ሆኖ ለሥራችን መጠነኛ ተግዳሮት መፍጠሩ አልቀረም። የምንሠራው ሥራ ሦስት ነገሮችን አጣምሮ የያዘ ነበር። ታሪካዊ ሕንጻዎችን መጠገንና ለእይታ ማብቃት፣ ግቢውን ማጽዳትና ማስተካከል፤ እንዲሁም አዳዲስ ነገሮችን በግቢው ላይ መጨመር።

ግቢው አምስት ታሪካዊ ሕንጻዎች አሉት። ዕንቁላል ቤቱን ጨምሮ የዳግማዊ ምኒልክ ግቢ አለ፤ ከዚያም ፊት ለፊት ዙፋን ቤቱ ቆሟል። ከዙፋን ቤቱ በስተቀኝ ከመቶ ሃያ ዓመታት በላይ የተከማቹ መዛግብት ያሉበት የጽሕፈት ሚኒስቴር ሕንጻ አለ። ከዚያ አጠገብ ዙፋን ችሎት የጽሕፈት ሚኒስቴር ግቢ ጎረቤት ሆኖ ፊቱን ወደ ፓርላማው አዙሮ ይገኛል። ከዙፋን ቤቱ በስተግራ ደግሞ የግብር አዳራሹ አለ። እነዚህን ሕንጻዎች ጠግነን፣ የውስጥ ታሪካዊ ዕቃዎቻችን አሟልተንና ለጎብኝዎች ምቹ አድርገን ማዘጋጀት ይጠበቅብናል። ከግብር አዳራሹ አጠገብ የነበረው የወታደሮች ዳቦ ቤት መነሣት ነበረበት። ምክንያቱም ለግብር አዳራሹ የውበትም የደኅንነትም ችግር ፈጥሮበት ነበር። ዙፋን ችሎቱ ኮሎኔል መንግሥቱና በኋላም ሁለት ጠቅላይ ሚኒስትሮች ኖረውበታል። እርሱን በባለ አምስት ኮከብ ሆቴል ደረጃ አስይዞ መጠገንና ለእንግዳ መቀበያነት ማዋል መጠነኛ ሥራ ፈልጎ ነበር።

ከዕንቁላል ቤቱ ዙሪያ የነበረው ዳዋና ጥሻ መነሣት ሲጀምር ግቢው የብርሃን ውጋጋን እየፈነጠቀበት መጣ። በውስጡ ሊቀመጡ የሚገባቸውን ታሪካዊ ዕቃዎችም ከያሉበት ተሰባሰቡ። ዙፋን ቤቱ የኢትዮጵያን የመንግሥትና የሃይማኖት ታሪክ ሊያሳይ በሚችልበት መንገድ ተዘጋጀ። በውስጡ ከተፈጸሙት ታሪኮች ጋር የሚያያዙ ቅርሶችን አመጣን። ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ ሀገሪቱን የአስተዳደሩትን የልጅ ኢያሱን፣ የንግሥት ዘውዲቱን፣ የቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴን፣ የኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን፣ የአቶ መለስ ዜናዊን እና የአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝን ሀገራዊ አስተዋጽዖ የሚያሳዩ መግለጫዎች ተቀመጡበት። የግብር አዳራሹ ከነ ግርማ ሞገሱና ታሪካዊ ቅርሶቹ ተዘጋጀ። ከቅርስነቱ በተጨማሪ መንግሥታዊ መስተንግዶዎችን ለማድረግ እንዲችል ሆኖ ተሠራ። ለሸገር ፕሮጀክት ለጠራነው የገቢ ማሰባሰቢያ በተጋባዥ ሰው አምስት ሚሊዮን ብር የተከፈለበት የራት ግብዣ የተደረገው እዚያ ነው። ይኼም በቀጣይ ለሚከናወኑ ሥራዎች በር ከፋች ነበር።

ያም ሆኖ ግቢው ገና ያልተነኩ ብዙ ተግባራትን ይፈልግ ነበር። በርግጥም ግቢውን ማስተካከል ቀላል ሥራ አልነበረም። ፍርስራሹን ማንሣት፣ ገደሉን መሙላት፣ የውኃና የፍሳሽ መሥመሮችን እንደ አዲስ መዘርጋት፣

የእግረኛና የመኪና መንገድ መሥራት፣ ያረጁ ዛፎችን ማስወገድ፣ አዳዲስ ዛፎችንና ሣሮችን መትከል፣ ከፊታችን የሚጠብቁን ተግባራት ነበሩ። በካዛንቺስ በኩል ባለው በር ለሚገባ ሰው ፊት ለፊቱ የሚያገኘው ውብ ጉብታ አለ። ይሄንን ውብ ጉብታ ተዝናንቶ በእግር የመጓዣ ሥፍራ አድርጎ ለማመቻቸትና ገደሉን ለመሙላት የጭነት መኪኖች ስድስት ሺሕ ጊዜ ተመላልሰዋል። ፍርስራሽ ቤቶችን፣ የወዳደቁ መኪኖችንና የቆሻሻ ክምሮችን አንሥተናል። በዚህ መልኩ ገደሉ ተሞልቶ፣ ሣር ተተክሎ፣ የእግር መሄጃ መንገዱ ተቀይሶና ሁሉ ነገር ተደላድሎ የዛሬውን መልክ አገኘ።

ኢትዮጵያ፣ ጥቁር አንበሳ መጠሪያዋ የሆነ የአናብስት ሀገር ናት።ቤተ መንግሥት በኢትዮጵያ ታሪክ ከእንስሳት ተለይቶ ኖሮ አያውቅም። በተለይ አናብስት ከአብያተ መንግሥታችን አይጠፉም። ከዙፋን ቤቱ ጀርባና ከጽሕፈት ሚኒስቴር ቢሮ አጠገብ የአንበሶች መኖሪያ ነበረ። በብረት የታጠረው ቤታቸው ዛሬም አለ። አሁን ደግሞ አናብስቱን በዋሻ ውስጥ ለማድረግ ነው የታሰበው። በረሐ የወረድን እንዲመስለን። በተቻለ መጠን ቀረብ ብለን አናብስቱን ለማየት እንድንችል ዕድል ለመፍጠር ታስቦ የተገነባ ማራኪ ስፍራ ነው።

ያንን ዋሻ ጎብኝቶ ወደላይ ቀና የሚል ሁሉ የኢትዮጵያ ድንቅ ዕጽዋት የተሰባሰቡበትን ባለ ግመል መናፈሻ ያገኛል። ግመል የአርብቶ አደሩ ዋና ትራንስፖርቱ፣ ምግቡና መጠጡ ጭምር ነው። ቤተ መንግሥቱ ለሕዝብ እንዲዘጋጅ ሲታሰብ አንዱ ዓላማ ግቢው ኢትዮጵያን እንዲመስል ማድረግ ነበር። የጎደለውን ሞልቶ፣ የጠመመውን አቃንቶ ኢትዮጵያን እንዲመስል ማድረግ ተገቢነቱ አያጠያይቅም። በዕጽዋት ፓርኩ ውስጥ ከመላው ኢትዮጵያ የመጡ ቅመማ ቅመሞች፣ የመድኃኒትና የምግብ ቅጠላ ቅጠሎች ሁሉ ቦታ ተሰጥቷቸዋል። የእግር መንገዱ፣ ከግራና ቀኝ መሬቱን አቅፎ የያዘው ግንብ፣ በየስፍራው ያሉ ቤቶች፣ ወንበሮቹና በጥንቃቄ የተነደፉት ቅርጻ ቅርጾቹ ሁሉ ጥንቃቄ በተሞሉ የጠቢባን እጆች የተሠሩ ናቸው። ፓርኩን የሚጎበኝ ሰው እያንዳንዱን ድንጋይ እየተመለከተ፣ እየመረመረና እያደነቀ ይጓዛል። በዕጽዋቱና ተክሎቹ መካከል ስንራመድ በእናቶቻችን ጓሮ ያለፍን ይመስል የቅጠሎቹና የቅመሞቹ ሽታ ያውደናል።

በታችኛው በኩል ወደ ግቢው የገባ ሰው አስፓልቱን ይዞ ከተጓዘ በስተግራው ትንሿ ኢትዮጵያን ያገኛል። ሁሉም ክልሎች የሚወክላቸው አንድ አንድ እልፍኝ በዚያ ተዘጋጅቶላቸዋል። በክልሎቹ የሚገኙ ሕዝቦችን፣ ባህላቸውን፣ ቅርሳቸውን እና ጥበባቸውን የሚያሳዩበት እልፍኝ ተመድቦላቸዋል። መላዋን ኢትዮጵያ ዞሮ ለማየት ዕድል ያላገኘ ሰው፣ ትንሿ ኢትዮጵያን በቤተ መንግሥት ውስጥ ያገኛታል። ሀገራችንን በጨረፍታ የተመለከተው ጎብኚ፣ ወደ ፊት ደግሞ ጊዜውንና ገንዘቡን አብቃቅቶ ክልሎቹን ለመጎብኘት ይመጣል። በስተግራ አፍንጫ በርን እያየ ወደ ግብር አዳራሹ የዘለቀ ሰው፣ ከፊት ለፊቱ የምግብ ሜዳው፣ ከቀኙ ግብር አዳራሹ፣ በስተግራው ደግሞ የእንስሳት ፓርኩ ይታየዋል።

ግራውን ይዞ ወደ እንስሳት ፓርኩ ሲዘልቅ ከሁለት መቶ ሃምሣ በላይ እንስሳት የሚገኙበትን በአዲስ አበባ

የመጀመሪያውን የከተማ ውስጥ የእንስሳት ፓርክ ያገኛል። በዛፍ የሚንጠለጠሉ፣ በእግር የሚሽከረከሩ፣ በክንፍ የሚበርሩ፣ በባሕር የሚኖሩ እንስሳት እዚያ ፓርክ ውስጥ አሉ። ወደ ሌላው ዓለም ሄደን ልናያቸው ያልቻልነውን እንስሳት ከሀገር ሳንወጣ እናያቸዋለን። በክልሎች ዞረን ያላየናቸውን እንስሳት እዚያ እናያቸዋለን። የእንስሳት ዓለምን እዚሁ ለልጆቻችን ማሳየት የሚያስችለን አማራጭ እናገኛለን።

አንድነት ፓርክ ሲከፈት ከመላ ሀገሪቱ ኢትዮጵያውያን ጎርፈዋል። ዳያስፖራዎች ፕሮግራም ይዘው መጥተዋል። አፍሪካውያን በኢትዮጵያ አየር መንገድ ትራንዚት መንገደኞች ሆነው ጎብኝተውት አልፈዋል። ከሌላው ዓለም ለሚመጡ ጎብኝዎች ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻ መሆኑን ታዋቂ ዓለም አቀፍ ብዙኃን መገናኛዎች ዘግበዋል። በእርግጥ ሥራው አልጋ በአልጋ አልነበረም። ያለማቋረጥ ክትትል ማድረግ ይፈልጋል፡፡ ከባለሞያዎቹ ጋር የቤተኛ ያህል መግባባትና አብሮ መሥራትን ይጠይቅ ነበር። እኔም የማገኛትን ውሱን የዕረፍት ጊዜ ፕሮጀክቱን በመጎብኘት፣ የመፍትሔና የመነቃቃት ምክንያት ለመሆን የበኩሌን ጥሬያለሁ። የየዕለቱ ሥራ እኩለ ሌሊት ድረስ ይቀጥል ነበር። ሐላፊዎች፣ ባለሞያዎችና ሠራተኞች እስከ ዕኩለ ሌሊት እየተጉ ማየት ለራሴም አንድ የመነቃቃት ምንጭ ሆኖልኛል።

በዚህ መሐል የቀደመውን የሚያስንቅ ሐሳብ ይመጣል። እግር ጥሏቸው ሥራውን ሊጎበኙ ብቅ ያሉ ባለሞያዎችም፣ ቢቀር ኖሮ የሚያስቆጭ መልካም ሐሳብ ያመጣሉ። በዚህ መልኩ በመጡ ሐሳቦች ከአንድም ሁለት ጊዜ የዕቅድ ክለሳ _ ስለመደረጉ አስታውሳለሁ። መጠነኛ ወጪ ቢያስጨምርም ፓርኩን በማሻሻል በኩል ካለው ሚና አኳያ ከአስተያየነው ጭማሪው እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በዚህ መንገድ በስድስት ወራት ውስጥ አንድነት ፓርክ ከእንስሳት ፓርኩና ከሀገር በቀል ዕጽዋት መንደሩ በቀር ሌላው ክፍል በስኬት ተጠነቀቀ።

ለጉብኝት ክፍት ሲደረግ ከሰዎች ያገኘነው ምላሽ ለሌላ ሥራ እንድንበረታ እንጂ በስንፍና ባለንበት እንድንገታ አላደረገንም። በቀን እስከ ሁለት ሺሕ ሰዎች የሚጎበኙት የሀገሪቱ ሕዝቦች መገናኛ ማዕከል ሆነ። ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ ጎልማሶችና አረጋውያን እኩል የሚወዱት ሥፍራ ሆነ፡፡ አረጋውያን ትዝታቸውን፣ ሕፃናት ተስፋቸውን ያዩበታል፤ ወጣቶች ደግሞ ዛሬያቸውን ይኖሩበታል።

ቤተ መንግሥቱን መክፈታችን በራሱ ተአምር ተደርጎ ታየ። ዘግቶ፣ ተዘግቶና ተዘጋግቶ መኖር፣ መንግሥትንና ሕዝብን አራርቆ ቆይቷል። እንደ እውነቱ ከሆነ የመንግሥት ቤት የሕዝብ ንብረት መሆን ካልቻለ፤ መንግሥት የሕዝብ አገልጋይ፣ ሕዝብስ የመንግሥት ባለቤት ሊሆን እንዴት ይችላል? ቤተ መንግሥት የሕዝቡ ሀብትና ታሪክ ነው። ሀብትና ንብረቱን ከሕዝቡ ወስዶ ሕዝቡ እንዳይደርስበት ገድቦ መቀመጥ መንግሥታዊ ምቀኝነት ነው፡፡ በተቀረው ዓለም በሥራ ላይ ያሉ አብያተ መንግሥታቱን ሕዝብ የሚጎበኝበት ሥርዓት አለ። ቢቻልማ ሁሉንም ወደ ሕዝብ አዘዋውሮ ጽሕፈት ቤታችንን ወደ ሌላ ቦታ መቀየር ብንችል መልካም ነበረ። ያም ሆኖ

ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ላድርግ ማለቱም የሚቻልም ተገቢም አልሆነም።

በአንድነት ፓርክ የተገኘው ምላሽና የሕዝቡ ደስታ የበለጠ ብርታት ሆነን። እንደ ሀገር ያለንን እምቅ ሀብት አውጥተን ጥቅም ላይ እንድናውለው ይገፋፋል። ሥራው ሳያልቅ መቆም የለበትም ብለን አሰብን። ጊዜ ደግሞ እንደዘወትር ልማዱ እንደሮጠ ነው። ሁላችንም ሰው ነንና ያለን ጊዜ የተገደበ ነው። በተሰጠን ጊዜ ካልሠራንበት ደግሞ ውሎ አድሮ ቁጭትና ጸጸት ውስጥ ይጥለናል እንጂ ደስታ አይተርፈንም።

**ካልተሳፈሩበት ቶሎ ተሽቀዳድሞ፣**

**ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ፤**

**እንዳሉት ከበደ ሚካኤል።**

ለአብነት ቀለል ስለሚል የአንድነት ፓርክንና የአዲስ አበባ ፕሮጀክቶችን አነሣን እንጂ፣ በተለይም ለሀገራችን ግዙፍ የሆነ አዎንታዊ ሚና በሚያበረክቱ ማክሮ ኢኮኖሚክ ጉዳዮች የሚከናወኑት ተግባራት ከዚህም ከፍ ያለ ትጋት የሚሹ ናቸው።ከዚህም አኳያ በዚያም ዘርፍ ጥንቃቄ የተሞላበት የሌት ተቀን ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። በማንኛውም አጋጣሚ የሚሠሩት ሥራዎች ለወቅቱና ላለንበት ማኅበረሰብ ትክክል መሆናቸውን፣ ሀገርን መጥቀማቸውንና ከሌብነት በጸዳ መልኩ መከናወናቸውን በአገኘነው አጋጣሚ ከማረጋገጥ ወደ ኋላ አንልም። ኢትዮጵያ በሞቱላት ልጆች እዚህ ደርሳለች። የእኛም ትውልድ በድህነትና በኋላ ቀርነት ያደፈ ስሟን ለማጥራት በምኞትና በወሬ ሳይሆን በፈጠራና በሥራ ተግተን ማስመስከር ይጠበቅብናል። የእንጦጦውንና የአራት ኪሎውን የሸገር ፓርክ ፕሮጀክት በተመሳሳይ ጊዜ ነበር የጀመርነው። የአራት ኪሎው የሸገር ፓርክ ፕሮጀክት ከተማዋን የሁላችንም ውብ መናኸሪያ የሚያደርጋት ነው። የተለያየ መጠን ያላቸው አምፊ ቴአትሮች፣ የአትክልት ስፍራዎች፣ ሰው ሠራሽ ሐይቅ፣ የመዝናኛ ስፍራዎች፣ ጽዱ ወንዝ፣ ለማንበቢያና ለማረፊያ የሚሆኑ ምቹ ቦታዎች፣ የሕፃናት መጫዎቻ መንደሮች፣ በእግር የመጓጓዣ ምቹ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ ለሰርገኞች የሚሆኑ መዝናኛና ማረፊያ ቦታዎችን ያካትታል።

በአንድ ጊዜ ከዓሥር ሺሕ በላይ ሰዎች ቦታውን ሊጎበኙት ይችላሉ። በብዙ ሺሕ ለሚቆጠሩ ወጣቶች የሥራ ዕድል ይከፍታል። የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭ ወገኖች ገቢያቸውን ያሳድጉበታል። ከንቲባዎቻችን ልምድ ያሳምሩበታል። ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆኑ አካባቢዎች ይፈጠሩበታል። ብሩህ ነገር አይተን ብሩህ ተስፋን እንሰንቅበታለን።

ቱሪዝም ትልቁ ሀብታችን ነው ብለን በየጊዜው ብናወራም ገና ምንም አልተጠቀምንበትም። ብዙዎቹ የምናስጎበኛቸው ነገሮች ቀደምት አባቶቻችን ያወረሱንና ተፈጥሮ ያደለችን ነገሮች ናቸው። ባለን ሀብት ላይ ዕሴት ጨምረን ወደ ገንዘብ ልንቀይራቸው የሚገቡን እልፍ ሀብቶች አሉን። ነገር ግን የምንዘፍንላቸውን ያህል

አንቆጭም፤ የምንቆጨውንም ያህል አልሠራንበትም። ሀብት ላይ ተኝተን እያንቀላፋን፣ በድህነት አረንቋ ውስጥ ሰጥመን እንሰቃያለን። ቅንጡ ድህነት።

የእንጦጦውም ፕሮጀክት በዚሁ መንገድ የተወለደ ነው። ከአንድ መቶ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠሩ ዛፎች የሞሉት ደን ነው። ኮረብታ፣ ገደል፣ ሜዳ፣ ተዳፋት፣ ፏፏቴ፣ ሸለቆዎች አሉት። ከተማው ሸሽቶ ሸሽቶ ጥሎት እየሄደ ነው። ውስጡ ያለውን ሀብት ግን ያየው የለም። ከውጭ የመጡ ጥቂት ቱሪስቶች ብቻ በእግር ለመሄድና ከተማዋን ከላይ ወደታች ለመመልከት አናቱ ላይ ይወጣሉ። ከዚያ ውጭ የሚንቀሳቀሱት በዚያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን ለመሳለም አለፍ ገደም የሚሉ የአካባቢው ነዋሪዎች ብቻ ናቸው።

እንጦጦ ልዩ ሆኖ ተሠርቷል። አራት የመኪና መግቢያ በሮች ይኖሩታል። የእግረኛና የብስክሌት መንገድ ተሠርቶለታል። የሥዕል ጋለሪ፣ ቤተ መጻሕፍት፣ ስታዲዮም፣ ድንኳን የመትከያና ጫካ ውስጥ ቁጭ ብሎ የማንበቢያ ሥፍራዎች፣ ሌሊቱን በተራራው ላይ የማሳለፊያ መኝታ ቤቶች፣ የፈረስ መጋለቢያ፣ የሕፃናት መኪና መንጃ፣ ለእግረኞች ማረፊያዎች፣ ከተራራ ላይ ሆኖ ፏፏቴ የመመልከቻ ሠገነት ሁሉም ይኖሩታል። ጥናት ለማድረግ፣ ድርሰት ለመድረስ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብ፣ ለመወያት፣ ለስብሰባ፣ ምቹ ሆኖ የከተማይቱ የከፍታ ገነት ሆኖ እያለቀ ነው። እንጦጦ ራሱ ዐይን ቢኖረው እስከ ዛሬ ያሳለፈውን ዘመን መለስ ብሎ አይቶ መደመሙ አይቀርም። እስከ ዛሬ እዚሁ ነበርኩ? ዛሬ ምን ተፈጠረ? ብሎ ራሱን በጠየቀ ነበር። ገና ለሕዝብ በይፋ ክፍት ሳይሆን አዲሳበቤዎች ፓርኩን ለማየት ያላቸው ጉጉት ልብን ያሞቃል። እዚያ ለዘመናት ማገዶ ቅጠል ሰብስበው ወገባቸው እስኪጎብጥ ላይ ታች የሚሉ እናቶች፣ ልጆቻቸው በሚያገኙት የሥራ ዕድል ወይንም በሌሎች መንገዶች ከፓርኩ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅም ያገኛሉ። የፓርኩ እውነተኛ ባለቤትም ሆነው ይበልጡን ያሣምሩታል፤ በሚል ተስፋ በመቶ የሚቆጠሩ እናቶች ከእንጨት ለቀማ ወጥተው ተደራጅተው ለፓርኩ ግብዓት እንዲያቀርቡ እየተሠራ ነው።

የወንዞች ዳርቻ ልማት ፕሮጀክታችን፣ የቱሪዝም አድማሳችንን ለማስፋት ሲባል አዲስ አበባን ጽዱና ውብ ለማድረግ ታሳቢ ተደርጎ የተጀመረ ነው። የወንዞቹ ንጽሕና መጓደል እንደ ባለቤት በወንዞቹ ዙሪያ የሚኖሩ ጥቂት ግለሰቦች የሚጠየቁበት ጉዳይ አይደለም። ወደ ወንዞቹ ፍሳሾችንና ኬሚካሎችን የሚለቁ ሆስፒታሎች፣ ሆቴሎች፣ መሥሪያ ቤቶችና ልዩ ልዩ ተቋማትን ጨምሮ፣ ቆሻሻና ፍሳሽ አወጋገድን የሚከታተሉ ቢሮዎችና የከተማው ማዘጋጃ ቤት፣ እንዲሁም ሌሎች እዚህ ያልጠቀስናቸው አካላት የችግሩ ተጠያቂዎችም ተጠቂዎችም ናቸው። በአጠቃላይ እንደ ማኅበረሰብ የወደቅንበትና በጋራ ሠርተን የምናስተካክለው ጉዳይ ነው። ነገሩ እንዲህ በቀላሉ ለአንድ ባለሀብት ሰጥተን ሊፈታ የሚቻል ጉዳይ አይደለም። ምንም እንኳን የምናወራው በዋናነት ስለ ሁለት ወንዞች ቢሆንም እነዚህ ወንዞች እየተጠማዘዙ እያንዳንዱን የአዲስ አበባ መንደር እየታከኩ ያልፋሉ። በአጠቃላይ ከሃምሳ ስድስት ኪሎ ሜትሮች በላይ ይሸፍናሉ። በወንዞቹ ጽዳት አንድ ሆቴል ወይም ጥቂት ግለሰቦች አያተርፉም፤ ሁሉም የከተማው ነዋሪ ተጠቃሚ ስለሚሆንበት ባለቤትነቱን የሁላችንም ያደርገዋል።

በዚህ ዕሳቤ ፕሮጀክቱ ተጀመረ። በመጨረሻም የአፍሪካችን የዲፕሎማሲ መዲና የሆነችው አዲስ አበባችን ከቆሻሻ የጸዳች ከተማ ትሆን ዘንድ የመጀመሪያው ድንጋይ ተወረወረ። የድጋፍ እጃቸውን በዘረጉልን የውጭ አጋሮቻችንና የሀገር አለኝታ ባለሀብቶቻችን የሰጡንን አንድ ላይ አድርገን ለታሪካዊ ሥራ ተነሣን። ለዚህም እንዲያግዝ ባለ አምስት ሚሊየን ብር የራት ግብዣ በአንድነት ፓርክ፣ በታሪካዊው የግብር አዳራሽ ገበታ ቀርቦ ጥሩ ውጤትም አስገኘ። በዚህ መልኩ ገንዘቡ ጠርቀምቀም ሲል ከሌሎች የሸገር ፕሮጀክቶቻችን ጎን ለጎን የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክታችንንም በሦስት ዓመት ውስጥ ገንብተን ለማጠናቀቅ ተንቀሳቀስን። ከእንጦጦ ተራራ እስከ አቃቂ ወንዝ የሚዘረጉ ወንዞችን ማጽዳት ውስብስብ ሥራ ነው። በዝናብ ጊዜ በከተማው የሚፈጠረውን ጎርፍ ወደ ወንዞቹ እንዳይገባ የሚከላከል አዲስ የፍሳሽ መሥመር መገንባት አለበት። ቀድሞ ከወንዞቹ ጋር ለተገናኙ ቆሻሻ መሥመሮች መፍትሔ ለመስጠት አማራጭ መሥመሮችን መገንባት ግድ ይላል። እንዲህ ያለው ነገር ሥራው አልጋ ባልጋ እንዳይሆን ያደርገዋል። ሆኖም ግን ታቅዷልና መሠራት አለብት፣ ተጀምሯልና ሊፈጸም ይገባል።

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የእውነትም አዲስ አበባ እንደስሟ አዲስ ትሆናለች። ከወንዞቹ ዳርና ዳር የእግረኛ መንገዶች ብቻ ሳይሆን የብስክሌት መሥመሮች ይኖሩታል። አረንጓዴ መስኮችን ጨምሮ ዙሪያውን አረፍ ብለው የሚዝናኑባቸው መናፈሻዎች ይኖራሉ። በጥሩ መልኩ ዲዛይን የተደረጉ ድልድዮች፣ የውኃ ትራንስፖርትና የንግድ ማዕከላት በፕሮጀክቱ ተካትተውበታል። አስጎብኝዎች ቱሪስቶችን ይዘው ሲዘዋወሩ በየመሐሉ ዐረፍ የሚሉባቸው ምግብ ቤቶች፣ ካፌዎችና ሌሎች አገልግሎት መስጫዎችም የበለጠ ያደምቁታል። ሌላው የከተማችን ታሪካዊ ዕንቁና አረንጓዴ ወርቅ የኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ነው። ሥራውን አጠናቀን ለሕዝብ ክፍት ከማድረጋችን በፊት ቁልፍ ሥራዎችን ስለሚሻ ለዚህ የሚያስፈልገውን እገዛ ከፈረንሳይ መንግሥት አግኝተናል።

ኢዮቤልዩም እንደ አራት ኪሎው ቤተ መንግሥት ብዙ ታሪኮችን በጉያው ይዟል። ከመቶ ዓመታት በላይ የተከማቹ መዛግብት፣ የወግ ዕቃዎች፣ መጻሕፍት፣ ሰነዶች ሞልተውታል። ከየትኛውም ማዕዘነ ዓለም የሚመጡ ቱሪስቶች ሊያዩዋቸው የሚናፍቋቸው አንቲክ የሆኑ መኪኖችና የባቡር ፉርጎዎች እንደ መናኛ ዕቃ አቧራ እየጠጡ ሞታቸውን በመጠባበቅ ላይ ነበሩ። በዚያ ላይ ግቢው በራሱ በደን የተሞላ ምደረ ገነት ነው። ከኢኮኖሚክ ኮምሽን ፎር አፍሪካ /ኢሲኤ/ ፊት ለፊት እስከ ፍል ውኃ ያለው ስፍራ እንደገና ተስተካክሎ፣ ምግብ ቤቶችና የጉብኝት ማዕከሎች ኖረውት ሲሠራ፤ ሀብታችን መዳፋችን ውስጥና ዐይናችን ሥር ተደብቆብን የኖረ ለመሆኑ እማኝ ይሆናል። ፕሮጀክቱ በሦስት ምዕራፍ ሊሠራ ዕቅድ ተይዟል። በውስጡ ያለው ታሪክ የጠገበ ሀብታችን ለጎብኝዎች ክፍት ሲሆን፣ ለቁጥር አታካች ቱሪስቶች /በተለይም ከአፍሪካ ሀገራትና ከጥቁሩ ዓለም የሚመጡ ሰዎች/ ውሎና አዳራቸው አዲስ አበባ ይሆናል።

ከቤተ መንግሥቱ አጠገብ ከሠላሳ ሺሕ በላይ አንባቢ የሚይዝ ትልቁ ቤተ መጻሕፍት ይገነባል። በሀገራችን መጠጥ ቤቶች ለመግባት ከሚደፍረው መቶ ሰው አንዱ እንኳን ወደ ቤተ መጻሕፍት ለመግባት ብርክ ብርክ ሲለው እናያለን። ለምን ያልን እንደሆን መጠጥ ቤቶቹ እንግዶቻቸውን ለማስተናገድ በራቸው ወለል አድርገው የከፈቱትን ያህል ቤተ መጻሕፍቱ ክፍት ስላልሆኑ ነው። ኢትዮጵያ እንድትለወጥ ከፈለግን ዕውቀትና ዐዋቂነትን ማበረታታት የቅድሚያ ቅድሚያ ማግኘት አለበት። ለዕውቀትና በጎ ሐሳብ ቦታ የሚሰጥ ማኅበረሰብ መገንባት አለብን። ከሃምሣ ዓመታት በፊት የተገነባ አንድ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት ይዘን የማንበብ ባህልን ለማዳበር ማሰቡም ዘበት ነው። ብንችል የክልልና የዞን፣ የወረዳ አብያተ መጻሕፍት ያስፈልጉናል። "ሮም በአንድ ቀን አልተሠራችም" እንዲሉ ሁሉን ዛሬ ማድረግ ይከብድ ይሆናል። ዳሩ ግን የሺሕ ማይሎች ጉዞ በአንድ ርምጃ ይጀመራልና አንድ ኢትዮጵያን የሚመጥንና ለአንባቢዎቹ ገነት የሆነ ተምሳሌታዊ ቤተ መጻሕፍት መሐል መዲናችን ላይ እንገነባለን።

ፒያሳ ከጊዮርጊስ ፊት ለፊት የምንገነባው የዓድዋ ሙዝየምም እየመጣ ነው። ዓድዋን እንኮራበታለን፤ በየዓመቱም እንዘክረዋለን። ድሉ ከእኛ አልፎ የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ድል ከሆነ አንድ ክፍለ ዘመን አልፎታል። ዓድዋን የሚመጥን ማዕከል ግን እስከ አሁን የለም። ባለፉት ሁለት ዓመታት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ስንዘዋወር የሀገር ሽማግሌዎች ደጋግመው ካነሧቸው ነገሮች አንዱ፤ እንደ ሀገር የሚያስተሳስሩን ሰበዞች እንዲጠናከሩ የበኩላችንን እንድንወጣ ነው። በዚህ በኩል ዓድዋን ከአየነው በአራቱም አቅጣጫ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ የጋራ የሚያደርገን አንዱ ሰበዝ ነው። ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ያሉ ሕዝቦቻችን የአያቶቻቸውን ገድል በኩራት ያነሡታል። ዳሩ ግን ለዚህ የሚመጥን የታሪክ ማስታወሻ ገና አላኖርንም።

እነማን ነበሩ የዘመቱት? ከየብሔረሰቡ እነማን ተሳትፈው ምን ሠሩ? በሥነ ቃላቸው ተሰናስሎ የሚገኘው ዓድዋ ለእነርሱ ምንድን ነው? በታሪካቸው ውስጥ ምን ቦታ ይዞ ይኖራል? ከጦር መሪዎቹ ጎን ለጎን የእምነት አባቶች፣ ሐኪሞች፣ አዝማሪዎች፣ አገልጋዮች፣ የውጭ ሀገር ሰዎች፣ ወዘተ... ተሳትፈዋል። የእነዚህ ሁሉ አብሪ ታሪክ ገና በሚመጥናቸው መልኩ አልተከተበም። ስለ ዓድዋ በመላው ዓለም ብዙ ተብሏል። እነዚያን መዛግብት፣ ፎቶዎች፣ ሥዕሎች፣ መጻሕፍት፣ ጋዜጦች፣ ፊልሞች አልሰበሰብናቸውም። ዓድዋን ገና በሚገባ አላጠናነውም። ዳዋ የበላውን ታሪካችንን አጥንተን ስላልተጠቀምንበት አንዳንድ ጊዜ የዓድዋ ልጆች አንመስልም። የዓድዋን ታሪክ እያጠና ለመጪው ትውልድና ለቀረው ዓለም የሚያስተምር የምርምር ማዕከል ያስፈልገናል። የዓድዋ ቅርሶች መሰብሰብ አለባቸው። አፈ ታሪኮቹ መመዝገብ አለባቸው። የየአካባቢው አስተዋጽዖ በመብራት እየተፈለገ በተገቢው ቦታ መቀመጥ አለበት። ያን ጊዜ ዓድዋን እንዳይረሳ አድርገን ለትውልድ እናስተላልፈዋለን።

ምን ይሄ ብቻ፤ ሐረር ሄደን ጀጎልን፣ ጂማ ሄደን የአባ ጂፋር ቤተ መንግሥትን፣ ትግራይ ተሻግረን የዐፄ ዮሐንስን ቤተ መንግሥትና ገርዓልታን፣ ጎንደር ተሻግረን ጎሐ ተራራንና የፋሲል ግንብን፣ አፋር ሄደን ኤርታሌን፣ ጋምቤላ ወርደን ባሮን፣ ደቡብ ወርደን ጨበራ ጩርጩራን መገንባታችን አይቀሬ ነው። የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው። አንዱ የሌላውን ሀብት ለማየት ወደ ሌላው ካልሄደ ስለ ሀገራችን ያለን መረጃ የተሟላ አይሆንም። ይበልጥ በተጓዝን፣ ይበልጥ በተገናኘን፣ ይበልጥ በተቀራረብን ወቅት እንተዋወቃለን። እንግባባለን። አብረን እንሠራለን፤ አብረን እናድጋለን። ዋናው ዓላማችን፣ ቱሪስት ስቦ ሀብት ማካበት ብቻ ሳይሆን፤ ኢትዮጵያዊ መስተጋብርን በመፍጠር፣ ኢትዮጵያዊ ገመድና ትስስርን ማጠንከር ነው።

ግሪኮች ሲተርቱ “አንድ ኅብረተሰብ ወደ ከፍታ የሚጓዘው አዛውንቶች በጥላው እንደማይጠለሉ እያወቁ ጭምር ዛፍ መትከል ሲችሉ ነው” ይላሉ። አካሄዳችን በልቼው ልሙት ከሆነ ልጅ መውለድ ብቻውን ትርጉም የለውም። ዘርን ሜዳ ላይ መበተን ብቻውን ትውልድን አንድ ጋት አያስጉዘውም። ለቀጣዩ የሚሆነውን በጎተራው ሞልቶ ማዘጋጀት፣ አድጎ እስኪያብብ መከባከብ፣ ፍሬው ሌላ ፍሬ ማፍራት ስለመቻሉ ማረጋገጥ፣ እንኳንስ ማሰቢያ አእምሮ ለተሰጠው የሰው ልጅ ቀርቶ በደመ ነፍስ የሚኖሩት ምስጥና ጉንዳኖች በወግ በወጉ የሚፈጽሙት ተግባር ነው። ኢትዮጵያችን በደን ሀብት ጥሩ ደረጃ ከነበረችበት ዘመን አንሥቶ ምድሩ ሌጣውን እስከ ቀረበት የዛሬው ዘመን ድረስ የኖሩት አባት አያቶቻችን ከመትከል ይልቅ መንቀልን፣ በቦታው ከመተካት ይልቅ መና ማስቀረትን እንደ ባህል ማድረጋቸው ምን ያህል የተሳሳተ አካሄድ እንደነበረ ዛሬ አፍጥጦ የሚታይ እውነታ ሆኗል። በአንድ ፊት ሕዝባችን ወደ ሰማይ እያንጋጠጠ የተፈጥሮ ዝናብን ጠብቆ የሚያርስና ኑሮውን በኋላ ቀር ግብርና የመሠረተ አሳዛኝ ሕዝብ ነው። በሌላ ፊት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የደን አያያዛችን መጨመርና መተካትን ሳይሆን መቀነስና ማውደምን እንደ ባህል ያጸና ነው።

ታዲያ ዕድገት በየት በኩል ሊመጣ ይችላል? ይህ እኩይ ልማድ ሳይውል ሳያድር መለወጥ አለበት። ግብርናችንን ለማዘመን መስኖና ሌሎች ዘመናዊ አሠራሮችን መተግበራችን ጅማሮ ነው። ሆኖም ግን ከደን አያያዝ ጋር በተገናኘ ለረጅም ዘመን የተጠናወተን ተፈጥሮን የማውደም አባዜ እስካልተሰበረ ድረስ በአንድ ፊት ስንሞላ በሌላ ፊት ማጉደላችን አይቀሬ ይሆናል። “አረንጓዴ አሻራን የማኖር ጉዟችንን በተለየ ትኩረት ለመሥራት የተነሣነውም በዚህ ምክንያት ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥሯ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ የፈጠረባት ጫና አለ። ለመኖሪያ ቤት መሥሪያና ለእርሻ በሚል የሚመነጠረው መሬት ሰፊ ነው፡፡ ከዚህ በባሰ ደግሞ ዛፎች ለማገዶ ፍጆታነትም ይቆረጣሉ። ይሄም አፈሩ በውኃ እንዲሸረሸር፣ ብዝኃ ሕይወት እንዲመናመን፣ የካርቦን ልቀት ከዕለት ወደ ዕለት እንዲጨምር፣ በተዘዋዋሪ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲባባሱ መንገድ ከፍቷል። በተጨማሪም እንደ ክፉ ዘመድ እየቆየ የሚጎበኘንን ድርቅ መቋቋም ተስኗት በተደጋጋሚ ስትንገዳገድ እንደኖረች ሁላችንም እናውቃለን። ይህ ድርቅ አንድም ከዓለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ሁለትም በገዛ

ባህላችን አውድመን ያራቆትነው ደናችን ባስከተለው ጦስ ምክንያት የሚከሠት እንደሆነ ግልጽ ነው።

በአራት ዓመታት ውስጥ ከሃያ ቢልዮን በላይ ችግኞችን በመላ ኢትዮጵያ ለመትከል አልሞ የተነሣው የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክት፤ ሀገራችን በየዘመናቱ የሚገጥማትን ድርቅ እስከ ወዲያኛው የማስቀረት ዐቅም እንዳለው ምንም ጥርጥር የለውም። የችግሩን መገለጫ ትተን የችግሩን መነሻ ለመቅረፍ ነው ዓላማችን። ይህ ዓላማችንና የዓለምን ሪከርድ የመስበር ኢትዮጵያዊ ወኔያችን አግዞን፣ በ2011 ዓ.ም ላይ መላው ሕዝባችን ተባብሮ፣ በአንድ ቀን ብቻ ከሦስት መቶ ስድሳ ሚልዮን በላይ ችግኞች መትከል ችሏል።

በዓመቱ መጨረሻ ላይ አራት ቢልዮን መድረሱ የተአምር ያህል ብዙዎችን አስደንቆ ነበር። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ልብ የሚያሞቅ ተሳትፎ ያደረጉ ዜጎቻችን ቁጥራቸው ቀላል አልነበረም።

የችግኝ ጉድጓዶቹን ካዘጋጁት አንሥቶ ግንዛቤ በመፍጠር ሕዝቡን እስከ አነሣሡት ግለሰቦችና ተቋማት፣ በተከላው ላይ ንቁ ተሳትፎ ካደረጉ ሰዎች፣ የተተከለውን እየቆጠሩ መልሰው ለሕዝቡ በማሳወቅ መነቃቃትን እስከ ፈጠሩት ብዙኃን መገናኛዎች ሁሉም ምስጋና ይገባቸዋል። ምንም እንኳን ሁላችንም ያለን ሀገር አንድ ቢሆንም፤ በሐሳብ፣ በገንዘብና በቁሳቁስ ድጋፍ ለአደረጉ አካላት፣ ለውዷ ሀገራችን ለአደረጉት ትልቅ አስተዋጽዖ ያለኝ ክብር በምንም የሚሰፈር _ አይደለም። በቀጣይ ዓመታት ለምናከናውናቸው የችግኝ ተከላ እንቅስቃሴዎችና የተከልናቸው ችግኞችም እንዲጸድቁ ለምናደርጋቸው ክብካቤዎች ከወዲሁ ወገባችንን መታጠቅ ይገባናል።

መደመር ዐቅምን በመሰብሰብና ዕውቀትን በማከማቸት ወረት የማካበት ሂደት ነው። እንደ እርሾ እየሆነ የሚያገለግለውና በዘመናት ጉዞ ውስጥ የሀገርን ሀብት እንዲበዛ የሚያደርገው የሚጨበጥ ወርቅና አልማዝ ብቻ ሳይሆን እንደ አረንጓዴ አሻራ ዓይነት ከዕንቁ የነጠረ መልካም ባህል ጭምር ነው። ከላይ ያየናቸው ሌሎች ፕሮጀክቶችም በቱሪዝም ገቢ ከማስገኘት፣ ታሪካዊ ዕሴቶችን ጠብቆ ከማቆየት፣ ንጹሕ የሆነ የሥራ ከባቢን ከመፍጠር፣ ኢትዮጵያዊ መሠረቶችን ከማጽናት ባለፈ፤ ዋነኛው ታሳቢያቸው ለወደፊት እንደ እርሾ የሚያገለግል የመደመር ባህል ጥሎ ማለፉ ነው። ከለውጥ ሁሉ ጥልቁና ትልቁ ለውጥ፣ በትጥቅ ትግል መንግሥትን ገርስሶ በሌላ መተካት ወይም ከሕዝባዊ ዐመፅ በሚወለድ አብዮት አዲስ ርእዮተ ዓለምን ማስፈን ሳይሆን፤ በግለሰብ የአስተሳሰብ ለውጥ ላይ የሚመሠረተው ማኅበረሰባዊ የባህል ለውጥ ነው።

ዐቅምና ሁኔታ ስለሚገድበን፣ አሁን የምንፈልገውን ሁሉ በአንድ ጊዜ ማድረግ አንችል ይሆናል። የምንችለውን ሁሉ ግን ማድረግ አለብን። የምንችለውን ሁሉ ከማድረግ ሊገድበን የሚችል ነገር ቢኖር ስንፍና ብቻ ነው። ለእርሱ ደግሞ ቦታ የለንም። ድህነትን በሂደት ማጥፋት አይቻልም። የድኾች መንገድ ተብሎ በዓለም ላይ የተነጠፈ መንገድ አለ። ይህም ድኻ እንዲህ ያድርግ እንዲህ ይኑር እንጂ እዚህ ላይ ምን አገባው? የሚባል አባባል አየሩን ይዞታል። "ድኻ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ ንቃቃት ይገድለው ነበር፣ "የማያልፍለት ድኻ ሀብታም ይጋብዛል' ወዘተ… የሚሉ አባባሎችን እኛም ተቀብለናቸው ራሳችንን እንጨቁንበታለን። ድኾችንና ድህነትን

ሳይለይ የሚጨፈልቅ፣ ድኾችን ከድህነታቸው ከማላቀቅ ይልቅ አጣብቆ ለማቆየት የሚተጋ አስተሳሰብና ባህል ጊዜው አልፎበታል። አጋዥ ከአገኘን የዓመቱን በወር፣ የወሩን በሳምንት፣ የሳምንቱን በዕለት እንሠራለን። አጋዥ ካላገኘን የሳምንቱን በወር የወሩን በዓመት እንፈጽማለን። መቼም ቢሆን ግን መሥራታችንን አናቆምም፤ ከመንገዳችን አንገታም፤ ወደ ኋላም አንልም። በመደመር መንገድ ወደ ብልጽግና መዳዛችንን እንቀጥላለን።